# ዘሌዋውያንና ዕብራውያን ት.መ.ሟ.



PROPERTY OF THE
LAPSLEY-BROOKS FOUNDATION, INC
375 WILLOW WOOD ST.
PLANO, TEXAS 75094
USA

መግቢያ

ትምህርት 1 - ኦሪት ዘሌዋውያን መግቢያ

ትምህርት 2 - ኦሪት ዘሌዋውያን፥ ም. 1-3

ትምህርት 3 - ኦሪት ዘሌዋውያን፥ ም. 4-10

ትምህርት 4 - ኦሪት ዘሌዋውያን፥ ም. 11-13

ትምህርት 5 - ኦሪት ዘሌዋውያን፥ ም. 14-16

ትምህርት 6 - ኦሪት ዘሌዋውያን፥ ም. 17-22

ትምህርት 7 - ኦሪት ዘሌዋውያን፥ ም. 23-25

ትምህርት 8 - ኦሪት ዘሌዋውያን፥ ም. 26-27

ትምህርት 9 - የዕብራውያን መ፥ጽሐፍ መግቢያ

ትምህርት 10 - ዕብራውያን፥ ም. 1-2

ትምህርት 11 - ዕብራውያን፥ ም. 3፡1-4፡13

ትምህርት 12 - ዕብራውያን፥ ም. 4፡14-5፡14

ትምህርት 13 - ዕብራውያን፥ ም. 6

ትምህርት 14 - ዕብራውያን፥ ም. 7

ትምህርት 15 - ዕብራውያን፥ ም. 8

ትምህርት 16 - ዕብራውያን፥ ም. 9

ትምህርት 17 - ዕብራውያን፥ ም. 10

ትምህርት 18 - ዕብራውያን፥ ም. 11

ትምህርት 19 - ዕብራውያን፥ ም. 12

ትምህርት 20 - ዕብራውያን፥ ም. 13ና ክለሳ

# ኦሪት ዘሌዋውያንና ዕብራውያን

## መግቢያ

### የመጀመሪያ ቀን:-

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ የተልእኮ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የምናጠናው በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኘውን የኦሪት ዘሌዋውያንን መጽሐፍና የአዲስ ኪዳን የዕብራውያን መጽሐፍ በአንድነት ይሆናል። የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ቅድስናውና ከሕዝቡ ስለሚፈልገው ዓይነት ቅድስና ይነግረናል። እሥራኤላውያን ምሕረቱን ተቀብለው ከእግዚአብሔር ኅብረት እንዲኖራቸው ሲሉ ማቅረብ የሚገባቸውን መሥዋዕት በግልጽ ያስረዳል። እነዚህ መሥዋዕቶች የመጨረሻው ዘላለማዊ መሥዋዕት የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያንፀባርቁ ምሳሌያዊ ምልክቶች ናቸው። የዕብራውያን መጽሐፍ ደግሞ የተመሠረተው በዘሌዋውያን ላይ ባሉት ሐሳቦች ላይ ነው። ይህ መጽሐፍ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉት ካህናትና መሥዋዕት ጊዜያዊ እንደነበሩ ያስፈልጉም የነበረው የመጨረሻው ሊቀ ካህንና መሥዋዕት የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ እንደነበር ያሳየናል። የዕብራውያን መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን የሚገልጸው በአብ ቀኝ ተቀምጦ የሚማልድልን ሊቀ ካህን ስላለን የምንቀበለውንም በረከት ጭምር ነው። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ጥላቻ ኃጢአት ለሚሠሩ ሰዎች በፀጋው ያዘጋጀውን የደኅንነት መንገድና ከልጆቹ የሚጠብቀውን የተቀደሰ አኗኗር በበለጠ የምንረዳው እነዚህን ሁለት መጻሕፍት አጣምረን ስናጠና ነው።

ይህንን መጽሐፍ በምታጠናበት ወቅት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን መማሪያ በጥንቃቄ አንብብ። በጥንቃቄ አስበህ ለጥያቄዎቹ መልስ ስጥ። የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት አድርገን በግል ማጥናት እንደሚገባን ማወቅ ይገባናል። ይህም ሊሆን የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን በደንብ ስናጤንና ጥያቄ ስንጠይቅ ነው። ስለዚህም ወደ ማብራሪያው ከመሄድህ በፊት ቀስ ብለህ የተሰጠህን ክፍል አንብበህ ጥያቄዎቹን መልስ። ማብራሪያው ላይ ያልተጠቀሱ ነገሮችን በዚህ አጋጣሚ ልታገኝ ትችላለህ። ማብራሪያው አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ

ላየው ነገር የሰጠው ትርጓሜ ብቻ እንደሆነ አስተውል። ስለ መልሶቹና እያሰብክ በዚህ ጥናት ያገኘኸውን ቁም ነገር በሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሞክር። የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ብቻ ሳይሆን ልንጠብቀውና ልንታዘዘውም ይገባናል፤ ሮሜ 15:4። «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» ይላል።

ይህ መጽሐፍ እንደ ጥናት መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን እንደ ማብራሪያም እንዲያገለግል ተደርጎ ነው የተዘጋጀው። ኦሪት ዘሌዋውያንንም ሆነ ዕብራውያንን ስታጠና ወይም ስትማር ይህን መጽሐፍ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

የጥያቄዎችን መልሶች በደብተር ላይ ጻፍ። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ከሌለህ ለጥናትህ ስለሚረዳህ ለማግኘት ሞክር። ሌላ የኦሪት ዘሌዋውያንና የዕብራውያን ማብራሪያ ካገኘህ ከዚህ መጽሐፍ ጋር አብረህ ብታጠና ይረዳሃል። አዲስ የተተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ ብትጠቀም ይመረጣል።

ትምህርቶቹ ለተማሪው በሚመች ሁኔታ በአምስት ቀናት ተከፋፍለው ይገኛሉ። የአንዱን ቀን ክፍል አንዴ እንደተቀመጥክ ለመጨረስ ሞክር። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ከሌሎቹ ረዘም ይላሉ፥ ስለዚህ ሳምንታዊው ስብሰባ ከመድረሱ በፊት ትምህርቶቹን ማጠናቀቅህን እርግጠኛ ሁን። በትምህርቶቹ ጣልቃ ብዙ የምታነባቸው ጥቅሶች ተሰጥተዋል። «ተመልከት» ተብሎ ትዕዛዝ የተሰጠባቸውን እንድትመለከታቸው። «ተመልከት» የሚል ትዕዛዝ ያልተሰጣቸውን ግን እንደፍላጎትህ ልትመለከታቸውም ላትመለከታቸውም ትችላለህ።

# ትምህርት አንድ

## የኦሪት ዘሌዋውያን መግቢያ

ኦሪት ዘሌዋውያን ከሙሴ አምስት የሕግ መጻሕፍት መካከል አንዱ ነው። ኦሪት ዘፍጥረት ስለ ዓለም አፈጣጠርና የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆኑት ስለ እሥራኤላውያን ይናገራል። ኦሪት ዘጸአት ደግሞ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እሥራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት አውጥቶ ከእነርሱ ጋር በሲና ተራራ ቃል እንደገባ የሚገልጸውን ታሪክ ያካተተ ነው። ኦሪት ዘሌዋውያን ደግሞ ለቃል ኪዳኑ ሕዝብ የተሰጠውን ሕግ ያካተተ ነው። ይህ ሕግ የተሰጠው ሕዝቦቹ እግዚአብሔርን በትክክል እንዲያመልኩና በሱ ፊት የተቀደሱ ሕዝቦች ሆነው እንዲኖሩ ነው። ኦሪት ዘኍልቁ ደግሞ የእሥራኤል ሕዝብ ከሲና ተራራ በኋላ ባለማመናቸው ምክንያት በምድረ በዳ ስለ መንከራተታቸው እና በኋላም ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ስለ መዘጋጀታቸው የሚያወሳ ታሪክ ነው። ኦሪት ዘዳግም ደግሞ ወደ እሥራኤል ምድር ከመግባታቸው በፊት ሙሴ እንደገና ለአዲሱ ትውልድ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለ መስጠቱ የሚናገር ታሪክ ነው።

# ኦሪት ዘሌዋውያን ስለሚለው ርዕስ

1ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘሌዋውያን የሚለው ርዕስ በግዕዝም ሆነ በአማርኛ ትርጉሙ ምንድነው? ትርጉሙን የማታውቀው ከሆነ አንድ የኦርቶዶክስን ቄስ ጠይቅ።

«ኦሪት ዘሌዋውያን» የሚለው ስያሜ የመጣው «ሌዋውያንን በተመለከተ» ከሚለው ትርጉም ከያዘው ከግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሌዊ ከያዕቆብ ልጆች መካከል አንዱ እንደነበር ታስተውላለህ። እግዚአብሔር የካህናት ዘር አባት እንደሆነ መርጦታል። የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ለካህናት የተሰጡ መመሪያዎችን ይዟል። እነዚህም መመሪያዎች የተሠጡት ለቅዱሱ አምላክ የሚቀርበውን የአምልኮ ሥርዓት ንጽሕና ለማረጋገጥ ሲባል ነው። ኦሪት ዘሌዋውያን ለካህናት የተሰጡ መመሪያዎችን ብቻ ያካተተ አልነበረም። መላው የእሥራኤል ሕዝብ የተመረጡ ሕዝቦች እንደሆኑና በእግዚአብሔር ፊት እየኖሩም የማያቋርጠውን በረከት ከእግዚአብሔር ሊቀበሉ የሚያስችላቸውንም መመሪያ ሁሉ ያጠቃልላል።

እኛም ብንሆን በእግዚአብሔር የተመረጥን ሕዝቦች ነን። ሁላችንም ካህናት ነን (1ጴጥ.2፡9 ተመልከት)። እግዚአብሔር እርሱን እንዴት በትክክል እንደምናመልከውና በእርሱም ፊት እንዴት በተቀደሰ ሕይወት መኖር እንደምንችል የሚያሳዩንን መመሪያዎች ሰጥቶናል። መመሪያዎቹ ሁሉ የሚገኙት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በደንብ ባወቅን መጠን፥ ለእግዚአብሔር ያለን አምልኳችንም በዚያው መጠን ንጹሕና አስደሳች ይሆናል። በተጨማሪም ሕይወታችን በሱ ፊት የበለጠ የተቀደሰ ይሆናል። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የሰጠንን መመሪያዎች ምን ያህል ታውቃለህ?

2ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘሌዋውያን 27፡34 አንብብ።

ሀ) በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ የሚገኙት ትዕዛዞች የተሰጡት ለማነው?

ለ) እነዚህን ትዕዛዞች የተቀበለው የት ሆኖ ነው?

## ጸሐፊው

ኦሪት ዘሌዋውያን 27፡34 እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሕግጋት ለሙሴ በሲና ተራራ ላይ እንደሰጠው ይናገራል። ነገር ግን ሙሴ ማን ነበር? ምንስ ዓይነት ሰው ነበር? ሕዝቡን እንዲመለከት እግዚአብሔር ሙሴን እንዴት ጠራው?

3ኛ ጥያቄ:- በራስህ የግል ጥናት ላይ ተመርኩዘህ ስለ ሙሴ የምታውቀውን ነገር በሙሉ በዝርዝር ጻፍ።

- ከየትኛው ወገን ነበር?

- የተወለደበት ሁኔታ ከሌላው ለየት የሚያደርገው ነገር ምንድነው?

ሲያስተምሩ እንዳይቸገሩ ብሎ ነው። በሌላ አነጋገር መጽሐፉ እንደ መምህራን መመሪያ ተደርጎ ነው የተጻፈው።

የአሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡- አንደኛው ክፍል፡- ስለመሥዋዕቶቹ ኃጢአተኞች እንዴት ይቅር ተብለው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ግደስ እንደሚችሉ የሚያስረዳ ነው፤ (ምዕራፍ 1-15)።

ሁለተኛው ክፍል፡- እግዚአብሔር የሚመለከባቸውን የተለያዩ ሕጋጋት ያስረዳል። በተጨማሪም በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ንጹሕ መሆን እንደሚችል ያሳያሉ፤ (ምዕራፍ 16-27)። የአሪት ዘሌዋውያንን መጽሐፍ ዋና ዋና ሐሳቦች ሰፋ ባለ መልካቸው የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) እግዚአብሔርን ለማምለክ ሲባል የተሰጡ አምስቱ ዋና ዋና መሥዋዕቶች፤ (ምዕራፍ 1-7)

1. አምስቱ ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ መሥዋዕቶች እንዴት እንደሚቀርቡ የሚያሳዩት፤ (ምዕራፍ 1-6፡7)።

2. መሥዋዕቶቹን በተመለከተ የተሰጡ ተጨማሪ መመሪያዎች፤ (ምዕራፍ 6፡8-7)።

ለ) የእግዚአብሔርን አምልኮ ለመምራት የአሮንና የካህናቱ ዝግጅት፤ (ምዕራፍ 8-10)።

ሐ) በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሆኖ ስለ መገኘት የተሰጠ ትዕዛዝ (ምዕራፍ 11-15)።

መ) ኃጢአታቸውን የሚያስተሰርዩበት በዓል፤ (ምዕራፍ 16)።

ሠ) በእግዚአብሔር የተመረጡ ቅዱሳን ሰዎች በቅድስና እንዴት መኖር እንደሚገባቸው የተሰጠ መመሪያ፤ (ምዕራፍ 17-25)።

ረ) የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅም ሆነ በመተላለፍ ሊኖሩ የሚችሉትን በረከቶችና ቅጣቶች የሚያሳይ፤ (ምዕራፍ 26)።

ሰ) ለእግዚአብሔር የሚሰጡ ስለቶችን በተመለከተ የተሰጡ ሕጋጋት (ምዕራፍ 27)።

ዛሬ እነዚህን ሕጋጋት በስፋት በምንመለከትበት ወቅት ሊያስገርሙን ይችላሉ፥ ነገር ግን በንጻሩም ብዙ ጠቃሚ የሆኑ እውነታዎችን ሊያስተምሩን ይችላሉ። በመጀመሪያ እኛ እንዴት አድርገን እንደምናመልከውና እንደምናቀርበው የሚወስነው እግዚአብሔር እራሱ እንደሆነ ማስተዋል ይገባናል። ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ሁሌ እሱ ያዘጋጀውን የአምልኮ መንገድ መጠቀም አለብን። በራሳችን መንገድ ተነሣሥተን እንዳናመልከው መጠንቀቅ ይኖርብናል።

4ኛ ጥያቄ፡- ሰዎች አንዳንዴ እንዴት አድርገው ነው የእግዚአብሔርን አምልኮ መንገድ ከመጠቀም ይልቅ የራሳቸውን አስተሳሰብ በመጠቀም እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሞክሩት?

ሁለተኛ እግዚአብሔር ስለ አምልኮአችን ብቻ ሳይሆን ስለ ጥቃቅኗ የአኗኗራችን ሁኔታ ሁሉ ያስባል። ከሌሎች ጋር ስላለን ግንኙነት የሕይወታችንን ንጽሕና በተመለከተ ስለ አበላላችንና ስለ አጠጣጣችን እንኳ ያስባል፥ (1ኛ ቆሮ. 10፡31)። በአምልኮአችን ብቻ ሳይሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝቦች ሁለንተናችንም የተቀደሰ ሊሆን ይገባዋል።

5ኛ ጥያቄ፡- ለኛ ተራና የተለመዱ መስለው የሚታዩን ነገሮች ለእግዚአብሔር ስም ግን ክብርን ወይም ውርደትን ሊያደርሱ የሚችሉ አንዳንዶችን ጥቀስ።

## የኦሪት ዘሌዋውያን መሪ ሐሳብ

6ኛ ጥያቄ፡- ኦሪት ዘሌዋውያን 11፡44-46፥ 19፡2 ተመልከቱ።

ሀ) የእግዚአብሔር ባህርይ እንዴት ሆኖ ነው የተገለጠው?

ለ) እግዚአብሔር የእሥራኤላውያን ባህርይ እንዴት ዓይነት መሆን አለበት ይላል?

የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ መሪ ሐሳብ «ቅዱስ» በሚለው ቃል ሊጠቃለል ይችላል። በአጠቃላይ በመጽሐፉ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ነው የተጠቀሰው። ሕዝቦቹም ልክ እንደ እርሱ «ቅዱሳን» እንዲሆኑ ይፈልጋል።

7ኛ ጥያቄ፡- በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ «ቅዱስ» የሚለውን ቃል ተመልከት። «ቅዱስ» የሚለውን ቃል ትርጓሜ በእራስህ አባባል ጻፈው።

የቅድስና መሠረቱ መለየት የሚለው ሐሳብ ነው። ይህ የመለየት ሐሳብ ሁለት መልኮችን ይይዛል። እነርሱም፡-

አንደኛው፡- ከአንድ ነገር ልዩ የመሆንን ወይም የመለየትን ሐሳብ ያመለክታል። እግዚአብሔር ቅዱስ ተብሎ የሚጠራው ከራሱ ፍጥረታት ሁሉ የተለየና ታላቅ የሆነ በመሆኑ ነው። በዚህም መልኩ የእሥራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር በተመረጡበት ወቅት ከአሕዛብ ሁሉ ስለተለዩ ቅዱሳን ናቸው፤ (ኦሪት ዘሌዋውያን 20፡26)። እግዚአብሔር ያንን ሁሉ ትዕዛዝ የሰጠበት ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሕዝቦች ካልሆኑ ጋር ያላቸውን ልዩነት ለማመልከት ነው።

ሁለተኛ፡- ቅድስና ኃጢአትን ለማመልከት እንጠቀምበታለን። እግዚአብሔር ቅዱስ የሆነው ከፍጥረታት ሁሉ የተለየ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ምንም ኃጢአት ስለሌለበትም ጭምር ነው። እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ቅዱስ እንዲሆኑ ራሳቸውን ከኃጢአት እንዲጠብቁ ጠራቸው። ነገር ግን ቅድስና እራሱ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት መኖር ማለትም ነው። እሥራኤላውያን እራሳቸው ከኃጢአት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በፍቅር በሠላምና በቅድስና የተሞሉ ሊሆኑ ይገባቸዋል። በእውነት ቅዱስ ለመሆን ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይጠይቃል። ይህ በእምነትና በመታዘዝ የተገነባው ግንኙነታችን በዕለት ዕለት ኑሮአችን መታየት ይኖርበታል።

እንዲህ እያለ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ታግዘን የእግዚአብሔርን ባህርይ በሕይወታችን እናሳያለን ማለት ነው።

እኛም ብንሆን የተቀደስን ሕዝቦች እንደሆንንና የተቀደሰ ኑሮ እንድንኖር ተጠርተናል! (1ጴጥ.1፡15-16፥ 2፡9-10 ተመልከቱ)። ከዓለም የተለየን እንድንሆን ነው እግዚአብሔር የመረጠን። ሕይወታችን ከማያምኑ ሰዎች ሕይወት የተለየ መሆን አለበት። የተለየ ነውን?

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድ ክርስቲያን ቅዱስ መሆኑን ሊያስመሠክር የሚችልባቸውን አንዳንድ መንገዶች ግለጽ።

ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች የተቅደሰ ሕይወት ሊኖራቸው ያልቻለበትን ምክንያት ዘርዝረህ ጻፍ። እንዴት አድርገህ ነው የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖራቸው ልታበረታታቸው የምትችለው?

## በኦሪት ዘሌዋውያን ያሉት ቁልፍ ቃላት

ለኦሪት ዘሌዋውያን ዋና ዋና ትምህርቶች መሠረት የሆኑ ሁለት ቁልፍ ቃላት አሉ። አንደኛ «ቅዱስ» የሚለው ቃል ነው። ቃሉ ከዘጠና ጊዜ በላይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሷል።

9ኛ ጥያቄ፡- ኦሪት ዘሌዋውያን 20፡26 ተመልከት። ይህን ጥቅስ በቃልህ አጥና።

ሁለተኛው ቃል «ማስተሰረይ» ነው። (በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ይህንን ቃል ተመልከት) ይህ ቃል አርባ አምስት ጊዜ በኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ላይ ተጠቅሷል። «ማስተሰርይ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ ነው። በዚህ የደኅንነት መንገድ አማካኝነት ኃጢአተኛው ሊያሟላ የሚገባውን ነገር ያሳየዋል። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ለመሥዋዕት የቀረበችው ንጹህ እንስሳ ነበረች የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ የምትከፍት። በአዲስ ኪዳን ጊዜ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ነው ለኃጢአተኛው ሰው የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ የሚከፍትለት።

10ኛ ጥያቄ፡- ኦሪት ዘሌዋውያን 17፡11 ተመልከት። በቃልህ አጥናው።

## የኦሪት ዘሌዋውያን ዋና ዓላማ

በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ከእሥራኢላውያን ጋር ቃል ኪዳን እንዳደረገ ተመልክተናል። እነርሱ የእርሱ ሕዝቦች እርሱ ደግሞ አምላካቸው መሆን ነበረበት። እግዚአብሔር በመካከላቸው ይኖር ነበር። የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ የተጻፈው እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እርሱን ማምለካቸውን እንዳያቋርጡና በመካከላቸው ሁሌ የእርሱ መኖር እንዳያቋርጥ ሲባል ነው። እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ይባርክ የነበረው ቅድስናቸውን ሲጠብቁ ብቻ ነበር።

11ኛ ጥያቄ:- እንዴት ነው ይህ እግዚአብሔር እኛን ከሚያስተዳድርበት ሥርዓት ጋር የሚመሳሰለው?

# ሦስተኛ ቀን:-

## የኦሪት ዘሌዋውያን ዋና ዋና ትምህርቶች

1. እግዚአብሔር በሕዝቦች መካከል ይኖራል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ይገኝ የነበረው በተለይ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በኋላም በቤተ መቅደስ ውስጥ ነበር። ይህ ክብሩ ይንፀባረቅበት የነበረው ቦታ ነው። ስለዚህም ሁሉም መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው በእግዚአብሔር ፊት ነው። በተጨማሪም የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ እግዚአብሔር ልጆቹን ስለሚቀናቀኑ ማንኛቸውም ነገሮች ግድ እንደሚለው ያስተምረናል። አኗኗራችን በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ይታያል። ስለዚህም ነው ልጆቹ በቤታቸውም ጥምር ንጹሐንና የተቀደሱ መሆን የሚገባቸው።

12ኛ ጥያቄ:- 1ኛቆር.3:16-17፥ 6:19-20 አንብብ። ክርስቲያን በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተሰጠው ስያሜ ምንድን ነው?

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በተለይ ይገኝባቸው የነበሩት ቦታዎች የመገናኛው ድንኳን ወይም ቤተ መቅደሱ ነበሩ። ዛሬ ግን እግዚአብሔር ክብሩን በቤት (በሕንፃ) ውስጥ አያኖርም። እንዲያውም ክብሩንና እሱነቱን በተሰበሰቡት በክርስቲያኖች ውስጥም ሆነ በግለሰብ ያኖራል። እያንዳንዳችን እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤተ መቅደስ ነን። ቤተ መቅደሳችንን በእኛ ውስጥ የሚኖረውን እግዚአብሔርን በሚያስከብር ሁኔታ እየተጠቀምንበት ነውን?

13ኛ ጥያቄ:- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የመሆናችን እውነታ በአካላችን ያለንን አመለካከትና አኗኗራችንን የሚለውጠው እንዴት ነው?

2. ኃጢአተኛ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ኅብረት ሊኖረው የሚችለው በመሥዋዕት ብቻ ነው። በኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ውስጥ አሥራ ሰባቱ ምዕራፎች መሥዋዕትን በተመለከተ የተለያዩ ሁኔታን በማስታከክ ገለጻ ይሰጣሉ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ኃጢአት እንደሚሠሩና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውም ኅብረት እንደሚጠፉ ተገምቶ ነበር። በዚህም ምክንያት አሥራ ሰባት የሚያህሉ ምዕራፎች በመሥዋዕት እንዴት አድርጎ የእሥራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት እንደገና ሊያድስና ሊያጎለብት እንደሚችል ይናገራሉ።

14ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘሌዋውያን 17:11 አንብብ።

ሀ) ለሕዝቡ ኃጢአት ስርየት ሲባል ምን ነበር የሚጠቀሙት?

ለ) ኢየሱስ ለእኛ ካደረገው ነገር ጋር እንዴት ነው የሚመሳሰለው? (ዕብራውያን 9:11-14 ተመልከቱ)

በመሥዋዕቶቹ ጊዜ የንጹሕ እንስሳ ደም ጥፋተኛ በሆነው ኃጢአት የሚሸረውና እግዚአብሔርም የሚቀበለው ይህንን ደም ነው። ኃጢአት በሠራን ቁጥር ሌላ አዲስ መሥዋዕት ከማድረግ ኢየሱስ ለእኛ ሲል ደሙን አንዴ ስላፈሰሰ ኃጢአታችን በሞላ ተሰርዮልናል።

3. እግዚአብሔር ከሕዝቦቹ ጋር ያለው ግንኙነት የተመሠረተው በቃል ኪዳት ላይ ነው። በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን ገባ። ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ በኦሪት ዘሌዋውያን ላይ ባይጠቀስም የመጽሐፉ መሠረት የሆነው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን መግባቱ ነው። የመጀመሪያው የመጽሐፉ አጋማሽ የቃል ኪዳት ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚኖርባቸው ሲያሞለክት ሁለተኛው አጋማሽ ደግሞ የቃል ኪዳት ሕዝብ እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ይናገራል።

ዛሬ በአዲሱ ቃል ኪዳን ሥር ነው የምንኖረው፤ (ዕብ8፡7-13)። እግዚአብሔር በፀጋው በጌታ ኢየሱስ በመጠቀም ይህንን ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ከእኛ ጋር ገባ። እግዚአብሔር ቃል የገባልንን በረከቶች ተካፋዮች እንዲሆን ለእግዚአብሔር የታዛዥነት ሕይወት ልንኖር ይገባል።

4. የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ሊመስል ይገባል። እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ሕዝቡም ቅዱስ መሆን አለበት፤ (ቆላ.1፡2፥ 1ጴጥ.1፡2፥ 2፡9-10)። የኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ መሪ ሐሳብ ቅድስና እንደሆነ ተመልክተናል። እግዚአብሔር እራሱ ሕዝቡ ሊከተሉት የሚገባው ምሳሌ ነው። ንጹህ ያልሆነ ማንኛውም ነገር ሁሉ ጠርቶ ቅዱስ ሊሆን ይገባዋል። እኛም ልክ እንደ አባታችን ልንሆን ይገባናል። ሕይወታችን የእርሱን ፍቅር ትዕግሥትና ቅድስና ሊያንፀባርቅ ይገባል። እንደ አባታችን እንዳንሆን ሊያደርገን የሚችለውን ማንኛውንም ነገር ሁሉ ማውደምና ማስወገድ አለብን። ሕይወታችንን በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር ክብር ልናውለው ይገባል።

15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር ክብር ነው ወይ የምትኖረው?

ለ) አንዳንድ ጊዜ ሕይወትህ ንጹህ እንዳይሆን የሚያደርጉት አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

# አራተኛ ቀን፡-

## የመገናኛው ድንኳን

እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚገባ የተጠቀሱትን ትዕዛዛት ከመመልከታችን በፊት የማምለኪያ ቦታ ስለሆነው ስለ መገናኛው ድንኳን በትንሹም ቢሆን መመልከት ይኖርብናል። ስለ መገናኛው ድንኳን የተሰጠ ጠለቅ ያለ ትምህርት ክርስቶስ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ልናገኘው እንችላለን። ስለ አምልኮ በኦሪት ዘሌዋውያን የተሰጡት ሕግጋት የአምልኮ ቦታ ስለሆነው የመገናኛው ድንኳን ሁኔታ ስናጠና በደንብ ሊገቡን አይችሉም።

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኦሪት ዘጸአት 35፡30-38፡31፥ 40፡1-38 ያለውን አንብብ።

ለ) የመገናኛ ድንኳን የሚለውን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ተመልከት።

ሐ) ሁለቱን የመገናኛ ድንኳኑን ክፍሎች ጻፍ። ለአምልኮ የተጠቀሙባቸውን ስድስቱን መሣሪያዎች በዝርዝር ጻፍ።

በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ እሱ የሚኖርበትን ቤት ንድፍ ሰጠው። ይህ ቤት መገናኛው ድንኳን ነበር። የእስራኤል ልጆች በበረሃው ይንከራተቱ ስለነበር መገናኛው ድንኳን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ እንዲንቀሳቀስ ተደርጎ ነበር የተሠራው። በኋላ ላይ ሰለሞን ቋሚ የሆነውን እግዚአብሔር የሚመለክበትን የመጀመሪያውን ቤት መቅደስ ሠራ። እንደ መገናኛው ድንኳን ዓይነት ሆኖ ነበር የተሠራው፤ ያም ቢሆን ቤተ መቅደሱ በጣም ትልቅ ነበር። በሁለቱም መቅደሶች ውስጥ የእራሱን መኖር ለማብሰር ሲል እግዚአብሔር ክብሩን አኑሮአል! (1ኛ ነገሥት 8፡6-13)።

ከመገናኛው ድንኳን የሚከተሉትን ነገሮች ልንማር እንችላለን።

## 1. የመገናኛው ድንኳን ዓላማ፡-

እግዚአብሔር ከሰው እርቆ መኖርን አይፈልግም። ስለዚህ በእነርሱ መካከል ኖረ። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ መገናኛ ድንኳኑን ሕዝቡ ከሠፈረበት ቦታ እርቆ እንዲተከል አላደረገም። እንዲያውም በመካከላቸው እንዲተከል ነው ያደረገው። መገናኛው ድንኳንና የእግዚአብሔር አምልኮ በሕይወታችን ውስጥ ዋነኛውን ቦታ ሊይዝ ይገባዋል። እግዚአብሔር የሚኖረው በመካከላቸው ነበር! ይህም ቦታ እግዚአብሔር በከፈተው መንገድ ለሚመጣ ሰው ሁሉ ክፍት ነበር። እግዚአብሔር የመገናኛውን ድንኳን ዓላማ እንደሚከተለው አስቀምጦታል፡-

1. እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ይኖር ዘንድ (ኦሪት ዘጸአት 25፡8)
2. እግዚአብሔር ከኃጢአተኛው ጋር እዚያው ይገናኝ ዘንድ (ኦሪት ዘጸአት 25፡22)
3. እግዚአብሔር እራሱን በዚያው ቦታ ይገልፅ ዘንድ (ኦሪት ዘጸአት 29፡46)
4. እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በዚያው ቦታ ይናገረው ዘንድ (ኦሪት ዘጸአት 29፡42)
5. እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በዚያው ቦታ ይቅር ይለው ዘንድ (ኦሪት ዘሌዋውያን 4፡31)
6. እግዚአብሔርን በዚያው ሥፍራ ያመልኩት ዘንድ (ኦሪት ዘጸአት 28፡38) ነበር፥ እኛም እራሳችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ነን (1ኛ ቆሮ.3፡16-17)። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እግዚአብሔር ሊያደርጋቸው የሚፈልጋቸውን ማገኛቸውንም ነገሮች በእኛም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያደርግ ይፈልጋል።

**17ኛ ጥያቄ፡-** እግዚአብሔር ለመገናኛው ድንኳንና ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ዓላማ አነፃፅር። ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ስድስት ነገሮች ተግባራዊ የምታደርገው እንዴት ነው?

ከዚህ ቀጥሎ ስለ መገናኛው ድንኳን የተሰጠውን ሥዕላዊ መግለጫ አጥና።




## 2. በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያሉት ክፍፍሎች፡-

እግዚአብሔር ክብሩ የሚገኝበትን የመገናኛውን ድንኳን ክብሩ በማይጠበቅበት ቦታ መካከል አላስቀመጠውም። መገናኛው ድንኳን እግዚአብሔር የሚመለክበት ቅዱስ የሆነ ቦታ ነበር። ሰዎች ዝም ብለው የሚመጡበት፣ የሚሄዱበትና የፈለጉትን የሚናገሩበት ቦታ አልነበረም። በታላቅ ክብር ሊታይ የሚገባ ቦታ ነበር።

መገናኛው ድንኳን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።

ሀ) ከመገናኛው ድንኳን ውጪ:- ወደ መገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚያስገባ አንድ ትልቅ በር ነበር። ድንኳኑም በአንድ ትልቅ ግንብ የተከበበ ነበር። ምንም እንኳን አንድ ሰው እሥራኤላዊ ቢሆንም፥ እግዚአብሔርን ለማምለክ በዚህች አንድ በር በማለፍ ድንኳኑ ውስጥ መግባት ነበረበት። ልክ እንደበፊቱ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ መጥተው እንዲያመልኩት ቢፈልግም ሁሉም ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችሉት አንድና ብቸኛ በር በሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው፤ (ዮሐንስ 14:6፥ 10:9)።

ለ) የመገናኛው ድንኳን ግቢ:- በመገናኛው ድንኳን በር ስንገባ ወደ ግቢው እንደርሳለን። በዚህ የውጪኛው ግቢ ውስጥ ሁለት የማምለኪያ መሣሪያዎች አሉ። እነዚህም በነሐስ የተሠሩ መሠዊያና መታጠቢያ ሳሕን ናቸው። በዚህ በመገናኛው ድንኳን ግቢ ውስጥ ነበር እሥራኤላውያን መሥዋዕታቸውንና ምሥጋናቸውን የሚያቀርቡት። አንድ ተራ እሥራኤላዊ ይገባ የነበረው እዚህ ድረስ ነው። በዚህ ቦታ ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኛል፥ የእግዚአብሔርን ቃል ይማራል፥ ከእግዚአብሔር ለኃጢአቱ ስርየት ያገኛል። ይህ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ስለመሆን የሚያስረዳ ጥሩ ሥዕላዊ መግለጫ ይሆናል። በዚህ በክርስቶስ አካል ውስጥ ስንሆን ነው ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኘው፥ እርሱን የምናመልከውና ከእግዚአብሔር ልንማር የምንችለው።

ሐ) ቅዱስ ቦታ:- በግቢው ውስጥ 15 ሜትር በ5 ሜትር የሆነች አንድ ትንሽ ድንኳን አለች። ይህችም ድንኳን እግዚአብሔር የሚኖርባት የመገናኛው ድንኳን ናት። በዚህች ድንኳን ውስጥ ሁለት ክፍሎች አሉ፥ ሰፋ ያለው ክፍል ቅዱስ ቦታ ሲባል፥ ጠበብ ያለችው ደግሞ ቅድስተ ቅዱሳን በመባል ትታወቃለች። ወደ ቅዱስ ቦታ መግባት የሚችሉት ካህናት ብቻ ናቸው። በዚህ ቦታ እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር። የሚያገለግሉትም መብራቱን ሁሌ በማብራት የዕጣን መሥዋዕት በማቅረብና የእህሉን ቁርባን በመቀየር ነበር። እኛም እራሳችን የእግዚአብሔር ካህናት ነን፥ (1ጴጥሮስ 2:5)። እንደ እግዚአብሔር ካህናት እኛም በእርሱ ፊት መንፈሳዊ መሥዋዕታችንን ማቅረብ አለብን። የምስጋና መሥዋዕታችንን እናቀርባለን፥ ክብሩን በተመለከተ ለሌሎች እንመሠክራለን፥ ወዘተ።

መ) ቅድስተ ቅዱሳን:- በድንኳኑ በስተመጨረሻ አንዲት ክፍል አለች። ቅዱሱን ቦታ ከቅድስተ ቅዱሳኑ የሚለይ አንድ ትልቅ መጋረጃ አለ። በቅዱስተ ቅዱሳኑ ክፍል ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት አለ። ከዚህ ከቃል ኪዳኑ ታቦት በላይ የእግዚአብሔር ክብር የሚያርፍበት ቦታ ነበር። ከሊቀ ካህኑ በስተቀር ማንም እዚህ ቦታ መግባት አይችልም ነበር። እርሱም መግባት የሚችለው በዓመት አንዴ በማስተሰሪያ ቀን ብቻ ነው።

እንደምታስታውሱት ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ ጊዜ እነዚህን ሁለቱን ክፍሎች ይከፍል የነበረው መጋረጃ ተቀደደ። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ክብሩን

ሸሽጎ፣ ሰዎች በዛ ቦታ እንዲመጡም ከፈለጉ ብዙ ጥንቃቄዎችን እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል። አሁን ግን በክርስቶስ ደም በኩል ወደ እርሱ እንደርሳለን፣ ይህም የታላቁ አምላክ ዙፋን የሚገኝበት መንግሥት ሰማያት ድረስ ያለ ምንም ዕዳ በነፃነት ልንቀርብ እንችላለን ማለት ነው።

18ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 4:16፤ 10:19-22 አንብብ።

ሀ) ወዴት ነው ክርስቲያኖች በድፍረት የመግባት መብት የተሰጣቸው?

ለ) ይህን መንገድ የከፈተልን ማነው?

19ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከላይ ያየነውን የመገናኛውን ድንኳን ክፍፍል ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክፍፍል ጋር አነፃፅር።

በምን መልኩ ነው የሚመሳሰሉት? በምን መልኩስ ነው የሚለያዩት?

ለ) ይህንን ክፍፍል ከአንተ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ጋር ስታነፃፅረው እንዴት ነው?

## 3. በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያሉ ለአምልኮ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች:-

በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ስድስት ለአምልኮ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች አሉ። እያንዳንዱ መሣሪያ የራሱ የሆነ ሥራ አለው፤ ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ያመለክታል።

ሀ) በነሐስ የተሠራው መሠዊያ:-

በውጪኛው ግቢ ውስጥ የሚገኘው ይህ መሠዊያ ለኃጢአተኛው ዋነኛ የሆነ የአምልኮ መሳሪያ ነው። በዚህ ቦታ ላይ ነበር ሁሉም መሥዋዕቱን ለጌታ የሚያቀርበው። በእምነት መሥዋዕታቸውን ያቀረቡ ሰዎች በዚህ ቦታ ላይ ነበር ለኃጢአታቸው ስርየት የሚያገኙት።

ይህ የነሐስ መሠዊያ ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ጋር ሊነፃፀር ይችላል። ኢየሱስ እራሱን ለእኛ መሥዋዕት አድርጎ የሰጠው በመስቀሉ ላይ ነው። እዚያው መስቀል ላይ፤ ኢየሱስ የኃጢአታችንን ይቅርታና የደኅንነታችንን ዋጋ ከፈለልን።

ለ) በነሐስ የተሠራው መታጠቢያ ሰሐን:-

ይህም መሣሪያ የሚገኘው በውጪኛው ግቢ ውስጥ ነበር። ይህን መሣሪያ ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ አገልግሎት ለማቅረብ ሲፈልጉ ነበር ካህናቶቹ ብቻ የሚጠቀሙበት። ወደ መቅደሱ ቦታ ከመግባቱ በፊት ካህኑ እግሩንና እጁን ሁሌ ይታጠብ ነበር።

ይህ ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ መሥዋዕታችንን ስናቀርብ እራሳችንን ሁሌ ንጹሕ አድርገን ማቅረብ እንዳለብን ሊያስገነዝበን የሚችል ጥሩ ሥዕላዊ መግለጫ ነው። ምንም

እንኳ የኃጢአታችንን ዋጋ ኢየሱስ በመስቀሉ ቢከፍልልንም በእርሱ ፊት ሁሌ ንጹህ ሆነን ለመቅረብ ስንል ሁሌ ኃጢአታችንን መናዘዝ አለብን፤ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)።

ሐ) መቅረዝ፡-

በቅዱሱ ቦታ ከሚገኙት ሦስት የተለያዩ መሣሪያዎች ውስጥ አንዱ መቅረዙ ነው። ከወርቅ የተሠራው ይህ መቅረዝ ሁሌ ቀንና ማታ መብራት ነበረበት። ሁልቀን ካህናቶቹ ወደ ተቀደሰው ቦታ በመግባት መብራቱ እንዳይጠፋ ዘይት ይጨምሩበት ነበር። ይህ መቅረዝ ለቅዱሱ ቦታ ብርሃን ይሰጣል።

ካህናቶቹ መሥዋዕታቸውን ሲያቀርቡ መቅረዙ ብርሃን እንደሚሰጣቸው ሁሉ ኢየሱስም የዓለም ብርሃን ነው፤ (ዮሐ 8፡12)።

እኛም የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን የዓለምም ብርሃን ነን! (ማቴ.5፡14)።

መ) ገበታው፡-

ከመቅረዙ ፊት ለፊት ኅብስትና ዕጣን የተቀመጠበት አንድ በወርቅ የተሠራ ጠረጴዛ ነበረ። ኅብስቱ ሁልጊዜ በሰንበት ቀን በአዲስ ይተካ ነበር። የበፊቱን ኅብስት ካህኑና ልጆቹ በቅዱሱ ቦታ ሆነው ይበሉት ነበር። ይህ ኅብስት እግዚአብሔር ከእሥራኤላውያን ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳንና የዕለት ተዕለት ጉርሳቸውን የሚሰጣቸው እሱ እንደሆነ የሚገልጽ መታሰቢያ ነው፤ (ኦሪት ዘሌዋውያን 24፡8)።

ኢየሱስ ክርስቶስም የሕይወት እንጀራ ተብሎ ተሰይሟል! (ዮሐንስ 6፡35)። መንፈሳዊና ሥጋዊ ፍላጎታችንን የሚያሟላልን እሱ ነው፤ (ማቴ. 6፡25-34፤ ፊልጵ. 4፡19)።

ሠ) የዕጣን መሠዊያው፡-

ቅድስተ ቅዱሳኑን ከሚሸፍነው መጋረጃ ፊት ለፊት ዕጣን የሚጨስበት ከወርቅ የተሠራ ጠረጴዛ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት ዕጣኑ ሁሌ እንዲጨስ ካህኑ በቀን ሁለቴ እየገባ በዚህ ጠረጴዛ ላይ ዕጣን ይጨምር ነበር።

የሚጨሰው ዕጣን ብዙ ጊዜ የሚያመለከተው ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ጸሎት ነው። የእኛ ሊቀ ካህን የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንግሥተ ሰማያት በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ሁሌ ለእኛ ይማልድልናል! (ዕብራውያን 7፡25፤ ሮሜ 8፡31-34)። ዕጣኑ ሳያቋርጥ እንደሚጨስ ሁሉ እኛም ሳናቋርጥ እንድንጸልይ ታዘናል! (1ተሰ.5፡17)።

ረ) የቃል ኪዳኑ ታቦት፡-

ለኃጢአተኛው ዋነኛ የሆነ የአምልኮ መሣሪያ ከነሐስ የተሠራው መሠዊያ ነው። በእግዚአብሔር በኩል ሆነን ስንመለከተው ደግሞ ዋነኛው መሣሪያ ይህ የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው። ርዝመቱ 1.3 ሜትር ከፍታው 3/4 ሜትር የጎን ስፋቱ 3/4 ሜትር የሆነ ትንሽ የወርቅ ሳጥን በአንድ ወገን ሁለት ኪሩቤሎች በሌላው ወገን ደግሞ ሁለት ኪሩቤሎች የነበሩት ታቦት ነበር። የኪሩቤሎቹ ክንፎች በሳጥኑ ላይ ተዘርግተው ነበር።

ከክንፎቻቸው ሥር «የስርየት መክደኛ» ተብሎ የሚታወቀው የሳጥኑ መክደኛ ነበር። እንዲህ ተብሎ የተሰየመው በዓመት አንዴ በዚህ ክዳን ላይ ደም ሲረጭ ከምሕረቱ የተነሣ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ኃጢአት በሙሉ ይቅር ይል ስለነበር ነው። በታቦቱ ውስጥ አሥርቱ ትዕዛዝ የተጻፈባቸው ሁለቱ ፅላቶች፣ መና ያለበት የወርቅ መሶብና የለመለመችው የአሮን በትር ነበሩበት። የእግዚአብሔር ክብር ከስርየት መክደኛው በላይ ነበር የተቀመጠው። ከሌላው ቦታ ይበልጥ የእግዚአብሔር ክብር የሚገኝበት ቦታ እንደሆነ አድርገው ነበር የሚመለከቱት። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከሚገኙት የአምልኮ መገልገያዎች መካከል ይህ የቃል ኪዳኑ ታቦት ብቻ ነበር ወደ ሰለሞን ቤተ መቅደስ ውስጥ የገባው። ቤተ መቅደሱ በባቢሎናውያን በ586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከተደመሰሰ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የተነገረም ምንም ነገር የለም፤ (የዮሐ ራዕይ. 11፡19)።

ቦታ የለንም እንጂ ታቦቱን በተመለከተ ብዙ የተለያዩ እውነታዎችን ልናጠና በቻልን ነበር። እነዚህ እውነታዎች «ክርስቶስ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ» በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ። ምንም እንኳ ሙሴና ሌሎችም የእሥራኤል መሪዎች ቢሆኑ ሁሌ እውነተኛው የእሥራኤል ንጉሥ የነበረው እግዚአብሔር ነው። ታቦቱ ዙፋኑ ነበር። ታቦቱ የእግዚአብሔር መኖሪያ የሆነውን መንግሥተ ሰማያትን ሊወክል ይችላል። በሰማይ እግዚአብሔር በዘላለማዊው ዙፋን ላይ ተቀምጦ ይገዛል። ከዚያ ሆኖ ምድር ላይ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ሁሉ ይቆጣጠራል። ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን ለአብ ያቀረበው በዚሁ ቦታ ነው፤ (ዕብራውያን 9፡11-14)። አሁን በእምነት ጥያቄዎቻችንን ይዘን የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር በጸሎት በድፍረት ልንቀርብ እንችላለን። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊቀ ካህኑ በዓመት አንዴ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር እኛ በጸሎት አማካኝነት የፈለግነውን ያህል ጊዜ ልናደርግ እንችላለን። ይህ ታቦት ልባችንንም ሊያመለክት ይችላል። በሕይወታችን ላይ ይነግሥ ዘንድ ለመንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ልባችንን መስጠት ይኖርብናል። ምንም ጊዜ ቢሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ላለማድረግ በምንወስንበት ጊዜ፣ የሕይወታችን ንጉሥ እግዚአብሔር ሳይሆን እራሳችን እንድንሆን እየጣርን ነው ማለት ነው።

20ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትህ ንጉሥ መሆኑን በገሃድ ያሳየኸው በምን ዓይነት አኳኋን ነው?

በብሉይ ኪዳን ጊዜ አምልኮ ይደረግ የነበረው በአንድ በተወሰነ ሕንጻ ውስጥ ነበር። የዚህን ሕንጻ ንድፍ ያወጣ እግዚአብሔር ነው። እንደ እውነተኛው ሕያው አምላክ፣ የሚመለከበትን ሥርዓት ያወጣው እግዚአብሔር ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደምንምለከተው ግን እግዚአብሔር በአንድ በተወሰነ ቦታ ወይም ሕንጻ ውስጥ ብቻ አይመለክም፤ (ዮሐ.4፡21-24)። እግዚአብሔር እንደ ቤተክርስቲያን ባለ ሕንጻ ውስጥ አይኖርም። እግዚአብሔር የሚኖረው በሚያምኑት ሰዎች ልብ ውስጥ ነው። ስለዚህም እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን እያንዳንዳችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ነን። በልባችን ውስጥ እና በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል ነው ዋናው የአምልኮው ቦታ። እውነተኛ አምልኮ የሚደረገው ክርስቲያኖች በሚሰበሰቡበት ቦታ

ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ በልባችንና በሕይወታችን መደረግ አለበት ከእያንዳንዱ የአማኝ ልብ በመነሣት አምልኮ ከብዙ የእግዚአብሔር ልጆች ጋር በቡድን ሊደረግ ይችላል።

21ኛ ጥያቄ:- ሀ) በአንተ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ምዕመናን አምልኮ የሚኖረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ነው ብለው ያስባሉ? ለ) ክርስቲያኖች በኅብረት ለማምለክ ከመሄዳቸው በፊት ራሳቸውን በግል ያምልኮ ጊዜ እንዴት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያሚያሳዩ ምሳሌዎች ስጥ።

አምስተኛ ቀን:- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ፤ የመወያያ ጥያቄዎቹንም ተመልከታቸው።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ:-

መሪው ከ5-10 ደቂቃ የሚወስድ በዚህ ሳምንት ውስጥ ከተጠኑት ጥናቶች መካከል ያለ ሐሳብ ወይም ጥቅስ ወስዶ ለተማሪዎቹ የሚያካፍልበት የጥሞና ጊዜ ሊኖረው ያስፈልጋል።

2. ጸሎት:-

ለ10 ደቂቃ ያህል ስለ እያንዳንዳችሁና ስለ ቤተ ክርስቲያን ችግሮች ጸልዩ።

3. ክለሳ:-

ለ15 ደቂቃ ያህል በዚህ ሳምንት ትምህርት ላይ ክለሳ አድርጎ ትምህርቶቹን መጨረሳቸውን ለማረጋገጥና እንደገባቸውም ለማወቅ ሲሉ መምህሩ የተማሪዎቹን መልሶች ማረም አለባቸው። እያንዳንዱ ተማሪ ከትምህርቱ የተማረውን ነገር በዝርዝር ይጻፉ።

ለመሪው:- በዚህ ጊዜ ከዚህ ሳምንት ትምህርት የተውጣጣች አጠር ያለች ፈተና ለመስጠት ይፈልጉ እንደሆነ ይችላሉ።

4. ውይይት:-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከ45-60 ደቂቃ ያህል ጊዜ ወስዳችሁ ተወያዩባቸው። እያንዳንዱ ሐሳቡን እንዲያቀርብ ያረጋግጡ። እነዚህንም ጥያቄዎች ተግባራዊ የሆነ መልክ እንዲይዙ ያድርጓቸው።

ሀ) ከብሉይ ኪዳን ክህነት በምን መልኩ ነው የኛ ክህነት የሚለየው?

ለ) ዕለታዊ የሆኑ እግዚአብሔርን ልናስከብርበት የምንችልባቸው ነገሮች ምንድናቸው?

ሐ) 1. እንደ አንድ ቡድን ሆናችሁ «ቅዱስ» ስለሚለው ቃል ትርጉም ጻፉ።

2. ይህ ትርጓሜ ከእግዚአብሔር ባህርይ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

3. ከክርስቲያኖች ባህርይ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

4. በአኗኗራችን ውስጥ ቅድስናችንን ልናሳይ የምንችለው እንዴት ነው?

መ) እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እና በልባችን ውስጥ ያለውን አኗኗር አነፃፅር። እንዴት ነው የሚመሳሰሉት? እንዴትስ ነው የሚለያዩት?

ሠ) ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ሊመስሉ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝረህ ጻፍ። ቀልጭ ያሉ ምሳሌዎችን ስጥ።

ረ) እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለው ዓላማና ለእኛ ያለው ዓላማ እንዴት እንደሚመሳሰል በዝርዝር ጻፍ።

5. ጸሎት፡- የተማራችሁትን ነገር በተግባር እንድትፈጽሙት እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ በመጸለይ ስብሰባውን ጨርሱ።

# ትምህርት ሁለት

## ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 1-3

### የመጀመሪያ ቀን፡- መሥዋዕቶችን በተመለከተ የተሰጠ መግቢያ

አንድ እሥራኤላዊ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ከሚችለው አምስት መሥዋዕቶች ውስጥ በዚህ ሳምንት ሦስቱን እናጠናለን። እነዚህ መሥዋዕቶች የመጨረሻ መሥዋዕት ወደ ሆነው ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያመለክቱ ብቻ ሳይሆኑ እግዚአብሔርን ስናመልከው ከእኛ የሚጠብቅብንን ነገሮች ሁሉ ቁልጭ ባለ ሁኔታ የሚያሳዩንም ናቸው።

1ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር የሚመለከበትን ሥርዓት ለሰው ማሳየቱ ለምን አስፈለገ?

እግዚአብሔር ለሰው ከሚገልጸው እውነቶች ውስጥ ዋነኛው እንዴት መዳን እንደሚችሉና እንዴት እሱን ማምለክ እንደሚችሉ ማሳየቱ ነው። እግዚአብሔርን ለማምለክ ከመነሣሣት በፊት ይህን የመሥዋዕትነት ሐሳብ ቅድሚያ ቦታ ሊሰጠው ይገባል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቦቹ እሱን ለማምለክ ሲነሱ የሚመሩበትን መመሪያ ሰጥቷቸዋል። ምንም ዓይነት የአካል እንከል የሌለበትን እንስሳ መሥዋዕትን በማቅረብ ሊያመልኩት ይችላሉ። የእግዚአብሔር መጨረሻ መሥዋዕት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ በመስቀሉ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ እነዚህ በእምነት የቀረቡት መሥዋዕቶች ጊዜያዊ መንጻትን ይሰጡ ነበር። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ያሉትን መሥዋዕቶች በደንብ ከተረዳናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ኃጢአት ሲል የከፈለውን መሥዋዕትነት በጥሩ ግንዛቤ እንድንመለከተው ያደርጉናል። በኦሪት ዘሌዋውያን እነዚህ መሥዋዕቶች በዝርዝር ተብራርተው ይገኛሉ። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ጥሩ የመዓዛ ሽታ ያለው መሥዋዕት እኛም ልናቀርብ እንችላለን፤ (ፊልጵስዩስ 4፡18)። ለእግዚአብሔር ሕይወታችንን፣ ገንዘባችንንና ሁለንተናችንን ከሰጠን እራሳችንን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንደቀረብን ይቆጠራል። እርሱም በዚሁ ይደሰታል።

2ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 12፡1 አንብብ።

ሀ) እራስህን እንደ ሕያው መሥዋዕት አድርገህ አቅርበሃል? መቼ?

ለ) እራስህን እንደ ሕያው መሥዋዕት ባቀረብክ ጊዜ በሕይወትህ ውስጥ የተቀየሩትን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝረህ ጻፍ።

ይህ እራስን መሥዋዕት አድርጎ የማቅረብ ሐሳብ አዲስ አይደለም። በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥም እንኳ ቢሆን እራሱን የቻለ ለአማልክት የሚሰጥ መሥዋዕት አለ። እነዚህ መሥዋዕቶች ለአማልክቶች የሚሰጡት፥ እነሱን ለማስደሰትና በእነርሱ ፊት በጎ ሆኖ ለመታየት ነው። ወይም ደግሞ አማልዕክቱ በሰዎች ላይ ሲናደዱ እነርሱን ለማረጋጋት የሚደረግ ነው።

3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም መሥዋዕት የሚያቀርቡትን የተለያዩ ሃይማኖቶች ዘርዝረህ ጻፍ።

ለ) መሥዋዕቱን የሚያቀርቡበት ምክንያት ምንድነው? የማታውቀው ከሆነ ሰዎቹን ጠይቃቸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ሦስቱ ዋና ዋና ሃይማኖቶች መሥዋዕት ጋር የተያያዘ ከማቅረብ ደምብ አላቸው። ጣዖት የሚያመልኩ ሰዎች ለሚያመልኩባቸው ጣዖቶች ወይም ዛሮች የምግብ ስጦታ ይሰጣሉ። ለጠንቋይም ከብት ገዝተው ይሰጡና በእነርሱ ስም መሥዋዕት ያደርጋቸዋል። አንዳንድ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እና እስላሞች ደግሞ በአምልኳቸው ጊዜ መሥዋዕት ያቀርባሉ።

ለኃጢአት መሥዋዕት የማቅረቡ ደምብ በመጀመሪያ የደነገገው እግዚአብሔር ነው። አዳምና ሔዋን ኃጢአት በሠሩ ጊዜ እነርሱን ለመሸፈን ሲል እንስሳቱን ገድሏል። አቤልና ቃኤል የእንስሳ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል። እሬት ዘሌዋውያን ከመጻፍ በፊት እንኳን የእሥራኤል ሕዝቦች ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የማቅረቡን ነገር ያውቁት ነበር። ምናልባትም መሥዋዕት የማቅረቡ ነገር በጣም የተለመደ ስለነበር መሥዋዕቱን ሲያቀርቡ ከአይሁዳዊያን ውስጥ ያለውን ዓላማ በደንብ ላንረዳው እንችላለን። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ከሰጣቸው የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ እኛ ዛሬ እንዴት አድርገን እግዚአብሔርን ቀርበን ልናመልከው እንደምንችል የሚገልጽ ጥሩ ትምህርት ልናገኝ እንችላለን። ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ምንም የሚገልጹ ምሳሌዎች ልናገኝበት እንችላለን። ለብሉይ ኪዳንና ለአዲስ ኪዳን አምልኮ ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጡን ለሁሉም መሥዋዕቶች መሠረት የሚሆኑ አንዳንድ እውነታዎች አሉ።

1. «ማቅረብ» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ «ማስጠጋት» የሚል ትርጓሜ ነበረው። በብሉይ ኪዳን ኃጢአተኛ ሰው ወደ እግዚአብሔር ተጠግቶ ከእርሱ ጋር ኅብረት ሊኖረው የሚችለው መሥዋዕት ሲያቀርብ ነው።

በአረት ዘፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር በኤድን ገነት አዳምና ሔዋንን በየቀኑ ያነጋግራቸው እንደነበር እናነባለን። ኃጢአት በሠሩ ጊዜ ግን ወደ ኋላ ዞረው እራሳቸውን ከእግዚአብሔር ሸሸጉ። ከዚያን ጊዜ አንሥቶ እስካሁን ድረስ ሰው በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ርቋል። ይህም ቢሆን ቅዱስ የሆነው አምላክ አሁንም ከሰዎች ጋር ኅብረት ማድረግ ይፈልጋል፤ በዚያች ኃጢአት ምክንያት ግን ኅብረት ሊኖረው አልቻለም። ይህም በመሆኑ ኃጢአታችንን የሚሽረውን መሥዋዕት አድርጎ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ፈቀደ። ነገር ግን የእንስሳት ደም ለጊዜው ነው የኃጢአትን ዋጋ ሊከፍል የሚችለው። እግዚአብሔርም የኃጢአትን ዋጋ ሙሉ በሙሉ እንዲከፍል ብሎ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮ በመስቀል ላይ እንዲሰቀል አደረገ። ይህ ከሆነ በኋላ ቅዱስ አምላክ ከሰዎች ጋር ኅብረት ሊፈጥርበት የሚችልበት መንገድ ተከፈተ። የእግዚአብሔርን የደኅንነት መንገድ የተቀበሉ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር በእምነት መቅረብ ይችላሉ። ይህም ቢሆን የመቅረቡ ሐላፊነት ያለው በእኛ ላይ ነው። ያንን የተከፈተ በር በአግባቡ እየተጠቀምንበት ከእግዚአብሔር አብ ጋር በየቀኑ በጸሎት ኅብረት እንዲኖረን እያደረግን ነው? እግዚአብሔር ሲጠራን እንሰማለን?

2. መሥዋዕቶች ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። መጀመሪያ እንስሳት የሚሠዉበት የደም መሥዋዕት የተባለው ዓይነት ነበር። የመቃጠል መሥዋዕት ለዚሁ ጥሩ ምሳሌ ነው። ሁለተኛ የመሬት ውጤቶች የሚቀርቡት የመሥዋዕት ዓይነት ደግሞ ነበሩ፤ እነዚህም እንደ እህል፥ ዳቦ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው። ለዚህም የእህል መሥዋዕት የተባለው ጥሩ ምሳሌ ነው። የደም መሥዋዕት ዋና ዓላማው የሰውን ኃጢአት ማስታረቂያ ነበረ። ኃጢአት የሰው ልጆችን ከእግዚአብሔር ለያይቶአል። ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታን ሰጥቶ ኃጢአተኞች ከሆኑት ሰዎች ጋር ሊቀራረብ የቻለው ያኔ በሚፈስሰው ደም አማካኝነት ብቻ ነበር።

4ኛ ጥያቄ:- ኃጢአታችን በተመሳሳይ መንገድ እንዴት ሆኖ ነው የተሰረየልን? ለመልሱ ዕብራውያን 10:19 እንደገና ተመልከት። ደም ሳይፈስ ምንም ዓይነት ስርየት የለም፤ (ዕብራውያን9:22) በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለጊዜው ብሎ በወይፈንና በፍየል ደም በኩል እንዲሆን አድርጎት ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔር የመጨረሻ መሥዋዕት የሆነውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከ። በእርሱ ደም አማካኝነት ነው ይቅርታ አግኝተን ቅዱሱን አምላክ ልንቀርበው የቻልነው።

4. የደም መሥዋዕት ሲቀርብ፥ አቅራቢው ሁሌ እጁን በእንስሳው እራስ ላይ ያደርግ ነበር። ይህም የሰውዬው ኃጢአት በሙሉ እንስሳው ላይ እንደ ተጫነና ይህም ንጹሕ እንስሳ በኃጢአተኛው ፈንታ እንደሞተ የሚያመለክት ነው።

ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ማወቅ ለእኛ በቂ አይደለም ለእኔ ነው የሞተው ብለን ካላመንን ልንድን አንችልም። በብሉይ ኪዳን ኃጢአተኛው ኃጢአቱን በመናዘዝ በቀሠዋው እራስ ላይ ኃጢአቱን ሁሉ ማኖር አለበት። እኛም ብንሆን ኃጢአተኞች እንዲሆንንና እግዚአብሔር ኃጢአታችንን በሙሉ በክርስቶስ ላይ እንዳኖረ ማመን

አለብን፤ (2ኛቆሮ.5፡21)። እግዚአብሔር ለዓለም ብቻ ሳይሆን ለእኔና ላንተም ጭምር ነው የሞተው። ኢየሱስ ለኃጢአትህ መሥዋዕት ሆኖ እንደቀረበልህ በግልህ ተቀብለኸዋል?

5. መሥዋዕቶቹ ይቀርቡ የነበረው እግዚአብሔር በወሰነው ቦታ ላይ ነው። በብሉይ ኪዳን በነሐሱ መሠዊያ ላይ ወይም በኋላ ላይ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ነበር የሚቀርቡት።

ስለዚህ ዛሬም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ አንድ መንገድ ነው ያለው። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው፤ (ዮሐንስ 14፡6)። አንድ ሰው ደግ ሰው ከሆነ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ ይችላል። የሚሉ አያሌ ሰዎች አሉ። መልካም ሥራ መሥራት አንድ ዓይነት የደኅንነት መንገድ ነው። ሌሎች ደግሞ ሁሉም ሃይማኖቶች ወደ እግዚአብሔር ይመራሉ ብለው ያምናሉ። ብዙ ሌሎች የደኅንነት መንገዶችም እንዳሉ ይመስላቸዋል።

5ኛ ጥያቄ፡- ጥሩ በመሥራት ደኅንነት ይገኛል ብለው የሚያምኑ የአንዳንድ ሃይማኖቶችን ስም ዘርዝረህ ጻፍ።

ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ሲመጡ ነው ደኅንነትን የሚያገኙት። ማንም ደኅንነትን በሥራ ሊያገኝ አይችልም። ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ (ኤፌ.2፡8-9 ተመልከት)። አሁንም ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊደርስ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። የትኛውም ሃይማኖት ወደ መንግሥተ ሰማያት አያደርስም።

6. እያንዳንዱ መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው ጥሩ ከሆነው እህል ወይም እንስሳ ነበር። ነውር የሌለባቸው እንስሳትና ጥሩ የተፈጨ የዱቄት እህል ነበር የሚጠቀሙት። እግዚአብሔር የረከሰ ወይም ምርጥ ያልሆነ እንዲቀርብለት አይሻም።

6ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ «ያለ ነውር» የነበረው በምን መልኩ ነው? (ዕብራውያን 4፡15 ተመልከት)።

ኢየሱስ እንከን የሌለበት ንጹህ የእግዚአብሔር በግ ነበር። ኃጢአትም አላደረገም። ሆኖም እግዚአብሔር የኛን ኃጢአት በሱ ላይ በማድረግ የኃጢአት መሥዋዕት አደረገው። ምንም «ነውር» የሌለበት መሥዋዕትም ነበር። እኛም ብንሆን ራሳችንንና ምስጋናችንንም ነውር የሌለበት መሥዋዕት እንዲሆን ማድረግ አለብን። ይህም ልናደርገው የምንችለው በንጽሕናና በቅድስና ጠብቀን በበጎ ፈቃድ ስናቀርባቸው ነው።

7. እያንዳንዱ መሥዋዕት የሚቀርበው ከኃጢአተኛው የግል ንብረት ነው። እንስሳ ከሆነ ከበረት ውስጥ ካሉት ነበር የሚወሰደው እህል ከሆነ ደግሞ ከማሳው ነበር የሚያመጣው። መሥዋዕት የሚያቀርበው ሰው የዱር አራዊት ወይም በዱር የበቀለ እህል ይዞ መምጣት አይችልም ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት ኃጢአተኛውን መሥዋዕቱ ወጪ እንዲያስወጣው ስለተፈለገ ነው። ከበረቱ ውስጥ ካሉት እንስሶች ያንዱን ሞት ዋጋ ያስከፍለዋል። ይህም የሚያመለክተው ኃጢአት ዋጋ

እንደሚያስከፍል ወይም የኃጢአተኛውን ቤዛ እንደሚያስከፍል ነው። በመሥዋዕቱ ጊዜ የእንስሳው ሕይወት የሚያልፈው በባለቤቱ ኃጢአት ምክንያት ነው።

ብዙ ጊዜ ኃጢአት ስንሠራ በጣም ትልቅ ችግር እንዳልሆነ እንገምታለን፤ ምክንያቱም በቀላሉ ወደ እግዚአብሔር ቀርበ መናዘዝ ይቻላልና ነው። ነገር ግን ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ለእኛ በጣም ትንሽ የምትመስለን እንኳ በጣም እርኩስ የሆነች ነገር ናት። ኃጢአት ሁልጊዜ ወደ ሞት ያመራል። እኛን በሞት በመቅጣት ፋንታ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አኖረው። ለእኛ ሲል ሞተ። የእኛ ኃጢአት ነው ኢየሱስን ለሞት ያደረሰው። ለእኛ ይህንን ዓይነት ታላቅ ዋጋ በመክፈሉ ንጹህ የሆነ ሕይወት ለመኖር መጣር አይኖርብንም?

8. ኃጢአተኛው የራሱን መሥዋዕት እራሱ አያቀርብም ነበር። ለካህኑ ሰጥቶ ካህኑ ነበር መሥዋዕቱን በእርሱ ስም የሚያቀርብለት። ካህኑ ነበር በኃጢአተኛውም በእግዚአብሔር መካከል ቆሞ የአስታራቂነቱን ሐላፊነት የሚወጣው።

7ኛ ጥያቄ፡- 1ጢሞ. 2፡5 አንብብ። በእግዚአብሔር እና በእኛ መካከል የሚቆመው ማነው?

እንደ እግዚአብሔርም እንደ ሰውም ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት እኛን ለማቅረብ ብቁ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እሱ ቅዱስና ጻድቅም ነው። ልክ እንደ እኛ ተፈትኖ ምንም ኃጢአት አልሠራም። የእኛ ሊቀ ካህን በመሆኑ በአብ ቀኝ ቆሞ ለእኛ ይማልድልናል፤ (ዕብራውያን 7፡25 ተመልከት)።

8ኛ ጥያቄ፡- በትምህርታችን መሠረት አዲስ ኪዳንን ለማወቅ ሲባል ስለ መሥዋዕት ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ መኖሩ ለምን የሚያስፈልግ ይመስልሃል?

## ሁለተኛ ቀን፡- ኦሪት ዘሌዋውያን 1፥6፡8-13

## የሚቃጠለው መሥዋዕት

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 1-7 በሁለት ዋና ክፍሎች ይከፈላል። ከኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 1-6፡7 ያለው ስለ አምስቱ መሥዋዕቶች ይናገራል እነዚህም የሚቃጠል መሥዋዕት፥ የእህል ቁርባን፥ የኅብረት መሥዋዕት፥ የኃጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥዋዕት ናቸው። እነዚህ ምዕራፎች ካህኑና መሥዋዕት አቅራቢው ሊከተሏቸው የሚገባቸውን ሥነ-ሥርዓቶች ያመለክታሉ። ሁለተኛው ክፍል ኦሪት ዘሌዋውያን 6፡8-7፡38 በተለይ የተጻፈው ለካህናቱ ነው። ከሥራቸው ጋር በሚዛመድ ሁኔታ ስለ እያንዳንዱ መሥዋዕት ሠፋ ያለ ገለጻ ይሰጣሉ። ከአምስቱ መሥዋዕቶች ጋር የተያያዙ ስለሆኑ ሁለቱንም ክፍሎች በአንድ እናጠናቸዋለን።

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 1 እና 6፡8-13 አንብብ።

9ኛ ጥያቄ፡- ለሚቃጠለው መሥዋዕት ይፈቀዱ የነበሩት ምን ዓይነት እንስሳት ናቸው?

10ኛ ጥያቄ፡- የመሥዋዕት አቅራቢው ሐላፊነት ምንድነው?

11ኛ ጥያቄ፡- የካህኑስ ሐላፊነት ምንድነው?

12ኛ ጥያቄ፡- የሚቃጠለውን መሥዋዕት ከሠዋ በኋላ ለኃጢአተኛው በስተመጨረሻ ውጤቱ ምን ነበር?

የሚቃጠል መሥዋዕት በመጀመሪያ የተጻፈው ብዙ ጊዜ የሚዘወተረው እሱ በመሆኑ ነው። እያንዳንዱ እሥራኤላዊ ብቻ አልነበረም ይህን የሚቃጠል መሥዋዕት ያቀርብ የነበረው ካህናቶችም ጠዋትና ማታ ይህን የሚቃጠል መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር፤ (ኦሪት ዘጸአት 29፡39-42)። ለየት ባሉ የበዓል ቀኖች የሚቃጠለው መሥዋዕት በዛ ተደርጎ ይቀርብ ነበር፤ (ኦሪት ዘኁልቁ 28-29)።

በምዕራፍ 1፡1 ላይ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ መገናኛው ድንኳን እንደጠራው እናነባለን። ትዕዛዛቱን በሲና ተራራ ላይ ወጥቶ ከመቀበል ፈንታ ሙሴ በአዲሱ የመገናኛ ድንኳን ውስጥ ሳለ ነው እግዚአብሔር የተናገረው። የመገናኛው ድንኳን የሚል ስያሜ የተሰጠው እግዚአብሔር በዚያ ስለሚኖር ከሙሴም ከሕዝቡም ጋር በዚሁ ሥፍራ ስለሚገናኝ ነው። እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ በቀጥታ አልነበረም የሚናገረው። እግዚአብሔር ለሙሴ ይናገራል ሙሴም የሰማቸውን መመሪያዎች ሁሉ ለሕዝቡ ያስተላልፍ ነበር። እስቲ አራት ጥያቄዎችን በመጠየቅ የሚቃጠለውን መሥዋዕት እንመርምር።

1. ምን ዓይነት መሥዋዕቶች ነበሩ ለሚቃጠለው መሥዋዕት ይቀርቡ የነበረው?

ሦስት ዓይነት እንስሳት ለሚቃጠለው መሥዋዕት መቅረብ ይችሉ ነበር። የሚቀርበውን የመሥዋዕት ዓይነት በተመለከተ የግለሰቡ ሀብት ውሳኝነት ነበረው፤ ሀብታም የሆነው ወይፈን ያቀርብ ነበር። በጣም ሀብታም ያልሆነው ደግሞ ተባቱን በግ ወይም ተባቱን ፍየል ያቀርባል። ደሃው ደግሞ ቤት ውስጥ ያሳደገውን ዋኖስ ወይም እርግብ ያቀርባል።

በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፀጋ እናያለን። ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት መሥዋዕት ያቅርብ ብሎ ድንጋጌ አላወጣም። ችሎታቸውን ከቁጥር ውስጥ ከቶ አስበበታል። ሀብታም ከሆኑ ከእነርሱ ብዙ ይጠብቅ ነበር። ደሃም ከሆኑ ማምጣት እንዲችሉ አድርጎ ነው ያቀደው። ይህም ቢሆን ማንም ባዶ እጁን እንዲመጣ አልፈቀደም። አንድ የሆነ ነገር ማምጣት ነበረባቸው። ለኃጢአታቸው የግል ወጪ ማውጣት ነበረባቸው፤ (2ኛ ሳሙኤል 24፡24)። ለእኛም ቢሆን እግዚአብሔር ያለንን ስጦታዎችና ችሎታዎች እንድንጠቀምባቸው ይጠብቃል። እኛ መሥራት በማንችለው ነገር አይፈርድብንም። እርሱ ለእኛ የሰጠን ችሎታና ስጦታዎች ላይ በኃላፊነት የሚጠብቀው እኛን ነው። ንጹህ የሆኑ እንስሳትን ለመሥዋዕት እንደፈለገ ሁሉ ከእኛም ለእርሱ አገልግሎትና ሥራ የሚበልጠውን ነገር ይፈልጋል፤ (ትንቢተ ሚልክያስ 1፡6-14)።

13ኛ ጥያቄ፡- ይህ እውነታ እንዴት አድርጎ ነው ሊያበረታታህ የሚችለው?

እያንዳንዱ እንስሳ «ያለ ነውር» መሆን ነበረበት። አንካሳ ወይም ዕውር ሊሆን አይችልም ነበር። ተባት የሆኑ እንስሳት ብቻ ነበር የሚመጡት። ይህ ለምን እንደሆነ

እናውቅም። አንዳንድ ምሁራን ተባት የሆኑትን እንስሳት በአይሁዳውያን የተወደዱ ነበሩ ይላሉ። ሌሎች አንድ መንጋ በቁጥር ለማደግ ጥቂት ተባት ብቻ ይበቃሉ፤ በዚህ ምክንያት ነው ለዚህ ተግባር የዋሉት ይላሉ።

2. *መሥዋዕት የሚያመጣው ሰውዬ ሐላፊነት ምንድነው?*

የሚቃጠለው መሥዋዕት የሚቀርበው በአንድ ግለሰብ ብቻ ከሆነ ሙሉ ፈቃደኛ መሆን ነበረበት። እንደ ኃጢአት ወይም በደል መሥዋዕቶች ይህን የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ የነበረበት የተወሰነ ጊዜ አልነበረም። ያም ሆነ ይህ ካህኑ ዘወትር ለእሥራኤል ሕዝብ የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። በሚቃጠለው መሥዋዕት አማካኝነት እግዚአብሔር ሕዝቡን ሁሌ ማንጻትና ይቅርታ የሚያስፈልገው ኃጢአተኛ እንደሆነ እንዲያስተውል ያደርገው ነበር።

አንድ ሰው የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ከፈለገ ከራሱ የፍየል መንጋ ወይም የበግ መንጋ ወይም ወይፈኖች ወይም እርግቦች ነበር ለመሥዋዕት ማምጣት የሚችለው። በሱ ፈንታ የሚሞተውን እንስሳ የሚመርጠው እርሱ ነበር። ከዚያን በኋላ የነሐሱ መሠዊያ ከሚገኝበት ከውጪኛው የመገናኛ ድንኳን ግቢ ውስጥ መሥዋዕቱን ይዞ ይመጣል፤ በዚያም አንድ ካህን ይጠብቀዋል። በካህኑም ፊት እጁን በእንስሳው እራስ ላይ ይጭናል። ቀጥሎም ኃጢአቱን የሚናዘዝበት ጊዜም የነበረው ይመስላል። በኋላም መሥዋዕቱን ያመጣው ሰውዬ እንስሳውን ይገድላል፥ ይገፍና፤ የኋላ እግሮቹን ምንም ቆሻሻ እንዳይኖረው ጨጓራውንና አንጀቱን ያጥባል፤ በኋላም በደንብ እንደሚቃጠል አድርጎ እንስሳውን ይገነጣጥለዋል።

3. የካህኑስ ሐላፊነት ምን ነበር?

ከመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት ቆሞ ካህኑ በእግዚአብሔር ፊት ያገለግላል። ኃጢአተኛው እንስሳውን ሲያመጣ ካህኑ እንስሳው ለእግዚአብሔር እንደ መሥዋዕት ለመቅረብ ብቁ እንደሆነ ያያል። ኃጢአተኛው እንስሳውን ሲገድል ደሙን በሳህን ይቀበለዋል። ከዚያም ይህን ደም ይዞ በነሐስ የተሠራውን መሠዊያ ጎንና ጎኑን ይረጨዋል። በዚህ ጊዜ ኃጢአቱ ይቅር እንደተባለለት ለኃጢአተኛው ያረጋግጥለታል። እንስሳው ከተገፈፈ በኋላ ካህኑ በመሠዊያው ላይ እንጨቱንና እሣቱን ያዘጋጃል። በመጀመሪያ የእንስሳውን እራስ ከአንጀቱ የወጣውን ቅባት በመጨረሻም የተቀረውን የእንስሳውን ሥጋ በሙሉ በመሠዊያው ላይ ያኖራል። እነዚህ ነገሮች በሙሉ ይቃጠላሉ። ይቀር የነበረው ቆዳው ብቻ ነው፥ ይህም የካህኑ ንብረት ይሆናል።

የሚቃጠለው መሥዋዕት እርግብ ወይም ዋኖስ ከሆነ ካህኑ እርግቡን ይቀበልና አንገቱን ጠምዝዞ ደሙ በመሠዊያው ላይ እንዲፈስ ያደርጋል። ከዚህ በኋላ ላባዎቹንና የምግብ ማከማቻው ክፍል ይጣላል። በመጨረሻም ሆድ ዕቃው ይከፈትና በመሠዊያው ላይ እንዳለች በሙሉ ይቃጠላል።

ካህኑ በመሠዊያው ላይ ያለው እሳት እንዳይጠፋ ማድረግ ነበረበት። ይህ እሳት በመጀመሪያ የተለኮሰው በእግዚአብሔር ነው፤ (ኦሪት ዘሌዋውያን 9:24)። ቀንም ማታም ይህ እሳት ያለማቋረጥ መንደድ ነበረበት። ያለጥርጥር ይህ የሚያመለክተው

ለእግዚአብሔር ያልተቋረጠ አምልኮ መደረግ እንዳለበት ነው። መሥዋዕቶቹ ጨርሰው መቃጠል ነበረባቸው። በግለጻ ተነሥቶ የክህነት ልብሱን እንዳደረገ ካህኑ አመዱን ከመሠዊያው ላይ መጥረግ ነበረበት። ይህ የሚሆነው አመዱ ቅዱስ ነገር እንደሆነ ስለሚቆጠር ነው። ስለዚህም ይህን አመድ የሚነካው የተቀደሰውን ልብሱን ሲለብስ ነው። አመዱ የሚደፋው ከድንኳኑ ውጪ ስለሆነ በመጀመሪያ ካህኑ አመዱን ከመሠዊያው ቀጥሎ ባለው መሬት ላይ ያከማቻል። ከዚያም የክህነት ልብሱን ያወልቅና መደበኛውን ልብሱን ለብሶ ከግቢው ውጭ በተዘጋጀው የተለየ ቦታ ውስጥ አመዱን ይደፋ ነበር።

4. የሚቃጠል መሥዋዕት ለኃጢአተኛው ምን ውጤት ይሰጠዋል?

በመጀመሪያ ለኃጢአተኛው እንደ «ማስተሰርያ» ሆኖ መቅረቡን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል፤ (1፡4)። «ማስተሰሪያ» የሚለው ቃል ሁለት ዓይነት ትርጉም ሊኖረው ይችላል። አንደኛ፡- እግዚአብሔር መሥዋዕቱን ተቀብሎ ኃጢአተኛውን ይቅር እንዳለው ዓይነት ስናየው «ማንጻት» የሚል ትርጓሜ ሊኖረው ይችላል። ሁለተኛ «ካሣ መክፈል» የሚል ትርጓሜ ሊኖረው ይችላል፤ (አሪት ዘሌዋውያን 17፡11 ተመልከት)። ይህም ማለት እግዚአብሔር ኃጢአተኛው የእንስሳ ሕይወት ሰውቶ ስለ ኃጢአቱ ክፍያ ብታቀርብ እንደሚቀበለውና ሊደርስበትም ከሚችለው የሞት ቅጣት እንደሚያመልጥ ነው።

በሌላው ደረጃ ደግሞ መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር «ጣፋጭ ሽታ» ነው፤ (1፡9፥13፥17)። እንስሳው በጌታ ፊት በሚቃጠልበት ጊዜ የሚወጣው ጭስ ራሱ ለእግዚአብሔር ጥሩ ሽታ አልነበረም። ያም ባይሆን እንኳ እግዚአብሔር ጭሱን ሲያይ ኃጢአተኛውን ይቅር ብሎ ከሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረው ያደርግ ነበር። እግዚአብሔርም ከሁሉም በላይ ያስደሰተው ይህ ነበር።

## የሚቃጠለው መሥዋዕት ዓላማ

አንድ ሰው ለምን የሚቃጠለው መሥዋዕት እንደሚያቀርብ ትክክለኛ የሆነ ምክንያቱን አናውቅም። ምናልባትም ይህንን መሥዋዕት የሚያቀርብበት ምክንያት ለእይሁዳውያን በቀላሉ የሚገባቸው በመሆኑ አልተገለጸም ይሆናል። የሚቃጠል መሥዋዕት ለተለያዩ ምክንያቶች መቅረብ የሚችል ይመስላል። እነዚህም፡-

1. ያልታወቀ ኃጢአት ሳይኖር ዝም ብሎ ስለ ሰው ኃጢአተኛነት ይቅርታ ለመቀበል፤

2. የሚያመልከው ሰውዬ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት እንዲገልጽበትና በተጨማሪም አምላኪው በሙሉ ልቡ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ መሆኑን ለማሳየት፤

3. ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ እንክብካቤና ታማኝነት አምላኪው የሚያቀርበው የምስጋና መሥዋዕት ናቸው።

ዋናው ቁም ነገር መሥዋዕት ማቅረቡ እንዳልሆነ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ አስቀምጦታል። መሥዋዕቱን የሚያመጡት ሰዎች ከልብ መቅረብ አለባቸው። ከእግዚአብሔር በሚመላለሱበት ሁሉ ታዛገኝ ትሑቶችና የተቀደሰ ሕይወት ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይገባል። የአምልኮአችን ሥርዓት ከንጹህ ሕይወት የመነጨና ከልባችን የሆነ ካልሆነ እግዚአብሔር በአምልኮአችን አይደሰትም።

14ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ሳሙ.15:22-23፥ ትንቢተ ሚክ.6:6-8 አንብብና ከመሥዋዕት ይበልጥ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን የተለያዩ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

## ከሚቃጠለው መሥዋዕት የምንማራቸው ነገሮች

15ኛ ጥያቄ:- ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጥናታችን ውስጥ ለአንተም ሆነ ለቤተክርስቲያንህ ጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል ብለህ የምትገም ታቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

1. መሥዋዕትን በተመለከተ እግዚአብሔር ቁርጥ ያለ አቋም አለው። ይህ የሆነው ደኅንነት በጣም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር በመሆኑ ነው። ልንድን የምንችለው እግዚአብሔር በአዘጋጀው የደኅንነት መንገድ በኩል ስንመጣ ብቻ ነው። ይህ የደኅንነት መንገድ ሁሌ መሥዋዕት ማቅረብ ይጠይቃል። በኃጢአተኛው ፈንታ አንድ ንጹሕ የሆነ ነገር መሞት አለበት።

2. መሥዋዕት ይደረግ የነበረው በነሐሱ መሠዊያ ላይ ነው። ከዚህ በፊት ይህ መሠዊያ የኢየሱስን መስቀል እንደሚወክል አይተናል። ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ሆኖ የቀረበው በመስቀሉ ላይ ነው። እውነተኛ የሆነ ምሕረት ልናገኝ የምንችለው በመስቀሉ ብቻ ነው።

3. ለሚቃጠለው መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው እንስሳ «ያለ ነውር» መሆን እንደሚገባው ሁሉ የእግዚአብሔር የመሥዋዕት በግ የሆነው ኢየሱስም ምንም ኃጢአት አልነበረውም። በተመሳሳይ መንገድ እኛ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መሥዋዕት ያለምንም ኃጢአት የተቀደሰ መሆን አለበት! (ሮሜ 12:1 ተመልከት)።

4. የሚቃጠለው መሥዋዕት በሙሉ ተቃጥሎ ያለቀው በመሠዊያው ላይ ነው። ኢየሱስም የአብን ፈቃድ ለመፈፀም ለኃጢአት በመሞት ሁለንተናውን አሳልፎ ሰጥቷል። የሚቃጠለው መሥዋዕት ምንም ሳናስቀር ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት እንዳለብን ሊያመለክት ይችላል። ዕቅዳችንን፥ ምኞታችንን፥ ሀብታችንን፥ እኛነታችንን ወዘተ። ሙሉ በሙሉ እንደ መሥዋዕት ማቅረብ ይኖርብናል (ጳውሎስ ይህንን ነገር በሕይወቱ እንዴት ተግባራዊ እንዳደረገው በፊሊጲስዩስ 3:7-14 ላይ ተመልከት)።

5. ይህ የሚቃጠለው መሥዋዕት ለኃጢአተኛው ማስተሰርያ እንደሆነ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስም ሞት ለኛ ማስተሰሪያ ሆኗል! (ሮሜ 3:25)።

6. የሚቃጠለው መሥዋዕት ቀን በቀን የሚቀርበው ሰዎቹ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ሁል ጊዜ ለማስታወስ ነው። እኛም ብንሆን ምን ያህል ኃጢአተኞች እንደሆንን ተረድተን ወደ ጌታ ኢየሱስ ሁልጊዜ በመቅረብ ከኃጢአታችን መንጻት ይኖርብናል፤ (1ኛዮሐ.1፡7-9)።

7. ብዙ ጠቢባን ይህ የሚቃጠል መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ኃጢአት በመሞት የኃጢአትን ኃይልና ባህል ከእኛ ማስወገዱን የሚያመለክት ነው ይላሉ፤ (ሮሜ 6፡6-14)። የኃጢአት ተፈጥሮአችን ካሁን ወዲያ ኃጢአት እንድንሠራ ሊያስገድደን አይችልም። የክርስቶስ ሞት እግዚአብሔርን እንድናገለግል ነፃ አውጥቶናል። የተቀሩት መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ የሚደረጉት ግለሰቡ ባደረጋቸው የተወሰኑ ኃጢአቶች ተብሎ ነው። ይህ የሚቃጠል መሥዋዕት ግን ለተወሰኑ ኃጢአቶች ሳይሆን በአጠቃላይ ግለሰቡ በኃጢአት ስለነበረበት ሁኔታ ተብሎ የሚደረግ ነው።

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከሚቃጠለው መሥዋዕት ውስጥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ልንማራቸው የምንችላቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ከሚቃጠለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚገባን የሚያሳዩ ትምህርቶችን በዝርዝር ጻፍ።

ሐ) ክርስቲያኖችን እንዴት አድርገህ ነው ስለሚቃጠለው መሥዋዕት እያስተማርክ ሕይወታቸው ከመሥዋዕቱ የተመሳሰለ ባህርይ እንዳለው ልታስተምራቸው የምትችለው?

# ሦስተኛ ቀን፡-

## የእህል ቁርባን

## ኦሪት ዘሌዋውያን 2፥ 6፡14-23፥ 7፡9-10

* ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 2፥ 6፡14-23፥ 7፡9-10 አንብብ።

17ኛ ጥያቄ፡- የተለያዩት የእህል ቁርባኖች ምን ምንድናቸው?

18ኛ ጥያቄ፡- ቁርባኑን የሚያቀርበው ሰው ሐላፊነቱ ምን ነበር?

19ኛ ጥያቄ፡- የካህኑስ ሐላፊነት ምን ነበር?

20ኛ ጥያቄ፡- ቁርባኑን ከማቅረብ ምን ውጤት ይገኝ ነበር?

ሁለተኛ የመሥዋዕት ዓይነት ሆኖ የቀረበው የእህሉ ቁርባን ነው። ልክ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት ማንኛውም ሰው በፍላጎቱ ሊያቀርበው የሚችለው መሥዋዕት ነው። አቅራቢው በፈለገበት ጊዜ መሥዋዕቱን ሊያቀርብ ይችላል። ይህም ሆኖ ከሚቃጠለው መሥዋዕት ገና የእህሉ ቁርባን ሁሌ ጠዋትና ማታ መሥዋዕት መሆን ነበረበት። የእህሉ ቁርባን ስንዴ ወይም ገብስ ነበር። ይህ ቁርባን ከደም ጋር የተያያዘ አይደለም እህል ብቻ ነው። ምንም እንኳ ለብቻው ሆኖ ለእግዚአብሔር መቅረብ

የሚችል ቢሆንም ብዙ ጊዜ የሚቀርበው ከሚቃጠለው መሥዋዕት በኋላ ነው፤ (ኦሪት ዘኍልቁ 28፡1-8)። እንደሚቃጠለው መሥዋዕት ሙሉ በሙሉ አልነበረም የሚቃጠለው። ከሚቀርበው ውስጥ አንድ እፍኙ ብቻ ነው ይቃጠል የነበረው።

«የእህል ቁርባን» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ «ስጦታ» የሚል ትርጓሜ አለው። ይህ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ስጦታ እንደመስጠት ተደርጎ ነበር የሚቆጠረው።

ስለሚቃጠለው መሥዋዕት እንደጠየቅናቸው እስቲ ስለዚህኛው መሥዋዕትም አራት ጥያቄዎች እንጠይቅ።

1. ምን ዓይነት መሥዋዕቶች ነበሩ ለእህሉ ቁርባን ይቀርቡ የነበሩት?

የእህሉ ቁርባን ስንዴ ወይም ገብስ ብቻ ነበር የሚሆነው። ይህ ጥሬ እህል በአራት ዓይነት መልክ ሊዘጋጅ ይችል ነበር።

ሀ) እንደ ዱቄት፡- መልካም ዱቄት ማምጣት ይችሉ ነበር። በዱቄቱም ላይ የምግብ ዘይት ዕጣንና ትንሽ ጨው ተጨምሮበት ነበር እንደ መሥዋዕት የሚቀርበው።

ለ) በእቶን የተጋገረ፡- ይህ ከመልካም ዱቄት ያለ ምንም እርሾ እንደ ቂጣ እንጎቻ ሆኖ በእቶን እሳት ውስጥ የሚጋገር ነው። ዘይትና ጨው ይጨመርበት ነበር። በመጨረሻም ዕጣን ይደረግበታል።

ሐ) በምጣድ ላይ የተጋገረ፡- ይህ ደግሞ ትንሽ ሆኖ እንደ ቂጣ ጠፍጠፍ ያለ ዳቦ ነው። ትንሽ ዘይትና ጨው ተጨምሮበት ነበር የሚጋገረው። በኋላ ላይ ቂጣው ይቆረስና ዘይት ይጨመርበታል ዕጣንም ይጨመርበታል። ይህ ቂጣ ያለ እርሾ ሊዘጋጅ ይችላል።

መ) የተቆላ የእህል ቁርባን፡- ለዚህ ቁርባን የሚቀርበው ወዲያው ታጭዶ የመጣው እህል ነው። እህሉ ተቆልቶ ካበቃ በኋላ ዘይት፥ ጨውና ዕጣን ይጨመርበታል።

2. መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰውዬው ሐላፊነት ምንድን ነው?

መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው፥ ከላይ ካየናቸው አራት የእህል ቁርባን ማቅረቢያ ዘዴዎች የፈለገውን ለመጠቀም ሲችል እህሉን በቅድሚያ ማዘጋጀት ነበረበት። ከአዘጋጀ በኋላ ቁርባኑን በነሐስ በተሠራው መሠዊያ ላይ በማቅረብ ለካህኑ ማስረከብ ነበረበት።

3. የካህኑስ ኃላፊነት ምንድን ነው?

ካህኑ ከቀረበው መሥዋዕት ላይ አንድ እፍኝ ወስዶ በነሐሱ መሠዊያ ላይ ያቃጥለው ነበር። አንድ እፍኝ ይወስድ የነበረው ከዱቄት ወይም ከዘይቱና ከጨዉ ነበር። ሁሉም ለእግዚአብሔር ስለነበር የሚቀርበው ዕጣኑም ከመሥዋዕቱ ጋር አብሮ ነበር የሚቀርበው። ይህ የመሥዋዕቱ ክፍል «ለመታሰቢያ የሚቀርብ ነው»። በከፊል ቢቃጠልም እግዚአብሔር መሥዋዕቱን በሙሉ እንደተቀበለው አምላኪው ማረጋገጫ ማግኘት ነበረበት። ይህም የሚደረገው እግዚአብሔር ቸር መሆኑንና ፍላጎቱንም ሁሉ እንደሚያሟላለት አምላኪውን ለማሳሰብ ያህል ነው።

ከመሥዋዕቱ የቀረው የካህናቱ ድርሻ ነበር። ያለ እርሾ ጋግረው በመገናኛው ድንኳን ውጪኛ ክፍል ውስጥ ሆነው ይበሉት ነበር። የተጋገረ ወይም የተጠበሰ መሥዋዕት ከሆነ መሥዋዕቱን ያቀረበው ካህን ነበር የሚወስደው። ዱቄት ብቻ ከሆነ ማንኛውም ካህን ሊወስደው ይችል ነበር። ካህናቱ ወደየቤታቸው ወስደው መብላት አይፈቀድላቸውም ነበር። ለካህናት (ይኸውም ለአሮን የወንድ ዘሮች) ካልሆነ በቀር ማንም ሰው እንዲበላው ለመስጠት አይችሉም ነበር። ይህ ከመሥዋዕቱ በጣም የተቀደሰ ክፍል ነበር።

ሊቀ ካህኑ ለራሱና ለተቀሩት ካህናት የእህል ቁርባን የማቅረብ ኃላፊነት ደግሞ አለው። ካህናቱ የራሳቸው የሆነ መሬት ወይም እርሻ ስላልነበራቸው ይህንን መሥዋዕት ያቀርቡ የነበረው ለእነርሱ ከሚደርሳቸው ድርሻ ላይ ነበር። ካህኑ በእሳት የተጠበሰና የተፈተገ በኢፍ የተሰፈረ እህል ላይ ሁለት ሊትር ቢሆን ይመረጣል፣ ዘይት ጨምሮ ለእግዚአብሔር ያቀርባል። ግማሹ ጠዋት ከሚቃጠለው መሥዋዕት ሲቀርብ የተቀረው ግማሽ ደግሞ ከማታው መሥዋዕት ጋር አብሮ ይቀርባል። ይህ የእህል ቁርባን አንድ ሳይቀር በነሐሱ መሠዊያ ላይ ተደርጎ መቃጠል ነበረበት፤ ይህ የማይበላ መሥዋዕት ነው።

4. የዚህ የእህል ቁርባን የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው?

ልክ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት እግዚአብሔር ለራሱ «እንደ ጣፋጭ ሽታ» ሆኖ እንደሚቀርብለት አድርጎ ነበር የእህሉን ቁርባን የሚያየው። ይህ መሥዋዕት ከኃጢአት ጋር ስላለው ግንኙነት የተሰጠ ፍንጭ የለም።

## የእህሉ ቁርባን ዓላማና ምሳሌነት

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የእህል ቁርባን ዓላማ በግልፅ ባይሠፍርም ይህ ቁርባን የሚቀርበው ለሚከተሉት ምክንያቶች ይመስላል:-

ሀ) የአቅራቢውን ሥጋዊ ፍላጎቶች በማቅረብ ረገድ እግዚአብሔር ታማኝ በመሆኑ ለምሥጋና የሚቀርብ መሥዋዕት ነው።

ለ) እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንዴት እንደጠበቀ ለማሰብና መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው በእግዚአብሔር ፊት በታማኝነት እንደሚኖር ለማመልከት ነው።

ሐ) መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው ለእግዚአብሔር ሙሉ ልቡን ለመስጠት እንደሚፈልግ የሚገልጽበት ነው።

የእህሉ ቁርባን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ልናስገባው የሚያስፈልገን አንድ ዋና የሆነ ነገርን ያመለክታል። ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር ፊት የምስጋና ሕይወት ሊኖረን ይገባል። ጸሎታችን ሁልጊዜ በምስጋና የተሞላ መሆን አለበት፤ (መዝሙር (103)፡2)።

21ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ ካደረገልህ ነገሮች መካከል ምስጋና እንድታቀርብለት ሊያደርጉህ የሚችሉትን አንዳንድ ነገሮች በዝርዝር

4. የሚያገለግሉትን ሰዎች ፍላጎት እግዚአብሔር ያሟላ የነበረው መሥዋዕቱን በሚያቀርብለት ሰው በኩል ነበር። እህል ስለሌላቸው ምንም ዓይነት ምግብ ሊያገኙ የማይችሉት ካህናት የዕለት ጉርሳቸውን ያገኙ የነበረው የእህሉን ቁርባን ከሚያቀርበው ለጋስ ሰው ነው። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ መመሪያ ነው። ከወንጌላውያን ወይም ከመጋቢዎች አገልግሎት የሚጠቀሙ ሰዎች የእነዚህን ሰዎች የምግብ፥ የልብስ፥ ወዘተ. . . ችግር የማሟላት ሐላፊነት ነበረባቸው። ከዚህ ግን መረዳት ያለብን እራሳቸው ሰባኪዎቹም እንኳ ቢሆኑ (ካህናቱ) ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት የማቅረብ ሐላፊነት እንደ ነበረባቸው ነው።

22ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ቆሮ.9:4-14 አንብብ። ጳውሎስ የወንጌል ሰባኪዎችን ስለ መርዳት የሚናገረው ነገር ምንድን ነው?

5. አንዳንድ ሰዎች ይህ የእህል ቁርባን ከሙታን በኩር ሆኖ የተነሣውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክት ነው ይላሉ። የእህል ቁርባን ክፍል የሆነው ከሰብል ላይ የሚቀርበው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሠረት ለከርሞው የበለጠ እህል እንደሚያስገኝለት መሥዋዕት አቅራቢው ያውቃል። ልክ እንደዚሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መነሣት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሠረት እኛ ከሙታን እንደምንነሣ ያረጋግጥልናል! (1ኛ ቆሮ.15:20)።

6. ይህን የእህል ቁርባን ከጌታ እራት ጋር ልናነፃፅረው እንችላለን። ይህ የእህል ቁርባን አቅራቢው ለእግዚአብሔር ተገዢ እንደሆነና ምሥጋናውን ለማቅረብ እንደሚፈልግ የሚያሳይበት «መታሰቢያ» እንደሆነ ሁሉ የጌታም እራት ለእኛ እግዚአብሔር ልጁን አሳልፎ ስለሰጠን የምናመሰግንበትና እራሳችንን ከሙሉ ልብ ተነሣስተን ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንደምንሰጥ የምንገልፅበት ጊዜ ሊሆን ይገባዋል።

23ኛ ጥያቄ:- ሀ) ስለ አምልኮ ከእህሉ ቁርባን ልንማራቸው የምንችላቸውን የተለያዩ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ከእህሉ ቁርባን ትምህርት ውስጥ ያገኘኸውን ቁም ነገር ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ላሉ ምዕመናን እንዴት አድርገህ ነው ልታስተምራቸው የምትችለው?

## አራተኛ ቀን:-

## የደህንነት መሥዋዕት

ኦሪት ዘሌዋውያን 3፥ 7:11-38 አንብብ

24ኛ ጥያቄ:- ለኅብረት መሥዋዕት ይሰዉ የነበሩት የተለያዩ እንስሳት ምን ምን ነበሩ?

25ኛ ጥያቄ:- የተለያዩ የኅብረት መሥዋዕቶች ምን ምን ናቸው? ዓላማቸውስ?

26ኛ ጥያቄ:- የኅብረት መሥዋዕትን ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አነፃፅር። እንዴት ነው የሚመሳሰሉት? እንዴትስ ነው የሚለያዩት?

የምንመለከተው ሦስተኛው የመሥዋዕት ዓይነት ደግሞ የሰላም መሥዋዕት የኅብረት መሥዋዕት ወይም የምስጋና መሥዋዕት በመባል ይታወቃል። እንደፊተኞቹ ሁለት መሥዋዕቶች ይህም መሥዋዕት በፈቃደኝነት ነበር የሚሠዋው። ይህ መሥዋዕት የሚቀርብበት የተወሰነ የጊዜ ክልል አልነበረም። ልክ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት ከእንስሳ መሥዋዕት ጋር የተያያዘ ነው። እንደሚቃጠለው መሥዋዕትና እንደ እህሉ ቁርባን «ለእግዘአብሔር ጣፋጭ ሽታ» ነበር። ከሁለቱ ለየት የሚለው የኅብረት መሥዋዕት ቀን በቀን በቤተ መቅደሱ ይቀርብ የነበረውን መሥዋዕት ክፍል አለመሆኑ ነው።

1. ለኅብረት ምን ዓይነት መሥዋዕት ነበር ይቀርብ የነበረው?

ለኅብረት መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው ነውር የሌለበት እንስሳ ነበር ይኸውም እሥራኤላውያን እንዲበሉ ከሚፈቀድላቸው የቤት እንስሳዎች መካከል ነበር። እንስሳው ላም በግ ወይም ፍየል ሊሆን ይችላል፤ እርግብና ዋኖስ ሊሆን አይችልም። ተባት ወይም እንስት እንስሳ መቅረብ ይችላል።

2. የመሥዋዕት አቅራቢው ሰው ሐላፊነት ምንድን ነው?

የመሥዋዕቱ የመጀመሪያ ክፍል ሥርዓት ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር ይመሳሰላል። የኅብረት መሥዋዕትን ለየት የሚያደርገው፤ መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰውዬ ለእግዚአብሔር ወይም ለካህናቱ ተሰጥቶ የተረፈውን ሥጋ መብላቱ ነበር። የመሥዋዕቱ ሥነ-ሥርዓት ካለቀ በኋላ አቅራቢው የተቀረውን ሥጋ ወስዶ ከጓደኞቹና ከቤተሰቡ ጋር በመሆን በአንድ ወይም በሁለት ቀን ውስጥ መጨረስ ነበረበት። አጨራረሱም የሚወሰነው በመሥዋዕቱ ዓይነት ነው። ይህንን ሥጋ ይበላ የነበረው ሰው በሥርዓቱ መሠረት ንጹህ መሆን ነበረበት፤ (የሞተን ሰው ያልነካ፤ ወዘተ... አሪት ዘሌዋ.11-15)። ንጹህ ያልሆነ ሰው ሥጋውን ቢበላ እግዚአብሔር ሞት ይፈርድበት ነበር። («ያ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ» አሪት ዘሌዋ.7፡21)።

በመሥዋዕቱ እግዚአብሔር ስላደረገለት ነገር ምስጋና ለማቅረብ ቢፈልግ አቅራቢው ከእያንዳንዱ የእህል ቁርባን ዓይነት አምጥቶ በእግዚአብሔር ፊት መሠዋት ነበረበት። ይህ የእህል ቁርባን የካህናቱ ነበር።

3. የካህኑስ ሐላፊነት ምንድን ነው?

ካህኑ ከእንስሳው የፈሰሰውን ደም አጠራቅሞ በመሠዊያው ላይ መርጨት ነበረበት። የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስብ ሁለቱንም ኩላሊቶች የጉበቱንም ክፍል በመውሰድ በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ በመጨመር ያቃጥለው ነበር። ይህ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው የመሥዋዕቱ ክፍል ነው። ካህኑም በመቀጠል የእንስሳውን ፍርምባ ይወስድና ለእግዚአብሔር መቅረቡን ለማሳየት በእግዚአብሔር ፊት ያወዛውዘዋል። በኋላም ካህናቱ ሁሉ እንዲበሉት ይሰጣቸዋል። የኅብረት መሥዋዕቱን ለሚያቀርበው ካህን ቀኝ ወርቹና ቆዳው እንደ ድርሻው ታስቦ ይሰጠዋል።

4. የኅብረት መሥዋዕት ዓላማ ምንድን ነው?

27ኛ ጥያቄ:- አሪት ዘሌዋ.7፡12፤ 16 እንብብ። የተጠቀሱት ሦስቱ የተለያዩ መሥዋዕቶች ምን ምንድን ናቸው?

የዚህ የኅብረት መሥዋዕት ዋና ዓላማ መሥዋዕት አቅራቢው እግዚአብሔር ስላደረገለት ነገር ምስጋና ለማቅረብ ሲል የሚሠዋው ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው መፈለጉንም የሚገልፅበት ነው። በዚሁ መሥዋዕት ልናስተውለው የሚገባን አንድ ነገር አለ፤ እርሱም:- እግዚአብሔር መሥዋዕቱን መቀበሉንና ካህናቱም የመሥዋዕቱን ክፍል መውሰዳቸውን ብቻ ሳይሆን አቅራቢው ራሱ ከመሥዋዕቱ የመብላት መብት የነበረው በዚሁ ዓይነት መሥዋዕት ብቻ ነበር። ይህ የኅብረት መሥዋዕት ይታይ የነበረው ከእግዚአብሔር እና የእግዚአብሔር ባሪያዎች ከሆኑት ካህናት ጋር አቅራቢው የሚኖረው የአንድነት የመብል ጊዜ እንደሆነ ነው። በደስታውና በአከባበሩ ሥነ-ሥርዓት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቸርነት ያስታውሱ ነበር።

የኅብረት መሥዋዕትን በተመለከተ የተሰጡ ሦስት ዓላማዎች አሉ እነዚህም:-

1. የምስጋናው መሥዋዕት:- መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው እግዚአብሔር ስላደረገለት ትልቅ ነገር (ለምሳሌ፡ ከህመሙ ቢፈውሰው) በአፍ ብቻ ሳይሆን በተግባር ለማመስገን ከፈለገ ይህን የምስጋና መሥዋዕት ይሠዋል።

ለዚሁም:- አቅራቢው የእንስሳ መሥዋዕት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን የእህል ቁርባን መሥዋዕት ጭምር ነበር የሚያቀርበው። ይህ የምስጋና መሥዋዕት መበላት የነበረበት በዚያው በቀረበበት ቀን ነው። ለሚቀጥለው ቀን የተረፈ ሥጋ ካለ በሙሉ ይቃጠል ነበር።

2. የስለት መሥዋዕት:- አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ይህን ካደረክልኝ እንዲህ አደርጋለሁ ብሎ ቃል ከገባና እግዚአብሔር ለጸሎቱ መልስ ከሰጠው ይህን የስለት መሥዋዕት ያቀርብ ነበር፤ (ለምሳሌ፡ 1ኛሳሙ.1)።

እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶ መልስ ስለሰጠው ለማመስገን ሲል ነው ይህን መሥዋዕት የሚያቀርበው።

ለዚህ የስለት መሥዋዕት ነውር የሌለበት እንስሳ ነበር ተመርጦ የሚሠዋው። ሥጋውንም የሚበላው እስከ ሁለተኛው ቀን መጨረሻ ድረስ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ካላለቀ በሙሉ መቃጠል ነበረበት።

3. የፈቃድ መሥዋዕት:- ይህንን የፈቃድ መሥዋዕት የሚያቀርበው ሰው እግዚአብሔርን የሚያመልክበት የተወሰነ ምክንያት የለውም። በልቡ ምስጋናና ክብር ሊሰጥበት የሚያስገድደው ብዙ ነገር በመኖሩ ብቻ መሥዋዕት በመሠዋት ለእግዚአብሔር ምስጋናውን ያቀርባል።

የፈቃድ መሥዋዕት ብቻ ነውር ያለበት እንስሳ ለመሥዋዕት ማቅረብ ይቻል ነበር። ይህም ቢሆን እስከ ሁለተኛው ቀን መጨረሻ ድረስ ተበልቶ ማለቅ ነበረበት። ካላለቀ መቃጠል ነበረበት። መመሪያውን ሳይከተል ጊዜው ካለቀ በኋላ ሥጋውን የሚበላ ሰው

መሥዋዕቱን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርጋል፤ በእራሱም ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣበታል። ንጹህ ካለመሆኑ የተነሣ ላቀረበው ሰው ቁርባን ሆኖ አይቆጠርለትም፤ ከእርሱም ቢበላ ተጠያቂ እርሱ ራሱ ይሆናል።

እግዚአብሔር እነዚህን ሦስት የተለያዩ የኅብረት መሥዋዕቶች ሲቀበል የአቅራቢው ልብ በሀሴትና በምስጋና የተሞላ ከሆነ መሥዋዕቱ «ለጌታ ጣፋጭ ሽታ» ይሆናል። እግዚአብሔር በምስጋናው በጣም ደስ ይለዋል።

## የኅብረት መሥዋዕትን በተመለከተ ሌሎች ሥርዓቶች

መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው የሚበላውን ነገር ውስን ስለሚያደርገው እግዚአብሔር ምግብን በተመከተ አንዳንድ ሥርዓቶችን ለእሥራኤል ሕዝብ በሙሉ ሰጥቷል። እሥራኤላውያን ሁለት ነገሮችን እንዳይበሉ በጥብቅ ተከልክለው ነበር፤ እነርሱም፡-

1. ደም፡- የእንስሳውን ሕይወት የሚያመለክተውና ለኃጢአተኛው ስርየትን የሚያስገኘው ያ የሚረጨው ደም በመሆኑ ምንም ዓይነት ደም እንዲበሉ አልተፈቀደላቸውም። የእንስሳውንም ሥጋ ከመብላታቸው በፊት በሙሉ ደሙ ተንጠፍጥፎ ማለቁን ማረጋገጥ ነበረባቸው።

2. ስብ፡- የእንስሳው ስብ በሙሉ የእግዚአብሔር ነበር። እንስሳው ለመሥዋዕት ሲቀርብ ስቡ በሙሉ በመሠዊያው መንደድ ነበረበት። አንድ እንስሳ ወይም አውሬ ሞቶ ቢገኝ ስቡን በመጠቀም አንዳንድ ነገሮችን ሊሠሩ ይችሉ ነበር እንጂ፤ (ለምሳሌ፡ ጥዋፍ) ሊበሉት አይችሉም ነበር። ይህንን ትዕዛዝ እግዚአብሔር ለምን እንደሰጠ አናውቅም። ምናልባት ስብ በረከትንና ጥጋብን ስለሚያመለክት ይህን የእንስሳውን ስብ ባገኙ ቁጥር እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ የሰጣቸውን በረከቶች እንዲያስቧቸው ብሎ ይሆናል።

## በኅብረት መሥዋዕት የሚገኙ ምልክቶች

28ኛ ጥያቄ፡- ከኅብረት መሥዋዕት ላይ ያገኘኃቸውን ላንተም ሆነ ለቤተ ክርስቲያንህ ይጠቅማሉ ብለህ የምትገምታቸውን ትምህርቶች በመዘርዘር እንዴት ተግባራዊ ልታደርጋቸው እንደምትችል ጻፍ።

1. የኅብረት መሥዋዕት ኃጢአተኛ የሆነውን ሰው ከቅዱሱ አምላክ ጋር የሚያገናኘው በር በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አማካኝነት እንደተከፈተ ያስታውሰናል። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የኃጢአታችን ዋጋ ተከፍሎአል። አሁን የሚያገናኘው በር ክፍት ነው፤ እንደፈለግን ያለ ምንም ችግር በእግዚአብሔር ፊት ሁሌ በመቅረብ ከእርሱ ጋር ኅብረት ሊኖረን ይችላል።

29ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ዮሐ.1፡3፥6 አንብብ።

ሀ) ከማን ጋር ነው ኅብረት ያለን?

ለ) ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው?

ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ ከእግዚአብሔር ጋር እና ከመሰል አማኞች ጋር ያለውን ኅብረት የምትገልጸው እንዴት ነው?

በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምክንያት የተለየ ኅብረት የሚኖረን ከእግዚአብሔር አብ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም ሕዝብ ጋር ጭምር ነው።

2. የኅብረት መሥዋዕት ልክ እንደ ጌታ እራት ነው። ሁለቱም በመብል አማካኝነት የሚከበሩ የማስታወሻ ክብረ በዓሎች ናቸው። አንድ ሰው በኅብረት መሥዋዕቱ የእግዚአብሔርን በረከት ያስታውሳል። የጌታ እራት ደግሞ የበረከቶች ሁሉ ምንጭ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት የምናስታውስበት ነው። ስለዚህም ሁለቱም ክብረ በዓሎች ናቸው።

3. የእውነተኛ አምልኮ ትልቁ ክፍል ምስጋና ነው። ጌታን ያለማቋረጥ ለሰጠን ችሮታዎች ሁሉ እንድናመሰግን ትዕዛዝ ተሰጥቶናል። ቀኑን በሙሉ ስለ ሰጠን ችሮታዎች እያሰብን ማመስገን ይኖርብናል። አንዳንድ ጊዜ ግን በአፍ ብቻ ማመስገኑ በቂ አይደለም። አንዳንዴ

ለእግዚአብሔር ያለንን ምስጋና የሚገልጽ ነገር ማድረግ አለብን። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር በገንዘብ ባርኮን ከሆነ ከሰጠን ላይ የተወሰነውን ክፍል ለእግዚአብሔር በመስጠት ምስጋናችንን ልንገልጽ ይገባል።

30ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር የሰጠህን የተለያዩ በረከቶች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ለአንድ አፍታ በጸሎት እግዚአብሔርን አመስግነው።

ሐ) ምስጋናህን በተግባር ልትገልጽበት የምትችልባቸው አንዳንድ መንገዶች ምን ምንድናቸው? ይህንንስ ነገር አድርገሃል?

በዚህ ሳምንት ሦስት የተለያዩ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶችን አይተናል። የሚቃጠለው መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአታችንን ዋጋ የከፈለበትን መስቀል የሚያሳየን ሥዕላዊ መግለጫ ነው። እራሳችንን ለእግዚአብሔር አገልግሎት «ሕያው መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ እንደሚኖርብንም ያመለክተናል። የእህሉ ቁርባን እግዚአብሔር «የዕለት እንጀራችንን ስለሚሰጠን፤ በየጊዜው ፍላጎታችንን ስለሚያሟላልን ልንሰጠው የሚገባውን ምስጋና ያመለክታል። የሙታን ሁሉ በኩር የሆነውን ለእኛ ከሙታን እንደምንነሣ ቃል ኪዳን የገባልንን ኢየሱስ ክርስቶስንም ያመለክታል። የኅብረት መሥዋዕት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረን መንገዱን የከፈተውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል። ይህ በእርግጥ ፍጻሜ ያገኘው በመስቀሉ ላይ ነው። ከእግዚአብሔር አብ ከጌታ ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስና እግዚአብሔርን ስናመልክ ከሌሎች አማኞች ጋር ያለንንም ኅብረት ያሳየናል። እነዚህ ሦስቱ መሥዋዕቶች በትዕዛዝ ይደረጉ የነበሩ አይደሉም። እግዚአብሔር የሰውዬውን ልብ ሲነካ በራሱ ተነሣሥቶ የሚያቀርባቸው ነበሩ። እኛም ከኃጢአታችን ለመንፃት፥ ለማመስገን፥

ለማወደስና ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረን ሁልጊዜ ወደ አምላካችን የመቅረብ ሐላፊነት አለብን። ለመሆኑ ይህንን ሁሉ እያደረግን ነው?

## አምስተኛ ቀን:-ትምህርቱንከልስህለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ:-

ለመሪው:- በትምህርት አንድ ላይ ያሉትን ለመሪው የተሰጡትን መመሪያዎች ተከተል። የተወሰነልህን የጊዜ ገደብ ለእያንዳንዱ ክፍል መስጠቱን አትዘንጋ።

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) ሦስቱን የተለያዩ መሥዋዕቶች አነፃፅር። እንዴት ነው የሚመሳሰሉት? እንዴትስ ነው የሚለያዩት?

ለ) በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበሩትን መሥዋዕቶች ከኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት እና ከራሳችን መሥዋዕትነት ጋር አነፃፅር። እንዴት ነው የሚመሳሰሉት? እንዴትስ ነው የሚለያዩት?

ሐ) ከሚቃጠለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለብን ነው የምንማረው?

መ) ከእህሉ ቁርባን እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለብን ነው የምንማረው?

ሠ) 1. ከእግዚአብሔር ያገኘሃቸውን ልዩ ልዩ ጥቅሞች በዝርዝር ጻፍ።

2. እግዚአብሔርን ስለ እያንዳንዱ ጥቅም አመስግነው።

3. ለእነዚህ ጥቅሞች ያለህን ምስጋና በተግባር ሊገልጹልህ የሚችሉ አንተ ልተሰጣቸው የምትችላቸውን ስጦታዎች በዝርዝር ጻፍ።

5. ጸሎት

# ትምህርት ሦስት

## ኦሪት ዘሌዋውያን 4-10

## የመጀመሪያ ቀን:-

ኦሪት ዘሌዋውያን 4-5:13፤ 6:24-30 (የኃጢአት መሥዋዕት)

ባለፈው ሳምንት እግዚአብሔር ከእሥራኤላውያን የሚጠብቃቸውን ሦስት መሥዋዕቶች ተመልክተናል። እነዚህን ሦስት መሥዋዕቶች አቅራቢው በፈቃደኝነት ተነሣሥቶ እንእደሚያቀርባቸው ተመልክተናል። የሚቃጠለው መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን ውስጥ በጣም የተለመደው መሥዋዕት በሕዝቦቹ መካከል ባለው ኃጢአት የእግዚአብሔር መለኮታዊ ቁጣ እንዳይወርድ የሚያደርግ ነበር። ቅድሚያ የሚሰጠው ኃጢአተኛውን ብዙ ብር የሚያስወጣውና ብዙ ጊዜ መደረግ የነበረበት ለኃጢአት ትክክለኛ ካሣ የሆነ መሥዋዕት ነበር። ሌሎች መሥዋዕቶች የሚቀርቡት ከዚህ በመነሣት ነበር። የእህሉ ቁርባን እግዚአብሔር የዕለት ሲሳዩን ስለሰጠው አቅራቢው የሚያቀርበው መሥዋዕት ነበር። የኅብረት መሥዋዕት ደግሞ እግዚአብሔር ስላደረጋቸው የተወሰኑ ቸርነቶች ምስጋና የሚቀርብበት መሥዋዕት ነው።

በዚህ ሳምንት በመጨረሻ ላይ ያሉትን ሁለት መሥዋዕቶች ማለትም የኃጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥዋዕት እንመለከታለን። ከዚህ በመቀጠል እግዚአብሔር ካህናቱ የእሱን የአምልኮ ሥርዓት እንዲመሩ እንዴት ለይቶ እንደመረጣቸው በብሉይ ኪዳን እንመለከታለን። እግዚአብሔርን ለማምለክ ሦስት ነገሮች አስፈላጊ እንደሆኑ ተመልክተናል። እነርሱም:- 1. እንደ ቤተ መቅደስ ወይም መገናኛው ድንኳን ያለ ማምለኪያ ቦታ፥

2. የተለያዩ መሥዋዕቶችን ያካተተ የአምልኮ ሥርዓት፥

3. የአምልኮ መሪ የሆኑ ካህናት ነበሩ።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እነዚህን ሦስት የአምልኮ ክፍሎች በገሃድ የምናያቸው እንዴት ነው?

ለ) ተመሳሳይነቱ ምን ላይ ነው?

ሐ) ልዩነቱስ?

የመጨረሻዎቹ ሁለት መሥዋዕቶች የኃጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥዋዕት በገቢር በጣም ይመሳሰላሉ። በፈቃደኝነት የሚሠዉ ሳይሆን አንድ ሰው የተወሰኑ ኃጢአቶችን ከሠራ እነዚህን መሥዋዕቶች ማቅረብ አለበት። የኃጢአት መሥዋዕቱ የማንጻት መሥዋዕት ነበር። ይኸውም ኃጢአተኛውና በእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት የረከሰው የአምልኮውን ቦታ የሚያጸዳ መሥዋዕት ነው። ከእግዚአብሔር ቃል

እንደምናነበው ኃጢአት እግዚአብሔርን በጣም ያሳዝነዋል። ኃጢአት የሚያረክሰው ኃጢአተኛውን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳን እንደምናነበው ሌላውንም ነገር እንደ አምልኮ ቦታ የመሰለውንም ያረክስ ነበር። እግዚአብሔር በሕዝቦቹ መካከል መኖሩን እንዲቀጥል ሲባል ነበር ይህ የኃጢአት መሥዋዕት ኃጢአተኛውንና የአምልኮ ቦታውን ያፀዳ የነበረው።

2ኛ ጥያቄ:- አሪት ዘሌዋውያን 15:31፤ 16:19 አንብብ። በመገናኛው ድንኳን የሚሠራው እርኩሰት ምን ያስከትል ነበር?

2. ይህ ዛሬ እንዴት ነው ተግባራዊ የሚሆነው?

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ትልቁ ችግር ድህነት ወይም አለመማር ሳይሆን ኃጢአት እንደሆነ ነው የሚያስተምረን። ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ሰውን ከሰው ያለያያል።

3ኛ ጥያቄ:- በዓለም ላይ ዛሬ ይህም ነገር እውነት እንደሆነ የሚታየው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ሰዎች ይቅርታን የሚያገኙበት መንገድ ከእርሱ ጋር እና እርስ በርሳቸው እንደገና ኅብረት የሚፈጥሩበትን ሁኔታዎች አዘጋጅቶላቸዋል። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ይህ የተደረገው በእንስሳ ሞት ነው። በአዲስ ኪዳን ጊዜ ይህ የተደረገው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ነው።

በኃጢአት መሥዋዕት እንስሳው እንዴት መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ እንደሚገባው ትኩረት አይሰጠውም። በኃጢአት መሥዋዕት ውስጥ ዋናው ነገር ደሙ ነው። ኃጢአት የሠራውን ሰው ታይቶ ለመሥዋዕት የቀረበው እንስሳ ደም በእግዚአብሔር ፊት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ወይም በነሐሱ መሠዊያ ላይ ይረጭ ነበር።

አሪት ዘሌዋውያን 4-5:13፤ 6:24-30 አንብብ።

4ኛ ጥያቄ:- የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ የነበረባቸው አራቱ የሰዎች ዓይነት እነማን ናቸው?

5ኛ ጥያቄ:- የመሥዋዕቱ ልዩነት የደሙ አረጫጨት ለአራቱ ሰዎች የሚለያየው እንዴት ነበር?

6ኛ ጥያቄ:- ኃጢአት ለሠራው ሰው ይህ የኃጢአት መሥዋዕት ምን ውጤት ያስገኝለታል?

የኃጢአት መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው «ሳይታወቅ» ለሚፈጸም ኃጢአት ነበር። እግዚአብሔር እንዲህ ያለው ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ሆን ተብሎ ለአመፃ ያልተሠራ አለመሆኑን ለመግለፅ ነው። በብሉይ ኪዳን ጊዜ በአመፃ ተነሣሥተው በእግዚአብሔር ላይ ለሚሠሩት ኃጢአት የነፍስ ግድያ፥ አመንዝራነት፥ ጣዖት አምልኮ፥ በእግዚአብሔር ላይ መጥፎ መናገር ምንም ዓይነት ምሕረት አልነበራቸውም። የሚታወቁት የእግዚአብሔር ሕግጋት በሰዎች ውስጥ ባለው የኃጢአት ባህርይ አማካኝነት ሲጣሱ፤ እግዚአብሔር ሰዎች የሚነፁበትን መንገድ

ያዘጋጅላቸው ነበር። ይህ ከአዲስ ኪዳን ይለያል። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።

1. አራቱ የተለያዩ የኃጢአት መሥዋዕቶች

በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ የኃጢአት መሥዋዕት መቅረብ የሚገባቸውን አራት የተለያዩ ሰዎች እንመለከታለን። በሰውዬው ሥልጣን ላይ ተመርኩዞ መሥዋዕቱና የመሥዋዕቱ ደም ይታዩ የነበረው በተለያየ መልክ ነው።

1. ሊቀ ካህኑ፡- (ኦሪት ዘሌዋውያን 4፡3-12)

ሊቀ ካህንና የእሥራኤል ሕዝብ መንፈሳዊ መሪ የነበረው «የተቀባው ካህን» ነበር። በእግዚአብሔርና በመላው የእሥራኤል ሕዝብ መካከልም ይቆም ነበር። ሌሎቹ እሥራኤላውያን በቅድስና የመኖር ምሳሌ መሆን ነበረበት። ስለዚህም እሱ ኃጢአት ሲሠራ እርሱ ብቻ አይደለም ኃጢአተኛ የሚሆነው፤ በመላው የእሥራኤል ሕዝብ ላይ የኃጢአትን ዕዳ ያመጣል እንጂ። እግዚአብሔርን ለማገልገል ወደ ቅዱስ ቦታ የሚገባው እርሱ በመሆኑ እግዚአብሔር የሚመለከበትን ቤተ መቅደስንም ጭምር ነው የሚያረክሰው።

ሊቀ ካህኑ ኃጢአት ሲሠራ በጣም ውድ የሆነ መሥዋዕት ነው በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርበው። ከሁሉም በላይ ትልቅ የሆነውን ማለትም የወይፈንን መሥዋዕት የማቅረብ ሐላፊነት ነበረበት። ወይፈኑን አምጥቶ እጁን ይጭንበትና ኃጢአቱን ይናዘዛል፤ በኋላም ያርደዋል። በጥንቃቄ የወይፈኑን ደም በማጠራቀሚያ ሳሕን ውስጥ ያጠራቅማል። ወደ ቅዱሱ ቦታ ይገባል፤ ቅዱሱን ቦታ ከቅድስተ ቅዱሳን በሚለየው መጋረጃ ላይ ሰባት ጊዜ ደሙን ይረጫል። በዕጣኑ መሠዊያ ባሉት አራቱ ቀንዶች ላይ ትንሽ ከደሙ ይለቀልቃል። ይህ የሚደረገው በሊቀ ካህኑ ኃጢአት ረክሶ የነበረውን ቅዱስ ቦታ ለማንጻት ነው። የተቀረው ደም ደጅ ከሚገኘው በነሐስ ከተሠራው መሠዊያ በታች ይፈስ ነበር። ከዚህ በመቀጠል ሊቀ ካህኑ የወይፈኑን ስብ ሁለቱንም ኩላሊቶቹንና ከጉበቱም ከፊሉን በመውሰድ እንደ ደኅንነት መሥዋዕት በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል። የተቀረውን ሥጋ ወደ ውጭ አመድ ወደሚፈስበት ቦታ ይወስደዋል። በዚህም ሥፍራ ሥጋውን በሙሉ በእሳት ያቃጥለዋል።

2. የእሥራኤል ማኅበረሰብ፡- (ኦሪት ዘሌዋውያን 4፡13-21)

መላው የእሥራኤል ሕዝብ ምናልባት በመሪዎቹ ውሳኔ ምክንያት ቢያጠፋ የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። ሕዝቡ በሞላ በማጥፋቱ የሚያቀርበው መሥዋዕት ልክ እንደ ሊቀ ካህኑ ዓይነት ውድ መሆን አለበት። ሕዝቡን የሚወክለው ጉባዔ ወይፈኑን የማምጣት ኃጢአቱን የመናዘዝ ወይፈኑን የማረድ ኃላፊነት ሲኖርበት ካህኑ ደግሞ ደሙን በሳህን ውስጥ እንዲከማች ማድረግ አለበት። ደሙም በቅዱሱ ቦታ ተረጭቶ በዕጣን መሠሚያው ላይ ከተደረገ በኋላ የሊቀ ካህኑ ሥጋ ወደ ተቃጠለበት ቦታ ተወስዶ የወይፈኑ ሥጋ ፍጹም መቃጠል ነበረበት።

3. አንድ መኮንን ኃጢአትን ሲሠራ፡- (ኦሪት ዘሌዋውያን 4፡22-26)

አንድ መኮንን ኃጢአትን ሲሠራ ኃጢአቱም ሲታወቀው የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። በመሪነት ደረጃ ያለ በመሆኑ የእርሱ መሥዋዕት ከተራው እሥራኤላዊ መሥዋዕት መለየት ነበረበት። እንደ ሊቀ ካህኑና እንደ መላው የእሥራኤል ሕዝብ ኃጢአት የእሱ ኃጢአት የከረረ ችግር አይፈጥርም። በዚህ ምክንያት የእርሱ የኃጢአት መሥዋዕት ከፊት ካየናቸው ሁለት መሥዋዕቶች የተለየ ነው።

መኮንኑ ኃጢአቱ እንደታወቀው ተባት ፍየል ለመሥዋዕት ያቀርባል። በሌሎቹ መሥዋዕቶች እንዳየነው እጁን በፍየሉ እራስ ላይ በመጫን ኃጢአቱን ይናዘዛል፤ ፍየሉንም ያርደዋል። ደሙን በሳህን ላይ ካጠራቀመ በኋላ በነሐስ በተሠራው መሠዊያ ቀንድ ላይ ብቻ ያኖረው ነበር። ደሙ ወደ ቅዱስ ቦታ አይወሰድም። ልክ እንደ ደኅንነቱ መሥዋዕት የተቀረው ደም ይፈስና ስቡ ይቃጠል ነበር። ሥርዓቱን ያካሂድ የነበረውም ካህን የዚህን መሥዋዕት ሥጋ በመገናኛው ድንኳን መብላት ይችላል።

4. የተራው እሥራኤላዊ የኃጢአት መሥዋዕት:- (አሪት ዘሌዋውያን 4፡27-5፡13) አንድ ተራ እሥራኤላዊ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ከሠራ የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። የኃጢአተኛው ንብረት በፈቀደው መጠን ሦስት የተለያዩ መሥዋዕቶች ይፈቀዱ ነበር።

እነርሱም:- ሀ) ኃጢአተኛው በቂ ንብረት ብለው እንስት ፍየል ወይም እንስት በግ ማምጣት ነበረበት። ይህ መሥዋዕት የመኮንኑን ዓይነት ሥርዓት የተከተለ ነበር።

ለ) ኃጢአተኛው ችግረኛ ከሆነ ፍየል ወይም በግ ማምጣት የማይችል ከሆነ፥ ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት እርግቦች ሊያመጣ ይችላል። የመጀመሪያዋ እርግብ ለኃጢአት መሥዋዕት ትቀርባለች። ራሷን ይቆለምመዋል፥ ሳይቆርጠውም ደሟን በመሠዊያው ጎን ላይ ይረጫል። ሁለተኛዋ እርግብ ለሚቃጠለው መሥዋዕት ነበር የምትቀርበው። ሁለቱም እርግቦች ሙሉ በሙሉ ምንም ሳይቀር ይቃጠላሉ።

ሐ) በጣም ችግረኛ ከሆነ የኢፍ መስፈሪያ አንድ አሥረኛውን (2ኪሎ ያህል) መልካም ዱቄት ማቅረብ ይችላሉ። እንደ እህሉ ቁርባን ይህ የደስታ መሥዋዕት ባለመሆኑ ዘይት ወይም ዕጣን አይጨመርበትም። ካህኑ አንድ ጭብጥ ነሐስ መሠዊያው ላይ ካቃጠለ በኋላ የተቀረው የራሱ ይሆናል። እግዚአብሔር ኃጢአትን በተመለከተ በጣም ምሕረቱን ያበዛ ነበር። ኃጢአተኛው ሁልጊዜ የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። ነገር ግን ይህ መሥዋዕት የሚወሰነው በኃጢአተኛው ችሎታ ነው።

አንድን ሰው ኃጢአተኛ አድርገው የኃጢአት መሥዋዕት እንዲያቀርብ ሊያስገድዱ የሚችሉ አራት ነገሮች እግዚአብሔር በምሳሌ መልክ አስቀምጧቸዋል:- (ዘሌ.5፡1-4) እነርሱም:-

1. ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አንዱ ኃጢአት ሲሠራ ቀይቶ ለምስክርነት ቢጠየቅና ለመመስከር አሻፈረኝ ቢል ራሱ ኃጢአተኛ ይሆናል።

2. ማናቸውም ሰው ሳይታወቀው ርኩስ ነገር (የሞተ እንስሳ) ነክቶ ቢረክስና እራሱን በሥርዓቱ መሠረት ባያነጻ በታወቀው ጊዜ የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ አለበት።

3. ርኩሰቱን ሳያውቅ ርኩስን ሰው ቢነካ (ስለዚህ ነገር በኦሪት ዘሌዋ.11-15 ላይ በበለጠ እናያለን) የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ አለበት።

4. ማናቸውም ሰው ክፉ ወይም መልካም መሆኑን ሳያውቅ በችኮላ ቢምልና ክፉ መሆኑን ቢነገረው የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ አለበት።

2. የኃጢአት መሥዋዕት ትርጓሜ

የኃጢአት መሥዋዕት ወይም አንዳንዶች እንደሚጠሩት የማንጻት መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው ኃጢአተኛው ለሠራቸው «የተወሰኑ» የኃጢአት ዓይነቶች ነው። በተለይ እግዚአብሔር በሚመለከበት ውስጥ መገናኛው ድንኳን እርኩሰት የተፈጸመ ከሆነ ይህን መሥዋዕት ማቅረብ ያስፈልጋል። የኃጢአት መሥዋዕት የመጨረሻ ውጤቱ «ካህኑ ያስተሰርይለታል እርሱም ይቅር ይባላል»።

አንዳንድ ምሁራን እግዚአብሔር ይህ የኃጢአት መሥዋዕት ከተወሰኑ ኃጢአቶች እንዲያነጻ አድርጎ የፈጠረው ዋነኛ መንገድ ነው ይላሉ። የኃጢአት መሥዋዕት እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ይቅር ያለበትን የእግዚአብሔር ዘዴ ነው ብለው ያስባሉ። በዚሁም መንገድ ያ ሰውና እግዚአብሔርን ለያይቶ የነበረውን መለያ ሻረ። ሌሎች ምሁራን ደግሞ የኃጢአት መሥዋዕት ባደረገው መንጻት ላይ የበለጠ ትኩረትን ይሰጣሉ። የእንስሳው ደም መገናኛውን ድንኳን የሚያጸዳ ነገር ሆኖ ነበር የሚታየው። በተለይ በስርየት ቀን (ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 16) ደሙ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለውን የሕዝቡን ዓመታዊ ኃጢአት ያፀዳ ነበር።

7ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 9፡21-22 አንብብ። የብሉይ ኪዳኑ መገናኛ የሚፀዳው እንዴት ነበር?

3. በኃጢአት መሥዋዕት ውስጥ ያሉ ትምህርቶችና ምሳሌዎች

8ኛ ጥያቄ:- በራስህ ሕይወትና በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ተግባራዊ ልታደርጋቸው የምትችላቸውን በኃጢአት መሥዋዕት ውስጥ ያሉ መመሪያዎችን ዘርዝረህ ጻፍ።

(ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ነው የሞተው። የሞተው ለእያንዳንዳችን ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ኃጢአታችን በእኛ ላይ ያመጣውንም ርኩሰት ጭምር ነው ያስወገደልን። እኛ የነፃነው በተረጨው የኢየሱስ ክርስቶች ደም ነው! (1ኛ ጴጥ.1፡2፣ ራዕይ 7፡14)።

9ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ዮሐ.1፡7 እና ዕብራውያን 9፡12-14 አንብብ። የኢየሱስ ደም ያስገኛቸው ውጤቶች ምን ምንድናቸው?

(ለ) ምንም እንኳን ዛሬ ኃጢአት እንደ መገናኛው ድንኳን ያለውንሕንጻ ባያረክስ እኛን ያረክሰናል። ኃጢአት ስንሠራ ኃጢአታችንን መናዘዝ አለብን። በዚህም ጊዜ የኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል።

(ሐ) የመሪዎች ኃጢአት ከተራው ሕዝብ ኃጢአት እምብዛም አይበልጥም። ነገር ግን የእነርሱ ኃጢአት በተራው ሕዝብ ብዙ መዘዝን የሚያስከትል ነበር። አንድ መሪ በኃጢአት ሲወድቅ ብዙ ጊዜ ሌሎችም ተከትለውት በኃጢአት ይወድቃሉ። የሊቀ ካህኑና የመኮንኑ ኃጢአት ከፍ ያለ መሥዋዕት እንደጠየቀ ሁሉ የመሪዎችንም ኃጢአት ማስወገዱ በጣም ከባድ ነው።

10ኛ ጥያቄ:- (ሀ) በአንተ ወይም በሌላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎች የሠሩት ኃጢአት በቤተ ክርስቲያናት ያሉትን ሰዎች እንዴት እንደጎዳ ተመልክተሃል? (ለ) ሉቃስ 12፡48 እና ያዕቆብ 3፡1 መሪዎች እራሳቸውን ከኃጢአት እንዲጠብቁ የሚያስጠነቅቃቸው እንዴት ነው?

(መ) ከኃጢአት ከመንጻታችን በፊት ሁሌ ስለ ኃጢአታችን ንስሐ ልንገባ ያስፈልገናል! (ኦሪት ዘሌዋ.5፡5-6፥ 1ኛ ዮሐ.1፡9)።

# ሁለተኛ ቀን

## የበደል መሥዋዕት

ኦሪት ዘሌዋውያን 5፡14-6፡7፥ 7፡1-10

የመጨረሻው መሥዋዕት «የበደል መሥዋዕት ወይም የካሣ መሥዋዕት» በመባል ይታወቃል። ኃጢአተኛው ለበደለው እሥራኤላዊ ካሣ ለመክፈል ሲነሣሣ ወይም ከእግዚአብሔር ሲሰርቅ ነው ይህን የበደል መሥዋዕት የሚጠቀምበት። ከኃጢአት መሥዋዕት ለየት የሚያደርገውም ይህ ነው። ይቅርታ መጠየቁ ብቻ በቂ አይደለም፥ ለበደለው ወንድሙም ካሣ መስጠት ነበረበት።

አንድን ሰው ስንበድል፥ ብዙ ጊዜ ይቅርታ ብቻ ሳይሆን ካሣም መክፈል ይገባናል። የበደሉ መሥዋዕት ትክክለኛ የሆነ ይቅርታን ብቻ አልነበረም የሚያስገኘው፤ እግዚአብሔር ትክክለኛ የሆነ ካሣ መክፈሉን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ነው። ይህ ዛሬ ለእኛ ጥሩ መመሪያ ሊሆን ይችላል።

11ኛ ጥያቄ:- ይቅርታ ብቻ ሳይሆን ካሣ ሊያስከፍሉን የሚችሉ ኃጢአቶችን ለምሳሌ ያህል ጥቀስ።

* ኦሪት ዘሌዋውያን 5፡14-6፡7፥ 7፡1-10 አንብብ።

12ኛ ጥያቄ:- ለበደል መሥዋዕት ይሰጥ የነበረው እንስሳ ምን ነበር?

13ኛ ጥያቄ:- ለምን ዓይነት ኃጢአቶች ነው ኃጢአተኛው ይህን የበደል መሥዋዕት ማቅረብ የሚገባው?

14ኛ ጥያቄ:- ኃጢአተኛው የበደል መሥዋዕቱን ከማቅረቡ በፊት ሌላ ሊያደርገው የሚገባው ነገር ምን ነበር?

1. ከበደል መሥዋዕት ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች

እንደሚቃጠለው መሥዋዕት ወይም የኃጢአት መሥዋዕት ሳይሆን ለበደል መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው ተባት በግ ብቻ ነው። እንስሳው እንዴት እንደሚሠዋ የተሰጠው ማብራሪያ ትንሽ ነው። በነሐሱ መሠዊያ ላይ መቅረብ እንደነበረበት ግን እናውቃለን። ምንም እንኳን ባይጠቀስም፥ ኃጢአተኛው እጁን በእንስሳው ላይ ጭኖ ኃጢአቱን መናዘዝ ያለበት ይመስለናል፤ (ኦሪት ዘኁልቁ 5፡7)። ልክ እንደሚቃጠለው መሥዋዕት ደሙ በመሠዊያው ጎንና ጎን መረጨት ነበረበት፤ ስቡና የተወሰኑ የእንስሳው የሰውነት ክፍሎች እንደ ኅብረቱ መሥዋዕት መቃጠል ነበረብት። የተቀረው የእንስሳው ሥጋ የካህናቱ ነበር። ማንኛውም ካህን ይህንን ሥጋ በመገናኛው ድንኳን ውጪ ግቢ መብላት ይችል ነበር።

2. ለምን ዓይነት ኃጢአቶች ነበር ይህ የበደል መሥዋዕት የሚቀርበው?

የበደል መሥዋዕት የሚያስፈልጋቸውን ኃጢአቶች በሙሉ ማጤኑ ይከብዳል። ቢሆንም የሚከተሉት ኃጢአቶች እንደ ምሳሌ ተጠቅሰዋል:-

(ሀ) ማናቸውም ሰው ለእግዚአብሔር በተቀደሰው በማናቸውም ነገሮች ላይ ኃጢአት ቢሠራ የበደል መሥዋዕት ማቅረብ አለበት፤ (ኦሪት ዘሌዋውያን 5፡14)። ምናልባትም እነዚህ የተቀደሱ ነገሮች ከአምልኮ ቤተ መቅደሱ ጋር ሳይያያዙ አይቀሩም። ኃጢአተኛውም ለእግዚአብሔር አንድ ነገር እሰጣለሁ ብሎ ቃል ገብቶ ሳይፈጽመው ቀርቶ ይሆናል። ወይም ደግሞ ፍየል ማምጣት ሲኖርበት ሁለት እርግቦች አምጥቶ ይሆናል። ወይም በቤተ መቅደሱ ለጌታ መስጠት የሚገባውን አሥራት ሳይሰጥ ቀርቶ ይሆናል፤ እነዚህ ነገሮች በሙሉ የእግዚአብሔር ንብረት ናቸው፤ ኃጢአተኛው ግን ለጌታ መስጠት የሚገባውን ነገር አልሰጠም።

ኃጢአተኛው ለእግዚአብሔር አውራ በግ ብቻ ሳይሆን ማምጣት ያለበት ካህኑ በጌታ ላይ ያለውንም ዕዳ ገምግሞ እንዲያመጣ ያደርገው ነበር። ኃጢአተኛውም በእግዚአብሔር ላይ ያለበትን ዕዳ የዕዳውንም 20% ጨምሮ ለካህኑ ማስረከብ አለበት። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ይቅር የሚለው ዕዳውንና 20% ጭማሪውን ከፍሎ አውራ በጉን መሥዋዕት ካቀረበ በኋላ ነው።

(ለ) ማንኛውም ሰው በማያውቀው መንገድ እግዚአብሔር አትሥሩ ካላቸው ትዕዛዛት አንዲቱን መተላለፉንና የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ መኖሩን ድንገት ቢገነዘብ በደለኛ ይሆናል፤ (ኦሪት ዘሌዋ.5፡17)። ሕሊናው ኃጢአተኛ እንደሆነ ይጠቁመዋል። ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት አውራ በግ አቅርቦ መሠዋትነበረበት። እግዚአብሔርን እንዴት እንደበደለ በግልፅ ባለማወቁ ምክንያት 20% እንዲፍል አይደረግም ነበር።

(ሐ) አንድ ሰው ባልንጀራውን ቢበዘብዝ ወይም ከእርሱ ቢሰርቅ የበደል መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት፤ (ኦሪት ዘሌዋ.6፡1-3)። ለባልንጀራው ይመልስ የነበረው ዕዳውን በሙሉ ብቻ አይደለም፤ የዕዳውን 20% ጭምር ነው እንጂ። ይህም የሆነው ባልንጀራውን በማስቀየሙ ነው። ኃጢአተኛው እግዚአብሔርን ብቻ አልነበረም ይቅርታ የሚጠይቀው፤ የበደለውን ወንድሙንም ይቅርታ ጠይቆ እውነተኛነቱን ለማሳየት የወሰደውን ነገር መመለስ ነበረበት።

3. ከበደል መሥዋዕት የምናገኘው ትምህርት

15ኛ ጥያቄ፡- ከበደል መሥዋዕት ውስጥ ለቤተ ክርስቲያንህና ለአንተ ይጠቅማሉ ብለህ የምትላቸውን መመሪያዎች በዝርዝር ጻፍ።

(ሀ) ትንቢተ ኢሳይያስ 53፡7፥ የሚመጣውን መሢሕ ኢየሱስ ክርስቶስን «እንደ በደል መሥዋዕት» አድርጎ ያቀርበዋል። በእግዚአብሔር ላይ እጅግ በጣም ትልቅ ኃጢአት ብንሠራም በሱ ዓይን ብዙ የኃጢአት ዕዳ እንዳለብን ቢያውቅም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአታችንን ዋጋ በሙሉ በመስቀሉ ላይ ከፈለልን፤ (ቆላስይስ 2፡13-14)። (ለ) ማንኛውም ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ በመሆኑ ይቅርታ ያስፈልገዋል። በባልንጀራችን ላይ ኃጢአት ስናደርግ ደግሞ ይቅርታ ልንጠይቀው ይገባል። በእግዚአብሔር ዓይን ባልንጀራችንን ስንበድል የሚታየው እራሱኑ እንደበደልነው ነው። ሕይወታችን በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት ንጹህ ሊሆን ይገባል፤ (ማቴ.5፡23-24)። የወንጌል መልእክት ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ኅብረት እንዲኖረን አይደለም የሚገልጸው፤ ከሰው ጋርም ኅብረት ሊኖረን እንደሚገባ ይናገራል፤ (ኤፌሶን 4፡25፥ 32)።

16ኛ ጥያቄ፡- ማቴ.6፡14-15 አንብብ። ከእግዚአብሔር ይቅርታ እንድ ናገኝ ምን ማድረግ እንዳለብን ነው የሚናገረው የእግዚአብሔር ቃል?

(ሐ) ለእግዚአብሔር ስለት ተስለን ካልፈጸምነው ከእግዚአብሔር እንደ ሰረቅን ነው የሚቆጠረው። አሥራታችንና ምጽዋታችንን ካላቀረብን እንደ ስርቆት ነው የሚታየው። ብዙ ክርስቲያኖች መሪዎችም ጭምር ሊሰጡ የሚገባቸውን ስለማይሰጡ መንፈሳዊ ሌቦች ሆነው ነው የሚኖሩት። አንተስ በእግዚአብሔር ፊት ሌባ ነህ?

(መ) ባልንጀራችንን ከሰረቅን ይቅርታ ብቻ መጠየቁ በቂ አይደለም። ካሣ መስጠት ይገባናል። የሰረቅነውን ነገር መመለስ ይኖርብናል። እውነተኛ ሆነን መፀፀታችን የሚታወቀው ያለብንን ዕዳ ከፍለን አቋማችንን ስንቀይር ነው።

17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ሲሰርቅ ይህን ሥርዓት ይከተላል?

ለ) የሰረቀውን ዕቃ መልሶ ንስሐ ይገባል ወይስ ንስሐ ብቻ በቂ ነው ይላል?

ሐ) ዕቃውን መመለሱ ተገቢ ይመስልሃል?

እግዚአብሔር ከመያዛችን በፊት ኃጢአታችንን እንድንናዘዝ ይፈልጋል እንጂ ከመያዛችን በኋላ እንድንናዘዝ አይፈልግም።

በኦሪት ዘጸአት 22፡6-9 ላይ አንድ ሰው ወዳጁን ሰርቆ ቢጎዳው ወደ ፈራጆችም ቢቀርብ የሰረቀውን መልሶ በተጨማሪም የዕቃውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ መክፈል ነበረበት። ይህም ማለት የሰረቀውን ያህል እጥፍ መክፈል ነበረበት ሆኖም በራሱ አነሳሽነት መጥቶ ኃጢአቱን ቢናዘዝ የዋጋውን 20% ብቻ ነበር በተጨማሪ የሚከፍለው። እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች ዘንድ ታማኝ ሆነን እንድንገኝ ይፈልጋል። ከጎዳናቸው እነሱ መጥተው እስኪወቅሱን ድረስ መጠበቅ የለብንም፤ ነገር ግን ወደ እነርሱ ሄደን ኃጢአታችንን ተናዝዘን ዕዳችንንም መክፈል ይኖርብናል።

## የአምስቱ መሥዋዕቶች ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ እሥራኤላውያን እንዲያቀርቡ ያዘዛቸውን አምስቱን መሥዋዕቶች ተመልክተናል። እነዚህ አምስት መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር አምልኮ መሠረት ናቸው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ መሞት እነዚህ መሥዋዕቶች የተወሰነ ነገር አሳይተውናል። በተጨማሪም እግዚአብሔርን እንደሚፈልገው እንዴት ማምለክ እንደሚገባን ያሳዩናል። ስለ መስዋዕቶቹ ያለውን ማጠቃለያ በሠንጠረዥ ላይ ተመልከት።

በተለይ ኃጢአት በተመለከተ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡ ሦስት መሥዋዕቶች ነበሩ፤ እነርሱም፦-

1. የሚቃጠለው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት የሞት ፍርድ የተፈረደበትን ኃጢአተኛ ያመለክታል። በሰውዬው ሞት ፈንታ እግዚአብሔር የእንስሳውን ሞት ነው የሚቀበለው። እኛም ብንሆን ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኞች ነን፤ የኃጢአት ዋጋ ደግሞ ሞት ነው፤ (ሮሜ 3፡23)። እግዚአብሔር ግን በእኛ ፈንታ በመስቀል ላይ እንዲሞት ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ላከ። የክርስቶስን ሞት በሚያመለክተው ማለት በሚቃጠለው መሥዋዕት አማካኝነት ነበር ኃጢአተኛው ከሞት የዳነው።

2. የኃጢአት መሥዋዕት ደግሞ ኃጢአት የሚያመጣውን መዘዝ ያመለክታል። ኃጢአተኛው ስለ ኃጢአቱ ተጠያቂ ብቻ አይደለም፤ ኃጢአቱ እግዚአብሔርን የሚያመልክበትን መንገድ አርክሶታል። የእንስሳው ደም ነበር የሰውዬውን ኃጢአትና የአምልኮ ቦታውን የሚያፀዳው። ኃጢአት በሠራን ቁጥር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት ይቋረጣል ሕይወታችንም ይረክሳል። በዚህ ጊዜ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያለማቋረጥ ከኃጢአታችን ያነፃናል። በዚህ ምክንያት ነው መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር ያለ ማቋረጥ በመቅረብ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ የሚለው፤ (1ኛ ዮሐ.1፡9)።

3. የበደሉ መሥዋዕት ትልቅ ዕዳ ኖሮበት በእግዚአብሔር ፊት እንደበደለኛ የቀረበን ሰው ያመለክታል። ሰውዬው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቷል። ባለ ዕዳውም ሆኗል። እኛም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስንሠራ የእርሱ ባለዕዳዎች ነን። ለእኛም ኢየሱስ ክርስቶስ ዕዳችንን ስለ ከፈለልን እነሆ አሁን ነፃ ወጥተናል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ተባቱን በግ እንደ ዕዳ መክፈያ አድርጎ ይቀበለው እንደ ነበር ነገር ግን በተጨማሪም ሰዎችን ስንበድል የበደልናቸውን ለእነርሱ በመናዘዝ ከእነርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት እንድናስተካክል እግዚአብሔር ይፈልጋል።

የተቀሩት ሁለቱ መሥዋዕቶች ከምስጋና ጋር የተያያዙ ናቸው። እነርሱም፦-

1. የእህሉ ቁርባን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የዕለት ጉርሱን ስለሚሰጠው ስለሚባርከው ሕዝቡ የሚያቀርብለትን ውዳሴና ምሥጋና ያመለክታል። እኛም እግዚአብሔርን ስለሚሰጠን ነገር ሁሉ ማመስገን ይኖርብናል። ስለሚሰጠን ነገር ማመስገናችንን የምናመለክተው አሥራታችንንና መሥዋዕታችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ ነው።

2. የኅብረት መሥዋዕት ደግሞ እግዚአብሔር ስለሰጣቸው ልዩ በረከቶችና የጸሎት መልሶች የሚቀርበውን ምስጋና ያመለክታል። በተጨማሪም በእግዚአብሔር ቤት ሰብ ውስጥ ከሌሎች ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል።

ምንም እንኳ ወደ እግዚአብሔር ከኃጢአታችን ለመንጻት በመጀመሪያ ወደ እርሱ በንስሐ መቅረብ ቢኖርብንም አምልኮአችን እዚህ ላይ መቆም የለበትም። እንዲያውም እሱን በማመስገንና በማወደስ ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረን ማድረግ ያስፈልገናል።

18ኛ ጥያቄ:- እነዚህ አምስቱ መሥዋዕቶች ለአንተ ሕይወትና ለቤተ ክርስቲያንህ ስለ እውነተኛ አምልኮ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት እንዴት ነው?

ክርስቲያን ካሁን ወዲያ የደም መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም። ለኃጢአታቸው አሁንም የደም መሥዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎች ተሳስተዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው መሥዋዕት ነው። ለሰው ልጆች ኃጢአት ደሙን አፈሰሰ። ክርስቲያኖች ለኃጢአታቸው የደም መሥዋዕት ለማቅረብ ካሰቡ የኢየሱስ ሞት ሙሉ በሙሉ ኃጢአታቸውን እንደደመሰሰላቸው በሙሉ ልብ አያምኑም ማለት ነው፤ (ዕብራውያን 10:11-18)።

19ኛ ጥያቄ:- ሮሜ 12:1፥ ፊልጵ.4:18፥ ዕብ.13:15-16 አንብብ።

ሀ) ለእግዚአብሔር ማቅረብ የሚገባንን የተለያዩ መሥዋዕቶች ዘርዝረህ ጻፍ፤ (ጥቅሶቹን ተመልከተህ)።

ለ) እነዚህን መሥዋዕቶች በምን ዓይነት መንገድ በሕይወትህ እንደምታቀርባቸው ዘርዝረህ ጻፍ።

ሆኖም እኛም ብንሆን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ያለብን መንፈሳዊ መሥዋዕቶች አሉን፤ (1ጴጥ.2:5)። እነዚህ መንፈሳዊ መሥዋዕቶች የሚጀመሩት ለእግዚአብሔር ሁለንተናችንን አሳልፈን ሰጥተን የእርሱን ፈቃድ ጠብቀን እርሱ እንደፈለገ እንዲጠቀምብን ስናደርግ ነው። እነዚህ መሥዋዕቶች ንብረታችንንና ገንዘባችንን ለእግዚአብሔር መስጠትን በኢየሱስ ስም ለሌሎች ደግ መሥራትንና ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት ማቅረብን ያጠቃልላሉ። እነዚህን የመሳሰሉት መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር እያቀረብን ነው ወይ?

# ሦስተኛ ቀን:-

በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለው የአምልኮ ሥርዓት አጀማመር

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 8-9

እስካሁን ድረስ ባለው የአሪት ዘሌዋውያን ጥናታችን እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ያለውን የአምልኮ ሥርዓት እንዴት እንዳዳፈለቀ ተመልክተናል። በመጀመሪያ ለሙሴ በተሰጠው የማያወላውል ትዕዛዝ መሠረት እንዴት መገናኛ ድንኳኑ እንደተሠራ ተመልክተናል። ሁለተኛ ሕዝቦቹ በአምስት የተለያዩ መሥዋዕቶች ታግዘው እንዴት ቀርበው ከእርሱ ጋር ኅብረት መፍጠር እንደሚችሉ የሚያሳይ የተብራራ መመሪያ እግዚአብሔር ለሙሴ እንደሰጠው እናያለን። ዛሬ ደግሞ ካህናቱ እንዴት ነጽተውና ተለይተው የአምልኮ ሥርዓቱን ለመምራት እንደሚችሉ እንመለከታለን።

በቤተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ እግዚአብሔር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ሕዝቡን እንዲመሩ ያደርጋል። እንደ ካህናቱ በእግዚአብሔር መጠራት አለባቸው። የመሪዎችን ሥራ በተመለከተ በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ የተሰጡ ብዙ መመሪያዎችን ልናጤን እንችላለን።

20ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ መሪዎች ለአገልግሎት የሚመረጡት እንዴት ነው?

ለ) በሕይወታቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ጥሪ የሚያውቁት እንዴት ነው?

ሐ) ኃላፊነቶቻቸውስ ምን ምንድን ናቸው?

* ኦሪት ዘሌዋውያን 8-9 አንብብ።

21ኛ ጥያቄ:- ካህናቶቹን ቅዱሳንና መሥዋዕትን ለማቅረብ ብቁ የሚያደርጓቸው ለእግዚአብሔር የቀረቡ መሥዋዕቶች ምን ምንድን ናቸው?

22ኛ ጥያቄ:- በምዕራፍ 8 ላይ እነዚህን መሥዋዕቶች ያቀርብ የነበረው ማነው?

23ኛ ጥያቄ:- የእሥራኤልን ሕዝብና እራሱን ለማንጻት አሮን ያቀርብ የነበረው መሥዋዕቶች ምንና ምን ነበሩ?

24ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘጸአት 39:1-31 አንብብ።

* ለአሮንና ለካህናቱ የተሰፉትን የተለያዩ ልብሶች በዝርዝር ጻፍ።

እግዚአብሔር መገናኛ ድንኳኑን በሠራበት ወቅት አብሮ ለሊቀ ካህናትና ለካህናት የሚሆኑ የተለዩ ልብሶችን በሕዝቦች አማካኝነት ያሰፉ ነበር። ይህም የተደረገው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ለሚኖራቸው አገልግሎት ለይቶ ለማዘጋጀት ነው። መገናኛው ድንኳን ከተሠራ በኋላ የመሥዋዕቶቹን አቀራረብ በተመለከተ ተገቢው መመሪያ ከተሰጠ በኋላና ካህናቱ ከተለዩ በኋላ የሚቀረው እግዚአብሔር የሚመለከበት ጊዜ ነው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሙሴን አሮንንና አራት ልጆቹን፥ ልብሶቻቸውን፥ አሮንና ልጆቹ የሚቀቡትን የቅባቱን ዘይት፥ ወይፈን፥ ሁለት ደንግሌ በጎችና ቂጣ እንጀራ የሞላ ሌማት በእኔ ፊት መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ሰብስብ አለው። የእሥራኤል ሕዝብ በሙሉ በተለይም ሽማግሌዎቹ የሕዝቡን አምልኮ የሚመሩት ካህናቶች ተለይተው የሚመረጡበትን ይህን ቀን ለመመልከት ይወጡ ነበር።

እስካሁን ባለው የኦሪት ዘሌዋውያን ጥናታችን እንዳየነው ያለማቋረጥ የአምልኮ ሥርዓቱን በዝርዝር ይሰጥ የነበረው እግዚአብሔር ነው። አሁንም ደግሞ ሙሴ አሮንንና ልጆቹን ለክህነት የመረጠ፥ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለውን የአምልኮ ሥርዓት በዝርዝር የሰጠ፥ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ሕዝቡ ያስታውሳል። የተመረጡትና ሥርዓቱ የተደነገገው በእግዚአብሔር ነው እንጂ በሙሴ አይደለም። እነዚህ የእግዚአብሔር ምርጫ እንጂ የሙሴ አልነበሩም።

ይህ ለክህነት ተለይተው የሚቀርቡበት ሥርዓት በሙሴ ብቻ የሚሠሩ ብዙ ክንዋኔዎችን ያካተተ ነው።

ያላቸውን ለየት ያለ ሥልጣንና ሐላፊነት ያመለክታል። ይህን የክህነት ልብስ ያደርጉ የነበረው በመገናኛ ድንኳን ውስጥ ያለውን የአምልኮ ሥርዓት ሲመሩ ብቻ ነው። (3) በሊቀ ካህኑ አገልግሎት አማካኝነት እሥራኤልን የሚጎበኘው አምላክ ምን ያህል ኃያል ቅዱስና ጻድቅ እንደሆነ የሚያሳስቡ ልብሶች ናቸው።

እንደቀድሞው የተለዩ ሊቀ ካህናት ስለሌሉ ሁላችንም ካህናት ስለሆንን (1ኛ ጴጥ.2፡5፣ ራዕይ 1፡6)፣ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው አስታራቂ ጌታ ኢየሱስ በመሆኑ (1ኛ ጢሞ.2፡5)፣ መሪዎችን ከሌላው ሕዝብ የሚለይ ልብስ አያስፈልገንም። የተለየ የክህነት ልብስ የምንጠቀም ከሆነ ግን ልብሱ ለሰዎች ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር መስጠቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

26ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለምንድነው አንዳንድ ሰዎች ወይም መዘምራን የተለየ ልብስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያደርጉት? ዓላማቸው ምንድነው?

ለ) ይህ ነገር ጥሩ ነው ወይስ ጥሩ አይደለም? ለምን?

ሐ) ይህ ነገር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካለው ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

27ኛ ጥያቄ፡- የሐንስ ራዕይ 1፡13 አንብብ። የሊቀ ካህኑ ልብስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ካደረገው ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ ሊቀ ካህን ነው። በዚህም ምክንያት በመንግሥተ ሰማያት የሚያገለግለን የሊቀ ካህኑን ዓይነት ልብስ አድርጎ ነው።

ሦስተኛ፡- ሙሴ መገናኛ ድንኳኑንና በውስጡ የሚገኙትን የአምልኮ ዕቃዎች በሙሉ በቅባቱ ዘይት ቀባቸው። በነሐስ የተሠሩትን መሠዊያና ሳሐን ለተቀደሰ አምልኮ ለይቶ እንዳስቀመጣቸው ይጠቁማል። በብሉይ ኪዳን ዘመን የሚቀርቡ ነገሮች በእግዚአብሔር ዘንድ ለየት ሌላ ዓላማ የሚፈለጉ ናቸው። በዚህ ምክንያት ነው ሳሙኤል ዳዊትን የቀባው፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም መሢሕ ወይም «የተቀባ» የሚል ስያሜ የተሰጠው። ጌታ ኢየሱስ እንደ ዳዊት በእግዚአብሔር ለተለየ ዓላማ የተመረጠ ነበር።

አራተኛ፡- ሙሴ ለአሮንና ለልጆቹ በመጀመሪያ የኃጢአቱን መሥዋዕት በኋላም የሚቃጠለውን መሥዋዕት ያቀርባል። ይህ ለአሮን፣ ለልጆቹና፣ ለእሥራኤል ሕዝብ አሮን ኃጢአተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ሥርዓት ነው። የእግዚአብሔርን ልጆች ለማንጻት ከመዘጋጀቱ በፊት፣ አሮን እራሱን ከግል ኃጢአቱ ሁሉ ማንጻት ነበረበት። ለራሱ መሥዋዕት ማቅረብ የማይገባው ምንም ኃጢአት ያልነበረበት ዘላለማዊው ሊቀ ካህን ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው። እርሱ እራሱን ለኃጢአተኞች መሥዋዕት ለማቅረብ ብቻ ነው የመጣው።

የኃጢአቱ መሥዋዕት ሁለት ዓላማዎች ነበሩት። በመጀመሪያ ማደሪያውን ከኃጢአት ላማንጻት ነው። ስለዚህ የነሐሱ መሠዊያ ይፀዳና ለአምልኮ ይዘጋጅ ነበር። አሮንና ልጆቹ የሠሩት የተወሰነ ኃጢአት ባለመኖሩ በኃጢአት መሥዋዕት ጊዜ እንደሚደረገው ደሙን በቅዱስ ቦታ ወስደው በመጋረጃው ላይ ወይም በዕጣኑ መሠዊያ

ላይ አያደርጉም ነበር። ደሙ የሚረጨው በነሐሱ መሠዊያ ላይ ብቻ ነው። የተቀረው ሥርአዓት ደግሞ ለማንኛውም ሌቀ ካህን እንደሚሠዋው የኃጢአት መሥዋዕት ነበር የሚቀርበው።

እንደማንኛውም የሚቃጠል መሥዋዕት ለዚህ የሚቃጠል መሥዋዕት ይሠዋ የነበረው አውራ በግ ነው። ይህ ሥርዓት የካህናቱ የኃጢአት ዋጋ እንደተከፈለ እነርሱ ደግሞ እራሳቸውን ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ትዕዛዝ አሳልፈው እንደሰጡ የሚያመለክት ነው።

28ኛ ጥያቄ፡- እነዚህ ትምህርቶች ዛሬ ላሉት መሪዎች ምን ያህል ነው መልካም አርአያ የሚሆኑት?

አምስተኛ፡- ለአሮንና ለልጆቹ ቅድስና ብሎ ሙሴ ሌላ አውራ በግ ይሠዋል። ይህ መሥዋዕት ከደኅንነት መሥዋዕት ጋር ይመሳሰላል። ሙሴ የአውራ በጉን ደም ወስዶ የቀኝ ጆሮአቸውን ጫፍ፣ የቀኝ እጃቸውን አውራጣት፣ የቀኝ እግሮቻቸውን አውራ ጣት አስነካና በልብሳቸው ላይ ረጨው። ይህ ደም ለአገልግሎት መንፃታቸውን የሚያመለክት ነው። እንደ እግዚአብሔር ተወካዮች ጆሮአቸው የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት የተዘጋጀ መሆን እንዳለበት እጆቻቸው ተለይተው እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ የእርሱን ሥራ መሥራት እንዳለባቸውና እግሮቻቸው ደግሞ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን መንገድ ተከትለው መራመድ እንዳለባቸው የሚያሳስባቸው ሥርዓት ነው። ልብሶቻቸውም የተረጩት፣ ሁለንተናቸውን ለእግዚአብሔር እንደሰጡ ለማሳየት ነው።

29ኛ ጥያቄ፡- ይህ ሥርዓት ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ስለ መስጠት የሚያስተምረን ትምህርት ምንድነው? (ሮሜ 12፡ 1-2 አንብብ)።

ይህ ሥርዓት ከደህንነት መሥዋዕት ጋር በአውራ በጉ ምክንያት ይመሳሰላል። የእግዚአብሔር የሆነው በነሐሱ መሠዊያ ላይ ይሠዋ ነበር! የካህናቱ የሆነውን ደግሞ ሙሴ ይወስደው ነበር። የቀኝ ወርቹ የመወዝወዝ ቁርባንና የእህሉ ቁርባን ይሰጡ የነበሩት ለአሮን ነው! በስተመጨረሻም በመሠዊያው ላይ ይቃጠሉ ነበር። የተቀረውን ሥጋ አሮንና ልጆቹ በመገናኛው ድንኳን ውጪኛ ግቢ ውስጥ እንዲበሉ ሙሴ ትዕዛዝ ይሰጣል።

ስድስተኛ፡- ሙሴ ዘይቱንና ደሙን ቀላቅሎ እንደገና አሮንና ልጆቹን ቀባቸው። ይህ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሲዘጋጁ ከኃጢአት መንጻት እንዳለባቸው የሚያሳይ ሥርዓት ነው።

ሰባተኛ፡- ሙሴ አሮንና ልጆቹ ለሰባት ቀን ያህል ከማኅበሩ ድንኳን ደጃፍ ሳይወጡ እንዲቆዩ አዘዛቸው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርን በመገናኛ ድንኳን ውስጥ የማገልገል ሐላፊነታቸውን ለመወጣት ዝግጅት በማድረግ ላይ ነበሩ። በዚህ በሰባቱ ቀን ውስጥ ዕለት ዕለት በመሠዊያው ላይ ለእነርሱና ለመሠዊያው የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ወይፈን ይቀርብ ነበር! (ኦሪት ዘጸአት 29፡35)።

በመጨረሻም አሮንና ልጆቹ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ በደንብ እንዲጠብቁ ሙሴ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ትዕዛዙን ካልጠበቁ የእግዚአብሔር የሞት ፍርድ በላያቸው ላይ ይወሰንባቸዋል። የእግዚአብሔር አምልኮ ለእራሱ ለእግዚአብሔር የተለየ ነው፤ ስለዚህም ፕልቅ በሆነ አክብሮት ልንመለከተው ይገባል። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ መጠበቃቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። እግዚአብሔር ከእኛም ቢሆን ከአንገት በላይ የሆነ አክብሮት አይፈልግም፤ ሕግጋቱን ብሙሉ እንድንጠብቅለት ይፈልጋል።

አያሌ ክርስቲያኖች ዛሬ መሪዎቻቸው ለአዲስ አገልግሎት በሚመረጡበት ጊዜ የተለየ ዕለት አድርገው በመውሰድ በተለየ አኳኋን ያከብሩታል። ይህ ልማድ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በመሪዎቹ ላይ ያስቀመጠው ኃላፊነት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ሊያሳያቸውና ሊያስታውሳቸው ይችላል። ያለ ፕልቅ ሐሳብና ጸሎት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሥልጣንን መያዝ አይገባንም። የበጎቹ እረኞች በምንሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር ከእኛ ብዙ ነገር ይጠብቃል።

30ኛ ጥያቄ:- ለየት ባለ ጾምና ጸሎት አዳዲስ መሪዎችን የሚመርጡ ማኅበራትን ታውቃለህ? ለምንድነው እንደዚህ የሚያደርጉት?

ከስምንት ቀን ቆይታ በኋላ፥ በሙሴ መሪነት አሮን የሊቀ ካህንነት ማለት የእሥራኤል ልጆች የመንፈሳዊ መሪነት ሥራውን ጀመረ። ይህ ቀን በጣም ትልቅ የአምልኮ እንደሆነ ይታሰብ ነበር። ምክንያቱም «እግዚአብሔር ይገለጥላችኋል» (ኦሪት ዘሌዋውያን 9:4፤ 6) ብሎ ለአሮን ቃል የገባበት ቀን በመሆኑ ነው። ይህንን ቀን ምክንያት በማድረግም የእሥራኤል ሽማግሌዎች ተሰብስበው ነበር። አሮን አገልግሎቱን የሚጀምርበትን ቀን በሁለት ልንከፍለው እንችላለን። ይኸውም:-

አንደኛ:- አሮን ይህን የአምልኮ ቀን ለእራሱ መሥዋዕት በማቅረብ ነው የጀመረው። የሌሎችን መሥዋዕት ለማቅረብ ከመዘጋጀቱ በፊት ሊቀ ካህኑ እራሱን ሊያነጻ ይገባል። በመጀመሪያ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት እምቦሳ አቀረበ። ሰው የሚያውቀው ኃጢአት ባለመሥራቱ ደሙ ወደ ቅዱስ ቦታ በመውሰድ ፈንታ በነሐሱ መሠዊያ ቀንድ ላይ ብቻ ነው የተረጨው። ስለራሱ ኃጢአተኛነት በሕዝቡ ፊት ቆሞ ንስሐ መግባት ነበረበት። ስለሚቃጠለው መሥዋዕት ለራሱ ሲል አውራ በግ ማቅረብ ነበረበት።

ሁለተኛ:- አሮን ለሕዝቡ መሥዋዕት ያቀርብ ነበር። አራት ዓይነት መሥዋዕቶች ነበሩ የሚቀርቡት:-

1. ፍየል ለኃጢአት መሥዋዕት፥
2. አውራ በግና ጥጃ ለሚቃጠለው መሥዋዕት፥
3. በሬና አውራ በግ ለኅብረት መሥዋዕት ሲቀርቡ
4. የእህል ቁርባን ደግሞ ይቀርብ ነበር። ይቀርብ ያልነበረው መሥዋዕት የበደል መሥዋዕት ብቻ ነው። የተፈጸሙ በደሎች ባለመኖራቸው የዚህ መሥዋዕት

መቅረብ አስፈላጊ አልነበረም። እነዚህ መሥዋዕቶች በሙሉ ይቀርቡ የነበረው እግዚአብሔር በሰጣቸው ድንጋጌዎች መሠረት ነው።

የእነዚህ ሁሉ መሥዋዕቶች ዓላማ የተወሰነ ኃጢአትን ለማስተሰረይ አይደለም። ዓላማው በአሮንና በሕዝቡ ስላለው የኃጢአት ባህርይ አጠቃላይ የሆነ ንስሐ ለመግባት ነው። የእግዚአብሔር አምልኮ ይከናወን የነበረው እግዚአብሔር በደነገገው ሥርዓት መሠረት ነው። ኃጢአተኛው እሥራኤላዊ ለኃጢአቱ ከእግዚአብሔር ይቅርታ የሚያገኝበት እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበትና ከሱ ጋር ኅብረት ሊያደርግበት የሚችልባቸው መንገዶች ነበሩት።

31ኛ ጥያቄ፡- በአንድ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ ውስጥ አጠቃላይ የሆነ ንስሐ ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? የአንተ ቤተ ክርስቲያን ይህን ዓይነት ሥርዓት ትከተላለች?

አሮን አዲስ ሊቀ ካህን እንደ መሆኑ መጠን ፊቱን በነሐስ ከተሠራው መሠዊያ ፊቱን ወደ ሕዝቡ በማዞር ይባርካቸዋል። እንደ መንፈሳዊ ተወካይነቱ አሁን ኃጢአታቸው ስለተሰረየላቸው የእግዚአብሔርን በረከት ሊሰጣቸው ችሉአል።

በዚህም ጊዜ ሙሴ ብቻ ሳይሆን አሮንም እግዚአብሔርን ለመገናኘት ወደ ማደሪያው ድንኳን ገባ። ምን እንደተባለ አናውቅም። ነገር ግን ለእሥራኤል ሕዝብ ሙሴ ብቻ ሳይሆን አሮንም ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት እንደሚችል ያመለክታል። በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል አሁን የሚቆመው አሮን ነው። የእሥራኤል ሕዝብ መሪ በመሆናቸው አሮንና ሙሴ ሲወጡ ሕዝቡን ባረኩት።

በዚህ ጊዜ በድንገት ከእግዚአብሔር ማደሪያ እሳት ይወጣና በነሐሱ መሠዊያ ላይ የነበረውን መሥዋዕት ያቃጥላል። በመሠዊያው ላይ እሳት ሊኖር ይችላል፥ ሆኖም እግዚአብሔር መሥዋዕቱን እንደተቀበለ ብቻ ሳይሆን የአምልኮ ሥርዓቱንና የአሮን ሊቀ ካህን መሆኑንም ጭምር እንደተቀበለ ያሳየው መሥዋዕቶቹን በእሣት በማቃጠል ነው። በእሥራኤል ታሪክ እንደዚህ ዓይነት ነገር ሦስት ጊዜ ሆኖአል! (መሳፍንት 13፡15-23፥ 1ኛ ዜና 7፡1-3፥ 1ኛ ነገስት 18፡38-39)። የእግዚአብሔር ክብር በዚህን ጊዜ ለሁሉም ታይቷል። ይህ በሕዝቦቹ ውስጥ ትልቅ ደስታንና ምስጋናን ፈጠረ። እራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ሁሉን ቻይ ለሆነው እውነተኛ አምላክ በግምባራቸው ተደፍተው ሰገዱ።

በብዙ መልኩ የእሥራኤል ሕዝብ አምልኮ በሥርዓቶች የተሞላ ይመስላል። ለእኛ ይህ እንግዳ ሊሆንብን ይችላል። ይህም ቢሆን አንዳንድ እውነታዎችን ልንማርበት እንችላለን፡- ለምሳሌ፡- 1. የእግዚአብሔር አምልኮ በጣም አስፈላጊ ነው። እንደቀላል ነገር ልንመለከተው አይገባም። እራሳችንን ሳናዘጋጅ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አንችልም። የምንዘጋጀውም ኃጢአተኛነታችንን ተገንዝበን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ነው። የዘለዓለም መሥዋዕት የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በዚህ ጊዜ፥ ከዓመፃ ሁሉ አንጽቶን በእግዚአብሔር ፊት እንድንቀርብ ያስችለናል።

በብዙ መልኩ የእሥራኤል ሕዝብ አምልኮ በሥርዓቶች የተሞላ ይመስላል። ለእኛ ይህ እንግዳ ሊሆንብን ይችላል። ይህም ቢሆን አንዳንድ እውነታዎችን ልንግርበት እንችላለን፡- ለምሳሌ፡- 1. የእግዚአብሔር አምልኮ በጣም አስፈላጊ ነው። እንደቀላል ነገር ልንመለከተው አይገባም። እራሳችንን ሳናዘጋጅ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አንችልም። የምንዘጋጀውም ኃጢአተኛነታችንን ተገንዝበን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ነው። የዘለዓለም መሥዋዕት የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በዚህ ጊዜ፥ ከዓመፃ ሁሉ አንጽቶን በእግዚአብሔር ፊት እንድንቀርብ ያስችለናል።

2. መንፈሳዊ መሪዎች እንዲሆኑ በእግዚአብሔር የሚመረጡት ሰዎች ይህን የመሪነት ሥራ ተገቢ የሆነ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። ከሎሎች ይበልጥ ኃጢአተኛነታቸውን ተገንዝበው ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት የንስሐ ሕይወት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ሕያው የሆነውን አምላክ በተገቢ መንገድ ያገለግሉት ዘንድ ሕይወታቸውን በንጽሕና መጠበቃቸውን እርግጠኞች መሆን አለባቸው።

3. እኛ የምናመልከው አምላክ በክብርና በግርማ ነው የሚኖረው። እግዚአብሔር ክብሩን በብሉይ ኪዳን ጊዜ ለእሥራኤላውያን እንደ ገለጸው ሁሉ በአዲሱ ኪዳንም ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ገልፆታል፤ (ሉቃስ 2፡19፥ 9፡31)። በዳግም ምፅዓቱ ጊዜ እኛም ክብሩን እናያለን፤ (ማቴ.25፡31)። አምላካችን ቅዱስና ታላቅ በመሆኑ አምልኳችን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ሊሆን ይገባዋል፤ ምክንያቱም አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና፤ (ዕብ.12፡28-29 ተመልከት)።

32ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እነዚህ እውነታዎች ለአንተና ለቤተ ክርስቲያንህ እንዴት ጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በዝርዝር ጻፍ። ለ) የእነዚህን ሁለት ምዕራፎች ትምህርት በመጠቀም የእግዚአብሔርን ቅድስና ሕዝቡ ለአምልኮ ሲቀርብ ሊኖረው የሚገባውን ቅድስና ለቤተ ክርስቲያንህ ልታሳውቅ የምትችለው እንዴት ነው?

## አራተኛ ቀን፡-

## የናዳብና አብድዩ ሞት - ኦሪት ዘሌዋውያን 10

ምዕራፍ 10 የሚያሳዝን ታሪክ ነው። ይህ ነገር የሆነው እግዚአብሔር መሥዋዕቱን በእሳት በማቃጠል ለእሥራኤል ሕዝብ ክብሩን በገለጸበትና መሥዋዕታቸውን እንደተቀበለ ባሳየበት ቀን ነው። ነገር ግን ኃጢአት ወዲያውኑ ተሸሎክልኮ ገባና የእግዚአብሔር የፍርድ እሣት እንዲወርድ ሆነ።

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 10 አንብብ።

33ኛ ጥያቄ፡- ናዳብና አብድዩ የፈጸሙት ኃጢአት ምንድን ነው?

34ኛ ጥያቄ፡- አሮንና የተቀሩት ልጆቹ ምን እንዲያደርጉ ነው ሙሴ ያዘዘው?

35ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ለአሮን የሰጠው ትዕዛዛት ምን ምንድናቸው?

36ኛ ጥያቄ፡- በተቀሩት የአሮን ልጆች እግዚአብሔር የተናደደው ለምንድነው?

የአሮን የመጀመሪያ ልጆች የሆኑት ናዳብና አብድዩ ለተወሰነ ጊዜ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ በሙሴና በአሮን አካባቢ ነበሩ። በዘፀአት 24፡1 ላይ በሲና ተራራን ወጥተው የእግዚአብሔርን ክብር እንዳዩ እናነባለን። አሮን ለእርሱና ለሕዝቡ መሥዋዕት ሲያቀርብ አብረውት ነበሩ። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ክብር ተመልከተዋል። መሥዋዕቶቹን ለማቃጠል ከእግዚአብሔር ዘንድ የወጣውን እሳት ሁሉ አይተዋል። ይህም ሆኖ ወዲያውኑ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፉ። በዚህም ምክንያት በእግዚአብሔር እሳት ጠፉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ናዳብና አብድዩ «በእግዚአብሔር ፊት እርሱ ያላዘዛቸውን ሌላ እሳት አቀረቡ» ይላል። እጣጥናው ላይ ዕጣን በማኖር ወደ ቅዱስ ቦታ ገብተው በእግዚአብሔር ፊት እንደቀረቡ ጥርጥር የለውም። ይህ እንደ ኃጢአት ተቆጥሮ የእግዚአብሔር ፍርድ በእነርሱ ላይ እንዲሆን ያደረጉ ብዙ የተለያዩ አማራጮች አሉ፤ እነርሱም፡-

1. ለዕጣኑ የተጠቀሙበት ከሰል ትክክለኛው ላይሆን ይችላል። ለዕጣኑ የሚጠቀሙበት ከሰል ሁልጊዜ ይመጣ የነበረው ከነሐሱ መሠዊያ ላይ ነው፤ (ኦሪት ዘሌዋ.16፡12)። ነገር ግን ትክክለኛውን ከሰል ወስደው ማንደዳቸውን የሚጠቅስ ነገር የለም።
2. በጥናው ውስጥ ዕጣን ማቅረብ የሚገባው ሊቀ ካህኑ ሊሆን ይችላል። ካህናቱ ሁልጊዜ በዕጣኑ መሠዊያ ላይ ዕጣን መጨረሱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ሊቀ ካህኑ ደግሞ በስርየት ቀን ብቻ ነው በዕጣኑ መሠዊያ ላይ ዕጣን የሚያኖረው።
3. ለአምልኮ ያልተፈቀደ የዕጣን ዓይነት ተጠቅመውም ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር የሚመለከበት አንድ ዓይነት ዕጣን ብቻ ነው። እንግዲህ ሌላ ዓይነት ዕጣን ተጠቅመው ይሆናል።
4. ዕጣኑን ያቀረቡት ለአሮን ወይም ለሙሴ ሳያሳውቁ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር ከመጠየቅ ፈንታ በትዕቢትና በችኮላ ተነሣሥተው ማድረግ የማይገባቸውን ነገር አደረጉ።
5. ሰክረውም ሊሆኑ ስለሚችሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መተላለፋቸውን ላያውቁት ይችላሉ።

የመጀመሪያው እሳት መሥዋዕቱን በማንደድ የእግዚዘብሔርን ደስታ ይገልጻል፤ ሁለተኛው እሳት ግን ናዳብንና አብድዩን በፍርድ የገደለ ነው።

እግዚአብሔር ለምንድን ነው በዚህ ፍርድ ላይ ቁርጠኛ አቋም የያዘው? ሙሴ እግዚአብሔርን ቀርበው ሊያገለግሉት የሚፈልጉ ሰዎች በሙሉ እሱን መታዘዝና ቅድስናቸውን መጠበቅ እንደሚገባቸው ለአሮን ያሳስበዋል። ያለመታዘዝ እግዚአብሔርን ያዋርዳል፤ መታዘዝ ደግሞ እግዚአብሔርን ያስከብራል። እግዚአብሔር መሪዎቹን በሕዝቡ ፊት ሁሉ እንዲያከብሩት ይፈልጋል። ለአምልኮ ከመነሣታቸው

በፊት እነ አሮን የአምልኮን ነገር ተገቢ ትኩረት ሰጥተው እርሱን በሚያመልኩበት ጊዜ ትዕዛዛቱን መጠበቃቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ገልጾላቸው ነበር። የእግዚአብሔርን አምልኮ እግዚአብሔር እራሱ በጥንቃቄ የሚጠብቀውና የሚንከባከበው ነገር ነው። እግዚአብሔር ሰዎች እንዲያገለግሉት ሲመርጥ ብዙ ነገር ይጠብቅባቸዋል። ከሌሎች በላይ እነርሱ እራሳቸውን በቅድስና መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት እንደሚጀምር ሁሉ ብዙ ኃላፊነት ከሰጣቸውም ሰዎች ብዙ ይጠብቃል። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ትልቅ ሥልጣን ካለው ከሌሎቹ መሪዎች ይበልጥ ቅዱስና እግዚዘብሔርን የሚያስከብር ሕይወት እንዲኖር ጥንቃቄ ሊወስድ ይገባዋል! (ኦሪት ዘኁልቁ 20፡ 12 ሙሴ ኃጢአት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር የፈረደበትን ፍርድ ይናገራል)። በዚህ ምክንያት ነው እግዚአብሔር በመሪነት ቦታ ላይ ያሉትን ሰዎች ኃጢአት ከሌሎች ሰዎች ኃጢአት ይበልጥ የማያዳግም ዓይነት ፍርድ የሚሰጠው።

ናዳብና አብድዩ ከሞቱ በኋላ ሙሴ ሁኔታዎቹን ሁሉ መቆጣጠር ጀመሩ። በመጀመሪያ የአሮን ዘመዶች ሬሳዎቹን ከመገናኛው ድንኳን አውጥተው ውጪ እንዲቀብሯቸው አዘዘ። ይህንንም ያደረገው የእሥራኤላውያንን ንጽሕና ለመጠበቅ ሲል ነው። ምክንያቱም የሞተ ነገር የነካ ማንኛውም ሰው ይረከስ ነበርና ነው። ሊቀ ካህኑ ሆነ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ካህን ሬሣ ሊነካ አይፈቀድለትም ነበር። ሁለተኛ፡- አሮንም ሆነ የተቀሩት ሁለት ልጆቹ ባህላዊ የሆነውን የልቅሶ ምልክት እንዳያሳዩ አዘዘ። ልብሳቸውን ሊቀዱ ወይም ፀጉራቸውን ሊያንጨፈርሩ አይችሉም ነበር። እንዲያለቅሱ ያልተፈቀደላቸው በዘመዶቻቸው ላይ የወረደውን የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚቃወሙ ዓይነት ሆኖ እንዳይቆጠርባቸው ነው። ምንም እንኳን የአሮን ልጆች ቢሆኑም የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛና ጻድቅ ፍርድ እንደሆነ መቀበል ነበረበት። ሦስተኛ፡- ሙሴ የእሥራኤል ሕዝብ ለሞቱት ልጆቹ እንደሚያለቅስ ለአሮንና ለልጆቹ አረጋገጠላቸው። በመጨረሻም ሙሴ አሮንና ልጆቹ ከመገናኛው ድንኳን ወጥተው የቀብሩን ሥነ-ሥርዓት እንዳይካፈሉ አዘዘ። አሮንና ልጆቹ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተለዩ ናቸው። እግዚአብሔርን ማገልገሉ፣ ዘመዳቸውን ከመቅበርም ሁሉ ይልቅ በጣም ዋነኛ የሆነ ነገር ነው። ከጓደኞቻችን ጋር ሆኖ ከቤተሰቦቻችን ጋር ካለን ግንኙነት ኃላፊነት ሁሉ በልጦ መታየት የሚገባው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቁ ነው።

37ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔርን መከተላችን እንዴት ከቤተሰባችን ኃላፊነት በልጦ መታየት እንደሚገባው ምሳሌ በመስጠት አስረዳ።

በኦሪት ዘሌዋውያን ለመጀመሪያና ለመጨረሻ እግዚአብሔር በቀጥታ አሮንን ይናገረዋል። ሥራውን በተመለከተ ትዕዛዝ ይሰጠዋል።

በመጀመሪያ፡- እግዚአብሔርን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በሚያገለግሉበት ጊዜ አሮንና ልጆቹ ማንኛውንም የሚያሰክር መጠጥ እንዳይጠጡ ያዛቸዋል። በዚህ ምክንያት ነው ብዙ ሰዎች ናዳብና አብድዩ ዕጣኑን ሲያቀርቡ ሰክረው ነበር የሚል ግምት

ያደረባቸው። ምንም እንኳን እግዚአብሔር የሚያሰክር እንዳይጠጡ ለሰዎች ትዕዛዝ ባይሰጥም መጽሐፍ ቅዱስ እስከ መስከር ደረጃ እንዳይደርሱ ትዕዛዝ ይሰጣል። እኛ በእግዚአብሔር እንጂ በመጠጡ ኃይል ልንመራ አይገባም! (ኤፌሶን 5፡ 18)። በብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜያዊ የሆነ ናዝራዊ ስለት ወይም ቃል ኪዳን ያደረጉ ሁሉ የቃል ኪዳን ጊዜያቸው እስኪያበቃ ድረስ መጠጥ መጠጣት አይፈቀድላቸውም ነበር። ስለዚህም መጠጥን በተመለከተ እግዚአብሔር የብዙ መጠጣትን መዘዝ ስለሚያውቀው ከወዲሁ ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል።

ሁለተኛ:- እግዚአብሔር አሮንን እንደ ካህን ሥራው ሁለት መልክ የያዘ እንደሆነ ይነግረዋል። መጀመሪያ ያልተቀደሰውን ከተቀደሰው የመለየት ኃላፊነት ነበረበት። ይህም ማለት በእግዚአብሔር ፊት የእስራኤል ሕዝብ ቅዱስ እንዲሆን ምን ማድረግ እንደነበረበት የሚወስነው እርሱ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኅብረት የሚያሻክርባቸውንም የሚገጽላቸው እርሱ እራሱ እንደሆነ ነው። እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ የሰጣቸው ሕግጋት የዕለት ተዕለት ኑሮን በተመለከተ የሚሰጡት ግልፅ የሆነ ሥርዓት ስላልነበራቸው የትኛው የአኗኗር ዓይነት ቅዱስ እንደሆነና የትኛው እንዳልሆነ የመወሰን መብት ያለው ካህኑ እንደሆነ ነው።

ሦስተኛ:- ሕግጋቱን የሚያስተምረው እራሱ ካህኑ ነው። የእግዚአብሔርን ሕግጋት የማሳወቅና ለምን እንደሚጠብቁት ሕጉን የመግለጽ ሐላፊነት የተሰጠው ለካህኑ ነው።

38ኛ ጥያቄ:- ይህ መሪዎች ዛሬ ካላቸው ሐላፊነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር በቀጥታ ከአሮን ጋር በመነጋገር አሁንም ሊቀ ካህኑ እርሱ እራሱ እንደሆነ ያረጋግጥለታል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በልጆቹ ላይ ቢፈርድም አሮን የፈጸመውን በደል ባለመናሩ እግዚአብሔርን ማገልገሉን እንዲቀጥልበት ተፈቅዶለታል። በኋላም ሙሴ ወደ አሮንና ወደ ተቀሩት ልጆቹ ይቀርብና የእነርሱ ፋንታ የሆነውን የመሥዋዕቱን ድርሻ የመብላት ኃላፊነት እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል። ከኅብረቱ መሥዋዕትና ከእህሉ ቁርባን የሚተርፈውን ድርሻቸውን እነርሱና ልጆቻቸው መብላት ነበረባቸው።

በኋላም ከመታዘዝ ይልቅ የአሮን ልጆች የሁለተኛውን የኃጢአት መሥዋዕት ድርሻቸውን እንዳቃጠሉ ሙሴ ሲሰማ ተናደደ። የአሮን መልስ ግን ሁለቱ ልጆቹ ስለሞቱበት እርሱና የቀሩት ሁለቱ ልጆቹ ሥጋውን ለመብላት ብቁ እንዳልሆኑ የሚገልጽ ይመስላል። በአንድ በሆነ መንገድ እነርሱም በኃጢአት የረከሱና ሥጋውን ከበሉ ደግሞ እግዚአብሔር የሚፈርድባቸው ሆኖ ተሰምቷቸው ይሆናል። ይህ መልሳቸው እግዚአብሔርንና ሙሴን አርክቷል። በዚህም ምክንያት ይህንን ትዕዛዝ ባለመጠበቃቸው እግዚአብሔር አልፈረደባቸውም።

እኛ እግዚአብሔር መሪዎች አድርጎ የመረጠን ሰዎች ከዚህ ምዕራፍ ትልቅ የማስጠንቀቂያ ትምህርት ልናገኝ ይገባል። በሰዎች ላይ ሥልጣን ካለን ትልቅ ኃላፊነት ተሸክመናል ማለት ነው። እግዚአብሔር ከእኛ ብዙ ይጠብቃል። ሕይወታችን ሌሎች እንዲከተሉት አርአያ ሊሆን ይገባዋል። ስለዚህም ከሌሎች ሰዎች ይበልጥ ጠንክረን

መሥራትና ቅዱሳን መሆን ይገባናል። ከሌሎች ይበልጥ ቅድስናችንን መጠበቅ አለብን። በተለይ አምልኮን በተመለከተ የማስመሰል ባህርይ በሕይወታችን ውስጥ እንዳይሰርፅ መጠንቀቅ ይኖርብናል። ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ከሌለን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው ልናደርግ አንችልም። በኃጢአት ከወደቅን ደግሞ ብዙ ጊዜ ሌሎችንም በኃጢአት እንዲወድቁ እናደርጋለን። በዚህ ምክንያት ነው ያዕቆብ ብዙ ሰዎች መምህራን እንዳይሆኑ የሚያዘው፤ (ያዕቆብ 3፡1)። ብዙ ከተሰጠው ሰው ብዙ እንደሚጠበቅ ክርስቶስ ይናገራል፤ (ሉቃስ 12፡47-48)። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ወንጌላዊ ሰባኪ መምህር የመዘምራን አባል ወዘተ. . . ከሆንክ ሕይወትህ የተቀደሰ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብሃል። ለሌሎች አርአያ ልትሆን ይገባሃል። ታዲያ መልካም አርአያ ነህን?

39ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር የፈረደባቸውን የአንዳንድ መሪዎች ስም ጻፍ።

ለ) የአንድ መሪ ኃጢአት ምን ዓይነት ችግር ነው በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የፈጠረው?

ሐ) የዚህን መሪ ታሪክ በመጠቀም ሌሎች መሪዎች ሕይወታቸውን በንጽሕና እንዲጠብቁ ማስጠንቀቂያ የምትሰጣቸው እንዴት ነው?

## አምስተኛ ቀን፡-

### ትምህርቱን ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) 1. ከኃጢአት መሥዋዕት ዛሬ ያለውን አምልኮ በተመለከተ የምናገኘው ትምህርት ምንድነው?

2. የክርስቶስ ሞት እንደ ኃጢአት መሥዋዕት የሆነው እንዴት ነው?

3. መሪ የሆኑ ሰዎች ኃጢአት ሌሎች ሰዎችን ሊጎዳ የሚችለው እንዴት ነው?

4. ይህ መሪ የሆንን ሰዎች በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት እንዳይኖር ሊያስጠነቅቀን የሚችለው እንዴት ነው?

ለ) 1. ከበደል መሥዋዕት ዛሬ ያለውን አምልኮ በተመለከተ ልናገኘው የምንችለው ትምህርት ምንድነው?

2. የሚሰርቁ ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ይቅርታ ብቻ ነው የሚጠይቁት ወይስ ይቅርታ ሲጠይቁ የሰረቁትንም ነገር ይመልሳሉ? ይህን በተመለከተ የበደል መሥዋዕት የሚሰጠው ትምህርት ምን ይመስልሃል?

3. ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ሊሰርቁ የሚችሉት እንዴት ነው?

ሐ) 1. አምስቱንም መሥዋዕት ከልሱ። የእያንዳንዱ መሥዋዕት ዋነኛ ዓላማ ምንድነው?

2. ስለ ክርስቶስ፥ ስለ እግዚአብሔር አምልኮ፥ ስለ ኃጢአተ ኛነታችን፥ ወዘተ... የሚያስተምሩን ነገር ምንድን ነው?

መ) 1. የካህኑን መለየት እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው መለየት ጋር አነፃፅር።

2. የአሮን መለየት መሪዎች ለመሪነት ሥራቸው እንዴት እንደሚለዩ የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

ሠ) የእግዚአብሔርን ፍርድ በተለይ በመሪዎች ላይ ጥብቅ መሆኑን ስንመለከት ከናዳብና ከአብድዩ ሞት የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አራት

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 11-13

## የመጀመሪያ ቀን

## የብሉይ ኪዳን ሕጋጋት መግቢያ

የብሉይ ኪዳንን ሕጋጋት ለመመርመር ከመነሣታችን በፊት በጣም አንገብጋቢ ጥያቄ ልንጠይቅ ይገባል። ዛሬ በአዲሱ ቃል ኪዳን ሥር ከሚኖሩ ክርስቲያኖች ጋር ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለው ሕግ የሚዛመደው እንዴት ነው? በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከስድስት መቶ በላይ ሕጋጋት ይገኛሉ። እነዚህ ሕጋጋት ብዙዎቹ ለእሥራኤል ሕዝብ የተሰጡት በሲና ተራራ ላይ ነው፤ የሚገኙትም በኦሪት ዘጸአት፥ በኦሪት ዘሌዋውያን፥ በኦሪት ዘኍልቁና በኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ ነው።

ክርስቲያኖች ከብሉይ ኪዳን ሕጋጋት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያጤኑት በተለያየ መንገድ ነው። አንዳንዶቹ ሕጋጋቱ ከእኛም ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም ብለው ያስባሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ልንጠብቃቸው የሚገቡ አንዳንድ ሕጋጋት አሉ ብለው ሌሎቹን ይተዉአቸዋል።

ለምሳሌ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳኑን የምግብ ሕግ በመጠበቅ ንጹህ የሆኑ እንስሳት የሚባሉትን ሥጋ ብቻ ነው የሚበሉት። የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶች ደግሞ ቅዳሜ የአምልኮ ጊዜ ነው በሚለው ሐሳብ ላይ ያተኩራሉ።

ሆኖም የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት በሙሉ የሚጠብቅ ቤተ ክርስቲያን የለም። ስለዚህም የትኞቹን ሕግጋት መጠበቅ እንዳለብን የትኞቹንስ ሕግጋት መተው እንዳለብን መወሰን ያስፈልገናል። ልንጠብቃቸው የሚያስፈልጉትን ሕግጋት የምንመርጠው ወይም የምንወስነው እንዴት ነው?

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዛሬ መጠበቅ ይኖርብናል ብለው የሚያምኗቸው ሌሎች ሕግጋት እንዳሉ አንድ የኦርቶዶክስ ክርስቲያንን ጠይቅ።

ለ) ቤተ ክርስቲያንህ የምትጠብቃቸው አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት የትኞቹ ናቸው? እነዚህን ሕግጋት የምትጠብቀውስ ለምንድን ነው?

በመጀመሪያ:- «ኪዳን ምንድን ነው?» የሚለውን ጥያቄ እንመልሳለን። ሁለት የተለያዩ ፓርቲዎችን (ቡድኖችን) የሚያጣምር ስምምነት ኪዳን በመባል ይታወቃል። ስለዚህም ብሉይ ኪዳን የእሥራኤልን ሕዝብና እግዚአብሔርን ያጣመረ ስምምነት ነው። እንዲያውም በሲና ተራራ ላይ የተገባውን ቃል ኪዳን ታላላቅ ነገሥታት በጥንት ጊዜ ቅኝ ግዛት አድርገው ከሚያስተዳድሯቸው አገሮች ጋር የሚያደርጉትን ቃል ኪዳን ይመስላል። የቅኝ ግዛት ገዥዎች የታላቁን ንጉሥ ትዕዛዞች እንደሚጠብቁ ቃለ መሐላ ይፈጽሙ ነበር። ንጉሡም ይህን ካደረጉ እንደሚጠብቃቸውና እንደሚመርቃቸው ቃል ይገባላቸው ነበር። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ እንደሚባርክና እንደሚጠብቅ ቃል ኪዳን ገብቷል። ሆኖም ይህ ቃል እንዲፈጸም የእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ሕግጋት መጠበቅ ነበረባቸው።

አዲስ ኪዳን ደግሞ አዲስ ስምምነት ነው። ኢየሱስ በመስቀል ሊሞት ሲል ለደቀ መዛሙርቱ «ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው ደሜ የሚፈጸም አዲስ ኪዳን ነው» ብሏቸዋል። ስለዚህም በእግዚአብሔርና በእሥራኤል መካከል በተደረገው የድሮው ስምምነት ሥር አይደለም የምንኖረው፤ እኛ የምንኖረው በክርስቶስ ደም በኩል በእኛና በእግዚአብሔር መካከል በተደረገው ስምምነት አማካኝነት ነው፤ (ዕብ.8)። በተጨማሪ ሮሜ 6፡14ን ተመልከት። የተወሰኑ የድሮው ሕግጋት በሆነ መንገድ ከአዲሱ ቃል ኪዳን ጋር ተያይዘው እስካልተጠቀሱ ድረስ ልንከተላቸው የሚገቡን ቀጥተኛ ሕግጋት አይደሉም።

2ኛ ጥያቄ:- የብሉይ ኪዳን ሕግጋት እኛን የሚመለከቱ ካልሆኑ ዓላማቸው ምንድን ነው? ገላ.3፡19-25 በመመልከት የተለያዩትን ዓላማዎች በዝርዝር ጻፍ።

አዲስ ኪዳን ስለ ሕግ የሚከተሉትን ነገሮች ይናገራል:-

በመጀመሪያ:- ሕግጋቱን በመጠበቁ በእግዚአብሔር ጻድቅ የሚሆን ማንም ሰው እንደሌለ እናውቃለን። በብሉይ ኪዳን እንኳ የሚያምኑ እሥራኤላውያን ይድኑ የነበረው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። እግዚአብሔር እሥራኤላውያን በትክክል ሕግጋቱን እንደማይጠብቁ ስለሚያውቅ ወደ ይቅርታ የሚመራቸውን የመሥዋዕት ሥርዓት አዘጋጀላቸው።

ሁለተኛ፡- ሕግ እሥራኤላውያንን ኃጢአተኛ እንዲሆኑ አሳይቷቸዋል። ሕግጋቱን በትክክል መጠበቅ እንደማይችሉ በመረዳታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ኃጢአተኛ እንደሆነ ምሕረትና ይቅርታም እንደሚያስፈልጋቸው ተገንዝበዋል፤ (ሮሜ 3፡20)።

ሦስተኛ፡- እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይህንን ሕግ የሰጠው ሕዝቡ በኃጢአት እየሰለጠነ እንዳይሄድ ለመግታት ነው። ጳውሎስ ሕጉን ከእሥር ቤት ጋር ያነፃፅረዋል። ይህም ሕጉ ሰዎች ታላላቅ ወንጀሎችን እንዳይፈጽሙ ወይም ወደ ተሳሳተ ሃይማኖት እንዳይገቡ ተብሎ የረቀቀ እንደሆነ ይገልፃል። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የሆነውን የደኅንነት መንገድ ከመክፈቱ በፊት በጊዜያዊነት የሚያገለግል ነበር።

አራተኛ፡- ጳውሎስ ሕግን እንደሞግዚት እንደሆነ ይገልፃል። ዓላማው በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊጠብቁት የሞከሩትንና ዛሬም እንዲህ የሚያደርጉትን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መምራት ነው። ሕጉ የተሰጠው እሥራኤላውያንን ለመሢሑ ምፅዓት ለማዘጋጀት ነው።

አምስተኛ፡- የብሉይ ኪዳን ሕግጋት አንዳንድ የእግዚአብሔርን ባህርያት ያሳዩናል። በውስጣቸው የእግዚአብሔር ቅድስና ጽድቅና ፍቅር ይታይባቸዋል።

በእነዚህ ላይ በመመሥረት እግዚአብሔር ሕግን የሰጠው ለሚጠብቁት ሰዎች ደኅንነትን ለመስጠት አይደለም። በምትኩ የተሰጣቸው ለጊዜው እሥራኤላውያንን በዙሪያቸው ከነበሩት አሕዛቦች ኃጢአት ለመጠበቅ ሲባል ነው። ኃጢአተኛነታቸውን በማሳየት አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው ይገልጽላቸዋል። በዚህም ለክርስቶስ ምፅዓት እሥራኤላውያንን እያዘጋጀ ነበር ማለቱ ነው። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለት ዓይነት ዐበይት ሕግጋት ነበሩ። በመጀመሪያ ለእሥራኤል ሕዝብና ለመሪዎቻቸው የተሰጡ የተለያዩ ወንጀሎችንና ቅጣቶቻቸውን ያቀፉ ሕግጋት ነበሩ። እነዚህን መንግሥታዊ ሕግጋት ወይም የፍትሐ ብሔር ሕግ ብለን ልንሰይማቸው እንችላለን። ሁለተኛው የሕግ ዓይነት እሥራኤላውያን እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንደሚገባቸውና እንዴት በሱ ፊት ንጹሕ ሆነው መቆም እንደሚችሉ የሚገልጽ ነበር። እንዴት እንደሚያመልኩ የት እንደሚያመልኩ ካህናቱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ወዘተ... የሚያብራሩ ነበሩ። ዛሬ እነዚህን ሕግጋት መጠበቅ አይኖርብንም።

ልንጠብቃቸው የሚገቡን አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ግን አሉ። እነዚህ ሕግጋት በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደገና የቀረቡ ናቸው። እነዚህን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ልንከፍላቸው እንችላለን፡- የመጀመሪያው የፍቅር ሕግ ነው።

3ኛ ጥያቄ፡- ኦሪት ዘዳግም 6፡5 እና ኦሪት ዘሌዋውያን 19፡18 አንብብ። በእነዚህ ሥፍራ የሚገኙት ሁለት የፍቅር ሕግጋት ምን ምንድን ናቸው? እነዚሆ ሕግጋት በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተደገመ በየትኛው ሥፍራ ነው?

በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም እግዚአብሔርን ሰውንም በሁለንተናችሁ (በሙሉ ልብ፥ ሐሳብ፥ ኃይልና ነፍስ) መውደድ አለባችሁ የሚል ትዕዛዝ እናገኛለን፤ (ሉቃስ 10፡25-37)።

ሁለተኛ ለየት ባለ መልክ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተደነገጉትን አሥርቱን ቃላት መጠበቅ ይኖርብናል። እነዚህን «የሞራል ሕግጋት የሚል ስያሜ ልንሰጣቸው እንችላለን።

4ኛ ጥያቄ፡- አሪት ዘጸአት 20፡1-17 ተመልከት። በዚህ ሥፍራ የሚገኙትን ሕግጋት በዝርዝር ጻፍ።

በአሥርቱ ቃላት ውስጥ ከሚገኙት ሕግጋት ውስጥ ለእኛ ቀጥተኛ የሆነ ተግባራዊ የማይሆነው ሰንበትን የማክበሩ ነገር ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰንበት ቅዳሜ ላይ ነበር እንጂ እሁድ አልነበረም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የአምልኮ ቀን የመምረጡ ጉዳይ ይህን ያህል አሳሳቢ አይደለም። ቅዳሜም እሁድም ክርስቲያኖች ለአምልኮ እንደሚሰበሰቡ እናነባለን። አብዛኞቹ ብዙ ክርስቲያኖች ዛሬ እሁድ የአምልኮ ጊዜ የሚኖራቸው ጌታ ኢየሱስ ከሙታን የተነሣበትን ቀን ለማክበር ሲሉ ነው። በዚህ ምክንያት ነው እሁድ «የጌታ ቀን» በመባል የሚታወቀው። እሁድን ሰንበት ብሎ መጥራቱ ትክክል አይደለም። ይህም ቢሆን በእሁድ አምልኳችን ላይ ተግባራዊ ልናደርጋቸው የሚገቡን አንዳንድ የሰንበት ሥርዓቶች አሉ።

ይህም ቢሆን አንድ የምንመልሰው ጥያቄ ይቀረናል። በአዲሱ ኪዳን ሥር የምንኖረው ሰዎች እነዚህን ሕግጋት ለምንድነው ማጥናት የሚያስፈልገን? በመጀመሪያ ምንም እንኳ የብሉይ ኪዳን ሕግ በቀጥታ ለእኛ ባይሰጥ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በሲና ተራራ ለእሥራኤላውያን የተሰጠውን ሕግ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ልናጠናውና ልንረዳው ይገባል።

ሁለተኛ፡- ሕጉ የእግዚአብሔርን ባህርይ ያንፀባርቃል። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ዛሬም ከእኛ ቅድስና እንደሚጠበቅብን ልንግር እንችላለን። የደኅንነትና የምሕረት መንገድ በማዘጋጀቱ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለንመለከት እንችላለን። እንደተመለከትነው የአዲሱ ኪዳን የደኅንነት መንገድ የብሉዩን ዓይነት ፈር የያዘ ነው።

ሦስተኛ፡- እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን በሰጣቸው ሕግጋት ውስጥ ዛሬ እኛ ተግባራዊ ልናደርጋቸው የምንችላቸው ብዙ ሥርዓቶች አሉ። ምንም እንኳ ብዙዎች ሕግጋት እኛን በቀጥታ የሚመለከቱ ባይሆንም በውስጣቸው ያለውን ሥርዓት ማጤንና ለእኛ እንዴት ዛሬ ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማሰላሰል ይኖርብናል። እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ሕግ የሰጣቸው ሲጠብቁት ለመመልከት ብቻ አልነበረም። ሕግጋቱ የተሰጡበት የራሳቸው የሆነ ምክንያት ነበራቸው ስለዚህም እንደ አንድ ሕዝብ በሰላም እንዲኖሩ ተብሎ የተሰጣቸው ሕግ ዛሬ እኛ አብረን እንድንኖር ሊረዳን ይችላል። ከሕግጋት የሰዎችን ጤንነት ስለሚነኩ ነገሮች ልናጠና እንችላለን። መንግሥታት ትክክለኛና ጤናማ የሆነ ሕብረተሰብ እንዲኖራቸው ካቀዱ ሊከተሉዋቸው የሚገቡ ሕግጋት አሉ። እነዚህን ሕግጋት ስታጠኑ ለምንድነው እግዚአብሔር እነዚህን ሕግጋት

የሰጣቸው? ብላችሁ ጠይቁ። እኔም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ተግባራዊ ልናደርገው የምንችለው ምን ዓይነት መመሪያ ልንግር እንችላለን?

## ሁለተኛ ቀን:- የኦሪት ዘሌዋውያን 11-12 ጥናት

5ኛ ጥያቄ:- በአምስት ክፍፍል እርኩስና ንጹሕ ተብለው የተዘረዘሩት እንስሳት ምን ምንድን ናቸው?

6ኛ ጥያቄ:- አንድ እንስሳ (አጥቢ የሆነ) የሚበላ እንዲሆን ማሟላት ያለበት ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

7ኛ ጥያቄ:- አንድ ዓሣ የሚበላ እንዲሆን ማሟላት የሚገባው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

8ኛ ጥያቄ:- ሕዝቡ እንዲበሉ የተፈቀደላቸው ምን ዓይነት ነፍሳት ናቸው?

9ኛ ጥያቄ:- እርኩስ የሆነውን እንስሳ በድን የነካ ሰው ለመንጻት ምን ማድረግ ነበረበት?

10ኛ ጥያቄ:- በድኑ የነካቸው ነገሮች ምን መደረግ ነበረባቸው?

11ኛ ጥያቄ:- እሥራኤላውያን የትኛውን የእግዚአብሔር ባህርይ ነበር መከተል የነበረባቸው? (11:43-45)

12ኛ ጥያቄ:- ገና የወለደች መጫት ለመንጻት ስትል ምን ማድረግ ነበረባት?

ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 11-15 ያለው የሚያተኩረው እሥራኤላውያንን በልማድ እርኩስ ወይም እርኩስ የሚያደርጉት ነገሮች ላይ ነው። ዕብራዊው በእግዚአብሔር ዓይን «ቅዱስ» የሚሆነው ሕይወቱ በሞላ ተገምግሞ ነው። ግምገማው የሞራል ኃጢአቶችን፥ አበላላቸውን፥ ልጅ አስተዳደጋቸውን፥ አለባበሳቸውን፥ ወዘተ.. የሚያካትት ነው። በሕይወታቸው ውስጥ በማንኛውም ዓይነት መንገድ እንዳይረከሱ እግዚአብሔር አዝዞአቸዋል። በኦሪት ዘሌዋውያን 10:10 ላይ ካህኑ እርኩስ የሆነውን ነገር እርኩስ ካልሆነው የመለየት ሐላፊነት እንደነበረበት የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያበላሸውንና የማያበላሸውን ነገር ለይቶ የማወቅ ሐላፊነት እንደነበረበት ተመልክተናል። ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕ. 11-15 ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብና ካህናቱ ሊያረክሷቸው የሚችሏቸውን ነገሮች ለይተው የሚያውቁበትን መመሪያዎች ያካተተ ነው።

ምሁራን ብዙ ጊዜ ለምን እግዚአብሔር ይህን የረከሰና ያልረከሰ የሚል ሕግ ለሕዝቡ እንደሰጠ ይገረማሉ። አራት ዋና ዋና አስተሳሰቦች ግን አሉ። እነዚህም አንደኛ:- አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ሕግጋትን ፈጥሮ ሕዝቡ እንዲጠብቁት የማድረግ መብት አለው። ይላሉ። ስለዚህም እግዚአብሔር ይህን ሕግ የሰጠው ሕዝቡ ትዕዛዛቱን እንደሚጠብቅ ለመፈተን ነው።

ሁለተኛ:- ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔር እነዚህን ሕግጋት የሰጠው ለሃይማኖት ብሎ ነው ይላሉ። የረከሱት እንስሳዎች ብዙ ጊዜ በጣዖት አምልኮ ወይም በአረመኔዎች ዘንድ

ጥቅም ያላቸው ስለ ነበሩ ነው የተተዉት። እግዚአብሔር የአይሁዳውያን የአምልኮ ሥርዓት ንጹህ እንዲሆንና በአጎራባቾቻቸው አረመኔ ሕዝቦች አምልኮ አማካኝነት የተበከለ እንዳይሆን ይፈልግ ነበር። እንደ አንበሳ ያሉ እንስሳት በአይሁዳውያንና በአረመኔዎች ዘንድ ጥቅም ነበራቸው።

ሦስተኛ፡- ሌሎች ደግሞ እነዚህ ሕግጋት የተሰጡት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጤንነት ለመጠበቅ ሲባል ነው ይላሉ። እርኩስ የሆኑት እንስሳት ብዙ ጊዜ በሽታ ያላቸው ሲሆኑ የተቀሩት ንፁህ እንስሳት ደግሞ ለሕዝቡ ጤንነት ጠቃሚ ናቸው ይላሉ ሰዎቹ። ምንም እንኳ እሥራኤላውያን ባያውቁትም እግዚአብሔር ከበሽታዎች ሊጠብቃቸው በመፈለጉ ምክንያት ይህን ሕግ ሰጠን ይላሉ።

አራተኛ፡- እነዚህ ትዕዛዛት የተሰጡት የእሥራኤል ሕዝቦች ሃይማኖት ለየት ያለ እንደሆነ ለማሳየት ብቻ ሳይሆን አኗኗራቸውም ጭምር ለየት እንደሚል ለማሳየት ነው። ለእግዚአብሔር የሚሰጡት አክብሮት በሕይወታቸው ውስጥ በሙላት መታየት ይኖርበታል። ይህ ሲሆን በአካባቢያቸው ያሉት ያልዳኑት ሰዎች ሕይወታቸውን ተመልክተው የተለዩ ሕዝቦች እንደሆኑ ሊረዱ ይችላሉ።

አምስተኛ፡- አንዳንዶች እርኩስ ያልሆኑና የሆኑት እንስሳት የሚወክሉት ሌሎች ነገሮችን ነው ይላሉ። እርኩስ ያልሆኑት እንስሳት የእግዚአብሔር ሕዝብን ባህርይ የሚያመለክቱ ናቸው (ለምሳሌ፡- የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከአሳማ ጋር ሳይሆን ከበግ ጋር ያነፃፅራቸዋል)። እርኩስ የሆኑት እንስሳት ያልዳኑት ሰዎችን ልማዶች የሚያመለክቱ ናቸው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ የምግብ ሕግ የለም። ይህም እንዴት አድርጎ እርኩስና ያልረከሱ ተብለው የተለዩትን አሕዛብንና አይሁዳውያንን አንድ እንዳደረገ የሚያመለክት ነው።

በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 11 ላይ እግዚአብሔር እሥራኤላውያን ሊበሉት የሚችሉትን የሥጋ ዓይነት ይገልጽላቸዋል። በመጀመሪያ ሊበሉ የሚችሏቸውን እንስሳት ያሳያቸዋል። በመቀጠልም ስለ ዓሳዎች፥ ስለ አዕዋፎች፥ ስለሚበሩ ነፍሳትና በሆዳቸው የሚሳቡ እንስሳት ገለጻ ይሰጣቸዋል። ከእነዚህ እንስሳት መካከል አንዳንዶቹ ለኖህ ይታወቁ ነበሩ ምክንያቱም እርኩስ የሆኑና ያልሆኑትን እንስሳት ከውሃው ሙላት በፊት ያውቅ ነበርና ነው። ሆኖም በኦሪት ዘሌዋውያን ሰፋ ያለ ገለፃ ነው የምንመለከተው።

1. እንስሳት፡- (11፡1-8) እሥራኤላውያን የሚበሏቸው እንስሳት ሁለት ዋና ዋና ባህሪዎች ሊኖሯቸው ይገባል። አንደኛ የሚያመሰኳ እንስሳ መሆን አለበት። ሁለተኛ ሰኮናው የተሰነጠቀ ሊሆን ይገባዋል። እነዚህን ሁለት ነገሮች ያላሟላ እንስሳ አይበላም ነበር። ለምሳሌ እነዚህን ባህሪያት የማያሟሉ ሦስት እንስሳት ተጠቅሰዋል። ግመልና ጥንቸል የተሰነጠቀ ሰኮና ስለሌላቸው አሣማ ደግሞ የተሰነጠቀ ሰኮና አለው፥ ነገር ግን ስለማያመሰኳ፥ ሁሉም የማይበሉ ናቸው።

2. በውሃ ውስጥ የሚኖሩ:- (11:9-12) በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ሊበሉ የሚችሉት ሁለት ነገሮችን ካሟሉ ነው። አንደኛው ቅርፊት ሊኖራቸው ይገባል፤ ሁለተኛው ደግሞ ክንፍ ሊኖራቸው ይገባል። ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው የማይበሉ ናቸው።

3. ወፎች:- (11:13-19) በውኃ ውስጥ እንደሚኖሩትና እንደ እንስሳት አዕዋፍ የተለየ ማሟላት የነበረባቸው ነገር የለም። እርኩስ ወይም ንጹሕ የሚያሰኛቸው ምንም የተሰጠ ባህርይ የለም። በምትኩ እግዚአብሔር እርኩስ የሆኑትን ወፎች ዝርዝር ሰጥቷል። ከዝርዝሩ እንደምንመለከተው እርኩስ የሆኑት ወፎች የሞቱ እንስሳትን (በድን) የሚበሉ ናቸው።

4. የሚበሩ እንስሳት:- (11:20-23) በምድር ላይ የሚዘሉባቸው ሁለት ልዩ እግሮች የሌሏቸው እንስሳት አይበሉም ነበር። እንደ አንበጣ ያሉ ሁለት ልዩ እግሮች ያሏቸው እንስሳት ግን ይበሉ ነበር።

5. በመዳህ የሚንቀሳቀሱ:- (11:29-30) በመሬት ላይ የሚድህ ማንኛውም እንስሳ ለመብል አይሆንም ነበር።

አሪት ዘሌዋውያን 11:24-43 አንድ ሰው ከረከሰ እንዴት አድርጎ እንደሚነጻ የሚገልጹ ሕግጋትን ያካተተ ነው። እርኩስ የሆነውን እንስሳ የበላ ሰው ብቻ ሳይሆን፥ እርኩስ የሆነውን እንስሳ በድን የነካ ሁሉ ነበር የሚረከሰው። ሰዎች ሕይወት ያለውን የረከሰ እንስሳ ቢነኩ አይረከሱም የሚረከሱት በድኑን ከነኩ ብቻ ነው። ንጹሕ የሆኑ እንስሳት ሆነው በተፈጥሮ ምክንያት ያልሞቱን እንስሳዎች በድንም ከነኩ ይረከሳሉ። የሚቀጥለው ዝርዝር እርኩስ የሆነው ነገር እንዴት ንጹሕ እንደሚሆን ይገልፃል።

አንደኛ:- አንድ ሰው እርኩስ የሆነ በድን ከነካ በመጀመሪያ ልብሱን ማጠብ አለበት። ለተቀረው ጊዜ በዚያው ቀን እርኩስ ሆኖ ነበር የሚውለው የሚቀጥለው ቀን የሚጀምረው ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ነው ስለሚሉ አይሁዶች ይህ ሰዓት ሲደርስ ሰውዬው ንጹሕ ይሆናል። እርኩስ በሆነበት ጊዜ ውስጥ ሊሠራ ይችላል፥ ወዘተ... ነገር ግን ወደ መገናኛው ድንኳን ሄዶ እግዚአብሔርን ሊያመልክ አይችልም። ከሄደ እግዚአብሔር የሚመለክበትን ሥፍራ ያረክሳል ማለት ነው።

ሁለተኛ:- እርኩስ የሆነው የእንስሳ በድን በእንጨት በልብስ በቁርበት ወዘተ... ከተነካ ያ የነካው ነገር እርኩስ ነው፤ እስከምሽቱም ድረስ በውሃ ውስጥ መዘፍዘፍ ነበረበት፤ በኋላም ንጹሕ ይሆናል።

ሦስተኛ:- በድኑ ከሸክላ በተሠራ ዕቃ ላይ፥ በተዘጋጀ ምግብ ላይ፥ በሚጠጣ ውሃ ላይ ከወደቀ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች በሙሉ መውደምና መጥፋት ነበረባቸው።

አራተኛ:- ንጹሐን የሆኑ (እንደ ምንጭ) ነገሮች ላይ በድኑ ቢወድቅ አይረከስም፥ ምክንያቱም እራሳቸው በራሳቸው ስለሚፀዱ ነው።

እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ከሞተው እንስሳ ላይ በሽታ የሆነ ነገር በመኖሪያቸው አካባቢ እንዳይዛመት የሚያደርጉ ናቸው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር እነዚህን ሕግጋት

የሰጠበት ምክንያቶች ባናውቅም በፍቅር በመነሣሣት ነው ይህን የመሰለ ሕግ የሰጣቸው እንጂ ዝም ብለው እንዲጠብቁአቸው አይደለም። ዛሬም እንኳ ሳይንቲስቶች ከሞቱ ነገሮች በሽታዎች እንደሚዛመቱ ያስተምራሉ።

አሪት ዘሌዋውያን 11፡43-45 እግዚአብሔር እነዚህን ሕግጋት የሰጠበትን ዋነኛ ምክንያት ይገልጻል። እነዚህ ሕግጋት የሕዝቡን ልዩ መሆን የሚያሳዩ ናቸው። በአካባቢያቸው ካሉ ያልዳኑ ሰዎች ልምምድ እራሳቸውን ሲለዩ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ብቻ ሳይሆን በሁለንተናቸው ሕያው የሆነውን አምላክ እንደሚያከብሩ ሲያሳዩ፥ እራሳቸውን የሚመሩት በእግዚአብሔር ባህርይ መሠረት ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ እነርሱም ቅዱሳን ሆነው ነበር። ከግብፅ ያወጣቸው እግዚአብሔር ነው፥ የመረጣቸውም እግዚአብሔር ነው። ስለዚህም የእርሱ ቤተሰብ ለመሆናቸው እርሱን በመምሰል ሊገልጹት ይገባል።

13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የእግዚአብሔር ቤተሰብ ወገን መሆናችንን የምንገልጸው እንዴት ነው?

ለ) እ የምንጠብቃቸው አንዳንድ መንፈሳዊ ሕግጋት ምንድን ናቸው?

ሐ) ሊታዩ የሚችሉ አማኝ ካልሆኑ ሰዎች የተለየ የምናደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

መ) 1ኛቆሮ.10፡31 በሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ የምናደርገው እንዴት ነው?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እነዚህ የምግብ ሕግጋት ትልቅ ክርክርን አስከትለዋል። አሕዛብና አይሁዳውያን አብረው ኅብረት እንዳያደርጉ ይከለክላቸው የነበረው ይህ የምግብ ሕግ ነበር፤ (ገላትያ 2፡11-16)። ኢየሱስ ወደ ሰው ሆድ የሚገባ ነገር እንደማያረክስ ያስተምር ነበር። የሰውን ሕይወት የሚያበላሸው ከልቡ ውስጥ የሚወጣው ክፉ ነገር ነው፥ (ማቴ.15፡10-20)። በኋላም ላይ እግዚአብሔር የሠራው ነገር በሙሉ ንጹሕ እንደሆነ፥ መብላትም እንደሚችል ለጴጥሮስ አሳይቶታል። ሁሉም ሰው በእርሱ ዐይን እኩል እንደሆነና በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት መነሻ በማድረግ ሰዎችን እንደሚቀበልም አሳይቷል፤ (የሐዋ.10፡11-16)። ለእኛ በአዲስ ኪዳን ሥር ለምንተዳደረው ይህን ብሉ ያን አትብሉ የሚል ሕግ የለም። የምንበላው ምግብ የሚወሰነው በባህላችንና በፍላጎታችን ብቻ ነው።

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 12-15 የሚያተኩረው የእሥራኤላውያንን ሰውነት በሚያረክሱ ነገሮች ላይ ነው። አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 12 በመውለድ ስለሚመጣ መርከስ የሚያወሳ አጭር ምዕራፍ ነው። መሥዋዕት ከማስፈለጉና ከእርከሰናው ጊዜ ርዝመት አንጻር ስንመለከተው ይህ እርከሰና በድን ነክቶ ከሚመጣው እርከሰና ከበድ ያለ ይመስላል። አሁንም እግዚአብሔር እነዚህን ትዕዛዞች የሰጠበትን ምክንያት አናውቅም።

ልጆች መውለድን እግዚአብሔር ይቃወማል የሚል ጽሑፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝም። አዳምና ሔዋንን ልጆች ውለዱ፥ ብዙ ተባዙ ምድርንምሙሏት ብሎ አዟቸዋል። ልጆች ከእግዚአብሔር ለወላጆች የሚሰጡ በረከቶች እንደሆኑ ይናገራል ቃሉ። ስለዚህ ሴትዮዋ ስትወልድ ከሚወጣት ደምና ፈሳሽ ተነሥቶ ይመስላል ይህን ትዕዛዝ የደነገገው። ይህንን የምንለው ሴቶች በወር አበባቸው ጊዜ እንኳ እርኩስ እንደሚሆኑ ስለምናውቅ ነው።

እንዲት ሴት ወንድ ልጅ ከወለደች ለሰባት ቀን እርኩስ ትሆን ነበር። በስምንተኛው ቀን ልጁን ማስገረዝ ነበረባት። እንደምታስታውሰው መገረዝ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለቃል ኪዳኑ ሕዝብ እንደምልክት የሰጠው ሥርዓት ነው። መገረዝ ወንድ ልጅ ከቃል ኪዳኑ ሕዝብ መካከል እንደሆነ የሚቆጠር ሥርዓት ነው፤ (በሉቃስ 2፡21 ላይ ማርያም ኢየሱስን እንዳስገረዘች ተጠቅሷል)። ዶክተሮችም በስምንተኛው ቀን መገረዙ ጥሩ ጊዜ መሆኑን ይገልጻሉ። በስምንተኛው ቀን ሕመሙም እስከዚህም ነው፥ ብዙም ደም አይፈሰውም የሕፃኑም ሰውነት ቁስሉን ለማስታመም በቂ ጊዜ ያገኛል። አንዳንድ ዶክተሮች ካለመገረዝ መገረዙ ለጤንነት ጥሩ እንደሆነም ይናገራሉ። እስከ ሠላሳ ሦስት ቀን የመንጻትዋ ቀን እስከሚፈጸም ድረስ ሴትዮዋ ወደ ቤተ መቅደስ ገብታ ማምለክ አትችልም ነበር። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በሕፃንነት ጊዜ በማጥመቅ ልጁን ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ አስገባን ይላሉ። ይህ ነገር በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደሚገባ የሚያስረዳው ትምህርት በደንብ ሳይገባቸው በመቅረቱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሕፃንነቱ የተጠመቀ ሰው ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ ይገባል የሚል ጽሑፍ የለም። ይህ የሚሆነው አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ሲቀበል ብቻ ነው።

14ኛ ጥያቄ፡- ሕፃናትን የሚያጠምቁ የአንድ ወይም የሁለት አብያተ ክርስቲያናት ስም ዘርዝር። ከዚያ ቤተ ክርስቲያን አባል ጋር ተገናኝና ለምን ሕፃናትን እንደሚያጠምቁ ጠይቅ።

የተወለደችው ሴት ከሆነች የመገረዝ ሥርዓት የለውም ነበር። በማናውቀው ምክንያት ሴትዮዋ በዚህ ጊዜ ለሁለት ሳምንት ያህል ነበር እርኩስ የምትሆነው። ይህ ወንድ ልጅ ስትወልድ የምትረከሰው ቀን ዕጥፍ ነው።

የመንጻትዋ ወራትም ካለቀ በኋላ ወደ መገናኛው ድንኳን ሄዳ ሁለት መሥዋዕቶችን ታቀርብ ነበር። የመጀመሪያው የአንድ ዓመት ጠቦት የሚቃጠል መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል፤ ይህም መሥዋዕት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንደገና እንዲኖራት ያደርጋል። ሁለተኛው፤ ዋኖስ ወይም እርግብ ለኃጢአት መሥዋዕት ታቀርባለች። ይህም ከእርከስናው የሚያነጻት ነው። የእነዚህ መሥዋዕቶች አቀራረብ ቅደም ተከተል ከበፊተኛው ለየት ያለ ነው። (ያለፉትን ትምህርቶች ተመልከቱ) እናትየዋ በጣም ደሃ ከሆነች ለሚቃጠለውና ለኃጢአቱ ሁለት እርግብ ወይም ዋኖስ ማምጣት ትችላለች። (በሉቃስ 2፡22-24 ማሪያም ይህንን ሕግ ጠብቃለች። ጠቦት ለማምጣት ባለመቻልዋ ነው፤ ሁለት የእርግብ ጫጩቶች ያመጣችው። ይህም ደሃ እንደነበረች ይገልጻል)።

15ኛ ጥያቄ:- አንድ የኦርቶዶክስ አማኝን፥ ወንድ ልጅ መቼ እንደሚገረዝና እንደሚጠመቅ፥ ሴት ልጅ መቼ እንደምትጠመቅ ጠይቅ። ይህ የሆነበትንም ምክንያት የሚያውቅ ከሆነ ጠይቀው።

## ሦስተኛ ቀን:-

የኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 13-14 ጥናት

16ኛ ጥያቄ:- በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ እላያቸው ላይ ምልክት ከተገኘ የሚረከሱት ምንና ምንድን ናቸው?

17ኛ ጥያቄ:- ምልክቱ ሰውዬውን እንደሚያረክሰው ወይም እንደማ ያረክሰው ውሳኔውን መስጠት የሚገባው ማን ነው?

18ኛ ጥያቄ:- በሰዎች ላይ ሊወጡ የሚችሉ ምን ዓይነት ምልክቶች ናቸው የተዘረዘሩት?

19ኛ ጥያቄ:- አንድ ሰው ከበድ ያለ በሽታ ኖሮበት በካህኑ እርኩስ ተብሎ ከተወገዘ በኋላ ምን ማድረግ ነበረበት? (13፡45-46)።

20ኛ ጥያቄ:- እርኩስ የሆነ ሰው በነፃ ወደ እሥራኤላውያን መኖሪያ ሠፈር ገብቶ ለመኖር ምን ማድረግ ነበረበት?

21ኛ ጥያቄ:- በግድግዳዎቹ ላይ የሆኑ ነገሮች በቅለው ፍጹም ቢጠረጉ የማይጸዱ ቢሆኑ ምን መደረግ ይቻላል?

ኦሪት ዘሌዋውያን 13-14 የተለየ ምልክት ስላላቸው ሰዎች ወይም ዕቃዎች ነው የሚያወሳው። ሰው ከሆነ ሊድን የማይችል ቁስል፥ ሽፍታ፥ ቡግንጅ፥ ቃጠሎ ወይም በጭንቅላቱ ላይ ፍንክች የመሰለ ነገር ሊሆን ይችላል። እንደ ጨርቅ ወይም የቤት ግድግዳ ያለ ነገር ከሆነ እንደ የፎሮፎር ቋቁቻ ዓይነት ነገር ሊሆን ይችላል። እነዚህ ነገሮች ያልተለመዱና ሊተላለፉ የሚችሉ ነገሮች ናቸው። ስለዚህም እግዚአብሔር በሽታ የሚያመጡትን ነገሮች የመቆጣጠር ሐላፊነት የሰጠው ለካህኑ ነው። ካህኑም በሽታ ካለው እርኩስ ይለዋል፥ ምንም ዓይነት በሽታ ከሌለው ደግሞ አይቶ ንፁህ ነው ማለት አለበት።

እነዚህ ያልተለመዱ ምልክቶች በአጠቃላይ «ለምፅ» የሚል ትርጓሜ ያለው የዕብራይስጥ ስያሜ ነው ያላቸው። በሰለጠነው ዓለም ለምፅ የሚል ስያሜ የተሰጠው አንድ በሽታ አለ። ሆኖም በዕብራይስጥ ይህን ቃል በቆዳ ላይ ወይም በሌሎች ነገሮች ያለን ምልክት ለመሰየሚያ ይጠቀምበታል። እዚህ ላይ ዛሬ የሚታየውን ለምፅ ለመጥቀስ የተፈለገ አይመስለንም ምክንያቱም ብዙ ምሁራን በጥንት ጊዜ የለምፅ በሽታ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተራባው ያህል እንዳልተስፋፋ ይገልፃሉ።

1. የቆዳ በሽታ ያለበትን ሰው ለመመርመር የተሰጠ መመሪያ፤ (13፡1-46)

በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 13 ላይ በቆዳ ላይ ሊወጡ የሚችሉ በሽታዎች ዝርዝር ይገኛል። ካህኑም እነዚህን በሽታዎች ለይቶ ካወቀ በኋላ አንድን ሰው እርኩስ ወይም

ንጹሕ የሚልበት መመሪያም ጭምር ተሰጥቶታል። በሽታው አደገኛ መሆኑን ካህኑን ሊያሳውቁት የሚችሉ ሁለት መመሪያዎች ነበሩ። አንደኛው፥ ካህኑ በቁስሉ ላይ የበቀለውን ጠጉር ይመለከታል። እሥራኤላውያን በሰውነታቸው ላይ ጥቁር ፀጉር ብቻ ነው ያላቸው ስለዚህ ይህ ፀጉር በድንገት ነጭ ከሆነ በሽታው አደገኛ ነው ማለት ነው። ሁለተኛው፥ ካህኑ የደዌውን ጥልቀት ይመለከት ነበር። በጣም የጠለቀ ካልሆነ አደገኛ አይደለም። በጣም የጠለቀ ከሆነ ግን በሽታው አደገኛ ነው። ሰውዬውም እርኩስ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ምልክቶች አንድ ሰው ካሉበት እርኩስ ነበር። ይህንንም ሰው እሥራኤላውያን ከሚኖሩበት ሠፈር ያስወጡታል። ይህም የሚደረገው የሰውዬው በሽታ ወደሌሎች እንዳይዛመት ነው።

በሽታው አደገኛ ስለመሆኑ ካህኑ ጥርጣሬ ከገባው ሰውዬውን ለይተው ለሳምንት ወይም ለሁለት ሳምንት ያህል ያስቀምጡታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ደዌው ከዳነ ወይም ካልሰፋ ካህኑ ሰውዬውን ንጹህ ነህ ይለዋል። በሽተኛውም ልብሶቹን አጥቦ ከሌላው የእሥራኤል ኅብረተሰብ ጋር ይቀላቀላል። ደዌው ከሰፋና የባሰ ከመረቀዘ ግን ካህኑ ሰውዬውን እርኩስ ነህ ይለዋል።

ካህኑ እርኩስ ነህ እርኩስ አይደለህም ብሎ ለመወሰን እንዲቀለው የተለያዩ በሽታዎች ተሰይመውለታል:-

ሀ) ችፍታ:- ችፍታው በሰውነቱ ላይ በሙሉ ከተዛመተ ሰውዬው ንጹህ ነው ችፍታው የሚመረቅዝና ጥልቀት ያለው ከሆነ ግን ህመምተኛው እርኩስ ነበር።

ለ) እንደ ቡግንጅ ያሉት ቁስሎች:- የሰውዬው ደዌ ነጭ ሆኖ ከቀረ ካህኑ ይመረምረዋል። በዚያ አካባቢ ያለው ፀጉር ካነጣና ደዌው ጥልቀት ካለው ሰውዬው እርኩስ ነው። ፀጉሩና ቁስሉ ደህና ከሆኑ ንጹሕ ነው።

ሐ) ቃጠሎ:- አንድ ሰው ተቃጥሎ የፀጉሩና የቆዳው መልክ ቢቀየር እርኩስ ይሆናል። ለተወሰነ ጊዜ ከተገለለ በኋላ ደዌው ካልሰፋ ሰውዬው ንጹሕ ይሆናል።

መ) በራሱ ላይ ደዌ ያለበት:- አንድ ሰው በራሱ ላይ በደንብ የሚታይ ጥልቀት ያለው ደዌ ካለው እርኩስ ነው። ለተወሰነ ጊዜ ከተገለለ በኋላ ደዌው ካልሰፋ ሰውዬው ንጹሕ ይሆናል።

ሠ) ቆዳቸው ነጭ ጠቃጠቆ ያለበት:- ይህ ጠቃጠቆ ደብዘዝ ያለ መልክ ካለው በሽተኛው እርኩስ ይሆናል።

ረ) ፀጉራቸው የሚረገፍባቸው ሰዎች:- ቀላ ያለ ደዌ ወይም ቁስል ከሌለበት ሰውዬው ንጹሕ ነው።

ዶክተሮችና ዘመናዊ መድኃኒቶች ባልኖሩበት ወቅት፥ እግዚአብሔር የሕዝቦቹ ጤንነት የተጠበቀ እንዲሆን በቅድሚያ እነዚህን ማስጠንቀቂያዎች ሰጥቷል። እርኩስ ተብለው የሚለዩት ሰዎች ከበድ ያለ ችግር ያጋጥማቸው ነበር። ልብሶቻቸውን ይቀዱሉ፥ ፀጉራቸውን አይቆረጡም፥ ፊታቸውንም በባህሉ መሠረት ለለቅሶ ፊታቸውን እንደሚሸፍኑት ዓይነት አድርገው ይሸፍናሉ። በሰዎች ዓይን እነዚህ ሰዎች እንደ ሞተ

ሰው ነበር የሚታዩት ምክንያቱም ከሚወዷቸው ጋር እንኳን መገናኘት አይችሉምና ነው። በድንገት አንድ ንጹሕ ሰው በእነርሱ እንዳይበከል «ርኩስ ርኩስ » እያሉ በመጮህ ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ።

ምንም እንኳ ከኅብረተሰቡ የተገለሉ ቢሆኑም እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው ተስፋ ያደርጉ ነበር። ከደዌያቸው ከነጹ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እንደገና ኅብረት ይኖራቸዋል።

ወደ አዲስ ኪዳን ዞር ስንል ደግሞ ወደ ኢየሱስ መጥተው ፈውስን የሚያገኙት ብዙ ጊዜ ለምፃሞች መሆናቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። የሕይወታቸውን ጉስቁልና በመመልከት ልቡ ያዝንላቸው ነበር። ባለፉት ዓመታት ብዙ ሚስዮናውያን እንደ ለምፃሞች ከኅብረተሰቡ ለተገለሉት ሰዎች ኀዘኔታ ይሰማቸው ነበር። ክርስቲያኖች የፍቅራቸውን ጥልቀት ከኅብረተሰቡ የተገለሉትን ሰዎች በማፍቀር ሊገልጹት ይችላሉ።

22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በሥራቸው፥ በበሽታቸው፥ በአካለ ጎዶሎነታቸው ምክንያት ከኅብረተሰቡ የተገለሉ የአንዳንድ ሰዎች ስም ዘርዝር።

ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ከኅብረተሰቡ ለተገለሉት ሰዎች እጇን የምትዘረጋው እንዴት ነው?

ሐ) ይህን ዓይነት ተግባር የማትፈጽም ከሆነ ቤተ ክርስቲያንህ በምን ዓይነት መንገድ ነው የኢየሱስን ምሳሌነት ተጠቅመህ እነዚህን የተገለሉ ሰዎች ልትረዳ የምትችለው?

2. በተለያዩ ዕቃዎች ላይ የሚዛመቱ በሽታዎችን ለመመርመር የሚያስችሉ መመሪያዎች፤ (13፥47-59)

ያልተጠበቀ ምልክት በአንድ በቤት ግድግዳ ላይ በአጎዛ ላይ ወይም በጨርቅ ላይ ቢታይ ካህኑ ልክ እንደ ቆዳ በሽታው ጊዜ እርኩስነቱን ለመናገር ተመሳሳይ እርምጃዎችን ይወስዳል። በመጀመሪያ ካህኑ ምልክቱን በደንብ ይመለከታል። የሚሰፋ ዓይነት ነገር መስሎ ከታየው ካህኑ ለአንድ ሳምንት ያህል ለማረጋገጥ ይዘጋበታል። የሚሰፋ ሆኖ ከተገኘ ዕቃው ይቃጠል ነበር። የማይሰፋ ከሆነ ግን ታጥቦ እንደገና ለሳምንት ያህል ይዘጋበት ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ ደግሞ ምልክቱ ሙሉ በሙሉ ካልጠፋ ዕቃው እንደ እርኩስ ነገር ተቆጥሮ ይቃጠል ነበር። ምልክቱ ከጠፋ ዕቃው እንደ ንጹህ ይቆጠራል።

23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በጨርቅ ላይ ወይም በቆዳ ላይ እንደዚህ ዓይነት ምልክት አጋጥሞህ ያውቃል?

ለ) ምልክቱን ለማጥፋት ምን ተጠቀምክ?

ምንም እንኳ ዛሬ እንደ ቋቁቻ የመሳሰሉትን ነገሮች የሚያጠፋ መድኃኒት ቢኖርም በብሉይ ኪዳን ዘመን ግን የለም ነበር። አንድ ቋቁቻ ልብስ ላይ ከወጣ ወደ ቤቱ ሁሉ መዛመት ብቻ ሳይሆን ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት በቀላሉ ሊዛመት ይችላል። ስለዚህም እግዚአብሔር እነዚህን ማስጠንቀቂያዎች የሰጠው እሥራኤሎችን ለመጨቆን

ሳይሆን እነርሱ እንዲጠበቁና እንዲጠቀሙ ነው። እግዚአብሔር በእርግጥ የምሕረት አምላክ ነው፥ ፍላጎቶቻችንንም በሙሉ ያሟላልናል።

24ኛ ጥያቄ:- ለእኛ ጥቅምና ጥበቃ ተብለው ዛሬ እንድንጠብቃቸው በእግዚአብሔር የተደነገጉ አንዳንድ ሕጎችን ልትሰይም ትችላለህ?

25ኛ ጥያቄ:- ካለፈው ትምህርት፥ ጤንነታችንን በመጠበቁ ረገድ ልታገኘው የምትችለውን ትምህርት በዝርዝር ጻፍ።

**አራተኛ ቀን**:- ትምህርቱን ከልስና ለመወያየት የተሰጡትን ጥያቄዎች መልከትከት አድርገህ ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

**አምስተኛ ቀን**:- ትምህርቱን ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጅት አድርግ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ:-

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ:-

ሀ) 1. የተለያዩ የክርስትና ሃይማኖት ክፍሎች ሊጠብቋቸው የሚፈልጉትን የብሉይ ኪዳን ሕግ በዝርዝር ጻፍ። (ለምሳሌ አርቶዶክስ፥ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ወዘተ...)

2. እነዚህን ሕጋጋት የሚጠብቁት ለምንድን ነው፤

3. እነዚህን ሕጋጋት ለምንድን ነው የማትጠብቀው ብለው ቢጠይ ንዴት አድርገህ ነው ልትመልሳቸው የሚገባህ?

ለ) እግዚአብሔርን አፍቅሩና ሰዎችን አፍቅሩ የሚሉትን ሕጋጋት ከጠበቅ / አሥርቱን ትዕዛዛት እንዳሟላን የሚቆጠረው እንዴት ነው?

ሐ) 1. የብሉይ ኪዳንን ሕጋጋት ለመጠበቅ ስንል የምግብ ሕጋጋቱን ብንጠብቅና በባኅላችን መሠረት አትብሉ የተባለውን ነገር ብንጠብቅ ልዩነቱ ምንድን ነው?

2. አንዳንዴ የባህላችንን ተፅዕኖ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የምናመሳስለው እንዴት ነው?

3. እኛ ከምንበላው የምግብ ዓይነት ለየት ያለ ምግብ (ለምሳሌ: አሣማን፥ ግመልን ወዘተ... የሚበሉትን ሰዎች በምን ዓይነት አመለካከት ነው የምናያቸው? ይህ ትክክል ነው?

መ) 1. እንደ እግዚአብሔር ሕዝቦች እሥራኤላውያን መለየታቸውን በገሃድ ያሳዩት እንዴት ነው?

2. እንደ እግዚአብሔር ሕዝቦች መለየታችንን ዛሬ የምናሳየው እንዴት ነው?

3. መለየታችንን የሚያሳዩ አንዳንድ ዋና ዋና የሆኑ መንፈሳዊ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ሠ) 1. የሕዝቦችን ጤንነት በተመለከተ እግዚአብሔር ሕግጋቱን የሰጠው ለምንድን ነው?

2. ከእነዚህ ሕግጋት ልንማርና በተግባር ልንገልፀው የምንችለው ነገር ምንድን ነው?

ረ) 1. በኢትዮጵያ ውስጥ ከኅብረተሰቡ የተገለሉ አንዳንድ ጎሳዎች ምንድን ናቸው?

2. በኅብረተሰቡ ለተገለሉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንህ የእግዚአብሔርን የፍቅር ኃይል የምታሳየው እንዴት ነው?

3. ለእነዚህ ሰዎች የምታሳየውን ፍቅር ቤተ ክርስቲያንህ በምን ዓይነት መንገድ ልታሻሽለው ትችላለች?

5. ፀሎት

# ትምህርት አምስት

አሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 14-16

## የመጀመሪያ ቀን:-

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ14-15

ባለፈው ሳምንት አንድን ሰው ንጹሕ ወይም እርኩስ የሚያሰኙ የተለያዩ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን በማጥናት ነበር ያሳለፍነው። ከእነዚህ ብዙዎቹ እንደ መግደልና ማመንዘር የግብረ ገብነት ተላላፊ ኃጢአቶች ባይሆኑም እንደ ኃጢአት ምሳሌዎች በመሆን መገናኛውን ድንኳን እንደሚያቆሽሹ ዓይነት ሆነው ሊገለጹ ይችላሉ። እግዚአብሔር ሕዝቡ ኃጢአተኛ እንደሆነና መንፈሳዊ መንጻት እንደሚያስፈልገው ያሳይ የነበረው በበሽታ ነው።

ባለፈው ሳምንት መጨረሻም ካህኑ በሰው ላይ ወይም በዕቃ ላይ ያለውን ምልክት መርምሮ እንዴት እርኩስ ነው ወይም እርኩስ አይደለም እንደሚል ተመልክተናል። ዛሬ አንድ እርኩስ ሰው ወይም ነገር እንዴት መንጻት እንደሚችል (ዘሌዋ.14) ምን ዓይነት ወሲባዊ ግንኙነቶች እንደሚያረክሱ (ዘሌዋ. 15) እንመለከታለን። በተቀረው የሳምንቱ ቀናት ደግሞ በአይሁዳውያን ዘንድ እንደ ዋነኛ መንፈሳዊ ክብረ በዓል የሚቆጠረውን የስርየትን ቀን እናጠናለን።

ምንም እንኳ አንድ ሰው የሥጋ ደዌ ኖሮበት ከኅብረተሰቡ ቢገለልም ከዚህ በሽታው ሲነጻ ወደ ኅብረተሰቡ ተቀላቅሎ ይገባ የነበረው አንድ የተወሰነ የመንፃት ሥርዓትን ተከትሎ ነበር። እግዚአብሔር የምሕረት አምላክ ነው። ኃጢአተኞች መንገዱን መከተል ፈልገው ከእርሱ ጋር እንደገና ኅብረት ቢኖራቸው ፈቃደኛ ነው። እርኩስ ነው ተብሎ

ማግለሉ በጣም ቀላል ነበረ፤ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር እንደገና ኅብረት የመፍጠሩ ሂደት ደግሞ ከበድ ያለ ነበር። በኃጢአት ውስጥ መውደቁ ለእኛ ቀላል ቢሆንም ከወደቅን በኋላ የምንመለስበት መንገድ ደግሞ ከባድ ይመስላል። ኃጢአት ከመሥራት ይልቅ ይቅርታ መጠየቁ ነው የሚከብደው።

1ኛ ጥያቄ: - ብዙውን ጊዜ በኃጢአት መውደቅ ንስሐ ከመግባት ይልቅ ቀለል የሚለው እንዴት ነው? ምሳሌዎች ስጥ።

1. የአንድ ሰው ከማይነጻ በሽታ መዳን ወይም መንጻት (ዘሌዋ. 14:1-32)

* አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 14 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

2ኛ ጥያቄ: - አንድ ከለምፁ የነፃ ሰው ለመጀመሪያው ሥርዓት ያቀርባቸው የነበሩ አራት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

3ኛ ጥያቄ: - ከለምፁ የነጻው ሰው ለመጨረሻው መንጻት እንዲደርስ ለእግዚአብሔር ማቅረብ የነበረበት አራት የመሥዋዕት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

4ኛ ጥያቄ: - ለበደል መሥዋዕት የፈሰሰውን ደም ካህኑ ምን ያደርገው ነበር?

5ኛ ጥያቄ: - አንድ ሰው ድሃ ከመሆኑ የተነሣ አስፈላጊውን መሥዋዕት ማቅረብ ካልቻለ እግዚአብሔር ምን ዓይነት አማራጮች ነበር የሰጠው?

6ኛ ጥያቄ: - በአንድ እሥራኤላዊ ቤት ውስጥ የለምፅ ደዌን የሚያመጣው ማነው? (14:34)

7ኛ ጥያቄ: - አንድ ቤት ከነፃ በኋላ እንደገና ቢረክስና ደዌው ቢመለስበት የሚነፃው እንዴት ነው?

አንድ የረከሰ ሰው ከማኅበረሰቡ ጋር እንደገና ኅብረት የሚኖረው ከበሽታው ሲነፃ ነው። ወደ ኅብረተሰቡ የሚመለስበት እራሱን የቻለ ሥርዓት አለው። ይህም ሥርዓት በደረጃ ነው የሚካሄደው።

የመጀመሪያው ደረጃ የሚከናወነው ሕዝቡ ከሚኖርበት ክልል በግዴታ ተገልሎ በሽተኛው በሚኖርበት ሥፍራ ነው። ካህኑም ይህ ሰው የሚኖርበት ሥፍራ ድረስ መጥቶ እውነት ሰውዬው ከበሽታው ነፅቶ እንደሆነ ይመለከታል። መንፃቱ ከተረጋገጠም የሰውዬው ዘመዶችንና ወዳጆች አራት ነገሮችን ያመጡ ነበር። እነዚህም ሁለት ንጹህ እርግቦች ከነሕይወታቸው፥ የዝግባ እንጨት ቀይ ግምጃና ሂሶጵ ናቸው። በመጀመሪያ ከወፎቹ አንዱ ትገደልና ደሟ ንጹህ ውኃ በያዘ ሸክላ ውስጥ ይጠራቀማል። ከዚያም ሁለተኛዋ ወፍ የዝግባው እንጨት ቀዩ ግምጃና ሂሶጱ በመጀመሪያዋ ወፍ ደም ውስጥ ይነከራሉ። የተፈወሰውም ሰው በደሙ ሰባት ጊዜ ይረጭና ንጹህ ነህ ይባላል። የዝግባው እንጨት፥ ቀዩ ግምጃና ሂሶጱ ምን እንደሚያመለክቱ ትርጉማቸውን አናውቅም። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፃትን በተመለከተ የሚጠቀሱ ነገሮች ናቸው፤ (መዝ.(51):7)። ሕያው የሆነችው ወፍ ትለቀቃለች። ይህም በሽታው ሰውዬውን እንደለቀቀውና እንደነጻ የሚያመለክት ነው። ከዚህም በኋላ ሰውዬው ልብሱን ያጥባል፥

ሰውነቱን ይታጠባል ፀጉሩንም ይላጫል። ይህን ካደረገ በኋላ ወደ መኖሪያው ሥፍራ ገብቶ እንዲኖር ይፈቀድለታል። ይህም ቢሆን ግን ይኖር የነበረው ከድንኳኑ ውጭ ነው፥ ምክንያቱም የመንጻቱ ሥርዓት ስላላለቀ ነው።

ሁለተኛው ደረጃ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ነው የሚካሄደው። ከሳምንት በኋላ ሰውዬው እንደገና ይላጭና እራሱን ለመንፃቱ ሥነ-ሥርዓት ያዘጋጃል። በዚህም ጊዜ አራት የተለያዩ መሥዋዕቶችን ያቀርባል። እነዚህም የእህል ቁርባን፥ የበደል መሥዋዕት፥ የኃጢአት መሥዋዕትና የሚቃጠል መሥዋዕት ናቸው። የማይቀርበው የሠላሙ መሥዋዕት ብቻ ነበር። እነዚህን መሥዋዕቶች ካሟላ በኋላ ሰውዬው ከእሥራኤል ሕዝብና ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ያድሳል። በመጀመሪያ የሚሠዋው የበደል መሥዋዕቱ ነው። ደሙ በማጠራቀሚያ ውስጥ ከተጠራቀመ በኋላ በሰውዬው ቀኝ ጆሮ ጫፍ፥ በቀኝ እጁ አውራ ጣትና በቀኝ እግሩ አውራ ጣት ላይ ይረጫል። ይህ ሥርዓት ሰውዬው የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚሰማ፥ የእግዚአብሔርን ፍቃድ እንደሚፈጽምና የእግዚአብሔርን መንገድ እንደሚከተል የሚያመለክት ነው። (ይህ ልክ ካህኑ ለክህነት ዕጩ እንደሚሆንበት ዓይነት ሥርዓት ነው፥ ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 8)። እግዚአብሔር በሚገኝበት ቅዱስ ቦታ አቅጣጫ ሰባት ጊዜ ዘይት ይረጫል። ካህኑ ከዘይቱ ወስዶ በሰውዬው በቀኝ ጆሮ ጫፍ በቀኝ እጁ አውራ ጣትና በቀኝ እግሩ አውራ ጣት ላይ ያደርጋል። በመጨረሻም የሚነፃው ሰውዬ ራስ ላይ የተቀረውን ዘይት ያደርግበታል። የሚቃጠለውንና የኃጢአቱን መሥዋዕት ካቀረበ በኋላ ሰውዬው በመንፈስም ሆነ በሥጋ የነጻ ይሆናል። ይህም ስለሆነ ከእሥራኤል ሕዝብና ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ በሙሉ ኅብረት ይኖረዋል። ሰውዬው ደሃ ከሆነ ማቅረብ የነበረበትን ሁለት ጠቦት በእርግብ መቀየር ይችል ነበር።

2. በለምፅ ደዌ የረከሰ ቤት የሚነፃበት መንገድ (ኦሪት ዘሌዋውያን 14፡33-56)

ከርኩሰት መንፃት የነበረባቸው ሰዎች ብቻ አልነበሩም፥ ንብረቶቻቸው ሊረክሱ ስለሚችሉ ንብረቶቻቸውም መንጻት ነበረባቸው። በሽታንና ደዌን በንብረት ላይ የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው፥ (14፡34)። ካህኑ በቤቱ ውስጥ ደዌ እንዳለ ሲነገረው እንደተለመደው ቤቱ ንጹሕ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ያረጋግጣል። በመጀመሪያም በደዌው ያልተነካው የቤቱ ዕቃ በሙሉ ይወጣል። ከዚያም ቤቱን በደንብ ከተመለከተ በኋላ ለሳምንት ይዘጋዋል። በመጨረሻም ደዌው ተዛምቶ እንደሆነ ከፍቶ ይመለከታል። ከተዛመተ ደዌ ያለባቸው ድንጋዮች ከቤቱ ይፈርሱና ወደ ውጭ ተጥለው እንዲወጡና እንዲወድሙ ይደረጋል። ቤቱንም ያስፍቀውና እንደገና በአዲስ ጭቃ ያስመርገዋል። ደዌው ዳግመኛ ቢመለስና ቢሥፋፋ ቤቱን በጠቅላላ ያወድሙታል። ቤቱ በካህኑ ከተዘጋ በኋላ ውስጡ የሚገባ ሰው በሙሉ እርኩስ ይሆን ነበር።

ዳግመኛ ከተመረገ በኋላ ደዌው ካልተዛመተ የመንፃቱ ሥርዓት ይካሄድ ነበር። አሁንም ቤቱን ለማንጻት ሁለት ወፎች የዝግባ እንጨት፥ ቀይ ግምጃና ሂሶጵ ነበር የሚጠቀሙት። ከመኖሪያው ሥፍራ ተገልሎ የተፈወሰው ሰው የሚነጻበትን ዓይነት

ሥርዓት በመከተል ነበር ቤቱ የሚነጻው። ሆኖም ለቤቱ ተብሎ የሚቀርብ መሥዋዕት አልነበረም።

እነዚህን በጥንቃቄ የተዘጋጁ ማስጠንቀቂያዎች በመጠቀም ነበር እግዚአብሔር በመኖሪያው ሥፍራ በሽታ እንዳይዛመት ያደርግ የነበረው። ለእሥራኤል ሕዝቦች ደዌና በሽታ የኃጢአት ምልክቶች እንደሆኑ በግልጽ አሳይቷቸዋል። የእግዚአብሔር ምኞት ንጹሕ ሕዝብ እንዲሆኑ ነው። እርኩሰትና የኃጢአት ንኪኪ ያለበትን ማንኛውንም ነገር በጥንቃቄ ማስወገድ ነበረባቸው አለበለዚያ ያ ነገር ይዛመታል። ልክ እንደዚሁ በሕይወታችን ውስጥ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ኃጢአት በጣም አሳሳቢ ነው። በጥንቃቄ ወዲያውኑ ሊወገድ ይገባል፤ አለበለዚያ ተዛምቶ ለሌሎች ሰዎች ጠንቅ ሊሆን ይችላል። በሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያለውን ኃጢአት ባናስወግድ የኃጢአት ፍሬ ይዛመትና የቤተ ክርስቲያንን ቅድስና ያጠፋል።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ያልታወቀ ኃጢአት የሕይወትህን ወይም የቤተ ክርስቲያንህን ቅድስናና ምሥክርነት የሚያጎድፈው እንዴት ነው?

ለ) ኃጢአት ሲያንሰራራ እንደሚያስወግዱልን እርግጠኞች ሆነን የምንወስዳቸው እርምጃዎች ምን ምንድን ናቸው?

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 15 ከወንዶችና ሴቶች ብልቶች ውስጥ ስለሚወጡ ፈሳሾች ይናገራል። ይህን ምዕራፍ አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

9ኛ ጥያቄ፡- ከወንዶችና ከሴቶች በሚወጣው ፈሳሽ ምክንያት የሚረከሱት ነገሮች ምንድን ናቸው?

10ኛ ጥያቄ፡- ከሴቶች ወይም ከወንዶች የሚወጡት ሁለቱ ዓይነት ፈሳሾች ልዩነታቸው ምንድን ነው?

11ኛ ጥያቄ፡- ለማያቋርጡ ፈሳሾች ይደረግ የነበረው የመንጻት ሥርዓት ምን ዓይነት ነው?

1. ከወንዶች የሚወጡ ያልተለመዱ ፈሳሾች (ኦሪት ዘሌዋ. 15፡1-15)

በዚህ ክፍል ትኩረት የሚሰጠውና ከወንዶች ብልቶች ውስጥ ስለሚወጡ ያልተለመዱ ፈሳሾች ነው። ሰውዬው የማያቋርጥ የአባለዘር ብሽታ ካለው፥ በሽታው እስካልቆመ ድረስ እርኩስ ይባል ነበር። ሰውዬው የሚነካቸውን ነገሮች በተመለከተ ጥብቅ የሆኑ ማስጠንቀቂያዎች ተደንግገዋል። ሰውዬው የሚተኛበት አልጋ እርኩስ ይሆን ነበር። ሰውዬውን የሚነካ ሰው ወይም ሰውዬው የነካውን ማንኛውንም ነገር የሚነካ ሁሉ እርኩስ ይሆናል። ልብሱንና ሰውነቱን ካጠበና ከታጠበም በኋላ ለአንድ ቀን ያህል የረከሰ ይሆናል። ከሸክላ የተሠራ ማንኛውም ነገር መጥፋት ነበረበት። ሌሎች ዕቃዎችን ግን በውሃ ካጠቧቸው በኋላ እንደገና ሊገለገሉባቸው ይችላሉ።

እንደገና እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገውን እንክብካቤ እንመለከታለን። እግዚአብሔር በሽታ በእሥራኤል ሕዝቦች መካከል እንዳይዛመት ይቆጣጠር ነበር። እንደ ቂጥኝ፥ ጨብጥ፥ ኤድስ የመሳሰሉት የአባለዘር በሽታዎች በቀላሉ የሚተላለፉ

ናቸው። እነዚህ በሽታዎች በተለይ የሚተላለፉት፡- ሰዎች ካገቢቻው ጋር ብቻ ወሲባዊ ግንኙነት እንዲያደርጉ የሚደነግገውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሳይጠብቁ ሲቀሩ ነው። እግዚአብሔር እነዚህን መመሪያዎች የደነገገው እሥራኤላውያን አንዱ ለሌላው በሽታን ከማስተላለፍ እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው።

ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው ከፈሳሹ ሲነፃ ለሰባት ቀን ያህል ይቆይና ልብሱንና ሰውነቱን ያጥባል። በስምንተኛው ቀን ሁለት ዋኖሶች ወይም የርግብ ጫጩቶችን እንደ ኃጢአትና እንደሚቃጠለው መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀርባል። በዚህም ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ይነፃል። እግዚአብሔርንም መገናኛው ድንኳን ድረስ በመሄድ ሊያመልክ ይችላል።

12ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አስፈላጊ ጥንቃቄ ካልተወሰደ በቀላሉ ቶሎ ሊዛመቱ የሚችሉ ዛሬ በዓለማችን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የአባለዘር በሽታዎችን ዘርዝር። ለ) እነዚህ በሽታዎች እንዳይዛመቱ ቤተ ክርስቲያንህ ለአባላቷ ልትነግራቸው የምትችለው ምንድን ነው?

2. ከወንዶች የሚወጡ የተለመዱ ፈሳሾች (ኦሪት ዘሌ. 15፡16-18)

አንድ ሰው ዘሩ ቢፈስ እርሱና ዘሩ የነካው ማንኛውም ነገር እስከ ማታ ድረስ እርኩስ ይሆናሉ። ዘሩ የነካውን ማንኛውንም ነገርና ገላውን መታጠብ ነበረበት። እንዲሁም ከሴት ጋር ግንኙነት ሲያደርግም መታጠብ ነበረበት። ሁለቱም ገላቸውን ይታጠባሉ፥ እስከማታም ድረስ እርኩስ ይሆናሉ። ለዚህ ዓይነቱ ፈሳሽ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልግም።

የረከሱ ነገሮች በውሃ ይታጠቡ ብሎ እግዚአብሔር ስንቴ እንዳዘዘ ማስተዋሉ ጠቃሚ ነው። ሳይንቲስቶች ገላቸውንና ልብሳቸውን ቶሎ ቶሎ የሚያጥቡ ሰዎች ከማያጥቡ ሰዎች ይበልጥ ጤናማዎች እንደሆኑ ይናገራሉ። እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን የሰጣቸውን መመሪያዎች በመከተል እራሳችንን፥ ልጆቻችንንና ልብሶቻችንን በየጊዜው ማጠብ ይኖርብናል። በእነዚህም መመሪያዎች ስንታዘዝ እግዚአብሔር ጤንነታችንን ይጠብቅልናል።

3. ከሴቶች የሚወጡ የተለመዱ ፈሳሾች (ኦሪት ዘሌዋ. 15፡19-24)

አንዲት ሴት በወር አበባዋ ወቅት በሥርዓቱ መሠረት እርኩስ ነበረች። እርሷን የነካት ሰው ወይም እርሷ የነካችው ነገር በሙሉ የረከሰ ይሆን ነበር። እርሷን የነካት ልብሱንና ገላውን ማጠብ ነበረበት፤ እስከ ማታም ድረስ እርኩስ ነበር።

በወር አበባዋ ወቅት ከሷ ጋር ግንኙነት የሚያደርግ ሰው ለሰባት ቀን ያህል እርኩስ ይሆን ነበር። በዚህ ወቅት ማንም ሰው ከእርሷ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት እንዲያደርግ አይፈቀድለትም። ከሰባት ቀን በኋላም እርሷ ትነጻለች፤ ለዚህም መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልጋትም።

4. ከሴቶች የሚወጡ ያልተለመዱ ፈሳሾች (ኦሪት ዘሌዋ. 15፡25-30)

ሴቷም የወር አበባዋ ካለመቆም ቢፈስ ወይም ከወር አበባዋ ሌላ ያለተለመደ የማያቋርጥ ደም ቢፈሳት ደሙ እስኪያቆም ድረስ የረከሰች ትሆናለች። እንደ ወር አበባዋ ጊዜ ራስዋም ሆነች የነካችው ነገር በሙሉ የረከሰ ይሆናል። ሕመሙ ከለቀቃት ከሰባት ቀንም በኋላ ሴትዮዋ ንጹሕ ትሆናለች። በስምንተኛውም ቀን ያልተለመደ ፈሳሽ የሚፈሰውን ሰውዬ ዓይነት ሥርዓት ተከትላ በመገናኛው ድንኳን መሥዋዕቶችዋን ታቀርባለች።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ይህን ሕግ ለእሥራኤል ልጆች የሰጠበትን ምክንያት ባናውቅም እነዚህ ሕጋጋት እንደገና ስለ እግዚአብሔር ባህርይ ቅድስናና ሕዝቡ ቅዱሳን እንዲሆኑ ምኞቱን ያሳዩናል። እነዚህ ሥጋዊ የሆኑ እክሎች ኃጢአት አልነበሩም። እንዲያው ኃጢአት በሕይወታቸው ውስጥ የሚያስከትለውን ነገር እንዲያስተውሉ የሚያደርጓቸው ነገሮች ናቸው። ያልተለመደ የሆነ ነገር ሊቆጣጠሩትም የማይችሉት ነገር በሙሉ የመጣው ከአዳም እና ሔዋን ውድቀት ስለሆነ የኃጢአት ምሳሌ ነው። ኃጢአትና ርኩሰት ከሰዎች አዕምሮ መቼም ቢሆን የማይጠፉ ነገሮች ናቸው። ለዚህም ነው በሥርዓቱ መሠረት ንጽሕናቸውን እንዲጠብቁ እግዚአብሔር የሚያስጠነቅቃቸው በሥርዓቱ መሠረት ንጹሕ ያልሆነ ሰው ወደ መገናኛው ድንኳን ቢገባ ሕያውና ቅዱስ የሆነው አምላክ የሚኖርበትን ሥፍራ ነበር የሚያበላሸው። እርኩስነታቸው የእግዚአብሔር ፍርድ በላያቸው እንዲሆን ያደርጋል፥ (15፡31)። እግዚአብሔር ከሰጣቸው ትዕዛዝ እሥራኤላውያን ፈቀቅ ቢሉ በእርሱ ዐይን እንደ ኃጢአተኞች ነበር የሚቆጠሩት።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር የኃጢአት ውጫዊ ምልክት በሆኑ ነገሮች ላይ አያተኩርም። ትኩረት የሚሰጠው ግን በሰው ልብ ላይ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ይላል «ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ሐሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጎምጀት፥ ክፋት፥ ተንኮል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና፥ ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል»፤ (ማር.7፡14-23)። በኃጢአት መውደቅ ምን ያህል ቀላል እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ኃጢአትና የሚያስከትላቸው ችግሮች በሙሉ በአጠገባችን እንዳሉም መገንዘብ አለብን። የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን መጠን ከኃጢአት ነጽተን መኖር አለብን። ኃጢአት በሕይወታችን ውስጥ ሲያልፍ ወዲያውኑ መናዘዝና መንፃት ይኖርብናል። አለበለዚያ ከሕያው አምላክ ጋር ያለን ግንኙነት ይበላሻል በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን የተግሣፅ በትር ሊያጋጥመን ይችላል። ኃጢአታችን በአካባቢያችን ያሉትንም ሁሉ ቤተሰባችንን ልጆቻችንን ቤተክርስቲያናችንን አካባቢ ያሉትን ወዳጆቻችንን ወዘተ ይበክላል።

13ኛ ጥያቄ፡- ለአንድ አፍታ ሕይወትህን መርምርና ያረከሰህ ኃጢአት እንዳለ እይ።

ሁለተኛ ቀን፡-

## ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 16

ዛሬ በእሥራኤል ሕዝብ ዘንድ በጣም ትልቅ መንፈሳዊ ክብረ በዓል ስለሆነው ስለ ስርየት ቀን እንመለከታለን። እኛ የኢየሱስን የልደት ቀንና ፋሲካን እንደምናከብር ሁሉ አይሁዳውያንም እግዚአብሔርን በተለየ መልክ የሚያመልኩባቸው ቀናት ነበሯቸው።

14ኛ ጥያቄ፡- መንፈሳዊ የሆኑ በዓላቶች ለእግዚአብሔር ያለንን አምልኮ በተመለከተ የሚጠቅሙን ለምንድን ነው?

እንደምታስታውሰው እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሁለቱ የአሮን ልጆች በሞቱበት ጊዜ እግዚአብሔር አሮንን የካህናት አንዱ ኃላፊነት ለሕዝቡ ንጹሕ የሆነውንና እርኩስ የሆነውን ነገር ማሳወቅ እንደሆነ ነግሮታል፤ (ኦሪት ዘሌዋ.10፡10)። ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 11-15 ያለው ንጹሕ እና እርኩስ የሆኑትን ነገሮች በዝርዝር ይገልጻል። በዚያኑ የአሮን ሁለቱ ልጆች በሞቱበት ዕለት እግዚአብሔር የእርሱ ክብር ወደሚቀመጥበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ካህኑ መቼ መግባት እንደሚችል የተለየ መመሪያ ሰጥቷል፤ (ኦሪት ዘሌዋ.16፡1)። እግዚአብሔር የሚገኝበትን ቦታ መግባት የሚችለው ሊቀ ካህኑ ብቻ ሲሆን የሚገባውም በዓመት አንዴ በሚከበረው የስርየት ቀን ብቻ እንደሆነ እንመለከታለን። ሌላ ሰው ከገባ ግን፥ ልክ እንደ ናዳብና አብድዩ ይሞት ነበር። የስርየት ቀን ዓላማ በመጀመሪያ የእሥራኤልን ሕዝብ ከኃጢአት ማንጻት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በዚያ የአምልኮ ዓመት ወቅት ቤተ መቅደሱ ረክሶ እንደሆነ ለማንጻት ነው።

* ዘሌዋ.16 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ

15ኛ ጥያቄ፡- ለስርየት ቀን ሥርዓት እራሱን ዝግጁ ለማድረግ አሮን ያደርግ የነበረው ዝግጅት ምን ነበር?

16ኛ ጥያቄ፡- አሮን ለራሱ ወይፈን ማምጣት የነበረበት ለምንድን ነው?

17ኛ ጥያቄ፡- አሮን በወይፈኑ ደም ምን ነበር የሚያደርገው?

18ኛ ጥያቄ፡- አሮን ለኃጢአት መሥዋዕት በሚቀርበው የአውራ ፍየል ደም ምን ያደርግ ነበር?

19ኛ ጥያቄ፡- ሕዝቡ ለኃጢአት መሥዋዕት ያመጣው ሁለተኛው የአውራ ፍየል ምን ነበር የሚደረገው?

20ኛ ጥያቄ፡- የሁለተኛው አውራ ፍየል የቀረበበት ዓላማ ምን ነበር? (ከቁጥር 21-22)

21ኛ ጥያቄ፡- በስርየት ቀን የእሥራኤል ሕዝብ ማድረግ የሚገባው ነገር ምን ምን ነበር?

የስርየት ቀን ዓላማ የእያንዳንዱን እሥራኤላዊ ኃጢአት ማንፃት ሳይሆን የእሥራኤል ሕዝብ በአጠቃላይ የሚነጻበት ጊዜ ነው። የነገሥታት ንጉሥ የሆነው እግዚአብሔር ዙፋን ይገኝበት ወደነበረው ቅድስተ ቅዱሳን እንዴት መግባት እንደሚችል ግልጽ የሆነውን መመሪያ እግዚአብሔር ለሙሴ ሰጥቶታል። ይህንንም ያደረገው እግዚአብሔር የሚኖርበት ሥፍራ ቅዱስ በመሆኑ ነው። እንደምታስታውሰውም እግዚአብሔር ሕዝቡን ተገናኝቶ የሚናገራቸው በታቦት ላይ ተቀምጦ እንደሚሆን ቃል ገብቶላቸዋል፤ (ኦሪት ዘጸአት 25፡21-22)። ማንኛውም ሰው የተጠቀሰውን ሥርዓት ሳይከተል ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የገባ እንደ ናዳብና አብድዩ ይገደላል። ምንም እንኳ ለአይሁዳውያን በጣም ትልቅ የሃይማኖት ክብረ በዓል ቢሆንም ከሙሴ የሕግ መጻሕፍት ውጪ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ አናገኘውም።

22ኛ ጥያቄ፡- «የስርየት ቀን» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ተመልከትና በዚያ ቀን የሚደረጉትን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

## በስርየት ቀን የነበረው ሥርዓት የሚከተለው ነው፡-

1. በመገናኛው ድንኳን ውጪኛ ግቢ በሚገኘው የነሐስ ሳሕን ላይ ሊቀ ካህኑ ይታጠባል። በቀለም ያሸበረቀውን የሊቀ ክህነት ልብሱን ያወልቅና ሎሌዎች የሚያደርጉትን ዓይነት ልብስ ይለብሳል። መላእክትና ጻድቃን ሰማዕታት እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ይህን ዓይነት ልብስ እንደሚለብሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ (ትንቢተ ሕዝቅኤል 9፡2-3፥ ትንቢተ ዳንኤል 12፡6-7፥ ራዕይ 19፡8)።

2. ለራሱና ለሌሎቹ ካህናት የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርበውን ወይፈን ይዞ በነሐስ ወደተሠራው መሠዊያ አካባቢ ይቀርባል። ቀጥሎም ወይፈኑን ይገድልና ደሙን በሳሕን ውስጥ ያጠራቅማል።

3. በነሐሱ መሠዊያ አካባቢ ከሚገኘው ከሰል ትንሽ ወስዶ ጽናጽል ውስጥ ይከታል። ጽናጽሉንም ይዞ ቅድስተ ቅዱሳኑን ከቅዱሱ ቦታ ወደሚለየው መጋረጃ ድረስ ይሄዳል። በዚህም ቦታ ላይ ሁለት እፍኝ ዕጣን በጽናጽሉ ውስጥ ይጨምራል። የዕጣኑ ጭስ ሊቀ ካህኑ ታቦቱን ማየት እስኪያቅተው ድረስ በደንብ መጨስ ነበረበት።

4. ወደ ውጭ ወጥቶ ደሙን ያጠራቀመበትን ሳሕን ይዞ ይገባና ደሙን በታቦቱ ላይ እና በስርየቱ ክዳን ላይ ይረጫል። የሥርየት ክዳን ተብሎ የተሠየመው የታቦቱ ክዳን በመሆኑና እዚህ ክዳን ላይ የእግዚአብሔር ክብር በመኖሩ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ይህ ደም ሲረጭ የካህናቱና የሕዝቡ ኃጢአት ይሸፈናል፥ እግዚአብሔርም ይቅር ይላቸዋል። ሊቀ ካህኑም በታቦቱ ፊት ደሙን የሚረጨው ሰባት ጊዜ ነበር። ሰባት ቁጥር ፍጹምነትን የሚያመለክት ሲሆን ሊቀ ካህኑ ሰባት ጊዜ ሲረጭ ፍጹም ይቅርታ እንዳገኙ ያሳያል። ከዚህም በኋላ ወደ ነሐሱ መሠዊያ ይመለሳል። ይህ ሥርዓት ካህኑ የኃጢአት መሥዋዕት ሲያቀርብ ከሚያደርገው ጋር ይመሳሰላል፥ በስርየት ቀን ግን ለየት የሚለው ደሙ በታቦቱ ላይ መረጨቱ ነው። በኃጢአት

መሥዋዕት ጊዜ ደሙ ይረጭ የነበረው በመጋረጃው አካባቢ ነበር፤ (አሪት ዘሌዋውያን 4፡3-12)።

5. ለመላው ሕዝብ ሲሉ የእሥራኤል መሪዎች ያመጧቸውን ሁለት ፍየሎች ካህኑ ወደ ነሐሱ መሠዊያ ይወስዳቸውና ለኃጢአት መሥዋዕት ያዘጋጃቸዋል። ለሁለቱ ፍየሎች ዕጣ ይጣልና ከሁለቱ ዕጣ የወጣበት ይሠዋል ሌላው ደግሞ ይለቀቃል። አንዳንድ ሰዎች ካህኑ ይህን ዕጣ የሚያወጣው ኡሪምና ቱሚም የተባሉትን የከበሩ ድንጋዮች በመጠቀም ነው ይላሉ።

6. ለኃጢአት መሥዋዕት የሚቀርበው ፍየል ይሠዋና ደሙ በሳሕን ውስጥ ይጠራቀማል። ሊቀ ካህኑ ደሙን ይይዝና በሚከተሉት ነገሮች ላይ ይረጨዋል፡-

ሀ) የቃል ኪዳኑ ታቦት፡- በዚህ ሥፍራ በእግዚአብሔር ፊት ደሙን በማምጣት የሕዝቡ ኃጢአት እንዲሰረይ ያደርጋል።

ለ) የቃል ኪዳኑ ታቦት በሚገኝበት ሥፍራ በቅዱስተ ቅዱሳን ውስጥ፡- ይህ ቅዱስተ ቅዱሳን ባለፈው ዓመት ያረከሰውን ነገር ለማንጻት የሚቀርብ ነው።

ሐ) በወርቅ የተለበጠው ዕጣን መሠዊያ ላይ፡- (አሪት ዘጸአት 30፡10)።

መ) ቅዱሱ ቦታ፡- ይህ ቅዱሱን ቦታ ካረከሰው የካህናት ወይም የሕዝቡ ኃጢአት ለማንጻት የሚደረግ ነው።

ሠ) የነሐሱ መሠዊያ፡- በዚህ ሥፍራ የወይፈኑና የፍየሉ ደም በመሠዊያው ቀንድ ይደረጋሉ። ይህ የሚደረገው መሠዊያውን ለማንፃትና በሌላ ጊዜ መሥዋዕት እንዲቀርብበት ለማዘጋጀት ነው።

ረ) በነሐሱ መሠዊያ ፊት ለፊት፡- ይህ የሚደረገው ውጪኛውን ግቢ እርኩስ ከሆነ ነገር ለማንጻት ነው።

ይህ ደም ሁለት ዓላማዎችን ያካተተ ነው። በመጀመሪያ ባለፈው ዓመት ውስጥ ከካህናቱ እንሥቶ ተራው ሕዝብ የፈጸመውን ኃጢአት የሚሸፍን ነው። በሚቀጥለው ዓመት ውስጥ በሥርዓቱ መሠረት ሕዝቡ የሚነጻበት ጊዜ ነበር። ሁለተኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅዱስና ሕያው የሆነውን አምላክ የሚያመልከበትን የመገናኛ ድንኳን ለማንጻት ነው ።

7. ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህኑ እጆቹን በሁለተኛው ፍየል ላይ ይጭንና የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት ይናዘዛል። ይህም የሕዝቡን በደልና ኃጢአት በፍየሉ ላይ እንዳደረገ ያመለክታል። በመጨረሻም አንድ ሰው ፍየሉን ሁለተኛ ወደማይታይበት ምድረ በዳ ይሰደዋል። ይህም የእሥራኤል ሕዝብ ኃጢአት እንደተወገደና ከዚያም ቀን ጀምሮ እንደማይቆጠርባቸው የሚገልጸውን እውነታ ያመለክታል። በኋላ ግን በእሥራኤል ታሪክ ውስጥ እንደተገኘው ይህንን ፍየል ከተራራ ጫፍ ላይ የኋሊት በመወርወር ይገድሉት ነበር።

8. ፍየሉን ወደ ምድረ በዳ የነዳው ሰውዬ ተመልሶ ወደ መኖሪያው ሥፍራ ከመግባቱ በፊት ገላውንና ልብሱን ማጠብ ነበረበት። ይህም የሚሆነው በፍየሉ ላይ በሥርዓቱ መሠረት የነበረውን ኃጢአት ወደ መኖሪያው ሥፍራ ላለመመለስ ሲባል ነው።

9. ሊቀ ካህኑ የስርየት ቀንን ሥርዓት ሲፈጽም የለበሰውን ልብስ ያወልቅና እርኩስ የሆነውን ከራሱ ላይ ለማስወገድ ሲል ገላውን ይታጠብና የሊቀ ካህን ልብሱን እንደገና ይለብሳል።

10. ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህኑ በነሐሱ መሠዊያ ላይ ሁለት አውራ በጎች ለሚታጠለው መሥዋዕት ይሠዋል። አንደኛው ለራሱ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ለሕዝቡ ነው።

11. አንድ ሰው ይመረጥና ለኃጢአት መሥዋዕት የቀረቡትን እንስሳት በድን ከመኖሪያው ሠፈር ውጪ ይዞ ይወጣና ያቃጥለዋል። ወደ እሥራኤል ሕዝብ መኖሪያ ሠፈር ከመግባቱ በፊት ልብሱንና ሰውነቱን መታጠብ ነበረበት።

በዚህም አማካኝነት የሕዝቡ ኃጢአት ይሰረያል፤ የስርየት ቀን ክብረ በዓልም ይፈጸማል። አሁን ሕዝቡ ቅዱስ ነው፥ ስለዚህም እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ለሚቀጥለው ዓመት ይኖራል።

የስርየት ቀን በዓል ሕዝቡ ዝም ብሎ ቆሞ ሥርዓቱን የሚመለከትበት ጊዜ አይደለም። ይህን ጊዜ ሲያከብሩ ማድረግ የነበረባቸው የተለዩ ዝግጅቶች ነበሩ። በመጀመሪያ፥ ይህ ቀን «ታላቅ የሰንበት (የእረፍት) ቀን» ነው። ይህም ማለት ልክ እንደማንኛውም ሰንበት ምንም ሥራ አይሠሩም አይሁዳዊ የሆኑም ያልሆኑም ሁሉ ሐሳባቸውን በስርየት ቀን አከባበር ላይ በመሰብሰብ በውስጡ የሚታየውን የእግዚአብሔርን ፀጋና ትርጉሙን ሊያንፀባርቁ ይገባቸዋል። ሁለተኛ፥ ራሳቸውን የሚያዋርዱበት ጊዜ ነው። ይህ ምናልባት የጾም ጊዜን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። በብሉይ ኪዳን ፆም ሁልጊዜ ኃጢአትን ከመናዘዝ ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህም ይህ የስርየት ቀን ከመከበሩ በፊት የእሥራኤል ሕዝብ እራሱን መመርመርና ኃጢአቱን መናዘዝ ነበረበት። ዝም ብሎ በዓሉን ማክበሩ ብቻ እውነተኛ የሆነ ይቅርታን አያስገኝላቸውም። በእግዚአብሔር ፊት ውስጣዊ የሆነ ንስሐና ራስን ማዋረድ ሊኖር ይገባል።

23ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በአጠቃላይ እውነተኛ የሆነ የኑዛዜ ጊዜ እንዲኖረን ከፈለግን በግላችን ሊኖረን ከሚገባው የኑዛዜ ጊዜ ጋር ከላይ የጠቀስነው ሐሳብ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

## ሦስተኛ ቀን:-

ከስርየት ቀን አከባበር ብዙ የምንማራቸው ትምህርቶች ስለሚኖሩ የዛሬውን ቀን በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 16 ላይ ያሉትን የተለያዩ ትምህርቶች በመመልከት እናሳልፈዋለን። በመጨረሻም የዚህን የስርየት ቀን አከባበር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ እንደፈጸመው እናያለን።

24ኛ ጥያቄ፡- አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 16 እንደገና አንብብ። ስለ ሰው፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኃጢአትና ይቅር ስለ መባል ከዚህም ምዕራፍ ውስጥ የምታገኘውን ትምህርት በዝርዝር ጻፍ።

ምንም እንኳ ከስርየት ቀን አከባበር የምንማረው ብዙ ትምህርት ቢኖርም እዚህ ላይ የምንዘረዝረው የተወሰኑትን ሲሆን በምዕራፉ ውስጥ የሚገኙት በአብዛኛው አልተጠቃለሉም።

1. የእግዚአብሔርን ባህርይ በተመለከተ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ልንማር እንችላለን በመጀመሪያ ቅዱስ እንደሆነ እንማራለን። እሥራኤላውያን እኛ በአዲስ ኪዳን ዘመን የምንኖረው ሰዎች ያለንን ዓይነት መብት አልነበራቸውም። ለእነርሱ እግዚአብሔር ሁሌ የተለየ ነበር። የአምልኮው ሥፍራ በአጥር ተለያይቶ ነው የቆመው። በእግዚአብሔር አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ተቀደሰው ሥፍራ ውስጥ መግባት የሚፈቀድላቸው ካህናት ብቻ ነበሩ። እግዚአብሔር ወደሚኖርበት ቅድስተ ቅዱሳኑ በዓመት አንዴ ይገባ የነበረውም ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር። ይገባ የነበረውም በታላቅ ፍርሃት ነው፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ሕግጋት በሙሉ ካልጠበቀ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ይገድለዋልና ነው። ከዚህ ከብረ በዓል እግዚአብሔር ኃጢአትን በጣም እንደሚጸየፍና ማንም ሰው ወይም ዕቃ መኖሪያ በታውን እንዲያረክስበት የማይፈልግ መሆኑን እናያለን። እኛም የምናመልከው ይህንኑ ቅዱስ አምላክ ነው። በዚህም ምክንያት ነው «የሚያጠፋ እሳት» ተብሎ የተሰየመው፤ (ዕብራ.12፡29)።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር የምሕረት አምላክ እንደሆነ እንማራለን። አንድ እሥራኤላዊ ምንም ያህል ጊዜ ኃጢአት ቢሠራ እግዚአብሔር ይቅር ሊለው ፈቃደኛ ነበር። እግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብንና የስርየት ቀንን ያዘጋጀው ልጆቹ ንጹሕ እንዲሆኑለት ነው። እንደ ኃጢአታችን ብዛት እግዚአብሔር ቢቀጣን ኖሮ ሁላችንም ሟቾች ነበርን፤ (ሮሜ 3፡23)። ነገር ግን ምንም ጊዜ ቢሆን እግዚአብሔር ወደ እርሱ ለሚቀርቡ ሰዎች የምሕረት መንገድ ያዘጋጃል።

2. ከውድቀቱ በኋላ ስላለው የሰው ባህርይ ያስተምረናል። አንዳንዶች እንደሚያምኑት የሰው ልጅ በተፈጥሮ ንጹህ ሳይሆን ኃጢአተኛ ነው። ከሊቀ ካህኑ አንሥቶ እስከ ተራው የእሥራኤል ሕዝብ ድረስ በኃጢአት እንደተበከሉ ተመልክተናል። ከአዳም ውድቀት በኋላ የፈለግነውን ያህል ብንሞክር በኃጢአት መውደቃችን አይቀርም። ከአዳም የወረስነው «አሮጌው ተፈጥሮ» ሁሌ ወደ ኃጢአት ይስበናል። ስለዚህም ማናችንም በእግዚአብሔር ፊት ንጹሐን ሆነን ልንቀርብ አንችልም። ሁላችንም በኃጢአት ተበክለናል። በዚህ ምክንያት ነው የተለያዩ ሕግጋትን በመጠበቅ ልንድን የማንችለው። ሰው እራሱ ብቻ ሳይሆን የሚነካውም ነገር ጭምር ነው በኃጢአት የሚበከለው። ሰውዬው ኃጢአተኛ ከመሆኑም በላይ ኃጢአቱ በሚነካው ማንኛውም ነገር በመሬት ላይ፥ በትምህርት ውስጥ፥ በቴክኖሎጂ ወዘተ... ይታያል። የሰው ልጅ የሚነጻው ለምሕረት ፊቱን ወደ እግዚአብሔር ሲያዞር ብቻ ነው።

3. ሰውን ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚያቀርበው አንድ አስታራቂ ብቻ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን አስታራቂው «ሊቀ ካህኑ» ነበር። በአዲስ ኪዳን አስታራቂው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ (1ጢሞ.2፡5)። በብሉይ ኪዳን ዘመን ያለው አስታራቂ ድክመቱ የሚታየው በመጀመሪያ ሁሌ ለራሱ የኃጢአት መሥዋዕት በማቅረቡ ነው። ልክ እንደሌሎቹ ሰዎች ኃጢአተኛ በመሆኑ አስታራቂ ለመሆን ብቁ አይሆንም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ምንም ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመሆኑ በእግዚአብሔር እና በሰዎች መካከል ለአስታራቂነት ብቁ መሆን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው፤ (ዕብራ.5፡1-10 ተመልከት)።

4. የደህንነት መንገድ የሚወሰነው በእግዚአብሔር ነው እንጂ በሰው አይደለም። በምን ዓይነት ሁኔታ ቀርበው መሥዋዕታቸውን እንደሚያቀርቡ ሙሴ ለእግዚአብሔር አልነገረውም። በምትኩ ምሕረትን እንዲቀበሉ ከፈለጉ መከተል የሚገባቸውን የተወሰኑ መመሪያዎች እግዚአብሔር ሰጣቸው። ብዙ ጊዜ ሰው የራሱ የሆነ የደኅንነት መንገድ ነድፍ አውጥቶ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይፈልጋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው ምሕረትና ቅድስናን ልናገኝበት የምንችልበትን መንገድ ሊያሳየን የሚችለው።

5. የደኅንነት መንገድ ሁሌ ደም በማፍሰስ ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የእሥራኤላውያንን ኃጢአት ይቅር ሊል የሚችለው በእንስሳቱ ደም ወይም ደግሞ በሰውዬው ኃጢአት ፋንታ በሚሞተው እንስሳ አማካኝነት ብቻ ነው። ለእኛም ቢሆን የኢየሱስ ደም ወይም በእኛ ፋንታ በመስቀል ላይ በመሞቱ ነው የደኅንነት መንገድ ለሁላችንም ክፍት ሊሆን የቻለው።

25ኛ ጥያቄ፡- እነዚህን ትምህርቶች በመጠቀም በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን ምዕመናን ግንዛቤ በምን ዓይነት መንገድ ልታጠነክረው እንደምትችል በዝርዝር ጻፍ።

## አራተኛ ቀን፡-

26ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች ካነበብክ በኋላ የኢየሱስ ሞት እንዴት ከስርየት ቀን ይበልጥ የተሻለ ውጤቶችን እንዳስገኘ ዘርዝር አድርገህ ጻፍ። ዕብራውያን 7፡23-28፥ 9፡1-28፥ 10፡19-22፥ 13፡11-14።

| የስርየት ቀን | የኢየሱስ ሞት |
|---|---|
| 1. አስታራቂ የነበረው፥ ለእራሱ ኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ የሚገባውና ኃጢአተኛው ሊቀ ካህን ነው። | 1. አስታራቂው ኃጢአት የሌለበት ለሌሎች ኃጢአት ብቻ መሥዋዕት የሚያቀርበው ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። |
| 2. ሊቀ ካህኑ የሚሞትና በሌሎች | 2. ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ በመሆኑ |

| | |
|---|---|
| የሚተካ በመሆኑ ጊዜያዊ ነው። | ሌላ ሊቀ ካህን አያስፈልግም። |
| 3. ሊቀ ካህኑ ማቅረብ የሚችለው የእንስሳ መሥዋዕት ብቻ ነው። | 3. ለኃጢአታችን መሥዋዕት የሆነልን ኢየሱስ እራሱ ስለሆነ እንስሳ ። አልተጠቀመም |
| 4. ሊቀ ካህኑ የወይፈኑና የወጠጤውን ደም የእግዚአብሔር ክብር ይንሰራፋበት ወደ ነበረው ምድራዊ የመገናኛ ድንኳን ውስጥ ነበር ይዞ የሚገባው። | 4. ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን የወሰደው እውነተኛው የእግዚአብሔር በትረ መንግሥት ይገኛበት ወደ ነበረው ወደ መንግሥተ ሰማያት ነው። |
| 5. ለሚያመልከው ሰው፥ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ሁሌ ዝግ ነበር። ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በዓመት አንዴ መግባት የሚፈቀድለት ለሊቀ ካህኑ ብቻ ነው። | 5. የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት መጋረጃውን ቀዶ (ማቴ.27፡51) ወደ እግዚአብሔር የዙፋን ክፍል የሚወስደውን መንገድ ለሁሉም ሰው ክፍት አድርጓል። |
| 6. የእንስሳው መሥዋዕት ጊዜያዊ ይቅርታን ነበር የሚያስገኘው። በየዓመቱም ሁሌ መቅረብ ነበረበት። | 6. የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የተፈጸመው አንዴ ነው የሚያስገኘውም ዘላለማዊ ምሕረት ነው። |
| 7. ለኃጢአት መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው እንስሳ ሥጋ ከመኖሪያው ሥፍራ ውጪ ተወስዶ ነበር የሚቃጠለው። | 7. ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ከኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር ውጪ ነበር። |
| 8. ጊዜያዊው ምሕረት ይገኝ | 8. ዘላለማዊ የሆነው ምሕረት የተገኘው |

| | |
|---|---|
| የነበረው በሚረጨው ደም ብቻ ነበር። | በፈሰሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው። |
| 9. ደሙ መገናኛውን ድንኳን ከሰዎች እርኩሰት ያነጻ ነበር። | 9. የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተወሰደው ዘላለማዊ ቤተ መቅደስ ወደሆነው ወደ መንግሥተ ሰማያት ነው። |
| 10. ከኃጢአታቸው ይነጹ የነበሩት ሰዎች በመጾም ዝግጅት ማድረግ ነበረባቸው። | 10. ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በፀጋ ለመቅረብ በግል መንጻትና ዕለት ዕለት ምሕረትን ማግኘት ይገባናል! (ዕብራ. 10:22)። |
| 11. ወደ ምድረ በዳ ይለቀቅ የነበረው ፍየል የሕዝቡን ኃጢአት በሙሉ ነበር ይዞ የሚሄደው። | 11. የኢየሱስ ሞት ኃጢአታችንን በሞላ ነው ያስወገደልን። |

27ኛ ጥያቄ:- አሁን ላንድ አፍታ ኢየሱስን ስለፈጸመው ታላቅና ዘላለማዊ ከብሉይ ኪዳን ጊዜም ለሚበልጠው መሥዋዕቱ ምሥጋና አቅርብለት።

**አምስተኛ ቀን**:-የዚህንሳምንትትምህርትከልስናየመወያያጥቄዎቹን በመመልከት ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

በስርየት ቀን የሚደረገው ክብረ በዓል በጎልጎታ ተራራ ላይ ኢየሱስ ሲሞት የተደረገውን ክንዋኔ በሥዕላዊ መግለጫ የሚያሳይ ነው። በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ የስርየት ቀንንና የኢየሱስን ሞት ውጤቶች አነፃፅረናል። በሁሉም ላይ እንደምትመለከተው የኢየሱስ አሟሟት ብዙ መመሳሰል አለው፤ ቢሆንም የተከናወነው ሥራ በስርየት ቀን ከተፈፀመው እጅግ በጣም ይበልጣል። ይህንን ማነፃፀር የዕብራውያንን መጽሐፍ ስናጠና በስፋት እንመለከተዋለን።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) 1. ሰዎች ከተለያዩ እርኩስ ከሆኑ በሽታዎች ለመንጻት ከሚከተሉት ሥርዓቶች ምን ዓይነት መንፈሳዊ ትምህርቶችን እንማራለን?

2. እግዚአብሔር ለግላችን ጤንነት ምን ያህል እንደሚያስብ ነው የምንግረው?

ለ) ለተለያዩ በሽተኞች ከተሰጡ መመሪያዎች ውስጥ ጤንነታችንን ለመጠበቅ ስንል እኛ ልንከተላቸው የሚገቡን ነገሮች አሉን? እንዴት?

ሐ) ልቅ የሆነ ኃጢአት እንደ በሽታ የሚሰራጨው እንዴት ነው? ከአንተ ሕይወት ወይም ከቤተ ክርስቲያንህ ታሪክ ላይ በመጥቀስ ምሳሌ ስጥ።

መ) 1. ስለ ስርየት ቀን ስታጠና ያገኘሃቸውን ትምህርቶች አነፃፅር

2. እነዚህ ትምህርቶች ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው?

ሠ) 1. የሥርየትን ቀን ከክርስቶስ ሞት ጋር አነፃፅር። በምን ይመሳሰላሉ? በምንስ ይለያያሉ?

2. በብሉይ ቃል ኪዳን ሥር ሳይሆን በአዲሱ ቃል ኪዳን በመኖርህ ምክንያት ደስተኛ የምትሆነው ለምንድን ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት ስድስት

ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 17-22

## የመጀመሪያው ቀን:-

ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 17-18

በዚህ ሳምንት በዛ ያለውን የኦሪት ዘሌዋውያን ክፍል እናጠናለን። ይህም ክፍል ምዕራፍ 17-22 ያካተተ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ብዙ የተለያዩ ትዕዛዞችን እናገኛለን። ብዙዎቹ በአጠቃላይ ለእሥራኤል ሕዝብ የተሰጡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ለየት ባለ መልክ ለካህናት የተሰጡ ናቸው። እያንዳንዱን ትዕዛዝ ሳንመረምር ገረፍ ገረፍ እያደረግን እናልፋለን። ዋንኛው ነገር እግዚአብሔር እነዚህን ሕጋጋት የሰጠበትን ምክንያት ማወቁ ነው። እነዚህ ሕጋጋት እሥራኤል ለአምላኳ የምትሰጠውን ክብር የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ ቅዱስ ሕዝቧን ንጹህ ካልሆኑት ከአካባቢው ሕዝቦች የሚለዩ ነበሩ። የዚህ ክፍል ዋነኛ ጥቅሶች ኦሪት ዘሌዋውያን 18፡3-5 ናቸው። እሥራኤላውያን የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ጠብቀው እንዴት መኖር እንደሚገባቸው መገንዘብ የሚችሉት ትዕዛዛቱን ሲያጤኑ ነው፤ ስለዚህም የአጎራባች አገሮችን ባህል መከተል የለባቸውም። ትዕዛዙን በመጠበቅ ሕይወት ያገኛሉ። ትዕዛዙን ሳይጠብቁ አግኝ ያልሆኑ ሰዎችን አኗኗር ዘይቤ ከተከተሉ ግን ይቀጡ ነበር። ይህ ዛሬ ለእኛ ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው። ብዙ ጊዜ ዓለምን ለመምሰል እንፈልጋለን። ነገር ግን እንደ እሥራኤላውያን በምናደርገው ነገር ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰባችንና በምኞታችን ጭምር የተለየን እንድንሆን ነው የተጠራነው። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱስ መሆን አለብን።

2. እግዚአብሔር ለግላትን ጤንነት ምን ያህል እንደሚያስብ ነው የምንማረው?

ለ) ለተለያዩ በሽተኞች ከተሰጡ መመሪያዎች ውስጥ ጤንነታችንን ለመጠበቅ ስንል እኛ ልንከተላቸው የሚገቡን ነገሮች አሉን? እንዴት?

ሐ) ልቅ የሆነ ኃጢአት እንደ በሽታ የሚሰራጨው እንዴት ነው? ከአንተ ሕይወት ወይም ከቤተ ክርስቲያንህ ታሪክ ላይ በመጥቀስ ምሳሌ ስጥ።

መ) 1. ስለ ስርየት ቀን ስታጠና ያገኘሃቸውን ትምህርቶች አነፃፅር

2. እነዚህ ትምህርቶች ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው?

ሠ) 1. የሥርየትን ቀን ከክርስቶስ ሞት ጋር አነፃፅር። በምን ይመሳሰላሉ? በምንስ ይለያያሉ?

2. በብሉይ ቃል ኪዳን ሥር ሳይሆን በአዲሱ ቃል ኪዳን በመኖርህ ምክንያት ደስተኛ የምትሆነው ለምንድን ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት ስድስት

ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 17-22

## የመጀመሪያው ቀን፡-

ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 17-18

በዚህ ሳምንት በዛ ያለውን የኦሪት ዘሌዋውያን ክፍል እናጠናለን። ይህም ክፍል ምዕራፍ 17-22 ያካተተ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ብዙ የተለያዩ ትዕዛዞችን እናገኛለን። ብዙዎቹ በአጠቃላይ ለእሥራኤል ሕዝብ የተሰጡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ለየት ባለ መልክ ለካህናት የተሰጡ ናቸው። እያንዳንዱን ትዕዛዝ ሳንመረምር ገረፍ ገረፍ እያደረግን እናልፋለን። ዋንኛው ነገር እግዚአብሔር እነዚህን ሕግጋት የሰጠበትን ምክንያት ማወቁ ነው። እነዚህ ሕግጋት እሥራኤል ለአምላኳ የምትሰጠውን ክብር የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ ቅዱስ ሕዝቧን ንጹህ ካልሆኑት ከአካባቢው ሕዝቦች የሚለዩ ነበሩ። የዚህ ክፍል ዋነኛ ጥቅሶች ኦሪት ዘሌዋውያን 18፡3-5 ናቸው። እሥራኤላውያን የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ጠብቀው እንዴት መኖር እንደሚገባቸው መገንዘብ የሚችሉት ትዕዛዛቱን ሲያጤኑ ነው፤ ስለዚህም የአጎራባች አገሮችን ባህል መከተል የለባቸውም። ትዕዛዙን በመጠበቅ ሕይወት ያገኛሉ። ትዕዛዙን ሳይጠብቁ አማኝ ያልሆኑ ሰዎችን አኗኗር ዘይቤ ከተከተሉ ግን ይቀጡ ነበር። ይህ ዛሬ ለእኛ ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው። ብዙ ጊዜ ዓለምን ለመምሰል እንፈልጋለን። ነገር ግን እንደ እሥራኤላውያን በምናደርገው ነገር ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰባችንና በምኞታችን ጭምር የተለየን እንድንሆን ነው የተጠራነው። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱስ መሆን አለብን።

ምንም እንኳ ትምህርቱ የተከፈለው በሦስት ቀናት ቢሆንም በውስጡ ያሉት ትምህርቶች ረዘም ስለሚሉ ከፈለክ አራት ቀን ሰጥተኸው ልትጨርሰው ትችላለህ።

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 17 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ፡-

1ኛ ጥያቄ፡- እሥራኤላውያን ለመሥዋዕት የሚያቀርቧቸውን እንስሳት እንዲያርዱ የታዘዙት የት ነው?

2ኛ ጥያቄ፡- ይህንን የሚያደርጉበት ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው? (ቁጥር 5፥7)

3ኛ ጥያቄ፡- ደም እንዳይበሉ የታዘዙት ለምንድን ነው?

4ኛ ጥያቄ፡- ሊበሉት የሚችሉትን አውሬ ከገደሉ ምን ማድረግ ነበረባቸው?

5ኛ ጥያቄ፡- ሞቶ የተገኘን የእንስሳ ሥጋ እሥራኤላውያን መብላት ይፈቀድላቸው ነበር?

የኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 17 ትምህርት ትኩረት የሚሰጠው በእንስሳው ደም ትርጓሜ ላይ ነው። ኦሪት ዘሌዋውያን 17፡11 «የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፥ ደሙም ከሕይወት የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት» ይላል። በብሉይ ኪዳን እሥራኤላውያን ለእንስሳው ደም በተለየ ለመሥዋዕት በሚቀርበው ደም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው። በመጀመሪያ ደሙ ሕይወትን የሚያመለክት በመሆኑ በአክብሮት ሊያዩት ይገባል። ሁለተኛ የዚህ ደም መፍሰስ ነው ለኃጢአተኛው ምሕረትና ስርየትን የሚያስገኝለት። ምሕረትን የሚያስገኝ ማንኛውም ዓይነት መሥዋዕት በመሠዊያው ላይ ደም የመርጨትን ሥርዓት ያካተተ ነው። ምሕረት የማስገኘት ኃይል የነበረው ደሙ ራሱ አልነበረም። ደሙ እግዚአብሔር ለምሕረት የደነገገውን መንገድ የሚያመለክት ነበር። ስለዚህም ደሙ የእንስሳውን ሕይወት የሚያመለክት በመሆኑ ይህ ለመሥዋዕት የሚፈሰው ደም እንስሳው በኃጢአተኛው ፋንታ እንደሞተ የሚያመለክት ነው። በኃጢአተኛው ፋንታ የሞተው ኃጢአተኛው እንዳይሞት ነው።

ለመሥዋዕት የሚቀርበውን ደም ዓላማ ማወቁ፥ ለአዲስ ኪዳን ለሚኖረን ግንዛቤ መሠረት ይሆናል። አዲስ ኪዳን በጠቅላላው የሚያተኩረው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ባስገኘው ውጤት ላይ ነው። በዚህም ሥፍራ ደሙ የሚያመለክተው የኢየሱስን ሞት ነው። በእኛ ፋንታ በመስቀል ላይ በመሞቱ ለእኛ ስርየትንና ምሕረትን አስገኝቶልን ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ኅብረት እንዲኖረን ሆኗል።

6ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከትና የኢየሱስ ደም የፈጸመውን ሥራ በዝርዝር ጻፍ፤ ሮሜ 5፡9፥11፥ ኤፌ.1፡7፥ ዕብራ.10፡11፥ ራዕይ 12፡11።

በምዕራፍ 17 ላይ እግዚአብሔር እንስሳትን ስለ መብላትና መሥዋዕት አድርጎ ስለ ማቅረብ የሰጠው መመሪያ አለ። አምስት ሁኔታዎች ላይ ድንጋጌ አሳልፏል። በመጀመሪያ በእሥራኤላውያን መኖሪያ ሠፈር አካባቢ የመሥዋዕቱን እንስሳ

የመግደሉን ነገር እንመለከታለን፤ (ቁጥር 1-9)። ይህ ሕግ የሚመለከተው እንስሳን ለምግብነት የሚገድሉ ሰዎችንና የሚቃጠለውን ወይም የደኅንነት መሥዋዕት የሚያቀርቡትን ነው። ይህ ሕግ ለእሥራኤላውያን የተሰጣቸው ወደ ከነዓን ገብተው ከተበታተኑ በኋላ ሳይሆን በምድረ በዳ ውስጥ ሲንከራተቱ ስለ ነበር ነው። ለመሥዋዕት የሚሆን ማንኛውም ንጹህ እንስሳ መገደል የነበረበት በመገናኛ ድንኳኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነበር። ይህ የሆነበት ሁለት ምክንያቶች አሉ፡-

መጀመሪያ፡- እሥራኤላውያን የእግዚአብሔርንና የካህናቱን ድርሻ በትክክል ማስረከባቸውን እርግጠኞች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህም ከሆነ የካህናቱ ሰብዓዊ ፍላጎቶች የተሟሉ ይሆናሉ፤ በተጨማሪም እሥራኤላውያን የበረከት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ ይረዳሉ። 2) ሕዝቦቹ ለሌሎች አማልክት መሥዋዕት እንደማያቀርቡ ካህናቱ እርግጠኞች ሊሆኑ ይችላሉ። በቁጥር 7 ላይ እሥራኤላውያን ለሰይጣን መሥዋዕት እንዳያቀርቡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። በሌላ አነጋገር እንስሳዎቻቸውን ገብዕ ምድር ሳሉ ያመልኳቸው ለነበሩት የፍየል አማልክት እንዳይሰዉ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች አማልክት በስተጀርባ የአጋንንቶች ኃይል እንዳለ ያሳየናል፤ (1ቆሮ.10፡20)።

ይህን ሕግና በዚህ ምዕራፍ የተደነገጉትን ሕግጋት ያላከበረ ሰው «ይጠፋ» ነበር። ይህም ሰውዬው የሚፈረድበትን ቅጣት ያመለክታል። ቅጣቱ ምናልባት ሰውዬውን ከመኖሪያው ሠፈር ማግለል፥ ወይም ደግሞ በአጭሩ ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር እርግማን ሥር ይኖር ነበር፤ ይህም ለዘላለማዊው ፍርድ የሚደረግ መንፈሳዊ ሞት ማለት ነው።

ሁለተኛ፡- ደም እንዳይበሉ ወይም ከሥጋው ላይ ደሙን በደንብ ሳያጠነፍፉ እንዳይበሉ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸዋል፤ (ቁጥር 10-12)። ይህ ሕግ የተሰጠው ለእሥራኤላውያን ብቻ ሳይሆን በእሥራኤል ምድር ለሚኖር ማንኛውም ሰው ጭምር ነበር። በእሥራኤል የሚኖሩ ሰዎች እሥራኤላዊ ባይሆኑም የእግዚአብሔርን ህግ ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

ሦስተኛ፡- ለመሥዋዕት መቅረብ የማይችሉ ነገር ግን ሰው ሊበላቸው የሚችል የዱር አራዊቶችን በተመለከተ የወጡ ድንጋጌዎች አሉ፤ (ቁ. 13- 14)። አሁንም ደሙን ለየት ባለ ጥንቃቄ በአክብሮት እንዲመለከቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። ያደኑትን እንስሳ ደሙን በደንብ ካፈሰሱ በኋላ በአፈር እንዲከድኑት ታዘዋል። ይህም እግዚአብሔር እንስሳውን ሠርቶ ከፈጠረበት አፈር ነፍሱ እንደምትገባ የሚያመለክት ነው።

አራተኛ፡- ሞቶ የተገኘን እንስሳ ስለ መብላት የተሰጡ ድንጋጌዎች አሉ፤ (ቁ.15-16)። በሥርዓቱ መሠረት ያልተገደሉ እንስሳትን ሥጋ እሥራኤላውያን እንዳይበሉ በቅድሚያ ታዘዋል። ሞቶ የተገኘን እንስሳ ሥጋ ቢበሉ ይረክሱ ነበር። በሥርዓቱም መሠረት በምዕራፍ 11 ላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መከተል

የሚቃረን ነው። ከቅርብ ዘመድ ጋር መጋባትን እነርሱ እንደ መልካም ነገር ነበር የሚቆጥሩት (ለምሳሌ:- አብርሃም በአንድ በኩል እህቱ የሆነችውን ሴት አግብቷል)።

ሳይንቲስቶች ዘመዳሞች ሆነው ከሚጋቡ ሰዎች አካባቢ የሚወለዱት ሕፃናት ብዙ ጊዜ በሽተኛ እንደሚሆኑ ይናገራሉ። ስለዚህም እግዚአብሔር የሕዝቡን ጤንነት በመጠበቅ ላይ ነው ማለት ነው።

2. በወር አበባቸው ወቅት ሚስቶቻቸውን እንዳይገናኙ ታዘዋል፤ (ቁ.19)። ከዚህ በፊት እንዳየነው ይህ በወር አበባዋ ጊዜ የሚፈሳት ደም የመርገምዋን ጊዜ የሚያስታውስ በመሆኑ እሷና የምትነካው ነገር በሙሉ በሥርዓቱ መሠረት እርኩስ ነበር። እንደምንረዳው ሴትየዋ እራስዋ «ኃጢአተኛ» አልነበረችም። ነገር ግን፥ ይህ እንግዳ የሆነው የወር አበባ እሷንና ቤተሰቧን የኃጢአትን መዘዝ የሚያስታውሳቸውና የሚያመለክታቸው ነገር ነው። ይህ ሕግ ሴትዮዋን በወር አበባዋ ወቅት ወሲባዊ ግንኙነት በማድረግዋ ሊሰማት ከሚችለው ተጨማሪ ሕመም የሚጠብቅ ነው።

3. ከባልንጀራው ሚስት ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግ የለባትም፤ (ቁ.20)።

4. ሞሎክ ለተባለው ለከነዓናውያን አማልክት፥ ልጆቻቸውን እንዳይሰዉ አዟቸዋል፤ (ቁ.21)። ምንም እንኳ በወሲባዊ ግንኙነት አማካኝነት የሚመጣ ኃጢአት ባይሆንም እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ወሲባዊ ግንኙነቶች መካከል አብሮ ነው የተጠቀሰው፤ (2ኛ ዜና 33፡6 ላይ በይሁዳ ይህ ነገር እንዴት እንደተፈጸመ ይገልፃል)።

5. ከተመሳሳይ ፆታ ጋር መተኛት የለበትም፤ (ቁ.22)። ልክ ዛሬም እንደሚገኙት የዓለም አህጉሮች ከተመሳሳይ ፆታ ጋር መተኛት በዚያ ጊዜ ይኖሩ የነበሩትም አሕዛቦች ዘንድ እንደ ስሕተት አይቆጠርም ነበር። ሆኖም በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ይህ ልማድ የተከለከለ ነው።

6. ከእንስሳ ጋርም መተኛት የለባቸውም ነበር፤ (ከቁ.23-30)። ይህ በከነዓን ምድር የተለመደ ሥርዓት ነበር፤ ከዚህም በመነሣት የሕዝቡ አኗኗር ምን ያህል የረከሰ እንደነበር ልናይ እንችላለን። እግዚአብሔርም እንደተናገረው «በጣም የረከሱ በመሆናቸው ምድሩንም ሳይቀር በክለውታል»። ያ ምድር ሊነጻ የሚችለው አረመኔውን ሕዝብ ከቦታው በማባረር ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ነው እግዚአብሔር በከነዓን ውስጥ የሚኖሩትን መንግሥታት በሙሉ እሥራኤላውያን እንዲያጠፏቸው ትዕዛዝ የሰጠው። ከዚህም ትዕዛዝ ጋር እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን የከነዓናውያንን እርኩስ ሥርዓት ከተከተሉ እነርሱ ራሳቸው ምድሩን እንደሚበክሉና እራሳቸውም ያንን ምድር እንዲለቁ እንደሚደረጉ አስጠንቅቋቸዋል። ይህም ነገር ሆኖ እግዚአብሔር እሥራኤልንና ይሁዳን በምርኮ እንዲያዙ አድርጓል። እሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 20 እነዚህን ሕግጋት ያልጠበቁ ሰዎች ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚቀበሉ በዝርዝር ያስረዳል።

በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱት ብዙዎች ሕግጋት ዛሬ እኛም ልንጠብቃቸው የሚገቡን ናቸው። አዲስ ኪዳን ወሲባዊ ግንኙነትን በተመለከተ ንጽሕናችንን እንድንጠብቅ ጥሪውን ያስተላልፋል። ስለዚህም በአዲስ ኪዳን እንዳናመነዝር ከተመሳሳይ ፆታ ጋር

የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳናደርግ ከእንስሳት ጋር እንዳንገናኝ ወዘተ... ያስጠነቅቀናል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ግን በወር አበባዋ ጊዜ ከሴት አትገናኝ የሚል ትዕዛዝ አለመኖሩን ማስተዋሉ ይጠቅማል። በዚህ ምክንያት ይህ የብሉይ ኪዳን ሕግ በመሆኑ ዛሬ ላሉ ክርስቲያኖች ቀጥተኛ የሆነ ተግባራዊነት አይኖረውም። ሆኖም ለሚስቶቻችን ከምንሰጠው ክብር የተነሣ ተገቢ ያልሆነ ችግር እንዳናስከትልባቸው ስኁል ይሆነን መመሪያ መጠበቁ ይጠቅመናል።

11ኛ ጥያቄ:- ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የተለመዱት የወሲባዊ ግንኙነት ኃጢአቶች ከተጠቀሱት ውስጥ የትኞቹ ናቸው?

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የማይታዩት የወሲባዊ ግንኙነት ኃጢአቶች ከተጠቀሱት ውስጥ የትኞቹ ናቸው?

ሐ) የእነዚህን ኃጢአቶች ልምድ ያላቸው አማኞች አሉ?

እንደ እግዚአብሔር ልጆች ቅዱስና ንጹሕ ሕዝብ እንድንሆን ነው የተጠራነው። ይህ ንጽሕና ወሲባዊ ግንኙነትንም የሚያጠቃልል ነው! (ዕብራ. 13፡4)። ወሲባዊ ግንኙነት ሊኖረን የሚችለው ጋብቻ ከፈጸምነው ሰው ጋር ብቻ ነው። ሌላው የምናደርገው ወሲባዊ ግንኙነት በሙሉ በእግዚአብሔር ዓይን ኃጢአት ነው። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ በዚህ ሕግ ላይ ጭማሪ አድርጓል። በሕጉ መሠረት ያልተደገፈ ነገርን ብቻ ማድረጉ ሳይሆን በልባችን የምናስበው የተዛዛተ አስተሳሰብ ሁሉ ኃጢአት ነው።

12ኛ ጥያቄ:- ማቴዎስ 5፡27-30 አንብብ። በወሲባዊ ግንኙነት አማካኝነት የሚመጣ የኃጢአት ክብደት እንዴት አድርጎ ነው ኢየሱስ የገለጸው?

## ሁለተኛ ቀን:- ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 19

* ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 19 አንብብ።

13ኛ ጥያቄ:- ሕይወታቸውን በቅድስና ለመጠበቅ ሲሉ! የማንን ምሳሌነት ነው መከተል ያለባቸው?

14ኛ ጥያቄ:- ሕግጋቱን በሦስት ክፍል ከፈላቸው።

ሀ) የአምልኮ ልማዶች

ለ) ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያመለክቱ።

ሐ) የተለያዩ ሕግጋት።

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 19 እሥራኤላውያን ቅድስናቸው ሊያሳዩባቸው የሚጠብቁዋቸውን ሕግጋት ያካተተ ነው። አሁንም እግዚአብሔር የቅድስናቸው መለኪያ የእርሱ ባህርይ እንደሆነ ለእሥራኤላውያን ያመለክታቸዋል። የእግዚአብሔር ቅድስና የሚያጠቃልለው የእርሱን ታላቅነት ብቻ ሳይሆን ከኃጢአት መለዩቱንና ለፍጥረታት ሁሉ ያለውን የተቀደሰ ዕቅድንም ጭምር ያካተተ ነው። ልክ እንደዚሁ የእኛ ቅድስና ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ወይም ከተወሰኑ ኃጢአቶች ብቻ የሚለየን

አይደለም። ቅድስና በሕይወታችን በሁሉም አቅጣጫ ልንወስደው የሚገባንን በበጎ ሕሊና የተደገፈ ሥነ-ምግባር ጭምር ያካተተ ነው።

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 19 በተለያየ ክፍል የሚከፋፈሉ ሕግጋትን የያዘ ነው። ምዕራፉን በቅደም ተከተል ከማጥናት ይልቅ ሕግጋቱን በሦስት ክፍል ከፋፍለን እናጠናቸዋለን።

1. የአምልኮ ልምዶችን በተመለከተ የተሰጠ መመሪያ

ሀ) ሰንበትን እንደ ዕረፍትና እንደ አምልኮ ጊዜ መጠበቅ አለባቸው፥ (ቁጥር 3፡30)።

ለ) የደኅንነት መሥዋዕት ሲያቀርቡ ሥጋውን የመብላቱን ሥርዓት በተገቢው መንገድ መጠበቃቸውን ማረጋገጥ ነበረባቸው፤ (ከቁጥር 5-8)።

ሐ) ሐሰተኛ አምልኮዎችን ልማድ እንዳይኖርባቸውም ታዝዞዋል። ይህም ጣዖት ብቻ ማምለክ ሳያሆን፤ (ቁጥር 4) ወደ አስማተኞች ሞራ ገላጮች መናፍስት ጠሪዎችና ጠንቋዮችም አለመሄድን የሚያጠቃልል ነው፤ (ቁጥር 26፥ 31)። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በሰይጣን ኃይል አማካኝነት የሚሠሩና ሰዎችን የሚያስቱ ናቸው።

2. ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ግንኙነት በተመለከተ የተሰጠ መመሪያ።

15ኛ ጥያቄ፡- ሉቃስ 10፡25-37 አንብብ።

ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን ትዕዛዛት የሚያጠቃልሉ ሁለቱ ትዕዛዛት የትኞቹ ናቸው?

ለ) እንደ ባልንጀራችን ልንቆጥራቸው የሚገቡን እነማንን ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ከእኛ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በሙሉ እንደ ባልንጀራችን ነው የሚቆጠሩት። እግዚአብሔር እንዴት እራሳችንን ከኃጢአት እንደምንለይ ብቻ ሳይሆን እንዴት አድርገን የርሱን ጽድቅና ፍቅር ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ እንደምናንፀባርቅም ይገደዋል። በዘሌዋ.19 ያሉት ብዙዎቹ ሕግጋት ይህንን ሐሳብ ያንፀባርቃሉ።

ሀ) ከምድራቸው መከር ላይ በማስተረፍ ለድሆች እንክብካቤ ማድረግ ነበረባቸው፤ (ከቁጥር 9-10)።

16ኛ ጥያቄ፡- ዛሬ እኛ ገበሬዎች ባንሆንም ለድሆች እንክብካቤ ልናደርግ የምንችልባቸው መንገዶች ለምሳሌ ያህል ምንና ምን ናቸው?

ለ) ከባልንጀሮቻቸው ጋር በታማኝነት መኖር ነበረባቸው። ይህም ባልንጀራቸውን አለመካድ፥ አለመስረቅ፥ እርስ በእርስ በሐሰት አለመነጋገር፥ በሐሰት አለመማልና በባልንጀራቸው ላይ ግፍ አለማድረግ ማለት ነው፤ (ከቁጥር 11-13)። በተጨማሪም ንግድ ላይ ገዢውን በማይጎዳ መልክ በትክክል መሥራትንም የሚጨምር ነው፤ (ከቁጥር 35-36)።

ሐ) ስለ እነርሱ ተቀጥረው የሚሠሩትን ሠራተኞች በትክክል ማስተዳደር ነበረባቸው፤ (ቁጥር 13)።

መ) አካለ ስንኩል ለሆኑ ሰዎች ማሰብ ነበረባቸው። በእነዚህ ሰዎች ላይ ግፍ መሥራት የለባቸውም ነበር፤ (ቁጥር 14)።

ሠ) ለባለጠጋውና ለድሃው እውነተኛ የሆነ ፍርድ መሥጠት ነበረባቸው። ምንም ዓይነት አድልዎ አይፈቀድም ነበር፤ (ቁጥር 15)።

ረ) አፋቸውን በመሰብሰብ፥ ባልንጀራቸውን እንዳይሸነግሉ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው፤ (ቁጥር 16)።

ሰ) የባልንጀራቸውን አካልና ሕይወት እንዳይጎዱ ሲባል ሁሉን ነገር በጥንቃቄ መሥራት ነበረባቸው፤ (ቁጥር 16)።

ሸ) ስሜታቸውን በመጠበቅ፥ በሌሎች ሰዎች ላይ ጥላቻ እንዳያድርባቸው መጠንቀቅ ነበረባቸው፤ (ቁጥር 17)።

ቀ) ሌሎች ሲሳሳቱ በግልጽ በመገሠፅ ከእነርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ንጹሕ ማድረግ ነበረባቸው። ይህንን የሚያደርጉት የሰዎቹን የተሳሳተ አስተሳሰብ ለውጠው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንዲኖሩ ለማድረግ ነው። (ቁጥር 17)።

በ) ይቅር ለማለት ፈቃደኞች መሆን ነበረባቸው እንጂ ሌሎች ሲበድሏቸው ለመበቀል መነሣሣት የለባቸውም ነበር፤ (ቁጥር 18)። በትዕግስት የእግዚአብሔርን የፅድቅ ፍርድ መጠበቅ ነበረባቸው። ሌሎች እኛን ይቅር ብለው ፍቅራቸውን እንዲገልፁልን እንደምንፈልግ ሁሉ እነርሱም ለሌሎች ፍቅራቸውን መግለጽ አለባቸው።

ተ) ጽድቅንና የወሲባዊ ግንኙነታቸውን ንጽሕና በተመለከተ ጥንቃቄ መውሰድ ነበረባቸው፤ (ከቁጥር 20-22)። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ባሮች የጌታቸው ንብረት እንደሆኑ ነበር የሚቆጠሩት። ጌታውም የፈለገውን ነገር ሊያደርጋባቸው ይችላል። ሆኖም ብሉይ ኪዳን ባሮቹ የእግዚአብሔር ፍጡር በመሆናቸው መጨቆን እንደሌለባቸው በመደንገግ የጌታውን ነፃነት ውስን አድርጎታል። ስለዚህም ከሴት ባሪያው ጋር የተኛ ሰው የበደል መሥዋዕት በማቅረብ እንደ ኃጢአተኛ ከእግዚአብሔር ይቅርታን ሊሻ ይገባዋል። በዚህ ቦታ ጥፋቱ የሰውዬው ነው።

ቸ) ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ለግልሙትና መስጠት የለባቸውም (ቁጥር29)። ይህ ትዕዛዝ ምናልባት በዚያን ጊዜ ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ለጣዖት አምልኮና ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ለግልሙትና እንደሚሰጡ ሊያመለክተን ይችላል።

ኃ) ለሽመግሉ ሰዎች ክብር መስጠት ነበረባቸው፤ (ቁጥር 32)። ይህ ትዕዛዝ የተሰጠው ወጣቱ እንደልማዱ በትምህርት ከእርሱ በታች ስለሆኑ ወይም ሽምግል ብለው ዓቅም ስለሚያንሳቸው ሽማግሌዎችን እንዳይንቁ ለመጠበቅ ነው።

ነ) ከጎሣ ወይም ከዘመድ ካልሆነ ሰው ፍቅር ማሳየት ነበረባቸው። እነዚህ ሰዎች ባዕዳን ነበሩ፤ (ቁጥር 33)።

ብዙ ጊዜ እንግዶች በደንብ አይስተናገዱም ነበር። መብታቸውን የሚያስጠብቅላቸውም ሰው አልነበራቸውም፤ ይዘረፉም ነበር። እግዚአብሔር ግን ለእሥራኤላውያን እነዚህን ልክ እንደራሳቸው አድርገው ያከብሯቸው ዘንድ ትዕዛዝ ሰጠ።

17ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልንጠብቃቸው የሚገቡን ሕግጋት የትኞቹ ናቸው?

ለ) አማኝ ባልሆኑ ሰዎች የማይጠበቁት ሕግጋት የትኞቹ ናቸው?

ሐ) ክርስቲያኖች ለመጠበቅ የሚያስቸግራቸው የትኞቹ ሕግጋት ናቸው?

የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችውንንና ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምናሳየው ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ነው። በፍቅርና በክብር ሰዎችን የማንቀርብ ከሆነ እግዚአብሔርን እንወደውም ማለት ነው። የምንገናኛቸው ሰዎች ደሃም ሆኑ አካለስንኩል ያረጁ ወይም የተናቁ በፍቅር ለመቅረብ እንጥራለን? የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ሁሉ እያሳየን ነው?

3. ለእሥራኤላውያን የተሰጡ የተለያዩ ሕግጋት

ሀ) እንስሳቱን ዘሩንና ልብሱን እንዳይደባልቁ ወይም ሁለት ዓይነት እንዳያደርጉ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸዋል፤ (ቁጥር 19)። ይህ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ምክንያት አናውቅም። ምናልባትም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከዓለም ጋር በጋብቻ፤ በአምልኮና በሌሎች ልማዶች የተለዩ መሆናቸውን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ቅድስና መለየት ማለት ነው።

ለ) ፍሬውን ከዛፉ ላይ ለአራት ዓመት ያህል አይለቅሙትም ነበር፤ (ከቁጥር 23-25)። ለሦስት ዓመታት ያህል ፍሬውን በዛፉ ላይ ይተዉታል። በአራተኛው ዓመት ፍሬው በሙሉ የእግዚአብሔር ይሆናል፤ በአምስተኛው ዓመት ብቻ ነው ፍሬው ሊበላ የሚችለው። ይህ ፍሬ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ የሚያመለክት ሳይሆን ይህን በማድረጋቸው ፍሬው ይበዛላቸዋል፤ የዛፉም ሕይወት በደንብ ይጠበቃል።

ሐ) ደም ያለበት ሥጋ እንዳይበሉ አሁንም ደግሞ ያስታውሳቸዋል፤ (ቁጥር 26)።

መ) አማኝ ያልሆኑ ሰዎች በለቅሶ ጊዜ የሚከተሏቸውን ሥርዓቶች እንዳይከተሉ ታዘዋል፤ (ከቁጥር 27-28)። ይህም ለሞተው ዘመዳቸው ሲያለቅሱ ፀጉራቸውን አይቆረጡም ወይም ገላቸውን አይጎዱም ማለት ነው። ማዘኑ ይፈቀድላቸዋል፥ ቢሆንም ኀዘናቸውን መግለፅ የነበረባቸው አማኝ እንዳልሆኑ ሰዎች አልነበረም።

18ኛ ጥያቄ:- ዛሬ እንዴት መኖር እንዳለብን እነዚህ ትዕዛዛት ምን ያስተምሩናል?

# ሦስተኛ ቀን:-

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 20

* ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 20 አንብብ።

19ኛ ጥያቄ:- የሚያስቀጡ የተለያዩ ኃጢአቶችን ዘርዝረህ ጻፍ።

20ኛ ጥያቄ:- ለተለያዩ ኃጢአቶች የሚሰጡትን የተለያዩ የቅጣት ዓይነቶችን በዝርዝር ጻፍ።

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 20 የእግዚአብሔርን ልጆች ለቅጣት የሚያበቁ ኃጢአቶችን ያጠቃለለ ነው። እሥራኤላውያን የኀብረተሰቡን ቅድስና ለመጠበቅ ሳይጥሩ ዝም ብለው ኃጢአትን ብቻ እንዳይመለከቱ ታዘዋል። ስለዚህም እያወቁ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጥሱ ሁሉ መቀጣት ነበረባቸው። እንዲያውም አንድ ሰው ሰዎች ኃጢአት ሲሠሩ አይቶ እንዲቀጡ ባያደርግ ሰውዬው ራሱ ይቀጣ ነበር፤ (20፡4-5)። እነዚህ ትዕዛዛትና ቅጣቶች ተግባራዊ የሚሆኑት ለእሥራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ በፈቃደኝነት በእሥራኤል ምድር ለሚኖሩ ሰዎች ጭምር ነበር።

በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት ብዙዎቹ ኃጢአቶች ቅጣታቸው ሞት ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ለሞት የሚዳርጉ ኃጢአቶች ዝርዝር ይገኛል። አንዳንዶች በድንጋይ ተደብድበው ነበር የሚሞቱት፤ አንዳንዶች ደግሞ ይቃጠላሉ ወይም በሞት ፍርድ ውሳኔ ይገደላሉ።

1. ልጆቻቸውን መሥዋዕት በማቅረብ ሞሎክን የሚያመልኩት ወይም ደግሞ ሌሎች ለሞሎክ ሲሰጢ አይተው ዝም የሚሉ ሁሉ፥
2. ቤተሰቦቻቸውን የሚያዋርዱ፥
3. ከሌላ ሰው ሚስት ጋር የሚያመነዝር ሰው አመንዝራውም አመንዝራይቱም ይገደሉ ነበር።
4. ከቅርብ ዘመዶቻቸው ጋር የሚያመነዝሩ፥
5. ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት የሚያደርጉ፥
6. ከእንስሳት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉ፥
7. ጠንቋዮችንና መናፍስት ጠሪዎች የሆኑ ሁሉ ለሞት የሚዳርጉ ኃጢአቶች ነበሩ።

«ከሕዝባቸው መካከል ተለይተው ይጥፉ የሚል ፍርድ የሚያሰጡ ኃጢአቶችም ነበሩ። ምንም እንኳን ይህ ሞትን የሚያመለክት ቢሆንም የእግዚአብሔር ፍርድ በእነርሱ ላይ እንደሆነ የሚያመለክትም ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ከእሥራኤል ሕዝብ የተገለሉ መሆናቸውን የሚገልጽ ሊሆን ይችላል።

ለሞት ቅጣት የማይዳረጉት:-

1. ከቅርብ ዘመዶቻቸው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉ
2. እያወቁ በወር አበባዋ ወቅት ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉ ናቸው።

የአንዳንዶቹ ኃጢአት ቅጣት የሚፈጸመው በእግዚአብሔር ብቻ ነበር። የአንዳንዶቹ ቅጣት መካንነት ሲሆን የአንዳንዶቹ ደግሞ አልተጠቀሰም።

የእሥራኤል ሕዝብ ሕይወታቸውን በኅብረ ኅብነት ሆነ በሚከተሉት ልማድ እራሳቸውን (ንጹሕ) አድርገው አንጠብቅም ካሉ ልክ እንደ ከነዓናውያን ከቃል ኪዳኑ ምድር እንደሚያስወጣቸው እግዚአብሔር ምሎአል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ትኩረት የተሰጠው የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅድስናውን እንዴት መጠበቅ እንደሚገባው ነው፥ (ከቁጥር 7-8፥ 22-24፥ እና ቁጥር 26 ተመልከት)። ይህ ቅድስና አንዳንዴ ይጠበቅ የነበረው በእግዚአብሔር ቃል ኪዳንና ትዕዛዝ ሥር ለመኖር ፈቃደኛ ያልሆኑትን ሰዎች በመቅጣት ነበር። ሕዝቡ በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዳይቀበል ሲባል በደለኛው ክፍል ብቻ ይቀጣ ነበር። ከሌሎቹ ሕዝቦች ለይቶ እሥራኤላውያንን ያወጣ እግዚአብሔር ነው። መለየታቸውን መጠበቅ ነበረባቸው።

በአዲስ ኪዳን በኅብረትም ሆነ በግል ቅድስናችንን እንድንጠብቅ ታዘናል። ምንም እንኳ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅድስናችንን ለመጠበቅ ስንል የሞት ቅጣት ባንፈርድም ሕይወታቸውን በንጽሕና የማይጠብቁትን ሰዎች እግዚአብሔር በሞት ይቀጣል። (ለምሳሌ የሐዋርያት ሥራ 5፡1-11፥ 1ቆሮ.11፡30 ተመልከት)። ሆኖም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጸሙት ኃጢአቶች ለንሰሐ መቅረባቸውን ወይም በደሉን የፈጸመው ሰው ተገቢ የሆነ የሥነ ሥርዓት ቅጣት መቀበሉን የማረጋገጥ ሐላፊነት ለእኛ ተሰጥቶናል፥ (ማቴዎስ 18፡15-17፥ 1ቆሮ.5)።

21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በሕይወትህ ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን ቅድስና ተቆርቁረህ የገለጽከው እንዴት ነው?

ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ለቅድስና ተቆርቁራ በኃጢአት ፀንተው በሚኖሩ ሰዎች ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የገለጸችው እንዴት ነው?

# አራተኛ ቀን፡-

አሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 21-22

* አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 21 አንብብ።

22ኛ ጥያቄ፡- ይህ ምዕራፍ በተለይ የሚያመለክተው እነማንን ነው?

23ኛ ጥያቄ፡- ካህኑ በድኑን እንዳይነካ የተከለከለው ለምንድን ነው?

24ኛ ጥያቄ፡- አንድ ካህን ሴት ልጁ ጋለሞታ ከሆነችበት ምን ማድረግ ነበረበት?

25ኛ ጥያቄ፡- ካህኑ እንዳያገባ የተከለከለው ምን ዓይነት ሴት ናት? እንዲያገባስ የተፈቀደለት ምን ዓይነት ሴት ናት?

26ኛ ጥያቄ፡- ነውር ያለበት ካህን እንዳያደርጋቸው የተከለከሉ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

አሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 17-20 የሚያተኩረው በአጠቃላይ የእሥራኤል ሕዝብ ማድረግ በሚገባቸው ነገር ላይ ነው። አሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 21-22 ደግሞ

የተጻፈው ለአሮንና ለካህናቱ ነው። እነዚህ ምዕራፎች ካህናቱ ቅድስናቸውን ጠብቀው እግዚአብሔርን በመገናኛው ድንኳን እንዴት ማገልገል እንደሚችሉ የሚያሳዩ መመሪያዎችን ያጠቃልላሉ።

የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመሩ ሰዎች ከተራው ሕዝብ ይበልጥ ቅድስናቸውን የመጠበቅ ሐላፊነት አለባቸው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሁላችንም ቅዱሳንና ንጹሃን እንድንሆን ቢፈልግም የመሪዎቹ ሕይወት የቅድስናን ምሳሌነት ሊያንፀባርቅ ይገባዋል፤ በጣምም አስፈላጊ ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር መሪዎቹ እውነተኛ መሪ ለመሆን ከፊለት ሊከተሏቸው የሚገባቸውን መመሪያዎች ለየት አድርጎ ያቀርብላቸዋል። መሪው ቅድስናውን ሳይጠብቅ ምሳሌ የሚሆን ኑሮ በሕዝቡ ፊት የማይኖር ከሆነ ሕዝቡ የራሱን ቅድስናና የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አይጠብቅም።

27ኛ ጥያቄ:- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊ ሕይወት የምዕመናኑን መንፈሳዊ ሕይወት በምን ዓይነት መንገድ ነው ሊነካና ሊለውጥ የሚችለው?

ካህናቱ በእግዚአብሔር ፊት መገናኛ ድንኳን ውስጥ እንዲቆሙና ሕዝቡን በእርሱ ፊት እንዲወክሉ የተመረጡና በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ለሕዝቡ የሚማልዱ ናቸው። ስለዚህም የሞራልም ሆነ የሥርዓት ነውረኛነትን ይዘው ወደ አምልኮው ሥፍራ እንዳይቀርቡ የተለየ ጥንቃቄ መውሰድ ይገባቸው ነበር። ቆመው የሚሠሩት በእግዚአብሔር ፊት ስለሆነ ሕይወታቸው በቅድስና የተሞላ መሆን ይገባዋል፤ (ቁጥር 6 እና 8)። ቅድስናቸውን በመላው ሕይወታቸው ሊገልፁት የሚያስፈልገው:- በድን የሆነውን ነገር ባለመንካትና የሚያገቧቸው ሴቶች ነውር ያለባቸው ወይም የሌለባቸው በመሆን ነው። ኃጢአትን የሚያመለክት በዓለም ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር እና የኃጢአት መንስኤ የሆነ ማንኛውም ነገር ወደ እግዚአብሔር ፊት እንዳይቀርብ በደንብ መጠበቅ አለባቸው።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ልጆቹ ሕይወታቸውን ከኃጢአት እንዲጠብቁ ቢፈልግም እግዚአብሔር መንጋውን እንድንጠብቅለት ለመሪነት ለጠራን ሰዎች በተለይ ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በቤተሰብ ሕይወታችን፥ በሞራል (በሕሊናችን) ሕይወታችን፥ በሥራ ሕይወታችን ፥በመንፈሳዊ ሕይወታችን በሙሉ ሌሎች ሊከተሉት የሚችሉትን የቅድስና ምሳሌነት ሊኖረን ይገባል። እንዲህ ነን ወይ?

በምዕራፍ 21 ውስጥ ለካህናቱ የሚከተሉት መመሪያዎች ተሰጥቷቸዋል።

1. የሞተውን ነገር በመንካት እንዳይረከሱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ካለፉት ትምህርቶቻችን እንደምታስታውሱት የሞተ ነገር የነካ ሁሉ የረከሰ ይሆን ነበር። ስለዚህም ካህናት የሞተን ነገር በመንካት ወይም የሞተ ሰው ቤት በመግባት እራሳቸውን ማርከስ አልነበረባቸውም፤ (አሪት ዘኁልቁ 19፡ 11፥ 14)። ካህናቱ የቤተሰቦቻቸውን፥ ያላገቡ ልጆቻቸውን፥ የወላጆቻቸውን፥ ወዘተ... የቀብር ሥነ-ሥርዓት ብቻ ሊካፈሉ ይችሉ ነበር።

2. ካህናቱ እራሳቸውን መላጨትና ሥጋቸውን መቁረጥ አይችሉም ነበር። ይህ ትዕዛዝ እንደ አሕዛብ እንዳያለቅሱ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ የሚያመለከት ነው።

3. ለጋብቻ በሚመርጡት ሰው ላይ ጥንቃቄ መውሰድ ነበረባቸው። ከባልዋ የተፋታችውንና ድንግል ያልሆነችውን ሊያገቡ አይችሉም ነበር። በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ካህን ጋብቻ ንጹሕና ለሌሎች እንደምሳሌ የሚቀርብ ሊሆን ይገባዋል። ልጆቹም ቢሆኑ ለወደፊቱ የእሥራኤል ሕዝብ ካህናት የሚሆኑ በመሆናቸው ከንጹሕ የሆነ ግንኙነት የተገኙ ሊሆኑ ይገባል።

4. ልጆቻቸውን መቆጣጠር ነበረባቸው። የልጆቻቸው ሁኔታና አኳኋን አባቶቻቸውን ሊያሳዝን ይችላል። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ሕግ በግልጽ ሲቃወሙ፥ ለምሳሌ ጋለሞታ በመሆን ይገደሉ ነበር።

5. የአካል እንከን ያለበት ካህን እግዚአብሔርን ማገልገል አይፈቀድለትም ነበር። ዕውር፥ አንካሳ፥ ወዘተ. . . የነበሩ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል ብቁ አልነበሩም። ለመሥዋዕት የሚቀርቡት እንስሳት ነውር የሌለባቸው መሆን እንደሚኖርባቸው ሁሉ፥ እነዚህን መሥዋዕት የሚያቀርቡና መገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገቡ ሁሉ እንከን የሌለባቸው መሆን ነበረባቸው። ሆኖም እንከን ያለባቸው ካህናት ለመሥዋዕት ከሚቀርበው ውስጥ የካህናቱ ድርሻ የሆነውን መብላት ይችላሉ።

እንከን ያለባቸው ካህናት እንዲያገለግሉ ፈቃድ ያልተሰጣቸው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከአምልኮ ጋር የተያያዙ ነገሮች በሙሉ ነውር የሌለባቸው እንዲሆን መመሪያ አውጥቶ ነበር። ይህ መመሪያ የሚቀርቡትን መሥዋዕቶችንና በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙትን ካህናት የሚያጠቃልል ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ይህን መመሪያ የሰጠው የሞራል ወይም የሕሊና ንጽሕናን እንዲያመለክት ብሎ ነው፤ ያልተለመደ ማንኛውም ነገር የኃጢአት ምልክት ስለሆነ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ የለበትም። ሆኖም በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ትኩረት የሚሰጠው የውስጥ ንጽሕናን ነው እንጂ ውጫዊ የአካል ጉድለትን አይደለም። አንድ ሰው እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው አረማመድ ንጹሕ ከሆነ ማገልገል ይፈቀድለታል። በአዲስ ኪዳን አካለ ስንኩል የሆነ ለአገልግሎት መቅረብ አይችልም የሚል ትዕዛዝ የለም። እንዲያውም ከዲያቆናትና ከሽማግሌዎች የሚጠበቀውን ምግባር ስንመረምር እግዚአብሔር ብዙ ትኩረት የሚሰጠው መንፈሳዊና የአስተሳሰብ ብቃት ላይ እንደሆነ እንመለከታለን፤ (1ኛ ጢሞ. 3)።

28ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 9:13-14 አንብብ። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ብቃት ያሟላው እንዴት አድርጎ ነው?

ከሌሎቹ ካህናት ይበልጥ ብዙ ሊያሟላቸው የሚገቡ ነገሮች ያሉት ሊቀ ካህኑ ነው። የመጨረሻው ትልቁ መሪ እርሱ በመሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ንጽሕናውን መጠበቅ ይኖርበታል። ስለዚህም የሞተ ነገርን የቅርብ ዘመዶቹን እንኳ ቢሆን ሊነካና ሊያለቅስላቸው አይችልም ነበር። ሕዝቡን በእግዚአብሔር ፊት የማቅረቡን ሥራ

ለማሟላት ሲል እራሱን ንጹሕ አድርጎ መጠበቅ ነበረበት። የመገናኛውን ድንኳን ከሚያረክስ ነገር የመጠበቅ ሐላፊነትም ነበረበት።

29ኛ ጥያቄ:- ከዚህ ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስፈላጊ የሚሆን ምን ዓይነት ትምህርት እናገኛለን?

እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ በመሆን እርሱን የሚመለክበትን ሥርዓት በትልቅ ጥንቃቄ ነው ማከናወን ያለብን። የአምልኮውን ሥርዓት ንጽሕናና የምእመናኑ መንፈሳዊ ሕይወት የመጠበቁ ኃላፊነት ከሞላ ጎደል የተሰጠው ለመሪዎቹ ነው። በዚህ ምክንያት ነው የመሪነት ሥልጣን በታላቅ ጥንቃቄና ፈሪሀ እግዚአብሔር መታየት ያለበት። ሥልጣን ከሰጣቸው ላይ እግዚአብሔር ብዙ ይጠብቅባቸዋል።

* ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 22 አንብብ።

30ኛ ጥያቄ:- እርኩሳን ሆነው ላለ መሥዋዕት ለሚያቀርቡ ካህናት የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? (ቁጥር 9)።

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 22 ለካህናቱ የተሰጡትን መመሪያዎች ያካተተ የምዕራፍ 21 ቀጥያ ነው። በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የተሰጠው በመገናኛው ድንኳን የእንስሳ መሥዋዕት አቀራረብ ላይ ነው።

1. ካህኑ እርኩስ ከሆነ በመገናኛው ድንኳን እንዳይሠራና መሥዋዕት እንዳያቀርብ ጥንቃቄ መውሰድ አለበት፤ (ከቁጥር 1-9)። ለምፅ ያለበት ተንቀሳቃሽ እንስሳዎችን ወይም የሞተ እንስሳን ወዘተ. . . የሚነካ ሁሉ የረከሰ ነበር። ይህም ማለት በመገናኛው ድንኳን ለመሥራት አይችልም ብቻ ሳይሆን ከመሥዋዕቶቹ የካህናቱ ድርሻ ከሆነውም ላይ መብላት አይችልም ማለት ነው። ርኩስ ከሆነ የተለመዱትን ሕግጋት በመከተል እራሱን እንደገና ንጹሕ ማድረግ ነበረበት። ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት ማገልገል ይችል ነበር። ርኩስ ሆነው የሚያገለግሉ ሁሉ በእርሳቸው ላይ የእግዚአብሔርን ቅጣትና የሞት ፍርድ እንደጋበዙ ነው የሚቆጠረው።

31ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ቆሮ.11፡29-30 ተመልከተው ዛሬ ለእኛ የተሰጠውን ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ አጢን።

2. የካህናቱ ቤተሰብ የሆኑ ብቻ ናቸው በመሥዋዕቱ ላይ የካህናቱ ድርሻ ከሆነው ሊበሉ የሚችሉት፤ (ከቁ. 10-16)። ካህናት ያልሆኑ ለመሥዋዕት ከቀረበው ላይ ቢበሉ እንደሰረቁ ነው የሚቆጠረው። በዚህ ምክንያት ልክ እንደተበደለ መሥዋዕት የወሰደውን ለካህናቱ መመለስ ይኖርበታል።

3. ለስለት መሥዋዕት (ትምህርት ሁለትን ተመልከት)። ከሚቀርቡት እንስሳት በቀር ለሌሎቹ መሥዋዕት የሚቀርቡት እንስሳት በሙሉ እንከን የሌለባቸው መሆን አለባቸው፤ (ከቁጥር 17-25)። ለመሥዋዕት ከመቅረቡ በፊት እንስሳውን የሚመረምረው ካህን እንስሳው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለመቅረብ ብቁ መሆን ያለመሆኑን ያረጋግጣል፥ (ትንቢተ ሚልክያስ 1፡6-14፥ ይህ ትዕዛዝ እንዴት እንደተጣሰ የሚያሳይ ምሳሌ ነው)።

4. መሥዋዕትን በተመለከተ የተሰጡ ሌሎች ትዕዛዞች አሉ፤ (ከቁጥር 26-30)። የስምንት ቀን ዕድሜ ሳይኖረው ማንኛውም እንስሳ ለመሥዋዕት መቅረብ አይችልም ነበር። በተጨማሪም አንድ እንስሳ ከእናቱ ጋር በአንድ ቀን ለመሥዋዕት መቅረብ አይችልም ነበር። ካህናቱም፥ ለምሥጋና መሥዋዕት የሚቀርበውን የእንስሳ ሥጋ በሥርዓቱ መሠረት በጥንቃቄ መመገብ ነበረባቸው።

እሥራኤላውያንን ከግብፅ ያወጣቸው አምላክ ልጆቹ ሙሉ በሙሉ ትዕዛዙን እንዲጠብቁ ይፈልጋል። ይህ በተለይ ከካህናቱ የሚጠበቅ ነው። እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዛት በሙሉ መጠበቃቸውንና እግዚአብሔርን እንደ ሕይወታቸው ንጉሥ ማክበራቸውን እርግጠኞች መሆን ነበረባቸው። እኛም ብንሆን ከኃጢአት ባርነት ነፃ የወጣነው በእግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔርም ሕግ በፊታችን ነው። ስለዚህም እኛ እራሳችን እግዚአብሔር የሕይወታችን ንጉሥ መሆኑን በፊታችን ያስቀመጠውን ትዕዛዝ በፈቃደኝነት በመጠበቅ ልናሳይና ልንገልጽ ይገባናል።

32ኛ ጥያቄ:- ሀ) ኢየሱስ የሕይወትህ ጌታ መሆኑን በምን ዓይነት መንገድ ነው የምትገልጸው?

ለ) ዮሐንስ 14፡15 ተመልከት። እኛ እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆነ ከእኛ የሚጠበቀው ምንድን ነው?

አምስተኛ ቀን:- የዚህን ሳምንት ጥናት ከልስና ለውይይት የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በመመልከት ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ:-

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) ኦሪት ዘሌዋውያን 18፡1-5 አንብብ። ከእነዚህ ጥቅሶች ከእግዚአብሔር ጋር፤ ከዓለም ጋር ስላለን ግንኙነትና ትእዛዛቱን ስለመጠበቁ አስፈላጊነት የምንማረው ምንድን ነው?

ለ) ኦሪት ዘሌዋውያን 17፡11 ደኅንነታችን የተመሠረተበትን መመሪያ የሚያሳየው እንዴት ነው?

ሐ) በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 18 ላይ ያሉት ሕግጋት ጋብቻችንን በንጽሕና ለመጠበቅ አስፈላጊ መመሪያዎች ሊሆኑ የሚችሉት እንዴት ነው?

መ) 1. ከኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 19 ላይ ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት በተመለከተ ልንጠብቃቸው የሚገቡን አንዳንድ ትዕዛዞች ምን ምንድን ናቸው?

2. ብዙ ክርስቲያኖች ችግር የሚገጥማቸው ምን ዓይነት ግንኙነቶች ላይ ነው?

3. እነዚህን ጥቅሶች በመጠቀም ክርስቲያኖች ከሌሎች ሰዎች ጋር የበለጠ ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲኖራቸው ሊታበረታታቸው የምትችለው እንዴት ነው?

ሠ) ትምህርት ሃያ አንድ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና መጠበቁ ላይ ስላለው ሐላፊነት የሚያስተምረን ምንድን ነው?

ረ) በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕ.21-22 ላይ በመመርኮዝ እግዚአብሔር እንዴት ከተራው ምዕመን ይልቅ ከመሪዎቹ ብዙ እንደሚጠብቅ ተወያዩ።

5. ጸሎት

# ትምህርት ሰባት

ኦሪት ዘሌዋውያን 23-25

## የመጀመሪያ ቀን:-

ኦሪት ዘሌዋውያን 23:1-14

በዚህ ሳምንት ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 23-25 ያለውን እንመለከታለን። በዚህ ክፍል ላይ ትኩረት የተሰጠው ነጥብ እሥራኤላውያን ስለሚያከብሯቸው ለየት ያሉ ክብረ በዓላት ነው። በየሳምንቱ የሚያከብሩት የሰንበት በዓል ነበር። ከዚህም በላይ በየዓመቱ በየሰባት ዓመቱ እና በየ አሥራ አምስት ዓመቱ የሚያከብሯቸው ክብረ በዓል ነበሩ።

ክብረ በዓሎች ለእግዚአብሔር ሕዝብ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ዋናው ዓላማቸው ለየት ያለ ጊዜ ወስደን እግዚአብሔርን ስላደረገው ነገር እንድናመሰግን ለማድረግ ነው። ብዙዎቹን ክብረ በዓሎች ላይ የምናከብረው በፊት በተከናወኑት ክንውኖች ላይ ነው። ለመጥቀስ ያህል ገና ላይ የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን ነው የምናከብረው። ፋሲካ ላይ ደግሞ የጌታ ኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ እናከብራለን። በኦሪት ዘሌዋውያን የተጠቀሱት አንዳንዶቹ ክብረ በዓሎች ልክ እንደ መሥዋዕቶቹ ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያመለክቱ ናቸው።

ስለ እነዚህ ልዩ ልዩ ክብረ በዓላት ስናጠና የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ካለህ መዝገበ ቃሉ ስለእነዚህ በዓላት ያተተውን ነገር አንብብ።

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 23 እና ኦሪት ዘኍልቁ ምዕራፍ 28-29 የሚመሳሰሉ ምዕራፎች ናቸው። ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 23 የተፃፈው አዋቂ ካልሆነ ሰው አመለካከት ሆኖ ድግሶቹ መቼ እንደሚደረጉ ያብራራል። ኦሪት ዘኍልቁ ከምዕ.28-29 ያለው ደግሞ በእነዚህ ቀናት ካህናቱ የሚጠበቅባቸው ነገር ላይ ያተኩራል።

1ኛ ጥያቄ፡- አሪት ዘሌዋውያን 23፡1-14 አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች የተጠቀሱትን የተለያዩ ክብረ በዓሎች በዝርዝር ጻፍ።

በዛሬው ዕለት በአይሁዳውያን አቆጣጠር በዓመቱ መጀመሪያ አካባቢ የሚከበሩትን አራት ክብረ በዓሎችንና የሰንበትን ክብረ በዓል እናጠናለን።

1. ሰንበት (ቁጥር 3)

2ኛ ጥያቄ፡- አሪት ዘጸአት 20፡8-11 አንብብ። ሰንበትን በተመለከተ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን የሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? እግዚአብሔር የጠቀሰው ሰንበትን ለመጠበቅ መሠረት የሚሆነው ክንውን ምንድን ነው?

«ሰንበት» የሚለው ቃል የመጣው «ማቆም» ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ነው። ይህ ቃል እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ለስድስት ቀን ያህል ከሠራ በኋላ በሰባተኛው ቀን ሥራውን ማቆሙን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ያሉት ሕዝቦቹ ይህን የፍጥረት ሥርዓት እንዲከተሉ ፈልጎ ነበር። የሰንበት ቀን ተለይቶ የሚከበረው ለሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛ፥ እግዚአብሔር የሚመለከበት ለየት ያለ ቀን ነው። በሰንበት ቀን የየቀኑ መሥዋዕት ሁለት ጊዜ ነበር ለእግዚአብሔር የሚሠዋው፥ (አሪት ዘኁልቁ 28፡9)። ሁለተኛ የሰንበት ቀን፡- ሠራተኞች የሚያርፉበትና ሰውነታቸውን የሚያዝናኑበት ቀን ነው።

እግዚአብሔር የሰንበት ጥበቃን ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል። ስለዚህም ሰንበትን የማይጠብቅ ሁሉ እንደሚሞት እርግጠኛ ነው፥ (አሪት ዘኁልቁ 15፡32-35)። በአዲስ ኪዳን ዘመን አይሁዳውያን ሰንበትን በተመለከተ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን አውጥተው ነበር። እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሰንበትን ለየት ባለ አኳኋን ማክበሩን ሳይሆን ኢየሱስ የተቃወመው እነርሱ ያወጧቸውን እነዚህን ተጨማሪ ድንጋጌዎችን ነው ላለመጠበቅ የወሰነው።

3ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያኖች ለአምልኮ የሚቀርቡት በሳምንት ውስጥ በየትኛው ቀን ነው? ይህስ ለምን ሆነ?

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ ወዲህ በሳምንቱ ውስጥ ሰባተኛው ቀን የሆነውን የሰንበት ቀን አናከብርም፤ የምናከብረው እሁድን ነው። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣበትን ቀን ለማክበር ነው። በሮሜ 14፡5-6 እና በቆላስይስ 2፡16-17 ላይ ጳውሎስ ትልቁና ዋነኛ የሆነው ነገር የአምልኮው ቀን ሳይሆን በሳምንቱ ውስጥ በሚገኙት ቀናት በሙሉ በሕይወታችን እኛ እግዚአብሔርን ማስከበራችን እንደሆነ ጳውሎስ ያስተምረናል። ይህም ቢሆን ክርስቲያኖች እላይ ለጠቀስናቸው ሁለት ምክንያቶች ሲሉ እሁድን ማክበር ይገባቸዋል። የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰብበት ጊዜ ሊሆን ይገባዋል። ሰውነታችንንም የምናዝናናበትና ከሥራችን የምናርፍበት ጊዜ ሊሆን ይገባል። ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች እንኳ ለሰው ልጅ ጤንነት ይህ የዕረፍት ቀን አስፈላጊ እንደ ሆነ ተገንዝበዋል።

ከሰባት ቀናት ውስጥ አንደኛውን ለይቶ የማስቀመጡ መርህ ለአይሁዳውያን ክብረ በዓሎች ሊከተሉት የሚገባ ባህል እንዲሆን ገፋፍቷል። ተለይቶ የሚከበረው ሰባተኛው ቀን ብቻ ሳይሆን ለየት ባለ ሁኔታ የሚከበሩ ሰባት ክብረ በዓሎችም ነበሩ፤ ከእነዚህም ብዙዎቹ የሚከበሩት በሰባተኛው ወር ላይ ነበር። በተጨማሪም በየሰባት ዓመቱ «የሰንበት ዓመት» ይሆን ነበር። በመጨረሻም ሰባተኛው «የሰንበት ዓመት» ሁሌ በጣም ለየት ያለ ነበር የሚሆነው። ስለዚህ ነገር በዚህ ሳምንት ውስጥ ወደ በኋላ አካባቢ እናጠናለን።

2. ፋሲካ (ከቁጥር 4-5)

4ኛ ጥያቄ:- አሪት ዘጸአት 12፡ 1-30 አንብብ። የፋሲካ በዓል ዓላማ ምን ነበረ?

ዋነኛ የሆነው የመጀመሪያው የአይሁዶች በዓል ይከበር የነበረው በእነርሱ መንፈሳዊ የቀን አቆጣጠር መሠረት በመጀመሪያው ወር ላይ ነበር። አይሁዳውያን ሁለት የቀን መቁጠሪያዎች ነበሯቸው፥ ዓመቱን በመጋቢት ላይ የመጀመሪያው መንፈሳዊው የቀን መቁጠሪያና ዓመቱን በመስከረም ላይ የሚጀመረው ሕዝቡ የሚገለገልበት የቀን መቁጠሪያ ነበር።

የእሥራኤል ወንዶች ተገኝተው ሊያከብሯቸው የሚገባቸው ሦስት ክብረ በዓሎች ነበሩ። የፈለገውን ያህል ረጅም መንገድ ቢያስኬዳቸውም ክብረ በዓሉን ማክበር ነበረባቸው። ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው በዓል የፋሲካ ክብረ በዓል ነው። ሁለተኛው የበዓለ ሃምሳ ሲሆን፥ ሦስተኛው ደግሞ የዳሱ በዓል ነው።

የፋሲካው በዓል ሦስት የተለያዩ አከባበሮችን ያካተተ ነው። በመጀመሪያ ይኸው የፋሲካ በዓል ነበር። በማግስቱ ደግሞ የቂጣ በዓል ይከበራል። በሦስተኛ ደረጃ የመከራቸውን የበኩራት ነዶ የሚያቀርቡበት ክብረ በዓል ነበር። ይህ በዓል የሚከበረው የቂጣው በዓል በሚከበርበት ሳምንት ውስጥ ነው።

«ፋሲካ» የሚለው ቃል የተገኘው «በላይ ማለፍ» የሚል ትርጓሜ ካለው የዕብራዊ ቃል ነው። ይህም ቃል የተገኘው እሥራኤላውያን በግብፅ በሚኖሩበት ጊዜ መልአኩ በበራቸው ላይ ቀይ ደም የቀቡትን እሥራኤላውያን ሳይነካ በላያቸው ባለፈበት ወቅት ነው። ይህ የፋሲካ በዓል የሚከበረው ለፋሲካ የተሠዋውን ጠቦት ደም የእግዚአብሔር መልአክ በበሮቻቸው ላይ አይቶ የእሥራኤላውያንን የመጀመሪያ ልጆች ሳይገድል ያለፈበትን ቀን ለማክበር ነው። ይህ የፋሲካ በዓል ለአይሁዳውያን ዋነኛው ክብረ በዓል ነው፤ ይከበር የነበረውም በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን ላይ ነው።

በዚህ የፋሲካ ክብረ በዓል ላይ ትኩረት የሚሰጠው በፋሲካ ላይ በሚሠዋው ጠቦት ላይ ነው። በመጀመሪያ ግብፅ በነበሩበት ወቅት እያንዳንዱ ቤተሰብ ጠቦቱን አርዶ ደሙን በበሩ ላይ ቀብቶ የተቀረውን ሥጋ እንዲበላ ነበር የታዘዘው። ዓመታቶቹ በጨመሩ ቁጥር የፋሲካ በዓል አከባበርም በጣም እያደገ መጣ። በኢየሱስ ዘመን ላይ የተለየ ትርጓሜ ያላቸው ብዙ የአከባበር ባህሎች ነበሩት። የምርኮውን ጊዜ መራርነት የሚያመለክቱ መራር ቅጠላ ቅጠል ይበሉ ነበር። አራት ለየት ያሉ የወይን ጠጆችንም

ይጠጡ ነበር። ከእነዚህ የወይን ጠጆች መካከል አንደኛውን አንሥቶ ነው ኢየሱስ «ይህ ደሜ ነው» ያለው።

ፋሲካ የእግዚአብሔር በግ የሆነውን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት የሚያመለክት ነው፤ (1ኛ ዮሐ.1፡29፥ 1ኛ ቆሮ.5፡7)። እንዲያውም ኢየሱስ የሞተው ይህ በዓል ሲከበር ነው። እርሱ በሞተልን ሞትና ባፈሰሰው ደም አማካኝነት ነው ሁላችንም ከኃጢአት ባርነት ነፃ ልንወጣ የቻልነው። ዛሬ ይህን የፋሲካ ክብረ በዓል የምናከብረው የኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ በማሰብ ነው።

3. የቂጣ በዓል (ከቁጥር 6-8)

ምንም እንኳ በመጀመሪያ ይህ የቂጣ በዓል ተለይቶ የሚከበር ቢሆንም ወደ በኋላ ከፋሲካ ጋር አብሮ ነበር የሚከበረው። ይህ በዓል የሚጀመረው ፋሲካ በተከበረ በማግስቱ ነው። የቂጣ በዓል የሚል ስያሜ የተሰጠው እሥራኤላውያን ከዚህ ቀን አንሥቶ ለሳምንት ያህል ጊዜ እርሾ ያለበት እንጀራ ወይም በቤታቸው እርሾ ያለበትን ማንኛውንም ነገር መብላት ስለማይፈቀድላቸው ነው።

በዚህ ክብረ በዓል ወቅት እሥራኤላውያን ምንም ዓይነት ከባድ ሥራ አይሠሩም ነበር። ይህ ካባድ ሥራ አትሥሩ የሚለው ትዕዛዝ እንደ ሰንበቱ ጊዜ በጣም ከበድ ያለ ባይሆንም የዕረፍትና የመዝናኛ ጊዜ ይሆንላቸው ነበር። በሳምንቱ ውስጥ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ቀናት ለየት ያሉ ነበሩ፤ በእነዚህም ቀናት ለየት ያሉ ስብሰባዎች ይደረጉ ነበር። ከብዙ ጊዜ በኋላ ይህ የሳምንት ጊዜ እሥራኤላውያን ታሪካቸውንና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዞች የሚማሩበት ጊዜ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል የማንበቢያ ጊዜ ነበር።

ይህ የቂጣ በዓል ሁለት ዓላማዎች ነበሩት። አንደኛ፥ መንፈሳዊ ንጽሕና የሚደረግበት ጊዜ ነው። ኃጢአትን የሚያመለክተው እርሾ ከእሥራኤላውያን ሕይወት ውስጥ መወገድና መፅዳት ይኖርበታል። በዚህ ጊዜ አንድ እሥራኤላዊ ከቤቱ ውስጥ ምንም ዓይነት እርሾ እንደሌለ ማረጋገጥ እንደሚኖርበት ሁሉ በሕይወታቸውም የተደበቀ ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ካለ ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ማስወገዳቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

5ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ.5፡6-8 ተመልከት።

ሀ) በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እርሾ ከምን ጋር ነው የሚነፃፀረው?

ለ) በሌሎች ላይ ተጣብቆ መኖርን በተመለከተ የእርሾ ተጽዕኖ ምንን ይመስላል? ዳቦ በምን ይመሰላል?

በ1ኛ ቆሮንቶስ ጳውሎስ የፋሲካንና የቂጣ ክብረ በዓላትን ያገናኛል። ፋሲካ ኢየሱስ ለክርስቲያኖች የሞተውን ሞት የሚያመለክት ነው። የቂጣ በዓል ደግሞ ክርስቲያኖቹ እንደ እርሾ ከሚመስሉ በመላው ምዕመን መካከል ተዛምተው ሕይወትን ከሚያጠፉ ኃጢአቶች ነፃ መሆን እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው።

ሁለተኛ:- ይህ የቂጣ በዓል እሥራኤላውያን ከግብፅ ባርነት የወጡበትን ጊዜ የሚያከብር ነው። እግዚአብሔር ታዳጊያቸውና አዳኛቸው እንደሆነ ሊያስታውሳቸው የሚገባ በዓል ነው። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር የእኛም አዳኝና ታዳጊ ነው። በፋሲካ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እኛን የታደገበትን ቀን እናከብራለን። በላያችን ላይ የነበረውን የኃጢአት ኃይል ገርስሶ በነፃነት ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ኑሮ እንድንኖር ያደረገን መስቀሉ ነው።

4. የመከሩን በኩራት ነዶ በማምጣት የሚከበረው በዓል (ከቁጥር 9-14)

የቂጣ በዓል በሚከበርበት በሁለተኛው ቀን በመገናኛው ድንኳን አካባቢ ለየት ያለ አከባበር ይደረግ ነበር። እሥራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ እያንዳንዱ እሥራኤላዊ ከገብስ ማሳው «የበኩራት ነዶውን» ማምጣት ነበረበት። ካህኑም ይህንን ወስዶ በእግዚአብሔር ፊት ይወዘውዘውና ለእግዚአብሔር ያበረክተዋል። የበኩራት ነዶውን ከማበርከቱ ጋር የሚቃጠለውና የደህንነቱ መሥዋዕቶች ይሰዉ ነበር። ይህንን የበኩራት ነዶ እስከሚያበረክቱ ድረስ እሥራኤላውያን ከአዲሱ እህል ላይ ምንም አይበሉም ነበር።

በእሥራኤል የቂጣ በዓል ይከበር የነበረው ገብሱ አሽቶ ለአጨዳ በሚደርስበት ወቅት ነበር። ይህ ከላይ የጠቀስነው በዓል የሚከበረው ለሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው:- አንደኛ፥ የመከሩ ጊዜ በሚደርስበት ወቅት እግዚአብሔር ሥጋዊ ፍላጎታቸውን በማሟላቱ ለማመስገን ነው። ሁለተኛ፥ ከሚያመርቱት የእግዚአብሔርን ድርሻ የሚሰጡበትና ያመረቱት ሁሉ የራሳቸው ሳይሆን የእግዚአብሔር እንደሆነ የሚገልጹበት ጊዜ ነው። የተረፈውን ለእግዚአብሔር ከመስጠት የመከሩን በኩራት ነበር የሚሰጡት።

6ኛ ጥያቄ:- የእኛ አሥራትና በኩራት አሰጣጥ ከዚህ ጋር መመሳሰል ያለበት እንዴት ነው?

ይህ በኩራት የሆነውን ነገር የማቅረቡ ጉዳይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተለይም ኢየሱስ ክርስቶስንና የጥንት አማኞችን እንደ በኩር አድርጎ መቁጠር የተለመደ ነበር።

7ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት: ሮሜ 8:23፥ 1ቆሮ.15:20።

ሀ) በኩር ተብለው የሚጠሩት ነገሮች ምንድን ናቸው?

ለ) ጳውሎስ ይህንን ስያሜ የተጠቀመው ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

8ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከእነዚህ ክብረ በዓሎች የሚመሳሰሉ በቤተ ክርስቲያንህ የምታከብራቸው ምን ዓይነት ክብረ በዓሎች አሉ?

ለ) የትኞቹ ዓይነት ክብረ በዓሎች ናቸው እኛ የሌሎንና በአምልኮ ሥርዓታችንም ለእግዚአብሔር ክብር ስንል ልንከተላቸው የሚገቡን?

ሐ) እግዚአብሔር ከሰጠን ሥጋዊ በረከቶች በተመለከተ እንዴት አድርገን ነው ለእግዚአብሔር ያለንን ምሥጋና የምንገልጸው?

## ሁለተኛ ቀን:-

ኦሪት ዘሌዋውያን 23:15-44

9ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘሌዋውያን 23:15-44 አንብብ። በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ክብረ በዓላት በዝርዝር ጻፍ። የሚቻል ከሆነም የእነዚህን ክብረ በዓላት ዓላማም ጻፍ።

5. የበኩራት ቁርባን ክብረ በዓል (ከቁጥር 15-22)

በቂጣ በዓል ወቅት የበኩራት ነዶውን ካቀረቡ ከሃምሳ ቀን በኋላ ሌላ ክብረ በዓል ነበረ። ይህ ክብረ በዓል የተለያዩ ስያሜዎች ነበሩት፥ እነዚህም:- የበኩራት ቁርባን ክብረ በዓል፥ «የበኩራት ነዶ ቀን» ወይም «ጴንጤቆስጤ» ይባላሉ። በግሪኩ ቋንቋ ጴንጤቆስጤ የሚባል ስያሜ የተሰጠው ሌሎቹ ክብረ በዓላት ከተከበሩ ከሃምሳኛው ቀን በኋላ በመከበሩ ነው።

ይህ የበኩራት ቁርባን ክብረ በዓል የሚከበረው የገብሱ አጨዳ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው። ስለዚህም ዋነኛው ዓላማው እግዚአብሔር የሚበሉትን ምግብ ስለሰጣቸው ለማመስገንና እንደ ክብረ በዓል ለማክበር ነው ምስጋናቸውን የሚገልጹት፥ ለእግዚአብሔር የተለያዩ መሥዋዕቶችን ማቅረብና ከሰጣቸው ውስጥ የተወሰነው ክፍል ለሱ መልስ በመስጠት ነው። ይህም ቀን ድሆችንና በመካከላቸው የሚኖሩትን እንግዶች የሚያስቡበትና ለጋስ የሚሆኑበት ጊዜ ነው። ማሳቸውን ሙሉ ለሙሉ እንዳያጭዱና ሌላ የመቋቋሚያ መንገድ ለሌላቸው በመካከላቸው ለሚገኙ ድሆችና እንግዶች የማሳቸውን ዳር ዳሩን እንዲተዉላቸው ታዘዋል። በእዚህ ቀን ድሆቹና ካህናቱ በሕዝቡ ለጋስነት ብዙውን የሚፈልጉትን ነገር ያገኛሉ።

ከአዲስ ኪዳን ላይ እንደምንረዳው እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ላይ መንፈስ ቅዱስን ያፈሰሰው በዚህ የበዓል ቀን ነው። በብሉይ ኪዳን ይከበር የነበረው እግዚአብሔር የሚሰጠው ሥጋዊ በረከት ነበር! ጴንጤቆስጤ ግን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በመላክ በሕዝቦቹ ላይ የሚያወርደውን ታላቁን መንፈሳዊ በረከት ነው የሚጠባበቀው።

6. የመለከት ድምፅ መታሰቢያ (ከቁጥር 23-25)

የመጨረሻዎቹ ሦስት ክብረ በዓላት ማለትም የመለከት ድምፅ መታሰቢያ የስርየት ቀንና የዳስ በዓል ይከበሩ የነበረው በሰባተኛው ወር ላይ ነበር። ይህ ሰባተኛ ወር ይውል የነበረው ከወይንና ከሉፍ የመከር ጊዜ በኋላ ነበር። የዝናቡ ወቅት ከመድረሱና አዳዲስ ዘሮች ከመዘራታቸው በፊት ነው ይህ በዓል የሚከበረው።

በሰባተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ላይ ካህናቱ መለከቶቻቸውን እንዲነፉ ታዘዋል። ለዚህም ነው ይህ በዓል የመለከት ድምፅ መታሰቢያ በመባል የሚታወቀው። ይህ ቀን በሕዝቡ የቀን መቁጠሪያ መሠረት የመጀመሪያው ቀን ነው፤ ዛሬም እንደ አይሁዳውያን አዲስ ዓመት ይከበራል። ይህ ለምን መታሰቢያ እንደሚከበር ባይነገረንም

በዚህ ቀን መላው እሥራኤል ተሰስቦ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርብ ነበር። ምንም ዓይነት የተግባር ሥራ አይሠራም ነበር።

7. የስርየት ቀን (ከቁጥር 26-32)

ይህን ዋነኛ የሆነ ክብረ በዓል፥ ከዚህ በፊት በጥልቀት አጥንተነዋል፥ (ዘሌዋ. ምዕራፍ 16)። ለማንኛውም እስቲ የበዓሉን ዓላማ እንደገና እንመልከት። የስርየት ቀን ሁለት ዓላማዎች አሉት ብለናል። በመጀመሪያ የእሥራኤል ሕዝብ ኃጢአት የሚሰረይበት ጊዜ ነው። ሁለተኛ፥ የመገናኛው ድንኳን ለሚቀጥለው ዓመት አምልኮ ዝግጁ እንዲሆን የሚፀዳበት ጊዜ ነበር።

ምናልባት ይህ በዓል ከሌሎቹ በዓላት በታላቅ ክብር የሚከበር ሊሆን ይችላል። ሕዝቡ እራሱን የሚክድበት ጊዜ ነበር። ይህም በመፆምና በመጸለይ ኃጢአታቸውን ተናዘው እራሳቸውን ለበዓሉ ዝግጁ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ልክ እንደ ሰንበት ቀንም ምንም ዓይነት ሥራ አይሰሩም ነበር።

እንደምናስታውሰው ይህ በዓል ፍጻሜውን ያገኘው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችንን በመስቀሉ ላይ ተሸክሞ ከኃጢአታችን እንድንነፃ አድርጓል።

8. የዳስ በዓል (ከቁጥር 33-44)

ይህ የመገናኛው ድንኳን ድግስ በመባልም የሚታወቀው ክብረ በዓል ከሌሎቹ ዓመት በዓሎች ሁሉ በጣም በደስታና በሐሴት የሚከበር ነው። በመጨረሻ የሚከበረውን ይህን ዓመት በዓል መላው የእሥራኤል ወንድ መካፈል ነበረበት። ሰብሉ በሙሉ ተሰብስቦ የሚያልቅበት ጊዜ በመሆኑ እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ችሮታ በታላቅ ደስታ ሐሴት የሚያደርጉበት ጊዜ ነው። በእነዚህ ሰባት ቀናት ውስጥ ለየት ያሉ መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር ይሰጡ ነበር።

የዚህ ክብረ በዓል ዋና ዓላማ እሥራኤላውያን በምድረ በዳ ለአርባ ዓመት ያክል በተንከራተቱበት ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ችሮታ ለማስታወስ ነው። በዚህም ምክንያት ነው፥ ከቤቶቻቸው ወጥተው ትናንሽ ዳሶች የሚሠሩት። ለሰባት ቀን በዳስ ውስጥ በመሆን እግዚአብሔር በድሮው ጊዜ እንዴት እንደረዳቸውና አሁንም ሳያቋርጥ እንዴት የዕለት ፍላጎታቸውን እንደሚያሟላላቸው የሚያስቡበትና ጌታን የሚያመልኩበት ጊዜ ነው።

ወደ አዲስ ኪዳን ዘመን አካባቢ ከበዓላት ሁሉ በጣም ገናና የነበረው ይህ በዓል ነበር። በዓለም ተበታትነው የሚገኙት አይሁዳውያን በሙሉ ለዚህ በዓል ለመድረስ ሲሉ ወደ ኢየሩሳሌም ይመጡ ነበር። ዓመታት ባለፉ ቁጥር ይህም በዓል የሚከበርባቸውም ሥርዓቶች ጨመሩ። አይሁዳውያን ይህ በዓል መሲሁ መጥቶ ሲገዛ እግዚአብሔር የሚያወርደውን በረከት እንደሚያመለክት አድርገው ነው የሚመለከቱት። በዚህ ሳምንት ውስጥ የሚሰጧት ሰባ ወይፈኖች ሰባዎቹን የአሕዛብ ነገሥታት የሚወክሉ ሲሆን ወደ በኋላ ስለሚያገኙት ደኅንነትም የሚያመለክቱ ናቸው።

በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይበሩ የነበሩት ትላልቅ ሻማዎች ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ በዓለም ላይ የሚበራውን የእግዚአብሔርን ብርሃን ያመለክታል። በቤተ መቅደሱ የሚያደርጉት የውኃ ክብረ በዓላት ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ የሚያመለክቱ ናቸው።

10ኛ ጥያቄ:- መሲሕ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን የአይሁዳውያን ተስፋዎች ያሟላው እንዴት ይመስልሃል?

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 7-8 ላይ ኢየሱስ ወደ ዳሱ በዓል እንደሄደ እናነባለን። ካህናቱ በመሠዊያው ላይ ውኃ ሲያፈሱ ኢየሱስ «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ» ብሎ ጮኸ። ዮሐንስም ይህ መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ነው አለ፤ (ዮሐ.7:37-38)። በኋላም እነዚያ ትላልቅ ሻማዎች እየበሩ ሳለ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» ብሎ ተናገረ፤ (ዮሐንስ 8:12)። ኢየሱስ ይህ የዳስ በዓል ለአይሁዳውያን የሚያመለክተውን ተስፋ ሁሉ እንደሚያሟላ ነው የሚናገረው። ሆኖም ይህንን አላዩም አላመኑትምም። በምትኩም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሰቀሉት። ይህም በመሆኑ የአሕዛብና የአይሁዳውያን የደኅንነት መንገድ ተከፈተ፤ መንፈስ ቅዱስም ከላይ ወረደ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህ ክብረ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ በአሕዛብ ላይ ከነገሠ በኋላ ለሰው ልጅ በሙሉ የሚወርደውን በረከት እንደሚያመለክት አድርገው ይመለከቱታል።

11ኛ ጥያቄ:- ከእነዚህ በዓላት ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ ስግደት ምን እንማራለን?

# ሦስተኛ ቀን:-

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 24

12ኛ ጥያቄ:- አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 24 አንብብ። ሀ) ከቁጥር 1-9 በመገናኛው ድንኳን ያለውን አምልኮ በተመለከተ ለካህናቱ የተሰጡት መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

ለ) እግዚአብሔርን የተሳደበ ሰው ምን ዓይነት ቅጣት ነበር የሚሰጠው።

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 24 ለየት ያሉ ክብረ በዓላትን በሚጠቅስ ጽሑፍ መካከል ጣልቃ ገብ ነው። አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 23 በዓመቱ ውስጥ የሚከበሩትን ክብረ በዓላት የሚያትት ነው። አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 25 ደግሞ ለየት ስላሉ የሰንበት ዓመትና ስለ ኢዩቤልዩ ዓመት ያትታል።

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 24 ሦስት ዋና ዋና ሐሳቦችን ያመለክታል። በመጀመሪያ በመገናኛው ድንኳን በተቀደሰው ሥፍራ ውስጥ የካህናቱ የተለየ ሥራ ምን እንደሆነ ይናገራል። ሁለተኛ እግዚአብሔርን ተሳድቦ በድንጋይ ስለተወገረ ሰው ይናገራል። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የተለያየ ጥፋት የሚያጠፉትን ሰዎች እንዴት በትክክል እንደሚቀጡ የሚገልጹትን መመሪያዎች አካትቷል።

1. በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ያለው የካህናት ሥራ (ከቁጥር 1-9)

በዚህ ምዕራፍ ካህናቱ በተለይም ሊቀ ካህኑ መገናኛው ድንኳን ውስጥ ሆኖ በተቀደሰው ምዕራፍ ሊያከናውናቸው የሚገባቸውን ስለ ሁለት ሥራዎች እናጠናለን፤ እነዚህ ሥራዎች የዘወትር ሥራዎች ናቸው። እንደምታስታውሰው በተጠቀሰው ምዕራፍ ውስጥ ሦስት የአምልኮ ዕቃዎች ይገኛሉ። እነዚህም የዕጣን መሠዊያው መቅረዙና ገበታው ናቸው። እነዚህ መመሪያዎች መቅረዙንና ገበታውን በተመለከተ ነው የተሰጡት።

ሀ) መቅረዙ (ከቁጥር 1-4) በመቅረዙ ውስጥ ተገቢውን ዘይት አድርጎ በሰባቱም በኩል እሳት በእግዚአብሔር ፊት ሁሌ መንገዱን የማረጋገጡ ሐላፊነት የተጣለው በሊቀ ካህኑ ላይ ነው። በማለዳና በማታ ሊቀ ካህኑ እየገባ ልክ እንደ ኩራዝ ሁሌ አዲስ የወይራ ዘይት መጨመር ነበረበት። መብራቱ በጭራሽ መጥፋት አልነበረበትም።

ለ) የኅብስቱ ገበታ (ከቁጥር 5-9): - በየሳምንቱ አዳዲስ ኅብስት እየጋገሩ በገበታው ላይ መተካት ነበረባቸው። አሥራ ሁለት ኅብስት መጋገር ነበረባቸው፤ ለአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች አንድ አንድ ማለት ነው። ኅብስቱን በሁለቱ ተርታ አድርገው ነበር የሚያስቀምጡት። ሰንበት ላይ ሁሌ ካህናቱ በገበታው ላይ አዲስ ኅብስት ያደርጉና የበፊቱን ኅብስት እዚያው መገናኛው ድንኳን ውስጥ ሆነው ይበላሉ።

2. የተሳዳቢው በድንጋይ መወገር (ከቁጥር 10-16)

ሙሴ ከእግዚአብሔር ላይ እነዚህን ሕግጋት በመቀበል ላይ እያለ አንድ በጣም ከባድ የሆነ ነገር በእሥራኤላውያን መኖሪያ ሠፈር ውስጥ የተደረገ ይመስላል። አንድ እናቱ እሥራኤላዊት አባቱ ደግሞ ግብፃዊ የሆነ ሰው እሥራኤላዊ ከሆነ ሰው ጋር ተጣላና ሰውዬውን ለመርገም ሲል የእግዚአብሔርን ስም ይጠቀማል። እንደምታስታውሰው በአሪት ዘጸአት ምዕራፍ 20 ላይ ካሉት ትዕዛዞች መካከል «የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ» የሚል ነው። ከእግዚአብሔር አፍ ሰውዬውን እንዴት አድርገው እንደሚቀጡት እስኪነገራቸው ድረስ በግዞት አስቀመጡት። እግዚአብሔርም ሰውዬውን በድንጋይ ወግረው እንዲገሉት አዘዘ። ሰውዬው ሲራገም የሰሙ በሙሉ እንዲወግሩት ታዘዋል። እግዚአብሔርን የመሳደብ ቅጣት ሞት ነበር።

ለእኛ ይህ ፍርድ የጭካኔ ፍርድ ሊመስለን ይችላል ሆኖም ይህ ለእሥራኤላውያንና ለእኛ የተሰጠን በእግዚአብሔር ስም አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንድንወስድ ተብሎ ነው። ይህ በቀላሉ ልናየው የሚገባን ነገር አይደለም። ሆኖም አንዳንድ ሰዎችም ክርስቲያኖች እንኳ በእግዚአብሔርም ሆነ በኢየሱስ ስም ለመማል ይፈጥናሉ። በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን ስምና ክብር በማውረድ ጌታን በንቀት ይመለከቱታል። ለምሳሌ አዎ ወይም አይደለም ማለቱ በቂ ሆኖ ሳለ በችኮላ «እግዚአብሔርን» ብለን በመማል የእግዚአብሔርን ስም ክብር እናሳጣዋለን። ያለ ምንም ጥቅም «ኢየሱስን» በማለት ደግሞ የስሙን ክብር ዝቅ እናደርገዋለን።

13ኛ ጥያቄ: - ሀ) ክርስቲያኖች «እግዚአብሔርን» ወይም ይህን የመሰሉ መሐላዎች በመጠቀም የእግዚአብሔርን ስም ሲያቃልሉ ሰምተህ ታውቃለህ?

ለ) ለምንድን ነው ይህን የሚያደርጉት?

ሐ) ይህ በእግዚአብሔር ስም ላይ የሚያስከትለው ነገር ምንድን ነው?

3. በትክክል ለመቅጣት ሲባል የተሰጡ መመሪያዎች (ከቁጥር 17-23)

በብሉይ ኪዳን ዘመን የቅጣት ሕግ ዐይን ለዐይን፥ ጥርስ ለጥርስ፥ ስብራት ለስብራት ነበረ ይህን ቃል በቃል ስንመለከተው አንድ ሰው ዐይንህን ካወጣህ አንተ ደግሞ የሌላ ሰውን ዐይን አውጣ የሚል ትዕዛዝ አይደለም ያለው፤ (ለምሳሌ ኦሪት ዘጸአት 21፡26-27)። የዚህ ትዕዛዝ ዓላማ ቅጣቶችን የተወሰኑ አድርጎ ጎጂው ሰው እኩል በሆነ ቅጣት እንዲቀጣ ቅጣቶች ሁሉ በትክክል እንዲከናወኑና የጎሳ ወይም ግላዊ የሆኑ አመለካከቶችን እንዳይዙ ለማድረግ ነው። ስለዚህም ለእሥራኤላውያንና አብረዋቸው ለሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች የሚከተሉት መመሪያዎች ተሰጥተዋቸዋል፡-

ሀ) አንድ ሰው ሰውን ከገደለ እራሱ መገደል ነበረበት።

ለ) የሰው እንስሳን የሚገድል ሰው ለባለቤቱ ተመሳሳይ እንስሳን ለመግዛት በቂ የሚሆን ካሣ መክፈል አለበት።

ሐ) አንድ ሰው የባልንጀራውን አካል ቢጎዳ ተመጣጣኝ ካሣ መክፈል አለበት።

14ኛ ጥያቄ፡- ይህ የቅጣት ሕግ ሰውዬው ወይም ቤተሰቡ ቁጭቱን እንዳይወጣ ሊያደርገው የሚችለው እንዴት ነው?

15ኛ ጥያቄ፡- ማቴዎስ 5፡38-41 አንብብ። ኢየሱስ ክርስቲያኖችን ይህንን ሕግ እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ነው የተናገረው?

ሰዎች ማድረግ ያለባቸውን ትልቁን ነገር ለመጠቆም ሲል ኢየሱስ የሚጀምረው ከብሉይ ኪዳን ነው። በእግዚአብሔር ዐይን ዋነኛ የሆነው መበቀል ሳይሆን ፍቅርና ምሕረት ማድረጉ ነው። ስለዚህም ሌሎች ሲበድሉን እነርሱን ከመበቀል ይቅር ልንላቸው እንደሚገባን ተነግሮናል።

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንተ የምታውቀው ሰው እንደዚህ ዓይነት የይቅርታ መንፈስ ያሳየሽው ወይም ያሳየህ እንዴት ነው?

ለ) ብዙ ክርስቲያኖች ይቅርታ ከማድረግ ይልቅ ለመበቀል የሚገፋፉት ለምንድን ነው?

# አራተኛ ቀን፡- ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 25

17ኛ ጥያቄ፡- እሥራኤላውያን በዓመተ-ሰንበት ወቅት ማድረግ የሌለባቸው ነገር ምን ነበር?

18ኛ ጥያቄ፡- በዚህ ዓመተ-ሰንበት ያደርጓቸው የነበሩ ሌሎች ነገሮች ምን ምን ናቸው? (ኦሪት ዘዳግም 15፡1-18 ተመልከት)።

19ኛ ጥያቄ:- የኢዮቤልዩን ዓመት በተመለከተ ለእሥራኤላውያን የተሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበር?

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 25 ስለ ሁለት ለየት ያሉ ዓመታት ያትታል። የመጀመሪያው ዓመት ዓመተ-ሰንበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኢዮቤልዩ ዓመት ነው።

1. ዓመተ-ሰንበት (ከቁጥር 1-7)

በየሰባት ዓመቱ እሥራኤላውያን ለየት ያለ ዓመተ-ሰንበት የሚባለውን ያከብራሉ። ዓመተ-ሰንበት የሚል ስያሜ የተሰጠው በዚህ ዓመት ውስጥ ምንም ዓይነት እርሻ ስለማይዘራ የዕረፍት ዕለት በመሆኑ ነው። ምድሪቱም ሰዎቹም ማረፍ ነበረባቸው።

በዚህ የዕረፍት ዓመተ-ሰንበት ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ይከናወናሉ። በመጀመሪያ እርሻቸው እዳሪ ይሆናል፤ መዝራት፥ ማረስ ወይም ማጨድ የለም። በምትኩ መሬቱ ታርሶ ጠመውን ማደር ነበረበት። በዚህ ወቅት በዘሩቀደ ያልተቀረጠውና የበቀለውን እህል ብቻ ነበር መሰብሰብ የነበረበት። ይህ እህል የሁሉም በተለይ ግን የድሆች ሰዎች ነበር። በዚህም ዓይነት ምድሪቱና ሰዎቹ ለየት ያለ የዕረፍት ጊዜ ነበራቸው።

ሁለተኛ፤ በዚህ ዓመት እሥራኤላውያን ሁሉ የሚሠረዝላቸው ይመስላል፤ (ኦሪት ዘዳግም 15:1)። ነገር ግን በዚህ ዓመት የሚሠረዝላቸው ዕዳ ያለፈውንም ጊዜ ሁሉ ይሁን ወይስ መኸር በመጥፋቱ ምክንያት በዚሁ ዓመት የተበደሩት መሆኑ ግልጽ አይደለም።

ሦስተኛ አይሁዳዊ የሆኑ ባሮች ነፃነት የሚያገኙበት ወቅት ነው፤ (ኦሪት ዘዳግም 15:12)።

እግዚአብሔር እነዚህን ትዕዛዞች የደነገገው ለምንድን ነው? ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ምክንያቶች አሉ፥ እነርሱም:-

1. ምድሪቱ እንድታርፍና እንድትዳብር ጊዜ ለመስጠት ነው። ዛሬ እንደምናውቀው አንድ መሬት ያለ ማቋረጥ የሚታረስ ከሆነና አንድ ዓይነት ዘር ብቻ የሚዘራበት ከሆነ የመሬቱ የማልማት ኃይል ይቀንሳል። ስለዚህም እግዚአብሔር ይህንን ዓይነት ነገር የተጠቀመው መሬቱ የማልማት ኃይሉን እንዲያድስ ለማድረግ ነው።

2. እሥራኤላውያን ዐይናቸውን ሁሉን ነገር በሚሰጣቸው በእግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ ለማስተማር ነው። ስለዚህ ምድራዊ ሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማየት ፈንታ የሕዝቡ ሀሳብ በእግዚአብሔር ላይ ያተኮረ እንዲሆን ነው እርሱ ይህን ዓመት ለየት እንዲል ያደረገው። የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት የእርሱን እጅ መመልከት ነበረባቸው። ጊዜያቸውን እርሱን በማምለክ ማሳለፍ ነበረባቸው።

20ኛ ጥያቄ:- ሀ) ይህ ሁለተኛው ምክንያት በማቴዎስ 6:33 ላይ ካለው የኢየሱስ ትዕዛዝ የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) ይህን ትዕዛዝ በሕይወትህ መጠበቅህን የምታሳየው እንዴት ነው?

2. የኢዮቤልዩ ዓመት (ከቁጥር 8-55)

በየሐምሳ ዓመቱ ደግሞ ሌላ ለየት ያለ ዓመት ነበር። ይህም ዓመት የኢዮቤልዩ ዓመት በመባል ይታወቃል፤ (ቁጥ. 13)። አንዳንድ ምሁራን ይህ የኢዮቤልዩ ዓመት በየአርባ ዘጠኝ ዓመቱ ነው የሚከበረው ብለው ያስባሉ፤ በሌላ አነጋገር፤ በየሰባቱ የሰንበት ዓመት ማለት ነው። በብዙ መልኩ እንደ ዓመት-ሰንበት ነው፤ ሆኖም ይህን ዓመት በተመለከተ የተሰጡ ለየት ያሉ መመሪያዎች ነበሩ።

ልክ እንደ ዕረፍቱ ዓመት-ሰንበት ምንም ዓይነት ዘር አይዘራም፤ ሰብልም አይሰበሰብም። የኢዮቤልዩ ዓመት 50ኛው ዓመት ከሆነ ለሁለት ዓመት ያክል ምንም ዓይነት እርሻ አያርሱም ነበር ማለት ነው፥ ይህም ለዓመት-ሰንበቱና ለኢዮቤልዩው ዓመት ነው። የሚበሉትን ምግብ ከየት ያገኛሉ? እግዚአብሔርን በደንብ ከታዘዙ እግዚአብሔር በስድስተኛው ዓመት ላይ ለሰባተኛውም ዓመት የሚበቃ ምግብ እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸዋል። ልክ እንደዚሁ በአርባ ስምንተኛው ዓመት ላይ ለአርባ ዘጠነኛውና ለሐምሳኛው ዓመት እስከ ሐምሳ አንደኛው የመከር ጊዜ የሚያደርሳቸውን ምግብ ይሰጣቸዋል። እሥራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳኖች ጠብቀው በእነርሱም ለመታመን ፈቃደኛነታቸው የሚፈተንበት ትልቅ ትዕዛዝ ነው።

21ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ሥራችንን ለሁለት ዓመት ትተን በሱ ችሮታ ላይ እንድንታመን ትዕዛዝ ቢሰጠንስ እንታዘዘዋለን? በሕይወታችን ልንጠብቀው ከሚገባን ከዚህ ሁለት ዓመት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በተመለከተ የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

የኢዮቤልዩ ዓመት በሁለት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ያተኩራል። አንደኛ በአይሁዳውያን እጅ ውስጥ ባለው ንብረት ላይ ያተኩራል። እንደምታስታውሰው እሥራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር በገቡበት ወቅት ምድሪቱን በየነገዱ ከከፋፈሉ በኋላ ነው ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የተወሰነ የመሬት ክልል የሰጡት። ነገር ግን የማን መሬት ነበር? አሪት ዘሌዋውያን 25፡23 መሬቱ ወይም ምድሪቱ የእግዚአብሔር እንደሆነች ይናገራል። ለእያንዳንዱ ቤተሰብ መሬቱን የሰጠው እርሱ ሲሆን እነርሱ የምድሪቱ ጭሰኞች ነበሩ። የእግዚአብሔር በመሆኗ ምድሪቷን ሊሸጡ አይችሉም ነበር። ሆኖም አንድ ሰው የገንዘብ ችግር ቢደርስበት ምን ማድረግ ይችላል? አሪት ዘሌዋውያን 25፡14-34 የሚከተለውን መመሪያ ይሰጣል፡-

1. እሥራኤላዊው በተሰጠው ምድር ላይ ያለውን ሰብል ሊሸጥ ይችላል። ስለዚህም በምድሩ ላይ ያለውን ሰብል ሲሸጥ ለኢዮቤልዩ ዓመት ምን ያህል ጊዜ እንደሚቀረውና ምድሪቱ ምን ያህል ሰብል እንደምትሰጠው ማመዛዘን ነበረበት። እግዚአብሔር ከሰብሉ የሚገዙት ሰዎች ለደሃው ሰውዬ ተገቢ ድርሻውን እንዲከፍሉና በሰውዬው እንዳይጠቀሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸዋል።

2. አንድ እሥራኤላዊ ንብረቱን ለመሸጥ ቢገደድ የቅርብ ዘመዱ የሆነ ሰው ያንን መሬት ለመግዛት ጥረት ማድረግ አለበት እንጂ ሌላ የውጪ ሰው እንዲገዛው ማድረግ የለበትም።

3. የመጀመሪያው ባለንብረት መሬቱን መልሶ ለመግዛት ብቁ ከሆነ የመግዛት መብቱ የተጠበቀ ነው። ሆኖም እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ ያለውን የሰብሉን ዋጋ ለገዛው ሰውዬ መክፈል አለበት።

4. በኢዮቤልዩ ዓመት ላይ ንብረቱ ለቀድሞው ባለንብረት መመለስ ነበረበት። በዚህም ዓይነት ንብረቱ ሁሉ በቀድሞው ሰው እጅ ውስጥ ይቀመጣል።

5. በከተማ ውስጥ ያለ ማንኛውም ዓይነት ንብረት ሊሸጥ ይችላል። ባለንብረቱ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ንብረቱን መልሶ መግዛት ካልቻለ ንብረቱ የአዲሱ ባለቤት ቋሚ ንብረት ይሆናል። ይህ ሕግ የማይሠራው ለሌዋውያን ብቻ ነው።

6. ሌዋውያን እንደሌሎቹ ነገዶች የራሳቸው የሆነ መሬት አልነበራቸውም። በምትኩ አርባ ስምንት ከተሞችና በአካባቢዎቻቸው ያለው መሬት ነበር የተሰጣቸው፤ (ኦሪት ዘኁልቁ 35፡1-8)። እነዚህ ሌዋውያን ቤቶቻቸውን ሊቤዡ ይችላሉ፤ በኢዮቤልዩም ዓመት ላይ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል።

በዚህ በኢዮቤልዩ ዓመት የሚሆነው ሌላው ሁለተኛ ነገር የአይሁዳውያን ባሪያዎች ነፃ መውጣትና መለቀቅ ነው፤ (ከቁጥር 39-55)። በመሠረቱ አይሁድ የሆነ ሰው እንደ ተራ ባሪያ ሊገዛና ሊቆጠር አይችልም። ተቀጥሮ እንደሚሠራ ሰው ነበር የሚቆጠረው። የሚከተለው መመሪያ ብድራቱን ለመክፈል ሲል እራሱን ለባርነት አሳልፎ ለሚሰጥ ድሃ አይሁዳዊ የተሰጠ ነው፡-

1. በኢዮቤልዩ ዓመት ምግተኛው ከቤተሰቡ ጋር ተለቅቆ ወደ ትውልድ አገሩ እንዲሄድ ይፈቀዳል።

2. ጌታው ባሪያውን በርኅራኄ መግዛት ነበረበት። እግዚአብሔር ነፃ ሲያወጣቸው እሥራኤላውያን እራሳቸው የግብፆች ባሪያ እንደነበሩ በማስታወስ ነው ባለንብረቱ ሊያስተዳድረውና ሊገዛው የሚገባው።

3. ቋሚ ባሪያዎች ሊሆኑ የሚችሉት አይሁዳዊ ያልሆኑ ብቻ ናቸው።

4. በእሥራኤል ውስጥ አንድ አይሁዳዊ አይሁዳዊ ላልሆነ ሰው ቢሸጥ በኢዮቤልዩ ዓመት ነፃ የመውጣቱ መመሪያ ለእርሱም ይሠራል።

5. አንድ ሰው እራሱን እንደ ባሪያ ቢሸጥ የቅርብ ዘመዱ መልሶ ሊገዛው ይገባል። ወይም ደግሞ ባሪያው በቂ ገንዘብ ካገኘ ሁሌ ነፃነቱን የመግዛት መብት ነበረው። የሚከፍለው ክፍያ የሚተመነው የኢዮቤልዩ ዓመት ሲደርስ በሚቀሩት ዓመታት ተገምቶ ነው።

እግዚአብሔር እነዚህን ሕግጋት የሰጠው ለምንድን ነው? እነዚህ ሕግጋት እግዚአብሔር እኩል የሆነ ኅብረተሰብ እንዲፈጠር የተገለገለባቸው ናቸው። ሀብታሞች በድሃ ሰዎች ጉልበት እንዳይጠቀሙና ድሃው ሁሌ ነፃነቱንና ንብረቱን እንዳይነፈግ እግዚአብሔር ጥንቃቄ ያደርጋል። እነዚህ ሕግጋት ባይኖሩ ድሃው እየደኸየ ሀብታሙ ደግሞ እየበለጸገ ነበር የሚሄደው።

2. እግዚአብሔር ስሙን የሰደበ እንዲገደል ያዘዘው ለምንድን ነው?

3. የእግዚአብሔርን ስም እንዴት አድርገን መጠቀም እንዳለብን ነው ይህ የሚያስተምረን?

ሠ) የዘመኑ መንግሥታት በዓመተ-ሰንበትና በኢዮቤልዩ ዓመት ላይ የተሰጡትን መመሪያዎች ቢጠቀሙ ዓላማችን ጥሩ የመኖሪያ ቦታ ሊያደርጓት የሚችሉት እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት ስምንት

ኦሪት ዘሌዋውያን ከምዕራፍ 26-27

## የመጀመሪያው ቀን፡-

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 26

በዚህ ሳምንት የኦሪት ዘሌዋውያንን የመጨረሻዎቹን ሁለት ምዕራፎች እናጠናለን። ከዚህ በኋላ ደግሞ በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ያጠናናቸውን ዋና ዋና እውነታዎች እንከልሳለን።

እንደ ማንኛውም የጥንት ቃል ኪዳን ይህ የሲና ቃል ኪዳን የሚጠናቀቀው ትዕዛዙን ለሚጠብቁ ሁሉ በሚገኘው በረከትና በማይጠብቁት ላይ በሚመጣው ቁጣ ነው፤ (ኦሪት ዘፀአት 23፡25-33፥ ዘዳግ.28) ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 26 እሥራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ከጠበቁ የሚያገኟቸውን በረከቶች ዝርዝር ይዟል። ሆኖም በኦሪት ዘሌዋውያን የሚገኘውን ትዕዛዝ ንቀው ካልጠበቁት የሚያጋጥማቸውንም ቅጣት አካትቷል።

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 26 አንብብ።

1ኛ ጥያቄ፡- በኦሪት ዘሌዋውያን 26፡1-2 የተሰጡት ለየት ያሉ ትዕዛዞች ምንድን ናቸው? በኦሪት ዘሌዋውያን የተሰጡትን ብዙዎቹን ትዕዛዞች አጠር ባለ መልክ የሚያካትቱ ናቸው ልንል የምንችለው እንዴት ነው?

2ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዞች ከጠበቁ የሚያገኟቸውን የተለያዩ በረከቶች በዝርዝር ጻፍ።

3ኛ ጥያቄ፡- የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ካልጠበቁ የሚቀበሏቸውን የተለያዩ ቅጣቶች በዝርዝር ጻፍ። እነዚህ ቅጣቶች በእሥራኤል ታሪክ ውስጥ እንዴት እንደተፈጸሙ የሚገልጽ ምሳሌ ስጥ። (ለምሳሌ 2ኛ ነገ.24፡1-15)

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 26፥ የሚጀምረው እሥራኤላውያን በእግዚአብሔር ለመባረክ ከፈለጉ ሊጠብቋቸው የሚገባቸውን ዋና ዋና ትዕዛዞች በሚያጠቃልሉ ቁጥሮች ነው፤ (ከቁጥር 1-2)።

1. እሥራኤላውያን ማምለክ የነበረባቸው እግዚአብሔርን ብቻ ነው። ፍቅራቸውንና እምነታቸውን በእርሱ ላይ ማሳረፍ ነበረባቸው። የአምልኳቸውና የእምነታቸው መሠረት የሆነውን እግዚአብሔርን በምንም ነገር መተካት አልነበረባቸውም። ሦስት ዓይነት አምልኮዎች ተዘርዝረዋል፡-

ሀ) ከድንጋይ ወይም ከእንጨት የተቀረፁ ጣዖቶችን ተክላችሁ እንዳታመልኩ።

ለ) እግዚአብሔርን የሚወክሉ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ የተሠሩ ነገሮችን አታቁሙ።

ሐ) አማልክቶቻቸውን የሚወክሉ ሥዕሎችን መሣል የለባቸውም። ማምለክና ማመን የነበረባቸው አንዱንና ብቸኛውን የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔርን ነው። ይህ አምላክ መንፈስ በመሆኑ ቁሳዊ በሆነ ነገር ሊመስሉት አይችሉም።

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ፍቅራችንንና እምነታችንን ልንጥልባቸውና እንደ አምላካችን ሊሆኑብን የሚችሉ በዓለም ያሉ አንዳንድ ነገሮችን በዝርዝር ጻፍ።

ለ) የኢየሱስን ሥዕል በተመለከተ እነዚህ ትዕዛዛት የሚገልጹት ነገር ምንድን ነው?

2. እሥራኤላውያን ሰንበትን መጠበቅ ነበረባቸው። ይህ ሰንበት የቅዳሜው ብቻ ሳይሆን በየሰባት ዓመቱና በየሃምሳ ዓመቱ ያሉትን ሰንበቶችንም ያጠቃልላል። ልባቸውንና ሐሳባቸውን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ ይረዷቸዋል። በየሳምንቱ እርሱን ማምለክ ነበረባቸው። በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ሙሉ መታመን ለመግለጽ የተወሰኑ ዓመታት በመለየት እርሱ ሥጋዊ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሟላላቸው ያደርጋሉ።

3. የእግዚአብሔር ክብር ያረፈበትን ቤተ መቅደሱን ሁሌ ማስታወስ ነበረባቸው። መሥዋዕታቸውን ሊያቀርቡና ሊያመልኩት የሚችሉት በዚህ ሥፍራ ብቻ ነው። እግዚአብሔር መባቸውንና በእርሱ ላይ ያለባቸውን ነገር በሙሉ እንደተቀበላቸው ማረጋገጥ ነበረባቸው። በልባቸውና በእእምሯቸው ሁሌ በመካከላቸው በሚኖረው እግዚአብሔር ላይ ማተኮር ነበረባቸው።

5ኛ ጥያቄ፡- እኛ ክርስቲያን እንደመሆናችን መጠን ልባችን ሁሌ የእግዚአብሔርን ድምፅ እንዲሰማና ሕይወታችን ለእግዚአብሔር ሥራ ሁሌ ዝግጁ እንዲሆን ከማድረግ መቆጠብ የሌለብን ነገሮች ምንድን ናቸው?

እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር ቃል ኪዳን ባደረገ ጊዜ አምላካቸው እንደሚሆን በመካከላቸው እንደሚኖርና እያንዳንዱን የሕይወታቸውን ክፍል እንደሚባርክላቸው ቃል ገብቶላቸዋል። ሆኖም በረከቱ የሚወርድላቸው ትዕዛዛቱን በሙሉ ከጠበቁ ነው። እሪት ዘሌዋውያን 26፡3-13 በሦስት ሊከፈሉ የሚችሉትን እነዚህን በረከቶች ይዘረዝርልናል፡-

ሀ) እግዚአብሔር በንብረት ይባርካቸዋል፤ (ከቁጥር 3-5፥9)። ለምሳሌ:- እግዚአብሔር ዝናብ በወቅቱ በመላክ ጥሩ እርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል፥ ብዙ ልጆች ይኖራቸዋል፥ ታላቅ ሕዝብም ይሆናሉ።

ለ) እግዚአብሔር ለእነርሱና ለምድሪቱ ሰላምን ይሰጣል፥ (ከቁጥር 6-8)። ክፉዎች አራዊቶችን ከምድራቸው ያጠፋል። ጠላቶቻቸውን ድል አድርገው ሰላም ይኖራቸዋል። ከማንኛውም ዓይነት ባርነት ነፃ ይሆናሉ።

ሐ) እግዚአብሔር ማደሪያውን በመካከላቸው ማድረጉን ይቀጥላል፥ (1-13)። ከመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሆኖ በእነርሱ ላይ ይነግሣል። የበረከቶቻቸው ሁሉ ምንጭ እርሱ ይሆናል። ልክ አዳም እና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ይራመዱና ያወሩ እንደነበረው፥ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር በቅርብ ኅብረት በማድረግ ይናገራቸዋል።

6ኛ ጥያቄ:- ከእነዚህ በረከቶች ትዕዛዙን ከጠበቅን እግዚአብሔር እንደሚሰጠን ቃል የገባልን የትኞቹን ነው?

ከእርሱ ጋር ከተራመድንና ትዕዛዙን ከጠበቅን እግዚአብሔር ለእኛ ዛሬ ሊሰጠን ቃል የገባልን ብዙዎቹ በረከቶች ከበፊተኞቹ ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ሁሌ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል። ሆኖም የአዲስ ኪዳን ቃል ኪዳኖች ብዙ ትኩረት የሚሰጡት ውጫዊ በሆኑ በረከቶች ላይ ሳይሆን በመንፈሳዊ በረከቶች ላይ ነው። እግዚአብሔር ሥጋዊ ብልፅግና ወይም ሥጋዊ ሰላም ቃል ኪዳን አላደረገልንም። በምትኩ ቃል የገባልን ዘላለማዊ የሆነ መንፈሳዊ ሰላምና መንፈሳዊ ብልፅግና ነው። ይህ ቃል ኪዳን ዘላቂና ከበፊቱ በጣም የሚሻል ነው። በአካባቢያችን ብጥብጥ እንኳ ቢኖር በእግዚአብሔር ሰላምና ተስፋ ልንሞላ እንችላለን።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ቢያፈርሱና ትዕዛዙን ባይጠብቁ እንደሚቀጣቸው ተናግሮ ነበር፤ (ከቁጥር 14-46)። በጥንት ቃል ኪዳኖች ላይ የቅጣቱ ዝርዝር ከበረከቱ ይበልጥ ነበር፤ ይህም የሆነው ያለመታዘዝ የሚያመጣውን መዘዝ ለመግለጽና ለማስጠንቀቅ ሲባል ነው።

ሀ) ሥጋዊ የሆኑ በረከቶች አይኖራቸውም፥ (ከቁጥር 16-17)። ጤናም አይኖራቸውም፥ እርሻዎቻቸውም አያፈሩም።

ለ) ጠላቶቻቸው ያሳድዷቸዋል። የምድር አራዊቶችም በመካከላቸው ይሰደዳሉ፤ ጠላቶቻቸውም ይገዟቸዋል።

ሐ) ጦርነቶች ይኖራሉ፤ ከጦርነቶቹም የተነሣ ቸነፈርና ረሃብ ይሆናል፥ በሺ የሚቆጠሩ ይሞታሉ ምድሪቱም ባዶ ትሆናለች፥ ይደኸያሉም፥ (ለምሳሌ:- አሥር ቤተሰቦችን ለመመገብ አንዲት እንጀራ ትቀርባለች)። በጣም ከመራባቸው የተነሣም የራሳቸውን ልጆች ይበላሉ።

መ) ከተሞቻቸው ባድማ ይሆናሉ፥ የእግዚአብሔርም ቤተ መቅደሶች ይፈርሳሉ።

ሠ) ጠላቶቻቸው ለምርኮ ይወስዷቸዋል፥ በዚያም ጊዜ መሬታቸው በየሰባት ዓመቱ ይረፍ የተባለውን ትዕዛዝ እንዲጠብቁ የተነገራቸው ይፈጸማል፥ ምድሪቱም ታርፋለች።

በእሥራኤል ታሪክ ውስጥ እነዚህ ቅጣቶች በሙሉ ተፈጽመዋል። የእነርሱ ታሪክ ካለመታዘዝ የተነሣ በሽንፈት በቸነፈርና በጥፋት የተሞላ ነው። እንደ ቃሉም በባቢሎናውያንና በሶሪያውያን ወደ ምርኮ ተወስደዋል። በአንዳንድ መልኩ ስናየው፥ እሥራኤላውያን አሁንም ቢሆን የሚኖሩት በቅጣት ዘመን ውስጥ ነው።

ከእነዚህ ጥቅሶች በመነሣት የእግዚአብሔርን ፍርድ በተመለከተ ብዙ ቁልፍ የሆኑ ነገሮችን ልናይ እንችላለን። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፍርዶቹን በሙሉ በአንዴ አልነበረም የላከው። ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንመለከተው ንስሐ ገብተው ትዕዛዙን ለመጠበቅ አሻፈረኝ ሲሉ ነበር፤ ፍርዱ እየጨመረና ከበድ እያለ ይሄድ የነበረው። እግዚአብሔርም «በእንቢተኝነትም ብትሄዱብኝ ባትሰሙኝም እንደ ኃጢአታችሁ መጠን በመቅሠፍቱ ላይ ሰባት እጥፍ እጨምራለሁ» ብሎ ተናግሯል፤ (ቁጥር 18፥21፥24፥27)።

ሁለተኛ፡ ደግሞ እግዚአብሔር የሚቀጣው ለማጥፋት ሳይሆን ሰዎች ወደ እራሱ ለመመለስ እንደሆነ እናያለን። ካለመታዘዝ መንገድ እንድንመለስ ሲል እግዚአብሔር ብዙ ችግሮችን ያመጣብናል።

ሦስተኛ፡ የአለመታዘዝ ሥር ትዕቢት ነው፤ (ቁጥር 19)። ይህ ትዕቢት ከብልፅግናና ከማያቋርጠው የእግዚአብሔር በረከት የተነሣ ነው የሚመጣው። እግዚአብሔርን ለመስማት ፈቃደኞች ባለመሆናቸውም እሥራኤላውያን የራሳቸውን መንገድ ተከተሉ። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ፍርድ በእነርሱ ላይ ወረደ።

**7ኛ ጥያቄ፡- ለምንድን ነው እግዚአብሔር የሚቀጣን? ዕብራውያን 12፡5-11 ተመልከት።**

እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ጨርሶ እንደማያጠፋ ቃል ገብቷል፤ (ከቁጥር 40-45)። እግዚአብሔር ሊሽረው የማይችለውን ቃል ኪዳን ከአብርሃም ጋር ገብቷል። ስለዚህም እግዚአብሔር ንስሐ በገቡበት ወቅት ወዲያውኑ በረከቱን እንደሚያወርድላቸው ቃል ገብቷል። አሁንም ቢሆን ወደ እስራኤላውያን ተመልሶ ሊባርካቸው ይችላል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት ብዙዎቹ ትንቢቶች እነዚህ አሪት ዘሌዋውያን ላይ የተገለጹት በረከቶች በመጨረሻ ላይ በሚመጣው መሢሕ በኢየሱስ የምድር መንገሥ ጊዜ የሚወርደውን ታላቅ በረከት የሚያመለክቱና የሚጠባበቁ ናቸው።

ምንም እንኳ ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ከገባው ቃል ኪዳን በሚበልጠው በአዲስ ኪዳን ሥር ብንኖርም እግዚአብሔር ልክ እንደበፊቱ ከታዘዝነው እንደሚባርከን ካልታዘዝነው ደግሞ እንደሚቀጣን ቃል ገብቷል። እግዚአብሔር እርሱ ቅዱስ እንደሆነ እኛንም ቅዱስ ለማድረግ ወስኗል። ልክ እሳት ቆሻሻውን አቃጥሎ ወርቁን ንጹህ

እንደሚያደርገው እግዚአብሔር እኛን ልክ እንደ እሳቱ አጥር ሥነ-ሥርዓት ያስይዘን ዘንድ ብዙ መሣሪያዎችን ይጠቀማል።

8ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር ሥነ-ሥርዓት እንድትይዝና አድገህ ኢየሱስን የበለጠ እንድትመስል የተለያዩ ነገሮችን ሲጠቀም ያየኸው እንዴት ነው?

# ሁለተኛ ቀን:-

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 27

9ኛ ጥያቄ:- ለእግዚአብሔር ይህን እንሰጣለን ብለው ከተሳሉ በኋላ እሥራኤላውያን የሚያተርፏቸውና የሚያገኟቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 27 አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የገባቸውን ስለቶች መሐላዎች ያካተተ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ በተለይ አንድ ሰው ተቸግሮ የእግዚአብሔርን ዕርዳታ በሚፈልግበት ወቅት በፈቃደኝነት የሚሳላቸው ስለቶች ናቸው። ሆኖም ከሚያገኙት ነገሮች ላይ አንድ አሥረኛውን ወይም አሥራት የመስጠቱን ስለት እግዚአብሔር የሚጠብቅባቸውና ማድረግ ያለባቸው ነው።

10ኛ ጥያቄ:- አሪት ዘፍጥረት 28:20-22 ተመልከት። በዚህ ቦታ የተደረገው ስለት ምንድን ነው? ይህን ስለት ያደረገው ለምንድን ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሰዎች ይህን ካደረክልኝ እንዲህ አደርግልሃለሁ ብለው ለእግዚአብሔር ተስለዋል። ያዕቆብ ለጸሎቱ መልስ ካገኘ እግዚአብሔርን እንደሚያመልክና አሥራቱን እንደሚሰጥ ስለት ይገባል። ሆኖም አንዳንድ ስለቶች ቅጥ የሌላቸው ነበሩ፤ (ለምሳሌ መጽሐፈ መሳፍንት 11:29-40)። በእግዚአብሔር ፊት የገባነውን ስለት ሊያስረሱን የሚችሉ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም መጽሐፍ ቅዱስ ግን አንዴ ስለት ካደረግን ያንን ስለት መፈጸም እንደሚገባን በአንክሮ ያስጠነቅቀናል። ብዙውም የአሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 27 አንድ ሰው አንዴ ከተሳለ በኋላ ስለቱን እንዴት መስጠት እንደሚገባውና ከተሳላቸው ነገሮች ውስጥ ደግሞ ሊያገኛቸውና መልሶ ሊወስዳቸው በሚችላቸው ነገሮች ላይ የሚያተኩር ነው።

* በፈቃደኝነት የሚደረጉ ስለቶች

1. የሰው ስለቶች:- (ከቁጥር 1-8)

አንድ ሰው እራሱን ወይም ከቤተሰቡ ውስጥ አንዱን ሰው ለእግዚአብሔር ለመስጠት ሊሳል ይችላል። ይህን ያደረገው በችግር ውስጥ በነበረበት ወቅት ነው። አሁን ይህን ስለቱን ለመፈጸም ይፈልጋል፣ ነገር ግን እራሱን ወይም ከቤተሰቡ መካከል አንዱን በቤተ መቅደሱ አካባቢ ባሪያ ሆኖ እንዲሠራ አሳልፎ መስጠቱ ይከብደዋል። ምን ማድረግ ነበረበት? በቤተ መቅደስ ውስጥ ማገልገል የሚችሉት ሌዋውያን ብቻ በመሆናቸው እግዚአብሔር ሰውዬው የባሪያውን ዋጋ ከፍሎ እንዲመልሰው ፈቅዷል። ለዚህም የሚከተሉት መመሪያዎች ተዘርዝረዋል:-

ሀ) ሰዎቹ ዕድሜያቸው ከ20-60 ዓመት ከሆነ ለወንድ 50 የብር ሰቅል ለሴት ደግሞ 30 የብር ሰቅል መክፈል አለበት፥ (በዘመኑ አንድ ሰቅል የአንድ ወር ደሞዝ ሲሆን 50 ሰቅል የ50 ወር ደሞዝ ነው ማለት ነው)። የዋጋው ልዩነት የወንዱንና የሴቲቱን የችሎታ ልዩነትና እንደ ባሪያ የሚያወጡትን ዋጋ የሚያመለክት ነው።

ለ) ስለት የገባው ከ5-10 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ሰዎች ከሆነ ለወንዱ 20 የብር ሰቅል ለሴቲቱ 10 የብር ሰቅል በመክፈል ሊያስመልሳቸው ይችላል።

ሐ) ዕድሜያቸው እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ልጆች ለወንዶቹ 5 የብር ሰቅል ለሴቶቹ 3 ሰቅል በመክፈል ሊያስመልሳቸው ይችላል።

መ) ከ60 ዓመት በላይ ለሆኑት ለወንዶቹ 15 የብር ሰቅል ለሴቶቹ ደግሞ 10 ሰቅል መክፈል ነበረበት።

ሠ) ስለቱን ያደረገው ሰውዬ ደሃ በመሆኑ የሚከፍለው ቢያጣ ካህኑ ይገምተውና እንደሚችለው ያህል እንዲከፍል ያደርጋል።

እነዚህ የሚከፈሉት ዋጋዎች በጣም ውድ በመሆናቸው ለእርሱ ይህን ዓይነት ስለት እንዲያደርጉ ሰዎቹን አይገፋፉቸውም። ሆኖም ሳያስቡበት ዝም ብለው ከተሳሉ ስለታቸውን ለማስፈጸም ሲሉ ትልቅ ዋጋ መክፈል አለባቸው።

2. የእንስሳት ስለቶች (ከቁጥር 9-13)

ሀ) ለመሥዋዕትነት የሚቀርቡ እንስሳት፡- እነዚህ እንስሳት ሊለወጡ ወይም ሊመለሱ አይችሉም። ሰውዬው ለእግዚአብሔር የተሳለውን እንስሳ በተሻለ ወይም በከፋ እንስሳ ለመለወጥ ቢሞክር ሁለቱም እንስሳት የእግዚአብሔር ንብረት ይሆናሉ፤ ሁለቱም ይሠዋሉ።

ለ) የጋማ ከብትና የመሳሰሉት (ለምሳሌ ፈረስ፥ በቅሎ፥ ወዘተ. . .) መሥዋዕት መሆን የማይችሉ እንስሳት በካህኑ ፊት መቅረብ ነበረባቸው። ሰውዬው እንስሳውን ለመውሰድ ቢፈልግ፥ የእንስሳው ዋጋ ይገመትና በዋጋው ላይ 1/5ኛ በመጨመር ሊቤዠው ይችላል። ይህ ጭማሪ እንደ ቅጣት ነው። አለበለዚያ ግን የካህናቱ ንብረት ይሆናል።

3. የንብረት ስለት (ከቁጥር 14-25)

ሀ) አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ቅዱስ ይሆን ዘንድ ቤቱን (የቤተ ሰብ ውርስ ያልሆነ) ቢቀድስና ከእግዚአብሔር ላይ ሊቤዠው ቢፈልግ ካህኑ ከገመተው ዋጋ ላይ 20% መጨመር ነበረበት።

ለ) አንድ ሰው ከርስቱ እርሻ ላይ ለእግዚአብሔር ቢቀድስ መሬቱ የእግዚአብሔር ንብረት በመሆኑ በስለት መልክ ሊሰጠው አይችልም። በምትኩ ከመሬቱ ላይ ያመረተውን እህል በሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠት ነበረበት። መሬቱን ሊቤዠው ከፈለገ የመሬቱን መጠንና እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት ያመርታል ተብሎ የሚጠበቀውን የእህልን ግምትና 20% ጨምሮ መክፈል ነበረበት። ሰውዬው መሬቱን ለመቤዠት

ካልፈለገ በኢዮቤልዩ ዓመት ለእግዚአብሔር ይሆንና የካህናቱ ንብረት በመሆን ይተላለፋል።

ሐ) የገዛውን እርሻ ለእግዚአብሔር ቢቀድስ ይህ እርሻ የእርሱ የሚሆነው እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት ስለሆነ ከእርሻው ላይ የሚገኘው ሰብል ወይም የሰብሉ ዋጋ የእግዚአብሔር ነበር። በኢዮቤልዩ ዓመት መሬቱ ባለ ርስት ለነበረው ለመጀመሪያው ሰውዬ ይሰጣል።

4. የእንስሳት በኩራት በተመለከተ የወጣ መመሪያ (ከቁጥር 26-27)

የእንስሳት በኩራት በሙሉ የእግዚአብሔር በመሆናቸው ማንም ሊቀድሳቸው ወይም ሊያስመልሳቸው አይችልም ነበር። ሆኖም ለመሥዋዕት መቅረብ የማይችል ከሆነ ባለንብረቱ ግምቱንና የግምቱን 20% አብሮ በመክፈል እንስሳውን የመቤዠት አማራጭ ነበረው። ይህም ካልሆነ ይሸጥና ገንዘቡ ለካህናት ይሰጣል።

5. ለእግዚአብሔር ሲባል እርም የሆነ ነገር ሁሉ (ከቁጥር 28-29)

በእሥራኤል ውስጥ ሁሉን ነገር ማውደም ልዩ ስለት ነበር። ይህን ዓይነት መሥዋዕት ማቅረብ የሚችሉት የእሥራኤል መሪዎች የሆኑ ብቻ ይመስላል። እና ብዙ ጊዜም የሚቀርበው በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት ነው። በኢያሪኮ እንስሳት ሰዎችና ሌሎቹ ነገሮች በሙሉ እንዲጠፉ በታዘዘው ትዕዛዝ ውስጥ ይህ ስለት ልናየው እንችላለን፤ (ለምሳሌ፡ 1ኛ ሳሙ.15 ላይ ሳዖል ይህንን ትዕዛዝ አልጠበቀም)። በእንደዚህ ዓይነት የሚሰጡ ማንኛዎቹም ዓይነት ስለቶች መውደም ነበረባቸው እንጂ ሊቤዡ አይችሉም።

11ኛ ጥያቄ፡- ለእኛ ዛሬ የስለቶችን ጥቅም ምን ያህል ይመስልሃል? ስለቶቹስ አስፈላጊዎች ናቸው?

አንዳንድ ክርስቲያኖች ለአገልግሎት በሚመረጡበት ወቅት ለእግዚአብሔር የመሳሉን ነገር ያዘወትራሉ። አንዳንዶች አናገባም ብለው ይሳላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ስለት አድርጉ የሚል ትዕዛዝ የለም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ እንደ ካህን ወይም እንደ መነኩሴ የሚሠሩም ሰዎች አናገባም ብለው ስለት መግባት የለባቸውም። ይህ የአንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ልምድ ነው።

በትዕዛዝ መሠረት መፈጸም የሚገባቸው ስለቶች

አሥራትን በተመለከተ የተሰጠ መመሪያ (ከቁጥር 30-34)

እግዚአብሔር የእሥራኤል ሕዝብ የገቢ ምንጭ ከሆነው ነገር ላይ በሙሉ አሥራት እንዲሰጥ አዟል፤ ለምሳሌ ከእርሻዎቻቸውና ከከብቶቻቸው ላይ እንዲሰጡ ታዝዘዋል። ከሁሉ ነገር ላይ አንድ አሥረኛው የእግዚአብሔር ንብረት ነው። ይህን ነገር በተመለከተ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም፥ ልክ እንደ ስለት ያመረቱትን ነገር ለእግዚአብሔር ለይተው ያስቀምጣሉ። አሥራቱን ሊቤዥ ቢፈልግ በዋጋው ላይ የዋጋውን 20% በመጨመር ሊወስድ ይችላል።

እሥራኤላውያን እንስሳዎቻቸውን ለአሥራት በሚያቀርቡበት ወቅት አድልዎ እንዳያደርጉ በትክክል መርጠው እንዲሰጡ እግዚአብሔር ያስጠነቅቃቸዋል። መልካሙን ወይም ክፉውን መምረጥ የለባቸውም። እንስሳዎቹን ከበረት በሚያስወጡበት ጊዜ ከሚያልፏቸው ውስጥ አንድ አሥረኛው የእግዚአብሔር ንብረት ነበር የሚሆነው። (እሥራኤላውያን በጎቻቸውን የሚቆጣጠሩት በበትር ነው። በጎቹ ከበረት ውስጥ ሲወጡ እረኛው በበትሩ ያቆጣቸውና በሽታ እንዳለባቸው ይመረምራቸዋል። ከእረኛው በትር የሚያልፍ የሚለው ይህን ዓይነት ትርጓሜ ነው ያለው)።

ከዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን እውነታዎች መማር አለብን፡-

1. ለእግዚአብሔር የምንሳላቸውን ስለቶች በተመለከተ ጥንቃቄዎች መውሰድ ይገባናል። እግዚአብሔር ተሳሉልኝ ብሎ ትዕዛዝ አልሰጠንም። ነገር ግን ከተሳልን የፈለገውን ያህል ወጪ ያስወጣን እንጂ ስለታችንን መጠበቅና መፈጸም ይኖርብናል።

12ኛ ጥያቄ፡- መጽሐፈ መክብብ 5፡4-6 አንብብ። ስለ ስለት የሚናገረው ምንድን ነው?

13ኛ ጥያቄ፡- አንተና በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ አንዳንድ ሰዎች የተሳላችኋቸው አንዳንድ ስለቶች ምን ምንድን ናቸው? ስለቶቹን ጠብቃችሁ ፈጽማችኋል?

የሚሰጡ ነገሮችን እንሰጣለን ብለን ለእግዚአብሔር ባንሳልም ለጸሎታችን መልስ ከሰጠን አንዳንዴ ይህን እናደርጋለን ወይም ይህን እንሰጣለን ብለን እንሳላለን። እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ ሲሰጠን እነዚህን ስለቶች እንፈጽማለን ወይስ ስለታችንን እንረሳለን? ስለቶቻችንን ካልፈጸምን በእግዚአብሔር ፊት እንደ ሌባና እንደ ውሸታም ሆነን ነው የምንታየው። ብዙ ጊዜ በስብሰባዎች ላይ በመገኘት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሕይወታችንን አሳልፈን እንሰጣለን ብለን እንሳላለን። እነዚህን ስለቶቻችንን እናስታውሳቸዋለን ወይስ ስብሰባው እንዳለቀ ተመልሰን የራሳችንን ፍላጎቶች ለማሟላት እንሞክራለን? ይህን ካደረግን ከእግዚአብሔር ላይ መስረቃችንና መዋሸታችን አይደለም?

2. ካለን ነገር ላይ ቢያንስ ቢያንስ አንድ አሥረኛውን ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን። ይህ በተለያየ መልክ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል። ከገንዘባችን፥ ከምርታችንና ከጊዜያችን ላይ ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን። አሥራታችንንና መሥዋዕታችንን ለእግዚአብሔር ካልሰጠን ከእርሱ ላይ እንደሰረቅን ነው የሚቆጠረው።

14ኛ ጥያቄ፡- ትንቢተ ሚልክያስ 3፡6-12 አንብብ። አሥራታቸውን ስለማይሰጡ ሰዎች እግዚአብሔር ምን ይላል? አሥራት ለሚሰጡ እግዚአብሔር የገባው ቃል ኪዳን ምንድን ነው?

ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር ላይ በመስረቃችን በደለኞች ነን። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ ከደመወዛቸው አሥራት አይሰጡም። ተማሪዎች ካለቻቸው ትንሽ

ገንዘብ ላይ ለእግዚአብሔር እንዳይሰጡ ይቸገረናል ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ከሰጠን ላይ የተወሰነውን ነገር መልሰን መስጠት አለብን። በአፍ ብቻ ማመስገኑ በቂ አይደለም። እውነተኛ የሆነ በረከት ከእግዚአብሔር የምናገኘው መንፈሳዊም ይሁን ሥጋዊ እግዚአብሔርን አሥራት በመስጠት ስናከብር ብቻ ነው።

## ሦስተኛ ቀን፡- ከለሳ

በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ በተደጋጋሚ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተቀደሰ መሆን እንዳለበት ተመልክተናል። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ልጆቹ ነን ብለው የሚናገሩም ሰዎች ቅዱስ መሆን አለባቸው። ቅዱስ የሚለው ቃል ሁለት ሐሳቦችን የሚገልጽ ነው። አንደኛው፤ ከኃጢአት የመለየቱ ሐሳብ ነው። ስለዚህም ነው በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ የሚገኙት አንዳንዶቹ ትምህርቶች እግዚአብሔር እንደ ኃጢአት የሚቆጥራቸውን ነገሮች የሚያስተምሩት። ሁለተኛ ደግሞ ቅዱስ ልዩ ወይም ለየት ያለ ነገር ማለት ነው። እግዚአብሔር ከፍጥረታት ሁሉ የተለየ እንደሆነ ሁሉ ሕዝቡንም የጠራቸው በአካባቢያቸው በኃጢአት ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች የተለዩ እንዲሆኑ ነው። የኦሪት ዘሌዋውያን አብዛኛው ክፍል እሥራኤላውያን የተለዩ መሆናቸውን የሚያሳዩባቸውን ብዙዎቹን የአኗኗር ዘይቤዎች ያካተተ ነው። በአምልኳቸው የኅብረ-ሥጋ ግንኙነትን በተመለከተ በአመጋገብ ዘይቤያቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ንብረታቸውን በተመለከተ ባላቸው አስተሳሰብ እና ንግግራቸውን እመቆጣጠሩ ላይ የተለዩ መሆን አለባቸው።

1. አምልኮህን በተመለከተ ቅዱስ ሁን

በጥናታችን ላይ እንዳየነው እግዚአብሔርን ለማምለክ አራት ነገሮች ያስፈልጋሉ። አንደኛው፡ የሚመለከው ነገር መኖር አለበት፤ ይኸውም እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ያለማቋረጥ እርሱ ብቻ እውነተኛው አምላክ እንደሆነ ለእሥራኤላውያን ያሳስባቸዋል። ከእርሱ የተለየ ነገር ማምለኩ ስሕተት ነው። ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር የሐሰት ምሥሎች ወይም ጣዖቶች እንዳይሰርቁባቸው መጠንቀቅ አለባቸው። እውነተኛ ሃይማኖት የሚጀምረው በእውነተኛው አምላክ ላይ ባለ እምነት ነው።

ሁለተኛ፡ የማምለኪያ ቦታ ነው። እግዚአብሔር እሥራኤላውያን በበረሃ ውስጥ እንዲሠሩለት ያዘዛቸውን የመገናኛ ድንኳን በአጭሩ ተመልክተናል።

15ኛ ጥያቄ፡- መገናኛውን ድንኳኑንና በውስጡ የሚገኙትን የአምልኮ ዕቃዎችን ግለጽ። (ከተጠራጠርክ ትምህርት አንድን ተመልከት)።

እሥራኤላውያን እግዚአብሔርን ማምለክ የሚችሉት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ብቻ ነው። ሌላ ቦታ የሚደረግ የጣዖት አምልኮን የሚያመለክት ነው። ዛሬ እግዚአብሔር እርሱን የምናመልክበትን የተለየ ቤት ለይቶ አላቆመም። በምትኩ ልባችንን እንደ እራሱ ቤተ መቅደስ በመለየት በዛ ውስጥ ይኖራል። ቤተ ክርስቲያኖች ዛሬ ክርስቲያኖች ተሰብስበው እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚጠቀሙባቸው አመቺ ቦታዎች ናቸው። እንጂ እንደ ጥንቱ መገናኛ ድንኳን አይደሉም።

ሦስተኛ፡ የሚመለክበት ሥርዓት ወይም መንገድ መኖር አለበት። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሰዎች ወደ እርሱ ቀርበው እንዲያመልኩት ጊዜያዊ የሆነውን እንስሳ የመሠዋት ሥርዓት ሰጠ። እነዚህ መሥዋዕቶች የሚቃጠለው መሥዋዕት፥ የኃጢአት መሥዋዕት፥ የበደል መሥዋዕት፥ የደኅንነት መሥዋዕትና የእህሉ ቁርባን ናቸው። እያንዳንዱ መሥዋዕት የራሱ የሆነ ዓላማ ነበረው። በእነዚህም መሥዋዕት አማካኝነት ነው ወደ ቅዱሱ አምላክ የሚወስደው ለኃጢአት ስርየት የሚያስገኘውና አምልኮ ለሃሴት የሚያበቃው የብሉይ ኪዳን መንገድ የሚከፈተው።

16ኛ ጥያቄ፡- አምስቱን ዋና ዋና መሥዋዕቶች በክለሳ መልክ አጥናቸው። ዓላማቸው ምንድን ነው? (ትምህርት ሁለትና ሦስትን ተመልከት)።

የብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት መንገድ ጊዜያዊ ነበር። ሆኖም እውነተኛ መሥዋዕት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣበትን ቀን የሚያመለክት ነበር። ቀጥለን የምናጠናው የዕብራውያን መጽሐፍ ብዙው ክፍል እንዴት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ታላቁ ሊቀ ካህን እና እንደ ዘላለማዊው መሥዋዕት ሆኖ የጊዜያዊ መሥዋዕቶቹን ሥራ እንደፈጸመ ያመለክታል። የዚህ የደም ሐሳብ የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት ከማጤን አስፈላጊነት ጋር የተያያዘ ነው። በፈሰሰው ደም አማካኝነት ብቻ ነው ምሕረት የተገኘው፤ (ኦሪት ዘሌዋውያን 17፡11)። የእንስሳው ደም በኃጢአተኛው ሕይወት ፈንታ ስለ ኃጢአተኛው ኃጢአት ሲባል የተሠዋውን የእንስሳውን ሕይወት የሚያመለክት ነው። ልክ እንደዚሁ በእኛ ፈንታ ኢየሱስ መሞቱንና የደኅንነትን መንገድ መክፈቱን የሚያመለክተው ደሙ ነው።

በብሉይና በአዲስ ኪዳን የተወሰኑ የአምልኮ ሥርዓቶችን መከተላችን ለትክክለኛ አምልኮ ማስረጃ እንደማይሆኑ ያለማቋረጥ ያስገነዝቡናል። አምልኮ የሚጀመረው በልባችን ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት ነው። እውነተኛ የሆነ አምልኮ ሊኖር የሚችለው ኃጢአት ይቅር ሲባልና የሚያመልከው ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሙሉ ልቡ ሲጠብቅ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር የተወሰኑ ቀናትን በመለየት እሥራኤላውያን በእርሱ ላይ ሐሳባቸውን እንዲያተኩሩ አድርጓል። በየሳምንቱ የሚከበረው ሰንበትና ሌሎች ሰባት ክበረ በአሎች ነበሩ። ሰባተኛው ዓመትና ሃምሳኛው ዓመታት ለየት ያሉ ዓመታት ነበሩ። (ትምህርት አምስትና ሰባትን ተመልከት)። እግዚአብሔር እሥራኤላውያን ሐሳባቸውን በእርሱ ላይና በአምልኮ ላይ እንዲያደርጉ ለመርዳት የሚጠቀምበት መንገድ ነው።

ለአምልኮ የሚያስፈልገው አራተኛው ነገር የአምልኮው መሪ የሆኑት ካህናት ናቸው። ብዙዎቹ በኦሪት ዘሌዋውያን ላይ የሚገኙት መመሪያዎች ካህናቱ እንዴት ተለይተው የአምልኮውን ሥርዓት እንደሚመሩ የሚገልጽ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ሕዝቡን የሚወክሉ እነርሱ በመሆናቸው ሊወስዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ጥምር ያካትታል።

በጥናታችን ላይ የመጨረሻው ሊቀ ካህን ኢየሱስ እንደሆነ ተመልክተናል። በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አማላጅ ሆኖ የቆመው እርሱ ብቻ ነው። ካሁን ወዲያ

ሰው የሆነ ካህን ወይም አማላጅ አያስፈልገንም። ሆኖም ካህናቱ ልክ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደሆኑ ተመልክተናል። አኗኗራቸውንም በተመለከተ እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚጠብቀውን የቅድስና አኗኗር እንደ ምሳሌ የሚያሳይ መሆን እንዳለበት እግዚአብሔር ያሳስባቸዋል።

17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለአምልኮ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ ልንግራቸው የምንችላቸውን ትምህርቶች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) እነዚህ ነገሮች በቤተ ክርስቲያንህ ያለውን አምልኮ እንዴት አድርገው ነው ሊያሻሽሉት የሚችሉት?

# አራተኛ ቀን፡-

2. ጋብቻህንና የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ኑሮህ በተመለከተ ቅዱስ ሁን

እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው ቅድስና የግብረ-ሥጋ ግንኙነታችንንም የሚያካትት ነው። እግዚአብሔር ከጋብቻ በፊት ምንም ዓይነት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምድ እንዳይኖረን ያዘናል። ከጋብቻ በኋላም ጋብቻችን ከተሳሳተ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአቶች ነፃ መሆን አለበት።

3. የአመጋገብ ባህርይህን በተመለከተ ቅዱስ ሁን

አሪት ዘሌዋውያን እሥራኤላውያን ሊመገቡ የሚችሏቸውንና የማይችሏቸውን ምግቦች በዝርዝር ይገልጻል! (ትምህርት አራትን ተመልከት)። እግዚአብሔር እነዚህን ሕግጋት የሰጠበት ሁለት ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ ሕግጋቱ የተደነገጉት የሕዝቡን ጤንነት ለመጠበቅ ነው። ሁለተኛ እሥራኤላውያንን ካልተመረጡ ሕዝቦች ለመለየት ተብለው የተደነገጉ ሕግጋት ናቸው። እነዚህ የምግብ ሕግጋት ዛሬ እኛ ላይ ምንም ዓይነት ተግባራዊነት የላቸውም።

4. ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት በተመለከተ ቅዱስ ሁን

በብሉይ ኪዳንም ቢሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙነት በፍቅር ላይ መመሥረት እንደሚኖርበት እናነባለን። እግዚአብሔር ሕዝቦቹ ልክ እንደ እርሱ ፍቅር ምሕረትና ትክክለኛ ፍርድ እንዲያሳዩ ይፈልጋል። ስለዚህም ነው እግዚአብሔር ሕዝቦቹ ደሆችን እንዴት አድርገው መንከባከብ እንደሚገባቸው የሚገልጽ መመሪያ የሰጣቸው። ያለምንም አድልዎ ወይም ቅጣት ሕዝቡ በትክክለኛ ፍርድ የሚኖርበትም መመሪያዎች ተሰጥተዋል።

5. ንብረትህን በተመለከተ ያለህ አስተሳሰብ ቅዱስ ይሁን

ንብረቶቻቸውን በተመለከተ እግዚአብሔር የተወሰኑ መመሪያዎችን ለእሥራኤላውያን ሰጥቷል። የሚኖሩበት ምድርና ሁሉም ነገር የእርሱ እንደሆነ አስተምሯቸዋል። እነርሱ የንብረቶቹ ወኪሎች ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ሥጋዊ በረከት ላይ እንዳይታመኑ አስተምሯቸዋል። እንዲያውም ለሁለት

ዓመት ያህል እንዲያርሱ በሚያዛቸውም ወቅት እንኳን ቢሆን በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት መጠበቅ አለባቸው። በዛሬው ዓለም ኑሮን ማሸነፋችን የሚለካው ባለን ንብረት ነው፤ ስለዚህም በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ትምህርት ማስታወስ ይገባናል። ያለን ንብረት በሙሉ የእግዚአብሔር ስለሆነ በጥንቃቄ ለእርሱ ክብር ልናውለው ይገባናል። ለእኛ ክብር ወይም የግል ጥቅም መዋል የለበትም። አሥራትና ምፅዋት በመስጠት እርሱን ማክበር እንዳለባቸውም ያሳስባቸዋል።

6. ምላስህን በመጠበቅ ቅዱስ ሁን

እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ታማኞችና አደራ ተቀባዮች እንዲሆኑ ይፈልጋል፣ ይጠብቅባቸዋልም። ቃላቸውን መጠበቅ ነበረባቸው። ከሁሉም በላይ ለእግዚአብሔር የተሳሉትን ስለት መፈጸም ነበረባቸው።

ኦሪት ዘሌዋውያን እግዚአብሔር አሁድ አሁድ ስናመልከው ብቻ ሳይሆን ሁሌም የሕይወታችን ጌታ መሆን እንዳለበት ያስተምረናል። በሥራ ላይ፣ በትምህርት ገበታ፣ በቤተሰባችን መካከል፣ በጨዋታ ላይ፣ በአእምሮአችንና በንግግራችን እግዚአብሔርን ለይተን ማክበር አለብን። እኛም እንደ እግዚአብሔር ቅዱሳን መሆን ካለብን ከእኛነታችን እግዚአብሔር እንዲጠቀምበት ያልሰጠነው ምንም ክፍል ሊኖር አይገባም። ሁለንተናችንን ለእርሱ መስጠት አለብን።

18ኛ ጥያቄ፡- በእነዚህ ስድስት ነገሮች እግዚአብሔርን ያከበርከው እንዴት ነው? በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖርህ በሕይወትህ ውስጥ ልትቀይራቸው የሚገቡ ሌሎች ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

19ኛ ጥያቄ፡- እነዚህን ስምንት ትምህርቶች ከልስ። አንተና የቤተ ክርስቲያንህ አባላት በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንድትኖሩ የሚያደርጓችሁን በሕይወታችሁ ተግባራዊ ልታደርጓቸው የምትችሏቸውን የኦሪት ዘሌዋውያን መመሪያዎችን በዝርዝር ጻፍ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የመወያያ ጥያቄዎች

ሀ) 1. የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ከጠበክ እግዚአብሔር እሰጥሃለሁ ብሎ ቃል የገባልህ በረከቶች ምን ምንድን ናቸው?

2. በማይታዘዙ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር እቀጣቸዋለሁ ብሎ ቃል የገባው ቅጣቶች ምን ምንድን ናቸው?

ለ) 1. በዛሬ ጊዜ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው እንደ ጣዖት ሊያደርጓቸው የሚችሉ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

2. እራሳችንንና ሌሎችን ጣዖት የሆነ ነገር እንዳይኖርብን የምንጠብቀው እንዴት ነው?

ሐ) 1. አሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 27 ስለቶቻችንን ስለመጠበቅ የሚያስተምረን ምንድን ነው?

2. ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር የሚሳሉትን ስለትና ለሰዎች የሚገቡትን ቃል ኪዳን የመጠበቃቸው አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

3. አንተና ብዙ ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት የምታደርጓቸውን ስለቶች በዝርዝር ጻፍ። ስለቶቹ እንዴት እንደተፈጸሙ ግለጽ።

መ) 1. በአሪት ዘሌዋውያን ያሉትን ትምህርቶች ከልስ። ትምህርቶቹን ዘርዝረህ በአንድነት ጻፋቸው።

2. እነዚህን እውነታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ማስተማር እንደምትችሉ ተወያዩ።

5. ጸሎት

# ትምህርት ዘጠኝ

## የዕብራውያን መጽሐፍ መግቢያ

### የመጀመሪያ ቀን:-

በአሪት ዘሌዋውያን ጥናታችን፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን የማምለኪያ ቦታ የነበረውን መገናኛ ድንኳን የብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት አምልኮ ሥርዓትና የብሉይ ኪዳኑ የአምልኮው ሥርዓት መሪዎች የሆኑትን ካህናት ተመልክተናል። የዕብራውያን መጽሐፍ እነዚህን ነገሮች ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር ሁሉ ጥላ በማለት ይሰይማቸዋል! (ዕብራውያን 8:5፥10:1)። ዕብራውያን ጥናታችን የኢየሱስን ምዕዐትና የትንቢቶችን ፍጻሜ ከሚያመለክተው የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ይልቅ የሚሻለውን ኢየሱስ የከፈተውን የአምልኮ ሥርዓት እናጠናለን። በዚህ ሥፍራ እውነተኛ የሆነውን የእግዚአብሔር መኖሪያና መንፈሳዊ አምልኮ ስለሚካሄድበት መንግሥት ስማያት እናነባለን። አምልኮው የሚካሄደው የመጨረሻው ፍጹም መሥዋዕት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። ፍጹም የሆነውም ሊቀ ካህን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አዲስ ኪዳንን በሚመሠርትበት ወቅት ነው እራሱ ይህን አዲሱን የአምልኮ መንገድ ለሰው ልጆች በሙሉ የከፈተው።

አንድ ሰው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ትምህርቶች ካላወቀ የዕብራውያንን መጽሐፍ ለመረዳት ይከብደዋል። በዚህም ምክንያት ነው በመጀመሪያ አሪት

ዘሌዋውያንን የተመለከትነው። ይህም ሆኖ ብሉይ ኪዳንን በአዲስ ኪዳን በኩል ሆነን ካልተመለከትነው ልንረዳው አንችልም። የዕብራውያን መጽሐፍ ልናጠናው የሚገባን በጣም አስፈላጊ መጽሐፍ ነው ምክንያቱም የኢየሱስ ሊቀ ካህን መሆን በመስቀል ላይ በመሠዋት የተገኘውን ውጤትና ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የሚገኙትን ትንቢቶችና ሕጋጋት ሁሉ ፈጻሚ መሆኑን በግልጽ የሚያስረዳን በመሆኑ ነው።

**የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ**

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የዕብራውያንን መጽሐፍ ርዕስ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመልከት።

ለ) መጽሐፉን የጻፈው ማን ነው የሚለው?

የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈው ጳውሎስ ነው ይላል። ምንም እንኳን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ይህ የተለመደ አመለካከት ቢሆንም የመጀመሪያው የዕብራውያን ጽሑፍ ጸሐፊው ማን እንደሆነ አይናገርም። ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው አንዳንድ ሰዎች የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ጳውሎስ ነው ያሉት።

በሐቀ ከሄድን ግን እውነተኛው የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ አይታወቅም። የሚከተሉት ሐሳቦችም ተሰንዝረዋል፡-

1. ሐዋርያው ጳውሎስ፡- በየዘመኑ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብዙ ሰዎች ይህን መጽሐፍ የጻፈው ጳውሎስ ነው ብለው ያምናሉ። እነዚህ ሰዎች በዕብራውያን ውስጥ ያለው ሐሳብ ከሌሎቹ ከብዙ የጳውሎስ ጽሑፎች ጋር ይመሳሰላሉ ይላሉ። ጳውሎስ በታወቀ መምህር (ረቢ) የተማረ በመሆኑና ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቆ በማወቁ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ብቁ ነው ይላሉ።

ሆኖም ይህ አመለካከት አንዳንድ ችግሮች አሉት፤ አንደኛ፡- በዕብራውያን ውስጥ ያለው የቋንቋ አጠቃቀም ጳውሎስ በሌሎቹ መጽሐፍቱ ውስጥ ከጻፋቸው ጋር በጣም ልዩነት አለው። ሁለተኛ እንደ ጳውሎስ ልማድና ጸሐፊው ለአንባቢያኑ ስሙን አልጠቀሰም፤ (ለምሳሌ ሮሜ 1፡1፥ 1ኛቆሮ.1፡1 ወዘተ...)። ሦስተኛ ጸሐፊው ወንጌልን ከኢየሱስ ሳይሆን የኢየሱስን ትምህርት ከሰሙት የዓይን ምሥክሮች ላይ ነው የተቀበልኩት ነው የሚለው፤ (ዕብራውያን 2፡3 ተመልከት)። ሆኖም ጳውሎስ ወንጌልን የተቀበልኩት ከኢየሱስ ላይ ነው ይላል፤ (ገላትያ1፡11-12)። ስለዚህም ጸሐፊው ጳውሎስ አይመስልም።

2. አጵሎስ፡- አጵሎስ የተማረ ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቆ የሚያውቅ ከእስክንድርያ ወገን የመጣ አይሁዳዊ ሰው ነው፤ (የሐዋ.18፡24 ተመልከት)። በእስክንድርያ ያሉ አይሁዳውያን ስለ ብሉይ ኪዳን ያላቸው አመለካከትና የዕብራውያን ጸሐፊ ስለብሉይ ኪዳን ያለው ግንዛቤ በመመሳሰሉ ምክንያት ጸሐፊው አጵሎስ ነው የሚል ሐሳብ ተሰጥቷል።

3. በርናባስ፡- በርናባስ ምንም እንኳ ምናልባት ኢየሱስን በዓይኑ ባያይም በኢየሱስ የሚያምን የቆየ አማኝ ነው። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም የታወቀ ሰው ሲሆን

በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም ቀጥሎ በአንጾኪያ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። ዘሩ የአይሁድ ሌዊ በመሆኑ የብሉይ ኪዳንን ሥርዓቶች ስለመግሩ ምንም ጥርጥር አይኖረንም። የሐዋርያት ሥራ 4:36)። ከጳውሎስም ጋር በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሉ ከሚባሉት ወንጌላዊያን መካከል አንዱ ነበር።

2ኛ ጥያቄ:- በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ስለ እነዚህ ሰዎች በመመልከት፤ የሕይወት ታሪካቸውን ስለ አኗኗራቸው አንብብ።

ምንም እንኳ የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈውን ሰው በተመለከተ ያሉት የታወቁ ሐሳቦች እነዚህ ቢሆኑም ጸሐፊው ማን እንደነበር በእርግጥ የሚታወቅ ነገር የለም። ነገር ግን ጸሐፊው በብሉይ ኪዳንና በግሪኩ ቋንቋ በደንብ የሰለጠነ መሆኑን እናውቃለን። ስለ ኢየሱስ ከሌሎች ነው የሰማው እንጂ በዓይኑ አላየውም። ይህም ቢሆን ብሉይ ኪዳን ሙሉ በሙሉ እፍጻሜ ላይ ያደረሰው ኢየሱስ እንደሆነ በደንብ ተገንዝቧል። መልዕክቱን የሚቀበሉት ሰዎች የሰውዬውን ማንነት ስለሚያውቁ ስሙን መጻፍ አስፈላጊ አይሆንም።

# የመልዕክቱ አንባቢዎች

የዕብራውያን መጽሐፍ ለእነማን እንደተጻፈ አይጠቅስም። ምንም እንኳን አንዳንድ ምሁራን መልዕክቱ የተጻፈው አሕዛብ ለሆኑ ክርስቲያኖች ነው ቢሉም መልዕክቱ ለአይሁዳውያን ክርስቲያኖች የተጻፈ ነው የሚመስለው። መልዕክቱ ከተጻፈ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ነው ሀዕብራውያንሀ የሚል ስያሜ የተሰጠው። ይህም «ለዕብራውያን ወይም ለአይሁዳውያን ክርስቲያኖች የተጻፈ» ማለት ነው።

በአንደኛው ክፍለ ዘመን ብዙዎቹ ክርስቲያኖች አይሁዳውያን ነበሩ። በሐዋርያት ሥራ ኢየሱስ ካረገ በኋላ በሮማው መንግሥት ሥር የሚገኙ ብዙ አይሁዳውያን ኢየሱስ መሢሁ ነው ብለው እንዳመኑበት እናነባለን። ሃይማኖትን በተመለከተ አይሁዳውያን በሮማው መንግሥት ለየት ያሉ እንክብካቤዎች ስለሚደረግላቸው አይሁዳውያኖቹ ክርስቲያኖች በሮማውያኖቹ ጊዜ ስደት አልደረሰባቸውም ሆኖም የአሕዛብ ክፍል የነበረው ቤተ ክርስቲያን ሲያድግ ሮማውያኑ እንደተለየ ሃይማኖት ቆጠሩትና ክርስትናን አወገዙ። በዚህም ምክንያት አሁን አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነ ስደት ይደርስበታል። የዕብራውያን አንባቢዎች ስደት የተቀበሉ ቢሆንም እስካሁን ከመካከላቸው የሞተ ሰው የለም (ዕብራውያን 10:33-34)። ከሮማውያን የሚመጣው ስደት ከጨመሩ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ስደቱን ለማምለጥ ሲሉ ወደ ድሮው ሃይማኖታቸው ጁዲዝም እንለውጣለን። ብለው ማሰብ ጀመሩ፤ በዚህ ጊዜ ነው ጳውሎስና ጴጥሮስ በሮም ሞት የተፈረደባቸው።

ሮማውያኖቹ ስደቱን በሚያጧጡፉበት ጊዜ በፍልስጤም የሚገኙ አይሁዳውያን በሮማው መንግሥት ላይ አመፁ። ይህ ዓመፅ በ66 ዓ.ም. ተጀምሮ እስከ 70ዓ.ም ድረስ ቆይቷል። በእነዚህ ዓመታት አይሁዳውያን በሙሉ በዚህ ዓመፅ ውስጥ እንዲሳተፉ ተፅዕኖ ይደረግ ነበር። ይህንን ዓመፅ ያልደገፈ አይሁዳዊ ወይም ይህን

ጁዲዝም የተባለውን የአይሁዳውያንን ሃይማኖት ያልተከተለ ሰው ከራሱ ሕዝቦች ጠንከር ያለ ተቃውሞ ነበር። የሚደርስበት። ስለዚህም በእነዚህ ዓመታት ክርስቲያን የሆኑ አይሁዳውያን ክርስትናን ትተው ጁዲዝም ወደ ተባለው የእሥራኤል ሕዝብ ሃይማኖት እንዲመለሱ ከበድ ያለ ተፅዕኖ ተደርጎባቸዋል።

እነዚህ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች የት እንደሚኖሩ አናውቅም። አንዳንዶች በፈልስጤምና በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ አይሁዶች ናቸው ብለው ያስባሉ። ሆኖም ጸሐፊው ከእነርሱ ኢየሱስን ያየው ማንም የለም በማለቱ ይህ አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከተጻፈው ብሉይ ኪዳን ላይ ከመጥቀስ ጸሐፊው ብዙ ጊዜ ይጠቅስ የነበረው ሴፕቱጀንት ከተባሉት የግሪክ ቅዱሳት መጽሐፍት ነው።

የዕብራውያን መጽሐፍ ከፍልስጤም ውጪ ለሚገኙ አይሁዳውያን የተጻፈ ምንም እንኳ የተጠቀሱት ቦታዎች ብዙ ቢሆኑም ይህ መልዕክት የተጻፈው ሮም ውስጥ ለሚገኙ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች ይመስላል። ለዚህም ነው ጸሐፊው ሀከኢጣሊያ የሆኑት ሰላምታ ያቀርቡላችኋልሀ ብሎ የጻፈው። ይህም በሮማ የሚገኙ ክርስቲያኖች እዛው ሮም ውስጥ ለሚኖሩ ለሚያውቋቸው ሰዎች ሰላምታ ላኩ ማለት ነው። በተጨማሪም ለመጀመሪያ ጊዜ ከዕብራውያን መጽሐፍ የተጠቀሰው ሮም ውስጥ በሚገኘው የቤት ክርስቲያን መሪ ሲሆን ጊዜውም በ90 ዓ.ም. ነበር።

# የተጻፈበት ጊዜ

ጸሐፊው ማን እንደሆነና የተጻፈው ለእነማን እንደሆነ ስለማናውቅ የተጻፈበትን ጊዜ ለመናገር ይከብዳል። በ90ዓ.ም. አካባቢ ግን ይህን መልዕክት በቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ይገለገሉበት እንደነበር እናውቃለን። ጸሐፊው በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን ሥርዓት እስካሁን ቢጠቀሙበትም በአዲሱ የሚተካበት ጊዜ ቀርቧል ብሎ ስለጻፈ (ዕብራውያን 8፡13 ተመልከት)፤ ምናልባት ይህ መልዕክት የተጻፈው ከ70 ዓ.ም. ትንሽ ቀደም ብሎ ሳይሆን አይቀርም። በ70 ዓ.ም. ሮማውያን ፍልስጥኤማውያንን ድል አድርገው ቤተ መቅደሱን አፍርሰው አይሁዳውያንን በትነዋቸዋል። ከዛ ጊዜ አንሥቶ እስከዛሬ ድረስ አይሁዳውያን የሚያመልኩበት ቤተ መቅደስ የላቸውም፤ የብሉይ ኪዳኑም የመሥዋዕት አምልኮ ቀርቷል። ስለዚህ የዕብራውያን መጽሐፍ ከ65-70 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው የተፃፈው ብሎ ማሰቡ ከሁሉም የተሻለ ይመስላል።

3ኛ ጥያቄ፡- ስለ ዕብራውያን መጽሐፍ የተናገረውን ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ አንብብ።

# ሁለተኛ ቀን፡-

4ኛ ጥያቄ፡- የዕብራውያንን መጽሐፍ ከምዕ.1-13 ያለውን በሙሉ አንብብ።

ሀ) ኢየሱስ ይበልጣቸዋል የሚባሉትን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ለክርስቲያኖች የተሰጡትን የተለያዩ ማስጠንቀቂያዎች በዝርዝር ጻፉ።

ሐ) የዕብራውያንን መጽሐፍ ዋና ዋና ሐሳቦች በዝርዝር ጻፉ።

# ሦስተኛ ቀን፡-

## የዕብራውያን መጽሐፍ የተጻፈበት ምክንያት

5ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 2፡1-3 አንብብ። በእነዚህ ቁጥሮች ጸሐፊው ለአንባቢያኖቹ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

የዕብራውያን መልዕክት የተጻፈው አይሁዳውያን ክርስትናን ትተው ወደ ድሮው ጁዲዝም ወደ ተባለው ሃይማኖት ከሄዱ የሚከተላቸውን ችግር ለመግለጽ ነው። ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ያሉትን ቃል ኪዳኖች በሙሉ እንደፈጸመ ያሳስባቸዋል። የብሉይ ኪዳኑን የአምልኮ ሥርዓት ተክቶታል። ስለዚህም ወደ ድሮው የአምልኮ ሥርዓት ለመመለስ መሞከሩ ጥቅም ወደሌለው ሊያድን ወደማይችለው ነገር እንደመመለስ ነው የሚቆጠረው። ኢየሱስ ክርስቶስን ችላ ካሉት አንዱን ብቸኛውን የመዳን መንገድ ችላ ብለው እንደተዉት ነው የሚቆጠረው። በተጨማሪም ይህንን እምነት ለካዱ ምንም ዓይነት ሌላ የደህንነት መንገድ አይኖርም።

6ኛ ጥያቄ፡- ይህ መልዕክት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ችግር ውስጥ ላሉ ክርስቲያኖች ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

የዕብራውያን መጽሐፍ ዋና ዋና ሐሳቦች ዝርዝር

ከዚህ ቀጥሎ የዕብራውያን ዋና ዋና ሐሳቦች ዝርዝር እንገልጻለን።

1. ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ከገለጻቸው ራዕዮች ሁሉ ይበልጣል፤ (1፡1-4)።
2. ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ከነበሩት መሪዎች ሁሉ ይበልጣል፤ (1፡5-ምዕራፍ 7)።
   ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላዕክት በላይ ነው፤ (1፡5-2፡18)።
   ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ በላይ ነው፤ (3፡1-4፡13)።
   ሐ) ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮናውያን ካህናት ሁሉ ይበልጣል፤ (4፡14-7፡28)።
3. ኢየሱስ የከፈለው የመሥዋዕትነት ሥራ ከሁሉም ይበልጣል፤ (ከምዕራፍ 8-10)። ኢየሱስ ክርስቶስ የተሻለ ኪዳን መሠረተ። እሱም አዲሱ ኪዳን ተብሎ የተሰየመው ነው።
   ሀ) የአዲሱ ኪዳን ምሥረታ የጀመረው ኢየሱስ ነው፤ (ምዕራፍ 8)።
   ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ከፊተኛው በተሻለ ቤተ መቅደስ ነው፤ ( 9፡1-12)።
   ሐ) ኢየሱስ ክርስቶስ የተሻለ መሥዋዕት ነው ያቀረበው፤ (9፡13- ምዕራፍ 10)።

4. ክርስቲያኖቹ በኢየሱስ ያላቸውን እምነት እንዲጠብቁ የተደረገ የመጨረሻ ልመና፤ (ከምዕራፍ 11-12)።

5. ለክርስቲያኖቹ የተሰጠ የመጨረሻ ምክር፤ (ምዕራፍ 13)።

# አራተኛ ቀን፡-

## የዕብራውያን መጽሐፍ መሪ ሐሳብ

የዕብራውያን መሪ ሐሳብ አሥራ አምስት ጊዜ በተጻፈው ሀየሚበልጥሀ ወይም ሀየበላይሀ በሚለው ቃል ውስጥ ይታያል። የዕብራውያን ጸሐፊ የፈለገው የአይሁድ ክርስቲያኖች በአይሁድ ሃይማኖት ተስፋ ከሚያደርጉት ማናቸውም ነገር ኢየሱስ በጣም እንደሚበልጥ ለማሳየት ነው። ከዚህም ጋር በማነፃፀር ጸሐፊው አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን ከካደ ወይም ከተወ የሚያጋጥመውን ነገር ይገልጻል።

7ኛ ጥያቄ፡- ሰዎች ዛሬ ኢየሱስ ክርስቶስን ከመከተል ፈቀቅ የሚሉባቸውን ወይም የሚተዉበትን አንዳንድ ምክንያቶች ዘርዝረህ ጻፍ።

የዕብራውያን መጽሐፍ ዋና ዋና ትምህርቶች

የዕብራውያን መጽሐፍ ትምህርቶች ትኩረት የሚሰጡት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ስለ ሠራው ሥራ ነው። ክርስትናን ከሌሎች ሃይማኖቶች ለየት የሚያደርገው ዋነኛው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ምንም እንኳ ሌሎች ሃይማኖቶች በውስጣቸው ጥሩ ነገር ቢኖራቸውና ብዙ ጥሩ ጥሩ ሰዎች ቢከተሏቸውም ሰዎቹ ደኅንነትን የማያገኙት በኢየሱስ ክርስቶስ ስለማያምኑ ነው።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በሌላ ሃይማኖት ውስጥ ያሉ ጥሩ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ ብሎ የሚያምን ሰው ታውቃለህ?

ለ) ለምንድን ነው አንዳንዶ በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ወደ ገሃነም እሳት ይገባሉ ብሎ ማመኑ የሚከብደው?

9ኛ ጥያቄ፡- አንድ ሰው መዳን ከፈለገ ያለው አንድ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብለው የሚገልጹት እነዚህን ጥቅሶች ተመልከት፤ ዮሐ.14፡6 እና የሐዋ.4፡12።

ምንም እንኳ በሌላ ሃይማኖት ውስጥ ያሉትን ሰዎች መታገሡ ለአንዳንድ ክርስቲያኖች የተለመደ ቢሆንም የወንጌሉ እውነታ እነዚያ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ተቀብለው የሚያምኑና ትዕዛዙን የሚጠብቁ ብቻ ናቸው የሚድኑት ነው የሚለው። ሰዎች ጥሩ ከሆኑ ይድናሉ የምንል ከሆነ ኢየሱስ የሞተው ምንም ጥቅም ለሌለው ነገር ነው ማለት ነው። የዕብራውያን ጸሐፊ ቁልጭ አድርጎ እንደጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክድ ማንኛውም ሰው የመዳን ተስፋ የለውም የሚጠባበቀውም የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው። ይህ እውነታ ክርስቲያኖች በማንኛውም ሃይማኖት

ለሚገኙ ሰዎች እንዲመሠክሩ ያደፋፍራል። በዚህም ምክንያት ነው ጳውሎስ «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ» ብሎ የተናገረው።

10ኛ ጥያቄ:- ለእሥላሞችና ለአንዳንድ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት ለሌላቸው የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ይህ ምን ማለት ነው?

11ኛ ጥያቄ:- ከክርስቲያን ቤተሰብ ስለተወለድክ ወይም ጥሩ ሥራ ስለምትሠራ እድናለሁኝ ብለህ ታምናለህ? ሕይወትህን አሁን መርምርና በኢየሱስ ያለህ እምነት እውነተኛ ካልሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልብህ ገብቶ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲያደርግህ ጸልይ።

12ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች ወንጌልን በማካፈል ምን ያህል ቀልጣፎች ናቸው? ለ) እምነታቸውን በማካፈል በይበልጥ ቀልጣፎች እንዲሆኑ አንተስ እንዴት እያነሣሣሃቸው ነው?

ክርስትና የተመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስለሆነ የዕብራውያን ጸሐፊ በትምህርቱ ትኩረት የሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ ጸሐፊው ትኩረት የሰጣቸው ሦስት ዋና ዋና ትምህርቶች አሉ።

ሀ) የእግዚአብሔር ልጅ ባህርይ

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር ነው። የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው፤ ባህርይው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ዓይነት ነው፤ ዘላለማዊ ነው።
2. ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ሰው ነው። የሰውን አምሳያ ይዞ በመምጣቱ ልክ እንደ ሰው በኃጢአት ተፈትኗል፥ ተሰቃይቷልም።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት የለበትም። ምንም እንኳ ኃጢአት እንዲሠራ ቢፈተንም ኃጢአትን ድል አድርጎ ከኃጢአት ነፃ የሆነው እርሱ ብቻ ነው።
4. ኢየሱስ ክርስቶስ የሰዎች ሁሉ ሊቀ ካህን ነው። የሊቀ ካህንነቱንም ሙሉ መብት ያገኘው በመከራ ውስጥ በማለፍና በመታዘዝ ነው።
5. ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ ብሎ ከከበረ በኋላ በአሁኑ ጊዜ የደኅንነት ሥራውን ጨርሶ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል።

ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ መሪዎች ጋር ሲነፃፀር።

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ከታላላቅ መላዕክት ሁሉ በላይ ነው።
2. ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢያሱ ይበልጣል።
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህን ከነበረው ከአሮን ይበልጣል።

ሐ) የሊቀ ካህኑ የእግዚአብሔር ልጅ ሥራ

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ከበፊቱ የሚበልጠውን ቃል ኪዳን የመሠረተ ነው።

2. ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ታላቅና ፍጹም መሥዋዕት ሆኖ ነው።

3. ኢየሱስ ክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሥራውን ፈጽሞአል። ስለዚህም አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል።

4. ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን የሚኖረው ለእኛ ለመማለድ ነው።

5. ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን የሚሠራው ከበፊቱ በሚበልጠው ቤተ መቅደስ በመንግሥተ ሰማያት ነው።

በዕብራውያን ጥናታችን ትኩረት የምናደርገው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። ጸሐፊው እንደተናገረው የእምነታችን ራስና ፈጻሚ የሆነውን ኢየሱስን መመልከት ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር መኖሪያ ቦታ ወደ ሆነው ወደ መንግሥተ ሰማያት የምንደርሰው በምድራዊ ጊዜያችን ኢየሱስን ስንከተል ብቻ ነው።

13ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያኖች ሐሳባቸውን ወደ ኢየሱስ መሰብሰባቸውን እንዴት ማሳየት እንደሚችሉ ምሳሌ በመስጠት አስረዳ።

# አምስተኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና በውይይቱ ጊዜ እንድት ዘጋጅ የውይይቱን ጥያቄዎች ተመልከት።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የመወያያ ጥያቄዎች

ሀ) 1. አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት ለመተው የፈለጉት ለምንድን ነው?

2. ለምንድን ነው ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ያላቸውን እምነት የሚተዉት?

ለ) 1. ለምንድን ነው አንዳንድ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ጥሩ ሰዎች ወደ ገሃነም እሳት ይገባሉ ቢባሉ ማመኑ የሚከብዳቸው?

2. ሁሉም ሃይማኖቶች ጥሩና ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስዱ ልዩ ልዩ መንገዶች ናቸው ለሚልህ ሰው እንዴት አድርገህ ነው የምትመልስለት? ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስህን ተጠቀም።

ሐ) 1. የዕብራውያን ዋና ዋና ትምህርቶች ናቸው ብለህ የጻፍካቸውን ዝርዝር ከሌሎች ሰዎች ዝርዝር ጋር አነፃፅርና ለምን እንደ ዋና ትምህርት ዘርዝረህ እንደጻፍካቸው አስረዳ።

2. የጻፍካቸውን ዋና ዋና ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ ለሚገኙ ምዕመናን እንዴት አድርገው እንደሚግሯቸውና ተግባራዊ እንደሚያደርጓቸው ገለጽ።

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥር

ዕብራውያን ከምዕራፍ 1-2

## የመጀመሪያ ቀን:- ዕብራውያን 1፡1-3

በዚህ ሳምንት የዕብራውያንን የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምዕራፎች እናጠናለን። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የኢየሱስን ታላቅነት በሁለት ዋና ዋና መንገዶች እንመለከታለን። በመጀመሪያ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለሰዎች ከሰጠው ራዕዮች ሁሉ የሚበልጥና የመጨረሻ ራዕይ ነው። ሁለተኛ ከታላቁ መልአክም እጅግ ይበልጣል።

እኛ የምናመልከው አምላክ ዝምተኛ አይደለም። ለሰዎች የሚናገርና ፈቃዱን የሚገልጽ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይናገራል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለሰዎች በፍጥረታቱ ውስጥ ሆኖ ይናገራል! (ሮሜ 1፡18-20 ተመልከት)። ይህ መገለጥ ግንም ሰው ቢድንም ባይድንም ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ ነው። ሁለተኛ እግዚአብሔር ለሰዎች ቃሉ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይህ ደግሞ የተለየ መገለጥ በመባል ይታወቃል። ይህን ዓይነቱ መገለጥ የተሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ቃል ለሚማሩ ሰዎች ብቻ ነው።

1ኛ ጥያቄ:- የእግዚአብሔር ለሰዎች ፈቃዱን መግለጽና ሰዎችን ማናገሩ ለምንድን ነው አስፈላጊ የሆነው?

የእግዚአብሔርን ማንነትና ከእርሱ ጋር እንዴት አድርገን ኅብረት ሊኖረን እንደሚችል ልንገነዘብ የምንችለው በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነው። በዚህ ሥፍራ ነው እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ነገርና ወደ መንግሥተ ሰማያት የምንደርስበትን መንገድ የሚገልጽልን። እውነተኛውን ነገር ማወቅ የምንችለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዚህም ነው ትምህርቶች ሁሉ እውነተኛ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ ልንገመግም የምንችለው።

ብዙ የሐሰት ሃይማኖቶች ከእግዚአብሔር የመጡ ናቸው የሚሏቸው ብዙ ጽሑፎች አሏቸው። ለመጥቀስ ያህል እስላሞች ቁርዓን አላቸው። ሌሎች ክርስቲያን ነን የሚሉ ሐሰተኞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ክብደት ያላቸው ሌሎች መጻሕፍቶች አሉ ብለው ይናገራሉ።

2ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኙ ለየት ያሉ ጽሑፎች ወይም ራዕዮች ወይም ትምህርቶች የሚያስተምሩ አንዳንድ የሐሰት አስተማሪዎችን ወይም ሙዋርተኞችን ጥቀስ።

2. የጻፍካቸውን ዋና ዋና ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ ለሚገኙ ምዕመናን እንዴት አድርገው እንደሚግሯቸውና ተግባራዊ እንደሚያደርጓቸው ገለጽ።

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥር

ዕብራውያን ከምዕራፍ 1-2

## የመጀመሪያ ቀን:- ዕብራውያን 1፡1-3

በዚህ ሳምንት የዕብራውያንን የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምዕራፎች እናጠናለን። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የኢየሱስን ታላቅነት በሁለት ዋና ዋና መንገዶች እንመለከታለን። በመጀመሪያ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለሰዎች ከሰጠው ራዕዮች ሁሉ የሚበልጥና የመጨረሻ ራዕይ ነው። ሁለተኛ ከታላቁ መልአክም እጅግ ይበልጣል።

እኛ የምናመልከው አምላክ ዝምተኛ አይደለም። ለሰዎች የሚናገርና ፈቃዱን የሚገልጽ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይናገራል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለሰዎች በፍጥረታቱ ውስጥ ሆኖ ይናገራል፤ (ሮሜ 1፡18-20 ተመልከት)። ይህ መገለጥ ግንም ሰው ቢድንም ባይድንም ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ ነው። ሁለተኛ እግዚአብሔር ለሰዎች ቃሉ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይህ ደግሞ የተለየ መገለጥ በመባል ይታወቃል። ይህን ዓይነቱ መገለጥ የተሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ቃል ለሚማሩ ሰዎች ብቻ ነው።

1ኛ ጥያቄ:- የእግዚአብሔር ለሰዎች ፈቃዱን መገለጽና ሰዎችን ማናገሩ ለምንድን ነው አስፈላጊ የሆነው?

የእግዚአብሔርን ማንነትና ከእርሱ ጋር እንዴት አድርገን ኅብረት ሊኖረን እንደሚችል ልንገነዘብ የምንችለው በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነው። በዚህ ሥፍራ ነው እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ነገርና ወደ መንግሥተ ሰማያት የምንደርስበትን መንገድ የሚገልጽልን። እውነተኛውን ነገር ማወቅ የምንችለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዚህም ነው ትምህርቶች ሁሉ እውነተኛ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ ልንገመግም የምንችለው።

ብዙ የሐሰት ሃይማኖቶች ከእግዚአብሔር የመጡ ናቸው የሚሏቸው ብዙ ጽሑፎች አሏቸው። ለመጥቀስ ያህል እስላሞች ቁርዓን አላቸው። ሌሎች ክርስቲያን ነን የሚሉ ሐሰተኞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ክብደት ያላቸው ሌሎች መጻሕፍቶች አሉ ብለው ይናገራሉ።

2ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኙ ለየት ያሉ ጽሑፎች ወይም ራዕዮች ወይም ትምህርቶች የሚያስተምሩ አንዳንድ የሐሰት አስተማሪዎችን ወይም ሡዋርተኞችን ጥቀስ።

ለ) ከእነዚህ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ችግር የሚፈጥሩት የትኞቹ ናቸው? ምን ዓይነትስ መልስ ነው የሰጠሃቸው?

3ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያኖች እምነታቸውን ሰዎች በጻፏቸው ጽሑፎች ላይ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ መጣል አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

4ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን ምዕራፍ አንድን አንብብ። በምዕራፉ ውስጥ ያሉትን ሁለቱን ዋና ዋና ትምህርቶች ዘርዝረህ ጻፍ።

ዛሬ የእግዚአብሔር ልዩ ራዕይ በሁለት የተለያዩ መንገዶች እንደተገለጸ እንመለከታለን። በመጀመሪያ በብሉይ ኪዳን ከብዙ መቶ ዓመታት በላይ እግዚአብሔር እራሱንና ፈቃዱን በነቢያት አማካይነት ገለጸ። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ማንነቱንና ፈቃዱን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ገለጸ።

* ዕብራውያን 1፡1-3 አንብብ።

5ኛ ጥያቄ፡- ለቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔር የተናገረው በእነማን በኩል ነው? ጥቂቶቹን ለምሳሌ ያህል ጥቀስ።

6ኛ ጥያቄ፡- በዚህ ዘመን መጨረሻ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ነው የተናገረው?

7ኛ ጥያቄ፡- በነቢያት በኩል ከተሰጠው መገለጥ የልጁን መገለጥ የበለጠ የሚያደርጉትን ሁኔታዎችና ድርጊቶች በዝርዝር ጻፍ።

የዕብራውያን ጸሐፊ የጀመረው በዚያን ዘመን ደብዳቤ ሲጻፍ በሰላምታ ይጀምር እንደነበረው ዓይነት ሳይሆን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነት በመግለጽ ነው። እንዲህም ያደረገው ከእነዚህ ክርስቲያኖች ብዙዎች ክርስቶስን ለመተው እያሰቡ ስለነበር ነው።

የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ ከሞተ ከ40 ዓመት በኋላ ቢጽፍም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሲመጣ አንድ ትልቅ ነገር እንደተከናወነ ተረድቷል። ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር አዲስ ዘመን መጥቷል። አዲስ ኪዳን ታሪክን በሁለት ዋና ዋና ዘመናት ይከፍለዋል።

1. አሮጌው ዘመን የተጀመረው በአዳም ኃጢአት ሲሆን በአለመታዘዝና በሞት የተሞላ ዘመን ነው። አሁን ኢየሱስ ከመጣበት ጊዜ አንሥቶ ይህ አሮጌ ዘመን በአዲሱ ትውልድ በመተካት ላይ ይገኛል። ኢየሱስ በምድር ላይ ለመንገሥ በሚመጣበትም ወቅት አሮጌው ዘመን ሙሉ በሙሉ ይጠፋል።

2. አዲሱ ዘመን የተጀመረው ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣበት ወቅት ነው። አዲሱን ዘመን የመሠረተው ኢየሱስ ነው፤ በአሁኑም ጊዜ የአዳምን የኃጢአት ፍሬ በማስወገድ ላይ ነው። የኃጢአት ዋጋ ተከፍሏል፤ ሞትና ሰይጣንም ድል ተደርገዋል። ይህ ኢየሱስ የጀመረው ነገር አንድ ቀን ኢየሱስ በምድር ሁሉ ላይ ለመንገሥ በሚመጣበት ጊዜ ይፈጸማል። የዚህን የአዲስ ዘመን ፍጻሜ በጉጉት ነው የምንጠብቀው።

ጸሐፊው የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነት ያሳየው ኢየሱስን ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ጋር በማነፃፀር ነው። እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን የጻፈው በእነዚህ ነቢያት በኩል ነው። ምንም እንኳ እንደ ሙሴ፥ ዳዊት፥ ወይም ኢሳይያስ የመሳሰሉት ሰዎች ቃሉን እንዲጽፉለት እግዚአብሔር ቢጠቀምባቸውም እግዚአብሔር እራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንደገለጸው አድርገው በደንብ ሊገልጹት አልቻሉም። የኢየሱስ መገለጥ ከብሉይ ኪዳኑ የሚበልጠው በምን ዓይነት መንገድ ነው? ሁለቱም እንደሆነ እኩል የእግዚአብሔር ቃሎች ናቸው። አዎን ይህም ቢሆን በብሉይ ኪዳን ዘመን የተሰጠው መገለጥ እንደ አሁኑ ግልጽ ያልነበረ ብዙ ዓመታት የፈጀና ሙሉ ያልነበረ ነበር። ልጁን በመላክ እግዚአብሔር ባህርይውን፥ ፈቃዱንና የደኅንነት መንገዱን በግልጽ አሳየ። ከዚህም በላይ ስለ እግዚአብሔር መናገር ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣበት ጊዜ እርሱ እራሱ እግዚአብሔር በመሆኑ የእግዚአብሔርን ባህርይና ፈቃድ በዓይናችን እንድናየው አድርጓል። አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር ሲያወራ ከምንሰማ ብናየው እንደሚሻል ሁሉ እግዚአብሔርም ባህሪውን በኢየሱስ ሕይወት በኩል ግልጽ አድርጎ አሳይቶናል። በሚናገረው ቃል ብቻ ሳይሆን በሕይወቱም ጭምር ነው ስለ እግዚአብሔር ይገልጥ የነበረው። ይህም ነው የሱን መገለጥ በአፋቸው ብቻ ከሚናገሩት የጥንት ነቢያት የሚያስበልጠውና የበለጠ ግልጽ የሚያደርገው።

ጸሐፊው የእግዚአብሔርን በኢየሱስ መገለጥ ታላቅ የሚያደርጉትን ሰባት እውነታዎች የሚገልጸው፥ ኢየሱስን ልዩ የሚያደርጉትን ባህርያት በመጥቀስ ነው:-

1. ኢየሱስ የሁሉም ነገር ወራሽ ነው:- ጸሐፊው በዚህ በሰማይና በምድር ባሉ ነገሮች ላይ በሙሉ ለኢየሱስ ሥልጣን ተሰጥቶታል ማለቱ ነው።

2. ኢየሱስ የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው:- መጽሐፍ ቅዱስ በምድርና በሰማይ ያሉትን ነገሮች የፈጠረው ኢየሱስ እንደሆነ ያስተምረናል! (ዮሐንስ 1:3፥ ቆላ.1:16)።

8ኛ ጥያቄ:- ይህ በየትምህርት ቤቶቹ አዝጋሚ ለውጥ የተባለውን ትምህርት በተመለከተ የሚለው ምንድን ነው? ክርስቲያን በዚህ ነገር ሊስማማ ይችላልን?

3. ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጽ ነፀብራቅ ነው:- ከፀሐይ ውስጥ እየፈነጠቀ የሚወጣው ጨረር ከፀሐይ መለየት እንደማይቻል ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር በመሆኑ የእግዚአብሔር ክብር ሙሉ በሙሉ አለው። በምድር ላይ በነበረበትም ወቅት፥ ይህን መለኮታዊ ክብር በሕይወቱና በሥራው ገልጾታል! (ዮሐ.1:14፥ 18)

4. ኢየሱስ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ባህርይ ምሳሌ ነው:- ጸሐፊው አሁንም ደግሞ የኢየሱስ እግዚአብሔር መሆን ላይ ያተኩራል። ምንም እንኳ ሥጋ ለብሶ ሰው ቢሆንም አሁንም ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ታላቅነትና ኃይል በሙሉ ባህርዩም በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ይገኛል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ በምንም ዓይነት መንገድ አይተናነስም።

5. ኢየሱስ ሁሉን ነገር ያለማቋረጥ በኃይለ ቃሉ ይደግፋል:- ኢየሱስ ዓለምን ፈጥሮ ብቻ ዝም አላለም፥ አሁንም ቢሆን ዓለምን በራሱ ዕቅድና ሐሳብ ይመራል። ዓለማችን ሳትጠፋ እንደዚህ በትክክሉ ሥራዋን እያከናወነች ልትኖር የቻለችው በኢየሱስ ሥራ ነው። ከዚህም በላይ ኢየሱስ ዓለምን ደግፎ በሚያጸናበት ወቅት በታሪክ ውስጥ ዓላማውን ለመፈጸም ሲል በምድር ላይ የሚከናወኑትን ድርጊቶች በሙሉ እየመራ ነው።

9ኛ ጥያቄ:- በአካባቢያችን ረሃብና ጦርነት ሲኖር ይህ እውነታ እንዴት አድርጎ ነው ሊያጽናናን የሚችለው?

6. ኢየሱስ ራሱ ነው ከኃጢአታችን ያነጻን:- ጸሐፊው አሁን የሚያተኩረው ኢየሱስ በምድር ላይ በሠራው ሥራ ላይ ነው። ይህም በዕብራውያን ከሚገኙት ዋና ዋና ትምህርቶች አንዱ ነው። ሊቀ ካህን ሆኖ ከሰዎች ላይ ኃጢአታቸውን ማስወገድ የቻለ ኢየሱስ ብቻ ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ክብር ብቻ ሳይሆን ያሳየው በመስቀል ላይ በመሞት የእግዚአብሔር ፍቅርና ፀጋ ምን ያህል እንደሆነም ልዩ በሆነ መንገድ ገልጿል! (1ዮሐ.3፡16 ተመልከት)። በብሉይ ኪዳን ሥር ግን ሙሉ በሙሉ ከኃጢአት የሚያነጻ ነገር አልተደረገም። የኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች ሙሉ መንጻትንና ምሕረትን ያጎናጽፉቸዋል።

7. ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ:- በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ የሚለው ክርስቶስ ታላቅ እንደሆነና የሁሉም ነገር የበላይ እንደሆነ የሚገልጽ አባባል ነው። ኢየሱስ የተቀመጠው የመሥዋዕትነት ሥራውን ስለፈጸመ ነው። በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በክብሩና በኃይሉ ሁሉን ነገር ይገዛል! (ፊልጲስዩስ 2፡9-11 ተመልከት)።

ኢየሱስ በሰዎች መካከል በሚኖርበት ወቅት እንደ እግዚአብሔር በመሆን በበኩሉ የእግዚአብሔርን ባህርያት በደንብ ገልጿል። በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔር በኢየሱስ መገለጥ ከብሉይ ኪዳኑ እጅግ የበለጠ ነው።

በዚህ ክፍል ጸሐፊው ጌታ ኢየሱስ የተጫወታቸውን ሦስት ሚናዎች ይጠቅሳል። በመጀመሪያ፡ እንደ ነቢይ በመሆን እግዚአብሔር በሰዎች ያለውን የመጨረሻውን ራዕይ አወጀ። ሁለተኛ፡ እንደ ሊቀ ካህን የሰውን ልጆች በሙሉ ከኃጢአት አነጻ። ሦስተኛ፡ እንደ ንጉሥ መንግሥተ ሰማያት ከእግዚአብሔር አብ ጋር ሆኖ ይገዛል።

ከዚህም ባሻገር ጸሐፊው ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የሚሰጠው የመጨረሻው ራዕይ እንደሆነ ይገልጻል። ኢየሱስ ከመጣና ስለ እርሱ ሕይወትና ትምህርት የሚያስረዱ መጻሕፍት እስከ ተጻፉ ድረስ ከእግዚአብሔር ሌላ ራዕይ አያስፈልገም። እግዚአብሔር ታላቁንና ሙሉውን ራዕይ እስከ ላከ ድረስ ሌሎች ከዚህ የሚያንሱ ራዕዮች ሊልክ አይገባውም። ስለ እግዚአብሔር ልናውቀው የሚገባን ነገር በሙሉ እስከነ ፈቃዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጿል።

10ኛ ጥያቄ:- ይህ ሐሳብ ከእግዚአብሔር የተሰጠን አዲስ ራዕይ አለ ስለሚሉ ሃይማኖቶች የሚነግረን ነገር ምንድን ነው?

በአዲስ ኪዳን መጨረሻ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ራዕይ ያጠናቅቃል። ምንም እንኳ ብዙዎች የተለየና አዲስ ራዕይ ከእግዚአብሔር አግኝተናል ብለው የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አስመስለው ጽፈው ቢያቀርቡት ሐሰተኞች ናቸው። አዲስና ለየት ያለ መገለጥ ተሰጥቶናል የሚሉ ነቢያትም ሐሰተኞች ናቸው፤ (ራዕይ 22፡18-19)።

11ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ዛሬ ለእኛ የሚናገረን እንዴት ነው?

እግዚአብሔር የሚናገረን መጽሐፍ ቅዱስን በሕይወታችን ተግባራዊ እንድናደርግ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሚመራን ወቅት ነው። ምንም እንኳ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች (ነቢያት ብለን የምንጠራቸው) ለተወሰኑ ጊዜያት ለየት ባለ አኳኋን ቃሉን ተግባራዊ እንድናደርግ በሚፈልግበት ወቅት ቢጠቀምባቸውም እነርሱ የሚያውጁት ቃል ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር ሁሌ መስማማት አለበት። በትምህርት ቤትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የምንቀበላቸው ትምህርቶች እውነተኛ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ ለመፍረድ የምንችለው እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ በግልጽ የሚያስተምረንን ነገር በመመልከት ነው። ከእግዚአብሔር አዲስና ለየት ያለ ቃል ለማግኘት መጓጓት የለብንም በምትኩ የእግዚአብሔር ቃል ተማሪዎች ሆነን በዛሬው ጊዜ ቃሉን እንዴት አድርገን በሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ እንደምናደርገው እግዚአብሔርን መጠየቅ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ዛሬ እኛን ለመናገር የሚጠቀምበት ቃሉን ነው።

12ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የእግዚአብሔርን ቃል ማወቁ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

ለ) ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይስማማ ለየት ያለ ራዕይ አለን ለሚሉ ሰዎች እንዴት አድርገህ ነው መልስ የምትሰጠው?

- ሳታቋርጥ ሁሌ የእግዚአብሔርን ቃል የምትማር ተማሪ ነህ?

## ሁለተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 1፡4-14

በትናንትናው ጥናታችን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳናቱ ነቢያት ይበልጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ባሀርይ ስለሚገልጽ ከእነርሱ በላይ ታላቅ እንደሆነ ተምረናል። ዛሬ ደግሞ ክርስቶስ ከመላዕክት ሁሉ እንዴት እንደሚበልጥ እናጠናለን።

ሰዎች ደካሞች መሆናቸውን ስለሚረዱ እግዚአብሔርን በጣም ይፈራሉ፣ በዚህ ምክንያት እንደ አማላጅ ሆነው ሊያገለግሏቸው የሚችሉ ታላላቅ ፍጥረታትን ፍለጋ ይሄዳሉ። አንድ ተራ ሰው ፕሬዝዳንቱን ለማየት ቢፈልግ፣ በቀጥታ አይሄድም የሚሄደው ከፕሬዝዳንቱ በታች ባለ ለፕሬዝዳንቱ በሚቀርብ ሰው በኩል ነው። በሃይማኖትም ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ይከሰታል። በዚህም ምክንያት ነው ዛሬ ሰዎች ለትናንሽ አማልክት ብንሰግድ ስለ እኛ በታላቁ አምላክ ፊት ይማልድልናል ብለው የሚያስቡት። ሌሎች ደግሞ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከመሄድ እንደ ማርያም ወይም እንደ መላዕክት በመሳሰሉ ፍጥረታት በኩል እንቅረበው ይላሉ። በዚህ ምክንያት ነው

አንዳንድ ሰዎች ተለይተው ጻድቃን ሰማዕታት የሚል ስያሜ የሚሰጣቸው። አንዳንዶች ወደ እነዚህ ሰማዕታት ይጸልያሉ። ከሰማዕታቱ ታላቅነት የተነሳ ልመናቸውን በእግዚአብሔር ፊት ቢያቀርቡላቸው የሚፈጸምላቸው ይመስላቸዋል።

13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለምንድን ነው የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያኖቻቸው የመልአክ ወይም የጻድቅ ሰማዕታት ስያሜ የሚሰጡት? የማታውቅ ከሆነ ወደ አንድ የኦርቶዶክስ ቄስ ሄደህ ጠይቅ።

ለ) ለምንድን ነው አንዳንድ ሰዎች ለመላእክት ወይም ለሰማዕታት የሚጸልዩት?

ሐ) ይህ ልማድ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ነው ወይስ የሰዎች ባህል ነው?

ለአይሁዳውያን ከእግዚአብሔር በታች እንደ መላእክት ያለ ታላቅ ፍጥረት የለም። እነርሱ በጣም ትልቅ ኃይል ያላቸውና ታላላቅ ሥራዎችን የሚሠሩ ናቸው።

14ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከትና የመላእክቱን ኃይል የሚገልጹትን የተለያዩ ነገሮችን በዝርዝር ጻፍ፤ ዳንኤል12፡1፥ ሉቃስ1፡26-38፥ የሐዋ.12፡5-10።

የአይሁድ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት ለመተው ፈልገው ነበር። በዚህም ጊዜ ኢየሱስ ሰው ነው፤ ስለዚህም ከመላዕክት ያነሰ ነው እያሉ ይጠይቁ ነበር። አንዳንዶቹ መላእክቶችን የሚያመልኩ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህም ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ከየትኛውም መልአክ የበለጠ እንደሆነ ለማሳየት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ይመራቸዋል።

ይህ ለእኛ በጣም አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሐሰት ትምህርቶችን የሚያምኑ ሰዎች መቼም ቢሆን አይታጡም። እነዚህን የሐሰት ትምህርቶች የምንዋጋው እንዴት ነው? አፍ በሚያስይዙ ክርክሮቻችን ነው? አይደለም። ሁሌም ቢሆን በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመመሥረት ስሕተቶቹ የትኞቹ እንደሆኑ በማሳየት ሰዎችን ለመመለስ ጥረት ማድረግ አለብን።

15ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 1፡4-14 አንብብ።

ሀ) ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ የገለፀባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረህ ጻፍ።

ለ) ጸሐፊው ልጁ ከመላእክቶች እንደሚበልጥ የገለጸባቸው የተለያዩ ማስረጃዎች ምን ምንድን ናቸው?

አይሁዳውያን መላእክትን በጣም ያከብራሉ። ሰዶምና ገሞራን ብቻ አይደለም መላእክት ያጠፉት የሙሴንም ሕግጋት የሰጡት እነርሱ ናቸው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሕጉን ለሙሴ የሰጠው በመላእክት በኩል ነው ተብሎ በብሉይ ኪዳን ባይጠቀስም አዲስ ኪዳን በመላእክት በኩል ነው የተሰጠው ብሎ የሚገልጸውን

የአይሁዳውያንን አባባል ይደግፋል። አይሁዳውያን እንዲያውም መሢሑ መጥቶ መንግሥቱን በሚመሠርትበት ወቅት ታላቁ መላእክት ሚካኤል የመሢሁን ያህል ሥልጣን ኖሮት ከገርዎቹ መካከል አንዱ እንደሚሆን ይናገሩ ነበር። በትንቢተ ዳንኤል የምድር ነገሥታትን ስለሚቆጣጠሩ መላእክት እናነባለን፤ (ዳንኤል 10:20-21፥ 12:1)። ስለዚህም ጸሐፊው ለአይሁዳውያን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ ከየትኛውም መላእክት የሚበልጥ መሆኑን ማሳየት ነበረበት።

በቁጥር 4 ላይ የዚህ ክፍል ዋነኛ ትምህርት ተጠቅሷል። የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ መጠን ኢየሱስ ክርስቶስ ከየትኛውም መልአክ የሚበልጥ ስም አለው። አይሁዳውያን ስለ እግዚአብሔር ስም በሚናገሩበት ወቅት ስለስሙ ብቻ ሳይሆን ስለ ውስጣዊ ባህርይውና ስለማንነቱም ጭምር ነበር የሚናገሩት። በዚህም መልኩ ጸሐፊው የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር በመሆኑ በባህርይውና በኃይሉ ከየትኛውም መልአክ ይበልጣል ማለቱ ነው።

ጸሐፊው ከብሉይ ኪዳን ከሰባት ቦታዎች ላይ በመጥቀስ የእግዚአብሔር ልጅ ከየትኛውም መልአክ የበለጠ እንደሆነ ማረጋገጫ ይሰጣል። ካስተዋልከው የዕብራውያን ጸሐፊ ከብሉይ ኪዳን የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች አጻጻፋቸው ብሉይ ኪዳን ከተጻፈበት አኳኋን ለየት ያለ ነው፤ ይህም የሆነው ጸሐፊው በግሪክ የተተረጎመውን ሴፕቱጀንት የተባለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን ስለሚጠቀም ነው።

ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት የሚበልጥበትን ስድስት ምክንያቶች ይገልጻል። በመጀመሪያ ጸሐፊው የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነት የሚያሳየው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በመግለጽ ነው። የትኛውም መልአክ ተነሥቶ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ሊል አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ይህን ዓይነት ለየት ያለ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለው፤ በዚህም ምክንያት ሀአንድያ ልጅህ የሚል ስያሜም ሊሰጠው ይችላል፤ ይህንን ለመግለጽ ጸሐፊው የሚጠቅሳቸው ሁለት ጥቅሶች መዝሙረ ዳዊት 2:7 እና 2ኛሳሙ.7:14 ናቸው። ምንም እንኳ እነዚህ ጥቅሶች የተናገሩት ለዳዊትና ለሰለሞን ቢሆንም ሙሉ በሙሉ የተፈጸሙት መሢሕ በሆነው በዳዊት ልጅ በኩል ነው።

16ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር የኢየሱስ አባት የሆነው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው? የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው በሥጋ በመወለዱ ነው ወይስ ሁሌም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር? መጽሐፍ ቅዱስን በጥሞና ብንመረምር ኢየሱስ ከጥንት ጀምሮ ይኖር እንደነበርና ከአብ ጋር ያለው ግንኙነትም የተገለጸው አባት ከልጁ ጋር እንዳለው ዓይነት ግንኙነት ነው። መዝሙረ ዳዊት (2)፤ ለዳዊትና በዚያ ዘመን ይኖሩ ለነበሩት ነገሥታት ይነበብላቸው የነበረው በንግሣቸው ቀን ነው እንጂ በሚወለዱበት ቀን አልነበረም። በመንገሣቸውም ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት ይኖራቸዋል፤ ይህም ግንኙነት አባት ከልጁ ጋር እንዳለው ዓይነት ግንኙነት ነው የሚቆጠረው። አይሁዳውያን የመረጥኩት የሚለውን ቃል የሚጠቀሙበት ሰው ሲወለድ ብቻ ሳይሆን የመሢሑን የኢየሱስን ክብር

የሚያንፀባርቅ ግንኙነት በሚመሠረትበትም ወቅት ጭምር ነው። ይህን ቃል በጥምቀቱ ላይ (ሉቃስ 3፡22) እና በክብር በተለወጠበት ጊዜ (ሉቃስ 9፡35) ተጠቅመውበታል። ሆኖም በተለይ ዋና የተጠቀሙበት በትንሣኤው ላይ ነው፤ (ሮሜ 1፡4)። እግዚአብሔር ኢየሱስ የእርሱ ልዩ ልጅ መሆኑን ይፋ ያወጣው በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ጊዜ ነው።

ሁለተኛ፤ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መጀመሪያ ወይም በኩር ፍጥረት ነው፤ በዚህም ምክንያት መላእክት በሙሉ ለእርሱ እንዲሰግዱ ታዘዋል። እንደገና ጸሐፊው ሀበኩርሀ የሚለውን የተጠቀመው ልደቱን ለመግለጽ ሳይሆን ከሁሉ በፊት መኖሩንና በሁሉም ነገር ላይ ሥልጣን እንዳለው ለመግለጽ ነው፤ (ቆላ.1፡15 ተመልከት)። ለአይሁዳውያን «በኩር» የሚለው ቃል የኢየሱስን ፈጣሪነትና የሁሉ ነገር ጀማሪ መሆኑን የሚያመለክት ነው፤ ይህ መላእክትም ያጠቃልላል። ይህ አባባል ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር እግዚአብሔር አይደለም ማለት አይደለም። ስለዚህም እራሳቸው መላእክትም ቢሆኑ የተፈጠሩ በመሆናቸው ለኢየሱስ በመስገድ እርሱ ከእነርሱ በላይ እንደሆነ ያሳያሉ።

ሦስተኛ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝ ሰጪ ነው፤ መላእክቱ ደግሞ የእርሱ አገልጋዮች ናቸው። ቀደም ሲልም በመዝሙር (104)፡4 ላይ እግዚአብሔር በነፋስና በእሳት የተመለሱትን መላእክትን እንደሚቆጣጠር ይናገራል። ትዕዛዙንም ለመፈጸም ይገለገልባቸዋል።

አራተኛ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘላለማዊው ዙፋን ላይ ተቀምጦ የሚገዛው ዘላለማዊው አምላክ ነው። ከዘላለም እስከ ዘላለም ነግሠው የሚኖሩት እግዚአብሔርና ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ናቸው። ይህ ሥልጣን ለአንድ መልአክ እንኳ አልተሰጠም። በዚህ ሥፍራ ኢየሱስን እግዚአብሔር ብሎ ነው የጠቀሰው።

አምስተኛ፤ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር ነው። ጊዜም ሲያልፍ የሚለወጥ አይደለም። ፍጥረታት በሙሉ ይለወጣሉ፤ ጸንቶ የሚቆይ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ስድስተኛ፤ እግዚአብሔር መላእክቱን ኑ በስተቀኜ ተቀምጣችሁ ከእኔ ጋር ግዙ ብሎ አልተናገራቸውም። ይህ ዓይነቱ ቃል የተሰጠው ለእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ነው። በጥንት ጊዜ አንድ ንጉሥ ሌላኛውን በጦርነት ድል ካደረገ በተሸነፈው ንጉሥ ላይ ያለውን ሥልጣን ለማሳየት አሸናፊው ንጉሥ እግሩን አንሥቶ በተንበረከከው ንጉሥ እራስ ላይ ያደርገው ነበር። ልክ እንደዚያ ጊዜ ኢየሱስ አሁን ነግሦአል፤ አንድ ቀንም ጠላቶቹ በሙሉ ለእርሱ ይሰግዱና ሥልጣናቸውን በሙሉ ለእርሱ ያስረክባሉ፤ (ፊሊ.2፡9-11)።

17ኛ ጥያቄ፡- አሁን ላንድ አፍታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ታላቁ ሥልጣኑ አመስግነው። ጸሐፊው ስለ ታላቁ ሥልጣኑ እንደ ማስረጃ አድርጎ ያቀረባቸውን ስድስቱን ነጥቦች በመጥቀስ አመስግነው።

ከዕብራውያን መጽሐፍ ዋና ዋና ትምህርቶች ውስጥ አንዱ ይህ የእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አምሳያ ሰው ሆኖ መምጣቱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ

እግዚአብሔር ነው። በባህርይውም ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል ነው። ይህም ቢሆን ሙሉ በሙሉ ሰው ነው። ስለዚህም ሰው ሆኖ ደካማ መሆን እንዴት እንደሆነ ይረዳዋል፥ ሆኖም ምንም ዓይነት ኃጢአት አልሠራም። በዚህ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን የደኅንነት መንገድ የከፈተልን ብቻ ሳይሆን አሁንም ቢሆን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ለእኛ ይማልድልናል። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ልጆች ወደ እርሱ በድፍረት መቅረብ ይችላሉ። ይህም ስለሆነ በመላእክት ወይም በጻድቃን ሰማዕታት የምናመልከበት ምንም ምክንያት ሊኖረን አይገባም።

18ኛ ጥያቄ:- 1ኛጢሞ.2፡5 ተመልከት። ይህ ጥቅስ ወደ ጻድቃን ሰማዕታትና መላእክት ስለ መጸለይ የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳባችንን ከኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዳናነሣ በሌሎች ሰዎች ላይ እንዳናደርግ ያስጠነቅቀናል። ሰማዕታትን ወይም መላእክትን ወይም ደግሞ የታወቁ ሰባኪዎችን፥ ወንጌላውያን መከተሉ ቀላል ነው። እነዚህ ነገሮች በሙሉ የእግዚአብሔር ፍጥረታት ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የእግዚአብሔር ልጅ። ወደ እግዚአብሔር መምጣት የምንችለውም በእርሱ በኩል ብቻ ነው። በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ያለው አማላጅ እርሱ ብቻ ነው። ስለዚህ እርሱን እንጂ ሌላውን ላለመከተል መጠንቀቅ አለብን።

19ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ኢየሱስን ከመከተል ይልቅ ሰዎችን የሚከተሉት በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?

ለ) ይህም አደገኛ የሚሆነው ለምንድን ነው?

በምዕራፍ አንድ በስተመጨረሻ ላይ ጸሐፊው አንድ አስገራሚ የሆነ ተጨማሪ አስገራሚ ነገር ይጠቅሳል። እነዚህ መላእክት የበታች የሆኑት ከኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ከሰውም ጭምር ናቸው። የመላእክት ሌላ ሥራ የእግዚአብሔር ልጆችን ማገልገል ነው። እኛ ልናየውና ልናውቀው በማንችል ሁኔታ አሁን እንኳ እያገለገሉን ነው። እንደ እግዚአብሔር ልጆች በዘላለማዊው መንግሥት ወቅትና ከኢየሱስ ጋር እንነግሣለን። ይህ ኃይል ለመላእክት አልተሰጠም።

ጸሐፊው ክርስቲያኖች መዳናቸውን አንድ ቀን ይወርሳሉ ይላል። ይህም የክርስቲያኖች ደኅንነት ገና አልተጠናቀቀም ማለት ነው። አዲስ ኪዳን ደኅንነትን በሦስት አቅጣጫዎች ነው የሚመለከተው። አንደኛ፤ አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ከኃጢአት ቅጣት ይድናል፤ በዚህም መልኩ ደኅንነቱ ያለፈ ነገር ነው። ሁለተኛ፤ ክርስቲያኑ ከኃጢአት ኃይል ነፃ እየሆነ በሕይወቱ ክርስቶስን እየመሰለ ይሄዳል፥ ይህ ደግሞ አሁን የሚደረግ ነው። ሦስተኛ፤ ከኃጢአት ጠባሳነት ሙሉ በሙሉ ነጽቶ ኢየሱስን መስሉ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆምበትንም የወደፊት ጊዜ የሚያመለክት ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በሰጠን ደኅንነት ሐሴት ብናደርግም እግዚአብሔር ተስፋ ላደረገልን ለዚያ የመጨረሻ የደኅንነት ቀን እንድንደርስ ከወዲሁ ጥረት ማድረግ አለብን፤ (ፊል.2፡12)

20ኛ ጥያቄ:- በአሁኑ ጊዜ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው በየቀኑ ክርስቶስን ወደ መምሰል የምትቀየረው? ምሳሌዎችን ስጥ።

## ሦስተኛ ቀን:- ዕብራውያን 2፡1-9

21ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን ምዕራፍ 2ን አንብብ። የዚህ ምዕራፍ ዋና ዋና ትምህርቶች ምን ምንድን ናቸው?

የዛሬው ትምህርታችን በሁለት ክፍሎች ተከፍሏል። በመጀመሪያ ወንጌልን ትተው ወደ ብሉይ ኪዳን ሥርዓት ለመመለስ ለሚፈልጉ ሰዎች የተሰጠ ከባድ ማስጠንቀቂያ አለ፤ (ከቁጥር 1-4)። ሁለተኛው ኢየሱስ እንደ ሰው ሆኖ ከመላእክት ጋር የሚነፃፀርበት ክፍል ነው፤ (ከቁጥር 5-9)።

22ኛ ጥያቄ:- ሉቃስ 8፡4-15 አንብብ። እዚህ ላይ ለወንጌል የተሰጡትን የተለያዩ መልሶች በዝርዝር ጻፍ።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ወንጌልን ሲሰሙ የተለያየ መልስ እንደሚሰጡ ያስተምረናል። አንዳንዶቹ እውነቱን ወዲያውኑ ይቃወማሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በመጀመሪያ እውነቱን ያምኑና በኋላ ላይ በተለያየ ምክንያት ይተዉታል። በእምነታቸው ጸንተው እግዚአብሔር የሚፈልገውን ፍሬ የሚያፈሩ ግን ጥቂቶች ናቸው። በጸሐፊው ዘመን ይኖሩ የነበሩት የአይሁድ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት ትተው ወደ ሕዝባቸው ሃይማኖት የሚያስመልሳቸው ሁኔታ ገጥሟቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ጸሐፊው ከበድ ያለ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል።

23ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ምሥክርነት ሰጥተው ከክርስትና ዓለም የኮበለሉ ክርስቲያኖች አሉ?

ለ) እምነታቸውን ለመተው ያስገደዷቸውን የተለያዩ ምክንያቶች ዘርዝረህ ጻፍ።

ሐ) እምነታቸውን ትተው የሚኮበልሉ ጥቂት ሰዎች እንዲሆኑና ብዙዎች ፍሬ የሚያፈሩ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ለማድረግ ቤተ ክርስቲያንህ ምን ምን ነገሮችን ነው ማድረግ ያለባት?

በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ አምስት የተለያዩ ማስጠንቀቂያዎች ተጠቅሰዋል። የመጀመሪያው ክርስቲያኖች ለሰሙት ወንጌል ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ የሚያስጠነቅቅ ነው።

24ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 2፡1-4 አንብብ።

ሀ) በብሉይ ኪዳን ሕጉን የተላለፉ ሰዎች ምን ይሆኑ ነበር? አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

ለ) ለእነርሱ ከተሰጣቸው ሕግ ለእኛ የተሰጠን የደኅንነት ተስፋ የሚበልጠው ለምንድን ነው?

ሐ) የኢየሱስን ወንጌል ያልተቀበሉ ሰዎች መጨረሻቸው ምንድን ነው?

የዚህ ማስጠንቀቂያ መሠረት የተገኘው ብሉይ ኪዳን ከአዲስ ኪዳን ጋር ሲነፃፀር ነው። እንዳየነው በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ራዕዮች ወደ ሙሴ ይመጡ የነበሩት በመላእክት በኩል ነው፤ (የሐዋ.7፡53፥ ገላ.3፡19)። እንደምታስታውሰውም የእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ሕግ በሲና ተራራ ላይ በተቀበለበት ወቅት ትዕዛዙን እንጠብቀዋለን ብለው ቃል ገብተው ነበር። ሆኖም ትንሽም ሳይቆዩ ተላለፉት። በዚህም ምክንያት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ሞቱ። ትዕዛዙን በመተላለፋቸውና እምነተቢሶች በመሆናቸው እግዚአብሔር የማያዳግም ቅጣት ነው የሰጣቸው። እንዲያውም ከግብፅ ባርነት የወጡት ጎልማሶች በሙሉ የከነዓንን ምድር ሳያዩ እዚያው ምድረ በዳ ውስጥ ተንከራትተው ነው የሞቱት።

አሁን በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በኢየሱስ አማካይነት ታላቅ የሆነ ራዕይ ነው የሰጠው። ኢየሱስ ከመላእክት በላይ ነው፤ የሰጠንም የደኅንነት ተስፋ ከሁሉ በላይ ነው። ታዲያ ክርስቲያኖች ይህን ታላቅ ራዕይ ቸል ቢሉ የእግዚአብሔርን ቅጣት ያመልጣሉ? ጸሐፊው አያመልጡም ነው የሚለው። እንዲያውም ከበፊቱ የበለጠ ከበድ ያለ ቅጣት ነው የሚቀበሉት። ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ካልተቀበሉ ሌላ የደኅንነት መንገድ የለም። የሚቀረው ነገር ያ የእግዚአብሔር የገሃነም እሣት ፍርድ ነው። አንዳንዶቹ ለማስተማር እንደሚፈልጉት ወደ እግዚአብሔር የሚወስዱ ሌሎች አማራጭ መንገዶች የሉም።

25ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ሰዎች ደኅንነት ያለው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የሚለውን እውነታ ለመቀበል የሚከብዳቸው ለምንድን ነው?

ለ) ይህ እውነታ እስላሞችና በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ምን ይሆናሉ ነው የሚለው?

ኢየሱስ የሰጠንን የደኅንነት ተስፋ ታላቅ የሚያደርጉት ሦስት ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ ደኅንነቱ የተመሠረተው ከብሉይ ኪዳንና ከመላእክቱ ብዙ ብልጫና ሥልጣን ባለው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ የደኅንነቱን መንገድ አወጀ። ይህ ብቻ አይደለም፥ በመስቀል ላይም በመሞት የደኅንነቱን መንገድ ከፈተው።

ሁለተኛ፤ ወንጌልን የመሰከሩትና ያወጁት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ይኖሩ የነበሩትና ይሰሙት የነበሩት ሰዎች ናቸው። ጸሐፊው እንደሚናገረው ከሆነ ምንም እንኳ እራሱ ጸሐፊው በዓይኑ ኢየሱስን ባያየውም ከኢየሱስ ጋር አብረው የኖሩና መልእክቱን የሰሙ ሰዎች ጽሑፉን ሲጽፉ እንደነበሩ ይጠቅሳል። ክርስትና በታሪክ ውስጥ ሥርና መሠረት ያለው ሃይማኖት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ ኖሮ ሥራውን ፈጽሞ ከሞተ በኋላ ከመቃብር ተነሣ። ክርስትና በሰው ታሪክ ፈጠራ ላይ የተመሠረተ አይደለም።

ሦስተኛ፤ እግዚአብሔር እራሱ ሰዎች ስለ ወንጌል የሰጡትን ምሥክርነት እውነተኛ እንደሆነ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች አሳይቷል።

1. እግዚአብሔር ምልክትን ድንቅን ነገርንና ተአምራትን አድርጓል። እነዚህን ሦስት ቃላት ተአምራዊ የሆኑ ነገሮችን ለመግለጽ ስንፈልግ በመለዋወጥ

የምንጠቀምባቸው ናቸው። ምልክት የተባሉት የወንጌሉን እውነተኛነት የሚገልጹ በመሆናቸው ነው። ድንቅ ነገር የተባሉት በሚያዩዋቸው ሰዎች ላይ ፍርሃትና ድንጋጤን ያዘለ መገረም ስለሚያስከትሉ ነው። ተአምራት የተባሉት ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ስለሚገለጽባቸው ነው። 2. እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ሰጥቷል። አስተውል በዚህ ሥፍራ እግዚአብሔር ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ስጦታ ሰጠ አይልም፤ ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች በሙሉ በሕይወታቸው ውስጥ የሚኖር መንፈስ ቅዱስ አላቸው። መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች እራሱ የፈለገውን ዓይነት ስጦታ ይሰጣል፥ በእነርሱ ምኞት ወይም ጸሎት ላይ ተመሥርቶ አይደለም የሚሰጣቸው።

26ኛ ጥያቄ፡- ይህ ትምህርት አንዳንድ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ከሚያስተምሩት ትምህርት ለየት የሚለው እንዴት ነው?

ስደትን ከመፍራት ወይም በዓለም ላይ ሀብት ለማካበት ካለን ምኞት ተነሣሥተን እውነቱን ብንክድ ትርፋችን የዘላለም ቅጣት ነው። በዓለም ላይ ያለውን ጊዜያዊ ስደትም ሆነ ድህነት ተቀብለን ተስፋ የተሰጠንን ታላቁን የመዳን ቀን መጠባበቁ ምንኛ የበለጠ መልካም ነው።

27ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 2፡5-9 አንብብ።

ሀ) የሰው ልጅ ከመላእክት ጋር ሲወዳደር በአሁኑ ጊዜ ያለው ቦታ ምንድን ነው?

ለ) ኢየሱስ ከመላእክት በታች እንዲሆን የተደረገው እንዴት ነው?

ሐ) የወደፊቱ መንግሥት የሚሰጠው ለማን ነው?

ምናልባት አንዳንድ የአይሁድ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ሰው በመሆኑና በመስቀል ላይ ተሰቃይቶ በመሞቱ ከመላእክት በታች ነው ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ። ጸሐፊው ግን ክርስቲያኖችን ወደ መጀመሪያው የፍጥረት ዓላማ ይወስድና ኢየሱስ ይህን ዓላማ እንዴት እንደፈጸመ ያሳያቸዋል፤ (2፡5-9)።

ሁለት ዘመናት እንዳሉ ተመልክተናል። የመጀመሪያው ዘመን የተጀመረው በአዳም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተጀመረው በክርስቶስ ነው።

28ኛ ጥያቄ፡- ኦሪት ዘፍጥረት 1፡26-30 አንብብ።

ሀ) በማን አምሳል ነው የተፈጠረው?

ለ) እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ምን ዓይነት ሥልጣን ነው?

እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ሰውን በአምሳሉ ነው የፈጠረው። እንዲህ የተባለው ለሰው ልጆች ነው እንጂ ለመላእክት አይደለም። ይህ አምሳያነት በሰው ልጆች ውጫዊ ነገር ውስጥ ሳይሆን የሚታየው ከእንስሳ በሚለያቸው ባህርያት ውስጥ ነው። ለመጥቀስ ያህል የእግዚአብሔር አምሳል ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋርና እርስ በእርሳቸው ለመገናኘት፥ ለማሰብ፥ ለማቀድ፥ አንዳንድ ነገሮችን ለመስራት ባላቸው ችሎታ ይንፀባረቃል። እግዚአብሔር ሰዎችን በእራሱ አምሳያ መፍጠሩ ለሰዎች ያለውን ታላቅ ግምትና ዕቅድ ያሳየናል። ሆኖም በአዳም ውድቀት ምክንያት ሰዎች ለጊዜው

ከመላእክት በታች ሆኑ። ኢየሱስ ክርስቶስም የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም ሲል ሰው ሆኖ በመምጣቱ ለጊዜው ከመላእክት ያነሰ ቦታ ይዞ ነበር።

ሆኖም ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞቱና ከሙታን በመነሣቱ አዲስ ዓለምን ወይም አዲስ ዘመንን መሠረተ። ከሙታን የተነሣው ጌታ በመንግሥተ ሰማያት ነግሦአል፤ አንድ ቀንም በሁሉ ነገር ላይ ይነግሣል። እግዚአብሔር መላእክት አብረውት በአዲሱ ዓለም እንዲነግሡ መብት አልሰጣቸውም። እንዲያውም አብረውት የሚነግሡና አዳምን በፈጠረበት ጊዜ የነበረውን ምኞቱን የሚፈጽሙት እነዚያ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ናቸው፤ (ራዕይ 20፡6 አንብብ)። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች በመላእክት ላይ እንደሚፈርዱ ያስተምረናል፤ (1ቆሮ.6፡1-3)። ምንም እንኳ ይህ አሁን እውነት ባይመስልም አንድ ቀን ኢየሱስ በሁሉም ነገር ላይ እንደሚነግሥና አማኞችም ከእርሱ ጋር እንደሚነግሡ ከእግዚአብሔር ዘንድ እውነተኛ የሆነ ተስፋ ተሰጥቶናል።

ለኢየሱስ በክብርና በግርማ የመንገሡን መብት ያሰጠው ነገር ምንድን ነው? ይህ የሆነው ኢየሱስ እራሱን አዋርዶ ሰው በመሆኑ ነው፤ ለእግዚአብሔር ታዛዥ በመሆኑና በመስቀል ላይ በመሞቱ ነው። በዚህም ምክንያት የኢየሱስ ስም ከስሞች ሁሉ በላይ ሆነ።

ጸሐፊው ኢየሱስ የሞተው ለሰው ልጆች በሙሉ ነው ብሏል። በዚህም ጸሐፊው ኢየሱስ የሰዎችን ሁሉ የኃጢአት ዕዳ ከፍሏል ማለቱ ነው። ሆኖም በመሞቱ ምክንያት የሚገኘውን መልካም ነገር ሁሉም ሰው አይቀበለውም። ከመሞቱ የሚገኘውን መልካም ነገር ለመቀበል ሰዎች ኢየሱስ ስለ እነርሱ ብሎ በእነርሱ ፈንታ እንደሞተ በግል ማመንና መቀበል አለባቸው። አንተስ ተቀብለኸዋልን?

በዚህ ውስጥ ለእኛ የሚሆን መመሪያ እናገኛለን፤ ምንም በሰዎች ዐይን የተናቅንና እየተሰደድን የምንሰቃይ ብንሆንም በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት አጥብቀን ከያዝንና ከታዘዝነው እግዚአብሔር ያከብረናል። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋርም እንነግሣለን። የዓለምን ጥላቻ ታግሠን ከኢየሱስ ጋር በክብር ለዘላለም ለመንገሥ ብቁ መሆኑ ከሁሉ ነገር በላይ አይደለም?

# አራተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 2፡10-18

29ኛ ጥያቄ፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ሰው ሆኖ መምጣት በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ሰው ሆኖ በመምጣት ኢየሱስ እራሱን ለጊዜው ከመላእክት በታች አደረገ። ነገር ግን፤ ለምንድን ነው ኢየሱስ ሰው መሆን የነበረበት? ምክንያቱ ምንድን ነው? ተሰቃይቶስ መሞቱ ለምን አስፈለገ? ኢየሱስ ሰው የሆነው ለሁለት ታላላቅ ምክንያቶች ነው። በመጀመሪያ፡- ሰው ሆኖ የመጣው ሊያድናቸው ከመጣው ሰዎች ጋር እራሱን ለማመሳሰል ሲል ነው፤ (ከቁጥር 10-13)። ሁለተኛ፡- ሰዎችን ከኃጢአታቸውና ከሰይጣን ለማዳን ሲል ሙሉ ለሙሉ ሰው ሆኖ መምጣት ነበረበት፤ (ከቁጥር 14-18)።

30ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 2፡ 10-13 አንብብ።

ሀ) የመዳን ራስ የሆነው ማነው?

ለ) ልጆች ተብለው የተሰየሙትስ እነማን ናቸው?

ኢየሱስ ተሰቃይቶ የሞተው እራሱን ብቻ ለማክበር አይደለም። በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ እንዲከብሩ ጭምር ነው። እግዚአብሔር ኢየሱስን የላከበት ዋነኛው ምክንያት ይህ ነው። እግዚአብሔር አብ እንዴት እንደተገለጸ አስተውል። በመጀመሪያ የተፈጠረው ነገር በሙሉ «ለእርሱ ተገብቶታል»። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እኛንም ጨምሮ የፈጠረው ለክብሩ ነው። ሁለተኛ በእግዚአብሔር የተነሣ ሁሉ በእርሱ ሆነ፤ ይህም የሆነው ፈጣሪ እርሱ በመሆኑ ነው።

ለአማኞች «የመዳናቸው ራስ» ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የመዳን ራስ የሚለው ቃል ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ያመለክታል። በመጀመሪያ የክርስቲያኖች ደኅንነት የመሠረተው ኢየሱስ ነው። በመስቀል ላይ በመሞት የደኅንነትን መንገድ ከፈተ። ሁለተኛ፤ ከአማኞች በፊት በመሄድ የደኅንነትን መንገድ ገለጸላቸው፤ ከዚያም ወደ መንግሥተ ሰማያት ገባ።

ጸሐፊው ኢየሱስን ፍጹም እንዲሆን ተደረገ ይላል። ይህም ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር አልነበረም ወይም ኃጢአተኛ ነበር ማለት አይደለም። አዳኝ ለመሆን ወይም የሰዎች ሊቀ ካህን ለመሆን ሰው ሆኖ እስኪመጣ ድረስ ብቁ አልነበረም ማለት ነው። እግዚአብሔር እንደመሆኑ የሰዎችን ችግርና ውስን ባህርይ በተመለከተ ያካበተው ልምድ አልነበረውም። ነገር ግን ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሲመጣ መከራን ተቀበለ፥ ተፈተነ፥ በመጨረሻም ሞተ። የእኛ አዳኝ ለመሆን መሞት ነበረበት። የእኛ ሊቀ ካህን ለመሆን ደግሞ ሰው ሆኖ መጥቶ መኖር ነበረበት።

በስተመጨረሻም እግዚአብሔር ክርስቶስን ዝቅ ዝቅ ያደረገው አንድ ታላቅ መንፈሳዊ የሆነ ቤተሰብ ለመመሥረት ነው። ኢየሱስ በጥንት ጊዜ እግዚአብሔር መንፈስ ስለነበር ሰዎች ከተፈጠሩበት ንጥረ ነገር ለየት ያለ በመሆኑ ከሰዎች ጋር አንድ ሊሆን አይችልም ነበር። ነገር ግን አሁን ኢየሱስ ሰው በመሆኑ በእግዚአብሔር ከሚያምኑት ጋር አንድ ዓይነት ተፈጥሮ አለው። ይህ እውነታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአማኞች ጋር ያለውን ግንኙነት በሚያመለክቱ በሦስት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ላይ በግልጽ ተብራርቷል። አንደኛ፡- ኢየሱስ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ለሰዎች ገልጧል። ሁለተኛ፡- በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነት እንዴት መሆን እንደሚገባው እርሱ እራሱ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ በግልጽ አሳይቷል። ሦስተኛ፡- እራሱን ከእርሱ ጋር አንድ ቤተሰብ አደረገ። የአዲስ ኪዳን ታላቅ እውነታ የእኛ መዳን ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች መሆናችንን ነው፤ (ዮሐ. 1፡12-13፥ 1ኛዮሐ. 3፡ 1-2)። ኢየሱስ ወንድማችን እግዚአብሔር ደግሞ አባታችን ነው። ይህ ሁሉ ሊፈጸም የቻለው ኢየሱስ ሰው ሆኖ በመምጣቱ ነው።

31ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 2፡14-18 አንብብ። ኢየሱስ ሰው ሆኖ በመምጣቱ የተገኙትን የተለያዩ ውጤቶች በዝርዝር ጻፍ።

ከአዳም ውድቀት አንሥቶ ኃጢአትና ሞት በምድር ላይ ተንሰራፍተዋል። ሰው ሆኖ የሚፈጠር ሁሉ ይፈተናል፤ ይቸገራል በመጨረሻም ይሞታል። ኢየሱስ ሰው ሆኖ የመጣው እነዚህን ነገሮች ድል ለማድረግ ነው።

በመጀመሪያ፤ «የሞትን ኃይል» የያዘውን ሰይጣንን ድል አደረገ።

32ኛ ጥያቄ፡- ሰይጣን የሞትን ኃይል የያዘው እንዴት ነው? የፈለገውን ሰው መግደል ይችላልን?

ሰይጣን የፈለገውን ሰው ሊገል አይችልም። ሰይጣን የሞትን ኃይል የያዘው በሦስት የተለያዩ መንገዶች ነው። 1. የሰው ልጅ ኃጢአት እንዲሠራ የሚፈትነው እርሱ ነው፤ ይህም ኃጢአት የሰውን ልጅ ለሞት ይዳርገዋል። 2. ኃጢአታቸውን በመጥቀስ የሞት ፍርድ እንዲወሰንባቸው በእግዚአብሔር ፊት ይከሳቸዋል። 3. ምናልባትም እግዚአብሔር የአንድ ሰው ሕይወት በዚህ ላይ ማቆም አለበት ብሎ ሲወስን ሰይጣን ያንን ሰው እንዲገድለው ሊፈቅድለት ይችላል፤ 1ኛቆሮ.5፡4-5)። ኢየሱስ በመስቀሉ ላይ በመሞትና የኃጢአትን ዋጋ በመክፈል ሰይጣንን ድል አደረገው። በአሁኑ ጊዜ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጆች ሊከስበት የሚችልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለውም ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዓይን እነርሱ አሁን ጻድቃን ናቸው።

ሁለተኛ፤ ኢየሱስ ሰዎችን ከሞት ሰቆቃ አድኗቸዋል። ይህን ያከናወነው ሞትን ድል አድርጎ በመነሣቱ ነው። ምናልባት ከሁሉም ነገር በላይ የሰው ልጅ የሚፈራው ነገር ቢኖር ሞትን ነው። ሆኖም ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ወንድሞቹ የሆኑ ሁሉ ከሙታን እንደሚነሡ ቃል ስለገባላቸው ከዚህ ጊዜ ወዲያ ሞት የሚያስፈራ ነገር አይደለም፤ ሞት ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የሚያስገባ በር ብቻ ነው፤ (1ኛቆሮ.15፡54-56)

ሦስተኛ፤ ኢየሱስ ሰው የሆነው ሊቀ ካህን እንዲሆን ነው። በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ዋና ዋና ትምህርቶች ይህ አንዱ በመሆኑ ወደ በኋላ አካባቢ ሠፋ ባለ ሁኔታ እንመለከተዋለን። ካህን ለመሆን ሲል ኢየሱስ ሰው መሆን ነበረበት። ሰው እንደመሆናችን ያለንን ድክመት በደንብ ስለሚረዳው በምሕረት የተሞላ ሊቀ ካህናችን ነው። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጠብቆ በመስቀል ላይ መሞቱም ታማኝነቱን ይገልጻል። ኃጢአተኛ የሆኑም ሰዎች በእርሱ መታመንና ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርሱ መጣል ስለሚችሉ በዚህም መልኩ ታማኝ ነው። እንደ ሊቀ ካህን ለሰው ልጆች ኃጢአት መሥዋዕት የማቅረብ ሐላፊነት ነበረበት። ይህንንም የፈጸመው እራሱን ፍጹም መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ነው። የዚህም መሥዋዕት ውጤት ሀስርየትንሀ አስገኝቶልናል። በአሪት ዘሌዋውያን ጥናታችን ስርየት የሚለውን ቃል ደጋግመን ተመልክተነዋል። ይህም በኃጢአተኛው ላይ የእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ እንዳይወርድበት የሰውዬውን ኃጢአት ማስወገድ ማለት ነው። ምንም እንኳ በብሉይ

ኪዳን የመሥዋዕቱ ውጤት ጊዜያዊ ቢሆንም የኢየሱስ ሞት ግን ዘላለማዊ የሆነ ምሕረትን ነው የሚያስገኘው።

አራተኛ፤ ኃጢአት የመሥራት ፈተና ያለባቸውን ሰዎች ኢየሱስ ሊረዳቸው ይችላል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት በሰይጣን ተፈትኖ ነበር። በተለይ ወደ መስቀሉ ሄዶ እንዳይሰቃይ ነበር የተፈተነው። ስለዚህም ኃጢአት እንድንሠራ ተፅዕኖ የሚያደርግብንን ነገር ኢየሱስ ያውቀዋል። ተፈትኖ ሁሉንም ፈተናዎች በድል አድራጊነት ስለተወጣቸው፥ በሕይወታችን ላይ የሚመጡትን ፈተናዎች እንድናሸንፍ ብቁ ሊያደርገን ይችላል።

በአስገራሚ ሁኔታ እግዚአብሔር ደካማ ለሆኑ ኃጢአተኞች ከልብ የመነጨ ፍቅር አለው። ኢየሱስ መላእክትን ለመርዳት መልአክ ሆኖ አልመጣም። ግን ሰዎችን ለመርዳት ሰው ሆኖ መጣ። እንደ እግዚአብሔር ልጆች አሁን የምንቀበላቸው በረከቶች የራሳችን ሊሆኑ የቻሉት ኢየሱስ የክብር ቦታውን ለቅቆ ለእኛ ሲል በምድር ላይ ተሰቃይቶ ለመሞት ፈቃደኛ በመሆኑ ነው። ታዲያ የእግዚአብሔር ፍቅር አስደናቂ አይደለምን? አስተውል፥ ይህን ከመሰለ ታላቅ ፍቅር ሊለይህ የሚችል ምንም ነገር የለም፥ (ሮሜ 8፡31-39)።

33ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ይህንን ዓይነት ፍቅር ስለሰጠን የእኛ ምላሽ ምን መሆን አለበት? (ሮሜ 12፡1-2 ተመልከት)።

በዚህ ሳምንት አንዳንዶችን የዕብራውያን መጽሐፍ መሪ ሐሳቦች አጥንተናል። ኢየሱስ በመላእክትና በብሉይ ኪዳን ነቢያት ላይ ያለውን የበላይነት ተመልክተናል። ኢየሱስ ሰው ሆኖ የመጣበትን ምክንያት የኃጢአታችን መሥዋዕት መሆኑንና ሊቀ ካህናችንም ጭምር መሆኑን ተመልክተናል። ይህን ወደ ኋላ ላይ በተጨማሪ እናጠናዋለን።

# አምስተኛ ቀን፡-

ትምህርቱን ከልስና ለውይይቱ ጊዜ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ፡-

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ፡-

ሀ) በብሉይ ኪዳን የተገለጸውን የእግዚአብሔር ራዕይና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጸውን አነፃፅር።

1. እንዴት ነው የሚመሳሰሉት?

2. እንዴትስ ነው የሚለያዩት?

3. በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጸው የእግዚአብሔር ራዕይ የሚሻለው እንዴት ነው?

ለ) 1. ለሌሎች ኃይማኖቶች ለሐሰተኛ መምህራንና ነቢይ ናቸው ለሚባሉ ሰዎች፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ እንደሆነና ከዚህ ውጪ ሌሎች አዳዲስ ራዕዮች እንደሌሉ እንዴት አድርገህ ነው የምታስረዳቸው?

2. አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠኝ ለየት ያለ ትንቢት አለኝ ቢል ሰውዬው እውነተኛውን ነገር ስለመናገሩ ፍርድ የምንሰጠው እንዴት አድርገን ነው?

3. በቤተ ክርስስቲያንህ እንዲህ ዓይነት ችግር አለ?

ሐ) 1. ለምንድን ነው አንዳንድ ክርስቲያኖች በአማላጆች በኩል መጸለይ አለብን ብለው የሚያስቡት?

2. ይህ ነገር ክርስቶስንና የሊቀ ካህንነት ሥራውን ዝቅ የሚያደርገው እንዴት ነው?

መ) 1. ሰዎች በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት ለምን እንደሚክዱ አንዳንዶቹን ምክንያቶች ዘርዝረህ ጻፍ።

2. ቤተ ክርስቲያን ወይም ሌሎች ክርስቲያኖች አዳዲስ ክርስቲያኖች እንዲያድጉና ወደ ዓለም እንዳይመለሱ ለማድረግ ሲሉ ሊጫወቱት የሚገባቸው ሚና ምንድን ነው? ምሳሌዎችን ስጥ።

ሠ) 1. ኢየሱስ ሰው የሆነው ለምንድን ነው?

2. ለእግዚአብሔር ያለንን አገልግሎት በተመለከተ ጸሎታችንን በተመለከተ ወዘተ... ይህ ምን ዓይነት መተማመኛ ነው ሊሰጠን የሚችለው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ አንድ

ዕብራውያን 3-4፡13

## የመጀመሪያ ቀን፡- ዕብራውያን 3፡1-6

እስካሁን ድረስ ባለው የዕብራውያን መጽሐፍ ጥናታችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት ነገሮች ጋር ሲነፃፀር ተመልክተናል። በመጀመሪያ የተነፃፀረው ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ጋር ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የተነፃፀረው ታላቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ከሆኑት ከመላእክት ጋር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነዚህ ሁለት ነገሮች የላቀ እንደሆነ ተመልክተናል። በዛሬው ቀን ደግሞ ኢየሱስን ታላቁ የእሥራኤል መሪ ከነበረውና ሕጉን ለእሥራኤል ከሰጠው ከሙሴ ጋር እናነፃፅረዋለን።

1ኛ ጥያቄ፡- ጥናትህን ዕብራውያን 3-4፡13 በማንበብ ጀምር። ከዚህ ክፍል ያገኘሃቸውን ዋና ዋና ትምህርቶች በዝርዝር ጻፍ።

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ሳይሆን የታወቁ ሰዎችን መከተል ይጀምራሉ። እግዚአብሔር በአንድ ታላቅ ሰባኪ ወይም ወንጌላዊ ከተጠቀመ በኋላ ሰዎች ያንን ሰው መከተል ይጀምራሉ። እርሱ የሚናገረውና የሚሠራው ነገር በሙሉ ትክክል የሆነ ይመስላቸዋል። በተሳሳተ መንገድ ሊመራቸው ቢነሣም እነርሱ እርሱን ከመከተል ፈቀቅ አይሉም። ሐሰተኛ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን በቶሎ የሚዛመተው በዚህ ዓይነት መንገድ ነው።

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህን ዓይነት ነገር በቤተ ክርስቲያንህ ወይም በሌላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲደረግ ዓይተህ ታውቃለህ?

ለ) እንዴት እንደተደረገ አብራርተህ ግለጽ።

ሐ) ለምንድን ነው ይህ ዓደገኛ የሆነው?

ለእኛ ምሳሌያችንና እራሳችን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ወይም መሪ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዐይናችንን ወደ ሰዎች ማዞር ስንጀምር እነርሱ ሲወድቁ እኛም አብረን ከእነርሱ ጋር እንወድቃለን። ምንም እንኳ ጌታ በድንቅ ሁኔታ ቢጠቀምባቸውም ገና ሰዎች ናቸውና ሊወድቁ ይችላሉ። እኛ ልንከተለው የሚገባን እውነተኛው ምሳሌያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ለዚህም ነው ጸሐፊው «የሃይማኖታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ» ብሎ የሚያሳስበን።

አይሁዳውያን ሦስት ታላላቅ መሪዎች ነበሯቸው። የመጀመሪያው፤ የአይሁድ ዘር አባት የሆነው አብርሃም ነው። ሁለተኛው፤ ዓለምን ሊገዛ የሚመጣው መሢሕ አባት የሆነው ንጉሥ ዳዊት ነው። ሦስተኛው፤ ደግሞ የእሥራኤል መሪ በመሆን ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነፃ ያወጣው ሙሴ ነው። ከሦስቱ ውስጥ አይሁዳውያን ትልቅ ክብር ይሰጡ የነበረው ለሙሴ ነው። ሙሴ እሥራኤላውያንን ከባርነት ነፃ ማውጣት ብቻ ሳይሆን በመካከላቸውም ብዙ ተአምራት ይፈጽም ነበር። በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ይነጋገር ነበር። ደግሞም እግዚአብሔር በእርሱ በመጠቀም ታላቁን የብሉይ ኪዳን ሕግ በእርሱ በኩል ነው የሰጠው። ስለዚህም ጸሐፊው የብሉይ ኪዳን ጀማሪ የሆነውን ሙሴንና የአዲስ ኪዳን ጀማሪ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያወዳድራል። አይሁዳውያን ዐይናቸውን በእግዚአብሔር ላይ ከማድረግ እንደ ሙሴ ባሉ መሪዎች ላይ ነበር የሚያደርጉት። በኢየሱስ ያላቸውን እምነት ትተው ወደ ቀድሞው የሙሴ ሕግ ለመመለስ እያወላወሉ ነበር። በዚህም ምክንያት ጸሐፊው ኢየሱስ ከሙሴ እንደሚበልጥ ለማሳየት ሁለቱን ማለትም ሙሴንና ኢየሱስን ያወዳድራል።

3ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 3፡1-6 አንብብ።

ሀ) በቁጥር አንድ ላይ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠው ስያሜ ምንድን ነው? ምን ማለትስ ነው?

ለ) ሙሴና ኢየሱስ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ሐ) ኢየሱስ የሙሴ የበላይ እንደሆነ የተመለከተው እንዴት ነው?

መ) ክርስቲያኖች ታማኝ ሆነው ከቆዩ የምን ክፍል ነው የሚሆኑት?

ምዕራፍ ሦስት «ስለዚህ» በሚል ቃል ነው የሚጀምረው። ጸሐፊው ይህንን ቃል በመጠቀም በበፊቱ ምዕራፍ ያለውን ትምህርት ከዚህኛው ምዕራፍ ጋር ያገናኘዋል። ባለፈው ሳምንት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መጥቶ ለኃጢአታችን እንደሞተልን ተመልክተናል። ችግራችንን የሚረዳልንና በእርሱ ውስጥ ልናልፍ ሊረዳን የሚችለው ታማኝና መሐሪ ሊቀ ካህን የሆነው እርሱ ነው። ስለዚህም ጸሐፊው ክርስቲያኖች ዓይናቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል።

ጸሐፊው የአንድ ትልቅ ቤተሰብ ክፍል እንደሆንን ያሳስበናል። «ቅዱሳን ወንድሞች» የሚል ስያሜ ነው የሰጠን። ቅዱሳን የሆነው በእግዚአብሔር በመመረጣችን ነው። ወንድማማች የሆንነውን ደግሞ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ክፍል በመሆናችን ነው። ጸሐፊው እንደ እግዚአብሔር ልጆች የሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች እንደሆነም ያሳስበናል። እግዚአብሔር ከሰማያት ሆኖ ብቻ አይደለም የጠራን፥ ካሁን ወዲያ በምድር ላይ ዜግነት የለንም፤ እኛ ወደ እውነተኛው መኖሪያችን ወደ መንግሥተ ሰማያት እየተጓዝን ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ስለ መንግሥተ ሰማያት ጉዟቸው ማሰባቸውን አቁመው ስለ ምድራዊ ኑሮአቸው ሲያስቡና ሲጨነቁ ሁሌ ችግር ውስጥ ይገባሉ። አይቆዩም፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይወድቃሉ። ስለዚህም ጸሐፊው እነዚህን በስደት ላይ ያሉ ክርስቲያኖችን የመንግሥተ ሰማያት ዜጎች እንጂ የምድራዊው ዜጎች እንዳልሆኑ በማሳሰብ ሐሳባቸውን አሁን የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ ከማድረግ በመንግሥተ ሰማያት ላይ እንዲያደርጉ ይመክራቸዋል።

ከሁሉም በላይ ዐይናቸውን በሚያምኑበት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማድረግ አለባቸው። ኢየሱስን «ተመልከቱ» የሚለው ቃል ያለማቋረጥ ኢየሱስ ማን እንደሆነ፥ ምን እንዳደረገና ለእርሱ የሚሰጡት ትክክለኛ ምላሽ ምን እንደሆነ ማጥናት ማለት ነው። ሁለት ዋና ዋና አገልግሎቶችን የሚያንፀባርቁ ሁለት ስያሜዎች ለኢየሱስ ተሰጥተውታል። በመጀመሪያ ሐዋርያ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። በዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው ኢየሱስ ሐዋርያ የሚል ስያሜ የተሰጠው። ሐዋርያ የሚባል ሰው ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልእክት ይዞ የሚሄድ ነበር። በሕዝቡ መካከል የእግዚአብሔር ተወካይ ነበር። ልክ እንደዚሁ ኢየሱስ አብን ለመግለጽ የመጣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው፥ (ዮሐንስ 3፡34፥ 20፡21)።

ሁለተኛ፤ ኢየሱስ ሊቀ ካህን የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። የሊቀ ካህን ዋነኛው ሥራው ሕዝቡን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ነው። ሊቀ ካህንም ሐዋርያም የነበሩ የብሉይ ኪዳን መሪዎች ጥቂቶች ናቸው። የእግዚአብሔርን መልእክት ለሰዎች የሚያቀርቡ ነቢያት ነበሩ። ካህናት ደግሞ ሕዝቡን በመወከል በእግዚአብሔር ፊት ያተኩር ነበር። ስለዚህ የኢየሱስ ካህንም ሐዋርያም መሆን ከሌሎቹ የበለጠ በደንብ እንዲከበርና እንዲከተሉት ያደርጋል። በአንድ መልኩም ሙሴ እነዚህን ሁለት

ሐላፊነቶች አሟልቷል ልንል እንችላለን። ለእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚያቀርብ መልእክተኛ ነበር። ምንም እንኳ ሊቀ ካህን ባይሆንም (ይህ የአሮን ሥራ ነበር)፤ ካህን ሆኖ በማገልገል የሕዝቡን ጥያቄና ፍላጎቶች በእግዚአብሔር ፊት ያቀርብ ነበር።

በአንዳንድ መልኩ ሙሴና ኢየሱስ በጣም ይመሳሰላሉ። ሁለቱም የእግዚአብሔርን ሕዝቦች አርነት አውጥተዋቸዋል ሁለቱም በእግዚአብሔር ኃይል ታላላቅ ታምራት አድርገዋል። ሁለቱም በእግዚአብሔር ተመርጠው በሕዝቡና በእርሱ መካከል የተደረገውን ቃል ኪዳን ያቋቋሙ ናቸው። በመጨረሻም ሁለቱም ታማኞች ናቸው።

4ኛ ጥያቄ፡- አሪት ዘኁልቁ 12፡7 እና 1ኛቆሮ.4፡ 1-2 አንብብ።

ሀ) የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆነ ሰው የሚጠበቀው ባህርይ ምን ዓይነት ነው?

ለ) ይህ ባህርይ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት መገለጽ እንዳለበት አብራራ።

እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ ባህርይ ውስጥ በጣም የሚመለከተውና የሚያመሰግነው ታማኝነት መሆኑ በጣም የሚያስደንቅ ነው። እምነት ሊጣልባቸው የሚችሉና እግዚአብሔር በእጃቸው የሚሰጣቸውን ሐላፊነት በተገቢው መንገድ በታማኝነት የሚፈጽሙ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ነው እንጂ ሰውን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ መሆን የለበትም። እነርሱ የሚሠሩት ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው እንዳልሆነ ይገነዘባሉ። ይሁንና ዛሬ ይህንን ባህርይ በሕይወታቸው የሚያሳዩ ጥቂት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሉ።

ሙሴ ታላቅ ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ በላይ ነበር። የኢየሱስን ታላቅነት ለማሳየት ጸሐፊው የሚጠቀምበት ቤትን ነው። «ቤት» የሚለው ቃል ስለ ሕንፃ የሚናገር ሊሆን ይችላል፤ (ለምሳሌ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች የሚል ስያሜ ተሰጥቶናል። 1ኛቆሮ.3፡16) ወይም ደግሞ «በቤቱ ውስጥ ስለሚኖሩ» ሰዎች የሚገልጽ ሊሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሰዎች እንደ አንድ ታላቅ ቤተሰብ አድርጎ ነው የሚያስቀምጣቸው። ኢየሱስ ከሙሴ እንደሚበልጥ የተመለከተው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው። አንደኛ ሙሴ ከእግዚአብሔር ሰዎች መካከል አንዱ በመሆኑ የዚህ ቤት ክፍል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ የዚህ ቤት ነዳፊና ሠሪ ነው እንጂ ክፍል አይደለም። በዚህም ምክንያት ከሙሴ በጣም ይበልጣል።

ሁለተኛ፤ ሙሴ በእዚህ ቤት ውስጥ የሚያገለግል የእግዚአብሔር ሎሌ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በቤቱ ላይ ሥልጣን ያለው ነው።

5ኛ ጥያቄ፡- «ሎሌ»የሚለው የአማርኛ ቃል ምን ዓይነት ትርጉም ነው ያለው?

ጸሐፊው በዚህ ሥፍራ «አገልጋይ» የሚለውን ቃል የሚተካ ለየት ያለ ቃል ነው የሚጠቀመው። ይህ ቃል በቤት ውስጥ የሚሠራውን ተራውን ባሪያ ወይም ሠራተኛ የሚጠቅስ አይደለም። በምትኩ ይህ ስያሜ የተሰጠው በቤቱ ውስጥ የሚደረገውን

ብዙውን ነገር በበላይነት ለሚቆጣጠረው ዋነኛው አገልጋይ ነው። ምንም ያህል ታላቅ ቢሆንም ሙሴ የቤቱ ባለቤት ወይም ልጅ አልነበረም። ሙሴ እግዚአብሔርን በታማኝነት ቢያገለግልም ከኢየሱስ በታች ነበር። ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ልጅ ነበር። በዚህም ምክንያት ወራሽና ከአገልጋይ በላይ ሥልጣን ያለው ነው። እርሱ የቤቱ አውራና መሥራች ነበር። ኢየሱስ ከሙሴ በላይ ታላቅ መሆኑ ሙሴ ስለ ወደፊቱ በተነበየበት ትንቢት ላይ እንኳ ይታያል።

6ኛ ጥያቄ:- እሪት ዘዳግም 18:15 ተመልከት። በዚህ ሥፍራ የተሰጠው ትንቢት ምንድን ነው?

ሙሴ የመጨረሻው የእግዚአብሔር ነቢይ እኔ ነኝ አይልም ወደፊት የሚመጣ ከሱ የሚበልጥ የእግዚአብሔር ነቢይ እንዳለ ያመለክታል እንጂ። ይህ ትንቢት የተፈጸመው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ክርስቲያኖችም የታላቁ የእግዚአብሔር ቤት ወገኖች ናቸው ሆኖም የዚህ ቤት ወገኖች ለመሆናችን እርግጠኞች ለመሆን እስከ ምድራዊ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ ታማኞች ሆነን መኖር ይኖርብናል። አንድ ሰው የእምነት ቃል መስጠቱ የእግዚአብሔር ቤት ወገን መሆኑን ለማሳየት በቂ አይሆንም። ነገር ግን አንድ ሰው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ወገን ለመሆኑ ማስረጃ የሚሆነው እስከመጨረሻ ድረስ ታማኝ ሆኖ ሲቆይ ነው። ይህ ከባድ በሆነ የስደት ጊዜ ውስጥ መጽናትን የሚጠይቅ ነው። በተጨማሪም ይህ እምነታችንን እንዳንክድ የሚያደርገን ነገር ፈተና በሙታን ትንሣኤና በዘላለማዊው ሕይወት ተስፋችን መቋቋም አለብን ማለት ነው። በኢየሱስ ላይ ያለንን እምነታችንን ከተውን በመጀመሪያም የነበረን እምነት እውነተኛ አለመሆኑን ያሳያል።

እስከ መጨረሻው ፀንተን ስለ መቆማችን እርግጠኞች የምንሆነው እንዴት ነው? ታላቁ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ወገኖች ስለ መሆናችንና መንግሥተ ሰማያት ስለ መግባታችን እርግጠኞች ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ በመቆየት ነው። ታማኝ ሆነንስ የምንቆየው እንዴት ነው? አንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ በመከተል ነውን? አይደለም። ኢየሱስን በመመልከትና እርሱን በመከተል ነው። የፈለገውን ያህል ሸለቆና ተራራ የበዛበት መንገድ ቢሆንም ጌታን ከተከተልን ወደ መንግሥተ ሰማያት ቤታችን እንደርሳለን።

# ሁለተኛ ቀን:- ዕብራውያን 3:7-19

ለሁለተኛ ጊዜ የዕብራውያን ጸሐፊ ክርስቲያኖቹ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከደው ወደ ድሮው የሕግ እምነታቸው እንዳይመለሱ ያስጠነቅቃቸዋል! (3:7-4:13)። ጸሐፊው ለማስጠንቀቂያው መሠረት ያደረገው እሥራኤላውያን ለ40 ዓመት ያህል በበረሃ የተንከራተቱበትን ጊዜ በመጥቀስ ነው።

7ኛ ጥያቄ:- ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስን ከዶ ወደ ድሮው ሃይማኖት ወይም የኑሮ ዘይቤ መመለሱ መጥፎ የሚሆነው ለምንድን ነው?

ለ) ክርስቲያኖች ናቸው ተብለው የሚባሉ አንዳንድ ሰዎች እንዲህ የሚያደርጉት ለምን እንደሆነ ምክንያታቸውን ዘርዝረህ ጻፍ።

ብዙ ክርስቲያኖች ተብለው የሚጠሩ ሰዎች በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት በተለያየ ምክንያት ይተዋሉ። አንዳንዶች ቤተሰቦቻቸውን በመፍራት ነው። ሌሎች ደግሞ ብዙ ገንዘብና ሥልጣን ለማግኘት ባላቸው ምኞት ነው። የእግዚአብሔርን እውነት ለመካድ የምናደርገው ማንኛውም ዓይነት መከራ ምንም እንኳ በመጀመሪያ አካባቢ ጊዜያዊ የሆነ ሰላምና ብልፅግና ቢያስገኝልንም በኋላ ላይ የእግዚአብሔርን የፍርድ ገፈት ቀማሾች ያደርገናል፤ አንዱንና ብቸኛውን የደኅንነት መንገድ ከካድን ለእኛ ደኅንነት ተስፋ የሚሰጠን ሌላ ምንም ነገር የለም።

8ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 3:7-19 አንብብ።

ሀ) ጸሐፊው ስላለማመን ለክርስቲያኖቹ ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው ከመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ የትኛውን ክፍል በመጥቀስ ነው?

ለ) የዚህ የመዝሙረ ዳዊት ክፍል ጸሐፊ ማነው?

ሐ) ፊታቸውን ወደ ክሕደት እንዳያዞሩ ጸሐፊው ምን ዓይነት ምክር ነው የሚሰጣቸው?

መ) እስከ መጨረሻው ድረስ ጽኑዎች ከሆንን የምናገኘው ነገር ምንድን ነው?

ሠ) እሥራኤላውያን በእግዚአብሔር ባለማመናቸው ምን ዓይነት ቅጣት ነው የተቀበሉት?

የአይሁድ ክርስቲያኖች ከክሕደት እንዲቆጠቡ ለማስጠንቀቅ ጸሐፊው በቀድሞው አባቶቻቸው ላይ የሆነውን ነገር ይጠቅሳል። በዳዊት ከተጻፈው ከመዝሙር (95):7-11 ላይ ይጠቅሳል፤ (ዕብራውያን 4:7)። ሆኖም ጸሐፊው ይህንን ቃል የተናገረው መንፈስ ቅዱስ ነው ማለቱን አስተውል። ይህ ክፍል መጽሐፍ ቅዱስን እግዚአብሔር እንደጻፈው ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። ይህንን ያደረገው በሰዎች በኩል ነው። ነገር ግን ጸሐፊዎቹን ይመራ የነበረው መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህም የሆነው በስተመጨረሻ የጸሐፊዎቹ ቃል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እኩል እንዲሆን ነው፤ (2ጴጥ. 1:20፥21)።

በዚህ ክፍል ሁለት ታሪካዊ የሆኑ ክንውኖች ተጠቅሰዋል። አንደኛው፤ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመረመበት ጊዜ ነው፤ (ዘጸአት ምዕ. 17)። ቀጥሎም በአሪት ዘኁልቁ ምዕራፍ 14 ላይ የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር አንገባም ብሉ የተቃወመበት ጊዜ ነው።

9ኛ ጥያቄ:- ዘጸአት 16:35-17:7 አንብብ።

ሀ) በአሪት ዘጸአት ውስጥ በእርሱ ላይ ከማጉረምረማቸው በፊት እግዚአብሔር የሰጣቸው ነገር ምንድን ነው?

ለ) እሥራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ የፈጸሙት ኃጢአት ምንድን ነው?

ሐ) እግዚአብሔር ምን ዓይነት ተአምራት ነው ያደረገላቸው?

እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ብዙ ታላላቅ ተአምራትን አደረገላቸው። ቀይ ባህርን አድርቆ በመሬቱ ላይ እንዲያቋርጡ አድርጓቸዋል። የሚመገቡትን መናና ድርጭት ሰጥቷቸዋል። ሆኖም ወደ መራራው ውኃ ሲደርሱ እግዚአብሔር ተአምራት እንዲሠራላቸው ከመጠየቅ ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ላይ እና በሙሴ ላይ አጉረመረሙ። ይህ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንደሌላቸው ያሳያል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ውኃ ቢሰጣቸውም የእሥራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር እምነት እንደሌለው ያሳየበት ከእርሱ ጋር የተጣላበትና ትዕግሥቱን የተፈታተነበት ቦታ በመሆኑ ቦታው ማሳህ እና መሪባ ተብሎ ተጠራ፤ እነዚህም «መፈተንና መጣላት» የሚል ትርጓሜ ያላቸው ቃላቶች ናቸው። ለመዝሙረ ዳዊትና ለዕብራውያን ጸሐፊዎች ይህ ታሪካዊ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ባለመታዘዙ እና ባለማመኑ የእግዚአብሔርን ቁጣ በእራሱ ላይ እንዳያወርድ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ማሳየት እንዳለበት የሚገልጽ ጥሩ ምሳሌ ነው።

10ኛ ጥያቄ፡- ዘኁልቁ 13፡26-14፡35 አንብብ።

ሀ) እግዚአብሔርን በእሥራኤላውያን ላይ እንዲናደድ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?

ለ) ኢያሱና ካሌብ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ያሳዩት እንዴት ነው?

ሐ) ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባታቸውን በተመለከተ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን የሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው?

በዚህ ክፍል ላይ የተጠቀሱት ክንዋኔዎች የተፈጸሙት እግዚአብሔር እራሱን በታላቅ ኃይል በሲና ተራራ ከገለጸ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ነው። በዚህ ሥፍራ ለእሥራኤላውያን ሕጉን ሰጣቸው፤ እነርሱም ሕጉን ለመጠበቅ ቃል ገቡ። ወደ ተስፋይቱ ምድር ወሰን ወደሆነችው ወደ ከነዓን አካባቢ እንደደረሱ ምድሪቷን ለመውሰድና ጠላቶቻቸውን ለመውጋት ከመነሣታቸው በፊት አሥራ ሁለት ሰላዮችን ይልካሉ። ከእነዚህም ውስጥ አሥሩ ሰላዮች ምድሪቱን ለመውሰድ እንደማይችሉ ይናገራሉ። ሁኔታውን የተመለከቱት በእምነት ዓይን አይደለም። ሁለቱ ብቻ ናቸው፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ ጠላቶቻችንን ድል እናደርጋቸዋለን ብለው ሕዝቡን ለማሳመን የሞከሩ እስራኤላውያን ግን ለመግባት እምቢ አሉ። በዚህም ምክንያት ለመዋጋት ዕድሜያቸው በቂ የሆነ ሁሉ በምድረ በዳ ውስጥ ይሞታሉ ብሎ እግዚአብሔር ማለ። ያ ትውልድ በሙሉ እስኪሞት ድረስ ለአርባ ዓመት ያህል የእሥራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ተንከራተተ።

እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ልክ ከባርነት እንዳወጣቸው ሁሉ የአይሁድ ክርስቲያኖችንም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ከኃጢአት ነፃ አውጥቷቸዋል። ወደ ድሮው ሃይማኖታቸው ለመመለስ የሚያደርጉት ማንኛውም ዓይነት መከራ ልክ እንደ በፊተኞቹ እሥራኤላውያን ያለማመን ኃጢአት ሆኖ ይቆጠርባቸዋል። ይህም እሥራኤላውያን የቀመሱትን ዓይነት ቅጣት ያስከትልባቸዋል። እግዚአብሔር ተስፋ

ወደ ሰጠው ዕረፍት ሳይደርሱ ይጠፋሉ። ለእሥራኤላውያን ይህ ዕረፍት የተስፋው ምድር ነው። ለአይሁድ ክርስቲያኖች ደግሞ ይህ ዕረፍት መንግሥተ ሰማያት ነው።

11ኛ ጥያቄ:- ልክ የጥንቶቹ እሥራኤላውያን እግዚአብሔርን እንደተፈታተኑና ጠላቶቻቸውን በተመለከተ በእርሱ ለመታመን ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ሁሉ ዛሬ የሚገኙ ክርስቲያኖች ይህን የመሰለ ኃጢአት ሊሠሩ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝረህ ጻፍ።

ጸሐፊው አይሁዳውያኑ የጥንቶቹን እሥራኤላውያን ዓይነት አመለካከት እንዳይኖራቸው ያስጠነቅቃቸዋል። የጥንቶቹ እሥራኤላውያን ሁሌ ልባቸውን እልከኛ በማድረግ ወደ ጥፋት ይሄዳሉ። ክርስቲያኖቹ ኃጢአተኛና የማያምን ልብ እንዳይኖራቸው ከወዲሁ ጥንቃቄ መውሰድ ነበረባቸው።

የብሉይ ኪዳኑ አምላክና የአዲስ ኪዳኑ አምላክ አንድ በመሆኑ የአይሁድ ክርስቲያኖች ወደ ድሮው ሃይማኖታቸው ሲመለሱ እግዚአብሔርን መካዳችን አይደለም ብለው ሊከራከሩ ይችሉ ነበር። ነገር ግን የመጨረሻው የእግዚአብሔር ራዕይ የሆነውን ኢየሱስን በመካድ እራሱን እግዚአብሔርን ይክዱ ነበር። ይህም እውነተኛ እምነት እንደሌላቸው ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

ጸሐፊው ለክርስቲያኖቹ ሁለት ዋና ዋና ምክሮችን ሰጥቷቸዋል። የመጀመሪያው ቀን በቀን እየተገናኛችሁ ተመካከሩ የሚል ነው። ክርስቲያን የመጨረሻ የሚደክመው ለብቻው ሲቆም ነው። ነገር ግን በእምነታችን እንድንጸና እርስ በእርሳችን የምንደጋገፍ ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ታማኝ ሆኖ መቆሙ አይከብደንም።

12ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ የክርስቲያን ማጽናናት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነህ እንድትቆም ያደረገህ እንዴት ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ክርስቲያኖች የበለጠ እርስ በእርሳቸው እየተገናኙ እንዲጽናኑና እምነታቸውን እንዳይክዱ ልታደርግ የምትችለው እንዴት ነው?

ሁለተኛ! ጸሐፊው:- እምነታችሁን አጽንታችሁ ጠብቁ ብሎ ያስጠነቅቃቸዋል። ዋናው ነገር የመጀመሪያው እምነታቸው አይደለም። ኢየሱስን አጥብቀው እስከመጨረሻው መያዛቸው ነው! በመጨረሻ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር ተካፋዮች ለመሆናቸው ማረጋገጫ የሚሆንላቸው። ሁላችንም በልባችን ውስጥ ምንም ዓይነት ኃጢአት በተለይም የአለማመን ኃጢአት እንዳይኖር ለማየት ሐላፊነት መውሰድ ይኖርብናል። ኃጢአት የምንወስዳቸው እርምጃዎች ሁሉ ትክክል እንደሆኑ አድርገን እንድናስብ ስለሚያደርገን በጣም አሳሳች ነው። ለራሳችን ምክንያቶችን በመስጠት የምንሠራው ሥራ ትክክል አይደለም ብለን ማሰብ እስከናቆም ድረስ እንደርሳለን። ኃጢአት ወደ ብርሃን ወጥቶ የሚገለጠው ሕይወታችንን በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ውስጥ አድርገን ስናይ ብቻ ነው። ንስሐ መግባት የሚገባን አሁኑኑ ነው። ማናችንም ብንሆን መቼ እንደምንሞት አናውቅም። ንስሐ ለመግባትና ኢየሱስን ለመከተል የምንችለው አሁን ገና ሳንሞት ነው። አንዴ ከሞትን ወይም ኢየሱስ ዳግም ከመጣ በኋላ ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ዕድል አይኖረንም።

13ኛ ጥያቄ:- አሁን ለትንሽ ጊዜ ሕይወትህን መርምር። የተደበቀ ኃጢአት አለህ? ኢየሱስን ከልብ የማታምንባቸውና ትዕዛዛቱን የማትጠብቅባቸው መንገዶች አሉ? እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ ያለውን ኃጢአት በግልጽ እንዲያሳይህና ምሕረቱን እንዲሰጥህ ጸልይ።

# ሦስተኛ ቀን:- ዕብራውያን 4:1-10

በትናንትናው ዕለት እሥራኤላውያን ባለማመናቸው እግዚአብሔር ተስፋ ወዳደረገላቸው ወደ ዕረፍቱ እንዳልገቡ አይተናል። ዛሬ ደግሞ ለእኛ ተስፋ የተሰጠን ዕረፍት እንዳለ እንመለከታለን። ታዲያ ወደ ዕረፍቱ መግባታችንን እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል።

ለአማኝ በሕይወቱ ትልቁ ነገር ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት መግባትና ተስፋ ያደረገለትን በረከቶች መቀበል ነው። እዚህ በምድር ላይ ያለው ዕረፍትና የሕይወት በረከት የምናስብና እግዚአብሔርን እንዳናምን፥ እንዳንታዘዝ የሚያደርገን ከሆነ የዘላለማዊው ዕረፍት ወራሾች አንሆንም። የዕብራውያን ጸሐፊ ተስፋ ወደ ተሰጠን ወደ ዘላለማዊው ዕረፍት ስለ መግባታችን እርግጠኞች እንድንሆን ያስጠነቅቀናል።

14ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 4:1-10 አንብብ።

ሀ) ወንጌልን ከመስማት ጋር ለፍሬ እንዲሆንልን አብሮ መታከል ያለበት ነገር ምንድን ነው?

ለ) በቁጥር 1 ላይ ለክርስቲያኖች የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

ሐ) ለሚያምኑ ሰዎች የተሰጠው ተስፋ ምንድን ነው?

መ) የዕረፍቱ ተስፋ የተመሠረተው በምን ላይ ነው? (ከቁጥር 3-4)።

በዕብራውያን 4:1-10 ላይ ጸሐፊው በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት ለመተው ለሚፈልጉ አይሁዳውያን የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ ይቀጥላል። ይህንንም የሚቀጥለው ለሙሴና ለእሥራኤል ልጆች የተሰጠውን የዕረፍት ተስፋ እግዚአብሔር ከሰጠው የመንግሥተ ሰማያት ዕረፍት ጋር በማነፃፀር ነው። የመንግሥተ ሰማያት ዘላለማዊ ዕረፍት በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ ክፍት እንደሆነና ነገር ግን ልክ እሥራኤላውያን ባለማመናቸው በምድረ በዳ ውስጥ ተንከራትተው ዕረፍቱ እንደቀረባቸው ሁሉ እነዚያ በኢየሱስ የማያምኑትም ዘላለማዊው ዕረፍቱ እንደሚቀርባቸው ይናገራል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሚገኙት የእግዚአብሔር ሕዝቦችና በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሚገኙት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ብዙ መመሳሰሎች አሉ። ለሁለቱም ወንጌል ተሰብኮላቸዋል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በሙሴ በኩል በመሆን ሕዝቡ በእርሱ ካመኑና ትዕዛዙን ከጠበቁ እንደሚባርካቸው ቃል ገብቶ ነበር። ምንም እንኳ በዚህ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ባያውቁም ስለ ደኅንነቱ መንገድ በግልጽ ነው የተናገራቸው። ልክ እንደዚሁ በአዲስ ኪዳንም በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኩል ያለው የደኅንነት መንገድ በግልጽ ነው የተቀመጠው ቢሆንም ዋናው ነገር ወንጌልን መስበኩ ወይም መስማቱ አይደለም።

ዋናው ነገር ሕዝቡ ስለሰሙት ነገር የሚሰጡት ምላሽ ነው። የሰሙትን ነገር ማመንና መታዘዝ አለባቸው። ለእኛም ቢሆን የእግዚአብሔርን ቃል መስማቱና ማንበቡ ብቻ በቂ አይደለም፤ ቃሉን በመጠበቅም እምነታችንን መግለጽና ማሳየት ይኖርብናል። በብሉይ ኪዳን እሥራኤላውያን የከነዓን ጠላቶቻቸውን ድል እንደሚያደርጉና የተስፋይቱን ምድር እንደሚሰጣቸው እግዚአብሔርን ባለማመናቸው በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ሊያሳዩ አልቻሉም። ይህን ዓይነት ስሕተት ዛሬም ሊከሰት ይችላል። እግዚአብሔርን ለማመንና ትዕዛዙን ለመጠበቅ አሻፈረን ካልን በሕይወታችን ችግር ሲያጋጥመንም እግዚአብሔርን ከካድን እኛም ከእግዚአብሔር የተሰጠንን የዕረፍት ተስፋ ሳናገኝ እንቀራለን።

በዚህ ክፍል ያለው የጸሐፊው ገለጻ በጣም የተወሳሰበ ነው። ምናልባትም አይሁዳውያን «ዕረፍትን» በተመለከተ ስላለው ሐሳብ ሳይጠይቁት አይቀሩም። ያለምንም ጥርጥር ኢያሱ ሕዝቡን በሚመራበት ወቅት እሥራኤላውያን ወደ ዕረፍቱ አልገቡምን? ታዲያ ያ ዕረፍት ዛሬ ለእኛ እንዴት ክፍት ሊሆንልን ይችላል? ብለው ጠይቀውታል። ጸሐፊውም ምንም እንኳ እሥራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ቢገቡም ወደ እውነተኛው ዕረፍት እንዳልገቡ ያረጋግጥላቸዋል። ይህንን ክፍል በደንብ እንድናጤን ከተፈለገ አራት የተለያዩ ዕረፍቶች መጠቀሳቸውን ማስተዋሉ ተገቢ ነው። መጀመሪያ:- ለእውነተኛው ዕረፍት መሠረት የሆነ ከፍጥረት ጊዜ የታየው የእግዚአብሔር ዕረፍት አለ፤ (4:4)። ሁለተኛ:- በኢያሱ በኩል የተፈጸመው ወደ ከነዓን ምድር የመግባት ዕረፍት አለ፤ (3:7-19)። ሦስተኛ:- አማኝ ለሆኑ ሰዎች ክፍት የሆነው የአሁኑ ዕረፍት አለ፤ የደኅንነት ዕረፍት ብለንም ልንጠራው እንችላለን (4:1+3)። አራተኛ:- ወደ መንግሥተ ሰማያት ስንገባ የሚኖረን ዘላለማዊ ዕረፍት ነው፤ (4:10-11)።

ገለጻው በዚህ ቅደም ተከተል ነው የተጻፈው። እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ የሰጠው ተስፋ እስከ ዛሬ ድረስ ለእኛ ክፍት ነው፤ ምክንያቱም:-

1. እውነተኛው የእግዚአብሔር ዕረፍት የተመሠረተው ወይም የተጀመረው እሥራኤላውያን ከነዓን ሲገቡ ሳይሆን እግዚአብሔር ፍጥረታቱን ፈጥሮ ባረፈበት ወቅት ነው።

15ኛ ጥያቄ:- አሪት ዘፍጥረት 2:2 አንብብ። እግዚአብሔር ያረፈው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ስድስት ቀን ሠራ። በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር እንዳረፈ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር የፍጥረትን ሥራ መሥራትን አልቀጠለም። ልናስተውለውና ልንደነቅበት የሚገባን ነገር በኦሪት ዘፍጥረት ላይ እግዚአብሔር በስምንተኛው ቀን ሥራውን እንደገና ጀመረ የሚል ነገር አለመኖሩ ነው። ስለዚህም ለጸሐፊው የፍጥረታት ዕረፍት ገና ያላለቀና ሁሌም ያለ ነገር ነው። ነገር ግን ዕረፍቱ ምን ነበር? አለመሥራት ብቻ ነው? አይደለም፥ በሌላ መልኩ ስናየው እግዚአብሔር ሁሌ እየሠራ ነው፤ (ዮሐንስ 5:17)። እንግዲያስ እግዚአብሔር የመሠረተውና ሰዎች እንዲገቡበት የሚፈልገው ዕረፍት በእግዚአብሔርና በበረከቱ

ሐሴት የማድረግ ዕረፍት ነው። ይህ ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች አሁንም ክፍት ነው፤ ታዲያ መንፈሳዊ ነው እንጂ ቁሳዊ አይደለም።

2. እግዚአብሔር ተስፋ ያደረገላቸውን የከነዓን ዕረፍት እሥራኤላውያን ሙሉ በሙሉ አልፈጸሙም። መጀመሪያ ባለማመናቸው ይህ ዕረፍት ከእነርሱ ተወሰደ። ምንም እንኳ ከነዓን ከገቡ በኋላ በከፊል ቢያርፉም (ኢያሱ 21፡44)፤ እግዚአብሔር ያቀደው ፍጹም መንፈሳዊና ሥጋዊ ዕረፍት ግን አልተፈጸመም ነበር። ይህ በታሪክ ውስጥ እሥራኤላውያን ባሳለፉዋቸው ጦርነቶችና የአለማመን ልበ ደንዳናነት ይታያል። ይህ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስም የተደገፈ ነው። በመዝ.(95) ላይ ዳዊት እሥራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ከገቡ ከ400 ዓመት በኋላ ይህ ዕረፍት ለእግዚአብሔር ልጆች አሁንም ገና ክፍት እንደሆነ ይገልጻል።

3. ይህ የእግዚአብሔር ዕረፍት በእርሱ ለሚያምኑና ትዕዛዙን ለሚጠብቁ ሁሉ ሁሌም ክፍት ነው። ለዚህም ነው የዕረፍቱ ግብዣ ቭለዛሬህ የተባለው። በማናቸውም ጊዜ አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር በእምነትና በታዛዥነት ከቀረበ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠውን ዘላለማዊ ዕረፍትና ሰላም ይሰጠዋል። ይህ ዕረፍትና ሰላም በዚህች ሕይወቱ በከፊል ተፈጻሚነት ያገኛል። በኃጢአት እና በሞት ከመስጋት ያርፋል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመሆኑ የሚሰማው ደስታ አለ። ይህ ዕረፍት «የሰንበት ዕረፍት» ነው የሚባለው፥ ምክንያቱም የተመሠረተው በአካል ወደ ከነዓን በመግባት ላይ ሳይሆን እግዚአብሔር በፍጥረት ጊዜ ካረፈው የሰንበት ዕረፍት ጋር በመመሳሰሉ ነው።

4. ለክርስቲያኖች በመጨረሻ የሚሰጠው ዕረፍት የሚገኘው በመንግሥተ ሰማያት ብቻ ነው። እዚያ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጣቸው ነገሮች በሙሉ ይፈጸማሉ። ከችግሮቻችን ሁሉ እውነተኛ የሆነ ዕረፍት ይሆንልናል። ጸሐፊው በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ከፍጥረት በኋላ እንዳረፈ ሁሉ እኛም ምድራዊ ከሆነው ሥራችን እናርፋለን ነው የሚለው፤ (ራዕይ 14፡13)።

በዕብራውያን 4፡1-10 ላይ ያለው ትልቁ ማስጠንቀቂያ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ሰጠው ዕረፍት ለመግባት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ነው የሚለው። ይህ ዕረፍት በቅጽበት የምናገኘው ነገር ባይሆንም በቀላሉ ባለመታዘዝና ባለማመን ልናጣው የምንችለው ነገር ነው። ይህ ዛሬ ለእኛ በጣም አስፈላጊ የሆነ ማስጠንቀቂያ ነው። ብዙዎቻችን ያደግነው በክርስቲያን ቤተሰቦች መካከል በመሆኑ ወላጆቻችን ክርስቲያኖች ስለሆኑ እኛም ክርስቲያኖች ነን ብለን ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን የተሳሳተ እምነት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን በግላችን ማመንና እርሱን ደስ የሚያሰኝ የታዛዥነት ሕይወት ልንኖር ይገባናል። ለእግዚአብሔር እስከ መጨረሻው ድረስ ታማኝ በመሆን የእምነታቸውን እውነተኛነት የሚያሳዩ ብቻ ናቸው እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ሰጠው ዕረፍት ሊገቡ የሚችሉት። ዓለምን ለመከተል ወይም ወደ ሌላ ሃይማኖት ለመግባት የምናደርገው ማናቸውም ዓይነት ጥረት እግዚአብሔር የሰጠንን ዕረፍት ትተን በኋላ የምንፀፀትበት ነገር ይሆናል።

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ነው ያደግሽው?

ለ) ከሆነ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝህ የተቀበልከው መቼ ነው?

ሐ) በክርስቲያን ቤተ ሰብ ውስጥ ካላደክ በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው የግል እምነታቸው ከመታመን ፈንታ በወላጆቻቸው እምነት ላይ የሚታመኑ ሰዎች ታውቃለህ?

# አራተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 4፡11-13

እውነተኛ የሆነ ክርስትና ሰዎች በቀላሉ ሊከተሉት የሚችሉት በሰዎች የተለመደ ሃይማኖት አይደለም። ለመለወጥ ሳንሻ ዝም ብለን በአፋችን በኢየሱስ እናምናለን ማለትም አይደለም። በምትኩ ክርስትና ከእኛ ጠንከር ያለ ሥራ የሚጠብቅ ነው። ጳውሎስ እንዳለው ሁልጊዜ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ደኅንነታችንን መፈጸም አለብን፥ (ፊል.2፡12-13)። ይህም እራሳችንንና የቤተ ክርስቲያኖቻችንን ምዕመናን በተመለከተ ልንጠይቅ የሚገባው ጥያቄ «ብዙዎች እነዚህ ክርስቲያኖች ናቸው ይላሉ ወይ? የሚል ጥያቄ አይደለም ማለት ነው። ነገር ግን ምን ያህሉ ናቸው በእምነታቸው እያደጉ ክርስቶስን ወደ መምሰል የተቃረቡ? ብለን ነው መጠየቅ ያለብን። እውነተኛ እምነት የሚለካው በምንናገረው ነገር ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታችን አይደለም። እውነተኛ እምነት የሚለካው ምን ያህል ኢየሱስን በመምሰላችንና እስከ መጨረሻው ድረስ እምነታችንን በታማኝነት በመጠበቃችን ነው። አሁንም የዕብራውያን ጸሐፊ ፈተናዎቻቸውን ሁሉ ተቋቁመው ቀላሉን መንገድ ከመውሰድና ክርስትናን ከመካድ እንዲቆጠቡ ያበረታታቸዋል። ለፍርድ እግዚአብሔርን በሚቀርቡበት ጊዜ ውጤቱ ምን እንደሚሆን በመጥቀስም ያስጠነቅቃቸዋል።

17ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 4፡11-13 አንብብ።

ሀ) ክርስቲያኖች ምን እንዲያደርጉ ነው የታዘዙት?

ለ) የእግዚአብሔር ቃል ኃይል በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው የተገለጸው?

ሐ) የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ሕይወት ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ነው ያለው?

መ) እነዚህ ቁጥሮች ድርጊታችንንና ሐሳባችንን ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ያለንን ችሎታ በተመለከተ የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው?

እምነታቸውን በእርሱ ላይ ላደረጉ ለእግዚአብሔር ልጆች በሙሉ ነው ይህ የዘላለማዊ ደኅንነት ተስፋ የተሰጠው። ሆኖም እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደው መንገድ ቀላል ይሆናል ብሎ ቃል አልገባልንም። እንዲያውም እግረ መንገዱን ብዙ አደገኛ የሆኑ ነገሮች አሉት። አንድ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ሕይወቱ ዕድገት ላይ ትኩረት ሳይሰጥ ዝም ብሎ በየሳምንቱ ቤተ ክርስቲያን ቢመጣ በቂ አይሆንም! ክርስቶስን ወደ መምሰል ደረጃ ለማደግ የማያቋርጥ ሥራና ያላሰለሰ የግል ጥረት ያስፈልጋል። ስለዚህም የዕብራውያን ጸሐፊ ለክርስቲያኖቹ ያለውን ሐሳብና

ጭንቀት በዚህ መልኩ ጠቅለል አድርጎ ያስቀምጠዋል። በአንድ መልኩ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ የበረከት ተስፋ (ዕረፍት የተባለው) እፊታቸው በማስቀመጥ እስከ ምድራዊ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው ለመገኘት እንዲታገሉ ያበረታታቸዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ በእሥራኤላውያን ሕይወት ውስጥ የታየውን ዓይነት አለመታዘዝ በሕይወታቸው ከተለማመዱ ያንን ዕረፍት ወደ ማጣት እንደሚመራቸው ያስጠነቅቃቸዋል። በሌላ አነጋገር ወደ መንግሥተ ሰማያት ሳይሆን ወደ ገሃነመ እሳት ነው የሚሄዱት።

የእግዚአብሔር ልጆች ሕይወታቸውን እንዲመረምሩና ለእግዚአብሔርም ታማኞች ሆነው እንዲጸኑ ሊያደርጋቸው የቻለው ሌላው ምክንያት ደግሞ በሕይወታቸው የእግዚአብሔር ቃል በመሥራቱና በቅርብ ከእግዚአብሔር በደረሰባቸው ፍርድ ምክንያት ውስጥ ነው።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሌላው መጽሐፍ ቢጽፍም መጽሐፍ ቅዱስ በድን ሳይሆን ሕያውና የሚሠራ ነው። በምድር ላይ ካሉት መጻሕፍት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ለሕይወታችን የሚያስፈልገን መጽሐፍ የለም። ስለ ችግሮቻችንና በዓለም ላይ ስላለው ችግር እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መልስ የሚሰጥ መጽሐፍ የለም። የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑም ልክ እንደ እግዚአብሔር ሕያውና የሚሠራም ነው።

18ኛ ጥያቄ፡- ኢሳይያስ 55፡11 እና ኤርምያስ 23፡29 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ቃል ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ጋር ይነፃፀራል። በዚህ ጥቅስ ላይ ትኩረት የተሰጠው በሰይፉ የጥፋት ሥራ ላይ ሳይሆን በሰይፉ ስለት ላይ ነው። ሰው ሊሠራው ከሚችለው ማንኛውም ዓይነት የስለት መሣሪያ የበለጠ ስለት ያለው ነው። ጸሐፊው በጣም ስለት ያለውና ሰዎች ሊደርሱባቸው የማይችሉባቸውን ውስጣዊ ክፍሎች የሚደርስና የሚለያይ ነው ይለዋል። መንፈስና ነፍስ በጣም የተጣበቁ ነገሮች በመሆናቸው እነርሱን ለመለየት አይቻልም። የሚታዩም ነገሮች አይደሉም። ጅማትና ቅልጥምም እንደዚሁ የተጣባበቁ ነገሮች ናቸው። ይህም ሆኖ የእግዚአብሔር ቃል ለሌሎችና ለራሳችን የማይታዩ የሕይወታችን ክፍል ውስጥ በመግባት ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል።

አንዱ ዋነኛ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ሥራ በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ችግር ለእኛ ማሳየት ነው። የእግዚአብሔር ቃል እርኩስ የሆነውን ሥራችንን ብቻ አይደለም የሚገልጸው ከሌሎች ሰዎች ዓይን የተሰወረውን ሐሳባችንንና አመለካከታችንንም ጭምር ነው የሚያወጣው። ብዙ ጊዜ እንደ ክርስቲያን ትኩረት የምናደርገው በሰዎች ውጫዊ ምግባር ላይ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙ ትኩረት የሚሰጠው ልብ ላይ ነው። እኛ ስላለን አመለካከትና አስተሳሰብ በጣም ያስባል። ስለዚህም ከመጥፎ አስተሳሰብና ዕቅድ ተነሥተን አንድ ጥሩ ነገር ብንሠራ እንኳ እግዚአብሔር ስለዚህ ይፈርድብናል። በሌላ አነጋገር በንፁህ አስተሳሰብ ተነሣሥተን ስሕተት ያለው ነገር እንኳ ብንሠራ እግዚአብሔር ስለሚረዳው በሠራነው ሥራ ይባርከናል።

19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እንዴት ነው ይህ ብዙ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ትኩረት ከሚሰጡት ነገር ለየት የሚለው?

ለ) አንድ ክርስቲያን በተሳሳተ አስተሳሰብ ተነሥቶ ትክክል የሆነ ነገር ሊሠራ የሚችልባቸውን ሁኔታ ምሳሌዎች በመስጠት ግለጽ።

ሐ) አንድ ክርስቲያን አንዳንድ ነገሮችን ከበጎ አስተሳሰብ ተነሥቶ ሲያደርጋቸው ነገር ግን በሌሎች ዘንድ እንኳ እንደ ስሕተት ሊቆጠሩ የሚችሉ ምሳሌዎች ስጥ።

የእግዚአብሔር ቃል አያዳላም። ደሃም ሆንን ሀብታም ምንም ችግር የለውም ልባችንን በእግዚአብሔር ፊት በግልጽ በመክፈት ይፈርድብናል።

አማኞች እግዚአብሔርን ሊያታልሉ እንደማይችሉ መረዳት አለባቸው። በልባችን ውስጥ የተደበቁት ነገሮችና ፍጥረታት በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት የተገለጡ ናቸው። ከሌሎች ሰዎች ዐይን አንዳንድ ነገሮችን ልንደብቅ እንችላለን፤ እግዚአብሔር ግን አይታለልም። አንድ ቀን አስተሳሰባችንና ሥራችን በእግዚአብሔር ፊት ይመረመርና መልስ የምንሰጥበት ቀን ይመጣል፤ (1ቆሮ.4፡5)። በእርሱ ፊት እራቁታችንን እንደሆንን ነው የሚቆጠረው።

20ኛ ጥያቄ፡- ቅዱስ ሕይወት ስለ መኖር ይህ የሚሰጠን ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

ከዚህ ትምህርት ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ልንማር እንችላለን። በመጀመሪያ ሥራችንን ብቻ ሳይሆን አስተሳሰባችንንም ጭምር መመርመር እንዳለብን እንማራለን። እንደ ትዕቢት፥ ጥላቻ፥ ቅናት፥ ወዘተ... ያሉትን ድብቅ ነገሮች መመልከት ይኖርብናል። ምንም እንኳ ከበጎ ምግባር ጋር ቢታከሉም እነዚህ ነገሮች በእግዚአብሔር እንደ ኃጢአት ነው የሚቆጠሩት። ሁለተኛ፤ በእግዚአብሔር ተጠያቂዎች መሆናችንን በመገንዘብ እንድንኖር ያስተምረናል። እግዚአብሔር እንደ ሙሴና ኢየሱስ ታማኞች እንድንሆን ይፈልጋል። ታማኞች ነን?

21ኛ ጥያቄ፡- እነዚህ መመሪያዎች በምን ዓይነት ሁኔታዎች የክርስቲያንን ሕይወት ሊቀይሩ እንደሚችሉ በዝርዝር ጻፍ።

**አምስተኛ ቀን**፡- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጁ ሁን።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ፡-

ሀ) 1. አንዳንድ በኢትዮጲያ የሚታወቁ የክርስቲያን መሪዎችን ስም በዝርዝር ጻፍ።

2. አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስን ከሚከተሉት በላይ እነሱን ይከተሏቸዋል?

3. ለምንድን ነው ይህ አደገኛ የሚሆነው?

4. ዐይናችን በኢየሱስ ላይ ብቻ እንዲሆን የምናደርገው እንዴት ነው?

5. ይህ ምን ማለት ነው?

ለ) አንድ ታማኝ የቤተ ክርስቲያን መሪ ምን ዓይነት ባህርይ እንዳለው ግለጽ። ድርጊቱን፥ መንፈሳዊ ሕይወቱን እንዲሁም በጓደኞቹ፥ በቤተሰቦቹ፥ በእግዚአብሔር፥ በሥራው አካባቢ ያለውን አኗኗር በተመለከተ ምን ዓይነት ባህርይ ነው ያለው?

ሐ) 1. ለምንድነው ብዙ ክርስቲያኖች ወደ ዓለም የሚመለሱት?

2. በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ከክርስቲያኖች ጋር ቢገናኙ በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ ሊረዳቸው የሚችለው እንዴት ነው?

3. ቤተ ክርስቲያንህ በውስጧ ያሉ ክርስቲያኖች የበለጠ ተገናኝነተው እንዲበረታቱ ልታደርግ የምትችለው እንዴት ነው?

መ) 1. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን ዳግም እንደተወለዱ የሚቆጥሩ አሉ?

2. ለምንድን ነው ይህ ስሕተት የሆነው?

3. ለምንድን ነው የእግዚአብሔር ቃል ለደኅንነታችን እንድንኖርና እንድንተጋ የሚነግረን? ይህ ሐሳብ ጳውሎስ ደኅንነት በፀጋ ነው ብሎ ካስተማረው ትምህርት ጋር ሊነፃፀር የሚችለው እንዴት ነው?

ሠ) 1. የእግዚአብሔር ቃል ስሕተቶቻችንን ወደ ብርሃን የሚያወጣባቸውን የተለያዩትን መንገዶች ዘርዝረህ ጻፍ።

2. በምን ዓይነት መንገዶች ነው በልባችን ውስጥ ያለው ሐሳብ ከድርጊታችን የሚበልጠው?

3. አንድ ሰው ከቷሳሳተ ዕቅድ ተነሣሥቶ እንዴት ትክክል የሆነ ድርጊት ሊፈጽም እንደሚችል ምሳሌዎች በመስጠት አስረዳ።

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ ሁለት

ዕብራውያን 4፡14-5፡14

## የመጀመሪያ ቀን፡- ዕብራውያን 4፡14-16

በፈተናና በስደት ውስጥ አንድ ሰው በእምነቱ ጸንቶ ሊቆም የሚችለው እንዴት ነው? እራሳችንንና የቤተ ክርስቲያናችችንን ምዕመናን ከሐሰተኛ ሃይማኖት ወጥመድ ልናድን የምንችለው እንዴት ነው? ይህ በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው ዋነኛው ጥያቄ ነው። መልሱም ስለ ኢየሱስ ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል የሚል ነው። ወደ እግዚአብሔር የሚወስዱ ብዙ መንገዶች የሉም። ኢየሱስ የራሳቸውን ሃይማኖት ከመሠረቱ ታላላቅ ሰዎች መካከል ብቻ አይደለም። በምትኩ ግን ኢየሱስ በጣም ለየት ያለ ነው። ጸንተን ለመቆም ስለ ማንነቱ ሙሉና ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል። በመጀመሪያ በምድር ላይ ሆነ በሰማይ ላይ ከተፈጠሩት ፍጥረታት ሁሉ የበላይ ነው። ከጥንት ነቢያቶች መንግሥተ ሰማያት ላይ ካሉ መላእክትና ከታላቁ የብሉይ ኪዳኑ መሪ ከሙሴ እንደሚበልጥ ተመልክተናል። ሁለተኛ፣ ብቸኛው ሊቀ ካህን እርሱ ብቻ ነው። ሙሉ ደኅንነት የሚያስገኘውን የመጨረሻና ዘላለማዊ መሥዋዕት ያቀረበው እርሱ ብቻ ነው። ስለዚህ ሌላ የደኅንነት መንገድ አለ ብለው የሚሉ ሌሎች መሪዎች በሙሉ ሐሰተኞች ናቸው። ሊቀ ካህናችን እንደመሆኑ ከእኛ በጣም የራቀ አይደለም፤ በቅርብ ሆኖ በችግር ውስጥ ስናልፍ የሚረዳን ነው። ታላቅ ከመሆኑና ለእኛ ከሚሰጠን ያልተቆጠበ እንክብካቤ የተነሣ የሚያስፈልገንን ዕርዳታ እንደምንቀበል እርግጠኞች በመሆን በእርሱ በኩል በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር አብ መቅረብ እንችላለን። ለብዙ ክርስቲያኖች ከእምነታቸው መፈናቀል ምክንያት የሚሆነው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው ግንዛቤ የተሟላ አለመሆኑ ነው።

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ ሰዎች ሲታመሙ ሲደኸዩ ከቤተሰቦቻቸው ውስጥ ሰው ሲሞት ወደ ማን ነው የሚሄዱት?

ለ) ለምንድን ነው ብዙ ክርስቲያኖች በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ከመቅረባቸው በፊት ወደ ሰዎች የሚሄዱት?

ሰዎች የተለያዩ ችግሮች ሲያጋጥሟቸው ሊረዳቸው ወደሚችል ባለሙያ ነው የሚሄዱት። ከታመሙ ወደ ዶክተር ወይም ወደ ጠንቋይ ቤት ይሄዳሉ። ከደኸዩ ምግብ፥ ልብስና ገንዘብ ወደሚሰጧቸው ሰዎች ዘንድ ይሄዳሉ። ምንም እንኳ ሰዎች ሊረዱ ቢችሉም አንድ ክርስቲያን ችግር ሲያጋጥመው የመጀመሪያው እርምጃው ይህ መሆን የለበትም። በሰዎች ላይ የምንታመን ከሆነ ሁሌ የምንሸነፍና ተስፋ የምንቆርጥ ሰዎች ነው የምንሆነው። ስለዚህ ኢየሱስ ብቻ ፍላጎታችንን እንደሚያሟላልን እርግጠኞች በመሆን የመጀመሪያው ዕርምጃችን በጸሎት ወደ እርሱ መቅረብ መሆን አለበት።

የዛሬው ክፍል ዋነኛ ትምህርት የሚገኘው እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ

የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬም ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና በሚለው በኢየሱስ ቃል ውስጥ ነው፤ (ማቴ.11፡28-29)።

2ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 4፡14-16 አንብብ።

ሀ) ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ የተገለጸው እንዴት ነው?

ለ) ኢየሱስ ምን ዓይነት ሊቀ ካህን ነው?

ሐ) በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለክርስቲያኖች የተሰጡት ሁለት ትዕዛዞች ምን ምንድን ናቸው?

ባለፈው ሳምንት ጸሐፊው ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ሰጠው ዕረፍት ለመግባት እንዲተጉ እንዳሳሰባቸው አይተናል። ለመግባት ሲሉ ግን ብቻቸውን መጣርና መታገል የለባቸውም ነበር። ጸሐፊው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት ወደ መካድ ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ ሊረዷቸው የሚችሉ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች እንዳሉ ያሳስባቸዋል።

አንደኛ፤ ታላቁ ሊቀ ካህን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለላቸው። በዕብራውያን መጽሐፍ ከሚገኙት ዋና ዋና ትምህርቶች አንዱ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህን መሆን ሲሆን ይህንንም ሠፋ ባለ ሁኔታ በሚቀጥሉት ሦስት ትምህርቶች ላይ እንግረዋለን። ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ በዚህ ሥፍራ እንደገና ጸሐፊው ይገልጽላቸዋል።

1. ታላቁ ሊቀ ካህን ነው። ጸሐፊው ሀታላቅሀ የሚለውን ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዳውያን ከሚያውቋቸው ሊቀ ካህናት ሁሉ እጅግ የበለጠ መሆኑን ለመግለጽ ሲል ነው የሚጠቀምበት። ሊቀ ካህን ኢየሱስ የሚያገለግለው ምድራዊ በሆነ ቤተ መቅደስ ውስጥ ሳይሆን በመንግሥተ ሰማያት ላይ መሆኑን አስተውል። ጸሐፊው ኢየሱስን ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ከአሮን ዘር ጋር ነው የሚያነፃፅረው። እንደምታስታውሰው በስርየት ቀን ሊቀ ካህኑ ከመሠዊያው በቅዱሱ ቦታ በኩል ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ይገባል። ኢየሱስ ግን ታላቁን መስዋዕት በምድር ላይ ሆኖ ካቀረበ በኋላ እግዚአብሔር ወደሚኖርበት ወደ መንግሥተ ሰማያት ነው ያረገው። ጸሐፊው ከዚህ ቀደም ብሎ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ እንደተቀመጠም ገልጿል።

2. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። የእኛ ሊቀ ካህን እንደ አሮን ደካማና ኃጢአተኛ የሆነ ሰው አይደለም እሱ እግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህም በማንኛውም ዓይነት ችግር ሊረዳን ይችላል።

3. ኢየሱስ ሙሉ ሰው ነው እግዚአብሔር ተከተለው ብሎ ካዘዘው መንገድ ላይ ሊያፈናቅለው በሚችለው ፈተና ውስጥም ያለፈ ነው። ምናልባት እነዚህ የአይሁድ ክርስቲያኖች ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ስለሆነ ያለው ሰው በመሆናቸው የሚያጋጥማቸውን ችግር በደንብ አይረዳልንም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ ስለዚህም ጸሐፊው ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሲመጣ እነዚያ ማንኛውንም ሰው ሊያጋጥሙት የሚችሉ ችግሮችና መከራዎች ሁሉ ደርሰውበታል ብሎ እንደገና ያሳስባቸዋል። የሰዎችን

ድካመት ጠንቅቆ ነው የሚያውቀው። ለዚህም ማስረጃው የራሱ መፈተን ነው። ያለጥርጥር ጸሐፊው በዚህ ሥፍራ የሚጠቅሰው የኢየሱስን በምድረ በዳ ውስጥ መፈተን ነው፤ (ማቴ.ምዕራፍ 4)። ነገር ግን ከዚህም ሌላ የመስቀሉን መንገድ ትቶ ሌላ መንገድ እንዲከተል ተፈትኖ ነበር፤ (ሉቃስ 22:39-46)። ኢየሱስ ሰይጣን በአማኞች ላይ እምነታቸውን እንዲተዉና ለእግዚአብሔር እንዳይታዘዙ ሲል የሚያደርገውን ተፅዕኖ ያውቅ ነበር። ኢየሱስ በፈተናዎቹ ውስጥ ሰይጣንን እንዳሸነፈው ሁሉ እኛም ተመሳሳይ ፈተናዎች ሲገጥመን ይረዳልንና ያግዘናል። በእኛና በኢየሱስ መካከል ያለው ልዩነት እኛ ወደ ኃጢአት የሚስበን የኃጢአት ተፈጥሮ አለን፤ እርሱ ግን የለውም። በኃጢአት ሳይወድቅ የኖረ ሰው እርሱ ብቻ ነው።

3ኛ ጥያቄ:- በምንጸልይበት ወቅት የሚያጋጥሙንን ችግሮች የሚረዳልን ሊቀ ካህን እንዳለን ማወቁና መረዳቱ እኛን የሚያጽናናን ለምንድን ነው?

በችግር ወቅት ለክርስቲያኖች ሁለተኛው አማራጭ ጸሎት ነው። ልክ በፖስታ ቤት በኩል ደብዳቤ እንደምንልከው ጸሎት እዚህ ምድር ላይ የሚደረግና ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚላክ ነገር አይደለም። በምትኩ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር አብ ፊት የሚያቀርበን ነገር ነው። በዚህም ሥፍራ በጸሎት የምናናግረው ከእኛ የበላይ ቢሆንም ለእኛ ግድ የሌለው አምላክ አይደለም። ስለዚህም ወደ አብ የምንቀርበው በፍርሃት ወይም ያለፍላጎት አይደለም። ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር የምንመጣው እኛን እንደሚረዳን ሙሉ በሙሉ በመተማመን ነው። እንደሚያዳምጠንም የምናውቀው ለእኛ ኃጢአት ሲል የሞተው አሁን መንግሥተ ሰማያት በመኖሩ ነው። የኃጢአት ዋጋ ተከፍሏልና ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድም ለልጆቹ ክፍት ነው። የፀጋው ዙፋን በብሉይ ኪዳን መገናኛ ድንኳን ውስጥ ካለው የስርየት መክደኛ ጋር ይመሳሰላል፤ ምክንያቱም ልንወድቅ ስንል የሚደግፈንን ፀጋ የምናገኘው በዚህ ሥፍራ ነው። በዚህ ሥፍራ በተጨማሪ እግዚአብሔር በኃጢአት ስንወድቅ ምሕረትና ይቅርታን ይሰጠናል። ከሁሉም በላይ ግን ኃጢአትን ድል የምናደርግበትን የእግዚአብሔር ኃይል የምናገኘው በዚህ ሥፍራ ላይ ነው። ለክርስቲያን ይህ ፀጋ ዙፋን የእግዚአብሔር ፍርድ የሚሰጥበትና የሚያስፈራ ቦታ አይደለም። በምትኩ ይህ የፀጋ ዙፋን እግዚአብሔር ሰዎች ሊያገኙት የማይገባቸውን ዕርዳታ የሚያገኙበት ቦታ ነው። ታዲያ ኃጢአተኛና ኃይል ወደ ሌለው ሰው ከመሄድ ለምንድን ነው ቀጥ ብለን ወደ እግዚአብሔር በመሄድ የሚያስፈልገንን ዕርዳታ የማንቀበለው?

4ኛ ጥያቄ:- ሀ) በምትጸልይበት ወቅት በእግዚአብሔር የፀጋ ዙፋን ክፍል ውስጥ የመሆንን እውነታ በምትጸልየው ጸሎት ላይ እና በጸሎት አቀራረብህ ላይ ያለው ተፅዕኖ ምንድን ነው?

ለ) ይህ ትምህርት የጸሎት ሕይወትህን የበለጠ እውነተኛና ኃይል ያለው ሊያደርገው የሚችለው እንዴት ነው?

የሚመጡብንን ፈተናዎች ልንቋቋም የምንችለው እንዴት ነው? በተለይ እምነታችንን ሊያስከድን የሚሞክረውን ፈተና ሁለት ዋና ዋና ትዕዛዞች ተሰጥተውናል።

አንደኛ፡ በኢየሱስ ላይ ያለንን እምነት አጥብቆ መያዙ የእኛ ሐላፊነት ነው። የፈለገውን ያህል ዋጋ ቢያስከፍለንም ኢየሱስን ለመከተል ወደ ኋላ ማለት የለብንም። ይህ የእኛ ሐላፊነት ነው። ሁለተኛ፡ ወደ ፀጋው ዙፋን መቅረብ አለብን። የእግዚአብሔርን ዕርዳታ የምንቀበልበት መንገድ ሁሌ ክፍት ነው። መታመን ያለብንም በሌሎች ሰዎች ላይ ወይም በእራሳችን ላይ ሳይሆን ለእኛ ክፍት በሆነው በእግዚአብሔር ኃይል ላይ ነው።

5ኛ ጥያቄ፡- ይህ ትምህርት ኃጢአት እንዲሠሩ ወይም በኢየሱስ ያላቸውን እምነት እንዲክዱ የሚፈተኑ ክርስቲያኖችን ሊረዳ የሚችልበትን የተለያየ መንገድ በዝርዝር ጻፍ።

## ሁለተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 5፡1-4

6ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 5፡1-10 አንብብ። ጸሐፊው ስለ ኢየሱስ ሊቀ ካህንነት የሚናገራቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

በብዙ ሃይማኖቶች የአምልኮ ሥርዓቱን የሚመሩት ካህናት ናቸው። በብሉይ ኪዳን ለክህነት ሥራ የተለዩት የአሮን ልጆች ናቸው።

7ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ካህናት ያላቸውን የተለያዩ ሃይማኖቶችን በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ካህናት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚለዩት እንዴት ነው?

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፥ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፥ ሂንዱዎች ወዘተ... የአምልኮ ሥርዓታቸውን የሚመሩላቸው ካህናት አሏቸው። አንዳንድ ሰዎች ካህንነታቸውን ለየት ካሉ የቤተሰብ ወገኖች ጋር ያያይዙታል። ሌሎች ደግሞ ካህን ለመሆን ለትምህርቱና ለሥልጠናው ቅድሚያ ይሰጣሉ። ሆኖም ካህናት ከሌላው ሕዝብ ይለያሉ፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከልም ያሉ ናቸው። ማለትም አማላጆች ናቸው።

8ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 5፡1-4 አንብብ።

ሀ) አንድ ሰው ሊቀ ካህን ለመሆን ማሟላት ያለበት ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

ለ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ማሟላት ካለበት ነገሮች ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ እስካሁን ሦስት ጊዜ ለኢየሱስ «ሊቀ ካህን» የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፤ (2፡17፥ 3፡1፥ 4፡15)። ነገር ግን ይህ ለአይሁዳውያን ትልቅ ችግር ፈጥሯል። በብሉይ ኪዳን ከሌዊ ወገን ሆነው በአሮን የዘር ግንድ ውስጥ ያሉ ሰዎች ብቻ ነበሩ ካህናት ሊሆኑ የሚችሉት። ኢየሱስ ግን ከዳዊት የዘር ግንድ ውስጥ ያለ ከይሁዳ ወገን የነበረ ሰው ነው። ታዲያ እንዴት ሊቀ ካህን ሊሆን ይችላል? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ጸሐፊው አንድ ሰው ሊቀ ካህን ለመሆን የሚያስፈልጉትን ሁለት ዋና ዋና መመዘኛዎች አስቀድሞ ይገልጻል።

1. ሊቀ ካህኑ ሰው መሆን አለበት። የሊቀ ካህኑ ዋና ሐላፊነት ሰዎችን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ስለሆነ እራሱ ሰው መሆን አለበት። ለዚህም ነው

የእሥራኤል ሕዝብ ሊቀ ካህን በመሆን እስራኤላዊው አሮን የተመረጠው። የሊቀ ካህኑ ሥራ መንፈሳዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ሕዝቡን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ነው። በብሉይ ኪዳን ይህ በተለይ መሥዋዕትና መባን ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነው።

9ኛ ጥያቄ፡- በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይሠዉ የነበሩት አምስት የተለያዩ የመሥዋዕት ዓይነቶች በዝርዝር ጻፍ! (ትምህርት ሦስትና አራት)።

«መባ» የሚለው ስያሜ በፈቃደኝነት የሚሰጡትን መሥዋዕቶች (የደኅንነቱን መሥዋዕትና የእህሉን ቁርባን) ሲያመለክት፥ የኃጢአቱ መሥዋዕት ደግሞ የደም መሥዋዕቶቹን የሚቃጠለው፥ የኃጢአትና የበደል መሥዋዕቶችን ያመለክታል።

ሊቀ ካህኑ ሰው በመሆኑ ለኃጢአት የተጋለጠ ነው። ስለዚህም አንድ ኃጢአተኛ ወደ እርሱ ሲቀርብ የመናደድና የመበሳጨት ሥልጣን አልነበረውም። በየዓመቱ ሊቀ ካህኑን ኃጢአተኛ መሆኑን የሚያስታውሰው ነገር ነበር። «በስርየት ቀን» ለሕዝቡ የኃጢአት መሥዋዕት ከማቅረቡ በፊት ሊቀ ካህኑ ለእርሱ የኃጢአት መሥዋዕት ያቀርብ እንደነበር ታስታውሳለህ። እርሱም ኃጢአተኛ በመሆኑ በእርሱ በኩል ከእግዚአብሔር ይቅርታ ለማግኘት የሚመጣውን ሰው በትሕትና መቀበል ነበረበት። ሊቀ ካህኑም በተሰበረ መንፈስ (በርኅራኄ) ማገልገል ነበረበት። ሊቀ ካህኑ የተፈጸሙትን ኃጢአቶች በቸልተኝነት መመልከትም የለበትም፤ ሆኖም ኃጢአተኞችን ማመናጨቅና መጨቆን የለበትም። ካለማወቅ የተነሣ የሚደረጉ ኃጢአቶች በዝርዝር ተገልጸዋል፥ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ውስጥ ይቅርታ የሚያገኙት ኃጢአቶች ከሰው ድካም የተነሣ ሊፈጸሙ የሚችሉ ኃጢአቶች ብቻ ናቸው። በእመጸኛነት ተነሣሥቶ ለሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ምንም ዓይነት መሥዋዕት የለም፤ (አሪት ዘኍልቁ 15፡28)።

2. የእሥራኤል ሕዝብ ሊቀ ካህን የሚመረጠው በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ወይም እራሱ እራሱን አይሾምም ነበር። ለምሳሌ በእሥራኤላውያን ላይ ሊቀ ካህን ሆኖ እንዲሠራ አሮንን የሾመው እግዚአብሔር ነበር እንጂ በእሥራኤላውያን ምርጫ አይደለም።

በነገው ቀን ጸሐፊው ኢየሱስ እነዚህን ሁለት ነገሮች እንዴት እንዳሟላ የሚጠቅስበትን ክፍል እንመለከታለን። ይህም ቢሆን እነዚህ ሁለት መመሪያዎች ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ጥምር ተግባራዊነት አላቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሌሎች የቤተክርስቲያን ምዕመናን ጋር እኩል እንደሆኑ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ለትዕቢት ምንም ቦታ የለውም። ልክ እንደምዕመናኖቹ እነርሱም ኃጢአተኞች ናቸው። አባሎቻቸውን በማመናጨቅና በመጨቆን ከሚፈርዱባቸው ይልቅ (በቸርነትና በርኅራኄ) ሊመሯቸው ይገባል። ምንም እንኳን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ኃጢአት ሳይገለጽ ዝም ብሎ እንዲቀር ለማድረግ ባይችሉም ኃጢአት ለሠራው ሰው ርኅራኄን ማሳየት የለባቸውም።

10ኛ ጥያቄ:- ሀ) እላይ በጠቀስነው አኳኋን የሚመሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለምሳሌ ያህል ጥቀስ። የእነርሱ አገልግሎት ለሌሎች ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው?

ለ) ይህንን የማይከተሉና አባሉቻቸውን በማመናጨቅና በመጨቆን የሚመሩ መሪዎችን ለምሳሌ ያህል ጥቀስ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልክ እንደ ካህናት ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ጥሪ ያስፈልጋቸዋል። ሰዎች ለክብሩ ለትልቅነቱ ወይም ለገንዘብ ሲሉ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን ቢፈልጉ ስሕተተኞች ናቸው። የእግዚአብሔር ጥሪ በልባቸው ካልተሰማቸው እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ሕዝቡን አይመሩትም።

11ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች የእግዚአብሔርን ልዩ ጥሪ ተቀብለናል ብለው ስለሚያስቡ ነው የሚመሩት?

ለ) የእግዚአብሔር ጥሪ ተሰምቷቸው በሚመሩ መሪዎችና ለገንዘብ፥ ለክብር ሲሉ ወይም ሰው ስለ መረጣቸው በሚመሩ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት ምን ዓይነት ነው?

12ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘጸአት 19:5-6 እና 1ኛጴጥ.2:5 አንብብ።

ሀ) እስራኤል የተሰጣት ስያሜ ምንድን ነው?

ለ) ክርስቲያኖች የተሰጣቸው ስያሜ ምንድን ነው?

ሐ) በምን ዓይነት መንገድ ነው መጠራታቸውን ማሟላት ያለባቸው?

ክርስቲያኖችም እሥራኤላውያንም የእግዚአብሔር ካህናት መባላቸውን ማስተዋሉ በጣም ይጠቅማል። እሥራኤላውያን ለአሕዛብ ካህናት በመሆን እነርሱን ወደ እግዚአብሔር ለማምጣት መጣር ነበረባቸው። ልክ እንደዚሁ እኛም ለማያምኑ ካህናት በመሆን እነርሱን ወደ እግዚአብሔር ለማምጣት መጣር ይኖርብናል።

ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝ ትልቅ እውነታን ያነሣል። የመጨረሻውን መሥዋዕት ያቀረበ ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑና ሁሉም ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ካህናት በመሆናቸው ካሁን ወዲያ የተለዩ የሰው ካህናት ያስፈልጉናልን? መልሱ አያስፈልጉንም ነው።

13ኛ ጥያቄ:- ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ሃይማኖቶች ውስጥ በካህናት የሚጠቀሙትን የተለያዩ ሃይማኖቶች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ለምንድን ነው ካህናት የሚል ስያሜ የተሰጣቸው?

ሐ) ሥራቸው ምንድን ነው?

ሰዎችን ለይቶ ካህናት የሚል ስያሜ መስጠቱ በጣም አደገኛ ነው። በመጀመሪያ: የእኛ አማላጅና ሊቀ ካህን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። በኢየሱስ በኩል ሳይሆን በሌላ ሰው በኩል ወደ እግዚአብሔር ለመሄድ ካሰብን በድርጊታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት በቂ አይደለም ማለታችን ነው። ሁለተኛ፤ ክርስቲያኖች በሙሉ ወደ

እግዚአብሔር የመቅረብ እኩል መብት አላቸው ከማለት በክርስቲያኖች መካከል ደረጃዎችን እንፈጥራለን፤ ደረጃዎቹም ለየት ያለ ጥሪ ያላቸው ካህናትና ተራው ምዕመን ናቸው። በጌታ መስቀል አካባቢ ግን ሁሉም እኩል ናቸው። ማንም ከማንም አይበልጥም። ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን፥ እንደዚያም ሆኖ ግን ሁላችንም ካህናት ነን። ልንመልሰው የሚገባን የክህነት ጥሪያችንን እየፈጸምነው ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ነው።

## ሦስተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 5፡5-10

በተደጋጋሚ የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊቀ ካህን እንደሆነ ይጠቅሳል። ሆኖም የአይሁድ ክርስቲያኖች ካህን የሚሆነው የአሮን ዘር እንደሆነ ስለሚያውቁ ይህንን በተመለከተ ጥያቄ ነበራቸው። ስለዚህም ጸሐፊው በዚህ ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ሊቀ ካህን እንደሆነና ነገር ግን ከአሮን ወገን እንዳልሆነ ያሳያል። በትናንትናው ዕለት አንድ ሰው ሊቀ ካህን ለመሆን ሁለት ነገሮችን ማሟላት እንዳለበት ተመልክተናል። አንደኛ፡ በእግዚአብሔር ፊት ለሚያቀርባቸው ሰዎች የሚራራ እንዲሆን ሲባል እራሱ ሰው መሆን ነበረበት። ሁለተኛ፡ ሊቀ ካህን እንዲሆን በእግዚአብሔር የተመረጠ መሆን ነበረበት።

14ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 5፡5-10 አንብብ።

> ሀ) ጸሐፊው የኢየሱስ ሊቀ ካህንነት ከእግዚአብሔር መሆኑን ያሳየው እንዴት ነው?
>
> ለ) ኢየሱስ ሰው እንደሆነና የሌሎች ሰዎች የሃዘናቸው ተካፋይ እንደሆነ ያሳየው እንዴት ነው?

ጸሐፊው የሚጀምረው የኢየሱስን ሊቀ ካህንነት መመረጥ በመጥቀስ ነው፤ (ከቁጥር 5-6)። ይህንንም የሚያሳየው በብሉይ ኪዳን የሚገኙ ሁለት ጥቅሶችን በመጥቀስ ነው። በመጀመሪያ መዝሙረ ዳዊት (2)፡7 ይጠቅሳል። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ይህ ጥቅስ ከሙታን የተነሣው መሢሕ መሆኑን የሚያሳየውን የእግዚአብሔርን ድንጋጌ ለማሳየት ተጠቅመንበታል፤ (የሐዋ.2፡36)። እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሢሕና ሊቀ ካህን እንዲሆን በእግዚአብሔር ተመርጧል፤ (ቁጥር 10)።

ሁለተኛ፡ ጸሐፊው የሚጠቅሰው መዝሙረ ዳዊት (110)፡4 ነው። በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው የሚያሳየው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮን ወገን ሳይሆን ከመልከ ጼዴቅ እንደሆነ ነው። ጸሐፊው ይህንን እውነታ በዚህ ሥፍራ ጠቅሶ ያልፈዋል። በምዕራፍ 7 ላይ ግን ያብራራዋል። የኢየሱስ ሊቀ ካህንነት ጊዜያዊ መሆኑ ቀርቶ ዘላለማዊ ነው።

ጸሐፊው እነዚህን ሁለት ጥቅሶች አብሮ በማስቀመጥ ከዚህ በፊት የአይሁድ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰምተውት የማያውቁትን ያሳያቸዋል። በብሉይ ኪዳን ሁለት የተለያዩ መሪዎች ነበሩ። አንደኛው የእሥራኤል መንግሥት ፖለቲካዊ

ንጉሥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእሥራኤል ሕዝብ መንፈሳዊ መሪ የሆነው ሊቀ ካህን ነው። እነዚህ መሪዎች በጣም ኃያል እንዳይሆኑ ሁለቱም ተለያይተው ነበር የሚቀመጡት። በዚህም ምክንያት ብዙ አይሁዳውያን በመጨረሻዎቹ ዘመናት በእሥራኤል ሁለት የተለያዩ ገዢዎች ይኖራሉ ብለው ያስቡ ነበር። መሚሑ በመንግሥታት ላይ የፖለቲካ ገዢ ይሆናል። ሆኖም ሕዝቡን በመንፈሳዊ ነገሮች የሚመራ የተለየ ሊቀ ካህን ይኖራል። የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ንጉሥ ብቻ መሆኑን ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕዝብም መንፈሳዊ መሪ እንደሆነ ነው የሚያሳየው። መንግሥተ ሰማያት ውስጥ ንጉሥና ሊቀ ካህን ሆኖ ይኖራል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅና ዘላለማዊው ሊቀ ካህን በመሆኑ ለሞት ከተዳረገውና ሰው ብቻ ከሆነው ከአሮን ይበልጣል።

ኢየሱስ ለሊቀ ካህንነት በእግዚአብሔር መመረጡ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ሰው በመሆኑም የሰዎችን ድካመት ያውቃል፤ ድካመታችንንም በደንብ ይረዳልናል፤ (ከቁጥር 7-10)። የኢየሱስ ምድራዊ ኑሮ የሥጋው ወራት በመባል ነው የሚታወቀው። ሀሥጋሀ የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ የኃጢአት ተፈጥሮን የሚገልጽ ሳይሆን ከትንሣኤው በፊት የነበረውን ምድራዊ ኑሮውን የሚገልጽ ነው።

ኢየሱስ ከሰዎች ጋር አንድ መሆኑን ለመግለጽ ጸሐፊው ኢየሱስ በጌተሰማኒ ያሳለፈውን ጊዜ ለትውስታ በመጥቀስ ለክርስቲያኖቹ ይነግራቸዋል።

15ኛ ጥያቄ፡- ማቴዎስ 26፡36-46 አንብብ።

> ሀ) በጌተሰማኒ ያሳለፈውን ሰቆቃ ኢየሱስ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው የሚገልጸው? (ቁጥር 38)።
>
> ለ) ለአባቱ ያቀረበው ምልጃ ምን ነበር?
>
> ሐ) ለአባቱ ያለውን ታዛዥነትና አክብሮት በምልጃው አስታኮ የገለጸው እንዴት ነው?

ምንም እንኳ በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ ብዙ በጸሎት እንባውን ያፈሰሰባቸው ጊዜያት ሊኖሩ ቢችሉም ከሁሉም በላይ አሳሳቢና አስቸኳይ የነበረው ታልፎ የተሰጠበት ምሽት ነበር፤ ማለትም ሊሰቀል አንድ ቀን ሲቀረው በዚያ በጌተሰማኒ ኢየሱስ በጣም ተጨነቀ፥ የዕብራውያንም መጽሐፍ « ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን አቀረበ» ይላል። የእግዚአብሔር ቁጣ ከብዶት ነበር። ሰውም የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመሆኑ የዓለምን ኃጢአት ሁሉ የመሸከሙን፥ የአባቱን ቁጣ የመቀበሉንና ከአባቱ የመለየቱን እውነታ ሲያጤነው በጣም ተሸበረ። እኛ በፈተና ጊዜ ያለንን ዓይነት ችግር ነው ኢየሱስ ያሳለፈው። የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል በእኛ ላይ ተጨማሪ ችግር እንደሚያመጣብን ሁሉ በኢየሱስም ላይ አምጥቶበታል። ኢየሱስ የመከራን ገፈት ተቀብሎ እንደ ማንኛውም ሰው ሞቷል።

ጸሐፊው ኢየሱስ ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸለየ፤ ጸሎቱም ተሰማለት ይላል። ምንም እንኳ ሰዎች ይህን ጥቅስ በተመለከተ የተለያየ ግንዛቤ ቢኖራቸውም

የተሰማለት የጸሎቱ ክፍል መስቀሉን የማስቀረቱ ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር እርሱን ከሙታን የማስነሣቱ እውነታ ነው። ሰው እንደመሆኑ ኢየሱስ እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን ፅዋ ለመጠጣት የሚያስችላቸውን ዕርዳታ ለማግኘት ሲል በጸሎት ወደ አብ መቅረብ ነበረበት።

ኢየሱስ በሚፈተንበትና በሚሰቃይበት ወቅት ሁለት ነገሮች ተፈጽመዋል።

1. ኢየሱስ በመከራ ውስጥ በማለፍ ታዛዥነት ተምሯል። ይህን ስንል ለአብ ታዛዥ ያልነበረበት ጊዜ ባይኖርም እግዚአብሔርን መታዘዝ ወደ ትልቅ መከራና ወደ ሞትም ሊመራ እንደሚችል ተምሯል ማለታችን ነው። ታዛዥነቱ ወደ መስቀሉ እስከመራው ጊዜ ድረስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሲል የተቀበለው መከራ አልነበረም። ስለዚህም የአይሁድ ክርስቲያኖችን ያጋጠማቸው ዓይነት መከራ ነው የተቀበለው።

2. ኢየሱስ ፍጹም ሆነ። ይህም ከዚህ በፊት ኃጢአተኛ ነበር ማለት አይደለም። በምትኩ ግን ሊቀ ካህን እንዲሆን ሊያልፍባቸው የሚገቡትን መንገዶች (ለምሳሌ፤ መንፈሳዊ፥ ስሜታዊና፥ ሥጋዊ፥ የሆኑ መከራዎች) በማለፉ የእኛ ሊቀ ካህን ለመሆን ብቁ ሆኗል ማለት ነው።

የታላቁ ሊቀ ካህን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ሞትና ትንሣኤ ውጤት «የዘላለም መዳን» መሆን ነው። በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህኑ ለሕዝቡና ለእራሱ ኃጢአት መሥዋዕቱን በተደጋጋሚ ነበር የሚያቀርበው፤ ኢየሱስ ግን ለኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ እራሱን ያቀረበው አንዴ ነው። በመሥዋዕቱና በአብ ቀኝ የተቀመጠው ዘላለማዊ ሊቀ ካህን በመሆኑ ለሚያምኑበት ሁሉ የዘላለም መዳን ምንጭ ሆነላቸው። ይህን ነገር በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ላይ ሠፋ ባለ ሁኔታ እንመለከተዋለን።

16ኛ ጥያቄ፡- እነዚህ ስለ ኢየሱስ የሚነገሩ እውነታዎች በስደት ያሉ ክርስቲያኖች እምነታቸውን እንዳይክዱ ሊያበረታቷቸው የሚችሉት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ነገር ግን ይህ ታላቅ የዘላለም መዳን የሚሰጠው «ለሚታዘዙለት ሁሉ» ብቻ መሆኑን ማስተዋል አለብን። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉም ሰው መሞቱ እውነት ቢሆንም ከዚህ ደኅንነት ከሚገኘው መልካም ነገር ተጠቃሚ የሚሆኑት እነዚያ በኢየሱስ የሚያምኑ ብቻ ናቸው። ክርስቲያን ነን ብለው የሚሉ ሰዎች በሙሉ አይድኑም። ለደኅንነት የሚያበቃ እውነተኛ እምነት ያላቸው እነዚያ ኢየሱስን በመታዘዝ እምነታቸውን የሚገልጹ ናቸው።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ኢየሱስ ልንከተላቸው የሚገቡንን የሚከተሉትን ምሳሌዎች ትቶልናል።

(1) በመከራዎች ውስጥ በማለፉ ምክንያት እንዳደገ ሁሉ እግዚአብሔር ክርስቲያኖች እንዲያድጉ ሲል የሚጠቀምበት ዋነኛው መሣሪያ መከራ ነው፤ (ያዕቆብ 1፡2-4፥ ሮሜ 5፡3-5)። በኢየሱስ ያለንን እምነት እውነተኛነት የምናሳየው ብዙውን

ጊዜ በመከራ ጊዜ ነው። በበረከትና በነፃነት ጊዜ ማመኑ በጣም ቀላል ነው። በመከራና በስደት ጊዜ ግን በታማኝነት ጸንቶ መቆሙ ከባድ ነው።

(2) ኢየሱስ ፈቃዱን ለአብ አስገዝቶ እንደታዘዘ ሁሉ ክርስቲያኖችም ፈቃዳቸውን ለአብ አስገዝተው እርሱን የመታዘዝ ሐላፊነት አለባቸው።

(3) በመከራው ጊዜ ኢየሱስ በእራሱ ኃይል እንዳልተማመነ ሁሉ ክርስቲያኖችም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መጣራት አለባቸው። በእግዚአብሔር መታመን ሕይወቱን ለእርሱ መስጠትና ቢሞትም እንኳ ከሞት ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል።

17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰዎች በኢየሱስ ያላቸውን እምነት የሚተዉበት የተለያዩ ምክንያቶች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) በመቀጠልም ክርስቲያኖች የኢየሱስን ምድራዊ ሕይወት እንደ ምሳሌ በመጠቀም በስደት ውስጥ እንዴት ጸንተው ሊቆሙና ለእግዚአብሔር ታማኝ ሊሆኑ እንደሚችሉ በዝርዝር ጻፍ።

በስደት ውስጥ በምናልፍበት ወቅት አንዱ በጣም ሊያበረታታን የሚችለው ነገር እኛ የምናልፍበትን መከራ አስቸጋሪነት የሚረዳልን በመንግሥተ ሰማያት ያለ ሊቀ ካህን መኖሩን መገንዘባችን ነው። መረዳት ብቻ ሳይሆን በችግራችን ውስጥ ኃይልና ጽናትን በመስጠት ሊረዳንም ይችላል። እምነታችንን ከመተው ዐይናችንን እርሱ ላይ ካደረግን እምነታችን ይጠነክራል! በመጨረሻም ልክ እንደ እርሱ እንከብራለን።

# አራተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 5፡11-14

አንዱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ችግር መንፈሳዊ ሕፃንነት ነው። የዳንነው ዘላለማዊውን ፍርድ ለማምለጥ ብቻ ሳይሆን በሕይወታችን ኢየሱስን እስክንመስል ድረስ ለማደግም ነው። ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች ከዳኑበት ጊዜ አንሥቶ እስከሚሞቱበት ጊዜ ድረስ አያድጉም። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው ግንዛቤ ሥር እየሰደደ አይሄድም። በዚህም ምክንያት ለእርሱ ያላቸው አገልግሎት ደካማ ነው። ብዙ ጊዜም የስደት ፍንጭ ሲታይ ቶሎ ብለው እምነታቸውን ይተዋሉ። ወይም ደግሞ በቀላሉ በሐሰተኛ ትምህርት ይወሰዳሉ። የአንድ ቤተ ክርስቲያን ኃይል የሚወሰነው በመሪዎች ዕድገት ላይ ብቻ ሳይሆን በአባሎቹም ዕድገት ላይም ነው።

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ የሚገኙት ክርስቲያኖች አብዛኞቹ በእምነታቸው ሕፃናት ናቸው ወይስ ጎልማሶች?

ለ) ጎልማሳ የሆነ ክርስቲያን የሚያሳያቸው አንዳንድ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

ሐ) ሕፃን የሆነ ክርስቲያንስ የሚያሳያቸው አንዳንድ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት በመልከ ጼዴቅ ሹመት ላይ እንዴት እንደተመሠረተ ከመግለጽ ፊንታ ጸሐፊው ክርስቲያኖቹ በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት እንዳይተዉ እንደገና ከበድ ያለ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ዕብራውያን 5፡11-6፡20 ለክርስቲያኖች የተሰጠውን ሦስተኛውንና ከባዱን ማስጠንቀቂያ ያካተተ ነው። በዕብራውያን ምዕራፍ 7 ላይ ደግሞ ጸሐፊው የኢየሱስን ሊቀ ካህንነት በተመለከተ ወደሚያስተምረው ትምህርቱ ይመለሳል።

19ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 5፡11-6፡20 አንብብ።

ሀ) በዚሁ ክፍል ለክርስቲያኖች የተሰጡት ዋና ዋና ማስጠንቀቂያዎች ምን ምንድን ናቸው?

20ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 5፡11-14 እንደገና አንብብ።

ሀ) በዚህ ክፍል እንደሚታየው ሕፃን የሆነ ክርስቲያን ያለው አንዱ ባህርይ ምንድን ነው?

ለ) ጎልማሳ የሆነ ክርስቲያን ያለው አንዱ ባህርይስ ምንድን ነው?

ምንም እንኳ የአይሁድ ክርስቲያኖች ለብዙ ዓመታት ክርስቲያኖች ቢሆኑም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች የነበራቸው እውቀት ውስን ነበር። በመንፈስ ሕጻናት ነበሩ። ጸሐፊውም የኢየሱስን ሊቀ ካህንነት በሠፊው ለማስረዳት ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ክርስቲያኖቹ ስለ እግዚአብሔር ቃል የነበራቸው እውቀት ውስን በመሆኑ ገለጻው ከብዶት ነበር። እነዚህ ሕፃን ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ቃል ያላቸውን ግንዛቤ አላሠፉትም ነበር። በዚህም ምክንያት ባመኑበት ወቅት የተቀበሏቸውን መሠረታዊ ትምህርቶች ነው ሊረሱ የሚችሉት።

21ኛ ጥያቄ፡- ይህን ዓይነቱ ችግር በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እንደሚታይ አብራራ።

አዳዲስ ክርስቲያኖችን አሁን ከተወለዱ ሕፃናት ጋር ነው የምናነፃፅረው። ሕፃናቱ ለማደግ ወተት እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ አዳዲሶቹም ክርስቲያኖች መሠረታዊ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነታዎች ማጥናት ይኖርባቸዋል። ልጆች ሲያድጉ ሥጋ መብላት እንደሚለማመዱ ሁሉ ክርስቲያኖችም በእምነታቸው እያደጉ ሲመጡ ጥልቅ የሆኑትን እውነታዎች መረዳትና መጠበቅ መማር ይኖርባቸዋል። ጸሐፊው መሠረታዊ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነታዎች አንድ ትንሽ ልጅ ትምህርት ቤት ሲገባ ከሚማራቸው የመጀመሪያዎቹ ትምህርቶች ጋር ያነፃፅረዋል። አንድ ልጅ ፊደል ብቻ አጥንቶ በትምህርቱ ካልገፋበት የተማረው ነገር ምንም አይጠቅመውም። ልክ እንደዚሁ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚገኙትን መሠረታዊ የሆኑ እውነታዎችን ብቻ አጥንተው ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን ዕውቀትና ታዛዥነትን የማያጎለምሱ ከሆነ ለእግዚአብሔር የማይጠቅሙ ደካማ ሰዎች ናቸው።

22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አዲስ ለሆኑ ክርስቲያኖች የሚያስፈልጉትን አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ እውነታዎችን በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ክርስቲያኖች በእምነታቸው ካደጉ በኋላ የሚያስፈልጓቸውን አንዳንድ ዋና ዋና የሆኑ እውነታዎችን ዘርዝረህ ጻፍ።

አንዱ ጎልማሳ የሆነውን ክርስቲያን ሕፃን ከሆነው የሚለየው አንዱ ዘዴ ጥሩውን ከክፉ ከሆነው የመለየት ችሎታው ነው። ይህ ቀላል አይደለም። ዓለም ጥሩ የሚመስሉ ነገሮችን ታስተምራለች። ግን እነዚህ ነገሮች ክፉ ናቸው። ጎልማሳ የሆነው ክርስቲያን የእግዚአብሔርን እውነታ ያለማቋረጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያጠና በማያዳላ ሁኔታ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ጠቃሚ የሆነውን ነገር መጥፎና ክፉ ከሆነ ነገር መለየት ይችላል። አስተውል! ይህ ብዙ ልምድ የሚጠይቅ ነገር ነው። ይህ ልምድ የሚመጣው «የጽድቅን ቃል» ወይም ጠንካራውን ምግብ ከማወቅና ከመገንዘብ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት የሆነውን ነገር ብቻ አይደለም የሚያስተምረን ክፋት በሞላበት ዓለም ውስጥ እንዴት አድርገን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ልንኖር እንደምንችልም ጭምር ነው የሚያስተምረን። መንፈሳዊ ጎልማሳነት የሚታየው ለክርስትና ሕይወት ዕድገት እንቅፋት የሆኑትንና ያልሆኑትን ነገሮች ጠንቅቆ መረዳቱ ላይ ነው።

23ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዓለም የምታስተምራቸው ጥሩ የሆኑ ነገሮች ሆነው ለክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ዕንቅፋት የሆኑ አንዳንድ ነገሮችን በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ቤተ ክርስቲያን አባሎችዋን እንዴት አድርጋ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንዲያድጉና እነዚህን ጎጂ የሆኑትን ነገሮች እንዲያጤኑ ለማድረግ የምትጠቀምባቸውን አንዳንድ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ሕፃናት ነን ወይስ ጎልማሶች? የእግዚአብሔርን ቃል በተግባር ላይ በማዋል የዓለምን ነገሮች በመመርመርና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ነገር በመምረጥ ጎልማሳነታችንን ልንገልጽ ይገባናል። እግዚአብሔር አሁን ባለንበት የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ እንዳንረካ ነገር ግን ሁልጊዜ የማደግ ፍላጎትን በውስጣችን ያድርግልን! (ኤፌሶን 1፡16-19)።

# ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) 1. ኢየሱስ ሰው በመሆን የተማራቸውን የተለያዩ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ። (2፡9-18፤ 4፡14-16፤ 5፡7-10)

2. በመንግሥተ ሰማያት የሚኖር ይህን የመሰለ ሊቀ ካህን ስላለን የምናገኛቸውን ጥቅሞች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) 1. የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከካህናት ጋር አነፃፅራቸው። እንዴት ነው የሚለያዩት?

2. እንዴትስ ነው የሚመሳሰሉት?

3. ለምንድን ነው አንዳንድ ክርስቲያኖች በአምልኮ ሥርዓታቸው ውስጥ ምድራዊ በሆኑ ካህናት የሚጠቀሙት?

4. ለምንድን ነው ይህ አደገኛ የሚሆነው?

ሐ) 1. መከራ መታዘዝን ሊያስተምረን የሚችለው እንዴት ነው? አሳድገንስ እንዴት ነው?

መ) 1. የቤተ ክርስቲያንህ መንፈሳዊ ደረጃ በተመለከተ ተወያዩ። በጎለመሰ ደረጃ ላይ ነው ያለው ወይስ ገና እንጭጭ ደረጃ ላይ ነው?

2. የጎልማሳነቱ ወይም የእንጭጭነቱ ደረጃ በምን መልክ ነው የሚታየው?

3. አባላቷ የበለጠ እንዲያድጉና እንዲጎለምሱ ለማድረግ ቤተ ክርስቲያንህ ልታደርገው የምትችለው ነገር ምንድን ነው?

4. አዳዲስ ክርስቲያኖችን ልናስተምራቸው የሚገባን መሠረታዊ የሆኑ እውነታዎች ምን ምንድን ናቸው?

5. ከበድ ያሉ እውነታዎች ሆነው ጎልመስ ያሉት ክርስቲያኖች ሊያጤኑዋቸው የሚገባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ ሦስት

ዕብራውያን ምዕራፍ 6

## የመጀመሪያ ቀን:- ዕብራውያን 6:1-3

ባለፈው ሳምንት ኢየሱስ የእኛ ሊቀ ካህን ለመሆን ብቁ ያደረጉትን መመዘኛዎችን አጥንተናል። በእግዚአብሔር የተመረጠ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ሰው በመሆኑም ጭምር የእኛ መፈተንና መቸገር ግድ እንደሚለው ተመልክተናል።

በተጨማሪም ሦስተኛው ማስጠንቀቂያ የሚጀምርበትን ዕብራውያን 5:11-6:20ን ማጥናት ጀምረን ነበር። በዕብራውያን 5:11-14 ክርስቲያኖቹ አሁንም ገና ሕፃናት በመሆናቸው ምክንያት ጸሐፊው ሲገስፃቸው እናያለን። አንዱ የሕፃንነት ምልክት የወንጌልን እውነታ በጥልቀት ለማወቅ ፍላጎት ማጣት ነው። ሌላው የሕፃንነት ምልክት ደግሞ ለእምነታችን ጎጂ የሆኑትን ነገሮች ካልሆኑቱ የመለየት ችሎታ አለመኖር ነው።

1ኛ ጥያቄ:- እነዚህ ሁለቱ የሕፃንነት ምልክቶች በአንተ ሕይወት ወይም በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚገለጹት እንዴት ነው?

ይህ ያለማደግ ወይም የሕፃንነት ችግር በዓለም ዙሪያ የሚታይ ችግር ነው። ምናልባትም የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ይህ የአባላቷ በእግዚአብሔር ዕውቀት ያለማደግና በሙሉ ሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ቃል ያለ መጠበቁ ነገር ነው።

2ኛ ጥያቄ:- ብዙ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ተግባራዊ የማያደርጓቸውን ጠንከር ያሉና ጥልቅ መንፈሳዊ እውነታን ያዘሉ አንዳንድ እውነታዎችን ዘርዝረህ ጻፍ።

በዛሬው ትምህርት ጸሐፊው ክርስቲያኖቹ መንፈሳዊ ሕፃንነታቸውን ወደ ኋላ ትተው በእምነታቸው እንዲያድጉ ያበረታታቸዋል። የክርስትናን መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ በማለትም ይቀሰቅሳቸዋል። መንፈሳዊ እድገታችን ሲቆም ወዲያውኑ መንፈሳዊ በድንነት ሥር ይሰዳል። ስለዚህም ክርስቲያኖቹ ለመንፈሳዊ ዕድገታቸው ዕንቅፋት ሊሆን የሚችለውን በማስወገድ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲጎለምሱ ማንኛውንም ዓይነት ጥረት እንዲያደርጉ ታዝዘዋል።

3ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 6:1-20 አንብብ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙትን ዋነኞቹን ዕውነታዎች ዘርዝረህ ጻፍ።

4ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 6:1-3 አንብብ።

ሀ) የስድስቱን መሠረታዊ ትምህርቶች ስም በዝርዝር ጻፍ።

ለ) እያንዳንዱ ምን ማለት እንደሆነ በማብራራት በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት እንደምታስተምሯቸው ግለጽ።

ባለፈው ሳምንት አንድ ሰው ክርስቲያን ለመሆን ማወቅ የሚገባው መሠረታዊ ትምህርቶች እንዳሉ ተመልክተናል፤ ሆኖም ከእነዚህ ትምህርቶች በላይ ግንዛቤውን ማዳበር ይኖርበታል። በዕብራውያን 5:12 ላይ እነዚህን ትምህርቶች ጸሐፊው «መሠረታዊ የእግዚአብሔር እውነታዎች» ብሎአቸዋል አሁን ደግሞ «ስለ ክርስቶስ መሠረታዊ ትምህርቶች» የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል።

በዕብራውያን 6:1-3 ላይ ጸሐፊው እንደ መሠረታዊ ትምህርት የሚቆጥራቸው ስድስት የተለያዩ ትምህርቶች አሉ። እነዚህን ስድስት ትምህርቶችን በተመለከተ የሚያስደንቀው ነገር ከአይሁዳውያን መሠረታዊ ትምህርቶች ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸው ነው። ክርስትና ነክ የሆነ ባህርይ የላቸውም። ነገር ግን የጥንት ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን እውነታ ላይ በመመሥረትና በእነዚህ በአይሁዳውያን ልማዶችና ትምህርቶች በመጠቀም የክርስቶስን ትምህርት በተመለከተ ተጨማሪ ትርጓሜ ሰጥተውባቸዋል። እነዚህም ትምህርቶች ለአዳዲስ ክርስቲያኖች መሠረታዊ ለሆኑ ትምህርቶች መሠረት የጣሉ ናቸው።

1. ወደ ሞት ከሚመራው ሥራ ንስሐ መግባት፤ የአንድ አማኝ ለወንጌል የሚሰጠው የመጀመሪያ ምላሽ ንስሐ ነው። ለመዳን በግሉ ምንም ዓይነት ጥረት ቢያደርግ ደኅንነት ማግኘት እንደማይችል ሊረዳ ይገባዋል። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ቁጣ በላዩ ላይ ሊያስከትሉበት ለሚችሉት ለማንኛውም ዓይነት ልማዶች ጀርባውን መስጠት ይኖርበታል። ንስሐ መግባት ይቅርታን መጠየቅ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን አንድ ሰው የድሮውን የአኗኗር ዘይቤውን ቀይሮ እግዚአብሔርን የሚያስከብር አዲስና የተቀደሰ ሕይወት መኖር ማለት ነው።

አንዳንድ ምሁራን እነዚህን ሥራዎች ሰው በመልካም ሥራው ደኅንነቱን የሚያገኝባቸው ጥረቶች አድርገው ይቆጥሯቸዋል።

5ኛ ጥያቄ፡- ኃጢአተኛው ወደ እግዚአብሔር መጥቶ ለመዳን ሲፈልግ ወደ ሞት የሚመሩት ሥራዎች ትቶ ንስሐ መግባት አለበት። እስቲ ከእነዚህ ሥራዎች መካከል አንዳንዶቹን ግለጽ።

6ኛ ጥያቄ፡- ኤፌሶን 2፡8-9 ተመልከት።

ሀ) ይህ ጥቅስ አያድነንም የሚለው ምኑን ነው?

ለ) ይህ ጥቅስ አንድ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ አለበት ነው የሚለው?

2. እምነት በእግዚአብሔር፤ የዳንነው በእግዚአብሔር ፀጋ ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደኅንነትን በነፃ ከፍት አድርጎልናል። ሆኖም ደኅንነቱ በሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን እያንዳንዳችን በእምነት ልንቀበለው ይገባናል። የደኅንነት ጠንሳሽ በሆነው በእግዚአብሔር ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል። በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራውንም ሥራ ማመን አለብን።

እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ትምህርቶች የኃጢአተኛውን የመጀመሪያ ደኅንነት የሚመለከቱ ናቸው። በቤተ ክርስቲያናችን የምንሰብከው ንስሐ የመግባትንና በክርስቶስ የማመንን አስፈላጊነት ብቻ ከሆነ ምንም ዓይነት ዕድገት አይኖርም። ለማደግ በእነዚህ ሁለት አስፈላጊ የሆኑ ትምህርቶች ላይ መገንባት ይኖርብናል።

7ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ ስለሚሰበኩት ስብከቶች አስብ። ብዙዎቹ ንስሐንና ደኅንነትን በተመለከተ የተሰበኩ ናቸው ወይስ ክርስቲያኖች ጎልማሳ እንዲሆኑ የተሰበኩ ናቸው? አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

3. ስለ ጥምቀቶች፤ ጸሐፊው በዚህ ሥፍራ በአዲስ ኪዳን ጥምቀትን በተመለከተ ከምንጠቀምበት ለየት ያለ ቃል ነው የሚጠቀመው። በአይሁድ ሃይማኖት በመንጻት ሥርዓታቸው ጊዜ የሚጠቀሙበትን ቃል ነው የጠቀሰው። ጸሐፊው የአይሁድ ክርስቲያኖችና አይሁዳውያን ለውጫዊ የመንጻት ሥርዓት የሚከተሏቸውን ልማዶች እንዲተዉና ስለ እግዚአብሔር የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖራቸው ጥረት እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል። እነዚህ ጥምቀቶች ውኃ በመርጨት ከኃጢአት የመንጻት ልማድንና (ሕዝቅኤል 36፡24-27) ሌሎቹን የተለያዩ ጥምቀቶች የሚያመለክቱ ሊሆኑ ይችላሉ። የኢየሱስንና የመጥምቁ ዮሐንስን፤ የሐ.3፡16-22። እንደገና የጥምቀት ትምህርት

ለቤተ ክርስቲያኒቷ አስፈላጊ ነው። ሆኖም ከዚህ ጋር በማከል አዳዲሶቹን ክርስቲያኖች ጥልቅ ወደ ሆኑት እውነታዎች መምራት ይኖርብናል።

8ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለምንድን ነው የኦርቶዶክስ ካህናት አባሎቻቸውን በየዓመቱ ውኃ የሚረጩት?

ለ) ይህ ድርጊት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ነው?

4. እጆችንም ስለ መጫን በሰው ላይ እጅ መጫን በብሉይ ኪዳን ብዙ ትርጓሜ የነበረው የአይሁድ ልማድ ነው። አይሁዳውያን አንድን ሰው ለመባረክ ይጠቀሙበታል፤ (ማቴ.19፡13-15)። አንድን ሰው ለተለየ ሥራ መርጦ አንድ ቡድንን ወክሎ እንዲሠራ ለማድረግ ይጠቀሙበት ነበር፤ (የሐዋ.6፡6)። በሽተኞችንም ለመፈወስ ይጠቀሙበታል፤ (የሐዋ.28፡8)። በመጨረሻም አንዳንዴ በአዲሱ አማኝ ላይ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ለማመልከት ይጠቀሙበት ነበር።

እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ነገር አዲስ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ይህንን ነገር ማድረግ አለባችሁ ተብለን አለመታዘዛችንን ነው እግዚአብሔር በአዲሱ አማኝ ላይ መንፈስ ቅዱሱን የሚያወርደው ሲያምን ነው እንጂ እጆችን በመጫንና ለመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ አይደለም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህንን ዓይነት ነገር የተደረገው አይሁዳውያን በታሪክ ደኅንነትን ይቀበላሉ ብለው የማያስቧቸው ጎሳዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን በመጡበት ወቅት ብቻ ነው፤ (የሐዋ.8፡14-17፤ 19፡6)። እግዚአብሔር በሐዋርያቱ በኩል ይህንን ዓይነት ድርጊት ያደረገው እንደ ጥንታውያኑ የአይሁድ ደቀ መዛሙርቶች እነርሱም በቤተ ክርስቲያን እኩል ሥልጣን እንዳላቸውና ያንኑ መንፈስ ቅዱስ እንደተቀበሉ ለመግለጽ ነው። በእነዚህ ጥቅሶች በመጠቀም አንድ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስን ሊቀበል የሚችለው እጆችን በመጫን ነው ለሚለው ትምህርት እንደ ምርኩዝ ልንጠቀምባቸው አንችልም።

9ኛ ጥያቄ:- ይህ ትምህርት አንዳንድ የክርስቲያን ቡድኖች ከሚያስተምሩት ትምህርት የሚለየው እንዴት ነው?

እጆችን መጫን በተመለከተ የፈለገውን ዓይነት እምነት ቢኖረንም ጸሐፊው ወደ ጎልማሳነት የማይመራ የመጀመሪያ መሠረታዊ ትምህርት የሚል ስያሜ ሰጥቶታል። እነዚህ ትምህርቶች ተወት በማድረግም ለበለጡ እውነታዎች ቦታ መስጠት አለብን።

እነዚህ ሁለቱ የመጨረሻ ዶክትሪኖች የሚመለከቱት በቤተ ክርስቲያን አዳዲስ ክርስቲያኖች የሚደረጉትን ልማዶች ነው እንጂ ለጎለመሱ ክርስቲያኖች የሚደረጉትን ልማዶች አይደለም። መንፈሳዊ ጎልማሳነትን የሚያመለክቱ አይደሉም።

5. ስለ ሙታን ትንሣኤ፤ ለአንድ አዲስ ክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት በሚሰጡት ትምህርቶች ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ከሙታን የመነሣቱ ዕርግጠኛነት ነው። እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት ተስፋ ስለ ሰጠን ሞትን የምንፈራበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

6. ስለ ዘላለም ፍርድ፤ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ለማምጣት ከምንጠቀምባቸው ዶክትሪኖች መካከል አንድ ቀን ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ፍርድ እንደሚቀበሉ የሚገልጸው ትምህርት ነው። የማያምኑ ወደ ገሃነመ እሳት የሚያምኑና የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ደግሞ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይሄዳሉ። ከእነዚህ እውነታዎች አብሮ አዳዲስ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ምግባራቸውን ተመልክቶ ሽልማት እንደሚሰጣቸውም ሊማሩ ይገባል።

እነዚህ የመጨረሻ ሁለት ትምህርቶች ኢየሱስ ዳግመኛ ወደ ምድር የሚመጣበትን ጊዜ የሚያመለክቱ ናቸው። ነገር ግን ልክ እንደሌሎቹ ልንገነባባቸው የሚገቡን መሠረታዊ ትምህርቶች ናቸው።

ምንም እንኳ የዕብራውያን ጸሐፊ ክርስቲያኖቹ ሕፃናት መሆናቸውን ቢገነዘብም ሊያድጉ የሚችሉት ጠንካራና ጠጣር ያለውን ዶክትሪን ብቻ ሲማሩ እንደሆነ ተረድቷል። ይህንን በተረፈው የመጽሐፉ ክፍል ይፈጽመዋል። ሰዎችን መሠረታዊ የሆኑትን እውነታዎች ብቻ በመመገብ እንዲያድጉ ልንረዳቸው አንችልም። በምትኩ ግን የእግዚአብሔርን ሙሉ ፈቃድ ወይም ምክር በፊታቸው ማስቀመጥ ይኖርብናል፤ (የሐዋ. 20፡20፥ 27)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደመሆናችን በክርስቶስ ሊያጎለምሱን የሚችሉትን እውነታዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መፈለግ ይኖርብናል። በስብከታችንና በትምህርቶቻችን ውስጥ ዕቅድ በማውጣት ሁሉንም ዕውነታዎች ማስተማራችንን እርግጠኞች መሆን አለብን። እነዚያን ጥቂቶቹን መሠረታዊ ትምህርቶችን ብቻ አይደለም ማስተማር የሚገባን።

10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያንህ አዳዲስ ክርስቲያኖችን ከመሠረታዊ ትምህርቶች ወደ ጠንከር ያለው የእግዚአብሔር እውነታ እንዴት እንደምታሸጋግር በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ጠንከር ካሉት እውነታዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ምን ምን ይመስሉሃል?

## ሁለተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 6፡4-8

በዛሬው ዕለት የምናጠናው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ከባድ ክፍሎች አንዱን ነው። የዚህ ክፍል ዋነኛ ዓላማ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመናቸውን ካስመሠከሩ በኋላ እምነታቸውን ለመተው ለሚፈልጉ ሰዎች የተሰጠ ከባድ ማስጠንቀቂያ ነው።

11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኢየሱስ ላይ የነበራቸውን እምነት የተዉ የአንዳንድ የታወቁ ክርስቲያኖች ስም ዝርዝር ጻፍ።

ለ) ለምን ይመስልሃል እምነታቸውን የተዉት?

12ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 6፡4-8 አንብብ።

ሀ) እምነቱን የካደ ሰው ምን ማድረግ አይችልም ነው የሚለው ጸሐፊው?

ለ) አንድ ክርስቲያን ያለውን አምስት የተለያዩ በረከቶች በዝርዝር ጻፍ። እያንዳንዳቸውንም ግለጽ።

ሁላችንም ብንሆን በኢየሱስ የነበራቸውን እምነት የተዉ የእውቀት ሰዎችን ስም መጥቀስ እንችላለን። ታዲያ እነዚህ ሰዎች እምነታቸውን ሲተዉ አብረው ደኅንነታቸውንም ያጡ ክርስቲያኖች ናቸው ማለት ነው? ወይስ እምነታቸውን በመካዳቸው መጀመሪያውንም ቢሆን እውነተኛ የኢየሱስ አማኞች አልነበሩም ማለት ነው?

13ኛ ጥያቄ፦ ሀ) አንድ ክርስቲያን ደኅንነቱን ሊያጣ ይችላል ብለህ ታስባለህ?

ለ) ይህንን እውነታ ያስተምራሉ ብለህ የምትገምታቸውን አንዳንድ ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥቀስ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች አንድ ክርስቲያን ታላቅ ኃጢአት በመሥራቱ ወይም በኢየሱስ ላይ ያለውን እምነት በመካዱ ደኅንነቱን ያጣል ብለው ያምናሉ። ግንዛቤያቸውንም እንዲደግፍላቸው እንደ ዕብራውያን 6፡4-6 ያሉትን ዓይነት ጥቅሶች እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ። ለእነርሱ የእዚህ ጥቅስ ፍሬ ሐሳብ በጣም ቀላል ነው። ይህ ጥቅስ የደኅንነትን በረከቶች የተቀበሉ በሙሉ እምነታቸውን ከካዱ ደኅንነታቸውን ያጣሉ ይላሉ። ሆኖም እነዚህ ክርስቲያኖች አንድ ክርስቲያን እንደገና በማመን ደኅንነቱን መልሶ ሊያገኝ ይችላል ብለው ያምናሉ።

በዚህ አመለካከት ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ችግሮች አሉ። አንደኛ፤ እግዚአብሔር ልጆቹ እንዳይወድቁ ይጠብቃቸዋል ለሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተገቢውን ምላሽ አይሰጡም።

14ኛ ጥያቄ፦ እውነተኛ ክርስቲያን አይጠፉም የሚሉትን እነዚህን ጥቅሶች ተመልከት፡ ሮሜ 8፡28-39፥ ዮሐ.10፡28-30፥ ይሁዳ 24፥ ዕብራ.7፡25።

ሁለተኛ፤ እንደ ዕብራውያን ጸሐፊ ገለጻ ከሆነ በኢየሱስ የነበረውን እምነት ሙሉ በሙሉ የካደ ሰው ወደ ደኅንነት ሊመለስ አይችልም። ለእኛ ጸሐፊው ሀከወደቁ በኋላ ወደ ንስሐ መምጣት አይቻልምሀ ነው የሚለን።

ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ እውነተኛ ክርስቲያን ተመልሶ ደኅንነትን ያላገኘ ሰው ሊሆን አይችልም ብለው ያምናሉ። እነዚህ ሰዎች፦ ሰዎች ክርስቲያን ነን ብለው ሊያስመስሉ ይችላሉ፥ ነገር ግን በኢየሱስ ያላቸውን እምነት ከካዱ በመጀመሪያም እምነታቸው እውነተኛ እንዳልነበረ የሚያሳይ ማስረጃ ነው ይላሉ። በተጨማሪም የእኔ የሆኑት አይጠፉም የሚለውን የኢየሱስን የተስፋ ቃል እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ፤ (ዮሐንስ 10፡25-30)። በተጨማሪም ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያንን የተዉት ሰዎች ከመጀመሪያም አንሥቶ ክርስቲያኖች አልነበሩም ይላል፤ (1ዮሐ.2፡19)። ምንም እንኳ እንደ ይሁዳ ሰዎችን ሊያታልሉ ቢችሉም በእውነቱ የእርሱ የሆኑትን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

የትኛውንም አመለካከት ብናምን እምነታችንን መመሥረት ያለብን የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ በሚያስተምረው ክፍል ላይ ነው እንጂ ከልምድ ባካበትነው

አመለካከታችን ላይ መሆን የለበትም። የዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ የተልእኮ ትምህርት መጽሐፍ ጸሐፊ እውነተኛ ክርስቲያኖች እንደማይጠፉና እስከ መጨረሻው በእምነታቸው እንደሚጸኑ የሚገልጸው አመለካከት በበለጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ነው ብሎ ይቀበለዋል።

የዕብራውያን ጸሐፊ፣ እነዚያ በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት የሚክዱ ሰዎች አምስት ቁልፍ የሆኑ ነገሮችን ያደርጋሉ ይላል። በመቀጠልም እነዚህን አምስት ነገሮች ስለሚያደርጉ ሀእነርሱን ወደ ንስሐ ማምጣት የማይቻል ነውሀ ይላል።

1. ብርሃን የበራላቸው፤ ጸሐፊው በዚህ ቦታ የሚገልጸው የወንጌሉ ብርሃን ሕይወታቸው ዘልቆ ገብቶ የሰሙበትንና የተረዱበትን ጊዜ ነው። አንዳንዶች ይህ ክፍል እነዚህን ሕፃናት የሆኑት ክርስቲያኖች ወንጌሉን በደንብ ተረድተው አምነውበታል የሚል ትርጓሜ ነው ያለው የሚል ግንዛቤ አላቸው። ሌሎች ደግሞ ይህ የሚያመለክተው እነዚያን የወንጌሉ መልእክት በደንብ የገባቸውንና በግላቸው ግን መቀበልም ያልተቀበሉትን ሰዎች ነው ብለው ያስባሉ። እራሳቸውን ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ለማመን ሕይወታቸውን አሳልፈው አልሰጡም።

2. ሰማያዊውን ስጦታ የቀመሱት፤ ስጦታ የሚባል ስያሜ የተሰጣቸው ብዙ ነገሮች አሉ በአዲስ ኪዳን። የደኅንነት፥ የዘላለማዊ ሕይወት፥ የመንፈስ ቅዱስ ወዘተ... ስጦታዎች አሉ። ጸሐፊው እዚህ ላይ የሚጠቅሰው ስጦታ አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን የሚቀበላቸውን ስጦታዎች በሙሉ ላይሆን አይቀርም። አንዳንድ ሰዎች ይህ ሀየቀመሱትሀ የሚለው ቃል ክርስቲያን ሳይሆን ዝም ብሎ በክርስቲያኖች መካከል በመኖር በረከቶቹን ያየና የተገነዘበን ሰው የሚያመለክት ነው ብለው ያስባሉ ውኃ በአፉ ውስጥ አድርጎ ሳይጠጣው እንደሚተፋው ዓይነት ሰው ነው። ሌሎች ደግሞ ሀየቀመሱትሀ የሚለው ቃል በረከቶችን ብቻ የሚወክል አይደለም ይላሉ። ሙሉ በሙሉ የደኅንነት በረከቶች የተቀበሉና ክርስቲያኖች የሆኑ ሰዎችን የሚጠቅስ ነው፤ (ለምሳሌ፤ ዕብራውያን 2፡9፥ የሐዋ. 10፡10)።

3. ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች የሆኑ፤ ጸሐፊው በእነዚህ ሰዎች መካከልና በሕይወታቸው ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መኖር በታምራት የተደገፈ ማስረጃ እንዳለው ይናገራል፤ (ዕብራውያን 2፡4)። እንደገና መንፈስ ቅዱስ በእንዴት ያህል ሥልጣን ነበር በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ይመላለስ የነበረው የሚለው ሐሳብ ላይ ምሁራን ይከራከራሉ። አንዳንዶች ከክርስቲያኖች ጋር በመኖራቸውና ስለ ተአምራቶች ምሥክሮች በመሆናቸው የተወሰነ ደረጃ ድረስ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ተለማምደውታል ብለው ያስባሉ። ሆኖም ልባቸው መቼም ቢሆን የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ አልነበረም። ሌሎች ደግሞ እውነተኛ ክርስቲያኖች ስለነበሩ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ነበሩ ብለው ያስባሉ።

4. መልካሙን የእግዚአብሔር ቃል የቀመሱ፤ እነዚህ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ዓበይት ትምህርቶች በሚገባ ተምረዋል። ያውቁታል፥ ተረድተውታል፥ በትንሹም ቢሆን መልካምነቱን በሕይወታቸው አይተውታል። አንዳንዶች እነዚህ ሰዎች

ወዘተ... በኋላ ላይም ለመቀጣጫ ብሎ እግዚአብሔር ልቡን አደነደነው፤ ዘጸአት 9፡12፥ 10፡20፤ ሮሜ 1፡18-32 ተመልከት)።

16ኛ ጥያቄ:- ሀ) ክርስቲያኖች የማያዳግም ኃጢአት ሠርተናል፥ ለእኛ ካሁን ወዲያ ምንም ዓይነት ምሕረት አይኖርም ሲሉ ሰምተህ ታውቃለህ?

ለ) ምን ዓይነት መልስ ሰጠሃቸው?

ሐ) ይህ እምነታቸው እውነተኛ ነው?

እግዚአብሔር እንዳይቀበለን የሚያደርግ እኛ ልንሠራው የምንችለው ኃጢአት የለም ነገር ግን በተደጋጋሚ እውነቱን ካልተቀበልንና እያወቅን በእግዚአብሔር ላይ የምናምፅ ከሆነ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ ማመን የማንችልበት ደረጃ ላይ እንደምንደርስ ብዙ ጊዜ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። ወደ ክርስቶስ ለመመለስ የሚፈልግ ሰው ልቡ ደንድኖ ማመን የማይችልበት ደረጃ ላይ እንዳልደረሰ ያሳያል። ለመመለስ ግድ የሌላቸው ግን ልባቸው እየደነደነ መሆኑን ያሳያሉ።

ክርስቲያን ሆኖ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ንስሐ የሚገባውንና ክርስቲያን ነኝ እያለ ሙሉ በሙሉ እምነቱን የሚክደውን መለየቱ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ ነገር ግን ንስሐ ገብቶ ተቀባይነትን አገኘ። ይሁዳ ኢየሱስን ካደ ነገር ግን ንስሐ አልገባም። በኋላ ላይም የደነደነው ልቡ ንስሐ እንዳይገባ ከለከለው። ክርስቲያኖች በታላቅ ኃጢአት ሊወድቁ ይችላሉ፥ በኋላ ላይ ግን ንስሐ ይገባሉ። ድነናል ብለው በኃጢአት ከወደቁ በኋላ ንስሐ የማይገቡ ሰዎች መጀመሪያውንም እውነተኛ እምነት ይኑራቸው አይኑራቸው በጣም አጠያያቂ ነው።

ሰዎች በኢየሱስ ያላቸውን እምነት ሲክዱ ምን ማድረጋቸው ነው? ጸሐፊው እንደሚለው «ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታል ያዋርዱትማል»። ጸሐፊው እምነታቸውን በመካዳቸው ኢየሱስ ይሰቀል ከሚሉት ጋር አንድ ላይ ይተባበራሉ ማለቱ ነው። በድርጊታቸውና በንግግራቸው የኢየሱስን ስም ያዋርዳሉ። ብቸኛውን የደኅንነት መንገድ በመካዳቸው እነዚህ ሰዎች ካሁን ወዲህ ምንም ዓይነት ተስፋ የላቸውም።

እነዚህን ጥቅሶች ለመረዳት የሚያስችሉ ሦስት ዋና ዋና አመለካከቶች አሉ። እያንዳንዱ አመለካከት የራሱ የሆነ ችግር አለው። ስለዚህም እምነታችንን ሙሉ በሙሉ በእነዚህ ጥቅሶች ላይ እንዳናደርግ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ከዚህ ጋር የሚዛመዱ ሌሎች ጥቅሶችንም መመልከት ይኖርብናል። ሆኖም የዚህ ክፍል ዋነኛ ትምህርት እውነተኛ አማኝ በእምነቱ እንደሚጸና ነው። እምነቱን ለመተው የሚያደርገው ማንኛውም ዓይነት ሙከራ ክርስቲያን አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ንስሐ አለመግባት ደረጃ ላይ ሊያደርሰው የሚችለውን ወደ ልበ ደንዳናነት ላይ የመድረስ አደጋ መቅረቡንም የሚያመለክት ነው። እምነታችንን ላለመካድ ትልቅ ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርብናል። ሌላ ከዚህ ልንረዳው የምንችለው ነገር ከኢየሱስ ጋር የግል የሆነ ግንኙነት ሳይኖራቸው ዝም ብለው ውጫዊ የሆነ የክርስትና መልክ ኖሯቸው የሚኖሩትን ወደ እውነቱ ለማምጣት በጣም እንደሚከብድ ነው።

17ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያኖች ነን ብለው የሚያስቡትን ነገር ግን ከኢየሱስ ጋር እውነተኛ የሆነ ግንኙነት የሌላቸውን ሰዎች ለማነጋገር ሞክረህ ታውቃለህ? እነዚህን ሰዎች ማሳመኑ የሚከብደው ለምንድን ነው?

1. የመጀመሪያው አመለካከት እነዚህ እውነተኛ ክርስቲያኖች የነበሩና በአሁን ጊዜ ደኅንነታቸውን አጥተው ለመመለስ የማይችሉ ናቸው የሚል ነው። አምስቱንም የደኅንነት በረከቶች ሙሉ በሙሉ ተለማምደዋቸዋል። ነገር ግን አሁን በኢየሱስ የነበራቸውን እምነት በመካዳቸው ምክንያት ደኅንነታቸውን አጥተዋል። ይህ ከሆነ የሚሰጠው ትርጓሜ ጸሐፊው እነዚህ ሰዎች ወደ ንስሐ ሊመለሱ አይችሉም ያለውን ልናስታውሰው ይገባል። ይህን አመለካከት ክርስቲያኖች ደኅንነታቸውን ሊነጠቁ አይችሉም ከሚሉት ሌሎች አመለካከቶች ጋር አብረን ልናገናኘው ይገባል።

ሌሎቹ ሁለት አመለካከቶች የተመሠረቱት፡- እውነተኛ ክርስቲያኖች በምንም ዓይነት ደኅንነታቸውን አያጡም በሚለው ግንዛቤ ላይ ነው።

2. ሁለተኛው አመለካከት እነዚህ ጥቅሶች ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ነገር ግን እውነተኛ ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎችን ያመለክታሉ ይላል። ምንም እንኳ የደኅንነት ፍሬዎችን ያሳዩ ቢመስሉም እምነታቸውን መካዳቸው እውነተኛ አማኞች እንዳልሆኑ ያሳያል (ለምሳሌ፡- እሥራኤላውያን ቀይ ባሕርን አቋረጡ፥ በደመናው ሥር ኖሩ፥ መና ተመገቡ፥ ይሁን ቢሆን ባለማመናቸው ሞቱ)። አምስቱም የተዘረዘሩት በረከቶች ክርስቲያኖች ነን ብለው የሚመሥክሩ ክርስቲያን እንደሆኑ የሚያስመስሉና የክርስትናን ሕይወት በረከቶች እስከመለማመድ የደረሱ ሰዎችን የሚያመለክቱ ናቸው። ሆኖም በማያወላውል ሁኔታ ኢየሱስን በካዱ ጊዜ እምነታቸው እውነተኛ እንዳልሆነ አስመሥክረዋል።

3. ሦስተኛው አመለካከት ደግሞ ጸሐፊው እውነተኛ ለሆኑ ግን ላላደጉ ክርስቲያኖች ነው የሚጽፈው የሚለው ነው። ይህ አመለካከት ያላደጉት ክርስቲያኖች እነዚህን አምስት በረከቶች እንደተለማመዱ ያምናል። እምነታቸው እውነተኛ ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ ግን፥ እምነታቸውን ለመካድ አስበው ነበር። ስለዚህም ለእነዚህ ላላደጉ ክርስቲያኖች ጸሐፊው ይህንን ሊሆን የማይችለውን የደኅንነት ማጣት መላምት ይገልጽላቸዋል። ይህንን የሚያደርገው የአይሁድ ክርስቲያኖች ወደ ድሮው የአይሁድ ሃይማኖት እንዳይመለሱ ለማስፈራራት ነው። ጸንተው እንዲቆሙ ያስጠነቅቃቸዋል። ጸሐፊው ደኅንነታቸውን አጥተዋል ብሎ የሚጠቅሳቸው ሰዎች የሉም። በ5፡12 ላይ በቀጥታ የሚናገረው ክርስቲያኖቹን ነው፥ በ6፡1-3 ላይ ወደ ፍጹም ሄደን እንሂድ በሚለው ላይ እራሱን ይጨምራል፥ በ6፡4-6 ደህንነትን ስለማጣት ሲናገር የሚናገረው ስለ ሌሎች ነው። እንዲያውም ጸሐፊው እነዚህ ክርስቲያኖች እውነተኛ አማኞች እንደሆኑና እምነታቸውን እንደማይከዱ ሙሉ እምነት አለው፥ (6፡9-12)።

በ6፡7-9 ላይ ጸሐፊው የሰጠውን ትምህርት ፍሬ ሐሳብ የሚገልጽበት አንድ ሥዕላዊ መግለጫ ይሰጠናል። የእግዚአብሔርን ጸሐይና ዝናብ የሚያገኙ ሁለት መሬቶች ነበሩ። አንደኛው ፍሬ አፈራ፤ ሁለተኛው ግን አላፈራም። አንደኛው በረከትን ያገኛል፥

20ኛ ጥያቄ:- ማርቆስ 12:28-31 ተመልከት።

ሀ) ታላቋ ትዕዛዝ ምንድን ናት?

ለ) ሁለተኛዋ ታላቅ ትዕዛዝስ ምንድን ናት?

እግዚአብሔርንና ሌሎችን ስለ መውደድ የሚናገሩት ሁለቱ ታላላቅ ትዕዛዞች በጣም የተዛመዱ ናቸው። እግዚአብሔርን ከወደድን ሌሎችን ውደዱ የሚለውን ትዕዛዙን እንጠብቃለን። ሌሎችን ከወደድን ደግሞ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅርና አክብሮት እናሳያለን። በዚህም ምክንያት ነው ጸሐፊው ክርስቲያኖቹ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ሌሎችን በመርዳት ገለጹት የሚለው። ምንም በስደት ላይና በጥርጥር ውስጥ ቢሆኑም ፍቅር ስለነበራቸው ጸሐፊው አሁንም እምነት እንደነበራቸው ሙሉ መተማመን ነበረው፤ (ዕብራውያን 10:32-34 ተመልከት)። 21ኛ ጥያቄ:- በምን ዓይነት መንገድ ፍቅር በሕይወትህና በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እንደሚገለጽ በዝርዝር ጻፍ።

ይህም ሁሉ ቢሆን ጸሐፊው ትጋት እንዲያሳዩ ይገፋፋቸዋል። ስደቱና ፈተናው እምነታቸውን እንዲክዱና ፍቅር ከማሳየት እንዲቆጠቡ እንዳያደርጋቸው ማድረግ አለባቸው። የእውነተኛ እምነት ማስረጃ የሚሆን አንድ ባህርይ ይቀራቸው ነበር። ይህም ጸንቶ መቆም ነው። በመጨረሻ ላይ የዘላለማዊ ሕይወት ተስፋውና የሰማያት ክብርን የራስ የማድረጊ ነገር እውን የሚሆነው ጸንቶ በመቆም ነው።

ለክርስቲያን ትልቁና አደገኛው ነገር ስንፍና ነው። ከስንፍና የተነሣ ቃሉን የማናጠና ከሆንን ክርስቶስን ለመምሰል መሻቱ ከሌለንና ለሌሎች የመመሥከርና ፍቅር የማሳየት ፍላጎቱ ከሌለን ወደ ውድቀት እያመራን ነው ማለት ነው። ክርስቶስን ወደ መምሰሉ የመድረሱ ጉዳይ ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ ነው፤ (ፊልጵ.2:12)።

በስደት ውስጥ እምነታቸውን ጠብቀው ጸንተው መቆሙ እንዴት እንደሆነ ለመረዳት የእግዚአብሔር እንደሆኑ ያስመሠከሩና የሱን በረከት የተቀበሉትን ሰዎች ምሳሌ መከተል አለባቸው። ያለምንም ጥርጥር በጸሐፊው አእምሮ ውስጥ ያሉት በምዕ.11 ላይ የጠቀሳቸው ጻድቃን ሰማዕታት ናቸው። ከዚህም ሌላ በቤተ ክርስቲያናቸው ታማኞች የነበሩ ሰዎች ስለነበሩ የእነርሱንም ምሳሌነት ጥምር መከተል ነበረባቸው።

22ኛ ጥያቄ:- በምን ዓይነት መንገድ ነው የቅዱሳንን ምሳሌነት መከተላችን የበለጠ መልካም ሰዎች ሊያደርገን የሚችለው? ነገር ግን እምነታችን በሰዎች ላይ አለመሆኑን ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው። እምነታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። በጣም ጻድቅ ነው የሚባለው እንኳ ሊወድቅ ይችላል። ምንጊዜም ታማኝ ሆኖ የሚጸናው ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

23ኛ ጥያቄ:- ዮሐንስ 15:1-17 አንብብ።

ሀ) ፍሬ ስለሚያፈሩቱ ኢየሱስ ምን ይላል?

ለ) ፍሬ ስለማያፈሩትስ ምን ይላል?

ሐ) የሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው?

# አራተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 6፡ 13-20

አንድ ክርስቲያን ጸንቶ በመቆም እንዴት አድርጎ የተስፋውን ቃል እንደሚቀበል ለማሳየት ጸሐፊው ስለ አብርሃም ሕይወት ይጠቅሳል። አብርሃም የአይሁድ ሕዝብ የሥጋ አባት ብቻ ሳይሆን በእምነት የእግዚአብዝሔር ቤተሰብ ለሚሆኑ ሁሉ ጭምር የመንፈስ አባት ነው። ስለዚህም የእርሱ ሕይወት የእግዚአብሔር ልጆች በእምነት ጸንተው እንዴት አድርገው የእግዚአብሔርን ተስፋ እንደሚቀበሉ የሚገልጽ ጥሩ ምሳሌ ነው።

24ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 6፡ 13-20 አንብብ።

ሀ) እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው? ይህ የተስፋ ቃል የሚገኘው የት ነው?

ለ) አብርሃም ለተስፋው ቃል ምን ዓይነት ምላሽ ነው የሰጠው?

ሐ) ከቁጥር 18 ላይ ሁለቱ የማይለወጡ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

በኦሪት ዘፍጥረት 12፡2-3 ላይ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እሰጥሃለሁ ዘሩም ታላቅ ሕዝብ ይሆናል የሚል የተስፋ ቃል ሰጥቶታል። አብርሃም ይህን የተስፋ ቃል ተቀበለው፤ ቢሆንም ይህ የተስፋ ቃል የተፈጸመው ይስሐቅ ሲወለድ ከ25 ዓመት በኋላ ነው። አብርሃም ለእግዚአብሔር ታዛዥ በመሆን ይስሐቅን ለመሠዋት ፈቃደኛ በሆነበት ወቅት እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ኪዳን ያድስለታል፤ በዚህ ጊዜ ግን መሐላም ታክሎበታል፤ (ኦሪት ዘፍጥረት 22፡16-18 ተመልከት)። ጸሐፊው የሚናገረው ስለ እነዚህ ሁለት ክንዋኔዎች ነው። ይህም ሆኖ አብርሃም የሞተው እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃሎች በሙሉ ሳይፈጸሙ ነው።

ሰዎች የቃላቸውን እውነተኛነት ለመግለጽ መሐላ ይፈጽማሉ። በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ቃላቸውን እንዲቀበሏቸው በፈራጁ በእግዚአብሔር ስም ብለው ይምላሉ። መሐላ በሚያደርግበት ወቅት አንድ ከራሱ በላይ በሆነ ነገር ነው የሚጠቀመው። ከእግዚአብሔር በላይ ያለ ማንም ባለመኖሩ እግዚአብሔር መሐላ የሰጠው በራሱ ስም ነው። እንደ ሰዎች ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ሁሌም ቢሆን እውነት ነው። በዚህም ምክንያት ቃለ መሐላ ሊያደርግ አይገባውም። ነገር ግን የተስፋ ቃሉን እውነተኛነት ለአብርሃም በደንብ አድርጎ ለማረጋገጥ ሲል እግዚአብሔር ቃለ መሐላ ያደርጋል። ይህ የተስፋ ቃልና መሐላ የተስፋውን ቃል የተወሰነ ክፍል ፍጻሜ ላየው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን የዚያ የተስፋ ቃል ወራሾች ለሆንነው ለእኛም ጭምር ነው። የመንፈሳዊው አባታችን የአብርሃም ልጆች እንደመሆናችን መጠን ለአብርሃም የተሰጠው የበረከትና የዘላለማዊ ሕይወት ተስፋ ለእኛም የተጠበቀ ነው።

ሁለቱ የማይለወጡት ነገሮች ምንድን ናቸው? አንደኛ፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው የበረከት ቃል ኪዳን ነው። ሁለተኛ፤ የቃል ኪዳኑን እውነተኝነት ያስረገጠበት

የመሐላ ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች እንደ ቃሉ የጸኑ ናቸው። ስለሚይኖሽ ለአብርሃምና ለእኛ የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች በእርግጥ ይፈጸማሉ።

በረከቱ ምንድን ነው? ለአብርሃም በረከቱ በከፊልም ቢሆን በይስሐቅ መወለድና በእሥራኤል ልጆች አማካይነት ተፈጽሟል፤ ሆኖም መንፈሳዊ የሆነም የተስፋ ቃል ነበር፤ (ዕብራውያን 11፡10፥ 15-16 ተመልከት)። ለአብርሃም የተሰጠው የተስፋ ቃል የመጨረሻ ፍጻሜ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። ተስፋችን የተመሠረተው እግዚአብሔር ለአብርሃም በሰጣቸው የተስፋ ቃል ኪዳኖች መፈጸም ላይ ነው። የዘላለም ሕይወትና የመንግሥተ ሰማያት ቃል ኪዳኖች እስካሁን ድረስ በአማኝ ፊት ያሉ ያልተፈጸሙ ቃሎች ናቸው። ሆኖም እግዚአብሔር ለአብርሃም እንደሰጠው ቃል ኪዳኖች እነዚህም በእርግጥ ተፈጻሚ ናቸው።

በመከራ ጊዜ መጽናናትን የምናገኘው ሐሳባችንን በችግራችን ላይ በማድረግ ሳይሆን ዐይናችንን እግዚአብሔር በሚያዘጋጅልን ዘላለማዊ መኖሪያ ላይ በማድረግ ነው፤ (ዮሐ.14፡1-4)። ይህንን ተስፋ ለመግለጽ ጸሐፊው ሦስት ተምሳሌቶችን ይጠቀማል፡ አንደኛ፤ መሸሸጊያና መጠጊያችን ነው። በብሉይ ኪዳን ነፍስ ገዳዮች ይሸሹባቸውና ከጠላቶቻቸው እጅ ይድኑባቸው ዘንድ የተዘጋጁ ስድስት የመማጸኛ ከተሞች ነበሩ፤ (ዘኁልቁ 35፡6፥ 9-32)። ልክ እንደዚሁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ክርስቲያኑ ከእግዚአብሔር ቁጣና ከኃጢአተኞች ፍርድ ይድናል።

ሁለተኛ ተስፋችን ልክ እንደ መልሕቅ ነው። መልሕቅ ከትልቅ ብረት የተሠራ ወይም ድንጋይ ሲሆን በወደብ አካባቢ መርከቡ ቀጥ ብሎ እንዲቆም የሚያደርገው ነው፤ (ስለ መልሕቅ የተሰጠውን ማብራሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ተመልከት)። የእኛ መልሕቅ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃልና ይህን የተስፋ ቃል ሀእርግጥና ጽኑህ የሚያደርገው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በስደት ላይ እንኳ ብንሆን በምንም ዓይነት አያሳፍረንም።

ሦስተኛ፤ ተስፋችን የተመሠረተው ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ በገባው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። በሌላ አነጋገር ወደ መንግሥተ ሰማያት ቀድሞን የሚገባና እኛም እንደምንገባ ማስተማመኛ የሚሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህኑ ወደ መገናኛው ድንኳን ቅድስተ ቅዱሳኑ ይገባ የነበረው በዓመት አንዴ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ ቅድስተ ቅዱሳንና የመጨረሻ መድረሻችን ወደ ሆነው ወደ መንግሥተ ሰማያት አንዴ ገባ። በመልከ ጼዴቅ ሹመት ላይ ሆኖ ልክ እንደ ሊቀ ካህኑ ለእኛ ባለማቋረጥ ይማልድልናል።

ጸሐፊው በዕብራውያን 5፡10 ላይ ወደ አለው ትምህርቱ እንደገና ይመለሳል። አብርሃም የተስፋውን ቃል እንደሚያገኝ እርግጠኛ ስለሆነበት ስለ መሐላው ቃል በሚያስብበት ጊዜ የመልከ ጼዴቅ ክህነትን በተመለከተ እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል ትዝ ይለዋል። አሁን በምዕራፍ 7 ላይ ወደ እዚህ ትምህርት ይመለሳል።

ጌታ ኢየሱስን እንድንክድ ሊያደርጉን የሚችሉ ፈተናዎች ሲያጋጥሙን ሁለት አስፈላጊ የሆኑ እውነታዎችን ልናስታውስ ይገባናል። አንደኛ፤ ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ

ምንም ዓይነት የደኅንነት መንገድ የለም። እርሱን ከተውን ለእኛ ትርፋችን የእግዚአብሔር ቁጣ ነው። ለቤተሰባችን ወይም ስለኑሮአችን ማሰባችን ወይም ስደትን መፍራታችን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን እምነት እስከመተው ሊያደርሰን አይገባም፥ ምክንያቱም እምነታችን ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች በላይ ነው። ሁለተኛ፤ እግዚአብሔር መንግሥተ ሰማያት ወስዶን የዘላለምን ሕይወት ሊያጎናጽፈን ቃል እንደገባልን መገንዘብ ይገባናል። እነዚህ የተስፋ ቃሎች በእርግጥ የሚፈጸሙ ናቸው፤ ሆኖም እነርሱን ለማግኘት ስንል ጸንተን መቆም ይኖርብናል።

25ኛ ጥያቄ፡- ከምታውቃቸው ሰዎች እነማን ይመስሉሃል፤ በዚህ ትምህርት በጣም ሊጠቀሙ የሚችሉ? የተማርኸውን ነገር አካፍላቸው።

**አምስተኛ ቀን**፡-የዚህንሳምንትትምህርትከልስናለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) 1. ስድስቱ መሠረታዊ ትምህርቶች ምን ምንድን ናቸው?

2. እነዚህ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ የሚሰጡት እንዴት ነው?

3. ቤተ ክርስቲያንህ በምን ዓይነት መንገድ ነው ክርስቲያኖችን ለማጎልመስ የምትጥረው?

4. በትምህርት መልክ ሊሰጡ የሚገቡ አንዳንድ ጠለቅ ያሉት እውነታዎች የትኞቹ ናቸው?

ለ) 1. አንድ ክርስቲያን ደኅንነቱን ስለማጣቱ ቤተ ክርስቲያንህ የምትሰጠው ትምህርት ምን ዓይነት ነው?

2. ይህንን አመለካከት የሚደግፉ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?

3. በዕብራውያን 6፡4-6 ላይ ካሉት ሦስት አመለካከቶች የትኛውን ነው የምትደግፈው? ለምን?

ሐ) 1. በምን ዓይነት መንገድ ነው እውነተኛውን ክርስቲያን ከሐሰተኛው የምንለየው?

2. አንድ ሕይወት እንደተለወጠ የሚገልጹትን አንዳንዶቹን ፍሬዎች ግለጽ።

መ) 1. እስካሁን ድረስ ከምንጠብቃቸው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች አንዳንዶቹን ጻፍ።

2. ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነን እንድንቆይ እነዚህ የተሰፉ ቃሎች የሚያበረታቱን እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ አራት

*ዕብራውያን ምዕራፍ 7*

## የመጀመሪያው ቀን:- ዕብራውያን 7፣1-3

ለክርስቲያን በጣም አደገኛ የሆነው ምድራዊ የሆነ ሊቀ ካህን ያስፈልግሃል ወይም እግዚአብሔርን ስታመልክ በአምልኮህ የሚረዳህ ምድራዊ የሆነ አማላጅ ያስፈልግሃል የሚለው ትምህርት ነው። እነዚህ የአይሁድ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ምድራዊ የሆነ ሊቀ ካህን የሚፈልጉ ይመስላል። ይህም ሲሆን በመንግሥተ ሰማያት ላይ በእግዚአብሔር ፊት የቆመ ምድራዊ ያልሆነ ታላቅ ሊቀ ካህን እንዳላቸውን አልተገነዘቡም።

በምድር ላይ የተለመደው አንድ ተራ ሰው መሪ ወደሆነ ሰው መቅረብ ከፈለገ በመሐከል ሊያገናኙት በሚችሉ ሰዎች በኩል ማለፍ አለበት። ስለዚህም ትንሽም ትሁን ሥልጣን ያለውን ወዳጁን ወይም ዘመዱን ይፈልግና እርሱን ወክሎ እንዲቀርብለት ያደርጋል።

1ኛ ጥያቄ:- ይህ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ምሳሌ ስጥ። ይህ ግንዛቤ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲለውጥ ሊያደርጋቸው የሚችልበት መንገድ አለን?

ይህ የአማላጅ ሐሳብ የሚነሣው ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሚያስቡበት ወቅት ነው። በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከመጸለይ ወደ መላእክት ወይም ወደ ማሪያም አንዳንዶች ደግሞ ወደ ጻድቃን ሰማዕታት ይጸልያሉ። ሸክማቸውን ቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከመውሰድ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ይሄዱና እንዲጸለይላቸው ይጠይቁታል።

የዕብራውያን መጽሐፍ ትልቁ ትምህርት ለእኛ የሚያስፈልገን አንድ አማላጅ ብቻ የሚለው ነው። እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መሪዎች፥ ካህናት ወይም ጻድቃን ሰማዕታት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል እንደ አማላጅ ሆነው ሊቆሙ አያስፈልግም። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መብት አለን። በእኛ በኩል ወደ መሪዎች ሄደን እንዲያማልዱን የምናደርገው ማንኛውም ዓይነት ጥረት መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ወደ እርሱ ለመቅረብ የሚያስችለን ክፍት መንገድ መኖሩን የሚያስተምረውን ትምህርት እንደመቃወም ነው የሚቆጠረው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ካህናችን ሆኖ

2. ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነን እንድንቆይ እነዚህ የተሰፉ ቃሎች የሚያበረታቱን እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ አራት

ዕብራውያን ምዕራፍ 7

## የመጀመሪያው ቀን:- ዕብራውያን 7:1-3

ለክርስቲያን በጣም አደገኛ የሆነው ምድራዊ የሆነ ሊቀ ካህን ያስፈልገሃል ወይም እግዚአብሔርን ስታመልክ በአምልኮህ የሚረዳህ ምድራዊ የሆነ አማላጅ ያስፈልግሃል የሚለው ትምህርት ነው። እነዚህ የአይሁድ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ምድራዊ የሆነ ሊቀ ካህን የሚፈልጉ ይመስላል። ይህም ሲሆን በመንግሥተ ሰማያት ላይ በእግዚአብሔር ፊት የቆመ ምድራዊ ያልሆነ ታላቅ ሊቀ ካህን እንዳላቸው ግን አልተገነዘቡም።

በምድር ላይ የተለመደው አንድ ተራ ሰው መሪ ወደሆነ ሰው መቅረብ ከፈለገ በመሐከል ሊያገናኙት በሚችሉ ሰዎች በኩል ማለፍ አለበት። ስለዚህም ትንሽም ትሁን ሥልጣን ያለውን ወዳጁን ወይም ዘመዱን ይፈልግና እርሱን ወክሎ እንዲቀርብለት ያደርጋል።

1ኛ ጥያቄ:- ይህ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ምሳሌ ስጥ። ይህ ግንዛቤ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲለውጥ ሊያደርጋቸው የሚችልበት መንገድ አለን?

ይህ የአማላጅ ሐሳብ የሚነሣው ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሚያስቡበት ወቅት ነው። በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከመጸለይ ወደ መላእክት ወይም ወደ ማሪያም አንዳንዶች ደግሞ ወደ ጻድቃን ሰማዕታት ይጸልያሉ። ሸክማቸውን ቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከመውሰድ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ይሄዱና እንዲጸለይላቸው ይጠይቃሉ።

የዕብራውያን መጽሐፍ ትልቁ ትምህርት ለእኛ የሚያስፈልገን አንድ አማላጅ ብቻ የሚለው ነው። እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መሪዎች፥ ካህናት ወይም ጻድቃን ሰማዕታት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል እንደ አማላጅ ሆነው ሊቆሙ አያስፈልግም። በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መብት አለን። በእኛ በኩል ወደ መሪዎች ሄደን እንዲያማልዱን የምናደርገው ማንኛውም ዓይነት ጥረት መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ወደ እርሱ ለመቅረብ የሚያስችለን ከፍተ መንገድ መኖሩን የሚያስተምረውን ትምህርት እንደመቃወም ነው የሚቆጠረው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ካህናችን ሆኖ

የሠራውንም ሥራ እናቃልላለን። ይህን ስንል ወደ ክርስቲያኖች ሄዳችሁ እንዲጸልዩላችሁ መጠየቅ አትችሉም ማለታችን አይደለም። የእናንተም የእነርሱም ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባሉ መልስም ይሰጣችኋል።

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በክርስትና ውስጥ ይህን የአማላጅ ነገር መጠቀም በእግዚአብሔር ዓይን ሁሉም አማኝ እኩል ነው ከሚለውና አንድ አማላጅ አለ ከሚለው ትምህርት ጋር የሚቃረነው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ለ) ይህ የተሳሳተ አስተሳሰብ የሌሎችን እና የአንተን ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት በምን መልኩ ነው ተጽዕኖ ያለው?

የአይሁድ ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳኑን የአምልኮ ሥርዓት በታላቅ አክብሮት ይመለከቱት ስለነበር ወደ ድሮው የአይሁድ ሃይማኖት ለመመለስ ይወላውሉ ነበር። ስለዚህም ከምዕራፍ 7-10፥ ጸሐፊው የብሉይ ኪዳን አምልኮ ምሰሶ የነበሩት ሦስቱ ዋና ዋና ነገሮች እንደተተኩ ያስረዳል። በመጀመሪያ፤ የሙሴ ሕግ መሠረት የሆነው ቃል ኪዳንና የአምልኮው ሥርዓት በአዲሱ ኪዳን ተተክቷል፤ (ምዕራፍ 8)። ሁለተኛ፤ የአሮን ዘር ሊቀ ካህናት ከእርሱ በሚበልጠው በመልከ ጼዴቅ ክህነት ተተክቷል፤ (ምዕራፍ 7)። ሦስተኛ፤ መሥዋዕት የማቅረቡ ሥርዓት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ተተክቷል፤ (ምዕራፍ 9-10)።

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብዙ እውነታዎችን የሚያስተምረን በምሳሌዎች ነው። እነዚህ ምሳሌዎች የሚገኙት በብሉይ ኪዳን ሲሆን የተፈጸሙትም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ታሪክን ስለሚቆጣጠር እነዚህን ክንዋኔዎችና ሰዎች በመንግሥተ ሰማያትና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተፈጸሙትን እውነታዎች በጥልቀት ለማሳየት ይጠቀምባቸዋል። ለመጥቀስ ያህል፡- የብሉይ ኪዳኖቹ መሥዋዕቶች ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ያመለክቱ እንደነበር ተመልክተናል። በበረሃው የተደረገው መንከራተትና ይህን የመሳሰሉ ሌሎች ክንውኖች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ምክንያት የሚያጋጥማቸውን ችግር ያመለክታሉ። እንደ ኢየሩሳሌም ያሉ በታዎች የመንግሥተ ሰማያት ተምሳሌቶች ነበሩ። እንደ መገናኛው ድንኳን ያሉ ነገሮችም የመንግሥተ ሰማያት ተምሳሌቶች ነበሩ። በመጨረሻም እንደ አዳም ሙሴ፥ ኢያሱ፥ ያሉ ሰዎች ፍጹም ሰው የነበረው የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌቶች ነበሩ። በዚህ ሳምንት የዕብራውያን ጸሐፊ በታሪክ ውስጥ በግልጽ ስለማይታየው የኢየሱስን ክህነት ሊመስል ስለሚችለው መልከጼዴቅ የሚል ሥያሜ ስለተሰጠው ሰው የሰጠውን ማብራሪያ እንመለከታለን።

3ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን ምዕራፍ 7 አንብብ። በመቀጠልም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከቁጥር 1-3 ባለው ክፍል ላይ በመመርኮዝ መልስ።

ሀ) ለመልከ ጼዴቅ የተሰጡት ሁለት ስያሜዎች ምንድን ናቸው?

ለ) መልከ ጼዴቅ እናትና አባት የለውም ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሐ) መልከ ጼዴቅ በምን መልክ ነው ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር የሚመሳሰለው?

ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ሊቀ ካህን እንደሆነ ለመገንዘብ የአይሁድ ክርስቲያኖች ችግር አጋጥሟቸዋል። በብሉይ ኪዳን ከሌዊ ወገን ሆነው የአሮን ዝርያ የነበራቸው ብቻ ነበሩ ካህን ሊሆኑ የሚችሉት። እንዴት ታዲያ ኢየሱስ ሊቀ ካህን ሊሆን ይችላል? ለዚህ መልስ ለመስጠት ጸሐፊው ወደማይታወቀው መልከ ጼዴቅ የሚባል ስያሜ ወደ አለው ያመራል።

4ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘፍጥረት 14:17-20 እና መዝሙር(110):1-4 አንብብ።

ሀ) በምን ዓይነት መንገድ ነው አብርሃምና መልከ ጼዴቅ የተገናኙት?

ለ) የመልከ ጼዴቅን ሊቀ ካህንነት በተመለከተ እግዚአብሔር የገባው ቃል ኪዳን ምን ነበር?

ጸሐፊው በ5:10 ላይ ስለ መልከ ጼዴቅ ጀምሮት ወደ ነበረው ይመለሳል፤ ቀደም ብሎ ያቋረጠው ክርስቲያኖቹ ገና ሕጻናት በመሆናቸው ነበር። ያም ሆነ ይህ ጥልቅ የሆኑ እውነታዎችን ማስተማሩን ይቀጥላል። የዕብራውያን ጸሐፊ የሚሰጠው ማብራሪያ በጣም ከባድ ነው፤ ይህ እንደዚህ ሊሆን የቻለው ጸሐፊው የተለመደውን የዘመኑን የአተረጓጎም ዘይቤን ሳይሆን የአይሁዳውያን የአተረጓጎም ዘይቤን ስለሚጠቀም ነው። የጸሐፊው ዓላማ ኢየሱስና መልከ ጼዴቅ እንደሚመሳሰሉ የኢየሱስ ካህንነት እንደ መልከ ጼዴቅ እንደሆነና ከአሮን እንደሚበልጥ ለማሳየት ነው።

ኦሪት ዘፍጥረት አብርሃም ታላቅ ጦርነት ገጥሞ ጠላቶቹን ከአሸነፈ በኋላ ብዙ ምርኮ ይዞ ሲመለስ ከመልከ ጼዴቅ ጋር እንደተገናኘ ይገልጻል። ሲገናኙ አብርሃም ለመልከ ጼዴቅ ከምርኮው ላይ አሥራት ከሰጠው በኋላ መልከ ጼዴቅ ይባርከዋል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መልከ ጼዴቅን በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ይመስለዋል። አንደኛ፤ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚታዩ ሁለት አመራሮችን አጣምሮ በመያዙ ይመሳሰላሉ። መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥና የእግዚአብሔር ሊቀ ካህን ነበር። በነገራችን ላይ ሳሌም የኢየሩሳሌም ከተማ ልዩ መጠሪያ ነው። በሙሴ ሕግ እነዚህ ሁለት ጥምሮች ሊኖሩ አይችሉም፥ ነገር ግን ልክ እንደ መልከ ጼዴቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥም ሊቀ ካህንም ነው።

ሁለተኛ፤ የሁለቱ የአመራር ሥርዓት አንድ ዓይነት ነው።«ሳሌም» ሰላም ማለት ሲሆን «መልከ ጼዴቅ» ደግሞ «የጽድቅ ንጉሥ» ማለት ነው። በዚህም ጽሐፊው የመልከ ጼዴቅ መንግሥት በሰላምና በጽድቅ ላይ የተመሠረተ ነው ማለቱ ነው። መሢሑ ሲነግሥ ከሚታዩት ዐበይት ነገሮች ውስጥ ሰላምና ጽድቅ ናቸው።

5ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከትና ወደፊት ስለሚመጣው ስለ መሢሑ መንግሥት ማብራሪያ ስጥ፤ (ኢሳይያስ 32:1-2፥ 16-18)።

ሦስተኛ፤ ሁለቱም ዘላለማዊ ናቸው። በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው የሚሰጠው ማብራሪያ ትንሽ ከበድ ይላል። አይሁዳውያን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተነገረውን ብቻ

ሳይሆን ያልተነገረውንም ነገር ማወቅ ይፈልጋሉ። ይህም ቢሆን ሁሉቱንም ይመራ የነበረው እግዚአብሔር ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበሩት ታላላቅ ሰዎች (ለምሳሌ፡- ሙሴ፣ አሮን፣ አብርሃም) ትውልዳቸው ከየት እንደሆነ ወላጆቻቸው እነማን እንደነበሩ እንዴት እንደሞቱ ገለጻ ተሰጥቷል። ሆኖም የመልከ ጼዴቅ ትንሽ ለየት ይላል። እናትና አባቱ እነማን እንደነበሩ ከየትኛው ወገን እንደነበረና እንዴት እንደሞተ አልተገለጸም። ምንም እንኳ መልከ ጼዴቅ እናትና አባት የነበረው ሰውና በመጨረሻም የሞተ ቢሆንም ጸሐፊው ይህንን በመጥቀስ ለእሥራኤላውያን እንደ ምሳሌ ሆኖ የሚጠቅማቸው ነገር ባለማግኘቱ ይህንን ለእሥራኤላውያን በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሳይጠቅስ ያልፋል። ስለ ሞቱ የተጠቀሰ ነገር ባለመኖሩ እስካሁን ድረስ ሊቀ ካህን ሆኖ የሚኖር ይመስላል። ስለዚህም መልከ ጼዴቅ መጀመሪያና መጨረሻ ስላልነበረው፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይመስላል። ጸሐፊው እዚህ ላይ የሚጠቅሰው የኢየሱስን መወለድና መሞት ሳይሆን እግዚአብሔር እንደመሆኑ ከጥንት አንሥቶ እስከ ዘላለም የመኖሩን ጉዳይ ነው የሚጠቅሰው። ስለዚህም የእርሱ ካህንነት ልክ እንደ መልከ ጼዴቅ ዘላለማዊ ነው እንጂ እንደነ አሮን በመሞት የሚቋረጥ አይደለም።

6ኛ ጥያቄ፡- የክርስቶስ ሊቀ ካህንነት ዘላለማዊ የመሆኑ እውነታ አስፈላጊነቱ በምን ዓይነት መንገድ ነው?

## ሁለተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 7፡4-10

በትናንትናው ዕለት ጸሐፊው የኢየሱስንና የመልከ ጼዴቅን መመሳሰል ነበር የገለጸው። በዚህ ክፍል ደግሞ የመልከ ጼዴቅ የሊቀ ካህንነት ሹመት ከአሮኑ እንዴት እንደሚበልጥ ያስረዳል። እንደገና የመልከ ጼዴቅን ታላቅነት ለአይሁዳውያን ለማገለጽ ጸሐፊው የአይሁዳውያንን የአተረጓጎም ዘይቤ ነው የሚጠቀመው። አስተውል! ጸሐፊው እነዚህን እውነታዎች የሚያስተምረው ክርስቲያኖቹ ወደ ድሮው የአይሁድ የአምልኮ ሥርዓት ሊቀ ካህን ወደ መፈለጉ ወደ መሥዋዕትና የቤተ መቅደስ ሥርዓት ለመመለስ እንዳይወላውሉ ነው። እኛም ብንሆን ሐሳባችንንና ተስፋችን ምድራዊ በሆኑ መሪዎች ላይ መጣል የለብንም። ታላላቅ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይነሣሉ ሆኖም ብዙ ሳይቆይ እንደ ጥላ ያልፋሉ። የሐሰት ትምህርቶች ብዙ ጊዜ የሚጀመሩት ሰዎችን ወደ እራሳቸው ለመሳብ በሚፈልጉ ሰዎች ነው። እንደ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ መሆኑን ማመንና በዚህ ላይ መጽናት ይኖርብናል። መከተል ያለብን እርሱን ብቻ ነው እንጂ ታላላቅ ሰዎችንም ጭምር መሆን የለበትም። የሰዎች ትምህርት እውነተኛና ትክክለኛ እንደሆነ ለማረጋገጥ ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ማነፃፀር አለብን። ይህ ካልሆነ የሐሰት መምህራንና ትምህርታቸው ከኢየሱስ ሊለያዩን ነው።

7ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስን ከመከተል የበለጠ ሰዎችን የሚከተሉት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ለ) የምንግራቸውን ትምህርቶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ማነፃፀሩ ለእኛ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

8ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 7:4-10 አንብብ። መልከ ጼዴቅ ከአሮን ሊቀ ካህንነት እንደሚበልጥ ለማሳየት ጸሐፊው የተጠቀመባቸው ሁለት መንገዶች ምንድን ናቸው?

ኢየሱስ በመልከ ጸዴቅ ሥልጣን ሊቀ ካህን ከሆነና የሙሴ ሕግ ደግሞ በአሮን ደረጃ ሌላ ሊቀ ካህንነት ከመመሥረት የትኛው ነው የሚበልጠው? ለዚህ መልስ ለመስጠት ጸሐፊው በኦሪት ዘፍጥረት ወደ ተፈጸመው ክንዋኔ ይመለሳል።

መልከ ጼዴቅ ከአብርሃም እንደሚበልጥ የሚገልጹ ሁለት ነገሮች:- አብርሃምና መልከ ጼዴቅ ሲገናኙ ተከናውነዋል። በመጀመሪያ ደረጃ አብርሃም ከምርኮው ላይ አንድ አሥረኛውን በአሥራት መልክ ለመልከ ጼዴቅ ሰጥቷል።

9ኛ ጥያቄ:- ኦሪት ዘኁልቁ 18:21-29 አንብብ። ሌዋውያን መቀበል የነበረባቸው የማንን አሥራት ነው?

በብሉይ ኪዳን ሥርዓት የካህናትና የሌዋውያን አንዱ ሐላፊነት ከሕዝቡ ላይ አሥራት መሰብሰብ ነው። የክህነትንና በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የመቆምን ሥልጣን የሰጣቸው እግዚአብሔር ነው። ሆኖም በኦሪት ዘፍጥረቱ ታሪክ ላይ ለመልከ ጼዴቅ አሥራት የሰጠው አብርሃም ነው። ይህም መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ሊቀ ካህን እንደመሆኑ («በሕይወት እንዲኖር የተመሠከረለት እርሱ ነው») ከአብርሃም ይበልጥ ነበር ማለት ነው። ጸሐፊው አብርሃም ብቻ አይደለም አሥራት የከፈለው ነው የሚለው። መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎች ሁሉ ራስ አዳም እንደሆነና በሆነ መንገድ ከእርሱ ጋር በኅደን ኅነት ሰዎች ሁሉ ኃጢአት እንደሠሩ እንደሚገልጸው ሁሉ፥ (ሮሜ 5:12)፥ የአብርሃም የልጅ ልጅ የነበረው ሌዊም በአብርሃም በኩል ለመልከ ጼዴቅ አሥራት ከመስጠቱ ክንዋኔ ጋር ተባብሯል። ስለዚህም፥ የመልከ ጼዴቅ ከአብርሃም መብለጥ ብቻ ሳይሆን በሕጉ መሠረት የካህናት ሁሉ አባት ከሆነው ከሌዊም እንደሚበልጥ ነው የሚታየው። ስለዚህም መልከ ጼዴቅ ከማናቸውም የአሮን ሊቀ ካህናት ይበልጣል።

ሁለተኛ፤ አብርሃም የመልከ ጼዴቅን በረከት ተቀብሏል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይባርኩ የነበሩት ካህናት ናቸው። ለአይሁዳውያን በረከት እግዚአብሔር ሰውዬውን እንዲባርክ ብቻ የሚነገር ቃል ሳይሆን እንደ ትንቢት ነበር የሚቆጠረው። ምክንያቱም ለካህኑ እግዚአብሔር ሥልጣን ስለሰጠው ሰውዬው በረከቱን እንደሚቀበል እርግጠኛ ነበር። በልማድ በረከት የሚሰጠው በሥልጣን አነስ ላለው እንደመሆኑ (ለምሳሌ፤ ሊቀ ካህናት ለሕዝቡ)፥ መልከ ጼዴቅ አብርሃምን መባረኩ፥ መልከ ጼዴቅ ከአብርሃምና ከልጆቹ የሚበልጥ መሆኑን ይገልጻል። ከመልከ ጼዴቅ ወገን ከነበረውም ከኢየሱስ ክርስቶስ ያነሱ ነበሩ።

የዚህ ክፍል ዋነኛ ትምህርት የኢየሱስ ክርስቶስ የሊቀ ካህንነት ሥልጣን በመልከ ጼዴቅ ደረጃ በመሆኑ ከአሮን ደረጃ ይበልጣል። ይህም የተረጋገጠው ለአሮን ክህነት

ሐላፊ የነበሩት አብርሃምና ሌዊ የበታች መሆናቸውን ለማሳየት አሥራት ከፍለዋል፥ በዚህም ላይ በረከትን ተቀብለዋል።

10ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከሌሎች ሃይማኖቶች መሪዎች ጋር ስናነፃፅረው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ነው?

ለ) ኢየሱስን ትተን ሌሎች ታላቅ የሃይማኖት መሪዎችን ስለመከተል ይህ ክፍል የሚያስተምረን ምንድን ነው?

ሐ) ሰዎች የሚከተሉዋቸውን የተለያዩ የሃይማኖት መሪዎችን ስም ዝርዝር ጻፍ።

ከኢየሱስ ጋር ስናነፃፅራቸው የሁሉም ሃይማኖት መሪዎችንና ሃይማኖቶቹም በሙሉ ከኢየሱስ የበታች ናቸው። ምንም እንኳ ወደ ሌላ ሃይማኖት ለመለወጥ ፈተና ቢገጥመንም የትኞቹም ቢሆኑ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነት ጋር ሊወዳደሩ እንደማይችሉ ማስተዋል ይገባናል።

# ሦስተኛ ቀን:- ዕብራውያን 7፡11-22

የጌታ ኢየሱስ መምጣት ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? እርሱ ያመጣው ለውጥ የሚያዘግም ነው? ይህን ነገር እራሳችንን በተመለከተ ልንጠይቅ ይገባናል! ይህም ብቻ ሳይሆን ብሉይ ኪዳንንም በተመለከተ ተመሳሳይ ጥያቄ መጠየቅ አለብን። የክርስቶስ መምጣት የእግዚአብሔርን አምልኮ በትንሹ ብቻ አይደለም የለወጠው። የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት እንዳለ ነው የተለወጠው። እንዲያውም ለአምልኮ ሥርዓቱ መሠረት የሆነ ቃል ኪዳን ነው የተለወጠው። በሙሴ ሕግ ተመሥርቶ የነበረው ብሉይ ኪዳን እንዳለ በአዲስ ኪዳን ተተካ።

11ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 7፡11-22 አንብብ።

ሀ) የቀድሞውን የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት ጸሐፊው እንዴት አድርጎ ነው የሚያብራራው? (ቁጥር 18)።

ለ) ከክህነቱ የሹመት ለውጥ አብሮ የሚመጣው ነገር ምንድን ነው?

ሐ) ለካህንነት ብቁ ከሚያደርጉት ነገሮች ላይ በአዲሱና በብሉይ ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

መ) በብሉይና በአዲሱ ክህነት ውስጥ የእግዚአብሔርን መሐላ በተመለከተ ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

አንዱ የዕብራውያን ጸሐፊ ዋና ዓላማ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በብሉይ ኪዳን ላይ ያስገኘውን ታላቅ ለውጥ ማሳየት ነው። ኢየሱስ ሲመጣ የነቢያትን ትንቢቶች ፈጽሟል። ሙሴን በመተካት የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ሆኗል። በሕግ ላይ የተመሠረተውን የመሥዋዕት ማቅረብ የአምልኮ ሥርዓት የነበረውንና የአምልኮውን ሥርዓት የሚመሩ ካህናት የነበሩትን ብሉይ ኪዳን ለውጦታል። እነዚህ ነገሮች በሙሉ

የተተከተ በኢየሱስ ነው። የመጨረሻውን መሥዋዕት ከከፈለ በኋላ ኢየሱስ ዘላለማዊ ሊቀ ካህን ሆነ፥ የተሻለም አዲስ ኪዳን መሠረተ።

በቁጥር 11 ላይ ጸሐፊው የድሮው ሊቀ ካህንነት አንድን ሰው ፍጹም ማድረግ ከቻለ ለምንድን ነው እግዚአብሔር በመዝሙር (110)፡4 አዲስ ሹመት ያለው ሊቀ ካህንነት ለማስነሣት ቃል የገባው? የሚል ጥያቄ ይጠይቃል። ጸሐፊው ፍጹም ሲል ሙሉ ተቀባይነትንና ምሕረትን ካስገኘ ማለቱ ነው። በመልከ ጼዴቅ ደረጃ ሌላ ክህነት ለመመሥረት ቃል መግባቱ የበፊቱ ክህነት በቂ አለመሆኑን ያሳያል። ክህነቱ የተመሠረተበት ሕግ እንኳ «ደካማና የማይጠቅም» እንደሆነ ነው የተገለጸው።

12ኛ ጥያቄ፡- ገላትያ 3፡23-25 አንብብ። የብሉይ ኪዳን ሕግ ሥራ ምን ነበር?

የብሉይ ኪዳኑ ሕግ ምንም ቢሆን ደኅንነትን አያስገኝልንም። ስለዚህም የምትደክም የሚል ስያሜ ተሰጠው፥ (ሮሜ 8፡3)። ከዚህ በተረፈ ግን ሌሎች ሁለት ተግባሮች ነበሩት፥ 1. ደኅንነት እንደሚያስፈልገን በመጠቆም ደኅንነት ሊያስገኝልን የሚችለውን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥርጊያ መንገድ አዘጋጀ። 2. ሰዎች ወደ ሌሎች የባሱ ኃጢአቶች እንዳይገቡ የመከላከል ተግባር ፈጽሟል። (ለበለጠ ማብራሪያ ትምህርት 4 ተመልከት)።

የአሪት ዘሌዋውያኑ ክህነትና ሕጉ በጣም የተዛመዱ ናቸው። ሕጉ ከተቀየረ በግድ ክህነቱም መቀየር አለበት ማለት ነው። ልክ እንደዚሁ ክህነቱም ከተቀየረ ሕጉም የግድ መለወጥ አለበት። (ለምሳሌ፡ አዲስ መሪ የአንድን አገር ሥርዓት ከተቆጣጠረ ፖሊሲዎቹም ይለወጣሉ። አዲስ የምርጫ ሕግ ሲፈጠር ደግሞ የአንድ አገር መሪ አብሮ ይለወጣል)።

በሙሴ በኩል በተሰጡት ሕጎቻቶች መሠረት እግዚአብሔር አሮንን ሊቀ ካህን አድርጎ ከሾመ ከብዙ ዘመን በኋላ እግዚአብሔር በመልከ ጼዴቅ ሥልጣን ያለ አዲስ ክህነት እንደሚያቋቁም ቃል ገባ! (መዝ./110/፡4)። በእርግጥ እግዚአብሔር በዚህ ቦታ ያመለከተ የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ኢየሱስ ከይሁዳ ወገን (የንጉሥ ወገን) ስለነበር በሕጉ መሠረት ሊቀ ካህን ለመሆን ምንም ሥልጣን አልነበረውም። ሕጉ ለክህነት ብቁ የሚያደርገው በአሮን የዘር ግንድ ውስጥ የነበሩት ነው እንጂ በሌላ ውስጣዊ በሆኑ መመዘኛዎች መሠረት አልነበረም። ሊቀ ካህኑ ትሑትና እግዚአብሔርን የሚፈራ መሆን አለበት አይልም። አንድ ሰው እናትና አባቱ ሌዋውያን የሆኑ እውነተኛ ከሌዊ ወገን የነበረ ሰው ከሆነና በቤተ ዘመድ ውርሱ ሁሉንም መመዘኛዎች ካሟላ ማንኛውም የአሮን ልጅ ሊቀ ካህን ለመሆን ይችላል።

13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የሊቀ ካህኑ መመዘኛ ዛሬ ካለው የቤተ ክርስቲያን መሪ መመዘኛ ጋር የሚለየው እንዴት ነው?

ለ) ዛሬ ካለው የቤተ ክርስቲያን መሪ አመራረጥ ዘይቤ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

እንደ መልከ ጼዴቅ ካለው አዲስ የክህነት ሹመት ጋር አዲስ ሕግና ቃል ኪዳን አስፈላጊ ነው ይላል ጸሐፊው። በአዲሱ ኪዳን ላይ በመመሥረት በሌሎች ሻል ባሉ መመዘኛዎች ምክንያት ኢየሱስ ሊቀ ካህን ሊሆን ይችላል። ለኢየሱስ ክርስቶስ ካህን መሆን መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ ዘላለማዊ መሆኑ ነው። በመዝ./110/፡4 ላይ ባለው የትንቢት ቃል መሠረት እንደምናየው ሊጠፋ የማይችል ሕይወት ነበረው፤ (ለዘላለም ካህን)። ስለዚህም ውጫዊ የሆኑት ነገሮች ላይ ከማተኮር አዲሱ ክህነት የሚያተኩረው ውስጣዊ ሕይወት ላይና የካህኑ ሥልጣን ላይ ነው። በተጨማሪም ሥራው በሚሞቱ ሰዎች ከሚፈጸም (ከአሮን ወገን የነበሩት ካህን ይሞቱ ስለነበር በየጊዜው መተካት ነበረባቸው) አዲሱ ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ስለሚኖር በሌላ ሳይተካ እርሱ ይሠራዋል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ክህነት ከአሮን የሚበልጥበት አንድ ሌላ ምክንያት አለ። እግዚአብሔር አሮንን የመረጠው በትእዛዙ (በሕጉ) ላይ ተመሥርቶ ነው እንጂ በመሐላ ላይ አልነበረም። የመልከ ጼዴቅ ሊቀ ክህነት ግን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ባደረገው ቃለ መሐላ ላይም የተመሠረተ ነበር፥ (ዕብራ.6፡17-18 ስናጠና ስለ መሐላ ያደረገውን ጥናት አስታውስ)። የእግዚአብሔር መሐላ ዘላለማዊ የሆነ ሊወገድ ወይም ሊለወጥ የማይችል ሊቀ ካህን ነው።

ይህ መሐላ የኢየሱስን ሊቀ ካህንነት ብቻ ሳይሆን የሚያረጋግጠው ለአዲሱም ኪዳን መሠረት ነበር። የክህነት ለውጥ የትዕዛዞችንና የቃል ኪዳንን ለውጥ ያስከትላል። የአዲስ ኪዳን ተያዥ ኢየሱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን እንደ ቃል ኪዳኑ መሥራች ሰውም እግዚአብሔርን እንደሚያስታርቅ አድርጎ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ለሚያምኑ እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል እንደሚፈጸምላቸው ሐላፊነቱን የወሰደ እርሱ በመሆኑ እንደ ተያዥም አድርጎ ነው የሚያቀርበው።

በአዲሱ ኪዳን ላይም በአዲሱ ክህነት ላይ በመመሥረት ነው «ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል» የምንለው። የቀድሞው ቃል ኪዳን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መሰናክል ላይ ትኩረት ያደርጋል። በሮቹና መጋረጃዎቹ ኃጢአተኛው ወደ ውስጥ እንዳይገባ ይከለክሉታል። አዲሱ ቃል ኪዳን ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ለኃጢአተኛው ክፍት አድርጎለታል ስለዚህም የተሻለ የተስፋ ቃል ነው።

የአይሁድ ክርስቲያኖች መሥዋዕት ወደ ማቅረቡ የካህናትንና የቤተ መቅደስ ሥርዓት ወደነበረው ወደ ድሮው የአምልኮ ሥርዓት ለመመለስ ያስቡ ነበር። ይህ ግን ካሁን ወዲያ ሊሆን የማይችል ሆነ። ኢየሱስ ከመጣ በኋላ ሌላ መሥዋዕት ማቅረብ በጭራሽ አያስፈልግም። አዲስ የክህነት ሹመት ተቋቁሟል፥ የአምልኮውም ሥፍራ በሰው ሠራሽ ሕንፃ ውስጥ ሳይሆን በመንግሥተ ሰማያት ዙፋን ፊት ነው የሚሆነው።

እንዴ በኢየሱስ ካመንን ሁሉም ነገር መለወጥ አለበት። ሕይወታችን መለወጥ አለበት፡- ምክንያቱም አሁን አዲስ ፍጥረቶች ሆነናልና ነው። ይህም ምግባራችን፥

አመለካከታችን፥ አስተሳሰባችንና ስሜታችን በሙሉ በትንሹ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ መለወጥ አለበት።

14ኛ ጥያቄ:- ይህ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ምሳሌዎች ስጥ።

አንዱ በኢየሱስ ካመንን አምልኮአችን መቀየር አለበት። የቀድሞው የአምልኮ ሥርዓታችን የነበረው ሃይማኖታችን የሆነ ቢሆንም በአዲሱ ተተክቷል። ኢየሱስ እንዳለው በመንፈስና በእውነት ማምለክ ይኖርብናል። ምንም እንኳ ጓደኞቻችን የእነርሱን ሃይማኖት እንድንይዝና ወደ ድሮው ሃይማኖታችን እንድንመለስ ቢፈልጉም ለመዳን ከፈለግን ሌላ አማራጭ ሊኖረን አይችልም። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል የሚፈጸምላቸው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ቃል ኪዳኑን ለሚቀበሉ ብቻ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጣ መዲህ ሁሉም ነገር ተቀይሯል።

15ኛ ጥያቄ:- የኢየሱስ መምጣት ዓለምን፥ ሕይወትን፥ ወዘተ... እንዴት እንደቀየረ ምሳሌ ስጥ።

# አራተኛ ቀን:- ዕብራውያን 7:23-28

ኢየሱስ እንደ ሊቀ ካህን ከአሮንና ከብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት እንደሚበልጥ ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት ለምን እንደሚሻልና የእርሱ ሊቀ ካህን መሆን ለእኛ ያስገኘልን ታላቅ ነገር እንመለከታለን። ይህ አስተሳሰባችን በኢየሱስ ላይ እንድናደርግና እንደ ሊቀ ካህናችን ወደ እርሱ ብቻ እንድንሄድ ያበረታታናል። በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ የሚማልድልን ጸሎታችን እንደተሰማና ለችግሮቻችን መልስ እንደምንቀበል ማረጋገጫውን የሚሰጠን እርሱ ነው። መንግሥተ ሰማያት እስክንደርስ ድረስ ያለምንም ችግር በሰላም እንደምንጠበቅ ማስተማመኛውን የሚሰጠን እርሱ ነው።

16ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 1:23-28 አንብብ።

ሀ) የቀድሞው ክህነት እንዴት እንደሆነ ነው የተገለጸው?

ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸው እንዴት ነው?

ሐ) ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህን በመሆኑ ያስገኛቸውን ውጤቶች በዝርዝር ጻፍ።

ጸሐፊው የብሉይ ኪዳን ካህናትን ድክመት በሁለት መንገዶች ይገልጸዋል።

1. የብሉይ ኪዳን ካህናት ሁልጊዜ በሞት ይቀጡ ነበር። አንድ ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈራ ጥሩ ሊቀ ካህን ይነሣል። ሰዎች ይታመኑበታል፥ ወደ እውነትም ይመራቸዋል። በኋላ ላይ ግን ስለሚሞት ሊቀ ካህንነቱ በሰዎች ዘንድ ለማይከበርና ክፉ ለሆነ ሰው ይሰጣቸዋል፥ (ለምሳሌ፥ ዔሊና ልጆቹ 1ኛ ሳሙ.2-4)። በሞት ምክንያት ሊቀ ካህኑ መተካት ነበረበት፥ ይህም የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት አንዱ ድክመት ነው።

2. የብሉይ ኪዳን ካህናት ኃጢአተኞች ነበሩ፤ ወይም ጸሐፊው እንደሚገልጸው «ደካሞች» ነበሩ። በየቀኑ ለራሳቸው ኃጢአትና ለእሥራኤል ሕዝብ ኃጢአት ሲሉ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። (ይህንን እውነታ በስርየት ቀን ከሚደረገው ሥርዓት ላይ ልታስታውሰው ትችላለህ)

በሕግ ላይ ከተመሠረቱት የአሮን ሊቀ ካህናት በአንፃሩ ደግሞ በመሐላ ላይ የጸናው ሊቀ ካህን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለ። ጸሐፊው እሱ ታላቅ ነው የሚልባቸውን የተለያዩ ምክንያቶችን አስተውል።

1. ለዘላለም ስለሚኖር የእርሱ ሊቀ ካህንነት መቼም ቢሆን አይቆምም። በምንም ዓይነት ለሌላው ሰው አይሰጥም። በአሁኑ ወቅት የእኛ ሊቀ ካህን በመሆን በአብ ፊት ቆሞ ስለ እኛ ይማልድልናል።

17ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ ስለእኛ ይማልድልናል ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህ ለእኛ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ምሳሌ በመስጠት አስረዳ።

2. ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ነው። ለሌላ አነጋገር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት የለበትም። ኃጢአትም ስላልነበረው ለራሱ ሲል መሥዋዕት ማቅረብ አልነበረበትም። የተቀደሰው ሕይወት ኃጢአተኛ ከሆነው ሰዎች በሙሉ ልዩ ያደርገዋል። ይህም ኢየሱስ እራሱን ከኃጢአተኞች ይለያል ማለት አይደለም። እንዲያው እርሱ ወዳጃቸው ነው። ነገር ግን የቅድስና ባህርይው ከሌሎች ሰዎች ሁሉ ልዩ ያደርገዋል። ይህም ኢየሱስ ያቀረበው መሥዋዕት ለሌሎች ነው እንጂ ለእራሱ አይደለም ማለት ነው። በየቀኑ በምድራዊ ካህናት ይደረግ እንደነበረው መሥዋዕት የእርሱ የሚደጋገም አልነበረም።

3. ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ ነው። ይህ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ መጠን በአብ ቀኝ ተቀምጦ የመንገሥ ሥልጣኑን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔርን ምድር ላይ ሳይሆን እዚያው እሱ በሚገኝበት ሥፍራ ነው የሚያገለግለው።

ለማጠቃለል! ጸሐፊው ፍጹም የሆነው ኢየሱስ ነው የሚለው። የሁሉንም ኃጢአት ዕዳ ሊሸፍን የሚችለውን ሕይወቱን በመስጠቱ እርሱ እራሱ በመፈተኑና በመሠቃየቱ የሰዎችን ችግር ስለሚገነዘብና ለእኛ ሲማልድልን በመኖሩ ለእኛ ዘላለማዊ ሊቀ ካህን ለመሆን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

የኢየሱስ ሊቀ ካህን መሆን ለእኛ የሚያስገኝልን ውጤት ምንድን ነው? የዕብራውያን ጸሐፊ «በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል» ይላል። ኢየሱስ የሚሰጠው ደኅንነት ጊዜያዊም የሚታደስም አይደለም። ማንም ሰው ሊቀማን አይችልም። ኢየሱስ ያለ ማቋረጥ እንደ ሊቀ ካህናችን ሆኖ ስለሚሠራ ደኅንነታችን የተረጋገጠ ነገር ነው።

18ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ በመንግሥት ሰማያት የእኛ ሊቀ ካህን በመሆኑ የምናገኛቸውን አንዳንድ በረከቶች ግለጽ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት ለምንድን ነው በጣም አስፈላጊና ልናስተውለው የሚገባ ትምህርት የሆነው? እራሱ እግዚአብሔር በመሆኑ አዳኛችን ይህን ያህል ኃይል ያለው ነው። ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ አዳኝ ነው የእግዚአብሔርን መንገድ ለእኛ የከፈተልን እርሱ ነው፥ ያለማቋረጥም የሚያማልደን እርሱ ነው። ሙሉ በሙሉ ሰው፥ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር በመሆኑ እግዚአብሔር እኛን በእርሱ በኩል ይቀርበናል! እርሱ ደግሞ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ይስባል። ደካማና ኃጢአተኛ የሆነው ሰው ዘላለማዊ ከሆነ አምላክ እንደሚገናኝ ማረጋገጫ የሚሆነን ይህን የመሰለ ሊቀ ካህን በመኖሩ ነው።

19ኛ ጥያቄ:- ሀ) ይህን ዓይነት አዳኝና ሊቀ ካህን ከሌላቸው ሃይማኖቶች ይህ የሚለየው እንዴት ነው? ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ ችግሮቻችንን የሚያከናውንልን በምን ዓይነት መንገድ ነው? (ቁ.26)።

**አምስተኛ ቀን**:- ትምህርቱን ከልስና ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) በትምህርታችን ላይ በመመርኮዝ መልከ ጼዴቅና ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ለ) 1. ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሰዎች ዘንድ (ለምሳሌ:- በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፥ በቤተ ክርስቲያንህ) ሰዎችም ይሁን ሌሎች አስታራቂ ሲሆኑ የሥራ ድርሻቸው ምንድን ነው ተብሎ ነው የሚገመተው?

2. የኢየሱስ አማላጅነት ወይም አስታራቂነትስ በምን መንገድ ነው የሚመሳሰለው? በምን ዓይነትስ መንገድ ነው የሚለየው?

3. ኢየሱስ ለእኛ ይማልድልናል ስንል ምን ማለታችን ነው?

ሐ) 1. ኢየሱስ ክርስቶስ በመምጣቱ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተቀየሩት ነገሮች ምንድን ናቸው?

2. ብሉይ ኪዳንን የምናጤንበት መንገድ እንዴት አድርጎ ነው የሚለወጠው?

3. ኢየሱስ በሕይወታችን ሲገባ የተቀየሩት ነገሮች ምንድን ናቸው?

መ) «በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡት ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል» ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህንን ካለፈው ሳምንት ትምህርት ጋር አነፃፅር።

ሠ) ኢየሱስ ሊቀ ካህን በመሆኑ በምናገኛቸው የተሻሉ ሁኔታዎች ላይ ተወያይ።

* በሌሎች የዕብራውያን ትምህርቶች ላይ የተማርከውን ነገር በሐሳብ ውስጥ አድርጋቸው።

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ አምስት

ዕብራውያን ምዕራፍ 8

## የመጀመሪያ ቀን:- ዕብራውያን 8፡1-2

በዕብራውያን ጥናታችን ጸሐፊው ሐሳባችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዲያተኩር አድርጓል። ኢየሱስ የመጨረሻው ታላቅ የእግዚአብሔር ራዕይ እንደሆነ አሳይቷል። በሰማያት ካሉት ታላላቅ ፍጥረታት (መላእክት) ሁሉ የበላይ ነው። በምድር ላይ ከተነሡት ታላላቅ መሪዎች ሁሉ የበላይ ነው (ሙሴ)። ከካህናቶቹም ሁሉ የበላይ ነው (አሮን)። ጸሐፊው ለትምህርቱ ትኩረት ያደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቁና የመጨረሻው ሊቀ ካህን በመሆኑ ላይ ነው።

(ለጸሐፊው) ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ ሊቀ ካህን መሆኑን የሚገልጸው ትምህርት ትልቅ መጽናኛ ሆኖለት ነበር። እንደ አሮን ደካማ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ በመንግሥት ሰማያት ለእርሱ ቆሞ የሚያማልድለት ስለነበረው የፈለገ ፈተና ወይም ችግር ቢገጥመውም እንኳ በሙሉ ልብ እንዲጋፈጠው ረድቶታል። ይህም በመሆኑ የአይሁድ ክርስቲያኖች ወደ ድሮው ምድራዊ ሊቀ ካህንና ምድራዊ መሥዋዕት ሥርዓት መመለስ የሚያደርጉት ማንኛውም ዓይነት ሙከራ ሊገባው አልቻለም።

1ኛ ጥያቄ:- ኃጢአተኛ ሰው ወደ ሆነው ሊቀ ካህን መሄድና ወደ አፍቃሪውና ሁሉን ቻይ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ልጅ በመሄድ መካከል ያለውን የጥቅም ልዩነት አነፃፅር።

2ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን ምዕራፍ 8 አንብብ። የምዕራፉን ዋና ዋና ትምህርቶች ዘርዝረህ ጻፍ።

3ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 8፡1፡2 አንብብ። በሰማያት ስላለው ሊቀ ካህናችን ጸሐፊው የተናገረውን የተለያዩ ነገሮች ዘርዝረህ ጻፍ።

ዕብራውያን 1-2፤ ከዚህ በፊት የነበሩት ምዕራፎች ሊቀ ካህን ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምሩትን ትምህርትን የሚያጠቃልል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው ዘላለማዊው ሊቀ ካህን እንደሆነ ካሳየ በኋላ ጸሐፊው መለስ ይልና ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሊቀ ካህን ሆኖ እንዴት በታላቅ ቃል ኪዳንና በታላቅ ቤተ መቅደስ ውስጥ ሆኖ ከበፊቱ የተሻለ መሥዋዕት በማቅረብ እንደሚያገለግል ይገልጽልናል፤ (ከምዕራፍ 8-10)።

4ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 2:14-18፥ 4:15-16፥ 7:26-27 ደግመህ ተመልከት ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ ሊቀ ካህን እንደመሆኑ በእኛ ስም ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ዋና ዋና ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ቀደም ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ ሊቀ ካህን እንደመሆኑ እንዴት አድርጎ ለኃጢአታችን መሥዋዕት እንዳቀረበና በሰማያት ላይ ያለውን እግዚአብሔር እንድንቀርብ እንዴት አድርጎ መንገዱን እንደከፈተልን ተመልክተናል። አሁንም ቢሆን ለእኛ ቆሞ በማማለድ ለደኅንነታችን ዋስትና ይሰጠናል። ምንም እንኳ ኃጢአት ባይኖርበትም ስለ እኛ ከማሰብ አይቆጠብም። እኛ ወንድሞቹ ነን። እርሱ ራሱ በመቸገሩና በመፈተኑ የእኛን መፈተንና መቸገር ውድቀትም ጭምር ይረዳልናል። ለእኛ የሚያዝን ሊቀ ካህን ነው።

በዕብራውያን 8:1-2 ላይ ጸሐፊው የሚጠቅሰው ሊቀ ካህን ይህን ዓይነት ነው። አሁን ይህ ሁሉን ቻይና አፍቃሪ የሆነው ሊቀ ካህንና ንጉሥም ካህንም ሆኖ በኃያሉና በግርማዊው ቀኝ ተቀምጦ ነግሦአል። እውነተኛይቱ ድንኳን የምትገኘውም በመንግሥተ ሰማይ ነው እንጂ በምድር ላይ አይደለም። ሰው ሠራሽና ዝቅተኛ በሆነችው ሳይሆን እርሱስ የሚያገለግለው የእግዚአብሔር መኖሪያ በሆነችው በእውነተኛይቱ ድንኳን ውስጥ በሰማይ ነው። በነገው ጥናታችን ይህን ታላቅ ሰማያዊ ድንኳን በሥፋት እንመለከተዋለን። ልክ እንደ ምድራዊዎቹ ካህናት መሥዋዕት በማቅረብ ላይ ያለ ሳይሆን እራሱን እንደመሥዋዕት የሚያቀርብበትን ሥራ ፈጽሞ ተቀምጧል።

ይህን ዓይነቱ ታላቅ ሊቀ ካህን እያለን ወደ ብሉይ ኪዳኑ የአምልኮ ሥርዓት የምንመለስበት ምንም ምክንያት የለም ይላል ጸሐፊው። እኛ ክርስቲያኖች ችግር ሲያጋጥመን እምነታችንን የምንክድበት ምንም ምክንያት የለም።

# ሁለተኛ ቀን:- ዕብራውያን 8:3-6

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን ለማምለክ ሦስት የሚያስፈልጉ ነገሮች ነበሩ። እነዚህ ነገሮች በሙሉ የተመሠረቱት እግዚአብሔር ከሙሴና ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር በገባው በድሮው ቃል ኪዳን ላይ ነው። አንደኛ፤ የአምልኮ ሥርዓቱን የሚመሩ መሪዎች መኖር ይገባ ነበር። እነዚህም ዋነኛው መንፈሳዊ መሪ የነበረው ሊቀ ካህንና የተቀየሩ ካህናት ናቸው።

ሁለተኛ፤ የአምልኮ ልማዶች ወይም ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበት መንገድ ነበር። እነዚህም እግዚአብሔር የእሥራኤል ሕዝብ እሱን እንዲያመልክ ሲባል እንዲያቀርብ ባዘዘው መሥዋዕቶች በኩል ነበር።

ሦስተኛ፤ የማምለኪያ ሥፍራ ነበር፤ ይህም የመገናኛው ድንኳን ነው። በዚህ ክፍል ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ነገሮች እንዴት እንዳሟላ ይገልጻል።

5ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 8፡3-6 አንብብ። በብሉይ ኪዳን ለአምልኮ አስፈላጊ የነበሩትን ሦስት ነገሮች ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አድርጎ እንዳሟላ ተናገር።

በዚህ ክፍል ጸሐፊው ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የሦስቱን ምዕራፎች ሐሳብ ያካተተ ገለጻ ይሰጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህን እንደ ሆነ ቀደም ብሎ ገልጾታል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካህኑ እግዚአብሔርን መቅረብ የሚችለውን «ስጦታዎችና መሥዋዕቶችን» በማቅረብ ብቻ ነው። እነዚህ ስጦታዎችና መሥዋዕቶች ለብሉይ ኪዳን አምልኮ ይጠቀሙባቸው የነበሩት አምስቱ መሥዋዕቶች እንደነበሩ ተመልክተናል። ሊቀ ካህን እንደመሆኑ ኢየሱስ ሊሠዋ የሚገባው ነገር ያስፈልገዋል። ወደ ኋላ የእርሱ መሥዋዕት የራሱ ሕይወት እንደነበርና እንደ ብሉይ ኪዳኑ የወይፈን ወይም የፍየል ደም እንዳልነበረ እናያለን።

ለብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት የሚፈቀድላቸው እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርሱ መሥዋዕት ማቅረብ ብቻ ነበር። በምድራዊው ቤተ መቅደስ ይገኙ እንደነበሩት ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት መቅረብ አይፈቀድለትም ነበር፥ ምክንያቱም ሕጉ ይህንን እንዲያደርጉ የሚፈቅድላቸው ከሌዊ ወገን ለሆኑና የአሮን ቤተሰብ ለነበሩ ብቻ ነበርና ነው።

ይህን ስንል ኢየሱስ የሚያገለግልበት ቤተ መቅደስ የለውም ማለታችን አይደለም። የዕብራውያን ጸሐፊ የአይሁድ ክርስቲያኖች ሁለት የማምለኪያ ቦታዎች ወይም ሁለት መገናኛ ድንኳን እንዳሏቸው ያሳስባቸዋል። አንደኛው የሌላኛው ምሳሌ ወይም ጥላ ነው።

6ኛ ጥያቄ፡- አሪት ዘጸአት 25፡40 ተመልከት። መገናኛውን ድንኳንና የማምለኪያ መሣሪያዎቹን ስለ መሥራት ለሙሴ የተሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበር?

የዕብራውያን ጸሐፊ ምድራዊው መገናኛ ድንኳን እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ተራራ ላይ ያሳየው ቤተ መቅደስ አምሳያ እንደነበረች ያስታውቃቸዋል። በተራራው ላይ ሙሴ ያሳየውን ዓይነት ቅርፅ ያላትን ቤተ መቅደስ እንዲሠራ እግዚአብሔር ብርቱ የሆነ መመሪያዎች ሰጥቶት ነበር። የተሠራው ድንኳን የሌላኛው አምሣያ ስለነበር እውነተኛው ድንኳን አልነበረም። ምንም እንኳን ሙሴ እውነተኛውን መገናኛ ድንኳን ወይም መንግሥተ ሰማያትን መመልከቱን እርግጠኛ ባንሆንም የሠራው ድንኳን ያንን ያየውን የሚመስል ነበር። (ለምሳሌ፥ ልጆች እውነተኛውን መኪና የሚመስል አድርገው ከእንጨትና ከጭቃ መኪና ይሠራሉ። ነገር ግን እነርሱ የሠሩት መኪና እውነተኛ አይደለም)። የአንድ ሰው ጥላ እራሱ ሰውዬው ሳይሆን ሰውዬውን የሚያመለክት እንደሆነ ሁሉ የምድራዊውም መገናኛ ድንኳን በመንግሥተ ሰማያት ያለውን እውነተኛ ድንኳን የሚያመለክት ነበር፥ (8፡2)። መንግሥተ ሰማያት ያለው ድንኳን የተሠራው በእግዚአብሔር ነው እንጂ በሰው አይደለም። ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህ ጊዜያዊ ምድራዊ መገናኛ ድንኳን ሳይሆን የዚያ የሰማያዊው ድንኳን ሊቀ ካህን በመሆኑ ከአሮን የሚበልጥ ሊቀ ካህን ነው።

7ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ዕብራውያን 9:24፥ ራዕይ 21:22፥ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚገኘው የት ነው?

የመገናኛው ድንኳን ዋና ዓላማ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንዲኖር ለማድረግ ነው። ሆኖም ምድራዊው ድንኳን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መኖሪያ የሆነው አምሳያ ነው። ልክ በመንግሥተ ሰማያት ላይ ያለውን ዓይነት ድንኳን እናያለን ብለን መጠበቅ አይኖርብንም። ነገር ግን የብሉይ ኪዳኑ መገናኛ ድንኳን የእግዚአብሔር መኖሪያ የሆነውን መንግሥተ ሰማያትን የሚያመለክት ነው።

8ኛ ጥያቄ:- ሀ) 1ቆሮ.3:16-17፥ 6:19 ተመልከት። ለክርስቲያኖች በእነዚህ ጥቅሶች የተሰጠው ስያሜ ምንድን ነው?

ለ) በዚህ በብሉይ ኪዳን መገናኛ ድንኳንና በሰማያዊው ድንኳን መካከል ያለው መመሳሰል ምንድን ነው?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚያስደንቁት ትምህርቶች መካከል አንዱ የእግዚአብሔር እንደ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ መቅደስ ባለ ቦታ አለመኖር ነው። በምትኩ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር የሚኖርባቸው ሁለት ቤተ መቅደሶች እንዳሉ ይናገራል፥ አንደኛ፤ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነው የእያንዳንዱ ክርስቲያን ልብ ነው። ሁለተኛ፤ የክርስቶስ አካል ወይም ክርስቲያኖች አብረው ለአምልኮ ሲሰበሰቡ ይህ እራሱ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይባላል፤ «ሁለትም ሦስትም ሆነው በተሰበሰቡበት በዚያ እገኛለሁ» (ማቴ.18:20)። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ናቸው። እያንዳንዱ ክርስቲያንና ክርስቲያኖች በህብረት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ልክ እንደ ቀድሞው መገናኛ ድንኳንና እንደ ወደ ፊቱ ሰማያዊ ቤተ መቅደስ እግዚአብሔር በዚያ ስለሚኖር ነው። መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ስላደረ እራሱ እኛነታችን የእግዚአብሔር ማምለኪያ ቦታ ነው።

9ኛ ጥያቄ:- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች መሆናችንና እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ የመኖሩ እውነታ ባህሪያችንንና የአምልኮ ሥርዓታችን እንዴት ሊለውጠው ይችላል?

የኢየሱስ ሊቀ ካህንነት ከአሮን የበለጠ ታላቅ የሆነው እርሱ እውነተኛው ድንኳን ባለበት በመንግሥተ ሰማያት በማገልገሉ ብቻ ሳይሆን የኢየሱስ ካህንነት ታላቅ ነው፥ ምክንያቱም በታላቁ ቃል ኪዳን ላይ በመመሥረቱም ነው።

እንዳየነው በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዋና ዋና ቃል ኪዳኖች አሉ። አንደኛ፤ አሪታዊው ቃል ኪዳን ነው። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ወደ ሕዝቡ እንዲያመጣለት የተጠቀመበት ሰው ሙሴ ነው። በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ «የአስታራቂነት ሚና የሚጫወተው ሙሴ ነው፤ (ገላትያ 3:19)። አስታራቂ የምንለው ሰው (በብሉይ ኪዳን የእሥራኤልን ሕዝብ) እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያቀራርበውን ነው። በሕዝብ ላይ በመመሥረቱም በዚያን ጊዜ የቃል ኪዳኑ አገልጋዮች የነበሩ የአሮን ካህናት ናቸው። ሆኖም አዲስ ቃል ኪዳን ደግሞ አለ፥ ይኸውም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጀመረ ነው። የዚህ ቃል ኪዳን «አስታራቂም» እራሱ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲሱ ቃል ኪዳን ሊቀ ካህን በመሆኑና አዲሱ ቃል ኪዳን ደግሞ ከቀድሞ የሚበልጥ በመሆኑ ከአሪቱ ቃል ኪዳን ሥር ከነበረው የአሮን አገልግሎት ይህ የኢየሱስ አገልግሎት ታላቅና የሚበልጥ ነው ማለት ነው።

አዲሱ ቃል ኪዳን ከቀድሞው የሚበልጠው የተሻሉ ቃል ኪዳኖች ላይ በመመሥረቱ ነው። የቀድሞው ቃል ኪዳን ግን የተመሠረተው በእሥራኤላውያን ታዛዥነት ላይ ነበር፥ (ዘጸአት 19፡5-8፥ 24፡3-8)። አዲሱ ቃል ኪዳን የተመሠረተው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ ነው። የቀድሞው ቃል ኪዳን ውጫዊ ነበር፤ ምክንያቱም ትኩረት ይሰጥ የነበረው የማምለኪያው ቦታ ላይ ምድራዊ በሆኑ መሥዋዕቶች ላይና በካህናቶቹ ክብር ላይ በመሆኑ ነው። አዲሱ ቃል ኪዳን ግን ትኩረት የሚሰጠው ውስጣዊ ለሆነው ለሰዎች ልብ ነው። በነገው ዕለት አዲስ ቃል ኪዳን ከቀድሞው እንዴት እንደሚሻል ሰፋ ባለ ሁኔታ እናጠናለን።

10ኛ ጥያቄ፡- በምን ዓይነት መንገድ ነው በውስጣዊ አስተሳሰባችንና አመለካከታችን ላይ ትኩረት የሚሰጠው አዲሱ ቃል ኪዳን፥ ውጫዊ ነገሮች ላይ ትኩረት ከሚሰጠው የድሮ ቃል ኪዳን የሚበልጠው?

## ሦስተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 8፡7-8

በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር የተመሠረተው በ1400 ዓመት ዓ.ክ.ል.በ. በሲና ተራራ ላይ ነበር። ለብዙ ዓመታት በእግዚአብሔርና በእሥራኤል ሕዝብ መካከል ለሚኖረው ግንኙነት ይህ መሠረት ሆኖ አገልግሏል። በ600 ዓመት ዓ.ክ.ል.በ. ግን ኤርምያስ በትንቢቱ «ከብሉይ ኪዳን» የሚበልጥ «አዲስ ኪዳን» እንደሚመጣ ተንብዮ ነበር፤ (ኤርምያስ 31፡31-34)። አንድ አዲስ ሕግ በድሮው ምትክ እንደሚደነግገው ዓይነት ወይም ደግሞ አዲስ መንግሥት የፊተኛውን ገርስሶ እንደሚመሠረተው ዓይነት ይህ አዲስ ኪዳንም የበፊቱን በመተካት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝበት መሠረት ሆኗል። ኤርምያስ አዲስ ኪዳን ይደረጋል ብሎ መተንበዩ አንድ ቀን እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ቃል ኪዳን በሌላ ይተካል ማለቱ ነው። በተጨማሪም የድሮው ኪዳን ድክመት ያለውና የሚተካ ነው ማለትም ነው።

11ኛ ጥያቄ፡- ትንቢተ ኤርምያስ 7፡16-21 አንብብ። የእሥራኤል ሕዝብ የቀድሞውን ኪዳን ምን ያህል ነው የጠበቀው?

ምንም እንኳ ይህንን ኪዳን ሲቀበሉ እንጠብቀዋለን ብለው ቃል ቢገቡም የእሥራኤላውያን ታሪክ የተሞላው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ባለመታዘዝ ነው። ብሉይ ኪዳን ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለበትና እንዴት መኖር እንደሚገባው የሚገልጽ ትዕዛዝን ያካተተ ነው እንጂ የሕዝቡን ልብ ቀይሮ እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ የሚያደርግ አልነበረም። ባለመታዘዛቸውም የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ ወረደ። ዋናው ችግር የሰዎቹ ልብ ነው፤ ቢሆንም የቀድሞው ኪዳን እራሱን የቻለ ድክመት ስለነበረው የግድ አዲስ ኪዳን አስፈለገ።

12ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 8፡7-13፤

ሀ) የቀድሞውን ኪዳን በተመለከተ አዲስ ኪዳን ይኖራል የሚለው የተሰፋ ቃል ምን ዓይነት ትርጓሜ ነው ያለው?

ለ) ብሉይ ኪዳንን ከአዲስ ኪዳን ጋር አነፃፅር፤ አዲስ ኪዳን የሚበልጠው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

አዲስ ኪዳን የተፈጸመው ከእሥራኤልና ከይሁዳ ቤት ጋር መሆኑን አስተውል። እንደምታስታውሰው ኤርምያስ ትንቢቱን ይናገር የነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ በሁለት መንግሥት በተከፋፈለበት ወቅት ነው። የሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥት ወድሞ ሕዝቡ ተበታትኗል። የደቡብ የይሁዳ መንግሥት ደግሞ ትንሽ ቆየት ብሎ ተደምስሶ ሕዝቡ ሊበታተን ነበር። ይህም ቢሆን፤ ኤርምያስ አሻግሮ ያይ የነበረው፥ ሁለቱ መንግሥታት በአዲስ ኪዳን ሥር ሆነው የሚጣመሩበትን ጊዜ ነበር።

ምንም እንኳ አዲሱ ኪዳን የሚፈጸመው ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ለመንገሥ መጥቶ እሥራኤላውያን ሁሉ ሲያምኑበት ቢሆንም አዲስ ኪዳን የተጠነሰሰውና የተጀመረው ኢየሱስ በሞተበት ጊዜ ነው። ከዕለታት አንድ ቀን አዲሱ ኪዳን ለአይሁዳውያን በፈጽምላቸውም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሌሎች ሕዝቦች በሙሉ የዚህ አዲስ ኪዳን ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑ ያስተምራል።

13ኛ ጥያቄ:- ሉቃስ 22፡17-22 አንብብ። ኢየሱስ ለጽዋው የሰጠው ስም ምንድን ነው?

አዲሱን ኪዳን በተመለከተ፤ አራት ዋና ዋና ቃል ኪዳኖች ተሰጥተዋል:-

1. በአዲሱ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ሕግጋቱን በሕዝቡ ልብና አዕምሮ ውስጥ እንደሚያስቀምጥ ቃል ገብቷል። እንደምታስታውሰው እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሕግጋቱን ይጽፍ የነበረው ድንጋይ ላይ ነበር። ያሁኑ ቃል ኪዳን ግን ሕጉን ሰዎቹ ልብ ውስጥ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ሕግጋቱን እንዲጠብቁ ፈቃደኛ የሚያደርጋቸው አዲስ ልብም ለሕዝቡ እንደሚሰጥ የሚገልጽ ነው።

14ኛ ጥያቄ:- ትንቢተ ሕዝቅኤል 11፡19-20 አንብብ። የእሥራኤልን ሕዝብ ልብ በተመለከተ እግዚአብሔር የሚገባው ቃል ኪዳን ምንድን ነው?

ይህን አዲስ ኪዳን ታላቅ የሚያደርገው ሕዝቡ አዲስ ልብ ስላላቸው እውነቱን መረዳቱ ብቻ ሳይሆን ለእውነቱ ታዛዥ የሚሆኑበትን ኃይል ማግኘቱም ጭምር ነው። ከውጭ በሚመጣ ማስጠንቀቂያና ቅጣት ምክንያት ሳይሆን ታዛዥ የሚሆኑት ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅርና ከልባቸው ከመነጨ የመታዘዝ ፍላጎት የተነሣ ነው።

2. የእግዚአብሔር ሕዝብ በሙሉ እግዚአብሔርን በደንብ ያውቀዋል። ጸሐፊው የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ስለሚገልጹት እውነታዎች ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ስላለ ጥብቅ የሆነ የግል ግንኙነት ነው። ብዙ ጊዜ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርቶች ይረዱና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሁሉን ከሚችለው አምላክ ጋር የግል ግንኙነት አይኖራቸውም። ስለዚህም ስለ እግዚአብሔር ያውቃሉ እንጂ፥ በግላቸው አያውቁትም። ክርስቲያን ግን እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን የሚያውቀው እራሱም

በእግዚአብሔር የታወቀ ይሆናል፤ (ገላትያ 4፡9)። ስለዚህም እንደ ካህን ያለ መሐከል ላይ የሚቆም አስታራቂ አያስፈልገንም።

15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰዎች እውነቱን እያወቁ ኢየሱስን የማወቅ ባህርይ ሳይዙ የቀሩበትን ዓይነት ሁኔታ አይተህ ታውቃለህ?

ለ) ስለ ሕይወታቸው እስቲ ግለጽ።

ሐ) ለምንድን ነው ይህ የሆነው?

3.ካሁን ወዲያ እግዚአብሔርንና ትዕዛዙን ያለማወቅ ኃጢአት አይኖርም። በምትኩ ግን እግዚአብሔር እራሱ ሕዝቡ ታዛዥ እንዲሆን ያስተምረዋል። ምንም እንኳ ይህ እውነታ በከፊልም ቢሆንም በአማኙ ልብ ውስጥ በሚሠራው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ተፈጻሚነት ቢያገኝም ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት የሚያገኘው ኢየሱስ ወደ ምድር ለመንገሥ ከመጣና ሰውን በሙሉ በግሉ ሲያስተምር ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሕግ ዕውቀት ዓለም አቀፍ ስለሚሆነው ጥቂት ሰዎች ሳይሆኑ መላው የእግዚአብሔር ሕዝብ እውነቱን ይረዳል። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ካህናት ብቻ ነበሩ ሕጉን ጠንቅቀው የሚያውቁት፥ ባሁኑ ጊዜ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሲረዱ ብዙው ሕዝብ ግን የእግዚአብሔርን እውነት አያውቅም፥ ከላይ የጠቀስነው ከዚህ ለየት የሚል ነው።

16ኛ ጥያቄ፡- 1ዮሐ.2፡20፥27 አንብብ።

ሀ) ለአማኞች እውነቱን የሚያስተምረው አስተማሪ ማነው?

ለ) ለተወሰኑ ሰዎች እግዚአብሔር የማስተማርን ስጦታ ሰጥቷል ሲል ምን ማለቱ ነው? (ኤፌሶን 4፡11-13)።

አንዱ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የኢየሱስን በአማኙ ሕይወት መኖር እውን ማድረግና ለአማኙ የክርስትናን እውነታ ማስተማር ነው። ከተለያዩ ሥፍራዎች እንደምናየው ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ሌሎችን እንዲያስተምሩ አስተማሪዎችን ሾሟል፥ (ማቴ.28፡19-20፥ ኤፌ.4፡11፥ 1ጢሞ.4፡11)። ስለዚህም ዮሐንስ ሰዎች የሆኑ አስተማሪዎች አያስፈልጉንም አላለም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሰዎች እንዲጽፉለት ያደረገውን ቃል ይወስድና ክርስቲያኖች በሙሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል ቆጥረውት በሕይወታቸው ተግባራዊ እንዲያደርጉት ይረዳቸዋል። በአዲስ ኪዳን ፍጻሜ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ አዳዲስ እውነቶች መግለጽ ሳይሆን በሚያጋጥሙን የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል እውነታ እንዴት ተግባራዊ እንደምናደርግ ማሳየት ነው።

17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መንፈስ ቅዱስ አስተማሪ በመሆኑ የሰው አስተማሪ አያስፈልገንም ወይም የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት የለብንም ብለው የሚያስተምሩ ሰዎችን በዝርዝር ጻፉ።

ለ) በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በመጠቀም ይህ አመለካከት የተሣሣተ መሆኑን አሳይ።

4. በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሙሉ በሙሉ የሆነ የኃጢአት ይቅርታ ይኖራል። ምንም እንኳ ጊዜያዊ የሆነ የኃጢአት ይቅርታ ቢኖርም ኃጢአተኛ መሆናቸውን የሚያስታውሳቸው በየቀኑ የሚሠዉት መሥዋዕት ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ሲሞት ግን፥ የኃጢአትን ዋጋ ሙሉ በሙሉ በመክፈሉ የተሟላ የኃጢአት ይቅርታ ተገኝቷል። «ኃጢአታቸውን ደግሜ አላስብም» ሲል ስለ ኃጢአታቸው ተጠያቂ አይሆኑም፥ ቅጣትም አይደርስባቸውም ማለቱ ነው። ይህ ለእኛ ታላቅ የሆነ ቃል ኪዳን ነው። ምንም እንኳ በሥራችን ላይ የተመሠረተ ፍርድና ሽልማት ብንቀበልም ስለፈጸምናቸው ኃጢአቶች ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ዓይነት ፍርድ አንቀበልም፤ (ዮሐ.3፡18፤ ሮሜ 8፡1)። ይህ ሁሉ ምሕረት የተገኘው በመስቀሉ ነው።

13ኛ ጥያቄ፡- እነዚህ አራት በረከቶች፥ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚታዩት እንዴት ነው?

ለአዲሱ ኪዳን ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ አለመስጠቱን አስተውል። በብሉይ ኪዳን ግን በረከት የሚገኘው ሕግጋቶቹን ከጠበቁ «ብቻ» ነው፤ አዲስ ኪዳን ግን ለእግዚአብሔር ሕዝብ በረከት እንደሚሰጥ ብቻ ነው የሚገልጸው። እነዚህን የተስፋ ቃሎች ለሕዝቡ እንደሚሰጥ እግዚአብሔር ቃል ስለገባ በእርግጥ የሚሆኑና በሕዝቡ ጥረት ላይ የተመሠረቱ አይደሉም።

ከዚህ በፊት እንዳየነው የዕብራውያን መጽሐፍ የተጻፈው ከ70 ዓ.ም. ትንሽ ቀደም ብሎ ነበር። እንደምታስታውሰው ደግሞ እስከ 70 ዓ.ም. ድረስ አይሁዳውያን በቤተ መቅደሶቻቸው በመሥዋዕትና በሊቀ ካህናት ይጠቀሙ ነበር። በሌላ አነጋገር ብሉይ ኪዳን አሁንም ገና ይከተሉ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት አዲስ ኪዳን ተመሠረተ። ይህም ብሉይ ኪዳንን ተካ። ስለዚህም ጸሐፊው የቀድሞውን ኪዳን ሕግጋቱንና ሥርዓቱን «አርጊና ውራጅ» በመጥፋት ላይ ያለ ይለዋል። ምናልባትም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጸሐፊው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ቤተ መቅደሱና የአምልኮ ሥርዓቶቹ በሙሉ እንደሚጠፉ ሊያይ ችሏል።

በአዲሱ ኪዳን አማካይነት፥ ውጫዊ ከሆኑ የአምልኮ ሥርዓቶች ተገላግለናል። አሁን እውነተኛ አምልኮ በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ውስጥ ነው የሚካሄደው። አምልኮው «በመንፈስና በእውነት ነው፤ (ዮሐንስ 4፡23)። ይህም ሆኖ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ከመከተል አምልኮን የሥርዓት ነገር ያደርጉታል። እግዚአብሔርን ከልባችን የማናመልከው ከሆንና ዝም ብለን በሥርዓት የተጠመድን ከሆነ ልክ እግዚአብሔርን በልባቸው ሳይሆን በአፋቸው ብቻ ያመልኩ እንደነበሩት እንደ እሥራኤላውያን እንሆናለን። ይህን ስንል ምንም ዓይነት የአምልኮ ሥርዓት መኖር የለበትም ማለት አይደለም፤ (1ቆር.14፡40)። በምናመልክበት ጊዜ ምስጋናችን ከልብ የመነጨ እንዲያው እንደው ዝም ብሎ ከልምድ ብቻ የሆነ መሆን የለበትም።

19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ የሚገኙትን የተለያዩ የአምልኮ ሥርዓቶች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) እነዚህ ሥርዓቶች ከልብ ሳይሆን ዝም ብለው በልማድ ብቻ ሊከናወኑ የሚችሉት እንዴት ነው?

ሐ) አምልኮውን በከንፈር ብቻ ሳይሆን ከልብም ጭምር ለማድረግ ሲባል ምን ነገሮች ናቸው በአምልኮህ ውስጥ መለወጥ ያለባቸው?

# አራተኛ ቀን፡- ክለሳ

20ኛ ጥያቄ፡- ከዕብራውያን በተማርከው ትምህርት ላይ በመመርኮዝ ዋና ዋናዎቹን ትምህርቶች በዝርዝር ጻፍ።

የዕብራውያን መጽሐፍ ትምህርቶች በሁለት ዋና እውነታዎች ሊከፈሉ ይችላሉ። አንደኛ፤ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነት በተለይ ከብሉይ ኪዳን በማነፃፀር የሚያስተምረው ትምህርት ነው። እንዳየነው፡-

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው የተሰጠው መጨረሻው የእግዚአብሔር ራዕይ እንደመሆኑ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ይበልጣል፤ (1፡1-3)።

2. ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥተ ሰማያት ላይ ካሉት መላእክት በላይ ነው፤ (1፡4-14)

3. ኢየሱስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን መሪ ከነበረው ከሙሴ ይበልጣል፤ (3፡1-6)

4. ሊቀ ካህኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳኑ ሊቀ ካህን ከአሮን ይበልጣል፤ (5፡1-10፥7)። ይህ ነበር፥ የዕብራውያን መጽሐፍ የመጀመሪያ ትኩረት፤ ስለዚህም ስለ ሊቀ ካህኑ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ ብዙ የተሰጡ እውነታዎች አሉ። እስካሁን እንደተመለከትነው ኢየሱስ የእኛ ሊቀ ካህን ለመሆን ብቁ የሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-

ሀ) እስከ ዘላለም ይኖራል (እንደ መልከ ጼዴቅ)፤ ስለዚህም የእርሱ ሊቀ ካህንነት የማይለወጥና የማይሻር ነው።

ለ) ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔርና ሰው በመሆኑ፥ እግዚአብሔርን ከሰው ጋር ሰውንም ከእግዚአብሔር ለማስታረቅና አማላጅ ለመሆን ብቁ ነው።

ሐ) ነውር የሌለውን እራሱን ለኃጢአት መሥዋዕት አቀረበ። ይህ የሚቀርበው አንዴ ብቻ ነው እንጂ መደጋገም አይኖርበትም።

መ) ሙሉ ሰው በመሆኑ እንደማንኛውም ሰው ፈተና ገጥሞታል፥ ፈተና ውስጥ ያሉትንም እንዴት እንደሚረዳቸው ያውቃል።

ሠ) መከራንም ስለቀመሰ ወደ መከራ መግባትን ጠንቅቆ ያውቃል።

ረ) ኃጢአት የለበትም ስለዚህም ለእራሱ መሥዋዕት ማቅረብ የለበትም። የሚያቀርበው ለእኛ ብቻ ነው።

ሰ) ያለማቋረጥ የእኛ አማላጅ ሆኖ ስለሚሠራ ሙሉ ደኅንነት እንደምናገኝ ያረጋግጥልናል።

ሸ) የሚሠራውም እግዚአብሔር በሚገኝበት ሥፍራ ነው እንጂ በምድር ላይ አይደለም።

ቀ) እራሱን እንደ መሥዋዕት የማቅረቡን ሥራ ከፈጸመ በኋላ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል። በሙሉ ሥልጣንም ይገዛል።

5. ኢየሱስ የተሻለው የአዲስ ኪዳን አማላጅ ነው እንጂ የብሉይ ኪዳኑ አይደለም(ምዕራፍ 8)።

የአይሁድ ክርስቲያኖች ወደ ቀድሞው አምልኳቸው መመለስ የፈለጉት ከአይሁዳውያን ወንድሞቻቸው ስደት ለማምለጥ ሲሉ ነበር። ስለዚህም ጸሐፊው የብሉይ ኪዳን አምልኮ ያስፈልጓቸው የነበሩ ምክንያቶች በሙሉ በሌላ ታላቅ በሆነ ነገር እንደተተኩ ያሳያቸዋል። የብሉይ ኪዳንን አምልኮ መሠረቶች በመውሰድ የሚወክሏቸውን ነገሮች በእነርሱ ፋንታ ጣልቃ ያስገባል።

እነዚህን ሁለት ሰንጠረዦች እንፃፀር። አንዱ የብሉይ ኪዳን ሌላኛው ደግሞ የአዲስ ኪዳን ነው:-




መጀመሪያ ላይ መመሳሰላቸውን አስተውል። አዲሱም የቀድሞው ኪዳን የተመሠረቱት ከእግዚአብሔር ጋር በተደረገ ቃል ኪዳን ላይ ነው። በሁለቱም ላይ ለኪዳኖቹ መነሻ የሆነው የእግዚአብሔር ከሰው ጋር ኅብረት መፈለግ ነው። ለአምልኮው መሠረት የሚሆኑት እነዚህ ኪዳኖች ናቸው። የአምልኮው መሠረት ተመሣሣይነት

አለው። ሁለቱም፤ የተመሠረቱ በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ሲሆን (እንደምስሶ በሚመስሉ)። ሁለቱም ድንኳን ወይም ቤተ መቅደስ ካህናትና መሥዋዕቶች ያስፈልጓቸዋል።

ይህም ሆነ የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ከአዲስ ኪዳኑ የአምልኮ ሥርዓት የበታችነት ባህርይ ነበረው። ብሉይ ኪዳን የተመሠረተው ያለ ልብ ለውጥ ሊጠብቁ በሚገባቸው ሕግጋት ላይ ነበር። አዲስ ኪዳን ግን የልብ ለውጥን ይሰጣል፥ የተመሠረተውም በፍቅር ላይ ነው። የብሉይ ኪዳን ካህናት ኃጢአተኞች ነበሩ። አዲስ ኪዳን አንድ ካህን ብቻ ነበረው ይህም ኃጢአት የሌለበት ከጥንት ጀምሮ የሚኖረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። የብሉይ ኪዳን አምልኮ ይፈጸም የነበረው ሰው ሠራሽ በሆነ ቤተመቅደስ ውስጥ ነበር። የአዲስ ኪዳን አምልኮ ደግሞ የሚፈጸመው የእግዚአብሔር ዙፋን በሚገኝበት በመንግሥተ ሰማያት ነው። በብሉይ ኪዳን ጊዜያዊ የሆነ የኃጢአት መንጻት ያስገኝ የነበረውን የእንስሳ መሥዋዕት ያለማቋረጥ መደረግ ነበረበት። አዲስ ኪዳን ግን የተመሠረተው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በተሠዋው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ነው። ስለዚህም ምንም እንኳ ትንሽ የአምልኮ ጭላንጭል ቢታየንም ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ለእኛ በአዲሱ ኪዳን ሥር ላለነው ሰዎች የሚኖረውን እውነተኛ አምልኮ ነው።

ሁለተኛውና ዋነኛው የዕብራውያን መጽሐፍ ትምህርት ደግሞ አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለውን እምነቱን እንዳይተው የሚያስጠነቅቀው ክፍል ነው፤ (2፡1-4፥ 3፡7-4፡13፥ 5፡11-6፡12)። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ባለማመናቸው እግዚአብሔር ተስፋ ያደረገላቸውን የከነዓን ዕረፍት ሳያገኙ የሞቱትን አይሁዳውያን ምሳሌነት መከተል የለብንም። ከኢየሱስ ክርስቶስ ለመሸሽ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት እንዱን የደኅንነት መንገድ እንደመተው ነው የሚቆጠረው፤ በዚህም ምክንያት ሌላ ምንም ዓይነት ተስፋ የለም።

የአይሁድ ክርስቲያኖችና ዛሬ የሚገኙ የብዙ ክርስቲያኖች ችግር ኢየሱስ ክርስቶስ የመካድና ወደ ዓለም የመመለስ ፈተና ነው። ለሁላችንም ቢሆን ጸንተን እንድንቆም የሚያስፈልገን ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነና ሌላ የደኅንነት መንገድ አለመኖሩን መገንዘቡን ነው። ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚወስዱት መንገዶች ውስጥ አንድ አማራጭ አይደለም። እንዲያውም እርሱ በጣም ልዩ ነው፡- ወደ አብ የሚወስደው ብቸኛ መንገድ ነው። ስለዚህም ኢየሱስን ለመካድ የምናደርገው ማንኛውም ዓይነት ሙከራ ከእውነቱ የሚያርቀንና ኢየሱስን ዳግመኛ እንዳናምን ልባችንን ወደ መደንደኑ ሊያደርስ የሚችል ነገር ነው። አንዱ የእውነተኛ አማኝ ምልክት እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ መጽናቱ ነው።

21ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የተጠቀሱትን ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በመጠቀም እንዴት አድርገህ ምዕመናኖቹ እምነታቸውን ሳይክዱ በታማኝነት ጸንተው እንዲቆሙ ልታበረታታቸው የምትችልበትን መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

**አምስተኛ ቀን**፡-ትምህርቱንከልስናለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) በመንፈሳዊ ሕይወታችን ሊቀ ካህናችን አሮን ከሚሆን ኢየሱስ በመሆኑ ሊያጋጥመን የሚችለውን የተሻለ ነገር በዝርዝር ጻፍ።

ለ) የጠቀስናቸውን ሦስቱን ቤተ መቅደሶች ማለትም በብሉይ ኪዳኑ መገናኛ ድንኳን መንግሥተ ሰማያትንና የአማኞች ልብን አነፃፅር። የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? የሚለያዩትስ?

ሐ) የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት እንዴት ነው የአዲስ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ምሳሌና ጥላ የሚሆነው?

መ) 1. አዲሱ ኪዳን ከቀድሞው ኪዳን የሚበልጠው እንዴት ነው?

2. በቀድሞው ኪዳን ሥር ብንኖርና የአሁኑ አምልኳችን ተስፋችንና ደኅንነታችን ባይኖሩ ለእኛ ምን ልዩነት ይኖር ነበር?

ሠ) 1. በ1ኛዮሐ.2፡27 አስተማሪ አያስፈልግም ሲል ምን ማለቱ ነው?

2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ አስተማሪ ያለው ሥፍራ ምንድን ነው?

3. በማስተማሩ ዘርፍ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ምንድን ነው?

4. ሁለቱ አብረው የሚሠሩትስ እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ ስድስት

ዕብራውያን ምዕ. 9

## የመጀመሪያ ቀን፡- ዕብራውያን 9፡1-10

በዕብራውያን ጥናታችን ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዓት በተሻለ ነገር እንደቀየረው ያሳየናል። የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ያተኩር የነበረው ውጫዊ የሆኑ ነገሮች ላይ ሊቀ ካህን መገናኛ ድንኳንንና የእንስሳ መሥዋዕትን ያካተተ ነው። እነዚህ የአምልኮ ሥርዓቶች የሚፈጸሙት በሕጉ መሠረት ነው፥ ሆኖም የሕዝቡ ልብ ከእግዚአብሔር የራቀ ሊሆን ይችላል። በአዲስ

**አምስተኛ ቀን**፡-ትምህርቱንከለስናለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) በመንፈሳዊ ሕይወታችን ሊቀ ካህናችን አሮን ከሚሆን ኢየሱስ በመሆኑ ሊያጋጥመን የሚችለውን የተሻለ ነገር በዝርዝር ጻፍ።

ለ) የጠቀስናቸውን ሦስቱን ቤተ መቅደሶች ማለትም በብሉይ ኪዳኑ መገናኛ ድንኳን መንግሥተ ሰማያትንና የአማኞች ልብን አነፃፅር። የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? የሚለያዩትስ?

ሐ) የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት እንዴት ነው የአዲስ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ምሳሌና ጥላ የሚሆነው?

መ) 1. አዲሱ ኪዳን ከቀድሞው ኪዳን የሚበልጠው እንዴት ነው?

2. በቀድሞው ኪዳን ሥር ብንኖርና የአሁኑ አምልኳችን ተስፋችንና ደኅንነታችን ባይኖሩ ለእኛ ምን ልዩነት ይኖር ነበር?

ሠ) 1. በ1ኛዮሐ.2፡27 አስተማሪ አያስፈልግም ሲል ምን ማለቱ ነው?

2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ አስተማሪ ያለው ሥፍራ ምንድን ነው?

3. በማስተማሩ ዘርፍ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ምንድን ነው?

4. ሁለቱ አብረው የሚሠሩትስ እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ ስድስት

ዕብራውያን ምዕ. 9

## የመጀመሪያ ቀን፡- ዕብራውያን 9፡1-10

በዕብራውያን ጥናታችን ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዓት በተሻለ ነገር እንደቀየረው ያሳየናል። የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ያተኩር የነበረው ውጫዊ የሆኑ ነገሮች ላይ ሊቀ ካህን መገናኛ ድንኳንንና የእንስሳ መሥዋዕትን ያካተተ ነው። እነዚህ የአምልኮ ሥርዓቶች የሚፈጸሙት በሕጉ መሠረት ነው፥ ሆኖም የሕዝቡ ልብ ከእግዚአብሔር የራቀ ሊሆን ይችላል። በአዲስ

ኪዳን ውስጥ ግን እግዚአብሔር ትኩረት የሚሰጠው ውጫዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ሳይሆን ውስጣዊ በሆነው የሰው ልብ ላይ ነው። ስለዚህም ውጫዊ የነበሩትን የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓቶች በመንፈሳዊ ምሳሌዎቻቸው ቀየራቸው። ደካማ የሆነውን ሊቀ ካህን ዘላለማዊ በሆነው ሊቀ ካህን መገናኛ ድንኳን ይወክለው በነበረው በመንግሥተ ሰማያት ተካው፤ (ምዕራፍ 9)። ያለማቋረጥ ይሠዋ የነበረው የእንስሳ መሥዋዕት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሥዋዕት በሆነው በልጁ መሥዋዕት ተካው(ምዕራፍ 10)። ለብሉይ ኪዳን አምልኮ መሠረት የነበረውን ነገር በአዲሱ ኪዳን ቀይሮታል፥ (ምዕራፍ 8)።

1ኛ ጥያቄ፡- በምን ዓይነት መንገድ ነው አንዳንድ ክርስቲያኖች ውስጣዊ በሆነው የአንድ ሰው ልብ ላይ ከማተኮር ውጫዊ በሆነው አምልኮና የክርስቲያናዊ አኗኗር ላይ የሚያተኩሩት? ምሳሌዎችን ስጥ።

የሚያሳዝነው ብዙ ክርስቲያኖች ከውስጣዊ ነገሮች ይልቅ ትኩረት የሚሰጡት ውጫዊ ለሆኑት የክርስትና ነገሮች ነው። ትልቅ ትኩረት የምንሰጠው የማምለኪያ ቦታ ለሆነው ለቤተ ክርስቲያን ነው። ነገር ግን እውነተኛ አምልኮ በልባችን ውስጥ እንደሚካሄድ እንዘነጋለን። ወደ ዘላለማዊው ካህናችን ወደ ኢየሱስ ከመሄድ እንዲያማክሩን ወደ ምድራዊ መሪዎች ዓይናችንን እናዞራለን። በአንድ ሰው ልብ የሚካሄዱትን ለውጦች ከማየት የሰውየው ውጫዊ ምግባሮች ላይ እናተኩራለን። ውስጣዊ የሆኑ ለውጦች ካሉ ምግባራችንም አብሮ ይለወጣል። ሰዎችን ለማስደሰት ስንል ውስጣዊ የሆነው አስተሳሰባችንን፥ ስሜታችንን፥ ፍላጎታችንን፥ ወዘተ... ሳይለወጥ፥ ሳይቀየር፥ ውጫዊ ባህሪያችንን ልንቀይር እንችላለን። ስለዚህም ሁልጊዜም ቢሆን ትኩረት መስጠት ያለብን ልባዊ ለውጦች ላይ ነው።

2ኛ ጥያቄ፡- ውስጣዊ የሆነ ለውጥን የማያመለክቱ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንህ ከአባላትዋ አጥብቃ የምትጠይቃቸውን አንዳንድ ውጫዊ የሆኑ ምግባሮችን በመጥቀስ ማብራሪያ ስጥ።

3ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን ምዕራፍ 9 አንብብ። ዋና ዋናዎቹን ትምህርቶች በዝርዝር ጻፍ።

በዕብራውያን ምዕራፍ 9 ላይ ጸሐፊው የሚያመለክተው የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥፍራ የነበረውን መገናኛውን ድንኳን ነው። ከታላቁ የሰለሞን ወይም የሄሮድስ ቤተ መቅደስ ይልቅ መገናኛ ድንኳኑን የመረጠበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። አንደኛ፤ ለሌሎቹ ቤተ መቅደሶች መሠራት መሠረት የሆነው መገናኛው ድንኳን ነው። ሁለተኛ፤ መገናኛው ድንኳን ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ መንቀሳቀሱ ጊዜያዊ እንደነበር ያመለክታል። ይህም ለእሥራኤላውያንም ዋናው ነገር ውጫዊው ሕንፃ ሳይሆን በመካከላቸው የሚኖረውን ታላቅ አምላክ ማምለክ እንደሆነ አስተምሮአቸዋል።

4ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 9፡1-10 አንብብ።

ሀ) በቅዱስ ቦታ አሉ ተብለው የተዘረዘሩትን የተለያዩ የአምልኮ ዕቃዎች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ያሉትን የአምልኮ ዕቃዎች ዝርዝር ጻፍ።

ሐ) በቅድስተ ቅዱሳኑ ያሉት የአምልኮ ዕቃዎች በፊት ካጠናነው ለየት የሚሉት እንዴት ነው?

መ) የመገናኛውን ድንኳን አምልኮ እንዴት አድርጎ ነው የገለጸው?

ሠ) ጸሐፊው የቀድሞው ዓይነት አምልኮ ለምን ያህል ቆየ ነው ያለው?

መገናኛው ድንኳን የተሠራው በቀድሞ ኪዳን ላይ ተመሥርቶ ነው፤ (ኦሪት ዘጸአት ከምዕራፍ 25-40)። ጸሐፊው ስለ መገናኛው ድንኳን ከቁጥር 1-5 ገለጻ ይሰጣል።

መገናኛው ድንኳን ሁለት ክፍሎች ነበሩት። እነዚህን ሁለት ክፍሎች የሚለይ ትልቅ መጋረጃ ነበር። የመጀመሪያው ክፍል ሁለት የተለያዩ ዕቃዎች ይገኙበታል ተብሎ ተገልጿል። አንደኛው መቅረዙ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የመሥዋዕቱ ሕብስት የሚቀመጥበት ጠረጴዛ ነው።

በሁለተኛው ክፍል፤ ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ወርቃማው የዕጣን መሠዊያና (የወርቅ ማዕጠንት) የኪዳኑ ታቦት ይገኙበት ነበር። ካለፈው ጥናታችን እንደምናስታውሰው የወርቁ ማዕጠንት የነበረው በቅዱሱ ቦታ ውስጥ ነው እንጂ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ አልነበረም። ታዲያ ለምንድን ነው ጸሐፊው በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ነው ያለው ብሎ የጠቀሰው? በአመዛኙ ይህን ያለው በስርየት ቀን በዓል ላይ ይህ የወርቅ ማዕጠንት የሚጫወተው ትልቅ ሚና ስለነበረው ነው። በብሉይ ኪዳን ይህ የወርቅ ማዕጠንት ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር አብሮ በጣም የተቆራኘ ነገር ነው፤ (ዘጸአት 30፡6፥ 40፡5)። ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ሲገባ፥ ከወርቁ ማዕጠንት ከሰልና ዕጣን ይወስድ ነበር። ሊቀ ካህኑም በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ብቻ ሳይሆን በወርቁ ማዕጠንትም ላይ ደም ይረጭ ነበር። ስለዚህ ለአይሁዳውያን እነዚህ ሁለት ዕቃዎች በአምልኮም ሆነ በአስተሳሰባቸው አብረው የተያያዙ ነገሮች ናቸው።

ለጸሐፊው ዋነኛ የነበረው ዕቃ የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው። ይህ የሆነው በሰማያት ያለው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ክብር የሚያመለክተው ደመና በዚያ ታቦት ይኖር ስላነበር ነው። «የቃል ኪዳኑ ታቦት» የሚል ስያሜ የተሰጠው፥ እግዚአብሔር ከእሥራኤላውያን ጋር የገባው ቃል ኪዳን የሚያመለክቱትን አሥርቱ ቃላት የተጻፈባቸውን ሁለት ፅላቶች ስለያዘ ነው። ታቦቱ በወርቅ የተሠራ ሳጥን ሲሆን የስርየቱን መክደኛ በክንፋቸው የሚሸፍኑ ሁለት ኪሩቤሎች ከእያንዳንዱ ወገን ነበሩበት። የታቦቱ መክደኛ የስርየት መክደኛ ወይም የምሕረት መቀመጫ የሚል ስያሜ የተሰጠው ደሙ የሚረጨውና እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት ይቅር የሚለው በዚህ ሥፍራ ስለሆነ ነው። በታቦቱ ውስጥ ሦስት ነገሮች ነበሩ፤ እነዚህም፡- መና ያለበት የወርቅ መሶብ፥ የበቀለች የአሮን በትርና አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፉባቸው ሁለቱ ፅላቶች ነበሩ።

ሰለሞን ቤተ መቅደሱን ሲሠራ የቃል ኪዳኑ ታቦት ብቻ ነበር ያስቀመጠበት። በዚያን ጊዜ በታቦቱ ውስጥ የነበሩት ሁለቱ ፅላቶች ብቻ ነበሩ፤ (1ኛ ነገ.8፡9)።

ምናልባትም ፍልስጥኤማውያን ታቦቱን ሲወስዱ፤ የአሮንን በትርና መሶቡን ሳያስቀሩት አልቀረም፤ (1ኛ ሳሙ.4፡11)። ይህ የቃል ኪዳን ታቦት በ586 ዓመት ዓ.ክ.ል.በ. ባቢሎናውያን መጥተው ቤተ መቅደሱን ሲያወድሙት አብሮ ጠፍቷል። ከዚያን ጊዜ በኋላ የሚሠሩት ቤተ መቅደሶች በታቦቱ ፈንታ ያስቀምጡ የነበረው ጠፍጠፍ ያለ ድንጋይ ነው። የታቦቱን ወደ ኢትዮጵያ መወሰድ የሚያትተው አፈ ታሪክ፤ ታሪካዊ የሆኑ ማስተማመኛ ስለሌላቸው እውነተኛነቱ ያጠራጥራል።

ምንም እንኳን ለጸሐፊው ታቦቱና በውስጡ ያሉት ዕቃዎች መንፈሳዊ የሆነ ትርጓሜ ቢኖራቸውም ወደዚያ ጠልቆ ከማተት ተቆጥቧል። በምትኩ የመገናኛውን ድንኳን አምልኮ ድክመት ወደ መግለጹ ነው የሚሄደው፤ (ከቁጥር 6-10)።

ቅዱሱ ቦታ ውስጥ ማንኛውም ሰው ሊገባ አይችልም ነበር። ወደ ቅዱሱ ቦታ ለመግባት የሞከረው አንዱ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ተቀብሎ በለምፅ ተመቷል፤ (2ኛ ዜና 26፡16-23)። ካህናቱ ግን ወደዚህ ሥፍራ በየቀኑ በመግባት ሕብስቱን ይቀይሩና መቅረዙ ውስጥ ዘይት ይጨምሩ ነበር።

ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚቻለው በዓመት አንዴ ብቻ ነበር። ለስርየት ቀን ለሕዝቡና ለራሱ ሊቀ ካህኑ የሚሆነውን የኃጢአት መሥዋዕት ደም ይዞ መግባት ይችል የነበረው ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበረ።

ከብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ጸሐፊው ሁለት ድክመቶችን ተመልክቷል።

1. ወደ እግዚአብሔር ይወስድ የነበረው መንገድ ክፍት አልነበረም። ተራው ሕዝብ ወደ መገናኛው ድንኳን መግባት አይችልም ነበር። ወደ ቅዱስ ቦታ ካህናቱ መግባት ይችሉ ነበር፤ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ በዓመት አንዴ መግባት የሚፈቀድላቸው ሊቀ ካህናቶቹ ብቻ ነበሩ። ስለዚህም የቀድሞው ኪዳን በታቦቱ አማካይነት ማንም ሰው እንደፈለገው ወደ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ሥፍራ መግባት እንደማይችል አውጇል።

2. የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት በመሥዋዕት አማካይነት ጊዜያዊና ውስን የሆነ መንጻትን ነበር የሚያስገኘው። ሙሉ በሙሉ ሕዝቡን ሊያነጻ አይችልም ነበር። በዚህም ምክንያት ነው በየቀኑ መሥዋዕት ይቀርብና ሊቀ ካህኑም በየዓመቱ መሥዋዕት ያቀርብ የነበረው። ምዕመኑ በሥርዓቱ መሠረት ከኃጢአቱ ቢነጻም የሕሊናውን ክስ ግን ሊያስወግድለት አይችልም ነበር። የደሙ መሥዋዕት ይህንን ማድረግ ባይችልም፤ ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር በማመኑ ምክንያት ብቻ እግዚአብሔር ሕሊናውን ንጹህ ያደርግለት ነበር፤ (መዝ. /51/)።

5ኛ ጥያቄ፡- ዛሬ እኛ በክርስቶስ ከመገናኛው ነገር እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ለየት የሚሉት እንዴት ነው?

የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ያስገኙ የነበረው ጊዜያዊ የሥርዓት መጽናትን ነበር። ምግቦቹ (ለምሳሌ፡- የደኅንነቱ መሥዋዕት)፥ መጠጦቹና (ለምሳሌ በመሠዊያው ላይ የወይን ጠጅ ማፍሰሱ) የመንጻቱ ሥርዓቶች በሙሉ ምሳሌያዊ ነበሩ። «በመታደስ

ዘመን» ሊመጣ ያለውን እውነተኛ አምልኮ እንደ ምሳሌ ሊያሳዩ ለጊዜው የተሰጡ ናቸው። ይህ የመታደስ ዘመን አዲሱ ኪዳን ሲሆን ለሰዎች በእምነት አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ ነፃ የሆነ መንገድ በመስጠት ትኩረትን በልባቸው ላይ ያደርጋል።

ለእሥራኤል ሕዝብና ለእኛ ትልቁ ፈተናችን ውጫዊ የሆኑ የአምልኮ ምግባሮቻችን በእውነት እግዚአብሔር እንደምናመልክ ይገልጻሉ ብለን ማሰባችን ነው። እውነተኛ አምልኮ እንዲኖር ግን የሰው ልጅ ኃጢአትና የበደለኛነት ሕሊና መንጻት አለባቸው። ልብ ሳይቀየር ሥርዓቶችን ዝም ብለን ብንከተል ይህን አያስገኙልንም። እውነተኛ አምልኮ፥ በብሉይ ኪዳንም ውስጥ ቢሆን መጀመር ያለበት ከውስጥ ነው። እውነተኛ የሆነ የኃጢአት ንስሐ በእግዚአብሔር እውነተኛ የሆነ እምነትና ለእርሱ ሕግ እውነተኛ የሆነ ታዛዥነት ሊኖር ይገባል። ከዚህ በኋላ ነው ውጫዊ የሆነውን አምልኮ የሚቀበለው። ለእኛም ቢሆን እውነተኛ የሆነ አምልኮ መጀመር ያለበት ከልብ ነው። እንዲያው ዝም ብለን መዝሙር ስለምንዘምር መዘምራኖችን ስለምንሰማ የእግዚአብሔርን ቃል ስለምናዳምጥና አሥራታችንን ስለምንሰጥ ብቻ እውነተኛ አምልኮ ይዘናል ልንል አንችልም። ልባችንና ሕይወታችንም አብሮ በአምልኮ ውስጥ መሆን አለበት።

6ኛ ጥያቄ:- ሀ) ልብ ትክክለኛውን መንገድ ሳይዝ ዝም ብለህ ውጫዊ የሆኑትን ሥርዓቶች በመከተል እንዴት እግዚአብሔርን ታመልክ እንደነበር፥ ዘርዝረህ ጻፍ።

ለ) እንዴት አድርገህ እራስህንና የቤተ ክርስቲያንህን አባላት በመጀመሪያ ልባችሁን አዘጋጅታችሁ በእግዚአብሔር ፊት አምልኮአችሁ ተቀባይነት እንዲኖረው ልታደርጉ የምትችሉባቸውን መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

# ሁለተኛ ቀን:- ዕብራውያን 9፡11-14

የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥፍራ ስለሆነው ስለመገናኛው ድንኳንና በዚያ ሥፍራ ስላለው አምልኮ ድክመት ከገለጸ በኋላ ጸሐፊው ፊቱን ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማዞር በእርሱ ውስጥና በእርሱ በኩል ያለውን አምልኮ ይመለከታል።

7ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 9፡11-14 አንብብ።

ሀ) ኢየሱስ በሠራው ሥራ እና ሊቀ ካህኑ በስርየት ቀን በሚሠራው ሥራ መካከል ያለውን መመሳሰል አብራራ።

ለ) በብሉይ ኪዳን ዘመን ከተሠራው ሥራ የኢየሱስ ሥራ እንደሚበልጥ የሚያሳዩትን የተለያዩ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

በስርየት ቀን ስላለው የአምልኮ ሥርዓት ከጠቀሰ በኋላ ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደፈጸመው ወደሚገልጸው እውነታ ያመራል። የክርስቶስን ታላቅ ሥራ እንደ ምሳሌ እንዲያሳይ የሚመርጠው የስርየት ቀን ነው። ኢየሱስ «ሊመጣ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህን ነው የሚል ስያሜ የተሰጠው አዲስ ኪዳንንና በውስጡ

የሚገኙትን ታላላቅ የተስፋ ቃሎች እርሱ በመሥራቱ ነው። እነዚህ የተስፋ ቃሎች ገና ከአሁኑ በአማኞች ልብ ውስጥ ተፈጻሚነት ማግኘት ጀምረዋል።

8ኛ ጥያቄ፡- በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተሰጡት የተስፋ ቃሎች ውስጥ እስቲ አንዳንዶቹን ዘርዝረህ ጻፍ! (ትምህርት ስምንት ከልስ)።

ጸሐፊው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ከብሉይ ኪዳኑ በሁለት ምክንያቶች የተሻለ ነው ይላል፡-

1. አሁን አምልኮው የሚካሄደው በተሻለ ድንኳን ውስጥ ነው። የበፊቱ ድንኳን በመንግሥተ ሰማያት ባለው ድንኳን አምሳያ የተሠራች ነበረች። የአሮን ካህናት ይሠሩ የነበሩት በአምሳያው ድንኳን ውስጥ ሲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሚሠራው በእውነተኛው ድንኳን በመንግሥተ ሰማያት ነው። ይህ ሰማያዊ ድንኳን በሰው እጅ ሳይሆን የተሠራው በእግዚአብሔር ነው።

2. የተሻለ መሥዋዕት ነው የቀረበበት። በስርየት ቀን ሊቀ ካህናቱ ደሙን ይዘው ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ይገቡ ነበር። ይህ በየዓመቱ መደገም ነበረበት፤ ያስገኝም የነበረው ጊዜያዊ የሆነ ሥርዓታዊ ለውጥ ነበር። በሌላ አነጋገር ያነጻ የነበረው ውጫዊ የሆነ ነገር ብቻ ነው። ጸሐፊው «የጊደሩን አመድ» ሲጠቅስ ሌላን ሥርዓት መጥቀሱ ነው።

9ኛ ጥያቄ፡- ዘኁልቁ ምዕ.19 አንብብ። በዚህ ክፍል ላይ ስለተጠቀሰው ሥርዓት ገለጻ ስጥ። አመዱን ለምን ነበር የሚጠቀምበት?

በድን የሚነኩና በዚያም ምክንያት እርኩስ የሚሆኑ ሰዎች ይነጹ የነበረው በጊደሩ አመድ ነበር። ይህም አመድ ያስገኝ የነበረው ውጫዊ የሆነ ለውጥ ነበር።

ዳሩ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ በመስቀል ላይ ሲሞት ያፈሰሰው የራሱን ደም ነው እንጂ የእንስሳትን አልነበረም። ልክ ለመሥዋዕት እንደሚቀርቡት እንስሳት «ነውር የሌለበት ነበር። ጸሐፊው ይህን ሲል ምንም ኃጢአት የሌለበት ንጹሕና የተቀደሰ ሕይወት ነበረው ማለቱ ነው። ልክ እንደ እንስሳዎቹ ሞቱን ያመለክት የነበረው ደሙ የፈሰሰው ለኃጢአት ሲባል ነው። ብዙ የእንስሳ መሥዋዕቶች ይደረጉ ነበር፥ የኢየሱስ ሞት ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነበር። በመስቀል ላይ መሞት የነበረበት አንዴ ብቻ ነው። ይህ ሞቱ ደግሞ መንጻትን ለሁሉም ሰው እንደሚኖር አደረገው። የእንስሳ መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው ሰዎች በሆኑ ሊቀ ካህናት አገልግሎት ነበር! የኢየሱስ መሥዋዕት ግን የቀረበው በዘላለማዊው መንፈስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በኩል ነበር። መሥዋዕት አቅራቢ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ እራሱ መሥዋዕት ነው፥ ምክንያቱም እራሱን የሠዋው እራሱ ነውና ነው።

የእንስሳቱ መሥዋዕት ውጫዊ የሆነ መንጻት ነበር የሚያስገኘው የኢየሱስ ደም ግን የበለጡ ታላላቅ ውጤቶችን ነው የሚያስገኝልን። አንደኛ! ዘላለማዊ ምሕረቱን ያስገኝልናል። የኢየሱስ መሞት ለሚቀበሉት በሙሉ ምሕረትንና መንጻትን ያስገኝላቸዋል። ዘላለማዊ የሆነ የሕሊና ወይም የልብ መንጻት ያስገኝልናል። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት እንዲሻክር ያደረገውን ዋነኛ የችግር ፈጣሪ

የሆነውን ልቡን ነው ለመመለስ የሚጥረው። የዚህ መሻከር ውጫዊ ችግሮች የሆኑትን ሥርዓታዊ አለመንጻትን ለማስወገድ ግን አይጥርም።

የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በእምነት አማካይነት ከሕይወታችን ጋር ሲዋሐድ ሁለት ታላላቅ ነገሮች በሕይወታችን ይከናወናሉ። አንደኛ:- ወደ ሞት ከሚያደርሱ ሥራዎች መገላገል ነው። እነዚህም የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን የምንበድልበት የኃጢአት ድርጊቶችን ሆነው መንፈሳዊ እርኩሰትንም የሚያስከትሉትን ነው። እነዚህም በበኩላቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት መሰናክሎችን ፈጥረው በመጨረሻም መንፈሳዊ ሞትን የሚያስከትሉ ናቸው።

10ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከእነዚህ የኃጢአት ሥራዎች ወስጥ አንዳንዶቹ ምንድን ናቸው?

ለ) በራስህ ሕይወት ውስጥ ከእነዚህ ሥራዎች የተላቀከው እንዴት ነው?

ሁለተኛ:- ሕያውን አምላክ እንድናገለግል ነፃ ወጥተናል። እግዚአብሔር የሚያድነን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድንሄድ ብቻ አይደለም፤ የሚያድነን የበለጠ እርሱን እንድናገለግለውም ነው፤ (ኤፌ.2:8-10)። ብዙ ጊዜ ከኃጢአት ዕዳ በመዳናችን በጣም ሐሴት እናደርግና ሕይወታችን ተለውጦ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን ግን አናደርግም። አሁን ከዳንን በኋላ እግዚአብሔርን በትክክለኛው መንገድ ነው የማገለግለው? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። ወይስ አሁንም ወደ ሞት የሚመራውን የሥጋን ሥራ እየሠራን ነው?

11ኛ ጥያቄ:- ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ በመዳንህ ምክንያት እንዴት አድርገህ ልታገለግለው እንደምትችል አንዳንድ መንገዶችን ግለጽ።

ለ) ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያንህ አባላት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ኢየሱስን እያገለገሉት ነው? እንዴት?

## ሦስተኛ ቀን:- ዕብራውያን 9:15-22

በዕብራውያን 9:1-14 ላይ ጸሐፊው የብሉይ ኪዳንን መገናኛ ድንኳንና የአምልኮ ሥርዓቱን ከሰማያዊው ድንኳንና የኢየሱስ ደም ካስገኛቸው ውጤቶች ጋር ያነፃፅረዋል። አሁን ደግሞ በዕብራውያን 9:15-22 ላይ አዲሱ ኪዳን ለምን በደሙ መጀመር እንዳለበት ያብራራል።

12ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 9:15-22 አንብብ።

ሀ) ለተጠሩት የተሰጠው ተስፋ ምንድን ነው?

ለ) አንድ ኑዛዜ ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ፥ በመጀመሪያ ምን መደረግ አለበት?

ሐ) ብሉይ ኪዳን ሲጀመር እንዲጸናና በዝግጅት ላይ እያለ እንዲነጻ ያደረገው ምንድን ነው?

መ) በብሉይ ኪዳን ደም ሳይረጭባቸው ይነጹ የነበሩ አንዳንድ ነገሮችን ጥቀስ።

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያሉት የጸሐፊውን አባባልና አመለካከት ለማጤን ትንሽ ከበድ ይላል። ይህም የሆነው «ኪዳን» የሚለው ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ስለሚጠቀምበት ነው። በግሪክ ቋንቋ «ኪዳን» የሚለው ቃል በአንድ ጊዜ ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል። አንደኛ ሊለወጥ የማይችልና ብዙ ለየት ያሉ ቃል ኪዳኖችን የያዘ አንድ ሰው ሌላ የሚሰጠው ኪዳን ሊሆን ይችላል። ኪዳኑን የሚቀበለው ሊተወው ወይም ሊቀበለው ይችላል፥ ነገር ግን የማይለወጥና የማያከራክር ነገር ነው። (ለምሳሌ፤ ብሉይና አዲስ ኪዳን)፥ ሁለተኛ አንድ ሰው ሲሞት ንብረቱን ለሌላ ሰው ማውረስ ሲፈልግ ለኑዛዜ ይህን ቃል ይጠቀምበታል። አባት ለልጆቹ ለመስጠት የሚፈልጋቸውን ነገሮች በዝርዝር የሚጽፍበት ለቃለ ኑዛዜ የሚጠቅም ነው ማለት ነው። ስለ አዲስ ኪዳን ለመግለጽ የዕብራውያን ጸሐፊ ሁለቱንም ትርጓሜዎች ይጠቀማል።

ዕብራውያን 9፡ 15 የዚህን ክፍል ትምህርት ማጠቃለያ የያዘ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ከሞተ በኋላ አዲሱ ኪዳን ተጀመረ። በዚህም ምክንያት ኢየሱስ «የአዲስ ኪዳን መካከለኛ» የሚል ስያሜ ተሰጠው። መካከለኛ የሚለው ቃል እግዚአብሔርንና ሰዎችን በአዲስ ስምምነት ሥር የሚያገናኝ ማለት ነው። ሙሴ የብሉይ ኪዳን «መካከለኛ» ሲሆን ኢየሱስ ደግሞ የአዲስ ኪዳን «መካከለኛ» ነው።

በሥሩ ላሉት አዲሱ ኪዳን ለየት ያሉ ቃል ኪዳኖችን ሰጥቷል፥ (ዕብራውያን ምዕራፍ 8)። እግዚአብሔር የጠራቸውና ለዘላለማዊ ሕይወት የተመረጡት ሁሉ በዚህ በአዲሱ ኪዳን ሥር ውርስ የሆኑት ነገሮች በሙሉ ያገኛሉ። ልክ እንደ ኑዛዜ እነዚህ ቃል ኪዳኖች የተጀመሩት ወይም የተጠነሰሱት ከኢየሱስ ሞት ጋር ነው።

ጸሐፊው በዚህ ትምህርት ላይ አስደናቂ የሆነ ነገር ይጨምርበታል (ቁጥር 15)። የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በአዲሱ ኪዳን ሥራ ለሚኖሩ ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ ደኅንነትንና በረከትን የሚያስገኘው የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን የተላለፉትንም የሚቤዥ ሞትም ነው። ይህንን ሲል ጸሐፊው የኢየሱስ ሞት በአዲሱ ኪዳን ያሉትን ሰዎች ኃጢአት ብቻ ሳይሆን የተቤዠው በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበሩትንም አማኞች ኃጢአት ጭምር ነው የተቤዠው ማለቱ ነው። ይህ ደግሞ በጣም አስፈላጊ ነበር፥ ምክንያቱም የጠቦትና የፍየል ደም የሥርዓታዊ መንጻትን ብቻ ነበር እንጂ የሚያስገኘው፥ ሙሉ በሙሉ የሆነ መንጻትንና የኃጢአት ዋጋን አይከፍልም ነበር። ስለዚህም የኢየሱስ ሞት ወደ ኋላ እስከ አዳም ድረስ ወደ ፊት ደግሞ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በመድረስ ሰዎችን ከኃጢአታቸው ያነጻቸዋል።

13ኛ ጥያቄ፡- ይህ ሐሳብ ስለ ብሉይ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታት ደኅንነት የሚናገረው ነገር ምንድን ነው? እንስሳትን በመሠዋታቸው ደኅንነት አግኝተዋል?

አዲሱን ኪዳን ለመጀመር የኢየሱስ ሞት ለምን አስፈለገ? ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ተሰጥተዋል፡-

1. አዲሱ ኪዳን፤ ልክ ሲሞት እንደደረሰ ሰው የመጨረሻ ፈቃድ ሊጸና የሚችለው ኪዳኑን የሚፈጽመው ሰው ሲሞት ብቻ ነው፤ (ከቁጥር 16-17)። እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ኪዳኑን የሚፈጽመው ሰው ሐሳቡን ሊለውጥ ይችላል፤ ወራሾችም የሆኑት እስከ ሞት ድረስ ምንም ነገር አያገኙም፤ ስለዚህም አዲሱ ኪዳን እንዲጀመርና የኪዳኑን ውርሳችንን (በረከቶቹን) እንድንቀበል፥ በመጀመሪያ ደረጃ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በጣም አስፈላጊ ነበር።

2. እግዚአብሔር ይህን የደም መፍሰስ ሥርዓት የመሠረተው ኪዳኖቹን ለማፍለቅና ለማጽደቅ ነው። የመጀመሪያው የሙሴ ኪዳን የጸናው በፈሰሰው የእንስሳ ደም ነው። በዚህን ጊዜ ግን ኪዳኑን የሚያደርገው (እግዚአብሔር) ሳይሆን በእርሱ ምትክ የሚሞቱት እንስሳቱ ነበሩ። ልክ እንደዚሁ አዲሱም ኪዳን የጸናው በደም ነው። በዚህ ጊዜ ግን አዲሱን ኪዳን ለመጀመር የፈሰሰው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው።

14ኛ ጥያቄ፡- ኦሪት ዘጸአት 24፡3-8 አንብብ። ሙሴ ደሙን የረጨባቸው ሁለቱ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ብራውያን ላይ ከሚናገረው ይህ ለየት የሚለው እንዴት ነው?

የዕብራውያን ጸሐፊ ደሙ የተረጨው በመጽሐፉና በሕዝቡ ላይ ነው ማለቱና በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ መረጨቱን አለመግለጹ በጣም የሚያስደንቅ ነው። በዚህን ጊዜ በሂሶጵ፥ በውኃና በቀይ ጠጉር ተጠቅሟል ይላል። እነዚህ ነገሮች ደግሞ በኦሪት ዘጸአት ላይ አልተገለጹም። ምናልባትም ይህንን ተጨማሪ ትምህርት ያገኘው ከታወቀ የአይሁዳውያን ባህላዊ ታሪክ ላይ ሳይሆን አይቀርም።

3. እግዚአብሔር በደም አማካይነት ማንኛውም ነገር ከኃጢአት ጠባሳ ነፃ ሆኖ ለአምልኮ የተዘጋጀ እንዲሆን ደንግጓል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በስርየት ቀን በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ በዕጣኑ መሠዊያ ላይና በነሐሱ መሠዊያ ላይ ደም እንደሚረጭ ተገልጿል። ሆኖም ብሉይ ኪዳን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገኙት ማናቸውም ነገሮች በደም መንጻት አለባቸው አይልም። እንዲያውም ለሌሎቹ ዘይት ይጠቀሙ ነበር፥ (ዘጸአት 40፡9-11፥ ዘሌዋ.8፡10-11)። ይህም ቢሆን አሮንና ልጆቹን ለማንጻት ዘይትና ደም ይጠቀሙ ስለነበር ምናልባት መገናኛ ድንኳኑንም ለማንጻት እነዚህን ሁለቱን ነገሮች ሳይጠቀሙባቸው አይቀሩም፥ (ዘሌዋ8፡30)።

በዕብራውያን 9፡23 ላይ ጸሐፊው ሰማያዊው ድንኳን እራሱ በደም ነው የሚነጻው ይላል። ያሁኑ ደም ግን የኢየሱስ ነው።

ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን አንድ ነገር ለመንጻት በምትኩ ሌላ ነገር መሞት አለበት፤ ይህንንም ሞት የሚወክለው ደሙ ነው፥ የሚል ሥርዓት ላይ ነው የተመሠረቱት። ለኃጢአት መሥዋዕት እንስሳ ማቅረብ የማይቻለው በምትኩ ግን እህል መስጠት ከሚችለው ችግረኛ ሰው በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ከኃጢአት ለመንጻት የእንስሳ ደም ማፍሰስ ነበረባቸው። እንደ ብቻ ዕጣን (ዘኁልቁ 16፡46)፤ የማንጻት ውኃና እሳት፤ (ዘኁልቁ 31፡21-24) ለሕዝቡ ስርየትን ያስገኛሉ ተብሏል። ነገር ግን በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ሕግ ማንኛውም ነገር እንዲነጻ ደም ያስፈልገዋል የሚል

ነው። በዚህም ምክንያት ነው የእኛን ኃጢአት ለማንጻት ሲል እግዚአብሔር ኢየሱስ እንዲሞትና ደሙ እንዲፈስ ያስደረገው።

ይህ ስለ ትልቁ የኃጢአት ዋጋ ትምህርት ሊሰጠን ይገባል። በብሉይ ኪዳን ብንኖር ኖሮ ሁልጊዜ ኃጢአት በሠራን ቁጥር የሚሠዋ እንስሳ ማቅረብ ነበረብን። ኃጢአታችን ብዙ ወጪ ያስወጣን ነበር። ሆኖም በአዲስ ኪዳን የኃጢአታችን ዋጋ እራሱ እግዚአብሔር ከፈለልን። የሚወደውን አንዱን ልጁን ለእኛ እንዲሞት ላከው። እኛ እንዳንሞት ኢየሱስ የእኛ የኃጢአት መሥዋዕት ሆነ።

15ኛ ጥያቄ:- በመስቀል ላይ በመሞት የኃጢአትህን ዋጋ ስለ ከፈለልህ ኢየሱስን አመስግነው።

ኃጢአታችን የእግዚአብሔርን ልጅ ሞት የሚያክል ዋጋ ስላስከፈለ የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር መጣርና መሻት የለብንም? እግዚአብሔር እኛን ለማንጻት የከፈለው ዋጋ በደንብ ከገባን እግዚአብሔር ኃጢአትን ምን ያህል እንደሚጠየፍ ልናይና በእግዚአብሔር ዓይን እራሳችንን ንጹህ አድርገን ለመጠበቅ እንተጋ ነበር።

16ኛ ጥያቄ:- ለምንድን ነው አንዳንድ ክርስቲያኖች ኃጢአትን እንደ ትንሽ በመቁጠር ኃጢአት እንዲቆጣጠራቸው የሚያደርጉት?

# አራተኛ ቀን:- ዕብራውያን 9:23-28

በዓለም ታሪክ ውስጥ የኢየሱስ መስቀል ተገቢ የሆነ ትኩረት የተሰጠው ባይሆንም ከእግዚአብሔር በኩል ሆኖ ሲታይ ግን የታሪክ ሁሉ መሠረት ነው። የብሉይ ኪዳን አምልኮና ሥርዓት በሙሉ ያመለክቱ የነበረው ኢየሱስ የሚሞትበትን ቀን ነው። እንደተመለከትነው የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት እስከ ብሉይ ኪዳን ዘመን ድረስ በመዝለቅ ለጻድቃን ሰማዕታቱ ሙሉ ደኅንነትን አስገኝቷል። ይህም ብቻ አይደለም፥ በዚህ በአዲሱ ኪዳን ዘመን በኢየሱስ አምነን የምንኖረውንም ከኃጢአት ባርነት ነፃ አውጥቶናል።

17ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 9:23-28 አንብብ። ሀ) የኢየሱስ ደም የፈጸማቸው ሁለቱ ዋና ዋና ነገሮች ምንድን ናቸው? ለ) በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተጠቀሱ ሦስት ኢየሱስ የሚገለጥባቸው ወቅቶች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ምን ይሆናል? መ) ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ ምን ይሆናል?

የብሉይ ኪዳን ብዙው ክፍል ኢየሱስ ከመጣ በኋላ የሚሆነው ነገር የሚያሳይና የሚገልጽ ነው። ጸሐፊው የስርየት ቀን በመጥቀስ እሥራኤላውያን ከሚያውቁት የመንጻት ሥርዓት የሚበልጠውን ኢየሱስ የፈጸመውን ሥራ ለማመልከት ይጠቀምበታል። ሦስት ዋና ዋና ክንዋኔዎች ተጠቅሰዋል:-

1. ከትናንትናው ጥናታችን እንደምታስታውሰው የእንስሳቱ ደም አንደኛው ምክንያት የአምልኮ ሥፍራ የነበረውን መገናኛ ድንኳኑን ማንጻት ነበር። በስርየት ቀን

ሊቀ ካህኑ በድንኳኑ ውስጥ የሚገኙትን ዕቃዎች በሙሉ ያነጻ ነበር። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው ድንኳን በመንግሥተ ሰማያት የሚገኘው የእውነተኛው ድንኳን አምሳያ ስለነበር በዚህም ሥፍራ እራሱ የመንጻት ሥርዓት ይካሄድ ነበር። ሆኖም በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዳለው ተራ በሆነ በእንስሳት ደም አልነበረም። መንግሥተ ሰማያት ይጸዳና ለኃጢአተኞች የአምልኮ ሥፍራ በመሆን ይዘጋጅ የነበረው በእራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው፤ (ከቁጥር 23-24)።

ለምንድን ነው መንግሥተ ሰማያት መንጻት የነበረበት? አንዳንዶች ሰይጣን በመንግሥተ ሰማያት ላይ ሆኖ በማመጹ መንጻት አለበት ብለው ያስባሉ፤ (ቆላስይስ 1፡20)። እንደሚመስለን ግን መንግሥተ ሰማያት ይነጻ የነበረው እርኩስ በመሆኑ ሳይሆን ልክ እንደመገናኛው ድንኳን ኃጢአተኛው ሰው ከእግዚአብሔር የሚገናኝበት ሥፍራ በመሆኑ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲሱ ኪዳን መሠረት ለእኛ ጥቅም ሲል በመንግሥተ ሰማያት ሆኖ የአምልኮ ቦታችንን ያዘጋጃል።

በስርየት ቀን ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ይከናወናሉ። አንደኛ፤ ለኃጢአት መሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳትን መሠዋት ነበረባቸው። ሁለተኛ፤ ሊቀ ካህኑ መጋረጃ ውስጥ ገብቶ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ነበረበት። ኢየሱስም በመጀመሪያ እራሱን ለኃጢአት መሥዋዕት ካቀረበ በኋላ በመንግሥተ ሰማያት በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ነበረበት። በሰማያት የሚገኙትን ነገሮች የማንጻቱ ሥራ ከብሉይ ኪዳኑ ይበልጥ ነበር፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ያፈሰሰው የራሱን ደም እንጂ የእንስሳ ደም ባለመሆኑ ነው። ይህን ሥራ ታላቅ የሚያደርገው ሌላው ነገር መንግሥተ ሰማያት በሚገኘው ታላቁ ድንኳን ውስጥ መከናወኑ ነው። ምድራዊቷ ድንኳን ትነጻ የነበረችው በእንስሳ ደም ነበር፥ የኢየሱስ ሞት ግን የእግዚአብሔርን ቁጣ በማስወገድ፥ የእግዚአብሔርን የአምልኮው መንገድ ከፈተልን።

2. ኢየሱስ በመስቀል መሠዋት በተደጋጋሚ ይሠዉ ከነበሩት የብሉይ ኪዳን ሁሉ የበላይ ነበር፥ ምክንያቱም ኢየሱስ እራሱን ለኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ የነበረበት አንዴ ብቻ በመሆኑ ነው፥ (ከቁጥር 25-26)። በብሉይ ኪዳን ሰዎች ኃጢአት በሠሩ ቁጥር እንስሳትን መሥዋዕት ማቅረብ ነበረባቸው። በየዓመቱ ደግሞ ሊቀ ካህኑ በስርየት ቀን መሥዋዕት ያቀርብ ነበር። ኢየሱስ ግን ዘላለማዊ የሆነ ምሕረትንና መንጻትን ያስገኘልን ዘንድ መሞት የነበረበት አንዴ ብቻ ነበር። የኢየሱስ ሞት ሰዎችን ሁሉ ከኃጢአታቸው ማንጻት ባይችል ኖሮ ከአዳም ጊዜ አንሥቶ ሰዎች ኃጢአት በሠሩ ቁጥር በተደጋጋሚ መሞት ነበረበት ማለት ነው። ሆኖም የኢየሱስ ሞት ታላቅነት የታየው የተከናወነው አንዴ በመሆኑና በየትኛው ጊዜ ለነበሩ ሰዎች በመጥቀሙ ነው። ጸሐፊው እንደተናገረው በዘመናት ፍጻሜ ላይ ኢየሱስ በተገለጸበት ወቅት (ታሪክ ወደሚሸጋገርበት የመሢሑ ዘመን) በማያዳግመው ሞቱ ኃጢአትን ሁሉ አስወገዷል። ከአዳም ጊዜ አንሥቶ እስከ ኢየሱስ ለነበሩትም ሰዎች የኃጢአት ስዕዳቸው የተከፈለው በኢየሱስ ሞት ነው። ይህን ስንል ከአሁን ወዲህ ምንም ኃጢአት የለም ማለታችን

ሳይሆን የመጨረሻው የኃጢአት ዋጋ ተከፍሏል ዳግመኛ ስለ ኃጢአት የሞት ክፍያ አያስፈልግም ማለታችን ነው። ሆኖም ከሌሎች የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደምናየው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አማካይነት የሚገኘውን ምሕረት ሊቀበሉ የሚችሉት የኢየሱስን ሞት አምነው በሞቱ የሚተባበሩ ብቻ ናቸው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለሰዎች ሁሉ በቂ መሆኑ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች የጌታን እራት በተመለከተ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር ይቃረናል። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የጌታን እራት ሲያስቡ ኅብስቱና ወይኑ ወደ እውነተኛው የኢየሱስ አካል ይለወጣሉ ይላሉ። ይህም ኢየሱስ ስለ ሰዎች ኃጢአት እንደገና ተሠዋ ማለቱ ነው። ክርስቲያኖች ኅብስቱን ሲበሉና ወይኑን ሲጠጡ ኢየሱስ እንደገና በመሞት ለኃጢአታቸው ምሕረትን ያጎናፅፋቸዋል። አዲስ ኪዳን የኢየሱስ ሞት አንዴ ብቻ እንደሆነ አጥብቆ ያስተምረናል። የሚደገምም አይደለም። አንዴም በመሞቱ ቀድሞ ለነበረውና አሁን ለሚኖረው ኃጢአት ሁሉ ምሕረትን አስገኝቷል። ስለዚህም የጌታ እራት ከሁሉም ነገር በላይ የኢየሱስን ሞት የምናስብበት የምናከብርበትና ኅብስቱንና ወይኑን የምንወስደው ደግሞ በኢየሱስ ሞት እንደምናምን የምንገልጽበት ሥርዓት ነው።

በስርየት ቀን የሊቀ ካህኑ ከመጋረጃ ውስጥ ወጥቶ ወደ ሕዝቡ መምጣት ለሕዝቡ እግዚአብሔር መሥዋዕታቸውን እንደተቀበለና ለሚቀጥለው ዓመት ንጹሕ እንዲሆኑ ማስረጃቸው እንደሆነ ሁሉ የኢየሱስ ዳግመኛ ወደ ምድር መምጣትም ለሰው ልጆች የቀረበውን የኢየሱስን መሥዋዕት እግዚአብሔር እንደተቀበለው ማስረጃ ይሆናል፥ (ከቁጥር 27-28)።

ጸሐፊው የአይሁድ ክርስቲያኖች ሰዎች ሁሉ እንደሚሞቱ ያስገነዝባቸዋል እንዲ ከሞቱ በኋላ ሰዎች ሐሳባቸውን ሊለውጡ አይችሉም። በምትኩ የሚጠብቃቸው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። እንዴ ከሞትን ሌላ ዕድል የለንም። ስለዚህ እግዚአብሔርን ልናገለግል የምንችለው አሁን ነው።

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አሁን በሕይወት እያለን መኖር የሚገባን ሕይወት ይህ ከላይ የጠቀስነው ሐሳብ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ነው ማድረግ ያለበት?

ለ) እራስህን ለእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ዝግጁ ለማድረግ ከአሁኑ አገልግሎትህን እንዴት ልትቀይረው ትችላለህ?

ኢየሱስ ሰው በመሆኑ ሊሞት የሚችለው አንዴ ብቻ ነው። በመስቀል ሞቱ ያስገኛቸው ውጤቶች አንዴ የተደነገጉ በመሆናቸው ሊደገሙ አይችሉም። አንዴ የኢየሱስ ሞት የሚያምኑበትን የብዙዎቹን ኃጢአት አስወገደ።

ከሞት በኋላ ወደ አለው ሰዎች ሁሉ መቅረብ እንዳለባቸው ኢየሱስም መጀመሪያ ላይ መጥቶ በመሞት የጀመረውን ደኅንነት ፍጻሜ ላይ ለማድረስ ዳግመኛ ይገለጣል። የዚህም ጊዜ የአዲስ ኪዳን የተስፋ ቃሎች በገሃድ ይፈጸማሉ። ኢየሱስም በሰላምና በሙሉ ሥልጣን ይገዛል። ኃጢአት ይወድማል በምትኩም ጽድቅ ይነግሣል። በዚህም

ጊዜ በኢየሱስ የሚያምኑና እሱን የሚጠብቁ ሁሉ የመጨረሻውን የምሕረት ተጠቃሚ ይሆናል። ይህ የኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት በእግዚአብሔር ፊት የኢየሱስ መሥዋዕት ተቀባይነቱን ለሁሉም የሚገልጽ ማስረጃ ነው።

ስለዚህም ኢየሱስ፡- ሀ) ኃጢአትን ለማስወገድ (ቁጥር 20) ለ) የእኛ ሊቀ ካህን በመሆን በመንግሥተ ሰማያት በማንጻቱ ሥር ለመሥራት (ቁ.24) ሐ) ዳግም ሲመለስ ሙሉ ደኅንነትን ለማስገኘት (ቁ.28) ተገለጠ።

19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለምን ይመስልሃል ጸሐፊው በኢየሱስ ሞት ውጤቱ ላይ እንዲህ ዓይነት ትኩረት ያደረገው?

ለ) ለምንድን ነው ጸሐፊው ይህን ትምህርት ብዙ ጊዜ የሚደጋገመው?

ለክርስቲያን ከኢየሱስ ሞትና ከመስቀሉ የሚበልጥበት ነገር የለም። በመስቀሉ አማካይነት የኃጢአት ይቅርታን የደኅንነትን ተስፋ የእግዚአብሔር ልጅነትን ከክርስቶስ ጋር መንግሥን ወዘተ... እናገኛለን። ማናቸውም የምናገኛቸው ነገሮች በሙሉ የሚመነጩት ከመስቀሉ ነው። ስለዚህም ወደ ዓለም እንደገና በመመለስ ወይም ወደ ሌላ ሃይማኖት በመሄድ ከክርስቶስ መስቀል ገሸሽ ለማለት የምናደርገው ማንኛውም ዓይነት ሙከራ የደኅንነት ተስፋችን እንደተውነው የሚገልጽ ነው።

20ኛ ጥያቄ፡- ከኢየሱስ መስቀል የምናገኛቸውን ሌሎች ጥቅሞች እስቲ በዝርዝር ጻፍ። ከዚህ በኋላ ላንድ አፍታ ስለ እያንዳንዱ በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግን።

## ሳምንታዊው ስብሰባ፡-

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) 1. ሰዎች ከልባቸው ሳይሆን ዝም ብለው በውጫዊ ሥርዓት ብቻ እግዚአብሔርን ሊያመልኩ የሚችሉባቸውን መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

2. እራስህንና የቤተ ክርስቲያንህን አባሎች በመጀመሪያ ልባችሁን አዘጋጅታችሁ አምልኮአችሁ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ምን ዓይነት ዝግጅት ማድረግ እንዳለብህ በዝርዝር ጻፍ።

ለ) የሰርየትን ቀን የአምልኮ ሥርዓት ከኢየሱስ ሞት ጋር አነፃፅር።

1. እንዴት ነው የሚመሳሰሉት?
2. እንዴትስ ነው የሚለያዩት?

ሐ) በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ላይ በመመስከር ከጥቂት ነገሮች በቀር ሁሉም ነገር በደም እንዴት እንደሚነጻ አብራራ።

መ) 1. የኢየሱስ ሞት እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ስላለው አመለካከት የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው?

2. ለእግዚአብሔር ሊኖረን የሚገባው አመለካከት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ነው የምንማረው?

ሠ) በእግዚአብሔር አንፃር ስናየው ለምንድን ነው መስቀሉ በታሪክ ውስጥ ጉልሁን ሥፍራ የሚይዘው?

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ ሰባት

ዕብራውያን ምዕ.10

## የመጀመሪያ ቀን፡- ዕብራውያን 10፡ 1-18

ዕብራውያን ምዕራፍ 10 በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ የመሸጋገሪያ ምዕራፍ ነው። ዕብራውያን ምዕራፍ 1-9 ትኩረት የተሰጠው ስለ ኢየሱስ ማንነትና የመስቀሉ ሞት ያስገኘው ውጤት በሚገልጹ ትምህርቶች ላይ ነበር! ከምዕራፍ 10-13 ግን ጸሐፊው ክርስቲያኑ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንዴት መኖር እንዳለበት የሚገልጽበት ክፍል ነው።

1ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን ምዕራፍ 10 አንብብ። የዚህን ምዕራፍ ዋና ዋና ትምህርት በዝርዝር ጻፍ።

ጸሐፊው መንፈሳዊ ትምህርት በተመለከተ ለብዙ ጊዜ ሲናገር ክርስቲያኖች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ለመግለጽ ሲል ግን ለትንሽ ጊዜ ብቻ የተናገረው ለምን ይሆን? ብለን መጠየቅ አለብን። ለምንድን ነው ስለ ኢየሱስና ስለሞቱ ለመግለጽ 9 ምዕራፎችን ክርስቲያን በእምነቱ እንዴት መኖር እንደሚገባው ለማሳየት ግን 4 ምዕራፎችን ብቻ የሚፈጀው? በጳውሎስ መልዕክቶችም ውስጥ ተመሳሳይ ሁኔታ እናያለን! ብዙ ጊዜ የሚፈጀው ስለ ወንጌሉ በማብራራት ሲሆን ክርስቶያኖች እንዴት መኖር እንዳለባቸው በሚለው ላይ ግን ለትንሽ ጊዜ ነው የሚናገረው።

ይህ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚሰጡት ትምህርቶች በጣም ለየት ይላል። ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ሰዎች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው የሚያብራራ ትምህርት ላይ በዛ ያለ ጊዜ ሲወሰድ ስለ ደኅንነት፥ ስለ እግዚአብሔር ባህርይ፥ ስለ ኢየሱስ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ወዘተ. . . የሚያብራሩ ትምህርቶች በጥቂቱ ነው። በዚህም ብዙ ጊዜ እምነታችን የተመሠረተው ትክክል ነው ብለን በምንገምተው ቀጥታ መሠረት ላይ ነው እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተገኘው ትምህርት ላይ አይደለም። ይህም በመሆኑ ወደተሳሳተ ትምህርትና ልማድ ቶሎ እንወድቃለን።

ጸሐፊው ልክ እንደ ጳውሎስ የክርስቲያኖቹ እምነት ጽኑ በሆነ መሠረት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይፈልግ ነበር። በዚህም ምክንያት ስለ ብሉይና አዲስ ኪዳን መመሳሰል ስለ ኢየሱስ ታላቅነትና የኢየሱስ ሞት ስላስገኘው ውጤት በዝርዝር ያትታል።

የእግዚአብሔርን ቃል ጥልቅ ትምህርቶች ማወቁ ለክርስቲያኖች አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሰዎች የሐሰት ትምህርቶችን ሊቋቋሙ የሚችሉት ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኢየሱስ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ፥ ስለ ሰውና ስለ ደኅንነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠውን ትምህርት በደንብ ሲረዱ ነው።

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ችግር የፈጠሩ አንዳንድ የሐሰት ትምህርቶችን ግለጽ።

ለ) በዕብራውያን ላይ የተሰጡት ትምህርቶች ለአንዳንዶቹ የሐሰት ትምህርቶች መልስ ሊሰጡ የሚችሉት እንዴት ነው?

እኛ የምንኖረው ብዙ የሐሰት ትምህርቶች የቤተ ክርስቲያን አባላቶቻችንን ከእውነቱ ፈቀቅ በሚያደርጉበት ዘመን ነው። ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በጥልቅ ካልተማሩ የሐሰት ትምህርቶች በቀላሉ ያታልሏቸዋል። እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ያሉ ቡድኖች ስለ ኢየሱስና ስለ ጥምቀት የተሳሳተ ትምህርት ይሰጣሉ። ሌሎች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና በልሳን የመናገርን ነገር ወዘተ... በተመለከተ የተሳሳተ ትምህርት ይሰጣሉ። ለእነዚህ ሁሉ መልስ የሚሆነው በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ትዕዛዝ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት ማወቁ ነው። ስለዚህም ለሁላችንም በስሜታችንና በልምዳችን ላይ ከመመሥረት ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል ተምረን በእርሱ ላይ መመሥረት ያስፈልገናል።

3ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 10፡1-18 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ) በቁጥር 1 ላይ ለሕግ የተሰጠው ስም ምንድን ነው? ይህ ምን ማለት ነው?

ለ) የእንስሳው መሥዋዕት ሊፈጽመው የማይችለው ነገር ምንድን ነው?

ሐ) ሙሉ መንጻትን ለማስገኘት ኢየሱስ ምን አደረገ?

መ) ለምንድን ነው ጸሐፊው ሊቀ ካህናቱ ቆመዋል፥ ኢየሱስ ግን ተቀምጧል የሚለው?

ሠ) በአዲሱ ኪዳን የኃጢአት ይቅርታ ከተገኘ በኋላ ከዚህ በኋላ የማያስፈልገው ነገር ምንድን ነው?

እስካሁን ባለው የዕብራውያን ጥናታችን ጸሐፊው የብሉይ ኪዳንና በውስጡ የሚገኙትን የአምልኮ ሥርዓቶች ከአዲስ ኪዳንና ከውስጡ ከሚገኘው ታላቅ የአምልኮ ሥርዓቶች ጋር ያደረገውን መነፃፀር አጥንተናል። በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላችን ደግሞ ትምህርቱን ጠቅለል አድርጎ ለመጨረሻ ጊዜ ለማቅረብ እንደገና እንዴት በኢየሱስ ሞት አማካይነት አዲሱ ኪዳን እንደተጀመረ ያሳያል።

ጸሐፊው የብሉይ ኪዳንን ሕግ «ጥላ» ይለዋል(ቆላስይስ 2፡17)። በዚህም ካህናቱንና የአምልኮ ሥርዓቱን በተመለከተ የተሰጠው የብሉይ ኪዳን ሕግ የሚያመለክተውና የሚያንፀባርቀው በኢየሱስ መሥዋዕትነት የሚገኘውን ታላቁን እውነተኛ የእግዚአብሔር አምልኮ ነው ማለቱ ነው። ሕጉ ካህናቱና መሥዋዕቶቹ ሁሉ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የነበረው የመጨረሻዎቹ ዕቅዶች ናቸው ማለት አይደለም። እንዲያውም የመጨረሻ መሥዋዕት ታላቅ ሊቀ ካህን ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ ጥርጊያውን መንገድ የሚያዘጋጁ ነበሩ። ወይም ጸሐፊው እንደሚለው ሊመጣ ያለው በጎ ነገር ይህም በአዲስ ኪዳን ሥር የሚገኙትን በረከቶች ሙሉ በሙሉ ማለት ነው። የብሉይ ኪዳን ሕጎች በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚመጡትን ነገሮች እንደ ምሳሌ ሆነው የሚያመለክቱ ነበሩ።

የብሉይ ኪዳንን ደካማነት ለማሳየት ጸሐፊው በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ብዙ ማነፃፀሮች ያደርጋል።

1. በሕጉ ውስጥ ያሉት መሥዋዕቶች ሙሉ መንጻትን አያስገኙም፤ (ከቁ. 1-4)። በአንድ ጊዜ ብቻ ኃጢአተኛውን አያነጹትም፥ ይህም ሙሉ የኃጢአት ይቅርታን አያስገኙም፤ ኃጢአተኛውንም በነፃ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ሊያደርጉ አይችሉም ማለት ነው።

ለዚህ ብቁ አለመሆናቸው የሚረጋገጠው እነዚህ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች በየቀኑና በየዓመቱ መሠዋታቸው ነው። መሥዋዕቶቹ ሙሉ ይቅርታን ቢያጎናጽፉ ኖሮ በየዓመቱና በየቀኑ መሥዋዕት አይኖርባቸውም ነበር። በስርየት ቀን ይሠዉ የነበረው የኃጢአት መሥዋዕት ሕዝቡን ስለ ኃጢአት የሚያሳስብ ነበር እንጂ፤ ሕሊናቸውን ወይም ልባቸውን የሚያነጻ አልነበረም።

ጸሐፊው ኃጢአት መንፈሳዊ የሆነ ነገር እንደሆነ ለሕዝቡ ያሳስባቸዋል። የውጫዊ ሰውነትን መቆሸሽን ሳይሆን ኃጢአት የሚወክለው የልብን አለመንጻት ነው። የፍየልና የኮርማ ደም ውጫዊ የሚዳስሱ ነገር በመሆናቸው ውስጣዊ የሆነን ነገር ሊያነጹ አይችሉም።

ከዚህ በመቀጠል ጸሐፊው ከመዝሙረ ዳዊት(40)፡6-8 ላይ በመጥቀስ የፍየልና የኮርማን ደም ከኢየሱስ ምዕአት ጋር ያወዳድረዋል፤ (ከቁጥር 5-10)። በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበሩ ሰዎች እንኳን የእንስሳት መሞት ኃጢአተኛውን እንደማያነጻው ተረድተው ነበር፤ (ኢሳይያስ 1፡11፥ ሆሴዕ 6፡6)። የዕብራውያን ጸሐፊ መዝሙረ ዳዊት (40)፡6-8 ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምዕአት የተጻፈ ትንቢት አድርጎ ነው የሚቆጥረው። ምንም እንኳን ኢየሱስ ከጥንት ጀምሮ እንደ እግዚአብሔርነቱ ቢኖርም በምድር ላይ እንዲኖር እግዚአብሔር ሥጋን እንዳዘጋጀለት እናነባለን። እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ በመታዘዝ (እንደ ሰው አለመታዘዝ ሳይሆን) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጸመ። ወደ መስቀሉ የመራውም መታዘዝ ነው።

ምንም እንኳ ሕጉ ቢያዝም አንዴ ኢየሱስ መጥቶ ከሞተ በኋላ የእንስሳት መሥዋዕት አስፈላጊ እንዳልሆነ ጸሐፊው ተገንዝቧል። ይህም የሚያመለክተው በእንስሳት

መሥዋዕት ላይ ተመሥርቶ የነበረው የቀድሞው ኪዳን ማቫሩን ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ በኩልና ታዝዞ በመስቀል ላይ በመሞቱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች «ተቀድሰዋል»። የኢየሱስ ሞት ለሰዎች ሁሉ ያደረገው እንስሳት ሊፈጽሙት የማይችሉትን ነገር ነው። ሙሉ ይቅርታን በማገናጸፍ አማኙ በእግዚአብሔር ዐይን ሙሉ በሙሉ ንጹሕና ቅዱስ እንዲሆን አድርጓል።

እግዚአብሔርን በመታዘዝ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣበት ወቅት እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን አሳይቶናል። እግዚአብሔር ሕግጋቱን ብቻ መጠበቃችንን አይደለም የሚፈልገው። እግዚአብሔርን በውጫዊ እየታዘዝን ልባችን ከእግዚአብሔር የራቀ ሊሆን ይችላል። መሆን የነበረበት ግን ልክ እንደ ኢየሱስ በልባችን እግዚአብሔር ሆይ የአንተን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸም ነው የመጣሁት ማለትን ነው።

4ኛ ጥያቄ:- ይህን ዓይነቱ አመለካከትህ በሕይወትህ ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

2. የብሉይ ኪዳን ካህናት ሁሌ እንደቆሙ ነበር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የካህናት ንጉሥ በመሆን ተቀምጦ ይገዛል፥ (ከቁጥር 11-14)። በብሉይ ኪዳን መገናኛ ድንኳንና ቤተ መቅደሶች ውስጥ ካህናቱ የሚቀመጡባቸው ወንበሮች አልነበሩም። ይህም የሆነው መቼውም ቢሆን አገልግሎታቸው ስለማያልቅ ነው። ለሕዝቡና ለእራሳቸው ያለማቋረጥ ሁሌ መሥዋዕት ማቅረብ ነበረባቸው፤ ይህ የሆነው መሥዋዕቶቹ ሙሉ በሙሉ የሕዝቡን ኃጢአት ሊያስወግዱና መንጻቱን ሊሰጡ ስለማይችሉ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሁሉም ሰው ኃጢአት መሥዋዕት ያቀረበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። መሥዋዕት የማቅረቡ ሥራም ስለተፈጸመ መቀመጥ ይችላል። ምንም እንደ ሊቀ ካህን ለእኛ የመማለዱ ሥራ ቢቀጥልም መሥዋዕት የማቅረቡ ጉዳይ ግን ተፈጽሟል። ፍጹምና ታላቅ መሥዋዕት ስለነበርና አንድ ጊዜ ፈጽሞ በመቅረቡ ተቀድሰናል። ይህም በእግዚአብሔር ዐይን የኢየሱስ ሞት ከመዳናችን በፊት የነበረውን የኃጢአት ዕዳ ብቻ ሳይሆን ከዳንንም በኋላ ለምንፈጽመው ኃጢአት ዕዳውን ፈጽሞ ከፍሏል ማለት ነው። ዕዳው በመስቀሉ ላይ ተከፍሏል። የእግዚአብሔር ልጆች እስከሆንን ድረስ በኃጢአታችን ምክንያት ካሁን ወዲያ የሞትን ፍርድ አንቀበልም። ለኃጢአታችን ሙሉ ይቅርታን አግኝተናል።

5ኛ ጥያቄ:- ታዲያ ከዳንን በኋላ ለምንድን ነው ኃጢአታችንን መናዘዝ ያለብን? (1ኛ ዮሐ.1:9)

ጸሐፊው ፍጹም ነን ካሁን ወዲያ ኃጢአት አንሠራም አይልም። ስለዚህም ነው «አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን» ያለው። የእግዚአብሔር ሕይወታችንን የማንጻት ሥራ ገና አልተፈጸመም። ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን፤ ለምንፈጽማቸው ኃጢአቶች ሁሉ ኢየሱስ ዕዳውን ከፍሏል። ምሕረትን ተቀብለን ነጽተናል፤ እግዚአብሔርም ቅዱሳንና ጻድቃን እንደሆንን አድርጎ ነው የሚያየን።

ኃጢአታችንን የምንናዘዘው የሞቱን ቅጣት ለማስወገድ ሳይሆን ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ለመመለስና ለማደስ ነው። ክርስቲያኖች ኃጢአት

ሲሠሩ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ኅብረት በጊዜያዊነት የተቋረጠ ይሆናል። ይህን ስንል ግን እነዚህ ሰዎች አሁንም እንደዳኑና ኃጢአታቸው በክርስቶስ ደም እንደተሸፈነ ነው። ነገር ግን ኅብረት የላቸውም። ንስሐ መግባት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኅብረት ይመልስላቸዋል፥ መንገዱንም ከፍቶ በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት እንዲቆሙ ያደርጋል።

ኢየሱስ ለኃጢአት መሥዋዕት የማቅረቡን ሥራ ብቻ ሳይሆን የፈጸመው በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀምጧል። ይህ የሥልጣንና የክብር ቦታ ነው። አንድ ቀን ምድርን የሚገዛው ንጉሥ እንደሆነ ሆኖ በዚያ ተቀምጧል። ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶችም ጌታ ነው።

3. የአዲስ ኪዳን ቃል ኪዳን የክርስቶስን ሥራ ታላቅነት ያሳየናል (ከቁጥር 15-18)። መንፈስ ቅዱስ በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ስለ ሁለት ታላላቅ ነገሮች ተስፋ ሲሰጥ ስለ ክርስቶስ ሥራ ታላቅነት መሥክሮአል። አንደኛ፤ የእግዚአብሔር ሕግ ቁሳዊ በሆኑ ፅላቶች ላይ ሳይሆን ከሰዎች ልቦና ውስጥ እንደሚጻፉ ተናግሮአል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ ያውቁታል፥ ለሕጉጋቱም ታዛዥ ለመሆን ፍላጎቱ ይኖራቸዋል።

ሁለተኛ፤ መንፈስ ቅዱስ፡- ካሁን ወዲያ ኃጢአታቸው እንደማይታወስና በሕዝቡም ላይ እግዚአብሔር ቂም እንደማይዝባቸው ቃል ገብቶአል። በሌላ አነጋገር ሙሉ የሆነ ይቅርታ ይኖራል። ስለዚህም ሙሉ ይቅርታን ካገኘን መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገንም ነው የሚለው ጸሐፊው፤ (ቁጥር 15)።

ስለዚህም የአይሁድ ክርስቲያኖች ወደ ቀድሞው የአይሁድ ሃይማኖት የሚመለሱበት ምንም ምክንያት የላቸውም። የክርስቶስ መሥዋዕት ሙሉ በሙሉ ከኃጢአታቸው አንጽቷቸዋል። እኛም ብንሆን የጌታን እራት ኢየሱስ እንደገና እንደሞተ አድርገን መመልከት የለብንም ወይም ደግሞ በጥምቀት ጊዜ የሚረጨው ውኃ አንድ ዓመት ያህል ከኃጢአት ያነጻናል ብለን ማሰብ የለብንም። ኢየሱስ ክርስቶስ አንዴ ሞቷል፤ በዚህም ሞት እኛ በኢየሱስ የምናምን ከኃጢአታችን ሁሉ ነጽተናል።

6ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የጌታን እራት ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደገና እንደሞተልን አድርገን መመልከታችን ስሕተት የሚሆነው ለምንድን ነው?

ለ) እንደ ውኃ መርጨት ያሉትን ውጫዊ ነገሮች ከኃጢአት ያነጻሉ ብለን መመልከታችን ስሕተት የሚሆነው ለምንድን ነው?

7ኛ ጥያቄ፡- ለምንድን ነው ሁሉም ክርስቲያኖች የዚህን ጥናት ትምህርት ማወቅ ያለባቸው?

# ሁለተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 10፡19-25

ዕብራውያን 10፡1-18 የክርስትና እውነቶችን የሚገልጸው የዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ነው። ከዕብራውያን 10፡19 ጀምሮ እስከ መጽሐፉ መጨረሻ ድረስ ጸሐፊው በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት ምክንያት እንዴት መኖር እንደሚገባቸው

ተግባራዊ ምክር መስጠት ይጀምራል። ክርስትና እውነታዎቹን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ የሆነ አኗኗርን ያቀፈ ነው። ትክክለኛ አኗኗርና እውነታዎቹን ማወቅ አብረው በመሄድ ክርስቲያኑን ጠንካራ ያደርጉታል።

8ኛ ጥያቄ:- ትክክለኛ ዕውቀትና አኗኗር አብሮ የመሄድ አስፈላጊነት በሕይወትህ ውስጥ አጢነኸው ታውቃለህ?

9ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 10፡19-25 አንብብ።

ሀ) ለኃጢአታችን ሙሉ ይቅርታን ስላገኘን በድፍረት ምን ማድረግ እንችላለን ነው የሚለው ጸሐፊው?

ለ) ከቅድስተ ቅዱሳኑ መጋረጃ ጋር የሚያነፃፅረው ነገር ምንድን ነው?

ሐ) ለክርስቲያኖች የተሰጡት አምስት ትዕዛዞች ምንድን ናቸው?

መ) ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ማሟላት ያለብን ነገሮች ምንድን ናቸው?

ሠ) ጸሐፊው የሚያመለክተው የትኛውን ቀን ነው?

ዕብራውያን 10፡19 የሚጀምረው እንዲህ በሚል ቃል ነው:- ይህም ከዚህ በኋላ ጸሐፊው የሚሰጠው ትምህርት የተመሠረተው በበፊቱ ላይ ነው ማለት ነው። ባለፈው ክፍል ውስጥ ጸሐፊው ለኃጢአታችን ሙሉ ይቅርታ እንዳገኘንና መሥዋዕት በማቅረብ ይቅርታ መፈለግ እንደሌለብን አስተምሮናል።

ክርስቲያኑ ይቅርታን ስለተጎናፀፈ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ይችላል። የእግዚአብሔር ክብር የሚቀመጥበትን የመገናኛ ድንኳኑን ቅድስተ ቅዱሳን እንደ ምሳሌ በማቅረብ፥ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድንቀርብ ያበረታታል።

ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ «አዲስና ሕያው» የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። አዲስ የሆነው ጸሐፊው ይህንን መጽሐፍ ከመጻፉ ከጥቂት ዓመታት በፊት ቀደም ብሎ በኢየሱስ በመከፈቱ ነው። የብሉይ ኪዳኑ የድሮ መንገድ ሳይሆን የአዲሱ ኪዳን አዲስ መንገድ ነው። «ሕያው» የተባለው ከሙታን በተነሣው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን ስለምንቀርብ ነው።

ክርስቲያኖች በድፍረት በእግዚአብሔር ፊት እንዲቀርቡ የሚበረታቱት በሁለት ዋና ዋና መንፈሳዊ እውነታዎች ነው። አንደኛ፤ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት አዲስ መንገድ በኢየሱስ ደም በኩል ተከፍቶልናል። ይህ ደም የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የሚያመለክት ነው («በሥጋው በኩል»)፤ የኃጢአታችንም ዋጋ የተከፈለው በዚህ ሞት አማካይነት ነው። የክርስቶስ ሥጋ በመገናኛ ድንኳኑ ውስጥ ቅዱሱን ቦታ ከቅድስተ ቅዱሳኑ እንደሚለየው መጋረጃ ነው። አሁን ለሁሉም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ክፍት መሆኑን ለመግለጽ መጋረጃው ከላይ እስከ ታች እንደተቀደደ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ

ለሁሉም ሰው ከፈተ። ይህም ከብሉይ ኪዳን ጋር ይነጻጸራል። ምክንያቱም በዓመት አንዴ ወደ እግዚአብሔር እንዲገባ በብሉይ ኪዳን የተፈቀደለት ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር።

ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ («የእግዚአብሔር ቤት») የሚመራ ታላቅ ሊቀ ካህን አለን። ከዚህ በፊት እንዳየነው፥ ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ የሚግልድልን መንግሥተ ሰማያት ውስጥ ከእግዚአብሔር ፊት ሆኖ ነው። ስለዚህም ግርማው ወደሚያስፈራው የእግዚአብሔር የዙፋኑን ክፍል የምንቀርበው ያለ መሪ፥ አዳኝና አማላጅ አይደለም።

10ኛ ጥያቄ:- ክርስቲያን በምድር እየኖረ ሳለ፥ እንዴት አድርጎ ነው እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት የሚችለው?

ምንም እንኳ በሥጋችን በምድር ላይ የተወሰንን ብንሆንም በመንፈስ ግን ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ለእኛ ክፍት ነው። ጸሎት መንፈሳችንን እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ሥፍራ ይወስደናል። እዚያ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ለእግዚአብሔር ምሥጋናችንንና ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን። ጸሎት አንድ በጣም እሩቅ ለሆነ አምላክ የሚጸለይ ሳይሆን ዓለምን ወደሚቆጣጠረው አምላክ ዙፋን አማኙን የሚወስድ ነው። ይህ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠው ስጦታ አስደናቂ አይደለምን? ታዲያ እየተጠቀምንበት ነው?

በክርስቶስ ደም ስለነጻንና በመንግሥተ ሰማያት ላይ ያለ ሊቀ ካህን ስላለን ጸሐፊው ልንጠብቃቸው የሚገቡን አምስት ትዕዛዞችን ይሰጠናል።

1. በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ:- ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው መንገድ ተከፍቶልናል፤ በዚህ መንገድ በጸሎት አማካይነት መጠቀሙ የእኛ ፋንታ ነው።

11ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለምንድን ነው ብዙ ክርስቲያኖች ላንዳፍታ እንኳ ቢሆን ወደ እግዚአብሔር በጸሎት የማይቀርቡት?

ለ) ምን ያህል ጊዜ ነው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የምትቀርበው?

ወደ እግዚአብሔር ከመቅረባችን በፊት ማሟላት ያለብን አራት ነገሮች አሉ።

ሀ) ልባችን እውነተኛ መሆን አለበት፥ በዘልማድ እንዳልቀረብን ማረጋገጥ አለብን፥ ከሆዳምነት ወይም ከግብዝነትም እንዳይሆን እርግጠኞች እንሁን።

12ኛ ጥያቄ:- ከልባችን ሳንሆን እንዴት መቅረብ እንደምንችል ምሳሌዎችን ስጥ።

ለ) ወደ እግዚአብሔር በእምነት መቅረብ አለብን። ይህም በጸሎት አማካይነት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን እንደምንደርስ ማመንና መቀበል አለብን ማለት ነው። ጸሎታችንን እንደሚሰማና መልስ እንደሚሰጠን መተማመን አለብን። ምክንያቱም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አንችልም፤ (ዕብራውያን 11:6)። የአይሁድ ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ሲሉ በጥርጣሬ ወደ ቀድሞው የመሥዋዕት ሥርዓት እንዳይመለሱ፥ ወደ እግዚአብሔር ያለምንም ችግር መቅረብ እንደሚችሉ ሊነገራቸውና ሊረጋገጥላቸው ይገባል።

13ኛ ጥያቄ:- ያለ እምነት እንዴት ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ እንደሚችል የሚያሳዩ አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

ሐ) «ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ነው ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለብን። መንፈሳዊ እውነታን ለማስተማር ጸሐፊው በብሉይ ኪዳን የተለመደን ነገር ይጠቀማል። እንደምታስታውሰው በስርየት ቀን ሊቀ ካህኑ መሥዋዕቱን ለመሥዋዕት ማቅረቢያነት ለማዘጋጀት በደም ይረጨው ነበር። በዚህ ሥፍራ አማኙን ቁሳዊ በሆነ ነገር ስለ መርጨት አይደለም የሚናገረው። እንዳየነው ቁሳዊ የሆነ ነገር መንፈሳዊ ነገርን ሊያነጻ አይችልም። በምትኩ ግን ይህ የሚያመለክተው፥ አንድ ሰው ከኃጢአቱ ለመንጻት ሲል በኢየሱስ እንዳመነና ኃጢአቱን በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ተናዞ እንደነጻ ነው።

14ኛ ጥያቄ:- ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ከመቅረባችን በፊት ልባችንን ማንጻቱ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

መ) ሰውነታችንን በንጹሕ ውኃ መታጠብ አለብን። ለዚህ አባባል ሁለት የማንዛቢ አማራጮች ሊኖሩን ይችላሉ። አንዳንዶች ይህ የውኃ ጥምቀትን የሚያመለክት ነው ይላሉ። በጥምቀት ጊዜ በውኃ ውስጥ መግባቱ እግዚአብሔር ውስጣዊ ሕይወታችንን እንዳነጻን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ሥርዓት ነው። ባመዛኙ ግን ካህናት ለስርየት ቀን ለመዘጋጀት ሲሉ ገላቸውን እንደሚታጠቡ የሚያመለክት ነው! (ኦሪት ዘሌዋውያን 8:6)። በየቀኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መታጠብ እንዳለብን ለማስገንዘብ ጸሐፊው ቅኔያዊ በሆነ አነጋገር ይጠቀማል! (1ዮሐ.1:9)።

2. እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምሥክርነት እንጠብቅ:- ምንም ቢሆን በሕይወታችን እምነታችን እውነት ነው ወይም ደግሞ ክርስትና እውነተኛው መንገድ ነው ብለን የምንጠራጠርበት ወቅት አለ። ሆኖም ይህ ጥርጣሬ በውስጣችን ስላለ እምነታችንን መካድ የለብንም። እንዲያውም እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን እምነት አጥብቀን መያዝ አለብን። ክርስትና በተስፋ የተሞላ ሃይማኖት ነው እንጂ የተስፋ መቁረጥ አይደለም። ወደፊት ከሙታን መነሣትንና የኢየሱስ ክርስቶስን በቅድስና በምድር ላይ መንገሥ በተስፋ የሚመለከት ነው። እምነታችንን እንድንተው የምንፈተነው ዐይናችንን ምድራዊ በሆኑ ነገሮች ላይና በአሁን ጊዜ ችግራችን ላይ ስናደርግ ነው። ጸሐፊው በተስፋ በምንጠብቀው ዘላለማዊ ነገር ላይ ዓይናችንን እንድናደርግ ያሳስበናል! (2ቆሮ.4:16-18)።

በስደትና በችግር ወቅት ተስፋችንን እንድንጠብቅ የሚያደርገን የእግዚአብሔርን ታማኝነት ማወቃችን ነው። ስለ እምነታችን ተገቢውን ክፍያ ይሰጠናል። ቃል ኪዳኖቹን በሙሉ ይጠብቃል። ኢየሱስ ለልጆቹ ይመጣላቸዋል። ስለዚህ ለእኛ ታማኝ ለሆነው አምላክ እኛም ታማኞች መሆን አለብን።

15ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያን የሆነ ሰው ተስፋ የሚያደርጋቸው ነገር ግን ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ምንም ተስፋ የማይጥሉባቸውን ነገሮች ሠንጠረዥ ሥራና እስቲ በዝርዝር ጻፋቸው።

3. እርስ በእርሳችን ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ ትኩረት እንድናደርግ ያስፈልጋል፡- ብዙ ኃላፊነት ያለብን ለራሳችን ሕይወት ብቻ ይመስለናል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ሌሎችንም የመርዳት ሐላፊነት እንዳለብን ያስተምረናል። ጸሐፊው ሌሎችን በሁለት ዋና ዋና የሕይወታቸው ክፍሎች ውስጥ እንድንረዳቸው ያዘናል። አንደኛ፤ ከብቶችን እንደምንነዳበት ዓይነት ዱላ እርስ በእርሳችን በመቆስቆስ ፍቅር በሕይወታችን ውስጥ እንዲገለጥ ማድረግ አለብን። ሁለተኛ፤ የበለጡ ሥራዎችን ለእግዚአብሔር እንድንሠራ እርስ በእርሳችን መጽናናት አለብን። ይህም ወንጌልን በማሰራጨት በማስተማር ወይም በችግር ላይ ያሉትን በመርዳት ሊሆን ይችላል።

16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በእምነትህ ሌሎች ክርስቲያኖች የረዱህ እንዴት ነው?

ለ) ለፍቅርና ለመልካም ሥራ የተዘጋጁ እንዲሆኑ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖች ያነቃቃኸው እንዴት ነው?

4. ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር መሰብሰባችንን አንተው፡- ክርስቲያኖች አብረው ተሰብስበው በአንድነት ሲያመልኩና እርስ በርሳቸው ሲጽናኑ ያድጋሉ። ሆኖም ክርስቲያኖች አብረው ከመሰብሰብ የሚያፈገፍጉበት ሁለት ወቅቶች አሉ። አንደኛ፤ አንዳንድ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የሐሳብ መቃረን ሲኖራቸው መገናኘታቸውን ያቋርጣሉ። ሁለተኛ፥ የስደት መነሣት አዝማሚያ ካለ ክርስቲያኖች ከመሰብሰብ ይቆጠባሉ። የዕብራውያን ክርስቲያን ከአሕዛብ ጋር ሲሰበሰቡ ታይተው በሌሎቹ አይሁዳውያን እንዳይሰደዱ ይፈሩ ነበር፤ ችግራቸውም ይህ ነበር።

17ኛ ጥያቄ፡- በጥቃቅን ችግሮች ምክንያት ክርስቲያኖች አብሮ ከማምለክና ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ የተቆጠቡበትን ጊዜ አይተህ ታውቃለህ?

አንድ ክርስቲያን ለብቻው ጠንካራ ሆኖ ሊያድግ አይችልም። እግዚአብሔር የክርስቶስ ሰውነት በሆነው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስገብቶናል። ምንም እንኳ አንዳንዶች «እኔ መጽሐፍ ቅዱሴን የማነበውና የምጸልየው በቤቴ ውስጥ ነው» ቢሉም ይህ በቂ አይደለም። በእምነታቸውም መቼውም ቢሆን ጠንክረው አያድጉም። በዚህም ምክንያት ወዲያውኑ በኃጢአት ይወድቃሉ፥ በሐሰተኛ ትምህርትም ይያዛሉ ወይም እምነታቸውን ይክዳሉ።

5. እርስ በእርሳችን እንመካከር፡- ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ከጌታ መንገድ የሚፈናቀሉና በኃጢአት የሚወድቁ ሌሎች የሚጠብቋቸውና የሚመክሯቸው ክርስቲያኖች ሳይኖሩ ሲቀሩ ነው። ለማደግና በፈተና ላይ ጸንተን እንድንቆም አንዳችን ለአንዳችን እናስፈልጋለን። ስለዚህም ከቅናት፥ ከጥላቻ ወይም ከጭቅጭቅ ተነሥተን እርስ በእርሳችን እንድንጠፋፋ ሳይሆን ሁሌ እርስ በእርሳችን እንድንመካከር ነው መሻት ያለብን።

18ኛ ጥያቄ:- ክርስቲያኖች ተሰብስበው እንዲመካከሩ ቤተ ክርስቲያንህ አመቺ ሁኔታን የምታዘጋጀው እንዴት ነው?

ጸሐፊው ከሚሰጣቸው ትዕዛዛት መካከል ሦስቱ የሚመለከቱት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለንን ግንኙነት መሆኑን መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። ለምን? እውነተኛ ክርስቲያኖች የሆኑ ሁሉ የፈለጉት ቤተ ክርስቲያን አባል ይሁኑ፤ የአንድ ቤተሰብ አባሎች ናቸው። የእነርሱ ራስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለደኅንነታቸው ውድ የሆነውን ደሙን አፍስሶላቸዋል። ክርስቲያኖች አናሳ በመሆናቸው ሁሌም ቢሆን ስደት ያጋጥማቸዋል። እርስ በእርሳችን ከምንነካከስ የክርስቶስን አካል ለማጠንከር ስንል አብረን በመሥራት ለእርሱ ታማኝ ሆነን መቆም ይኖርብናል።

19ኛ ጥያቄ:- ሀ) የተለያዩ የክርስትና ቡድኖች እርስ በእርሳቸው እንዴት ለመጠፋፋት እንደሚጥሩ ምሳሌዎችን ስጥ።

ለ) አብረው በመሥራት እርስ በእርሳቸው ለእነርሱ ጥቅም ሲሉ ሊመካከሩና ሊጸናኑ የሚችሉባቸውን መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

ሐ) ሌሎችን ለማጽናናት የምትጥረው ምን ምን ነገሮችን በማድረግ ነው?

ለእግዚአብሔር መንግሥት አብረን መሥራት ያለብን ቀኑ እየቀረበ በመምጣቱ ነው። ቀኑ የተባለው በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣበት ቀን ነው። የጥንት ክርስቲያኖች በእነርሱ የሕይወት ዘመን ዳግም ምጽአት የሚሆን ይመስላቸው ነበር። እኛም የኢየሱስ ክርስቶስን ምፅአት ልንጠባበቅ ይገባናል። ያለምንም ቆይታ ኢየሱስ ይመጣል ብለን የምንጠባበቅ ከሆነ አንዳችን አንዳችንን ለማጥፋት ጊዜ አንወስድም ነበር። ጊዜያችንን ወንጌልን በማሰራጨትና ሌሎች እንዲያድጉ በመርዳት እያሳለፍን ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ታማኞች ሆነን እንጠባበቀዋለን።

20ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለጌታ ዳግም ምፅአት ዝግጁ ነህ? ይህንን በሕይወትህ የገለፅከው እንዴት ነው?

# ሦስተኛ ቀን:- ዕብራውያን 10:26-31

ለአማኞች የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልና ክፍት የደኅንነት መንገድ ለኃጢአተኞች መገኘቱ እራሱ ትልቅ በረከት ነው። ወንጌሉን ለማመንና ለመታዘዝ አሻፈረኝ ላሉ ሰዎች ደግሞ ይህ ወንጌል በእነርሱ ላይ ስለሚመጣው ታላቅ ፍርድ ይናገራል። ወንጌሉን የሚሰብኩትን ጳውሎስ እንደተናገረው በሚድኑትና በሚጠፉት ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና፤ ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ለእነዚያም ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን፤ (2ቆሮ.2:15-16)።

በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ሞት አማካይነት የተገኘውን ታላቅ ደኅንነት ካስረዳ በኋላ በፈተና ውስጥም ቢሆን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ታማኝ ሆነው ጸንተው መቆም እንዳለባቸው ከነገራቸው በኋላ ጸሐፊው በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት የአይሁድ ክርስቲያኖች እንዳይክዱ ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል።

21ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 10:26-31 አንብብ።

ሀ) አንድ ሰው በማወቅ ዝም ብሎ ኃጢአት የሚሠራ ከሆነ ውጤቱ ምንድን ነው?

ለ) ጸሐፊው የሚናገረው ስለምን ዓይነት ኃጢአት ነው?

ሐ) አንዱ በኢየሱስ ያለውን እምነት ሲክድ የሚሆኑት ሦስት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? (ቁጥር 29)

መ) የጌታን ባህርይ በተመለከተ ሰውዬው እምነቱን ላለመካድ ሲል ማስታወስ የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

ዕብራውያን 10:26-31:- በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ አራተኛው ዋነኛ ማስጠንቀቂያ ነው። እንደምታስታውሰው የአይሁድ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ክደው ወደ ቀድሞው ሃይማኖታቸው ለመመለስ ሲያመነቱ ነበር። ይህ የሆነበት ዋነኛው ምክንያት ስደትን በመፍራታቸው ነው።

22ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ክርስቲያኖች ላይ ከሆነው ነገር ጋር ይህ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው ኃጢአት ብሎ የሚናገረው የክሕደትን ኃጢአት ነው፥ ይህም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለን እምነት መተው ነው። ይህ ሐሳብ የተወሰደው በብሉይ ኪዳን በማወቅ በፈቃዱ የእግዚአብሔርን ኪዳን የናቀ ሞት እንደሚፈረድበት ከሚጠቅሰው ክፍል ላይ ነው።

የክሕደት ኃጢአት እጅግ አስቀያሚ የሆነው እንደገና ለማመን ባለመቻሉ ላይ አይደለም። ነገር ግን ሁለት የሚሆኑ ዋና ዋና ነገሮች አሉ። አንደኛ፤ እውነቱን አውቆ ለሚክድ ሰው ልቡ ይደነድንና እንደገና እውነቱን አውቆ ለማመን ይከብደዋል። ሁለተኛ፤ አንድ ሰው እውነቱን ከካደ በማያምኑ ሰዎች ጎራ ውስጥ ይመደባል። የኢየሱስ ክርስቶስን መሥዋዕትነት ከካደ ሌላ የመዳን መንገድ የለም። የእንስሳ መሥዋዕት ተመልሶ እንደገና የኢየሱስን መሥዋዕትነት ሊተካ አይችልም። ስለዚህ ከኃጢአት መሥዋዕት ውጪ የሚቀረው ነገር ቢኖር ከእግዚአብሔር ጠላቶች ጋር ለዘላለም በገሃነም ውስጥ መኖር ነው።

የዕብራውያን ጸሐፊ አንድ አስፈላጊ የሆነ እውነትን ያሳስበናል። ብዙ ሰዎች ማንኛውም ሃይማኖት የኃጢአት ምሕረትን አገናፅፎ አንድን ሰው ወደ መንግሥተ ሰማያት ለማድረስ ብቁ ነው ማለትን ይወዳሉ። አንድ ሰው አርቶዶክስም ሆነ ፕሮቴስታንት ወይም እስላም ምንም ልዩነት የለውም ይላሉ። በመጨረሻም ሁሉም ይድናሉ ጸሐፊው ግን ምሕረት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኩል ብቻና በሞቱም በማመን መሆኑን በአንክሮ ያመለክታል። ከዚህ የተለየ እምነት የሚከተሉ ማንኛቸውም ሰዎች በኃጢአታቸው ይጠፉና ተቀጥተውም ወደ ገሃነም ይወሰዳሉ።

23ኛ ጥያቄ:- ሀ) ይህ የሌላ እምነት ተከታዮች ለሆኑ ወንጌልን ስለማካፈል አስፈላጊነት የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው?

ለ) በኢየሱስ ብቻ ማመን ሳይሆን ሌሎችም ሃይማኖቶች ወደ መንግሥተ ሰማያት ይወስዳሉ ብለው የሚያምኑ ሰዎችን ታውቃለህ?

ሐ) እንዴት አድርገህ ነው መልስ የምትሰጣቸው?

በብሉይ ኪዳን ዘመን በማወቅ ኪዳኑን የማይቀበሉ ሰዎች በሞት ይቀጡ ነበር፤ (ለምሳሌ ዘሌዋውያን 24፡10-23)። አዲሱ ኪዳን የበለጠ በረከቶችንና የኃጢአት ሥርየትን የሚያጎናፅፍ ነው። ከእነዚህ በረከቶች ጋር ግን ከብሉይ ኪዳኑ ጊዜ የበለጠ ቅጣት አብሮት ይገኛል። ቅጣቱ ሥጋዊ ሞት ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን በገሃነም የዘላለም ሞት እንጂ።

24ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 2፡1-16 አንብብ። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል አውቀው በሚክዱ ሰዎች ላይ የሚደነገገውን ፍርድና የእግዚአብሔርን ቃል ባልሰሙ ሰዎች ላይ የሚፈረደውን ፍርድ በሚያነፃፅርበት ወቅት የሚናገረው ነገር ምንድን ነው?

ክርስቲያኖች ነን ብለው በኢየሱስ ያላቸውን እምነት ግን የሚክዱ ሰዎች በላያቸው ላይ ከፍተኛ ቅጣትን የሚያመጡ ሦስት ነገሮችን ያደርጋሉ፤ እነዚህም፡-

1. የእግዚአብሔርን ልጅ በእግራቸው ይረግጡታል። በሌላ አነጋገር ያምኑት የነበረውን ኢየሱስን ያዋርዱታል። ሌሎች በክርስቶስ ስም እንዲሳለቁ ያደርጋሉ። በዚህም የኢየሱስ ስም ተራ ይሆናል ማለት ነው።

25ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው እምነቱን ሲክድ ያየኸው እንዴት ነው?

2. የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር ይቆጥሩታል። በሌላ አነጋገር የአዲስ ኪዳን ጠንሳሽ የሆነውን የኢየሱስን ሞት እንደ ተራ ነገር አድርገው ይመለከቱታል። ኢየሱስ የሞተው ዝም ብሎ ነው፤ ከማንኛውም ሰው ደም የእርሱም ደም ምንም ለውጥ የለውም ይላሉ።

3. የፀጋውንም መንፈስ ያዋርዳሉ። በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት ይክዳሉ፤ የሚሰጣቸውንም ፀጋ ስጦታን አይቀበሉትም ማለት ነው።

26ኛ ጥያቄ፡- ትምህርት አሥራ ሦስትን ተመልከት። እነዚህ ቁጥሮች ስለ ክርስቲያኖች ነው የሚናገሩት ወይስ አይደለም ብለው የቀረቡትን የተለያዩ ሐሳቦች በዝርዝር ጻፍ።

በትምህርት አሥራ ሦስት ያጠናነው ዕብራውያን 6፡4-6 ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በዕብራውያን መጽሐፍ የተሰጡትን ማስጠንቀቂያዎች በተመለከተ ሦስት ዋና ዋና ትርጓሜዎችን ተመልከተናል።

አንደኛ፤ አንዳንዶች እነዚህ ቁጥሮች የተጻፉት እምነታቸውን ለመካድ ብሎም ደኅንነታቸውን ወደ ማጣቱ ደረጃ ስለደረሱት ሕፃን ክርስቲያኖች ነው የሚናገሩት ይላሉ።

ሁለተኛ፤ «እነዚህ፥ የዕብራውያን መጽሐፍ ደራሲ ክርስቲያኖችን ለማስፈራራት ሲል የከሕደታቸው ውጤት በእርግጥ የሚሆን ቢሆን ኖሮ ምንኛ አስከፊ ይሆን እንደነበር ለማሳየት ብሎ ባልሆነ ኃይለኛ ቋንቋ እንደተጠቀመ የሚመስላቸው በሳል ያልሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው» ብለው የሚያምኑ ሌሎችንም ሰዎች አይተናል። «በእውነተኛ ክርስቲያኖች ላይ ሊደርስ እንደማይችል ልበናው እያወቀ ዝም ብሎ የማይሆን ሁኔታን ነበር እያቀረበ የነበረው» ይላሉ።

ሦስተኛ፤ ሌሎች ደግሞ ጸሐፊው የሚጽፈው ከክርስቲያኖች ጋር ብቻ በማምለካቸው ክርስቲያኖች ነን ብለው ለሚያስቡ ሰዎች ነው ይላሉ። ሆኖም ጀርባቸውን ወደ ኢየሱስ አዙረው እምነታቸውን ከካዱ በመጀመሪያም እውነተኛ ክርስቲያኖች እንዳልነበሩ ማረጋገጫ ይሆናል። ወንጌሉ ልባቸውን ሳይለውጠው እራሳቸውን ክርስቲያን ብለው ይጠሩ ነበር። እውነተኛው የክርስቲያን መለኪያ እምነቱን እስከ መጨረሻ ድረስ አጥብቆ መያዙ ነው።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን የፍቅር፥ የምሕረት፥ የፀጋና የርኅራኄ አምላክ እንደሆነ ነው የምናየው። በእርግጥ ይህ እውነት ነው። ነገር ግን ይህ ስለ እግዚአብሔር የሚገልጽ ቁንጽል እውቀት ነው። እግዚአብሔር ጻድቅ ቁጡና የሚቀጣ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ከፀጋው የተነሣ ለኃጢአተኞች ሙሉ ደኅንነትን ያጎናፅፋቸዋል። ይህን ደኅንነት ሲክዱ ደግሞ እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው። አንዳንዶች በኃጢአትና በእርኩሰት የተሞላ ሕይወት ይኖሩ ይሆናል፥ የእግዚአብሔርን ቅጣት ግን አያመልጡም።

ጸሐፊው ሁለት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ይጠቅሳል፤ እነዚህም ኦሪት ዘዳግም 32፡36 እና መዝ. (135)፡ 14 ናቸው። እግዚአብሔር ታላቅና የሚፈራ አምላክ ነው። ዘላለማዊ ፈራጅ ነው፤ ሰዎች ሁሉ ፍርድን ይቀበላሉ። ክርስቲያኖች የሚፈረድባቸው ለጌታ በሠሩት ሥራ መሠረት ነው። ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የሚፈረድባቸው ባለማመናቸው ነው። ስለ ሕይወታችን በእግዚአብሔር ፊት ቆመን መልስ እንደምንሰጥ ሁልጊዜ ማስታወስ ይኖርብናል። ስደትን ለማምለጥ ስንል ወደ ዓለም ብንመለስ፥ ዘላለማዊ የሆነውን የገሃነም ቅጣት በላያችን ላይ እንደምናመጣ መገንዘብ ይኖርብናል። ለእግዚአብሔር ስንሠራ በኃጢአት ውስጥ እንድንኖር የሚያደርግ ፈተና ቢገጥመን እንኳ ይህቺ እራሷ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደምትመረመር ማወቅ አለብን።

27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ ሊመጣ ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ ለእግዚአብሔር ንጹህ የአገልግሎት ሕይወት እንድኖርህ እንዴት አድርጎ ሊረዳህ ይችላል? ለ) ይህ እውነታ ሌሎች ለእግዚአብሔር እንዲኖሩ ሊያበረታታቸው የሚችለው እንዴት ነው?

## አራተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 10፡32-39

ምንም እንኳ ጸሐፊው እምነታቸውን እንዳይክዱ ጥብቅ የሆነ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም እውነተኛ የሆኑት ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው እንደሚቆዩ

እርግጠኛ ነበር። ክርስቲያኖቹ እውነተኛ አማኞች መሆናቸውን ለማረጋገጥ መጀመሪያ ባመኑበት ወቅት ክርስቲያኖቹ የነበራቸውን ሕይወት ይጠቅሳል። ምንም እንኳ የአንድ ሰው ውጫዊ ባህርይ እውነተኛ ክርስቲያን ስለ መሆኑ ማስተማመኛ ባይሆንም አንድ ሰው በኢየሱስ ካመነ ምንጊዜም አዲስ ፍጥረት ነው። ሕይወቱ በመቀየሩ ምግባሩም የግድ ይለወጣል።

28ኛ ጥያቄ፡- በኢየሱስ አንዴ ካመንክ በኋላ ሕይወትህ እንዴት እንደተለወጠ አብራራ።

29ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 10፡32-39 አንብብ።

ሀ) ክርስቲያኖች በኢየሱስ የነበራቸው እምነት እውነተኛ እንደነበር የሚጠቁሙ የተለያዩ ምግባሮችን በዝርዝር ጻፋቸው።

ለ) በችግር ጊዜ በተለይ የሚያስፈልገው ባህርይ ምንድን ነው? (ቁጥር 38)።

ክርስቲያኖቹን በእምነታቸው ለማጽናት ጸሐፊው መጀመሪያ በክርስትና ሕይወታቸው የተፈጸመውን ነገር ያስታውሳቸዋል። የአይሁድ ክርስቲያኖች ባመኑበት ወቅት ወዲያውኑ ስደት መጣባቸው በዚህም በጣም ኀዘንተኞች ሆነዋል። ሆኖም ይህንን ሁሉ በደስታ ጸንተው አሳልፈውታል። ለወንጌሉ ሲባል የተጋፈጧቸውን አራት የተለያዩ ችግሮች ያስታውሳቸዋል።

1. በሕዝብ ፊት ተዋርደዋልም ተሰደዋልም። ምናልባትም በገበታ ቦታ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሄዱበት ወቅት ሕዝቡ ክርስቲያኖቹን ያበሽቋቸው ይሆናል።

2. መከራና ስደት ከተቀበሉት ጋር አንድ ሆኑ። እምነታቸውን ለመደበቅ አልሞከሩም። በባለሥልጣኖቹ መከራ ይቀበሉ የነበሩትን ለብቻቸው ችግሩን እንዲጋፈጡ አላደረጓቸውም። እንዲያውም አንዱ የእነርሱ አባል መከራ ሲቀበል እነርሱም ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ሳይሸሹ ይገልጻሉ።

3. ስለ እምነታቸው በእሥር ቤት ከነበሩ ጋር አብረው ያዝኑ ነበር። ምግብ በማምጣት ይጎበኟቸውና ያጽናኗቸው ነበር። ይህም እራሳቸውን መሸሸግ እንዳልፈለጉና አብረው ከእነዚያ ጋር ቢታሰሩም ፈቃደኛ ነበሩ ማለት ነው።

4. የንብረታቸውን መጥፋት በሙሉ ደስታ ነበር የተቀበሉት ሱቆቻቸውን ቤቶቻቸውን ወይም የእርሻ ቦታዎቻቸውን ሲያጡ ምንም አያጉረመርሙም ነበር። ስለ ኢየሱስ ስም ሲሉ መከራ እንደሚቀበሉ ስለተገነዘቡ ሁሉን ነገር በፀጋ ተቀብለዋል።

30ኛ ጥያቄ፡- ማቴ.5፡11-12 እና ያዕቆብ 1፡2-3 አንብብ። ለስደት የክርስቲያን ምላሽ ምን መሆን አለበት?

31ኛ ጥያቄ፡- በዚህ ሥፍራ እንደተገለጸው በአንተና በቤተ ክርስቲያንህ ላይ ተመሳሳይ ሁኔታ የገጠማችሁ እንዴት ነው?

ለዚህን ያህል ስደቱን ሲቋቋሙ ቆይተው እምነታቸውን ቢክዱ ምኝነት ነው። ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው በመቆማቸው ታላቅ ብድራት ይጠብቃቸዋል። ነገር ግን ቃል የተገባላቸውን ብድራት ለመቀበል መጽናት ያስፈልጋቸዋል።

ስደቱ እንዳያሸንፋቸው በእግዚአብሔር በመታመን መኖር እንዳለባቸው ለማሳየት ጸሐፊው ሌላ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ይጠቅሳል፤ (ዕንባቆም 2፡3-4)። በሚቀጥለው ሳምንት ጥናታችን የእምነት ምሳሌ የሆኑትን ከብሉይ ኪዳን ላይ እንመለከታለን። በዚህ ሰይጣን በነገሠበት ጨለማ ዓለም ውስጥ ጻድቃን የሆኑት የእግዚአብሔር ልጆች እምነታቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል። አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይገለጻል፤ ያኔ በእምነት ሳይሆን እያየነው እንከተለዋለን። አሁን ግን እስከ ሞታችን ድረስ ወይም እርሱ እስከመጣ ድረስ በእምነት ጸንተን መቆም አለብን። ይህን ስናደርግ ኢየሱስ ይዞ ስለሚመጣው ብድራት እርግጠኞች እንሆናለን። አሁን ለእግዚአብሔር ታማኝ ነህ ወይ? ለእርሱስ እየሠራህለት ነው?

**አምስተኛ ቀን፡-** የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ተዘጋጅ።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) የሐሰት ትምህርትን ለመቋቋም በቤተ ክርስቲያንህ ልታስተምራቸው የሚገባህን ዋና ዋና እውነታዎች በዝርዝር ጻፍ። እንዴት እንደምታስተምራቸው ዕቅድ አውጣ።

ለ) የኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ብሎ ወደ ምድር መጥቶ ለመሞት መፍቀዱና የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸሙ እኛ ለእግዚአብሔር መስጠት ለሚገባን ምላሽ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

ሐ) 1. ቤተ ክርስቲያንህ በዕብራውያን 10፡19-25 ላይ ያሉትን ትዕዛዞች የምትጠብቀው እንዴት ነው?

2. እነዚህን አምስት ትዕዛዞች መጠበቁ ለእነርሱ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

3. ቤተ ክርስቲያንህ እነዚህን ትዕዛዞች በተሻለ ሁኔታ ልታሟላ የምትችልባቸውን የተለያዩ መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

መ) 1. ባለፈው ዓመት በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ምን ያህል ክርስቲያኖች ናቸው እምነታቸውን የካዱ?

2. ለምንድን ነው እምነታቸውን የካዱት?

3. ዕብራውያን 10፡26-31 በመጠቀም በቤተ ክርስቲያንህ ያሉትን ክርስቲያኖች ከሕደትን በተመለከተ ማስጠንቀቂያ የምትሰጣቸው እንዴት ነው?

ሠ) 1. ክርስቲያኖች ስደትን በደስታና በእምነት መቀበል ያለባቸው ለምንድን ነው?

2. ይህ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት እንደተከናወነ ምሳሌዎችን ስጥ።

5. ጸሎት

# ትምህርት አሥራ ስምንት

ዕብራውያን ምዕራፍ 11

## የመጀመሪያ ቀን:- ዕብራውያን 11፡1-7

ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን በስተመጨረሻ አካባቢ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለውን ተመልክተናል፤ (ዕብራውያን 10፡38)። የክርስቲያን ዋነኛ ባህርያት አንዱ እምነት ነው። ማንኛውም ዓይነት ስደት ሊቋቋሙና እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ደስ ሊያሰኙ የሚችሉ እምነታቸውን ጠብቀው የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። እምነት ሁኔታዎች ሁሉ ድፍን ባሉበት ወቅት አንድን ሰው ለእግዚአብሔር ታማኝ አድርጎ የሚያቆየው ነገር ነው። ስለዚህም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) በራስህ ቃል እምነት ምን እንደሆነ ግለጽ።

ለ) በሕይወትህ ውስጥ እምነትህን እንዴት አድርገህ እንደገለጽክ ምሳሌዎችን ስጥ።

እምነት የሚለው ቃል በብዙ ሰዎች ዘንድ የተለያየ ትርጓሜ ይሰጠዋል። ለአንዳንዶች እምነት ማለት ሃይማኖት ነው፥ ለዚህም ነው በአማርኛ እምነትና ሃይማኖት የሚሉት ቃላት በጣም የሚዛመዱት ለሌሎች ደግሞ አንድን ነገር አመዛዝና እንደማመን ዓይነት ትርጓሜ አለው። ስለዚህም አንድን ሰው የተናገርኩትን ታምናለህ? ብለን የምንጠይቀው የአመኔታው ሁኔታ ስለሚለያይ ነው። በዚህ ምክንያት አንድ ሰው አማኝ ነው ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እምነትም ስንል ምን እንደሆነ ማብራራት ይኖርብናል።

ሰው ሁሉ እምነት አለው። አንዳንድ ሰዎች እምነታቸውን በሚሠሩት ጥሩ ሥራ ላይ ያደርጋሉ፥ አንዳንዶች ደግሞ በቤተ ክርስቲያናቸው ይተማመናሉ ወዘተ...። ታዲያ ዋናው ነገር አንድ ሰው እምነት አለው ወይ ሳይሆን በትክክለኛው ነገር ላይ ይተማመናል ወይ የሚለው ሐሳብ ነው። ወደ ደኅንነት የሚመራን አንድ ብቸኛ እምነት ነው።

2ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን ምዕራፍ 11 አንብብ። የተለያዩ ሰዎች እምነታቸውን እንዴት እንደገለጹ በዝርዝር ጻፍ።

# ትምህርት አሥራ ስምንት

ዕብራውያን ምዕራፍ 11

## የመጀመሪያ ቀን:- ዕብራውያን 11:1-7

ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን በስተመጨረሻ አካባቢ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለውን ተመልክተናል! (ዕብራውያን 10:38)። የክርስቲያን ዋነኛ ባህርያት አንዱ እምነት ነው። ማንኛውም ዓይነት ስደት ሊቋቋሙና እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ደስ ሊያሰኙ የሚችሉ እምነታቸውን ጠብቀው የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። እምነት ሁኔታዎች ሁሉ ድፍን ባሉበት ወቅት አንድን ሰው ለእግዚአብሔር ታማኝ አድርጎ የሚያቆየው ነገር ነው። ስለዚህም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ) በራስህ ቃል እምነት ምን እንደሆነ ግለጽ።

ለ) በሕይወትህ ውስጥ እምነትህን እንዴት አድርገህ እንደገለጽክ ምሳሌዎችን ስጥ።

እምነት የሚለው ቃል በብዙ ሰዎች ዘንድ የተለያየ ትርጓሜ ይሰጠዋል። ለአንዳንዶች እምነት ማለት ሃይማኖት ነው፣ ለዚህም ነው በአማርኛ እምነትና ሃይማኖት የሚሉት ቃላት በጣም የሚዛመዱት ለሌሎች ደግሞ አንድን ነገር አመዛዘና እንደማመን ዓይነት ትርጓሜ አለው። ስለዚህም አንድን ሰው የተናገርኩትን ታምናለህ? ብለን የምንጠይቀው የአመኔታው ሁኔታ ስለሚለያይ ነው። በዚህ ምክንያት አንድ ሰው አማኝ ነው ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እምነትም ስንል ምን እንደሆነ ማብራራት ይኖርብናል።

ሰው ሁሉ እምነት አለው። አንዳንድ ሰዎች እምነታቸውን በሚሠሩት ጥሩ ሥራ ላይ ያደርጋሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ በቤተ ክርስቲያናቸው ይተማመናሉ ወዘተ...። ታዲያ ዋናው ነገር አንድ ሰው እምነት አለው ወይ ሳይሆን በትክክለኛው ነገር ላይ ይተማመናል ወይ የሚለው ሐሳብ ነው። ወደ ደኅንነት የሚመራን አንድ ብቸኛ እምነት ነው።

2ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን ምዕራፍ 11 አንብብ። የተለያዩ ሰዎች እምነታቸውን እንዴት እንደገለጹ በዝርዝር ጻፍ።

ትክክለኛ የሆነ እምነት አራት ነገሮችን ያካተተ ነው። አንደኛ፥ እምነት ትክክለኛ የሆነ መሠረት ያስፈልገዋል። እምነታችን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መሆን አለበት እንጂ በመልካም ሥራችን ወይም በሐሰተኛ አማልክት ላይ መሆን የለበትም።

3ኛ ጥያቄ:- እምነታቸውን በተሳሳተ ቦታ ላይ የሚያደርጉ ሰዎችን ምሳሌ ስጥ።

ሁለተኛ፤ እምነታችን መመሥረት ያለበት በተረዳነው እውነት ላይ ነው። አንድ ስለሚያምንበት ነገር ጠንቅቆ ሳያውቅ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ቢል በቂ አይደለም። እውነተኛ እምነት ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ደኅንነት ወዘተ... ማወቅን ወይም መገንዘብን ያካተተ ነው። ይህ ዕውቀት በመጀመሪያ ላይ በከፊልም ቢሆን አንድ አዲስ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ ያለው ግንዛቤ በዚሁ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

ሦስተኛ፤ እምነት ራስን አሳልፎ የመስጠት ሁኔታን የሚጠይቅ ነው። ስለዚህም ለደኅንነቱ በኢየሱስ የሚያምን ማንኛውም ሰው በመልካም ሥራው ላይ መተማመኑን ትቶ ለመዳን ሲል ሙሉ እምነቱን ስለ ኃጢአቱ በሞተው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማድረግ አለበት። ይህ ሰው ሕይወቱን በሙሉ ለጌታ መስጠትና በሙሉ ልቡ ጌታን ለመከተል መወሰን አለበት። በኢየሱስ እናምናለን እያልን ሕግጋቱን የማንጠብቅ ከሆነ እምነታችን የሚያድነን ዓይነት አይደለም። በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ያደጉ ብዙ ሰዎች ወላጆቻቸው ክርስቲያን በመሆናቸው ለደኅንነት የሚያበቃ እምነት ያላቸው ይመስላቸዋል። እውነቱን ሊያውቁ ይችላሉ፥ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በእምነት እስካልተቀበሉት ድረስ እምነታቸው የሚያድናቸው አይሆንም።

4ኛ ጥያቄ:- ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ በእምነት ተቀብለኸዋልን? የተቀበልክበት ትክክለኛ ቀን ታውቀዋለህ? ካወቅኸው ጻፈው።

አራተኛ፤ እምነት ዝም ብለን በሐሳባችን የምንፈጽመው ነገር ብቻ ሳይሆን በተግባርም መገለጽ ያለበት ነገር ነው። በዚህ ምክንያት ነው ያዕቆብ «እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነው» ያለው (ያዕቆብ 2:24፥ 26)። በምዕራፍ 11 ላይ የዕብራውያን ጸሐፊው ዋና ሐሳብ ይህ ነው። የብሉይ ኪዳን የእምነት ሰዎች የታወቁት በታላቅ ችግር ጊዜ ለእግዚአብሔር ታዛዥ በመሆናቸው ነው እንጂ ትክክለኛ እምነት አላቸው ተብለው አይደለም። ስለዚህም የብሉይ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታት ለእኛ በአዲስ ኪዳን ሥር ለምንኖር የእምነት ምሳሌዎች ናቸው።

5ኛ ጥያቄ:- ለአንድ ክርስቲያን እምነቱን የሚገልጽለት ሥራዎቹ ምን ምንድን ናቸው? እምነት እንዳለው የሚያሳየውስ ምን ምን ነገሮችን ከመሥራት ሲቆጠብ ነው?

6ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 11:1-7 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ:-

ሀ) ደራሲው እምነትን እንዴት ይተረጉማታል? ምንስ ማለት ነው?

ለ) በእግዚአብሔር ሕዝቦች ሕይወት ውስጥ እምነት እንዴት መገለጽ እንዳለበት ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች ስም ዝርዝርና እምነታቸውንም እንዴት አድርገው እንደገለጹት ግለጽ።

ለዕብራውያን ጸሐፊ አንዱ ቁልፍ የሆነው የእምነት ነገር ሕይወትን ፊት ለፊት በማያዩት ነገር መሥርቶ መኖር ነው። እንደምታስታውሰው ጸሐፊው አዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ታላላቅ የሆኑ የተስፋ ቃሎች ሰጥቷል ብሏል። ሙሉ የኃጢአት ምሕረት እንደሚገኝና የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በሰዎች ልብ ላይ እንደሚጻፍ ቃል ኪዳን ተደርጓል። በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን እንደምንቀርብ ተስፋ ተሰጥቶናል። ይህም ሆኖ ከእነዚህ በረከቶች ውስጥ አንዱም ቢሆን በዓይን የሚታይ አይደለም።

እምነት በሰዎች ዓይን ሊታዩ የማይችሉትን ነገሮች እንደሚታዩና እርግጠኛ እንደሆነ አድርጎ ይቆጥራቸዋል። ምንም እንኳ የተመሠረተው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቢሆንም ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ለዓይን የሚታዩ ምልክቶችን አይሰጥም። ይህም ሆኖ አማኙ የሚኖረው እነዚህ የተስፋ ቃሎች እንደተፈጸሙ አድርጎ በመቁጠር ነው። «የጥንቶቹ ሰዎች» የዚህ ነገር አርአያ ናቸው፤ እኛም የእነርሱን ምሳሌነት መከተል አለብን። ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ሰዎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይዘውት የነበረው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ነው እንጂ እንዴት እንደሚፈጸም ምንም አያውቁም ነበር። በሥጋዊ ዐይናቸው የነገሮቹን መፈጸም እያዩ ከማመን በማይታየው የእግዚአብሔር ኪዳን ላይ እምነታቸውን በመጣል በእርሱ ላይ ሕይወታቸውን መመሥረቱን መርጠዋል። ባለን ወይም በምናየው ነገር ላይ ብቻ የምንተማመን ከሆንን ምንም እምነት ወይም ተስፋ የለንም ማለት ነው፤ (ሮሜ 8፡24)።

7ኛ ጥያቄ፡- የማይታዩ ነገሮች ሆነው ያመንከባቸው ወደ በኋላም ሕይወትህን የቀየሩትን አንዳንድ ነገሮች ለምሳሌ ያህል ግለጽ።

በክርስትና ሕይወት ውስጥ ብዙዎቹ ዋና ዋና ትምህርቶች በሥጋዊ ዓይን የማይታዩ ናቸው። (ለምሳሌ፤ ከሙታን መነሣት፥ ዘላለማዊ ሕይወት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ መንፈስ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር)። እነዚህ ነገሮች ከምናየውና ከምንዳስሰው ነገር ይበልጥ እውነተኛ ሆነው የሚታዩን በእምነት ዓይን ስናያቸው ብቻ ነው።

በዕብራውያን 11 ላይ ጸሐፊው ብዙ የእምነት ምሳሌዎችን ይሰጣል። ለምሳሌ፤ በመጀመሪያ እምነት ሊኖረን የሚያስፈልገው በፍጥረት ሥራ ላይ ነው (ቁጥር 3)። እግዚአብሔር ምድርን ሲፈጥር ማናችንም በምድር ላይ አልነበርንም። ስለዚህም ስሜቶቻችንን በመጠቀም እግዚአብሔርን ዓለምን ፈጥሯል ብለን ልናሳምን አንችልም። ይህ እውነት ለመቀበል የማይፈልጉ ዓለም እንዴት እንደተፈጠረ የሚገልጽ የራሳቸው የሆነ መላምት ያወጣሉ። ብዙዎች አዝጋሚ ለውጥ በሚባለው መላምት ያምናሉ። በዚህ መላምት ለማመን አንድ ክርስቲያን ሁሉን ነገር እግዚአብሔር ፈጥሯል ብሎ ለማመን የሚወስድበት ያህል ነው። ይህም የሆነው ማንም ሰው ዓለምን ሲፈጥር ባለማየቱ ነው።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ትምህርት ቤታችሁ ስለ አዝጋሚ ለውጥ ያስተምራል?

ለ) ሲያስተምራችሁ እንደ አግራሞ መላምት አድርገው ነው የሚያስተምሯችሁ ወይስ ሌላ ምንም አግራሞ የሌለው እውነተኛ ነገር ነው ብለው ነው የሚያስተምሯችሁ?

ሐ) ክርስቲያኖች በመሆናችሁ በዚህ መላምት ለሚያምኑ ሰዎች ምን ዓይነት መልስ ነው የምትሰጧቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ ያስተምረናል፤ (ዘፍጥረት ምዕራፍ 1)። እነዚህ በዓይናችን የምናያቸው ነገሮች በሙሉ የተገኙት ከምንም ነው። ይህን በእምነት መቀበል አለብን። አንድ አዝጋሚ ለውጥ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት በማይቀበሉ መላምቶች ማመኑ በእግዚአብሔር ቃል እንደማናምን ያስቆጥራል።

ሁለተኛው የእምነት ምሳሌ፤ የአቤል ሕይወት ነው፤ (ቁጥር 4) (ዘፍጥ.4፡3-7)። የአዳምና የሔዋን ልጆች ስለሆኑት ስለ አቤልና ስለ ቃኤል የተነገረውን ታሪክ ታስታውሳለህ? ሁለቱም ወደ እግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ፤ እግዚአብሔር ግን የአቤልን ብቻ ተቀበለ። ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች ተሰጥቷል። አንዳንዶች የአቤል መሥዋዕት ደም በመሆኑና የቃኤል ግን ባለመሆኑ ነው ይላሉ። ለዕብራውያን ጸሐፊ ግን እግዚአብሔር የቃኤልን ትቶ የአቤልን መሥዋዕት የተቀበለበት ምክንያት፡- አቤል «በእምነት» በማቅረቡ ነው። እግዚአብሔር ቃኤል አስተሳሰቡን ለውጦ እሱን በእምነት እንዲያመልከው አግራሞ ሰጥቶታል። ቃኤል ግን እምነት እንደሌለው ባለመታዘዙ አሳየ።

ከዚህ የምንማረው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ውጫዊው ተግባራችን ሳይሆን ውስጣዊው አመለካከታችን ነው፤ (ምሳሌ 15፡8)። እምነት የሚታየው ትክክለኛ የሆነውን ነገር ስንሠራ ብቻ ሳይሆን ልባችንም በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ ሆኖ ሲገኝ ነው፤ (ይህም ትሑት፥ ንስሐ የምንገባ፥ ወዘተ ስንሆን ነው)

ልክ የአቤል ደም የወንድሙን ሥራ በመቃወም እንደ ምሥክር ከምድር እንደ ጮኸ ሁሉ ዛሬም ለእኛ እንዴት አድርገን እግዚአብሔርን በእምነትና በእውነተኛ ልብ ቅንነት እንደምንቀርብ ሕይወቱ ምሳሌ ይሆነናል።

9ኛ ጥያቄ፡- ልባችን ቅን ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ባለመሆኑ ምክንያት በዛሬው ጊዜ እግዚአብሔርን ስናመልክ ተቀባይነት የሌለው ምን ዓይነት ሥራ ነው ልንሠራ የምንችለው?

ሦስተኛው የእምነት ምሳሌ፤ ሄኖክ ነው፤ (ከቁጥር 5-6) (ዘፍጥረት 5፡18-24)። ሄኖክ እምነቱን የገለጸው ከእግዚአብሔር ጋር በነበረው የጠበቀ ኅበረት ነው። ብሉይ ኪዳን «ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ» ይላል። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የጠበቀ ኅብረት ሕይወቱን የተቀደሰች እንድትሆን አድርጓታል። ስለዚህም እግዚአብሔርን በጣም ደስ በማሰኘቱ በብሉይ ኪዳን ሞትን ሳያዩ እግዚአብሔር ወሰዳቸው ተብለው ከተጠቀሱት ሁለት ሰዎች መካከል አንዱ አድርጎታል፤ (ሁለተኛው ሰው ኤልያስ ነው)።

በዕብራውያን 11፡6 ላይ ጸሐፊው እምነትን በተመለከተ አንድ ሌላ ዋነኛ የሆነ መመሪያ ይሰጣል። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ማንኛውም ዓይነት ሥራ ለመሥራት ከተፈለገ መሠረቱ እምነት መሆን አለበት። የሄኖክ በእግዚአብሔር መወሰድ እግዚአብሔር በሄኖክና በእምነቱ ደስ እንደተሰኘ ማረጋገጫ ይሆነናል። የፈለግነውን ያህል ጥሩ ነገር ብንሠራ በእውነተኛ እምነት ካልታገዘ እግዚአብሔርን ደስ አያሰኘውም። ይህም ለሌሎች መመሥከር፥ መመፅወት፥ ወዘተ... ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ የምንሠራው በእምነት ላይ በመመሥረት ነው። እግዚአብሔር ደስ የሚሰኘው እስከ መጨረሻው ጽኑ ሆኖ በሚቆም እምነት ላይ ብቻ ነው።

በእምነት ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ያስፈልጋሉ፡- አንደኛ! ወደ እግዚአብሔር ትክክለኛ አመለካከት መኖሩ ነው። ለሁሉም እምነት ወይም ሃይማኖት መሠረት የሆነው ሁሉን የፈጠረ አምላክ እንዳለ ማመኑ ነው። ያለዚህ ለደኅንነት የሚያበቃ ሊኖረን አይችልም። በእርግጥም እግዚአብሔር እንዳለ ካመንን በኋላ ነው በእርሱ ላይ ተመሥርተን እምነታችንን የምናሳድገው። ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችንም እንደሞተ፥ ወዘተ ማመን አለብን። ነገር ግን የዚህ መሠረቱ በእግዚአብሔር ሕልውና ያለን እምነት ነው።

ሁለተኛ! እግዚአብሔር ለሚሹት ሁሉ እሩቅ እንዳልሆነና እንዲሁም በማድረጋቸው ደስ እንደሚሰኝባቸው ማመን አለብን። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር ዝምተኛና የተሸሸገ አምላክ ሳይሆን በእውነተኛ እምነት ለሚጠሩት ሁሉ ፈጥኖ የሚደርስ ነው። ከፈለግነው ወደ እኛ እንደሚመጣ ቃል ገብቶልናል። «ጸሎታችሁን እሰማለሁ፥ እራሴን እገልጥላችኋለሁ፥ እድናችሁማለሁ» ብሎ ቃል ገብቶልናል! (ትንቢተ ኤርምያስ 29፡13)። እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚሰማና እንደሚያድነን ካላመንን መጸለይ አያስፈልገንም። ግን አስተውል፥ እርሱን የመፈለጉን ሐላፊነት እግዚአብሔር የሰጠው ለእኛ ነው። ልባችንን ለእግዚአብሔር የመከፈትና ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ የመፈለጉን ሐላፊነት መውሰድ ያለብን እኛ ነን። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር «ፈቃዴንና እራሴን እገልጥላችኋለሁ» ብሎ ቃል ይገባልናል።

10ኛ ጥያቄ፡- እነዚህ ሁለት ነገሮች በሕይወትህ ውስጥ የገለጡት እንዴት ነው?

አራተኛው የእምነት ምሳሌ የሆነው የኖህ ሕይወት ነው! (ቁጥር 7) (ኦሪት ዘፍጥረት 5፡28-9፡29)። ምንም እንኳ ባያየው ኖህ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ለሚያምን ሰው ጥሩ ምሳሌ ነው። እንደምታስታውሰው እግዚአብሔር ምድርን በውኃ አጠፋታለሁ ብሎ ተናግሮ ነበር። ምንም ዝናብ ሳያይ በአካባቢው ጎርፍ የሚያስነሣ ታላቅ ወንዝ ሳይኖር ኖህ ለብዙ ዓመት ያህል ትልቅን መርከብ ሲሠራ ነበር። ኖህ በእግዚአብሔር መታመኑን ያሳየው መርከቡን በመሥራቱ ነው። ይህ እምነቱ ለቤተሰቡ ደኅንነትን አስገኘለት። ይህ ብቻ አይደለም ይህ እምነቱ የእግዚአብሔርን የውኃ ጥፋት ፍርድ አስከተለ። የእምነትም ፍሬ ጽድቅ ሆነ።

እምነት በሰዎች ውስጥ አንድ ዓይነት በሆነ መንገድ አይገለጽም። የአንዳንዶች እምነት የታየው እግዚአብሔርን ባስደሰተው ልበ ቅንነታቸው ነው። ለሌሎች እምነት የተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደሚፈጸም የሚገልጽ ምንም ዓይነት ምልክት ሳይኖር ትልቅ መርከብ በመሥራት ነው። ሁሉም ግን ሕያው ከሆነው አምላክ ጥሩ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል። በእግዚአብሔርም ቃል መታመንና ምንም እንኳ በስተመጀመሪያ ላይ የተስፋ ጭላንጭል ባያዩም ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ መሥርተው ለመኖር ፈቃደኛ መሆን አለባቸው።

11ኛ ጥያቄ:- በሕይወትህ ውስጥ እምነትህ የተገለጸው እንዴት ነው?

# ሁለተኛ ቀን:- ዕብራውያን 11:8-19

ዕብራውያን ምዕራፍ 11 እምነት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚገለጽ የሚያትት ስለ እምነት የተጻፈ ምዕራፍ ነው። በዚህ ምዕራፍ ጸሐፊው በብሉይ ኪዳን ያሉትን ታላላቅ ሰዎች በመጥቀስ እምነት እንዴት ሕይወታቸውን እንደመራው ያሳየናል። በትናንትናው ዕለት ከፍጥረት ጊዜ አንሥቶ ምድር በውኃ ሙላት እስከጠፋችበት ጊዜ የነበሩትን የተለያዩ ሰዎች ተመልክተናል።

ዛሬ አምስተኛ የእምነት ምሳሌ የሆነውን አብርሃምን እንመለከታለን። የአብርሃም እምነት በእምነት መኖር እንዴት እንደሆነ በደንብ የሚያሳየን ምሳሌ ነው። ስለዚህም በብሉይ ኪዳን ላሉት እሥራኤላውያንና በአዲስ ኪዳን ላሉት ክርስቲያኖች ሁሉ የእምነት አባት ነው! (ሮሜ 4:11-12)።

12ኛ ጥያቄ:- ሮሜ 4:1-12 አንብብ። አብርሃም የጸደቀው እንዴት ነው?

13ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 11:8-19 አንብብ።

ሀ) አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ መታመኑን የሚያሳዩ በሕይወቱ ያሉ የተለያዩ ነገሮችን በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ከአብርሃም የእምነት አገላለጽና በእኛ ባለው የእምነት አገላለጽ መካከል ያለው መመሳሰል ግለጽ።

የአብርሃም እምነት በሕይወቱ በተለያየ ወቅት በደረሱ ሁኔታዎች በኩል ተገልጿል።

1. እግዚአብሔር ሲጠራው አብርሃም እምነቱን አሳይቷል! (ቁጥር 8-10) (ዘፍጥረት 12:1-3)። እግዚአብሔር አብርሃምን «የአባትህን ቤትና የተወለድክበትን ትተህ ውጣ» ብሎ በጠራው ጊዜ የጉዞው መጨረሻ ወዴት እንደሆነ አልነገረውም ነበር። ለአብርሃም ያለው «ወደማሳይህ ምድር ውጣ» ብቻ ነው። ዳግመኛ ላለመመለስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አብርሃም የተወለደበትን አገር ትቶ ይነሣል። እምነቱን በእግዚአብሔር ላይና በቃል ኪዳኑ ላይ (ሲፈጸሙ ባላያቸው) እንጂ፥ በፊት በነበረው የተመቻቸ ሕይወቱ ላይ ማድረግ አልነበረበትም። አሁንም እንደገና እምነትና ታዛዥነት አንድ ላይ የተጣመሩ ነገሮች እንደሆኑ እናያለን። ሁሌም ሁለቱ አብረው ሲጣመሩ ነው እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙ የሚችሉት።

አብርሃም የምትወርሳት አገር ናት ተብሎ ተስፋ ወደተሰጠው ወደ ከነዓን ምድር ቤቱን ትቶ ይነሣል። በዚህም ምክንያት ነው «የተስፋይቱ ምድር» የሚል ትርጓሜ የተሰጠው። በጣም የሚያስገርመው ነገር ግን አብርሃም አንዱንም የተስፋ ምድር በሕይወቱ ዘመን አለመቀበሉ ነው። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ ይኖር የነበረው በቤት ውስጥ ሳይሆን በድንኳን ውስጥ ነበር። ይስሐቅና የልጅ ልጁ ያዕቆብም ይኖሩ የነበሩት እንዲሁ ነው። የእሥራኤል ሕዝብ ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል የፈጸሙትና የውርሱን ምድር የተቀበሉት አብርሃም ከሞተ ከ400 ዓመት በኋላ ነው። ሕይወቱን በሙሉ አብርሃም እግዚአብሔር በሰጠው ምድር ላይ እንግዳ ነበር።

አብርሃም ለዚህ ያህል ጊዜ እግዚአብሔር ተስፋ ያደረገለትን ምድራዊ በረከት ሳይቀበል የኖረው እንዴት ነው? ይህ የሆነው መንፈሳዊ አይኖቹን በማይታዩት ዘላለማዊ ነገሮች ላይ በማድረጉ ነው። ይጠባበቅ የነበረው ምድራዊ የሆነ ከተማ ወይም መሬት ሳይሆን እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ በመንግሥተ ሰማያት ያዘጋጃት የነበረችውን ከተማ ነበር።

14ኛ ጥያቄ:- የዮሐንስ ራዕይ 21:1-4፥ 9-28 አንብብ።

ሀ) ይህቺ ዘላለማዊ ከተማ ስሟ ማን ነበር?

ለ) ስለ ከተማይቱ በአጭሩ ግለጽ።

አብርሃም የዘላንነት ኑሮ ሊቋቋመው የቻለው በመጨረሻ ላይ ይደርስባት የነበረው ዘላለማዊ ከተማ ኢየሩሳሌም እንደነበረች በመገንዘቡ ነው። እኛም ብንሆን ይህች እንደ ጥላ የምታልፍ ምድራዊ ሕይወታችን ላይ ከማተኮር ዐይናችንን በዘላለማዊዋ ከተማ ላይ ማድረግ አለብን፥ (2ኛቆሮ.4:16-18)።

15ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ክርስቲያን ዐይኑን በምድራዊ ነገሮች ላይ ማድረጉን ትቶ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ከተማ ላይ ቢያደርግ ሕይወቱ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚለወጥ በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ክርስቲያኖች ዐይናቸውን ዘላለማዊ ነገር ላይ እንዳያደርጉ የሚከለክሏቸውና በጣም አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸው የአንዳንድ ምድራዊ ነገሮችን በዝርዝር ጻፍ።

2. ሁለተኛው የእምነት ምሳሌነት በአብርሃም ሕይወት ውስጥ የታየው በይስሐቅ መወለድ ነው፥ (ከቁጥር 11-16)። እግዚአብሔር ልጅ እሰጥሃለሁ ብሎ የተስፋ ቃል በሰጠው ጊዜ እንደተጻፈው «አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት! (ዘፍጥረት 15:1-6)። አብርሃምና ሣራ ልጅ ሊኖራቸው እንደማይችል ተገንዝበው ነበር። በተፈጥሮ ልጅ የመውለድ ኃይላቸው አልቋል፥ ምክንያቱም አብርሃም የ75 ዓመት ሰው ሣራ ደግሞ የ65 ዓመት ዕድሜ ነበረች እና ነው። ይህም ሆኖ እግዚአብሔር አንድ ልጅ ብቻ ሳይሆን ልጆችህ እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ምድር አሸዋ ይበዛሉ የሚል የተስፋ ቃል ነው የሰጠው።

ምንም እንኳ የመጀመሪያውን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ከብዙ ዓመታት በኋላ (ከ25 ዓመት) ቢቀበልም እግዚአብሔር ስለ ልጅ በሰጠው የተስፋ ቃል ላይ ምንም ጥርጣሬ አልነበረውም። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን በመፈጸሙ ላይ ታማኝ እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር አብርሃምን አከበረ፤ የእሥራኤል ሕዝብን ዘር የሚያሠፋውም ልጅ ይስሐቅ ተወለደ።

16ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለብዙ ዓመታት ቆይተህ ያላገኘኸው እግዚአብሔር ላንተ የሰጠህ የተስፋ ቃል ካለ ምንድን ነው?

ለ) እግዚአብሔር ይህን የተስፋ ቃሉን እንደሚያከብር ማረጋገጫ የሚሆንህ ነገር ምንድን ነው?

ዕብራውያን ምዕራፍ 11፡13-16፥ ስለ አብርሃም፥ ስለ ይስሐቅ፥ ስለ ያዕቆብና ስለ ብሉይ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታት ታላቅ እምነት የሚገልጽ ማጠቃለያ ያካተተ ነው። እነዚህ ሰዎች በሕይወታቸው ዘመን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ተፈጽሞ አላዩም። ለምሳሌ ያህል አብርሃም ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፥ ታላቅ ምድር እሰጥሃለሁ፥ ወዘተ... የሚሉ የተስፋ ቃሎች ተሰጥተውታል፥ ነገር ግን እርሱ የሞተው የራሱ የሆነችው የመቃብሩን ቦታ ብቻ ይዞ ነበር። ለእርሱ ከነዓን ሁሌ «የተስፋይቱ ምድር» ነበረች እንጂ የእርሱ አልነበረችም። ሌሎች ስለ መሢሑ መምጣት ተስፋ ተሰጥቷቸው ነበር፤ ነገር ግን አላዩትም። ምንም እንኳ ይኖሩበት የነበረው ሁኔታ ከእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ባይጣጣምም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የነበራቸውን እምነት ግን እስከ መጨረሻው ድረስ ጠብቀዋል። የተስፋው ቃል እንዴት እንደሚፈጸም ግን በድንግዝግዝ ተመልክተውት ነበር። ስለዚህ አብርሃም ይስሐቅን የተመለከተው የታላቁ ሕዝብ የበኩር አድርጎ ነበር።

እምነታቸውን መጠበቃቸው ልባቸው የነበረው የማይታየው ዓለም ላይ እንደነበር ያሳየናል። አብርሃም ቢፈልግ ወደ አባቶቹ አገር ወደ ኡር ሄዶ የተስፋውን ቃል መፈጸም መጠባበቅ ይችል ነበር። በምትኩ ግን እንደ እንግዳ ነው የኖረው፤ የኡር ወይም የከነዓን ሰው አልነበረም። አብርሃምም የብሉይ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታት ይታመኑ የነበረው በእግዚአብሔር ላይ በዘላለማዊ ምድር ላይና ሊመሠረት ባለው ታላቅ ሕዝብ ላይ ነበር። እውነተኛው መኖሪያቸው ያለው ምድር ላይ ሳይሆን በሰማይ ላይ እንደሆነ ተረድተው ነበር። እምነታቸው እግዚአብሔርን በጣም ደስ አሰኝቶታል፥ ስለዚህም የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ተብሎ መጠራቱ ያኮራዋል።

17ኛ ጥያቄ:- ፊልጵ.3፡20፥ 1ጴጥ.2፡11 አንብብ።

ሀ) ክርስቲያኖች የተሰጣቸው ስያሜ ምንድን ነው?

ለ) የክርስቲያን እውነተኛው ዜግነቱ ምንድን ነው?

ሐ) ይህ ከአብርሃም አመለካከት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

መ) ይህን ዓይነቱን እዚህ ኢትዮጲያ ውስጥ እንዴት ልናዳብረውና ልናሳየው እንደምንችል ምሳሌዎችን ስጥ።

ምንም እንኳ የተወለድነው ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆንም እንደ እውነተኛው መኖሪያችን አድርገን ልናየው አይገባንም። ዕቅዶቻችንና ተስፋዎቻችን ከዚህ ምድር ጋር ብቻ የተቆራኙ መሆን የለባቸውም። ቤት ብንሠራ ሥራም ብናገኝ ወዘተ... እኛ እዚህ መፃተኞች እንደሆንን ማስተዋል ይኖርብናል። በመንፈስ ወደ ዘላለማዊ ቤታችን እየተጓዝን ነው። እኛ የመንግሥተ ሰማያት ዜጎች ነን። ስለዚህም «በዚህ ዓለም እንግዶችና መፃተኞች ነን»።

3. የመጨረሻው የአብርሃም እምነት ምሳሌነት የታየው ይስሐቅን ለመሠዋት በፈቀደበት ወቅት ነው። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉቹ በሙሉ በልጁ በይስሐቅ ይፈጸማሉ ካለ በኋላ እንደ መሥዋዕት አቅርበው ይለዋል፤ (ከቁጥር 17-19) (ዘፍጥረት ምዕራፍ 22)። አብርሃም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ጠንቅቆ ያውቃቸው ነበር፤ ታዲያ በሙሉ የተያዙት የተካተቱ በአንዱ ልጁ በይስሐቅ ውስጥ ነው። ይህም ሆኖ እግዚአብሔር ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋ ያዘዘዋል። አብርሃም፥ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ ብሎ እንዳዘዘው አያውቅም፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ይስሐቅ ከተሠዋ በኋላ እንደገና ሊያስነሣው እንደሚችል በመረዳቱ ለእግዚአብሔር ታዛዥ ሆነ። ለዚህም ነው ሎሌዎቹን «እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን» ያላቸው፥ (ዘፍጥረት 22፡5)። ምንም እንኳ እግዚአብሔር አብርሃም እጁን ልጁ ላይ እንዳይጭን ቢያደርገው አብርሃም ቁርጥ የሆነ ውሳኔ በመውሰዱ እግዚአብሔር፡- አብርሃም ልጁን ይስሐቅን እንደሠዋውና እርሱ መልሶ ከሙታን እንዳስነሣው ነው የቆጠረው። የይስሐቅ መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ልጁን ስለ እኛ ኃጢአት እንዴት አድርጎ መሥዋዕት እንዳቀረበ የሚያሳየን ሥዕላዊ መግለጫ ነው። ምን ዓይነት ታላቅ እምነት ነበር አብርሃም የነበረው? ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው አምላኩን በደንብ በማወቁ ነው። አንተ እግዚአብሔርን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ታውቀዋለህ?

አንዳንዴ እግዚአብሔር ለልጆቹ በጣም ከበድ ያለ ነገር ይጠይቃቸዋል ይህን የጠየቀበት ምክንያት በፈቃዱ ውስጥ ተሸሽጓል። የእምነታችንን ጥልቀት መግለጽ ያለብን በዚህን ጊዜ ነው። የእግዚአብሔርን መልካም ፈቃድ ዓላማ የምንቀበልና የምንጠብቅ ከሆነ እምነታችን ያድጋል የእግዚአብሔርም ዓላማ በሕይወታችን ተፈጻሚነት ያገኛል። ብዙ ጊዜ ግን እግዚአብሔር እምነታችንን ሲፈትን ዐይኖቻችንን ምድራዊ ነገሮች ላይ እናደርግና እግዚአብሔርን በእምነት መጠበቁን እንተወዋለን። የእኛን ፈቃድ ከእግዚአብሔር በላይ እናደርገዋለን። በዚህም ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር በረከቶች ያመልጡናል።

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር እምነትህን በከባድ ሁኔታ ፈትኖት ያውቃል? እንዴት እንደነበር አስረዳ።

ለ) ምላሽህ ምን ነበር?

ሐ) በእግዚአብሔር ላይ የነበረህን እምነት በተሻለ ሁኔታ ለማሳየት እንዴት አድርገህ ነበር ምላሽ መስጠት የነበረብህ?

# ሦስተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 11፡20-31

በዝርዝር ስለ አብርሃም እምነት ከተነተነ በኋላ ጸሐፊው ስለ ሌሎች ሰዎች እምነትም መናገሩን ይቀጥላል፤ በተለይም የእሥራኤልን ከባርነት አውጥቶ ወደ ከነዓን ምድር ስለ ወሰደው ስለ ሙሴ ይናገራል።

19ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 11፡20-31 አንብብ።

ሀ) እምነታቸውን የገለጹትን ሰዎች ስም በዝርዝር ጻፍ።

ለ) እያንዳንዱ ሰው በሕይወቱ እምነት እንዳለው የገለጸው እንዴት ነው?

አምስተኛው የእምነት ምሳሌ የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ነው፤ (ቁጥር 20) (ዘፍጥረት 27፡27-40)። የእግዚአብሔር ሰው የነበረው ይስሐቅ ከአብርሃም ዝቅተኛ ቢሆንም በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነቱን ጠብቆ ነው የኖረው። ይህን እምነቱን በተለይ የገለጸው ኤሳውና ያዕቆብን በባረከበት ወቅት ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው የተስፋ በረከቶች ሲፈጸሙ ባያይም፥ የእርሱ እንደሆኑ ግን አውቆ ነበር። መንፈሳዊ ዐይኑን በማይታዩት የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ በማድረግ ወደ ያዕቆብ አስተላልፏቸዋል። ምንም እንኳ ኤሳው ዋነኛውን በረከት መቀበል ቢኖርበትም ከይስሐቅ በረከትን ሳይቀበል አልቀረም። እነዚህ የፓትሪያርኩቹ በረከቶች እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርጋቸውን የሚጠቅሱ ትንቢቶች ነበሩ።

ስድስተኛው ምሳሌ የይስሐቅ ልጅ ኤሳው ነው፥ (ቁጥር 21)። ምንም እንኳ በሕይወቱ በራስ ወዳድነት የኖረ ከእግዚአብሔር የራቀ ቢሆንም እርሱ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት የገለጸው የማይታየውን የእግዚአብሔርን በረከት ለዮሴፍና ለሁለቱ ልጆቹ በማስተላለፍ በኩል ነው፤ (ዘፍጥረት 48፡8-20)።

ሰባተኛው ምሳሌ፤ ታላቁ ሰው ዮሴፍ ነው፤ (ቁጥር 22)። ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነቱን በብዙ መንገድ ቢያሳይም በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው አንዱ ብቻ ነው። ይህ የዮሴፍ የሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ ያለ ነውር ነው። ሊሞት ሲል ከብዙ ዓመታት በኋላ የሚፈጸመውን የእሥራኤል ልጆችን ከግዞት የመውጣትን ነገር ይተነብያል። ሲወጡም አጥንተን ወደ እሥራኤል ምድር ይዘው እንዲቀብሩት ይነግራቸዋል። ይህም ልቡ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረበት ግብፅ ውስጥ ሳይሆን እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ሰጠው ከነዓን ምድር ላይ እንደነበር ያሳየናል።

እነዚህ ሦስቱ ፓትሪያርኮች እምነታቸውን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ እንዴት አድርገው እንደያዙ የሚገልጹ ምሳሌዎች ናቸው። የእግዚአብሔርን በረከትና ተስፋ ለልጆቻቸው አስተላለፉ። በሕይወታቸው ዘመን ባይፈጸሙም እግዚአብሔር አንድ ቀን በረከቱን ፍጻሜ እንደሚያደርስላቸው ያውቁ ነበር። እኛም ብንሆን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በሕይወታችን ባይፈጸሙም እንኳ እስከ መጨረሻው ድረስ እስከንሞት ታማኞች መሆን አለብን።

ስምንተኛ ምሳሌዎች፤ የሙሴ ቤተሰብ ነው፤ (ቁጥር 23)። ይህ ቤተሰብ እምነቱን የገለጸው በግብፅ መንግሥት ልጆቻችሁን ግደሉ የሚለውን ትዕዛዝ በመጣስና ሙሴን ከሞት በማትረፍ ነው። ለንጉሡ አለመታዘዛቸው እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ እንዳደረጉ ያሳያል፤ በተለይም ሙሴ በእግዚአብሔር ለልዩ ምርጫ ሲገነዘቡ ለእነርሱም እምነት እንዳላቸው ማረጋገጫ ይሆናቸዋል። እነርሱን እምነታቸው መንግሥቱን እንዲቃወሙና የሚመጣውን ቅጣት ለመጋፈጥ እንዲቆርጡ አድርጓቸዋል። ቅድሚያ የሰጡት እግዚአብሔር መታዘዝን ነው።

20ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያንህ ያሉት ክርስቲያኖች እንደዚህ ዓይነት ከባድ ምርጫ ለመምረጥ የሚገደዱት እንዴት ነው?

ዘጠነኛው ምሳሌ፤ ታላቁ የእሥራኤል ሕዝብ መሪ ሙሴ ነው፤ (ቁጥር 24-28)። በዕብራውያን ምዕራፍ 3 ላይ ሙሴ የብሉይ ኪዳን መካከለኛ አስታራቂ እንደነበረ ተመልክተናል። የሙሴ ሕይወት ያለማቋረጥ የሚያሳየን የእግዚአብሔርን መኖርና ኃይሉን የሚያውቅ በዚያ ብርሃን ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚገባው የተገነዘበ ሰው ነው።

ጸሐፊው ሙሴ እምነቱን የገለጸባቸውን ብዙ ምሳሌዎችን ይጠቅሳል።

1. በፈርዖን ቤት ውስጥ አልኖርም እኔ የፈርዖን ባሮች የሆኑት የእሥራኤላውያን ወገን ነኝ በማለት እምነቱን ገልጿል። ሙሴ ያደገው በግብፅ ቤተ መንግሥት ውስጥ ነው። አንዳንድ ምሁራን ሙሴ አልጋ ወራሽ ነበር ይላሉ፥ ይህ ከሆነ ደግሞ ፈርዖን ከሞተ በኋላ የሚቀጥለው የግብፅ መሪ እርሱ ነው ማለት ነው። በዚህ እርግጠኞች ባንሆንም ሙሴ የአንድ የንጉሥ ልጅ ሊያገኝ የሚችለውን ጥሩ ትምህርትና ዕድል እንዳገኘ ግን እርግጠኞች ነን። ይህም ሆኖ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ እንዲያወጣለት ጥሪ እንዳደረገለት ተረድቷል። ምንም እንኳ በመጀመሪያ አካባቢ በራሱ ጊዜና ኃይል እሥራኤልን ለመምራት ቢሞክርም በመጀመሪያ አካባቢ እምነትን የገለጸው ከተደላደለው የፈርዖን ቤት ኑሮ የእሥራኤልን የባርነት ኑሮ በመምረጡ ነው። እሥሬልን እንዲመራ በእግዚአብሔር ስለተመረጠም ግብፅ እቆያለሁ ብሎ ቢመርጥ እንደ ኃጢአት ይቆጠርበታል። ስለዚህም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሲል ከብልፅግና ድህነትን፥ ከክብር ደግሞ ውርደትን መረጠ። ይህንን ያደረገው የማይታዩትን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በመንፈሳዊ ዓይኖቹ ይመለከት ስለነበር ነው።

21ኛ ጥያቄ፡- ለክርስቶስ ስም ሲሉ ከብልፅግና ይልቅ ድህነትን የክብር ቦታ ከሆነ ነገር ይልቅ ውርደትን የመረጡ የምታውቃቸውን ክርስቲያኖች እንደ ምሳሌ ጥቀስ።

2. ሙሴ ከግብፅ ወጥቶ በምድረ በዳ በመኖር እምነቱን ገልጿል። ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ዓይን ተቀባይነት ባይኖረውም ሙሴ ግብፃዊውን ሲገድል፥ ቤተ መንግሥቱ አልኖርም ብሎ ቁርጥ ውሳኔ አደረገ። በዚህም ጊዜ በዚች ምድር ተፈላጊ በመሆኑ መኮብለል ነበረበት። ታዲያ ለአርባ ዓመት ያህል እረኛ ቢሆንም በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነቱን አልተወም።

23ኛ ጥያቄ፡- በእነዚህ እግዚአብሔርን ደስ ባሰኙ የእምነት ምሳሌዎች ውስጥ የሚታዩት አንድ ዓይነት ነገሮች ምንድን ናቸው?

በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ ያሉ ሰዎች በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብለው በቃሉም ታምነው በዚያ ቃል ላይ ሕይወታቸውን መሥርተዋል። የሚያልፉበት ነገር ምንም ያህል ከባድና አስቸጋሪ ቢሆንም በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት ለእርሱ ታዛዦች እንዲሆኑ አደረጋቸው።

# አራተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 11፡32-40

ዕብራውያን 11፡3-31 ስለተወሰኑ የእምነት ሰዎች የሚናገር ነበር፥ ይህ ክፍል ግን የእምነት ውጤቶችን የሚመረምርና የሚገልፅ ነው።

24ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 11፡32-40 አንብብ።

ሀ) በእምነት ምክንያት የሚገኙትን የተለያዩ ውጤቶች በዝርዝር ጻፍ። እነዚህ ነገሮች እንዴት እንደተፈጸሙ የሚገልጹ ምሳሌዎችን ከብሉይ ኪዳን ላይ ወስደህ አሳይ።

ለ) በእምነታቸው ምክንያት ምን ዓይነት ስደቶች እንደ ገጠሟቸው በዝርዝር ጻፍ። በእነዚህ ስደቶች ውስጥ ያለፉ ሰዎችን ለምሳሌ ያህል ከብሉይ ኪዳን ላይ ጥቀስ።

በዕብራውያን ምዕራፍ 11 መጀመሪያ ላይ ጸሐፊው ከዘፍጥረት አንሥቶ እስከ ኢያሱ ጊዜ ያሉትን የጻድቃን ሰማዕታት ሕይወትን መረመረ። በመቀጠልም በመሳፍንት ዘመን (ለምሳሌ ጌዴዎን፥ ሳምሶን፥ ባርቅ፥ ዮፍታሔ) ወይም በነገሥታት ዘመን (ለምሳሌ ዳዊት) ወይም በነቢያት ዘመን (ለምሳሌ ሳሙኤልና ሌሎቹ ነቢያት) ስለነበሩት ሰዎች ከመጥቀስ ይልቅ አሁን ጸሐፊው እምነት የሚያስገኛቸው ታላላቅ ውጤቶችን ይመለከታል።

የተለያዩት የእምነት ውጤቶች ከቁጥር 33-35 ላይ ተጠቅሰዋል።

1. እምነት መንግሥታት ድል እንዲሆኑ አድርጓል። ይህም በኢያሱ ዘመን፥ በመሳፍንት ዘመንና በዳዊት ሕይወት ውስጥ ታይቷል።

2. እምነት ጽድቅ እንዲሰፍን አድርጓል። ይህም እግዚአብሔርን በሚፈሩ ነገሥታት ዘመን ታይቷል።

3. እምነት የተሰጠውን የተስፋ ቃል እንዲገኙ አድርጓል። ለምሳሌ፤ ዳዊት ከብዙ ዓመታት ቆይታ በኋላ የእሥራኤል ንጉሥ ሆነ።

4. እምነት የአናብስትን አፍ ዘግቷል። ያለምንም ጥርጥር ጸሐፊው የሚጠቅሰው ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ ያሳለፈውን ጊዜ ነው፤ (ዳንኤል ምዕራፍ 5)።

5. እምነት የእሳትን ኃይል አጥፍቷል። ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የዳንኤል ጓደኞች የሆኑት ሲድራቅ፥ ምሳቅና አብድናጎ እግዚአብሔር ያድናቸው አያድናቸው ሳያውቁ፥ ሞትን በመጋፈጥ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑበትን ጊዜ ነው፤ (ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 3)።

6. እምነት፥ አንዳንዶች ከሰይፍ ስለት እንዲያመልጡ አድርጓቸዋል። ለመጥቀስ ያህል ኤልያስ (1ኛ ነገ. 19፡2)፤ ኤልሣዕና (2ኛ ነገ. 6፡31) ኤርምያስ (ኤርምያስ 36፡ 19-26) ከነገሥታት እጅ አምልጠዋል።

7. እምነት የሰዎችን ድካም ወደ ብርታት ለውጧል። እንደምታስታውሰው ጌዴዎን ሦስት መቶ ሰዎችን ብቻ ይዞ ነበር ታላቁን ጦር የገጠመው፤ (መሳፍንት ምዕራፍ 6)።

8. እምነት ሰዎች በጦርነት ኃይለኞች እንዲሆኑና የባዕድ ጭፍሮችን እንዲያባርሩ አድርጓል። ይህ ብዙ በብሉይ ኪዳን ፈሪሀ እግዚአብሔር የነበራቸውን ነገሥታት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ (ለምሳሌ፤ ኢያሱና ጌዴዎን)።

9. እምነት፥ ሴቶች ሙታናቸውን ከሞት እንዲቀበሉ አድርጓል፤ (1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 17፥ 2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 4 ለምሳሌ ያህል ተመልከት)።

እግዚአብሔር በእምነት መደሰት ብቻ ሳይሆን እምነትን በመጠቀም ለእርሱ አስገራሚና አስደናቂ የሆኑ ነገሮችን እንድናደርግለት ችሎታን ይሰጠናል። በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት እኛ በማናስበው መንገድ እግዚአብሔር በእኛ እንደፈለገ እንዲጠቀም ያደርገዋል።

25ኛ ጥያቄ፡- ከራስህ ሕይወት ወይም ከቤተ ክርስቲያንህ ታሪክ እግዚአብሔር እምነት በመጠቀም ለእርሱ ክብር እንዴት ታላላቅና አስገራሚ ሥራዎች እንዲሠሩ እንዳደረገ ምሳሌዎችን ስጥ።

የእምነት ሕይወት በረከትን ብቻ አይደለም የሚያስገኝልን። ምንም እንኳ ለእግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎችን እንድንሠራ ቢያስችለንም ለክርስቶስ ሲባልም ብዙ መከራ ሊያመጣብን ይችላል። ብዙ ጊዜ እምነታችን ስደትን ያመጣብናል። እምነት የምቾትና የደስታ ማስተማመኛ አይሰጠንም። ከሞት በኋላ ሊመጣ ባለው ዘላለማዊ ዓለም ውስጥ ብቻ ነው የበረከትን ማስተማመኛ የሚሰጠን። ጸሐፊው በመቀጠልም በስደት ውስጥ ስለሚኖሩ የእምነት ውጤቶች ይጠቅሳል፤ (ከቁጥር 35-38)። በስደት ውስጥ እስከ መጨረሻው ታማኝ ሆነው ለእግዚአብሔር የቆሙት ሰዎች ለምሳሌ ያህል የተጠቀሱት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሳይሆን የአይሁድን ባህል በሚያንፀባርቁ መጻሕፍት (ለምሳሌ 1ኛ እና 2ኛ ማቃቢስ) እና እንደ መጽሐፈ አዋልድ ባለው ውስጥ ነው።

1. አንዳንድ ሰዎች ለመላቀቅ ከፈለጋችሁ እምነታችሁን ተዉ በሚል ሰበብ መዘበቻ በመሆን ብዙ መከራን ተቀብለዋል። ይህ ኤሌአደር በተባለው ካህን፥ በአቃቢያውያን ዓመፅ ጊዜ ግለት አይሁዳውያን በሦርያውያን ላይ ባመፁበት ወቅት ተገልጾአል።

ምንም እንኳ እርሱና ሌሎችም የሥጋ ሞት ቢሞቱም ተስፋቸው እግዚአብሔር ከዚህ ቀጥሎ እሰጠዋለሁ ባለው በሙታን ትንሣኤና በዘላለማዊ ሕይወት ላይ ተስፋ በማድረጋቸው ምንም ግድ አልሰጣቸውም ነበር።

2. አንዳንድ ሰዎች ተገርፈዋል፥ መዘባበቻ ሆነዋል፥ በወኅኒም ተከተዋል። ያለምንም ጥርጥር አንዳንዶቹ የአይሁድ ክርስቲያኖች በእነዚህ መከራዎች ውስጥ

አልፈዋል። ይህም ሆኖ በእምነታቸው ምክንያት ብዙ የብሉይ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታትም ተሰደዋል።

3. አንዳንድ ታማኝ ሰዎች በድንጋይ ተወግረዋል። የአይሁዳውያን የባህል መጻሕፍት ኤርምያስ በግብፅ ውስጥ በአይሁዳውያን እጅ የሞተው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነው ይላሉ።

4. አንዳንዶች በመጋዝ ለሁለት ተሰንጥቀዋል። አሁንም እንደገና የአይሁድ የባህል መጻሕፍት ኢይሳይያስ በንጉሥ ምናሴ እጅ የሞተው ለሁለት በመሰንጠቅ ነው ይላሉ።

5. አንዳንዶች በሰይፍ ሞተዋል! (1ኛ ነገ.19፡10፥ ኤርምያስ 26፡23፥ እና የሐዋ.12፡2 ለምሳሌ ያህል ተመልከት)።

6. አንዳንድ ለእግዚአብሔር ታማኝ የነበሩ ሰዎች በጣም ደህይተው የበግና የፍየል ሌጦ እስከ መልበስ በዋሻ ውስጥ እስከመኖር ወዘተ. . . ድረስ ደርሰው ነበር። ኤልያስና ኤልሣዕ ከብዙ ሺህ እሥራኤላውያን ጋር በሰሪያ መንግሥት ላይ ዓመፃ ያስነሡ ሰዎች እንደነበሩ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

26ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንህ በአንተም ሆነ በቤተ ክርስቲያንህ አንዳንድ አባሎች ላይ ስለሚደርሰው ችግር ማብራሪያ ስጥ።

ለ) ክርስቲያኖች በመሆናቸው ሀብታም እንሆናለን፥ ታላቅ ምድራዊ በረከትን እናገኛለን ብለው የሚያስቡ ሰዎች አሉን?

ሐ) ሁኔታው ሁሌ ይህ እንዳልሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዴት አድርገህ ነው የምታሳያቸው?

በዓለም ዓይን ስናየው የእምነት ሰዎች ብዙ ጊዜ ቦታ የማይሰጣቸው የሚጨቆኑ የሚጠሉና ስደት የሚያጋጥማቸው ሆነው እናገኛቸዋለን። የዓለምን ታሪክ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎች ስደት የተቀበሉበት ታሪክ ነው ብለን ልንጠቅሰው እንችላለን። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዓይን ደግሞ እነዚህ ሰዎች በጣም የተከበሩ ናቸው። ታላቁ ዘላለማዊ ስጦታ የእነርሱ ነው።

ከአዳም ጊዜ አንሥቶ እስከ ክርስቶስ ጊዜ ድረስ ያሉት የእምነት ሰዎች ምንም እንኳ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጣቸውን ነገሮች ሙሉ በሙሉ ባያገኙም እስከ መጨረሻው ድረስ ታማኞች ሆነው ተገኝተዋል። አዎ አንዳንዶች ምድራዊ የሆኑ የተስፋ ቃሎች ተሰጥተዋቸው እነዚያ የተስፋ ቃሎች የተፈጸሙላቸው አሉ። ነገር ግን ከሞቱ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእነርሱ የሚሆነውን መንፈሳዊ በረከት አልተቀበሉም ነበር። በሌላ አነጋገር ሙሉ የሆነ ምሕረት ዘላለማዊ ሕይወትና የአዲሲቷ የኢየሩሳሌምን አባልነት ኢየሱስ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ አላገኙም ነበር። እኛ ግን ከእነርሱ በተሻለ ደረጃ ላይ ነን ያለነው። ኢየሱስ በመሞቱ ከእነርሱ ጋር ሙሉ ምሕረትን ዘላለማዊ ሕይወትንና የመንግሥተ ሰማያት አባልነትን እንቀዳጃለን። የብሉይና የአዲስ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታትና ፍጹማን የሆኑት አብረው ነው። የብሉይና የአዲስ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታትም ፍጹማን የሆኑት አብረው ነው። እኛ ክርስቲያኖች የምንኖረው በአዲሱ

ኪዳን ሥር ነው ሊቀ ካህናችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ለእነርሱም ኃጢአት ሲል ሞቷል። ስለዚህም እንዲመንን ወዲያው እነዚህን በረከቶች እንቀበላለን። ልክ እንደ ጥንቶቹ ሰዎች የተስፋዎቹን ቃሎች መጠበቅ የለብንም። ነገር ግን የሕይወታቸውን ምሳሌነት በመከተል ከሞት በኋላ ያሉትን በረከቶች እንደምናገኝ እርግጠኞች መሆን አለብን።

27ኛ ጥያቄ:- ሀ) በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ላይ ተመሥርተህ እምነት ምን እንደሆነ ግለጽ።

ለ) እምነትህ ለእግዚአብሔር ምን ዓይነት ሥራ እንድትሠራ ረድቶሃል?

ሐ) እምነትህ ምን ዓይነት ፈተናዎችን ነው ወደ ሕይወትህ እንዲመጡ ያደረገው?

**አምስተኛ ቀን**:-ትምህርቱንከልስናለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) 1. የእምነት ትርጉም ስጥ። እምነት የሚለውን ቃል ሰዎች በተለያዩ መንገዶች የሚጠቀሙበት እንዴት ነው?

2. እምነት የሚለውን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀምንበት እንዴት ነው?

ለ) 1. በምን ዓይነት መንገድ ነው አብርሃም የአማኞች ሁሉ አባት የሆነው?

2. የአብርሃምን ሕይወት ከክርስቲያን ሕይወት ጋር አነፃፅር። እምነት መኖሩን የሚገልጹት ማረጋገጫዎች የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? የሚለያዩትስ እንዴት ነው?

ሐ) 1. ወደ «ሰማያዊው መንግሥት» መመልከታቸው በሙሴና በአብርሃም ሕይወት ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ነበር ያለው?

2. አንድ ክርስቲያን በምድር ላይ እንዴት ጥሩ ኑሮ እንደሚኖር ብቻ ከሚያስብ ሙሉ ሐሳቡን «ሰማያዊው መንግሥት» ላይ ቢያደርግ ሕይወቱ እንዴት ነው ልዩ ሊሆን የሚችለው?

መ) በምን ዓይነት መንገድ ነው ክርስትና አንዳንዴ ስለ ክርስቶስ ውርደትን መቀበል መደኸየትና መሰደድ የሚችለው? ይህ እንዴት እውነት እንደሆነ ለማሳየት በሕይወትህ ያጋጠመህን አንዱን ነገር ለምሳሌ ያህል ጥቀስ።

ሠ) ጸሐፊው የጥንት ሰዎች ፍጹማን የሚሆኑት ከእኛ ጋር ሲሆኑ ብቻ ነው ሲል ምን ማለት ነው?

# ትምህርት አሥራ ዘጠኝ

ዕብራውያን ምዕራፍ 12

## የመጀመሪያ ቀን፡- ዕብራውያን 12፡1-3

ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ድሎችና ሽንፈቶች የተመዘገቡበት መዝገብ ነው። ዛሬ በአዲሱ ኪዳን ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ደግሞ ብዙ ምሳሌዎችን ይዟል። እንዴት መኖር እንደማይገባን የሚገልጹ ምሳሌዎች አሉ፤ (1ኛ ቆሮ.10፡6-11፥ ዕብራውያን 3፡7-19)። ነገር ግን በእምነት እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳዩን ብዙ ጥሩ ጥሩ ምሳሌዎችም አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ብዙዎቹን በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ጥናታችን ላይ አይተናቸዋል። የብሉይ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታት ታላቅ የነበሩት በእምነታቸው ምክንያት ነው። ምንም ብዙ መከራና ስደት ቢያጋጥማቸውም በእምነታቸው ጸንተው ቆመዋል። ልክ እንደ እነርሱ በመንግሥተ ሰማያት ላይ ያለውን የማይታየውን በረከት ለመቀበል፥ በእምነታችን ጸንተን መቆም አለብን። የእነርሱን ምሳሌነት እንድንከተልና ለእግዚአብሔር ታማኞች ሆነን እንድንጸና የእነዚህን ታላላቅ ሰዎች ሕይወት ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማጥናት አለብን።

1ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን ምዕራፍ 12 አንብብ። የዚህ ምዕራፍ ዋና ዋና ትምህርቶች በዝርዝር ጻፍ።

2ኛ ጥያቄ፡- መንፈሳዊ ሕይወታችን ከሩጫ ውድድር ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ምሳሌ በመስጠት አስረዳ።

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ የአማኙን ሕይወት ከሩጫ ውድድር ጋር ያስተያየዋል፤ (1ቆሮ.9፡24-27፥ 2ጢሞ.4፡7)። ሁሉም ክርስቲያን በሩጫው ውድድር ላይ ተካፋይ ነው። ቋሚ ተመልካቾቹ ሩጫቸውን በታማኝነት የጨረሱት የብሉይ ኪዳን ጻድቃን ሰማዕታት ናቸው። ሰዎቹ የሚሮጡበት ሜዳ ሕይወት ነው። የሩጫው ፍጻሜ ሞት ነው። የሩጫው ፍጻሜ ሽልማቱ ከኢየሱስ ጋር የዘላለም ሕይወት ነው። ቁም ነገሩ ሩጫውን መጀመሩ ሳይሆን መጨረሱ ላይ ነው። በዚህ ሕይወት እሽቅድድም ውስጥ ሁሉም ሰው በታማኝነትና በጽናት ከሮጠ አሸናፊ ይሆናል።

3ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 12፡1-3 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ) በቁጥር 1 ላይ ምሥክሮች የሚላቸው እነማንን ነው?

ለ) አማኙ ሩጫውን በጽናት ለመሮጥ ከፈለገ፥ ማስወገድ የሚገባው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

ሐ) ክርስቲያኖች ዐይናቸውን የት ነው ማድረግ ያለባቸው?

መ) ኢየሱስን የገለጸው እንዴት ነው?

ሠ) ኢየሱስ በችግር አልፎ የመታገሥ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

ጸሐፊው ክርስቲያኖች በሩጫቸው እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተው የዘላለማዊውን ሕይወት ሽልማት ተሸላሚዎች እንዲሆኑ የሚያበረታቷቸውና የሚረዷቸውን ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ይጠቅሳል። አንደኛ፤ ጸሐፊው ለክርስቲያኖቹ በምሳሌነታቸው ሊያበረታቷቸው የሚችሉትን የቀድሞዎቹን ጻድቃን ሰማዕታት ያስታውሳቸዋል፤ (ዕብራውያን ምዕራፍ 11)። እነዚህን ምሥክሮች እንደ ጥንቱ የታወቁ ሰዎች በመሆን ሩጫውን ጨርሰው በእግዚአብሔር ፊት እንደሚያማልዱን ዓይነት አድርገን ልንቆጥራቸው አይገባም። ወይም ደግሞ እንዴት እንደምንሮጥ ቁጭ ብለው እንደሚመለከቱን ዐይነት አድርገንም መቁጠር የለብንም። ሚዳ እንደ አበበ በቂላና እንደሌሎች ታላላቅ ሯጮች ባሉ ሰዎች የተሞላና በሩጫውም እኛን እንደሚያበረታቱን ዓይነት አድርገን ልናየው ይገባናል። የብሉይ ኪዳን ታላላቅ ሰዎች የሕይወታቸውን ሩጫ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው በጽናት በመጨረሻው አሁን ሩጫውን ለምንሮጠው ለእኛ በታማኝነትና በጽናት ሮጠን የዘላለማዊውን ሕይወት ሽልማት እንድናገኝ ማበረታቻ መሆን አለባቸው። እነዚህን ሰማዕታት ለመጨረስ እንድንችል ከጎን ሆነው እንደሚያበረታቱን ዓይነት አድርገን ነው የምናያቸው።

አንድ ክርስቲያን ሩጫውን በተገቢው መንገድ እንዳይሮጥ እንዲደናቀፍ፥ እንዲወድቅና ሳያሸንፍ ሩጫውን ትቶ እስከመውጣት ድረስ የሚያደርሱት ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛ፤ በደንብ እንዳይሮጥ የሚያደርጉትን ነገሮች አሉ። ለምሳሌ:- አንድ ሰው በሰንሰለት ታስሮ ወይም ትልቅ ጋቢ ተከናንቦ ወይም በጣም ወፍሮ በደንብ ሊሮጥ አይችልም። ለሩጫው ተገቢውን ዝግጅት አላደረገም። ስለዚህ በሕይወት ሩጫ ውስጥ በተገቢው መንገድ እንዳንሮጥ የሚያደርጉንን ማንኛዎቹንም ዓይነት ነገሮች ልናስወግድ ይገባል።

4ኛ ጥያቄ:- መንፈሳዊ ሩጫን በተገቢው መንገድ እንዳንሮጥ ሊያደርጉህ የሚችሉ ልዩ ልዩ ነገሮችን ዘርዝር።

መንፈሳዊውን ሩጫ በደንብ እንዳንሮጥ መሰናከል የሚሆኑብን ብዙ ጥሩም መጥፎም የሆኑ ነገሮች አሉ። እነዚህም ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ለአንዳንዶች መሰናከል የሚሆንባቸው ብዙ ገንዘብ ወይም ሀብት ሊሆኑ ይችላሉ። ለሌሎች ደግሞ ከእግዚአብሔር የሚያሸሽ ሥራ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ ሥልጣን ሊሆን ይችላል፤ እነዚህ ሁሉ ተደናቅፈው እንዲወድቁ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። ማንኛውም ነገር ዐይናችንን ከእግዚአብሔር ላይ እንድናነሣና ከምድራዊ ነገር ጋር የሚያስሩን ነገሮች ሁሉ በደንብ ከመሮጥ የሚከለክሉን ሸክሞች ስለሆኑ መወገድ ያለባቸው ናቸው።

ሁለተኛ፤ ኃጢአታችንን ማስወገድ አለብን። እዚህ ላይ ጸሐፊው የተወሰኑ ኃጢአቶች አይጠቅስም። በምትኩ ግን በአማኙ ዙሪያ ያሉና በቀላሉ በመንፈሳዊ ሩጫው ጠልፈው ሊጥሉት የሚችሉትን የተለያዩ ኃጢአቶችን ነው የሚመለከተው። ለመጥቀስ ስግብግብነት፥ ቅናት፥ ጥላቻ፥ ትዕቢት፥ ዝሙትን ወዘተ... የመሳሰሉ አሉ።

መንፈሳዊ የሆነ ሰው ግን ትንሿ ኃጢአት እንኳ እንዳትጠልፈውና በመንፈሳዊ ሩጫው ላይ ችግር እንዳይፈጠርበት ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

5ኛ ጥያቄ፡- የምታውቃቸው ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ውስጥ ባለው ኃጢአት ምክንያት ተጠልፈው እንዴት እንደወደቁ ምሳሌ ስጥ።

መንፈሳዊው ሩጫ ልክ እንደ ማራቶን ነው፡- በጣም ረጅም ሩጫ ነው። የሚጀምረው በኢየሱስ ስናምን ነው። የሚጠናቀቀውም መንግሥተ ሰማያት ስንደርስ ነው። ስለዚህ ዋናው ነገር አሁን ምን ያህል ነው የምንሮጠው ብቻ ሳይሆን እስከ መጨረሻው ድረስ ምን ያህል በደንብ እንሮጣለን የሚልም መሆን አለበት። ለዚህም ነው በክርስትና ሕይወታችን ልናዳብረው የሚገባን ዋነኛው ባህርይ ጽናት ነው። ጊዜው አመቺ እንኳ ባይሆን ይህ ጽናታችን ያለማቋረጥ እንድንሮጥ ይረዳናል።

ሩጫውን በትክክል እንድንሮጥ የሚያበረታታን ሁለተኛው አነቃቂ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አንድ ሯጭ ሳይወድቅ በትክክል እንዲሮጥ ካስፈለገ ዐይኖቹ ቀጥታ የመጨረሻውን መስመር እንዲያዩ ማድረግ አለበት። ሌሎች ሯጮችን ወይም እግሩን ወይም ተመልካቾቹን ከተመለከተ ይወድቃል። በመንፈሳዊ ሩጫችን መጨረሻ ላይ ያለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህም በራሳችን ላይ ወይም ከመንገዳችን ሊያፈናቅሉን በሚችሉ ሰዎች ላይ ሳይሆን ዐይናችንን ማድረግ ያለብን በእርሱ ላይ ነው።

ስለ ኢየሱስ ሁለት ገለጻዎች ተሰጥተዋል። አንደኛ፤ የእምነታችን ራስ ነው። ራስ የሚለው ቃል ብዙ ትርጓሜዎች አሉት። እንደሚመስለኝ ጸሐፊው እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታማኝ በመሆን ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ የከፈተላችሁ ኢየሱስ ላይ ዓይናችሁን አድርጉ ማለቱ ነው። ለዚህም ነው ኢየሱስ «እኔም መንገድና እውነትም ሕይወትም ነኝ» ያለው፤ (ዮሐንስ 14፡6)። ኢየሱስም የሕይወትን ሩጫ ሮጦ ከእኛ በፊት ጨርሷል። የእርሱ የእግዚአብሔርን መንገድ አከፋፈት አንድ ሰው ከዚህ በፊት ሊደርስበት የማይቻልበትን ቦታ እንዲደርስ መንገድ እንደከፈተለት ዓይነት ሁኔታ ነው።

ሁለተኛ፤ ኢየሱስ የእምነታችን ፈጻሚ ነው። ሩጫውን ጨርሶ በመጨረሻው መሥመር ላይ ቆሞ የሚጠብቀን እርሱ ነው። እምነታችን የሚያድገውና እስከ መጨረሻው የምንጸናው በእርሱ በኩል ነው።

የኢየሱስ ሕይወት ብዙ መከራ ቢያጋጥመን እንዴት ጸንተን እንደምንቆም የሚገልጽ ጥሩ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሊሰቀልበት ያለው መስቀል በሰው ልጆች ዓለም ከሚሰጠው ቅጣት ሁሉ አስከፊው ነበር። ነፍሰ ገዳዮች ብቻ ነበሩ የሚሰቀሉት። ስለዚህም በመስቀል ላይ የሚሞቱ ትልቅ ውርደትን ነበር የሚቀበሉት። ኢየሱስ ግን መስቀሉንና ከሰዎች የደረሰበትን ተቃውሞ በፀጋ ነው የተቀበለው ምክንያቱም ከመስቀሉ አልፎ ይመለከት የነበረው ከእግዚአብሔር ጋር ይነግሥ የነበረበት መንግሥተ ሰማያትን በመሆን ነው። መጨረሻውን መመልከቱ የሚጸናበትን ኃይል እንዲያገኝ አደረገው።

እኛም ብንሆን ዐይኖቻችንን ችግሮቻችን ላይ ሳይሆን በሕይወት ፍጻሜና በመንግሥት ሰማያት ክብር ላይ ማድረግ አለብን። በዚህን ጊዜ በሩጫው ላይ እንደክምም፥ ሩጫውንም እናቋርጥ ብለን ተስፋ አንቆርጥም። ምንም እንኳ የዘላለማዊውን ሕይወት ደስታ በከፊል ብንቀበለውም አብዛኛው ያለው ከፊታችን ነው።

6ኛ ጥያቄ:- ሯጮች ከሚያደርጓቸው ልምምዶች በመነሣት፥ ለመንፈሳዊው ሩጫችን ሊረዱን የሚችሉ ምን ምን ነገሮችን ልንማር እንችላለን?

7ኛ ጥያቄ:- የታላላቅ መንፈሳዊ ሰዎችን ምሳሌነትና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መከተላችን በሩጫው ታማኞችና ጽኑዎች እንድንሆን ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው?

# ሁለተኛ ቀን:- ዕብራውያን 12:4-13

8ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለምንድን ነው ክርስቲያኖች መከራ የሚቀበሉት?

ለ) መከራ ሁሉ የኃጢአት ውጤት ነው፥ ወይስ እግዚአብሔር ሕዝቡ በሕመም፥ በስደት እስከ ሞት ድረስ የሚደርስ መከራ እንዲቀበሉ የሚያደርግበት ምክንያት አለው?

ብዙ በመከራና በችግር ውስጥ እያለን ለምን ይህን ዓይነት ችግር እንቀበላለን? ብለን ልናስብ እንችላለን። ልናየው የምንችለው የችግሩን ክብደት ነው እንጂ ለምን እንደሆነ አናውቅም። ስለዚህም እንደ ሕመም፥ ሞት ወዘተ. . . ያሉት ችግሮች ሲገጥሙን ብዙ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር መልካምነትና ዓላማ እንጠይቃለን። አንዳንዴ ክርስቲያኖች በመሳሳት፥ ሕመምና ሞት ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍርድ የኃጢአት ቅጣት የሚታይበት ነገር ነው ይላሉ። ነገሩ ግን ይህ አይደለም። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሕመምንና ሞትን እንደ ኃጢአት መቅጫ ቢጠቀምባቸውም እነዚህ ነገሮች በልጆቹ ሕይወት ውስጥ ዕድገት እንዲያስገኙም ይጠቀምባቸዋል።

9ኛ ጥያቄ:- ዕብራውያን 12:4-13 አንብብ።

ሀ) በዕብራውያን ክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ስደት ስለ እምነታቸው እንዲሞቱ አድርጓቸዋልን?

ለ) አንድ ክርስቲያን መከራ መቀበሉ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ሊያረጋግጥለት የሚችለው ነገር ምንድን ነው?

ሐ) የጌታ ተግሣፅ ዓላማው ምንድን ነው?

መ) የተግሣፁ ፍሬዎች ምንድን ናቸው?

ምንም እንኳ በምድራዊ ኑሮአችን እግዚአብሔርን ማመናችን ታላቅ በረከትንና ደስታን ቢያስገኝልንም ብዙ ጊዜ ደግሞ ችግርንም ያስከትላል። እግዚአብሔር እያንዳንዱ ክርስቲያን በተወሰኑ ዓይነት ችግሮች እንዲያልፍ በማድረግ ዓላማውን በእነዚያ ችግሮች ውስጥ ገቢራዊ ያደርጋል። ለብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን ጻድቃን

ሰማዕታት እግዚአብሔርን መታዘዛቸው እስከ ሞት የሚያደርስ ስደት እንዲደርስባቸው አድርጓል። የኢየሱስም ታዛዥነት ለእርሱ ኃጢአት ሳይሆን ለሌሎች ኃጢአት እንዲሞት አድርጎታል። የዕብራውያኑ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ንብረቶቻቸው ተወስደው ቢደበደቡም ለእምነታቸው እስከ ሞት ድረስ አልደረሱም ነበር። ከኃጢአት ጋር ያደርጉት የነበረው ትግል ደም እስከ መፋሰስ ድረስ አልደረሰም። ሆኖም የዕብራውያን መጽሐፍ ከተጻፈ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ስለ እምነታቸው ብዙ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን አጥተዋል።

በአማኙ ሕይወት የሚደርሰው የስደቱና የመከራው ዓላማ ምንድን ነው? ጸሐፊው እነዚህን መከራዎች «የጌታ ቅጣት» ይላቸዋል። ቅጣት የሚለው ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላሉ። ለኃጢአት የሚሰጥ ቅጣት ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ባህርያችንና መንፈሳችን የበለጠ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ለማመሳሰል የሚሰጥ ልምምድ ሊሆን ይችላል። ጸሐፊው የሚጠቅሰው ይህን ሁለተኛውን ትርጓሜ ነው።

ሰለሞን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ተግሣፅ አንድ መጥፎ የሆነ ነገር ሳይሆን አንድ ጥሩ ነገር እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር፤ (ምሳሌ 3፡፣11-12)። በዚህም ምክንያት በመከራ ውስጥ የሚያልፉት ሰዎች ጊዜውን እንደ ትምህርት ማግኛ ጊዜ እንዲቆጥሩት ይመከራቸዋል። እግዚአብሔር ያመጣባቸውን ተግሣፅ መቀበልና ከእርሱ ላይ መማር አለባቸው። በተጨማሪም ይህ እግዚአብሔር እንደሚወስዳቸው የሚያረጋግጡበት ነገር ነው።

ጸሐፊው ሁለት ዓይነት ልጆችን ያነፃፅራል። በመጀመሪያ አባት የሌላቸው ወይም ዲቃላዎች አሉ። በሚያድጉበት ወቅት አባታቸው ምንም አያስብላቸውም፥ በመሳሳታቸው አይቀጣቸውም ወይም ሥነ-ሥርዓት እንዲይዙ አያደርጋቸውም። በዚህም ምክንያት መጥፎ ምግባር ይዘው ያድጋሉ። ሁለተኛ ደግሞ አባት ያላቸው ልጆች በተለይ ወራሾች የሆኑት አሉ። ለእነዚህ አባታቸውም ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርግላቸዋል። መጥፎ ነገርን ከማድረግ እንዲቆጠቡ ሲሳሳቱ ወዲያውኑ ይቀጣቸዋል። ራሳቸው ጥሩ ሰዎች እንዲሆኑ፥ እራሳቸውን ጥሩ ሰዎች እንዲያደርጉ፥ ለሀገራቸውም ጠቃሚ ዜጎች እንዲሆኑና ሲያድጉም በተራቸው ጥሩ አባትና እናት እንዲሆኑ ተገቢውን ትምህርት ይሰጣቸዋል። መቅጣቱና ጥሩ ምግባር ማስያዙ ለእነርሱ ያለውን ፍቅርና አክብሮት የሚገልጽ ነው እንጂ ቁጣን ብቻ የሚገልጽ አይደለም።

10ኛ ጥያቄ፡- ይህ ወላጆች ልጃቸውን የመቅጣት ሐላፊነት እንዳላቸው የሚያስተምረን እንዴት ነው?

ልጆች በነበርንበት ወቅት የወላጆቻችንን ቅጣት ብዙ ጊዜ እንቃወም ነበር። ያለምንም ተፅዕኖና ተግሣፅ ያድጉ የነበሩት ልጆች ያስቀኑን ነበር። ይህም ሆኖ አንዳንዴ ያለ አግባቡም ወላጆቻችን ቢቀጡንም እናፈቅራቸዋለን። ካደግን በኋላ ግን እኛን ወላጆቻችን ያደረጉትን ጥረት እናደንቀዋለን።

ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር መንፈሳዊ አባታችን ነው። እኛ የእርሱ ልጆች ነን፤ (ዮሐንስ 1፡12)። ለእኛ ያለውን ፍቅር የሚገልጸው በኃጢአት ውስጥ እንድንኖር

እንዲሁ በመተው ሳይሆን በመከራ ውስጥ አሳልፎ እኛን ሥነ-ሥርዓት በማስያዝ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጎልማሳ የሆነ ሰው እግዚአብሔር እነዚህን መከራዎች እንደ ማሳደጊያ እንደሚጠቀምባቸው ስለሚገነዘብ መከራዎቹን በመቀበል ለመማር ይጥራል። ምንም እንኳ ለጊዜው የሚያስደስቱ ባይሆኑም እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ ዓላማ እንዳለው ያውቃል።

እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚመጡትን ነገሮች ለሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች ይጠቀምባቸዋል። አንደኛ፤ ቅጣቱ የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ያደርገናል። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱሳን እንድንሆን ይፈልጋል። ከኃጢአት ልንለይና ኢየሱስን እንድንመስል ከሚያደርጉን ነገሮች ልንቆጠብ ይገባል። ስለዚህም እግዚአብሔር በተግሣፅ ከኃጢአት እንድንሸሽና በእርሱ ፊት የበለጠ ቅዱሳን እየሆንን እንድንኖር ያደርጋል።

11ኛ ጥያቄ፡- የእግዚአብሔር ተግሣፅ ከኃጢአት እንድንሸሽ የረዳህ እንዴት ነው?

ተግሣፅ በሕይወታችን ቅድስናንና ሰላምን ይፈጥራል። ከእግዚአብሔር ጋር እና ከሰዎች ጋር እግዚአብሔርን የሚያስከብር ግንኙነት እንዲኖረንም ይረዳናል፤ (ያዕቆብ 1፡2-4)።

አንድ ሰው ሲናገር «እግዚአብሔር በአንድ ሰው በደንብ መጠቀም ከፈለገ በመጀመሪያ ልቡን ይሰብርና ዝቅ ያደርገዋል። ለታላቅ አገልግሎትም ከፍ የሚያደርገው እንዲህ ካደረገ በኋላ ነው» ብሏል። በሕይወትህ ከእግዚአብሔር ተግሣፅ ላይ ትምህርት እየወሰድክ ነው? ወይስ ከተግሣፁ እየሸሸህ ነው?

በእግዚአብሔር ተግሣፅ ሥር ሳለን የሚሰጡ ሁለት ምክሮችን ጸሐፊው ያሳየናል። አንደኛ፤ አንድ ሰው ለተግሣፁ እራሱን ዝግጁ ማድረግ አለበት። መንፈሳዊ እጆቻችንንና ጉልበታችንን በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል ጥናት ማጠንከር አለብን። በስደት ውስጥ እና በመከራ ውስጥ ጸንተን ለመቆምና ከእነርሱ ለመማር ቁርጥ የሆነ ውሳኔ ማድረግ አለብን።

12ኛ ጥያቄ፡- ወደ ሕይወትህ ከመድረሱ በፊት እንኳ ከእግዚአብሔር ተግሣፅ ለመማር እንዴት ዝግጁ እንደምትሆን ግለጽ።

ሁለተኛ፤ የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች ያሏቸውን ማቅናት አለብን። ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ሲፈተኑ ሊወድቁ ለሚችሉ የላላ እምነት ላላቸውም ጭምር ማሰብ ይኖርብናል። ሽንካላ የሆነ ሰው በቀላሉ ወድቆ እራሱን መጉዳት እንደሚችል ሁሉ የላላ እምነት ያለውም በችግር ወቅት ብዙ ሊጎዳ ይችላል። ስለዚህ እንዳይጎዳ ከእኛ በታች ያለውን ወንድም መርዳት ይኖርብናል።

13ኛ ጥያቄ፡- ሌሎች ክርስቲያኖች በችግር ወቅት እምነታቸው ሲላላ እንዳይጎዱ የምትረዳቸው እንዴት ነው?

# ሦስተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 12፡14-24

የዕብራውያን ጸሐፊ የሕይወትን ሩጫ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ መሮጥ ከፈለግን ከኃጢአት ጋር መዛመድ እንደሌለብን አስጠንቅቆናል። ክርስቲያን ሲኖር ኃጢአት ሕይወቱን እንዳያጠፋው በጥንቃቄ መኖር አለበት። በዕብራውያን 12፡14-18 ላይ ጸሐፊው ክርስቲያኑ በሕይወቱ ውስጥ ኃጢአት እንዳይገባባቸው መጠንቀቅ ያለባቸውን ቦታዎች ይዘረዝርልናል።

14ኛ ጥያቄ፡- ኃጢአት ክርስቲያኖችን የሕይወታቸው አስቸጋሪ እየሆነ በጣም የሚፈታተናቸው በየትና በየት ነው? ዘርዝር።

15ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 12፡14-24 አንብብ።

ሀ) ከክርስቲያኖች ሕይወት ኃጢአትን ለማስወገድ የተሰጡትን የተለያዩ ምክሮች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) ሁለቱን ተራሮች የሲናንና የጽዮንን ተራራ አነፃፅር። የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? የጽዮን ተራራ የሚበልጠው እንዴት ነው?

ሐ) የጽዮን ተራራ አባላት የሆኑት የተለያዩ የሰዎች ቡድኖች የትኞቹ ናቸው?

የክርስቲያን እምነት እራሱን በሦስት ዋና ዋና ግንኙነቶች ውስጥ ገሃድ ያደርጋል፡- አንደኛ፤ እምነታችን ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነትና ለእርሱ ባለን ታዛዥነት ይገለጻል።

ሁለተኛ፤ አንድ ሰው ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥም ይገለጻል። ለዚህም ነው ጸሐፊው «ከሰው ጋር ሰላምን ተከታተሉ» ያለው። ክርስቲያን ካልዳኑትም ከዳኑትም ጓደኞቹም ከሆኑትና ከሚያሳድዱት ሰዎች ጋር በሰላም መኖር አለበት።

16ኛ ጥያቄ፡- ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ከእርስ በእርሳቸውና ከማያምኑ ጋር ሰላም የማይኖሩባቸውን መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

ሦስተኛ፤ እምነት አማኙ ከኃጢአት ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ ይገለጻል። የአማኙ ሕይወት ሁሌ በቅድስና የተሞላ መሆን አለበት፤ ይህ የሚሆነው ከመጥፎ አስተሳሰብና ከኃጢአት በመቆጠብ ነው። በእምነታችን ስናድግ የኃጢአት ባህርያችን እየቀነሰ የበለጠ ግን ቅዱሳን እየሆንን ማደግ ይኖርብናል። በእግዚአብሔር ፊት ቅዱስ የሆኑት ብቻ ናቸው ቅዱሱን አምላክ የሚያዩት ብሎ እግዚአብሔር አስጠንቅቆናል።

የመጨረሻው ሁለት ነገሮች በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በልክ መሆን ያለባቸው ነገሮች ናቸው። አንዳንድ ክርስቲያኖች የፈለጉትን ያህል ዋጋ ቢያስከፍላቸው ሰላምን ለመፍጠር ይጥሩና ቅዱስ የመሆኑን አስፈላጊነት ይዘነጉታል። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል እንዳይኖር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ኃጢአት ችላ ብለው ያልፏቸዋል። ወይም ደግሞ በሕጉ የማይፈቀደውን ነገር ለማግኘት ጉቦ ይሰጣሉ። ይህ

ደግሞ ስሕተት ነው፥ ምክንያቱም ክርስቲያኑ ቅዱስ እንዲሆን ነው የተጠራው። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ከዓለምና ከሌሎች ኃጢአቶች ጋር ያላቸውን ማናቸውንም ግንኙነት ለማቆም ይፈልጋሉ። የሚመገቡት ክርስቲያኖች ጋር የሚኖሩት በክርስቲያኖች አካባቢ ኅብረት የሚያደርጉት ሥራ የሚሠሩት ወዘተ. . . ከክርስቲያን ቡድኖች ጋር ነው እንጂ የክርስትና ሕይወታቸውን በማያምኑ ሰዎች መካከል ገብተው እየኖሩ አይደለም። ስለዚህ ለዚህ ጨለማ ዓለም «ብርሃን» እና «ጨው» አይደሉም።

17ኛ ጥያቄ:- ሀ) በሰላም ለመኖር የሚፈልግ ክርስቲያን ቅድስናውን ችላ ሊለው የሚችለው እንዴት ነው?

ለ) ቅዱስ ለመሆን የሚፈልግ ክርስቲያን በማያምኑና በሰዎች ሁሉ ዘንድ እንደ ጨው መኖሩን ሊዘነጋ የሚችለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ሁሌ በሰላም ለመኖር ጥረት እንዲያደርጉ ያዝዛቸዋል። በምዕመናኑና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ብዙ ጊዜ እንዳለው ሽኩቻ ሳይሆን መኖር ያለበት ሰላም ነው። ክርስቲያኖች ከማያምኑም ሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር መጣር አለባቸው። ይህም ቢሆን ለሰላም ስንል ነው ብለን ለቅድስናችን ማስተባበሪያ መስጠት የለብንም። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱስ መሆን አለብን።

የዕብራውያን ጸሐፊ የክርስትና ሕይወትን እንዴት መኖር እንደሚገባን የሚገልጹ ሌሎች ማስጠንቀቂያዎችንም ይሰጠናል:-

1. ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፀጋ እንዳይጎድልባቸው መጠንቀቅ አለባቸው። ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው ታዛዥ ሆነው መኖራቸውንና ሙሉ በሙሉ እራሳቸውን ለእርሱ መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

2. በሕይወታቸው አንድ መራራ ሥር በቅሎ እንዳያስጨንቃቸው ማድረግ አለባቸው። በተለይ ይህ በአማኞች መካከል ተዛምቶ መከፋፈልን የሚፈጥረውን የሐሰተኛ ትምህርትን መዛመት የሚያመለክት ነው። ሆኖም በክርስቲያኖች መካከል ያለው ማንኛውንም ዓይነት ግጭትም የሚያመለክት ነው። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ቂም ይያያዛሉ። መሪዎች ከመሪዎች ጋር ይጋጫሉ፤ የቤተ ክርስቲያኖቹ አባላት በሌሎቹ ላይ ይነሣሉ። ከትዕቢትና ከፉክክር ጋር አብሮ ጎን ለጎን መራርነት ያድጋል። በዚህ ጊዜ መሪው ብቻ ሳይሆን የሚጎዳው፥ ልክ እንደ ተላላፊ በሽታ ወደ ሌሎች ይዛመትና ሕይወታቸውን በመራርነት ይሞላዋል።

18ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች ወይም አባላት ሕይወት ውስጥ መራራነት ሥሩን መስደድ የጀመረው እንዴት እንደሆነ አብራራ። ይህ መራራነት በቤተ ክርስቲያኒቱ ባሉት ሌሎች ሰዎች ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል?

3. ሴሰኝነት መኖር የለበትም። ይህም ከማግባታችን በፊት እግዚአብሔር ሚስት ወይም ባል እስኪሰጠን ድረስ እራሳችንን ንጹህ አድርገን መጠበቅ አለብን ማለት ነው። ካገባንም በኋላ ለባሎቻችንና ለሚስቶቻችን ታማኞች መሆን አለብን። ለሚስትዮዋም

ሆነ ለባልየው በእግዚአብሔር ዓይን ንጹህ አለመሆናቸው የሚታየው በእኩል ደረጃ ነው። ሁለቱም፤ በእግዚአብሔር በጽኑ ይወገዛሉ። ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ ግን ብዙ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ሰዎች ሴሰኞች ናቸው፤ በዚህም ሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ስም ያሰድባሉ።

19ኛ ጥያቄ:- እንዴት ነው ይህ በቤት ክርስቲያንህ ውስጥ ችግር የሆነው? ቤተ ክርስቲያንህስ ለችግሩ አልባት ያገኘችለት እንዴት ነው?

4. ክርስቲያኖች ለዚህ ዓለም የሚመቹ ሰዎች መሆን የለባቸውም። ጸሐፊው ክርስቲያኖች ስለ ዔሳው ሕይወት እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። (ዘፍጥረት ከምዕራፍ 25-27)። መንፈሳዊ በኩርናውን እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን በረከት ያጠቃለለውን ያዕቆብ በሚሰጠው ምግብ ለመሸጥ ፈቃደኛ ነበር። በኩርናውን መሸጡ ብቻ ሳይሆን የአባቱን የይስሐቅንም በረከት አጣ። ምንም እንኳ ወደ ይስሐቅ በእንባ ቢቀርብም ምንም ለውጥ አላገኘም (አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 27)። ለመንፈሳዊው ነገር ግድ ያለው መለወጥ የሚቻልበት ጊዜ ካለፈ በኋላ ነበር። ብዙ ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ አስጨናቂ የሆኑና በንስሐ እንኳ ሊለወጡ የማይችሉ ነገሮችን ያመጣብናል። የኤሳው ሕይወት በዘላለማዊው ብርሃን ውስጥ ሳይሆን እራሱን ብቻ ለማስደሰት የሚኖር ክርስቲያን ሕይወት ምሳሌ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የበለጠ ትምህርት ወይም ገንዘብ ወይም ዝና ለማግኘት ይጥራሉ። ልክ እንደ ኤሳው መንፈሳዊውን በረከታቸው ጊዜያዊ ለሆነው የሥጋ በረከት ሲሉ ይሸጡታል። በአኗኗራቸው ግን እግዚአብሔር ምንም እንደማይሰማው ሆነው ነው የሚኖሩት፤ ነገር ግን ለዓለም የተመቹ ሰዎች ናቸው።

20ኛ ጥያቄ:- ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በረከታቸውን ለጊዜያዊ ጥቅም ሊለውጡት የሚችሉት እንዴት ነው? ከምታውቃቸው ሰዎች ሕይወት ለምሳሌ ያህል ጥቀስ።

ዕብራውያን 12:18-29 በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አምስተኛውን የማስጠንቀቂያ ክፍል የያዘ ነው። ጸሐፊው የዕብራውያን ክርስቲያኖች ኢየሱስን በሌላ ነገር ተክተው እንዳይከዱት ያስጠነቅቃቸዋል።

ለማስጠንቀቂያው መሠረት እንዲሆነው ሁለቱን ታላላቅ ተራሮች ያነፃፅራቸዋል። አንደኛው ተራራ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳንን ሕግ የሰጠበት የሲና ተራራ ነው፤ (አሪት ዘጻግም 19:10-25፥ 20:18-21)። የብሉይ ኪዳን ሰዎች የእግዚአብሔርን ግርማና ኃይል ያዩት በዚህ ተራራ ላይ ነው። እንደምታስታውሰው፥ ተራራው በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት በተንቀሳቀበት ወቅት መብረቅና ዝናብ፥ የእንቢልታ ድምፅና አንድ በጣም ታላቅ ድምፅ ታይተዋል ተሰምተዋልም። ተራራው በጣም ታላቅ ስለነበር ተራራውን የነካ እንስሳ ወይም ሰው እንደሚገደል እግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር። ይህም በሰዎቹና በሙሴ ልብ ውስጥ ታላቅ ፍርሃትን አስከትሏል።

21ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር በሲና ተራራ እራሱን በገለጠበት ወቅት ከነበረው ሁኔታ ስለ እግዚአብሔር ባህርይ ልንማረው የምንችለው ነገር ምንድን ነው?

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ኃይሉንና ግርማውን ቢገልጽበትም የሲና ተራራ አንድ ተራ ተራራ ነበር። ዛሬ ወደ እሥራኤል ሄደህ ያን ተራራ ብትነካው ምንም አትሆንም። ለክርስቲያኖች ዛሬ ሌላ ታላቅ ተራራ አለ፣ ይህም የጽዮን ተራራ ነው።

22ኛ ጥያቄ:- ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ የጽዮን ተራራ የሚለውን ቃል ተመልከት። በየት ሥፍራ ነው የሚገኘው?

የጽዮን ተራራ ዳዊት ይዞ የእሥራኤል ዋና ከተማ ካደረገው የኢየሩሳሌም ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ነው። ዳዊት ቤተ መንግሥቱን የሠራበትና የእግዚአብሔር ክብር ይኖርበት የነበረው የሰለሞን ቤተ መቅደስ የተሠራበት ኢየሩሳሌም ውስጥ ነበር ይህ ተራራ የሚገኘው። ይህ የጽዮን ተራራ የእግዚአብሔር እውነተኛ መኖሪያ የሆነው መንግሥተ ሰማያትን እንደ ምሳሌ በመንፈስም የእግዚአብሔር ዙፋን ወደሚገኝበት አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የሚል ስያሜ ወዳላት ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ይችላል። (ዕብራውያን 4:16፥ ራዕይ 21:2)።

ጸሐፊው በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም የሚገኙትን የተለያዩ የሰው ቡድኖችን በዝርዝር ገልጿል።

1. ሕያው አምላክ የሚኖረው በዚያ ነው። በመንግሥተ ሰማያት የሁሉ ነገር ገዢና ፈጣሪ የሆነው በሙሉ ሥልጣን ዘላለማዊውና ሕያው አምላክ ሆኖ ይኖራል። እርሱ የሁሉም ዳኛ ነው። ያልዳኑት ባለማመናቸው ይፈርድባቸዋል፥ የዳኑት ደግሞ እንዴት አድርገው ሕይወታቸውን ለእርሱ አገልግሎት እንደተጠቀሙበት በማየት በእዚህ አኳያ ይፈርድባቸዋል።

2. አእላፋት መላእክት አሉ። ምን ያህል መላእክት እንዳሉ ማንም አያውቅም፤ ነገር ግን ለመቁጠር ከምንችለው በላይ ነው ያሉት፤ (ራዕይ 5:11-12)። በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ በደስታ እያገለገሉት ያከብሩታል ያመልኩታል።

3. በሰማይ የተጻፈ የበኩራት ማኅበር አለ። ይህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አንሥቶ ዳግመኛ እስከሚመጣ ጊዜ ድረስ ያሉትን የክርስቶስን አካል የሚሠሩትን አማኞች በሙሉ የሚያጠቃልል ነን። በክርስቶስ አምነው የሞቱትና እኛ በክርስቶስ አምነን የምንኖረው ሰዎች የዚህ የሰማያዊ ከተማ አባሎች ነው። አባሎቹን በተመለከተ ሁለት ነገሮች ተጠቅሰዋል። እንደ እግዚአብሔር ልጆች ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ «በኩራት» የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል። የሙታን በኩር ከሆነው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ናቸው፤ (ቆላ.1:15-18)። ሁለተኛ፤ ስማቸው መንግሥተ ሰማያት በሕይወት መዝገብ ውስጥ ተጽፏል፥ (ራዕይ 3:5)።

4. ፍጹማን የሆኑ ጻድቃን መንፈሶችም አሉ። ይህ የብሉይ ኪዳንን አማኞች የሚያመለክት ነው። ምንም እንኳ ቢድኑም ሙሉ ለሙሉ የነጹትና ፍጹም የሆኑት ኢየሱስ ለኃጢአታቸው ከሞተላቸው በኋላ ነው። መንፈሶች ናቸው ምክንያቱም በትንሣኤው አዲሱን አካላቸውን አልለበሱምና ነው። አሁን ያሉት በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ውስጥ ነው።

5. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በዚያ አለ። ደሙን በማፍሰስ የጀመረው የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ እንደሆነ አይተናል። የፈሰሰው የአቤል ደም የጠየቀው ፍርድንና በቀልን ነው፤ የኢየሱስ ደም ደግሞ ለኃጢአተኞች ክፍት የሆነውን ከኃጢአት የመንጻትንና ሙሉ ምሕረት የማግኘትን የምሥራች ያበሥራል።

23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እንዴት ነው መንፈሳዊና አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከምድራዊው የሲና ተራራ የምትበልጠው?

ለ) የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም አባል በመሆናቸው አማኞች ምን ዓይነት መጽናናት ነው የሚያገኙት?

# አራተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 12፡25-28

በትናንትናው ዕለት የአምስተኛውን ማስጠንቀቂያ የያዘውን ክፍል ማየት ጀምረን ነበር። ጸሐፊው የሁለቱን ኪዳኖች ዋነኛ ቦታዎች ነበር የሚያነፃፅረው የቀድሞው ኪዳን የተመሠረተው በምድራዊው ሲና ተራራ ላይ ነበር። እግዚአብሔር በዚያ ታላቅነቱን አሳይቷል። አዲስ ኪዳን ግን የተመሠረተው በመንፈሳዊና አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ነው። ምንም እንኳ ለዐይን ባትታይም በዚያች ሥፍራ እግዚአብሔር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መላእክትና ከጥፋት ጀምሮ የነበሩ አማኞች ይኖሩባታል። ክርስቲያኖች የዚህች ከተማ አባሎች በመሆናቸው ለሚያልፈው ምድራዊ ደስታ ብለን የዚህች ከተማ መንፈሳዊ አባልነት መተው ሞኝነት ነው።

24ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 12፡25-28 አንብብ።

ሀ) ጸሐፊው ለክርስቲያኖቹ የሚሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

ለ) የዓለምን መጨረሻ በተመለከተ የተሰጠው ትንቢት ምንድን ነው?

ሐ) የትኛው መንግሥት ነው የማይጠፋው?

መ) እግዚአብሔር ከምን ጋር ነው የተነፃፀረው?

ሁለቱን ኪዳኖች በሚያወዳድርበት ወቅት ጸሐፊው ክርስቲያኖች የአዲስ ኪዳንን በረከቶች እንዳይክዱ ያሳስባቸዋል። አዲስ ኪዳን ከቀድሞው የሚበልጥበት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ፡-

1. አንደኛ፤ የቀድሞው ኪዳን የተሰጠው ከሲና ተራራ ላይ ነው፤ ይህም ከምድር ላይ ነው ማለት ነው። ያንን ኪዳን አልቀበልም ያለ ሰው በሞት ይቀጣ ነበር። ሁለተኛው ኪዳን የተጀመረው ከመንግሥተ ሰማያት በመጣው በሞተውና ተመልሶ ወደ መንግሥተ ሰማያት በሄደው በኢየሱስ ነው። ይህን ሰማያዊ አዲስ ኪዳን ያልተቀበለ ምድራዊ ሞት ብቻ ሳይሆን የዘላለምን ሞት በላዩ ላይ ያመጣል።

2. የመጀመሪያው ኪዳን በተሰጠበት ወቅት፤ የሲና ተራራ ተንቀጥቅጦ ነበር። አንድ ቀን ደግሞ ኢየሱስ ዳግመኛ ሲመለስ ከዚህ የበለጠ መንቀጥቀጥ ይኖራል። በዚያን ጊዜም በምድር ላይ የሚገኙ ማንኛዎቹም ነገሮች ሰማያትን ጨምሮ (ኮከቦች፣

ፕላኔቶች፥ ወዘተ...) ሙሉ በሙሉ ይወድማሉ። የሲናም ተራራ እራሱ እንኳ ይወድማል። የሚቀሩት ነገሮች መንፈሳዊ የሆኑት ብቻ ናቸው፤ (ራዕይ 20፡11፥ 21፡1-2)። ስለዚህ ምድራዊ በሆኑ ነገሮች (ለምሳሌ፤ በገንዘብ፥ በቤት፥ በምድራዊ ዜግነት) መታመኑ ሞኝነት ነው ምክንያቱም ሁሉም ይጠፋሉና ነው።

3. ከማይነቃነቁትና ከማይጠፉት ነገሮች መካከል አንደኛውና ክርስቲያኖችም አባላት የሆኑበት የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ሁሉም ነገር ሲጠፋ የእግዚአብሔር ልጆችና የክርስቶስ አካል አባል የሆኑት ነቅነቅም አይሉም። ስለዚህም የዚህ የማይጠፋው መንግሥት አባሎች ሆነን መዝለቁ አስፈላጊ ነው።

ለእዚህ ማስጠንቀቂያ ሁለት ምላሾች አሉት። አንደኛ፤ ለትክክለኞቹ ነገሮች ቅድሚያ መስጠታችንን እርግጠኛ መሆን አለብን። ዓለምን ለመከተል ስንል ኢየሱስን ብንክድ ወደ ጥፋት እናመራለን። በተጨማሪም ምድራዊ በሆኑት በገንዘብ፥ በቤት፥ በመሬት፥ በኃይልና በሥልጣን ላይ ከታመንን እነዚህ ነገሮች በመጨረሻ ላይ ይወድማሉ። ከዚህ ሁሉ ግን ልክ እንደ አብርሃም ዐይናችንን ወደ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ከተማ ላይ ማድረግ አለብን፤ (ዕብራውያን 11፡10፥16)።

25ኛ ጥያቄ፡- ብዙ ክርስቲያኖች በማይጠፋው በመንግሥተ ሰማያት ነገሮች ላይ ከመታመን የበለጠ ምድራዊ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚታመኑት እንዴት ነው?

ሁለተኛ፤ እግዚአብሔርን በማመስገን እርሱን በትክክል ማምለክ ይኖርብናል። የዘላለማዊ መንግሥት አባሎችም ስላደረገን እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል። ያለማቋረጥ ስለሚገስጹንና ለመንግሥቱ ብቁ የሚያደርገን በመሆኑ ልናመሰግነው ይገባናል። ወደ እግዚአብሔርም ዙፋን በድፍረት መግባት አለብን፥ (ዕብራውያን 4፡16)።

ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በምንገባበት ወቅት ግን አንድ ልናስታውሰው የሚገባን ሌላ ነገር አለ። እግዚአብሔር ታላቁ ፈራጅ ነው። የሚያቃጥልም እሳት ነው። በሌላ አነጋገር ታላቅ ግርማው የሚያስፈራ ኃይል በመሆኑ ጠላቶቹን በሙሉ ያጠፋቸዋል። ስለዚህም ከድፍረቱ ጋር «አክብሮትና ፍርሃት» መታከል አለበት። በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በምንቀርብበትና በምናመልከው ጊዜ ሁለት እውነታዎችን በፊታችን አድርገን ልንጠብቃቸው ይገባናል። አንደኛ፤ እግዚአብሔር የሚወደን አባታችን ነው፤ ስለዚህም በሙሉ ልብ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እርሱ መቅረብ እንችላለን። ከዚህ ጋር ግን የእግዚአብሔርን ታላቅነት የኃጢአትና የግብዝነትን ጥላቻውን መገንዘብ ይኖርብናል። ስለዚህም ሕይወታችን ከኃጢአትና ከግብዝነት ነፃ እንደሆነ ከመረመርን በኋላ ወደ ፈራጃችን እንደምንቀርብ ማወቅ አለብን። ወደ ታላቁ አምላክ በፍቅርና በግልጽነት ለመቅረብ የሚችሉት ልባቸው ንጹሕ የሆኑ ብቻ ናቸው።

26ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ ስለ ጸሎት ጊዜያችንና በቤተ ክርስቲያን ስላለው የአምልኮ ጊዜያችን የሚያስተምረን ነገር ምንድን ነው? ለ) አንተና የቤተ ክርስቲያንህ አባላት ወደ እግዚአብሔር የምታቀርቡት የአምልኮ

መሥዋዕት የበለጠ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ሁለታችሁም መቀየር የሚገባችሁን ነገሮች በዝርዝር ጻፉ።

**አምስተኛ ቀን**፡-ትምህርቱንከልስናለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ) 1. መንፈሳዊው የሕይወት ሩጫ ከምድራዊው ሩጫ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

2. ለመንፈሳዊ ሩጫችን ዕንቅፋት የሚሆኑ ጥሩም መጥፎም የሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው?

3. አንተንና የቤተ ክርስቲያንህን አባላት በሩጫው ወቅት በተለይ የሚያስቸግራችሁ ኃጢአት የትኛው ነው?

4. በመንፈሳዊ ሩጫው ላይ ያሉትን ሌሎች ሰዎች የምታጽናና ባቸውን መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

ለ) 1. የእግዚአብሔር ተግሣፅ እንድታድግ የረዳህ እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ስጥ።

2. የእግዚአብሔር ተግሣፅ በችግር ውስጥም ቢሆን ፍቅሩን የሚገልጽልን እንዴት ነው?

3. እራሳችንንና ሌሎችን ለእግዚአብሔር ተግሣፅ ዝግጁ ለማድረግ ምን ምን ነገሮች ማድረግ እንችላለን?

ሐ) 1. ለምንድን ነው በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትንሽ ሰላም ያለው?

2. ሰላምን ለማስፈን ክርስቲያኑ መወጣት ያለበት ሐላፊነት ምንድን ነው?

3. ቅድስና ላንተና ለቤተ ክርስቲያንህ ችግር የፈጠረባቸውን መንገዶች ግለጽ።

4. ቅድስናና ሰላም ሁሌ መጣመር ያለባቸው እንዴት ነው?

መ) ብዙ ክርስቲያኖች እንደ ኤሣው ዓይነት ችግር ውስጥ የሚገቡት እንዴት ነው?

ሠ) ክርስቲያኖች የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም አባል መሆናቸው በምድራዊ ኑሮአቸው ሊያጽናናቸው የሚችለው እንዴት ነው?

ረ) 1. በአምልኳችን ወቅት የድፍረትና የፍርሃት የእግዚአብሔር ፍቅራችን የአክብሮታችን ሚዛናዊነት የምናሳየው እንዴት ነው?

ተጠርቷል። ሁለቱ ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዞች ፍቅርን የሚመለከቱ ናቸው። አንደኛ፣ እግዚአብሔር በሁለንተናችን መውደድ አለብን። ነገር ግን ሌሎችንም በተለይ ሌሎች የክርስቶስ አካል የሆኑትን ክርስቲያኖች መውደድ አለብን። ሐዋርያው ዮሐንስ ክርስቲያን ለመሆናችን አንዱ ማረጋገጫ ፍቅር ነው ይላል፣ (1ዮሐ.3፡11-18)። ሰይጣን ይህን ፍቅር ከክርስቲያኖች መካከል ለማጥፋት ይጥራል። በትናንሽ አለመስማማቶች በመጠቀም ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል። ሆኖም ለሁሉም ይህንን ፍቅር ሁሌ ለማሳየት መጣር አለብን፥ ምክንያቱም ኢየሱስ በሕይወታችን ላመጣው ለውጥ ምሥክር የሚሆነው ክርስቲያናዊው ፍቅራችንና አንድነታችን ነው፤ (የሐንስ 17፡20-23)።

3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የክርስቶስን ፍቅር የሚያንፀባርቁ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ለ) በምን ዓይነት መንገድ ነው የቤተ ክርስቲያንህ አባላት እርስ በእርሳቸው ፍቅር የሚሰጣጡት?

ሐ) አንተስ ፍቅርህን የምትገልጸው እንዴት ነው?

ዋና ዋናዎቹን የፍቅር ትዕዛዞች ከሰጠ በኋላ ጸሐፊው በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ፍቅር እንዴት እንደሚገለጽ የሚያሳዩ ሁለት የተለያዩ መንገዶችን ይጠቅሳል።

1. ክርስቲያኖች እንግዶችን በመቀበል ፍቅራቸውን ማሳየት አለባቸው፤ (ቁጥር 2)። በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይዘዋወሩ ነበር። በዚያን ጊዜ የነበሩት ሆቴሎች ሴትና አዳሪነት፥ ስርቆት የሚካሄድባቸው ስለነበሩ ለክርስቲያኖች ተስማሚዎች አልነበሩም። ስለዚህም ጸሐፊው ክርስቲያኖች ሌሎችንና በተለይ የማያውቃቸውን ክርስቲያኖች እንዲያስተናግዱ ይመክራቸዋል።

ሰዎችን እንዲያስተናግዱ ለማበረታታት በብሉይ ኪዳን የተለያዩ ሰዎች ያጋጠሟቸውን ነገሮች ያስታውሳቸዋል። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መልአኮች መሆናቸውን ሳያውቅ እንግዶቻቸውን ያስተናገዱ ነበሩ፤ (ለምሳሌ፡- ዘፍጥረት ምዕራፍ 18፥ መሳፍንት ምዕራፍ 6 እና 13)።

2. በእስር ላይ የነበሩትን ክርስቲያኖች ማስታወስ ነበረባቸው። ባመኑ በመጀመሪያው ጊዜ አካባቢ የዕብራውያን ክርስቲያኖች እሥር ቤት ካሉ አብረው ያዝኑ ነበር፤ (ዕብራውያን 10፡34)። የዕብራውያንም ጸሐፊ በዚህ ልማዳቸው በተለይም ስደት ሲባባስ በደንብ እንዲገፉበት ያሳስባቸዋል። ሌሎቹ ሰዎች ለብቻቸው እንዲሰቃዩ ከመተው ይልቅ እነርሱ በስደት ላይ ያሉ ክርስቲያኖች ቢሆኑ ኖሮ በሌሎች መረዳትን እንደሚሹ ሁሉ እነርሱም ሌሎችን መርዳት አለባቸው። አንዱ ትልቁ ምሥክር አንዱ አባላቸው ስለ እምነቱ እሥር ቤት ሲገባ ክርስቲያኖች አብረው ጸንተው መቆማቸው ነው።

4ኛ ጥያቄ:- በአንተ አካባቢ በስደት ወቅት የክርስቲያኖች መተሳሰብና መዋደድ ጠንካራ ምሥክር የሆነው እንዴት ነው?

ሁለተኛ፤ ጸሐፊው ስለ ክርስቲያኖች ጋብቻ ይመለከታል። አንዳንዶች ከማግባባት ይልቅ ለወንጌል ስርጭት ሲባል አለማግባት ነው ብለው እንደሚያስቡት ሳይሆን ጋብቻ ክቡር ነገር እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። ሆኖም በሁለቱም ማለት በባልየውና በሚስትየዋ ጋብቻው ንጹህ ሆኖ መጠበቅ አለበት። በሌላ አነጋገር መከባበር አለባቸው። የባልና የሚስት ግንኙነት የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ምሳሌ እንደመሆኑ በጋብቻ ውስጥ ሙሉ ንጽሕና መኖር አለበት፤ (ኤፌሶን 5:22-33)።

5ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለምንድነው ብዙ ክርስቲያኖች በተለይ ባሎች ለሚስቶቻቸው ታማኞች የማይሆኑት?

ለ) ሌሎች ክርስቲያኖች ጋብቻቸው ንጹህ እንዲሆን ልታስተምራቸው የምትችለው ነገር ምንድን ነው?

ጸሐፊው እግዚአብሔር የሚፈርድባቸው ሁለት የተለያዩ የወሲብ ኃጢአቶችን ይዘረዝራል። አንደኛ፤ ሴሰኝነት ነው። ይህ ላገቡ ሕጋዊ ያልሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ነው። ሁለተኛ፤ አመንዝራነት ነው። ይህ ደግሞ ከጋብቻ ውጪ በወንድና በሴት መካከል የሚደረግ ግንኙነትን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ያገቡም ሆኑ ያላገቡ እግዚአብሔር የጠራቸው ንጹህ እንዲሆኑ ነው፤ ካልሆኑ ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቀበላሉ።

6ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ከጋብቻ በፊት ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግ እንችላለን፤ ተፈቅዶልናል ብለው ያስባሉ? ለ) ይህ ለሕይወታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ የምትነግራቸውና የምትመክራቸው እንዴት ነው?

ሦስተኛ፤ ጸሐፊው ክርስቲያን ከንብረት ጋር ስላለው ግንኙነት በተለይ ስለ ገንዘብ ይመረምራል። ዛሬ የምንኖረው በገንዘብ ላይ እና በንብረት ላይ ብዙ ትኩረት በሚደረግበት ዓለም ውስጥ ነው። ገንዘብ ያላቸው የበለጠ ብዙ ገንዘብን ማግኘት ይጥራሉ። ገንዘብ የሌላቸው ደግሞ ገንዘብ ለማግኘት ያላቸው ምኞት ከሁሉም በላይ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በተለይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በገንዘቡ ምክንያት ኃጢአት ውስጥ ይወድቃሉ። ስለዚህ ነው ጳውሎስ «የክፋት ሁሉ ሥር ገንዘብ መውደድ ነው» ያለው፤ (1ኛ ጢሞ.6:10)። (የኢየሱስን ማስጠንቀቂያ በማቴዎስ 6:24 ላይ ተመልከት)።

7ኛ ጥያቄ:- ገንዘብ መውደድ አንተ የምታውቃቸውን ክርስቲያኖች በኃጢአት እንዲወድቁ ወይም በእምነታቸው እንዲላሉ ያደረጋቸው እንዴት ነው?

ጊዜያዊ የሆኑ እንደ ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ ያሉት ነገሮች ከማተኮር ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ይበቃኛል ብለው መቀበል አለባቸው። ሀብታም ከሆኑ ሀብት ጊዜያዊ እንደሆነ በመገንዘብ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መጠቀም አለባቸው። ደሆች ከሆኑ ደግሞ በጌታ ኢየሱስ ሀብታሞች ስለሆኑ እግዚአብሔርን

ማመስገን አለባቸው፤ (ያዕቆብ 2፡5፥5፡1-6)። ክርስቲያን እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሥፍራ ሁሌ ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት አለበት። እግዚአብሔር አልተውህም ብሎ ቃል ኪዳን እንደገባና ለችግሮቹ ሁሉ መፍትሔውን እንደሚያዘጋጅለት መገንዘብ አለበት። የሚያስፈልገንን የሚያውቅ እግዚአብሔር ነው እንጂ የእኛ የግል ፍላጎታችን አይደለም፤ (ማቴ.6፡25-35)።

በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ላይ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር እስከ መጨረሻው ታማኝ ሆነው የሞቱትን የብሉይ ኪዳን ሰዎችን ለዕብራውያን ክርስቲያኖች ያስታውሳቸዋል። አሁን ከቁጥር 7-8 ላይ ደግሞ በእነርሱ ጊዜ ስለነበሩት ሁለት የተለያዩ መሪዎች ያስታውሳቸዋል። አንደኛ፤ በመጀመሪያ ወንጌሉች የሰበኩላቸውን የቤተ ክርስቲያን መሪ የነበሩ የሞቱትን ሰዎች እንዲያስታውሱ ይጠይቃቸዋል። የእነዚህን ሰዎች ሕይወት ምሳሌነትና የሰበኩላቸውን ወንጌል ማስታወስ አለባቸው። ክርስቲያኖች እስከ ሞት ድረስ ታማኝ በመሆን የእነርሱን ምሳሌ መከተልም አለባቸው።

8ኛ ጥያቄ፡- የመጀመሪያዎቹን የቤተ ክርስቲያንህን መሪዎች ታስታውሳቸዋለህ? ከእነርሱ ሕይወት እንደ ምሳሌ ልትከተላቸው የምትችላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

ሁለተኛ፤ ጸሐፊው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመለክታል። ምንም እንኳ ሰው የሆኑ መሪዎች በሌሎች ቢተኩም አንዳንዶቹም በኃጢአት ቢወድቁም አንድ የማይለወጥ የቤተ ክርስቲያን መሪ አለ። ይህ መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ ብቻ ሳይሆን ባህርይውም መቼውም የማይለወጥ ነው። ዛሬም የሚሰጠን በመስቀል ላይ ለእኛ የነበረው የበፊቱን ፍቅር ነው። እንደ ሊቀ ካህናችን ያለማቋረጥ በመሥራት ሁልጊዜ በመንግሥተ ሰማያት ሆኖ ለእኛ ይማልድልናል። ኢየሱስ መሪያችን በማድረግ ታማኞችና ንጹሆች በመሆን ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን መስጠት አለብን። ይህን እያደረግን ነው?

ጸሐፊው በሐሰተኛ ትምህርት እንዳይወሰዱ ያስጠነቅቃቸዋል። የቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች ትምህርት ትንሽ ደከም ሲል የሐሰተኛ አስተማሪዎቹ ትምህርት የሚያስደስትና የሚያነቃቃ ይሆናል። የበለጠ የተለየና እንግዳ በሆነ ቁጥር ብዙ ሰዎች ወደ ትምህርቱ ይሳባሉ። ያለምንም ጥርጥር በዕብራውያኑ ዘመን የነበሩት የሐሰተኛ አስተማሪዎች በሥርዓቱ መሠረት ስለሚበሉት ምግቦች (ንጹሕና ንጹሕ ያልሆኑ ተብለው በብሉይ ኪዳን የተዘረዘሩትን) በመናገር ክርስቲያኖች ሕጉን እንዲጠብቁት ፈልገው ይሆናል። አካሄዳቸውን የመሠረቱት ደብዛው ሊጠፋ ባለው በብሉይ ኪዳን ሕግ ላይ ነበር። ስለ ምግብ የተሰጡት ትዕዛዞች ወይም የትኛዎቹም ትዕዛዞች አንድን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲኖረው ሊያደርጉ አይችሉም። ስለዚህም ትኩረት መስጠት ያለበት ውስጣዊው የክርስቲያኑ ሕይወት ላይ ነው እንጂ፥ በውጫዊ የሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ መሆን የለበትም።

9ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ የተደነገጉ አንዳንድ አዳዲስ ሕግጋትን ሰዎች የበለጠ መንፈሳዊነታችንን ይገልጹልናል ብለው የሚያስቧቸውን እስቲ በዝርዝር ጻፍ።

ለ) አንድ ሰው እነዚህንም ሕግጋቶች ጠብቆ ሊያድግ አይችልም?

እንደ እግዚአብሔር ልጆች ማዳመጥ ያለብን የእግዚአብሔርን ቃል ነው እንጂ እንግዳ ትምህርቶችን አይደለም። እግዚአብሔር ሰዎች ፈቃዱንና እርሱን የበለጠ እንዲያውቁ የሚያደርገው በቃሉ በመጠቀም ነው። ትክክለኛውን ከተሳሳተው ሊለዩ የሚችሉት የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቁት ብቻ ናቸው፤ (ዕብራውያን 5:11-13)። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጣዊውን ሰው ያጠነክርልናል። ይህም የተመሠረተው በፀጋ ላይ ነው፤ ምክንያቱም የመንፈሳዊ ዕድገት የሚመጣው ውጫዊ የሆኑ ሕግጋትን በመጠበቅ ሳይሆን እግዚአብሔር በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ሲሠራ በሚገኘው የልብ ለውጥ ሳቢያ ነው።

የዕብራውያን ክርስቲያኖች ወደ ቀድሞው የመሥዋዕት ማቅረብ ሥርዓት ወደነበረው ወደ ሙሴ ሕግ ለመመለስ ሲወላውሉ ነበር። እንደምታስታውሰው የአንዳንዶቹን መሥዋዕቶች ሥጋ ካህናት መብላት ይችሉ ነበር። ሆኖም ለክርስቲያኖች ብቻ የሆነ ልዩ መሠዊያ አለ። በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው መሠዊያ ላይ ሰዎች የተለያየ አመለካከት አላቸው። የኦርቶዶክስና የካቶሊክ ክርስቲያኖች ይህን መሠዊያ እንደ ጌታ እራት አድርገው ያዩታል። ሆኖም ጸሐፊው በተደጋጋሚ በመጽሐፉ ውስጥ እንደገለጸው ክርስትና መንፈሳዊ ሃይማኖት ነው እንጂ በውጫዊ ነገሮች ላይ የተመሠረተ አይደለም። ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በሆነ ቦታ (መንግሥተ ሰማያት) እንደሚያመልኩና በዚያም ምንም ምድራዊ መሥዋዕት መሠዊያ ወይም ካህን እንደሌለ ጨምሮ አስተምሮናል። ስለዚህም ይህ መሠዊያ ኢየሱስ የኃጢአታችን ዋጋ የከፈለበትና መንፈሳዊ በረከቶችን የሚመነጨበት የኢየሱስ መስቀልን ይመስላል። ኢየሱስና እርሱ ያስገኘልን ደኅንነት መንፈሳዊ ምግቦቻችን ናቸው።

በዕብራውያን 13:11-14 ላይ ጸሐፊው የመንፈሳዊ እውነታ መሠረት ወደሆነው የስርየት ቀን ያመለክታል። እንደምታስታውሰው የስርየት ቀን ዕለት ለኃጢአት መሥዋዕት የቀረቡት እንስሳት ሥጋ ከመኖሪያው ሠፈር ውጭ ተወስደው ነበር የሚቃጠሉት፤ ምክንያቱም ንጹሕ ባለመሆናቸው ሠፈሩን ሊያረክሱት በመቻላቸው ነው። በእግዚአብሔር ፊት ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ይረጭ የነበረው ደሙ ብቻ ነበር።

ጸሐፊው ከኢየሱስ ሕይወት አንድ አስፈላጊ የሆነ መንፈሳዊ ምሳሌን ያያል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሞት የተሰቀለው በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ አልነበረም። ከከተማው ውጭ ነው እየመሩ ያስወጡት። የአይሁድ ሰዎች ኢየሱስን እንደ መሢሑ አድርገው ለመቀበል አልፈለጉም በተጨማሪም በእርሱ ሞት ከተማቸው እንድትረከስ አልፈለጉም ነበር። ኢየሱስ ለእነርሱ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ እንደሚሞት አልተገነዘቡም ነበር። በመስቀል ላይ ሲሞት ሊያድናቸው በመጣው ዘንድ ተቀባይነትን አጥቶ ተንቆ ነው የሞተው። የዕብራውያን ጸሐፊ ክርስቲያኖቹ የንቀቱ ተካፋዮች

እንዲሆኑና ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲቆሙ ጥሪ ያደርግላቸዋል። ሠፈሩ እንደ ትልቅ ነገር የሚቆጥራቸውን ነገሮች ቤተ መቅደሱን፥ የኢየሩሳሌም ከተማን፥ መሥዋዕቶቹን ወዘተ... የሚያመለክት ነው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተወገዱ ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ መከተል ያለባቸውም አይሁዶች ያልተቀበሉትንና ያናናቁትን መስቀል ነው። እንደ አብርሃም ተከታዮች የሚሆኑባት በመንፈሳዊዋ ኢየሩሳሌም ላይ ዓይናቸውን ማድረግ አለባቸው፤ (ዕብራውያን 11፡10፥ 14-16)።

የመስቀሉ መንገድ ወይም ለኢየሱስ ክርስቶስ መታዘዝን ዓለማውያን እንደ ሞኝነት አድርገው ይቆጥሩታል። በዚህም ምክንያት ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ የተናቁ ናቸው። ሆኖም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደዚሁ ነበር። እኛም ከዓለማውያን የሚሰነዘርብንን ጊዜያዊ የሆነውን ስድብ ተቀብለን ዐይናችንን ወደ መንግሥተ ሰማያት ወደሚጠብቀን ክብር ላይ ማድረግ ነው ያለብን። ይህን እያደረግህ ነው?

10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ለመስቀሉ ሲሉ የዓለምን ስድብ እንደማይቀበሉ የሚያሳዩት እንዴት ነው?

ለ) ሌሎች ክርስቲያኖችስ ለዘላለማዊው ክብር ሲሉ የዓለምን ስድብ መቀበላቸውን የሚያሳዩት እንዴት ነው?

## ሁለተኛ ቀን፡- ዕብራውያን 13፡15-25

ጸሐፊው በዕብራውያን ምዕራፍ 13 ላይ፥ በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ በተጻፉት እውነታዎች ላይ በመመርኮዝ የተወሰኑ ትዕዛዞችን ለክርስቲያኖቹ ይሰጣል። በትናንትናው ዕለት የክርስቲያን ፍቅርን፥ ጋብቻን፥ ወዘተ... በተመለከተ የሰጠውን ትዕዛዞች ተመልክተናል። በተጨማሪም የሐሰት ትምህርቶችንም በተመለከተ የሰጠውን ስሞታ አይተናል።

11ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 13፡15-25 አንብብ።

ሀ) ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ማቅረብ ያለባቸው ምን ዓይነት መሥዋዕቶችን ነው?

ለ) እነዚህ ቁጥሮች መሪዎችን በተመለከተ የምዕመናኖቹ ኃላፊነት ምንድን ነው የሚሉት?

ሐ) መሪው ለሕዝቡ ስላለው ሐላፊነትስ እነዚህ ጥቅሶች የሚናገሩት ምንድን ነው?

መ) እንባቢያኑን በተመለከተ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር ያቀረበው ልመና ምንድን ነው?

በብሉይ ኪዳን አማኞቹ ሲያመልኩት የእንስሳ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ እግዚአብሔር አዝዞአቸው ነበር። ያለምንም ጥርጥር በአዲሱ ኪዳን ሥር እግዚአብሔርን ማምለካቸውን የሚገልጽ አንድ የሆነ ዓይነት መሥዋዕት ማቅረብ አለብን ብለው ሳያስቡ አልቀሩም። ጸሐፊው ደግሞ በእርግጥ ክርስቲያኖች ሊሠዉት የሚገባ መሥዋዕት እንዳለ

ይጠቅስና እንደበፊቱ የእንስሳ መሥዋዕት ሳይሆን መንፈሳዊ መሥዋዕት ነው ይላቸዋል። መሥዋዕት የማቅረቡ ዕድል የተሰጠው ለተወሰኑ እንደ ሌዊ ነገዶች ለነበሩ ሳይሆን ለሁሉም ክርስቲያኖች ነው፤ ምክንያቱም ሁሉም ክርስቲያን ካህን ነውና፤ (1ኛ ጴጥ.2፡5)።

ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ ለሰዎች ሁሉ በከፈተው በክርስቶስ ደም ላይ በመመሥረት እውነተኛ የሆኑ መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር ልናቀርበው እንችላለን። አንደኛ፤ የምሥጋና መሥዋዕት መኖር አለበት። ልክ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ምሥጋና መሥዋዕት (ኦሪት ዘሌዋውያን 7፡12) ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ስለሰጣቸው በረከቶች ያለማቋረጥ ማመሥገን አለባቸው። ቋሳዊ የሆነ የምሥጋና መሥዋዕት ከመስጠት በአንደበታችን (የከንፈሮቻችን ፍሬ) ነው እግዚአብሔርን የምናመሠግነው።

12ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔርን የምታመሠግንባቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ሁለተኛ፤ ጸሐፊው መልካም ማድረግና ለሌሎች ማካፈል እራሱ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነው ይላል። ለሌሎች ፍቅር ስንሰጥና በችግራቸው ስንረዳቸው እግዚአብሔር ይህን እርሱን እንደምናመልከው አድርጎ ነው የሚቆጥረው። እነዚህም ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር እውነተኛ እንደሆነ የሚገልጹ ማስረጃዎች ስለሆኑ እርሱም ደስ ይለዋል።

13ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 12፡1 አንብብ። እንደ መሥዋዕት እንድናቀርብ የታዘዝነው ሌላ ነገር ምንድን ነው? ይህን አድርገሃል? እንዴት?

ጸሐፊው ለቤተ ክርስቲያኑ ምዕመናን ምክር ለመሪዎቹ ደግሞ ማስጠንቀቂያም ይሰጣል። የቤተ ክርስቲያኑ ምዕመናን እግዚአብሔር በላያቸው ለሾማቸው መሪዎች መታዘዝ አለባቸው። ትዕዛዙን በማክበር በመሪነት ሐላፊነቱ መሪ እንዲደሰት መጣር አለባቸው። ብዙ ጊዜ ምዕመናን አመራራቸውን በመቃወም ተጨማሪ ችግርና ሸክም በመሪዎቻቸው ላይ ይፈጥራሉ። በዚህም ለመሪዎቹ ብቻ ሸክም መብዛት ብቻ ሳይሆን መሪዎቹ በራሳቸው ግፊትና ኃይል ሲመሩም ምዕመናኖቹ ይጎዳሉ። ወይም ደግሞ ምዕመናኑ ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ ዝግ ያሉ፥ ያልተማሩና ለመሪነት እንደምንፈልጋቸው እንደሌሎቹ የሚደነቁ ባይመስሉም ዐይናቸውን «አዲስ» መሪዎች ላይ ያደርጋሉ። እነዚህ ብዙ ጊዜ የሐሰት ትምህርት የሚያመጡ ናቸው። ምንም እንኳ አሁን ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምዕመኑ ያሉትን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እንደሚታዘዙ እርግጠኞች መሆን አለባቸው። ይህ በተለይ መሪዎቹን ዘገምተኞችና ኋላ ቀር አድርገው ለሚቆጥሯቸውና በመሪነታቸው ለሚያምጹ ጎልማሶች ማስጠንቀቂያ ነው። እግዚአብሔር ተገዙ ብሎ ያዛቸዋል።

14ኛ ጥያቄ፡- በምን ዓይነት መንገድ ነው የቤተ ክርስቲያንህ አባላት ለመሪዎቻቸው የመሪነቱን ሥራ ቀላል ሊያደርጉላቸው የሚችሉት?

መሪዎችም በታላቅ ጥንቃቄ መምራት ይኖርባቸዋል፤ ምክንያቱም ስለ አባላቱ ሕይወት ተጠያቂ ናቸውና። መሪው የአባላቱን ችግርና መሠረታዊ ፍላጎቶች በቅርብ

መከታተል አለበት። ሊጎዷቸው የሚችሉ ነገሮችን ከወዲሁ በመረዳት እነርሱን ለመጠበቅ መሻት አለበት። አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዴት እንደጠበቀና እንደመራ መልስ መስጠት ሊኖርበት ነውና።

15ኛ ጥያቄ:- መሪዎች አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ቆመው መልስ እንደሚሰጡ ቢገነዘቡ በቤተ ክርስቲያንህ ያለው መሪነት ሊለወጥ የሚችለው እንዴት ነው?

ዕብራውያን 13፡1-17 በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ስላሉ ነገሮች ያመለክታል። አሁን ደግሞ ጸሐፊው ወደ መጽሐፉ መጨረሻ ግላዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ወደሚቅረቡ ጉዳይ ዞር ይላል። አንደኛ፤ ለእርሱ አብረውት ላሉት ክርስቲያኖች እንዲጸልዩላቸው ይጠይቃል። በነገር ሁሉ በቃልም ሆነ በተግባር መልካም ሕሊና እንዲኖረውና በንጹሕ ዓላማ ክርስቲያኖቹን እንደሚመራ ነው የሚጸልዩለት። ክርስቲያኖቹን ፈጥኜ ወደ እናንተ እንድመጣም ጸልዩልኝ ይላቸዋል።

ሁለተኛ፤ ለክርስቲያኖቹ የጸሎት መሥዋዕት ያቀርባል። ጸሎትን ያቀረበው ለሰላም አምላክ ነው። ይህን እግዚአብሔር ስያሜ የተጠቀመው በክርስቲያኖቹ መካከል ብዙም ሰላም ስላልነበርና እርስ በእርሳቸው በመጣላታቸው ወይም ደግሞ ሊመጣ ላለው ስደት ይቆሙበት ዘንድ የሚያስፈልጋቸውን ውስጣዊ ሰላም እንዲያገኙ ይሆናል። ይህ የሚወሰነው በውጫዊ ነገሮች ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ባለም ንጹሕ ግንኙነት ላይ ነው።

ጸሐፊው ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እግዚአብሔር መሆኑን ይገልጻል። ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ በመጽሐፉ ውስጥ በቀጥታ ተነግሮ ያለው በዚህ ሥፍራ ላይ ነው። ትንሣኤው ለዘላለማዊው አዲስ ኪዳን መሠረቱ ነው። በሌላ አነጋገር የኢየሱስ ከሙታን መነሣት ኢየሱስ ስለ ዓለም ሁሉ ያቀረበው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳገኘና በዚህም ላይ አዲሱ ኪዳን እንደተመሠረተ የሚያሳይ ማረጋገጫ ነው።

ጸሐፊው ኢየሱስን «ታላቁ እረኛ» ይለዋል። አይሁዳውያን እግዚአብሔርን ወደ ኋላም መሢሑን ይመለከቱት የነበረው እንደ እረኛ ነው፤ (መዝ.(23)፤ዮሐ.ምዕራፍ 10)። ከሙሴ እንኳ ታላቅ የተባለው በመብለጡ ነው። እርሱ እረኛም፥ መሪም፥ እና የእግዚአብሔር ሕዝብ መከታም ነው።

ጸሐፊው የሚጸልየው ለሁለቱ ዋና ዋና ነገሮች ነው። አንደኛ፥ ፈቃዱን እንዲፈጽሙ ክርስቲያኖቹን እግዚአብሔር በሚያስፈልጋቸው ነገር እንዲያስታጥቃቸው ነው። የክርስቲያን ሕይወት ለመኖር ሐላፊነቱ የክርስቲያኑ ብቻ አይደለም። ፈቃዱን እንዲፈጽም ረድቶት ክርስቲያኑ እንዲኖር የሚያደርገው እግዚአብሔርም ጭምር ነው። እግዚአብሔር ለሰዎች ኃይልን ይሰጣል፤ መሻቱንም በውስጣቸው አስቀምጦ ችሎታውን ይሰጣቸዋል፤ (ፊል.2፡12-13)።

16ኛ ጥያቄ:- ፈቃዱን በታዛዥነት እንድታደርግ እግዚአብሔር እንዴት ዓይነት ሁኔታዎች እንደሚረዳህ በዝርዝር ጻፍ።

ሁለተኛ፤ ጸሐፊው የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቱ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲያደርግ ይጸልያል። ጸሐፊው እግዚአብሔር ሕይወታችንን እንደሚቆጣጠር ተገንዝቧል። በተጨማሪም እግዚአብሔር የልጆቹን ጸሎት ፈቃዱን ለማከናወኛ እንደሚጠቀምበት ተገንዝቧል።

በመጨረሻም ጸሐፊው ምሥጋና ያቀርባል። ይህን የዘላለም ምሥጋና ያቀረበው ለእግዚአብሔር አብና ለእግዚአብሔር ወልድ ነው፤ ምክንያቱም ሁለቱም ከእኛ ምሥጋና ለመቀበል ብቁ ናቸው። አስተውል፤ ክብሩና ምሥጋናው የተሰጠው ለእግዚአብሔር አብ ብቻ ወይም ለኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን ለሁለቱም ነው። ይህ ቁጥር የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ከሚያስተምሩት ጋር የሚነፃፀር ነው።

በዕብራውያን 13፡22-25 ጸሐፊው አጠር አጠር ያሉ መደምደሚያ ሐሳቦችን ይሰጣል። በዕብራውያን መጸሐፍ ውስጥ የሰጣቸውን ትምህርት በደንብ እንዲያጤኑ ይጠይቃቸዋል። የጢሞቴዎስ መፈታት በመጥቀስ ከእርሱ አብሮ ለመምጣት መፈለጉን ይነግራቸዋል። ለመሪዎቹና ለአባላቱ ሁሉ ሰላምታ ይልካል። ከጣሊያን ሕዝብ የተላከ ሰላምታም ያቀርባል። ይህ የትውልድ አገራቸው ጣሊያን የነበረና ካሁን ወዲያ እዚያ የማይኖሩ ሰዎችን ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ በጣሊያን ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ከጣሊያን ውጭ ላሉ ክርስቲያኖች የተላከ ሊሆን ይችላል። በመጨረሻም የእግዚአብሔር ፀጋ በሁሉም ላይ እንዲሆን ይመኝላቸዋል።

የዚህን የዕብራውያን መጽሐፍ ጥናታችንን አገባድደናል። በዚህ ጥናት ውስጥ በደኅንነታችን ሥራ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጫወተውን ትልቅ ሚናና አሁንም ቢሆን በእርሱ የሊቀ ካህንነት አገልግሎት ላይ ምን ያህል እንደምንደገፍ ተምረናል።

17ኛ ጥያቄ፡- አሁን ላንድ አፍታ «ታላቁን የበጎች እረኛ» ስላፈቀርህ፣ ስለሞተልህና ያለማቋረጥ ስለሚንከባከብህ አመስግነው።

# ሦስተኛ ቀን፡- ክለሳ

የክርስትና ሃይማኖት የሚያተኩረው በአንድ ሰው ላይ ነው፤ እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የቤተ ክርስቲያን እራስና መሠረት እርሱ ነው። ክርስትና በጣም ለየት የሚል ሃይማኖት ነው። ይህን ስንል ክርስትና ደኅንነት የሚገኘው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው ብሎ በማስተማሩ ማለታችን ነው። ሌሎቹ መንገዶች ወደ ሞት ነው የሚያመሩት። ለዚህም ነው ኢየሱስ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፥ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ያለው፥ (ዮሐንስ 14፡6)።

18ኛ ጥያቄ፡- ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ የሚጥሩትን የአንዳንድ ሃይማኖቶች ዝርዝር ጻፍ።

የዕብራውያን መጽሐፍ ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ ይበልጥ የሚያተኩረው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይና በሥራው ላይ ነው። የተጻፈውም በኢየሱስ ያላቸውን እምነት ክደው ወደ ቀድሞው የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ለመመለስ ስለሚሹ ስለ ዕብራውያን

ክርስቲያኖች ነበር። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ ይህ የቀድሞው የአምልኮ ሥርዓት በአዲስ እንደተተካ ያስረዳቸዋል። ስለዚህም ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስንና የመስቀል ሞቱን በሦስት መንገዶች ከቀድሞው ኪዳን ጋር ያነፃፅረዋል።

1. ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ከሚገኙት ከማንኛዎቹም መሪዎች በላይ ነው።

19ኛ ጥያቄ: - ጸሐፊው ከኢየሱስ ጋር የሚያነፃፅራቸውን የብሉይ ኪዳን መሪዎች ስም ዘርዝር ጻፍ።

ሀ) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከተቀበሉት ነቢያት በላይ ነው፤ (1:1-4)። ይህ የሆነው እንደ እግዚአብሔርነቱ በሰዎች መካከል በመኖሩና የእግዚአብሔርን ቃል በመናገሩ ነው።

ለ) ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን ታላላቅ ተአምራት ከሚሠሩት መላእክት በላይ ነው፤ (1:5-14)። ይህ የሆነው እንደ መላእክቶቹ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ነው።

ሐ) ኢየሱስ የእሥራኤልን ሕዝብ ከግዞት ካወጣው ከሙሴ በላይ ነው፤ (3:1-6)። ሙሴ ከእግዚአብሔር ሕዝቦች አንዱ ነው፥ ኢየሱስ ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሥራች ነው። ስለዚህም ከሙሴ በላይ መከበር አለበት።

መ) ኢየሱስ፥ ከሊቀ ካህኑ ከአሮን በላይ ነው፤ (4:14-5:10፥7)። እንደ አሮን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአት ፈጽሞ ስለማያውቅ ለራሱ መሥዋዕት አላስፈለገውም። የኢየሱስ ሊቀ ካህንነት እንደመልከ ጼዴቅ ሹመት ዘላለማዊ በመሆኑ በየጊዜው በሌላ መተካት አያስፈልገውም። በተጨማሪም አሮን ያገለግል የነበረው ምድራዊው ድንኳን ውስጥ ነበር፥ ኢየሱስ ግን እግዚአብሔር በሚገኝበት በመንግሥተ ሰማያት ነው የሚያገለግለው።

የፈለግነውን መሪ ወይም ሌላ ሃይማኖት ብንከተልም ሰውና ምድራዊ ናቸው። ክርስትና ግን ለየት ይላል፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ሙሉ ሰው ሙሉ አምላክ ነው። ጣምራ ሰውም እግዚአብሔርም ሆኖ ልንከተለው የምንችለው ሌላ ማንም ሰው የለም። እንደ እግዚአብሔርነቱ ከጥንት ጀምሮ ነበር፤ የዓለምም ፈጣሪ ነው። እንደ ሰብአዊነቱ ደግሞ ምንም እንኳ ያለ ኃጢአት ቢሆንም ችግራችንን ይረዳል፥ ማንም ሰው ከሚረዳን በላይ ደግሞ ሊረዳን ይችላል። የእኛ ደካማ ጎን ፍላጎትና ሕመማችንንም ሙሉ በሙሉ ይረዳናል።

20ኛ ጥያቄ: - የኢየሱስ እግዚአብሔርና ሰውም መሆን እኛን የሚያበረታታን እንዴት ነው?

2. የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት የተመሠረተው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእሥራኤል ሕዝብ ከሰጠው ኪዳን በሚበልጥ ሌላ ታላቅ ኪዳን ላይ ነው፤ (ምዕራፍ 8)። ይህም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የተደረገ ቃል ኪዳን ይገለው ከሚል ማንኛውም ሃይማኖት ይበልጣል ማለት ነው። የቀድሞው በሕዝቡ ታዛዥነት ላይ

የተመሠረተ በመሆኑ የድርጊት ኪዳን ነበር። ታዛዥ ከሆኑ እግዚአብሔር እንደሚባርካቸው ዓመፀኞች ከሆኑ ግን እንደሚረግማቸው ቃል ኪዳን ገብቶ ነበር። የቀድሞው ኪዳን የሰዎችን ልብ ለውጦ ሰዎቹ እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ ብቁ አላደረጋቸውም ነበር።

በብሉይ ኪዳን ምንም ታላቅ ቢሆን አዲስ ኪዳን ከእርሱ ይበልጣል። የተመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ በተሰጠ የድርጊት ባልሆነ የተስፋ ቃል ላይ ነው። እግዚአብሔር የሰው ልጅ ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ይቅር እንደሚል ብቻ ሳይሆን የሚገልጸው በሰዎቹ ልብ ውስጥ ሕጉን በመጻፍ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዲጠብቁም ችሎታውን እንደሚሰጣቸውም ቃል ገብቷል።

3. የኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ከብሉይ ኪዳኑ መሥዋዕት ይበልጣል፥ (9-10፡18)። በብሉይ ኪዳን ኃጢአተኛ ኃጢአት በሠራ ቁጥር መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። በስርየት ቀን ሊቀ ካህኑ በየዓመቱ መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት። እነዚህ መሥዋዕቶች ለሚያመልከው ሰው ዘለቄታዊ የሆነ መንጻት አያስገኙም ነበር። የሥርዓት መንጻትን እንጂ የልብ መንጻትን አያስገኙም ነበር።

ሆኖም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ከዚህ በጣም የላቀ ነበር። ኢየሱስ እንደ መሥዋዕት ያቀረበው እራሱን ነው እንጂ እንስሳ አይደለም። የእርሱ መሥዋዕት የሚቀርበው አንዴ ነው እንጂ በየዓመቱ መደጋገም የለበትም። የእርሱ መሥዋዕት ለኃጢአተኛው ሙሉ የሆነ ምሕረት ስለሚያስገኝ እንደገና መደገም የለበትም። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ሙሉ የሆነ ምሕረትን የሚያስገኝ ሌላ መሥዋዕት የለም።

ጸሐፊው ስለ ኢየሱስ ማንነትና ስለ ሥራው ለመግለጽ ይህን ያህል ጊዜ የፈጀው ከእርሱ ጋር ሊወዳደር የሚችል ማንም አለመኖሩን ለማሳየት ነው። ሙሉ ደኅንነትን የሚያስገኝ ሌላ መንፈሳዊ መሪ ወይም ሃይማኖት እንደሌለ ጸሐፊው ያሳየናል። ስለዚህም የጥንቶቹን የዕብራውያን ክርስቲያኖችን እኛን ሌላ ሃይማኖት ብለን ኢየሱስን ለመካድ እንዳንነሣሣ ያስጠነቅቀናል።

የዕብራውያን መጽሐፍ በኢየሱስ ያላቸውን እምነት ለመካድ ለሚያስቡ አይሁዳውያን አምስት የማስጠንቀቂያ ክፍሎች አሉት፤ (2፡1-4፥ 3፡7-4፡13፥ 5፡11-6፡12፥ 10፡19-39፥ 12፡14-29)። የእነዚህ የማስጠንቀቂያ ክፍሎች ትርጓሜ ከባድ እንደሆነ ተመልክተናል። አንዳንዶች እነዚህ ክፍሎች የተጻፉት እምነታቸውን ካዱ ማለት ደኅንነታቸውን ማጣትና የዘላለም ቅጣት መቀበል እንደሆነ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ለሚገባ ክርስቲያኖች ነው ይላሉ።

ሌሎች ደግሞ ይህ ክፍል ምንም ለክርስቲያኖች ቢጻፍም በደንብ ያላደጉ ክርስቲያኖች እምነታቸውን እንዳይክዱ የተሰጡ በእውነተኛ ዕውቀት ላይ ያልተመሠረቱ ማስፈራሪያዎች ናቸው ብለው ያስባሉ።

በመጨረሻም አንዳንዶች ይህ ክፍል የተጻፈው በክርስቲያኖች መካከል ለብዙ ዓመታት በመኖር ራሳቸውን እንደ ክርስቲያን ለሚቆጥሩና ክርስቲያን ነን ብለው

ለሚናገሩ ሰዎች ነው ብለው ያስባሉ። በኢየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት ከካዱ በፊትም እውነተኛ ክርስቲያኖች እንዳልነበሩ ያስመሠክራሉ። ይህ ክፍል ክርስቲያኖች በኢየሱስ ያላቸው እምነት እውነተኛ እንደሆነ እንዲመረምሩ የሚያደርግና ክርስቲያን ነን ለሚሉ ሰዎች ደግሞ ከክርስቶስ ውጭ ደኅንነት እንደሌላቸው የሚያሳስቡ ናቸው።

የዚህ የማስጠንቀቂያ ክፍል ዋና ትምህርት ግን ግልጽ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ማረጋገጥ አለብን። በክርስቲያን ቤተሰብ ልናድግ እንችላለን ነገር ግን በኢየሱስ ለማመን የራሳችንን ውሳኔ ካላደረግን እምነታችን እውነተኛ አይሆንም። ሙሉ በሙሉ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ከካድን እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንዳልሆንን እናሳያለን። የእኛ ደኅንነት ግን እስከ መጨረሻው ድረስ በታማኝነት በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ተቀምጣለች። በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን ውጭ ሌላ የደኅንነት መንገድ የለም። ታዲያ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ እርግጠኛ ነህ?

የዕብራውያን ጸሐፊ እኛ በአዲሱ ኪዳን የምንኖር ሰዎች የብሉይ ኪዳኑን የአምልኮ ሥርዓት እንዴት ማጤን እንዳለብን ይነግረናል። ሕጉ መሥዋዕቶቹና ሊቀ ካህናቱ የመጨረሻውን መሥዋዕትና ሊቀ ካህን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክቱ ጊዜያዊ ምስሎች ናቸው። ሕጉ መሥዋዕቶቹና ምድራዊዎቹ ሊቀ ካህናት ሙሉ ትርጓሜ የሚኖራቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ ውስጥ ነው። ስለዚህም የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ኢየሱስ መስቀል ላይ በመሞት የከፈተው አምልኮ ሥርዓት ትንሽ ጭላንጭል ናት ማለት ነው። እውነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ የብሉይ ኪዳን አምልኮ ግን የዚህ ጥላ ነው። ስለዚህም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለውን ጥላ ሳይሆን እውነተኛውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው መከተል ያለብን።

21ኛ ጥያቄ፡- አንዳንዶቹን የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ለመከተል የሚፈልጉ ሃይማኖቶችን ይህ ነገር የሚነካቸው እንዴት ነው?

በዕብራውያን ምዕራፍ 11-13 ጸሐፊው እውነተኛ የሚያድን እምነት እንዴት እንደሆነ ይገልጻል።

1. የሚያድን እምነት አሁን በማይታዩት ነገር ግን መንፈሳዊ እውነታዎች በሆኑ ነገሮች ላይ እንድንኖር ያስገድደናል። ወደማይታዩት ነገሮችና የእግዚአብሔር ተስፋዎች በመመልከት እምነታችንን ሙሉ በሙሉ በእነርሱ ላይ ማድረግ እንጂ በሚታየው በዓለም ነገሮች ላይ ማድረግ የለብንም። የክርስቲያን ዓይን ያሉት በዘላለማዊ የእግዚአብሔር ከተማ ላይ ነው እንጂ፥ በዓለም ላይ አይደለም።

22ኛ ጥያቄ፡- አእምሮአችን ሊያስባቸው የሚገባ አንዳንድ የማይታዩ ነገሮችን ወይም ተስፋዎችን እስቲ በዝርዝር ጻፍ።

2. የሚያድን እምነት፤ ሁኔታዎች እንኳ ትርጉም የለሽ በሚሆንበት ወቅትም ቢሆን እግዚአብሔርን እንድንታዘዝና በእርሱ እንድንታመን ያደርገናል። አንዳንዴ እምነት የእግዚአብሔር ልጆች ታላቅ ሥራ እንዲሠሩ ያስደርጋቸውና ታላቅ በረከትን ያመጣል። በሌሎች ጊዜያቶች ደግሞ እምነት ታላቅ ስደትን ከዚያም አልፎ የተስፋ በረከት የለሽ ሞትንም ሊያስከትል ይችላል።

3. የሚያድን እምነት በሕይወታችን በችግር ውስጥና በስደት ውስጥ ስናልፍ ጸንተን እንድንቆም ይፈለግብናል።

4. የሚያድን እምነት ሕይወታችን በሙሉ ተለውጦ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመናችንን ያንፀባርቃል። በፊት ጥላቻ የምናበዛ ከሆነ፥ አሁን ማፍቀር እንጀምራለን። በፊት ስለ ራሳችን ብቻ የምናስብ ከሆነ አሁን ግን ለሌሎች ጥሩ እናደርጋለን። የምንታመነው በእግዚአብሔር ነው እንጂ ባለን ንብረት ላይ አይደለም። መንፈሳዊ መሪዎቻችንን እንታዘዛለን። ሕይወታችንን በሙሉ ለክርስቶስ ክብር ለማዋል እንወዳለን።

23ኛ ጥያቄ:- በኢየሱስ ላይ ያለህ እምነት ሕይወትህን እንዴት እንደ ለወጠው አንዳንድ ሁኔታዎችን ግለጽ።

የዕብራውያን ጸሐፊ ሕይወትን እንደ ማራቶን እሩጫ ይቆጥረዋል። ክርስቲያኖች በሙሉ የዚህ ሩጫ ውድድር ተካፋዮች ናቸው የሚገባደደውም ስንሞት ነው። የሩጫ ውድድር ዋናው ነገር የአሯሯጣችን ፍጥነት ሳይሆን መጨረሻችን ነው። ኃጢአትና የዓለም አምሮት ሩጫውን እንዳንሮጥ ዕንቅፋት ይሆኑብናል። በሐሰት ትምህርት ከተወሰድን እምነታችንን ከካድን ከሩጫው ውድድር እንወጣለን። መንፈሳዊ ሩጫህን የምትሮጠው እስከመጨረሻው ሮጠህ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን ነው? ወይስ ከሩጫው ለመውጣት እያወላወልክ ነው? ወንድሞችና እህቶች ዐይኖቻችሁን በኢየሱስ ላይ ብቻ አድርጉ። መስቀሉን ሲጋፈጥ እንኳ እንዴት ሩጫውን ይሮጥ እንደነበር ተመልከቱ። በሩጫው የመጨረሻ መስመር ላይ ቆሞ እየጠበቀህ ነው። ስለዚህ ለዚህ ሩጫ ዕንቅፋት የሚሆንብህን ማንኛውንም ነገር አስወግድ፤ ጽና። አንድ ቀን ከኢየሱስ ጋር ትገናኝና ቃል የገባልህን ሽልማት ታገኛለህ።

24ኛ ጥያቄ:- የዕብራውያን መጽሐፍ ትምህርት ላንተና ለቤተ ክርስቲያንህ አባላት አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

**አራተኛና አምስተኛ ቀን**:- አሪት ዘሌዋውያንና ዕብራውያንን ከልሰህ ለመጨረሻው ፈተና ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የመጨረሻው ፈተና ውሰድ
5. ጸሎት

# 5. ዘሌዋውያን - ዕብራውያን

## የጽሕፈት ሥራ ተግባር

እያንዳንዱ ተማሪ ለዚህ ትምህርት የዲፕሎማ ዋጋ ለመቀበል ተማሪው የሉክ ወረቀት 10 ገጽ ወይንም በደብተር 20 ገጽ ጽሑፍ መጻፍ አለበት። በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪው ከሚከተሉት አንዱን አርዕስት መርጦ መጻፍ አለበት።

1. ለመዳን የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን መጠበቅ አለብን ብሎ የተናገረውን አይሁድን እንደተገናኘህ አድርገህ ገምት። የዘሌዋውያንንና የዕብራውያንን መጽሐፍ በመጠቀም አንድን ሰው የሕግን ዓላማ በዘሌዋውያን ውስጥ እንዴት ታሳያለህ? ኢየሱስ ሕግን ሁሉ እንደፈፀመ ለአንድ ሰው እንዴት ታሳያለህ? በብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት እንደተወገደ እንዴት ታሳይለህ? ለመዳን ኢየሱስን ብቻ ማመን እንዳለባቸው እንዴት ታሳያቸዋለህ?

2. ብዙ ክርስቲያኖች በስደት ጊዜ እምነታቸውን ይክዳሉ። የዕብራውያንን ትምህርት በመጠቀም ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር በታማኝነት እንዲቆዩ እና በኢየሱስ ያላቸውን እምነት እንዳይክዱ ለማድረግ እንዴት በመጠየቅ ታበረታታቸዋለህ?